ያመተሐበት



ደራሲ
ማርዮ ፑዞ

ትርጉም
መጋየሁ ተበጀ

t.me/OLDBOOKSPDF

የጡት አባት

ደራሲ
ግርዮ ጉዞ

ትርጉም
ወጋየሁ ተበጀ

መስከረም 1982

t.me/OLDBOOKSPDF

የሽፋን ሥዕል ግርማ ደምሴ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቦሌ ማተሚያ ቤት

የተርጓሚው ማስታወሻ

በምእራቡ አለም ህብረተሰቡ አውቆት የተቋቋመው ህጋዊ መንግስት በአንድ በኩል የራሱን አመራር ሲሰጥ በሌላ በኩል በመንግስትና በህጉ እንዲሁም በህብረተሰቡ በጐ ፍላጐትና ሰላማዊ ህይወት ላይ ያመጹ የድብቅ አለም አመራሮች አቆጥቁጠው በፍላጐታቸው ብቻ ይመራሉ ።

እነዚህ ድብቅ አለም የሚመሩ ቤተሰቦች ከህጋዊው አለም ሰውረው ያቋቋሙት ድርጅት እጅግ ብዙ ህብት ቢያስገኝላቸውም ፥ የመንግስት ባለስልጣኖችን በመደለል የሌራቸው ተባባሪ ማድረግ ቢችሉም ፥ ያንን ሁሉ ህብት ፤ ሀይልና ዝና ያስገኘላቸውን የራሳቸውን ህልውና እንኳን ጠብቀውና አስጠብቀው መዝለቅ ሳይችሉ እየቀሩ አሟሟተ ጥፉ ሆነው ይገኛሉ ። መላው ቤተሰባቸውም ከስጋት እና ከስቃይ ተለይቶ አያውቅም ። የነሱም ህይወት ስጋት ላይ እንዳለ ሁሉ የመላ ህብረተሰቡ ህይወትም ከስጋት ነጻ ሳይሆን ይኖራል ።

የድብቅ አለም ቤተሰቦች ህጋዊ መተዳደሪያ ህጋዊ ንግድ ይሆናል ። እነዚህ ቤተሰቦች ብዙ ህብት ያካብታሉ ። የገቢያቸው ምንጮች አያሌ ይሆናሉ ። ነገር ግን ላገኙት ትርፍ ተገቢ ግብር መክፈል ባለመፈለግ ግብር እንዲምሯቸው ወይም እንዲቀንሱላቸው የመንግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለት ባለስልጣናትን ያሾልላሉ ። ለእነሱ ተስማሚ የሆነ የጎሣ አንቀጽ እንዲኖመጡ የምክር ቤት አባላትን ይሸ ነግላሉ ። ይመሰክሯቸውን ወይም ተፎካካሪዎቻቸውን ለማጥፋትና የሀብት የበላይነትን ለመፈጠር የብዙ ተቃ ዋሚዎቻቸውንና የተከታዮቻቸውን ደም ያፈሳሉ ። በዚህ ሙዘግብ መሠል የስላማዊ ሰው ሀይማኖትና ንብረት በከ ንቱ ያወድማል ። ሀገ የሚጠይቀውን አለመፈጸም ወይም ሀገ የሚከለክለውን ማድረግ የተለመደ ተግባራ ቸው በመሆኑ ለዚህ ተንኮላቸው ሀግ አስፈጻሚ ክፍል የመንግሳቸው ተባባሪ እንዲሆን ይፈልጋሉ ። ቢፈ ቅድ በመሸንገያ እንዲተባበራቸው ያስገድዱታል ። እምቢ ካለ ግን በሀይወት መኖር አይፈቀድለትም ።

እነሱ የሚመሩት አለም ከሠጋዊው አለም ጋር የይ ስመላ ነው የሚያስኝ ጦርነት በየጊዜው ያካሂዳል ። በሚነሳው ጦርነት አንዱ ሌላውን ለማጥፋት የተነሳ ይመስላል ። ግን ማናቸውም ሌላውን ለማጥፋት አልቻ ሉም ። ለመንግስት ባለስልጣን የገንዘብ ምንጮችና የፖለቲካ ተፎካካሪዎችን የሚያጠፉለት ተቋሞች በመ ሆናቸው ባይኖሩ እንኳን ይፈጥራቸዋል እንጂ መጥፋ ቸውን አይፈልግም ። አንዳንድ ጊዜ አንዱን በመደገፍ ከሌላው ጋር ባለስልጣኑ ትራኔ ውስጥ ሲገባ መደ በብር ወይ በበትር እጁን እንዲያነሳ ይገደዳል ።እሺ ካለ ከፊተኛው መዳጁ ጋር እምቢ ካለ ከአዲሱ ጋር ጠብ ይፈጥርና ስጋት ላይ ይጠድቃል ። የስጋቱ ማብቂያ አንድ ቀን በጉዞ ፣ በስብሰባ ፣ በመዝናኛ ወይም በስ ራው ላይ እንዳለ በመድሀኒት ፣ በአደጋ ወይም በመ ሳሪያ መጥፋት ብቻ ይሆናል ።

በሀብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ሀጋዊ ፈቃድ ከተሰጣቸው በኋላ ግላዊ ብልጽግናን ለማስፋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፋት ታላላቅ ደባዎች በመፈጸም ብቻ አልተወሰኑም ። እነዚህ የጥፋት መልእክተኞች የሚያሰራጩት አደንዛዥ እጽ የወጣቱ ሀይወት እንዲቃወስና ማህበራዊ አቋ ሙም እንዲናጋ ፣ አእምሮው ደንዘ ወደ ውድቀት እን ዲያመራ አድርጉታል ። ሌላ ቀርቶ በጥቁሮች ላይ ያላ ቸውን ጥላቻ ሊደብቁ አለመቻላቸውን መገንዘብ የሚ ቻለው ስርጭቱ በነሱ አካባቢ እንዲናኝ የሚያደርጉ ትን ጥረት ስንመለከት ነው ።

አደንዛዥ እጽ ሰብአዊ ጠንቅነቱ ከተረጋገጠ አን ስቶ አያሌ የመከላከል እርምጃዎች ተወስደዋል ። በአ ለም ላይ ስርጭቱን ለማቆም በመንግስታትና የሰው ልጆችን ደህንነት በሚመኙ ድርጅቶች አማካይነት ከፍ ተኛ ዘመቻ እየተካሄደ ነው ።

ይህ የጥፋት መርዝ ንግድ ብዙዎችን የናጠጡ ከበርቴዎች አድርጓቸዋል ። ታዲያ የነዚያ ከበርቴዎች ብልጽግና ቁጥር ስፍር በሌለው ደባ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የምንገነዘብ ስንቶቻችን ነን ? በሰዎች ሀይ ወት መጥፋት ፣ በታዳጊዎችና ጐልማሶች አእምሮ መደ ንዘዝ ፣ ባጠቃላይ በህብረተሰብ ስቃይ የተቆናጠጡት ብል ጽግና የማይገሰስ መስሎ ሲያስመካቸው ይቆይና በሚ ጋለጡበት ወቅት የውርደት ማቃቸውን መልበሳቸው አይቀርም ።

ለዚህ ነው ባልዛክ የተባለው ፈረንሳዊ ጸሀፊ "ከያንዳንዱ ሀብት በስተጀርባ አንድ ወንጀል አለ" ብሎ የተናገረው ።

የሰዎች ለሀያልነት የመብቃት ፍላጐቶችና የሚከ ተሉት ጉዞ እጅግ የሚያስደንቅ ነው ። አንዳንዱ ለሰው ልጆች ደህንነት እራሴን ቢዛ አድርጌ ታላቅ ስራ ሰርቼ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለታላቅ ሰውነት ልብታ ብሎ ይነሳና ታሪክ ሰርቶ ያልፋል ። አንዳንዱ የሰበሰበው ሀልቆ መሳፍርት የሌለው ሀብት አልበቃ ብሎት ሌሊት እንቅልፍ ፣ ቀን እረፍት እያጣ ሲባዝን ልቡ ፈንድቶ ይሞታል ። ታሪኩም አብሮት ይሞታል ። የሰው ልጅ ፣ ሁሉም እንዲያ መሆን ይችላል ማለት ባይቻልም ለታላቅነት የሚያበቃው ከውርደት የሚያደርሰው ፣ የነቃ የበቃ ፣ ካልሆነም በሀ ይወቱ ሳለ የሞተ የሚያደርገው ስራው መሆኑ ግልጽ ነው ። እንዲያ ለመብቃትም መስፈንጠሪያ መድረኩ ከማናቸውም ነቁጥ ላይ ተነስቶ ሊሆን ይችላል ።

የህዝቦች ሰላማዊ ህይወት ፣ ንብረትና የአገር ደህ ንነት ተጸራሪ የሆነው ማፊያ የካፒታሊስቱ አለም አጠ ቃላይ ገጽታ ያሳደገው የከተማ ፋኖዎች ስብስብ ነው። ህብረተሰባችን ይህን የመሰለው የጥፋት መልእክተኞች ድብቅ አለም ቡድን አይታይበትም ። ድንገተኛ ደራሽ ውንብድና በየአገሩ ብቅ ማለቱ የሚታይ ቢሆንም ለቁ ጥጥር አስቸጋሪ አይሆንም ።

ስለዚህ ይህን የመሰለ ውዝግብ ያልወረረው ህብ ረተሰባችን በሚያገኘው የደህንነት ዋስትና ምን ያህል የታደለ መሆኑን የሚገነዘበው የ'ጡት አባት'ን (ወይም የእንግሊዝኛ ርዕሱ 'ዚ ጎድ ፋዘር' የሚለውን መጽሐፍ) መሰል ጽሑፎች አንብቦ የጥፋታቸውን ገጽታ ሲረዳ ብቻ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሐፍ አንድ

'ከእያንዳንዱ ታላቅ ሀብት
በስተጀርባ አንድ ወንጀል አለ'
ባልዛክ

ምዕራፍ አንድ

አሜሪጐ ቦናሴራ ቆንጆ ልጁን በጭካኔ ደብድ በው ክብርዋን ሊወስዱባት የሞከሩትንና መንጋጋዋ በሽቦ ተሰፍቶ የሀኪም ቤት አልጋ ቁራኛ እንድትሆን ያበቋትን ሁለት ባለጌ ወጣቶች በፍትሀ ለመበቀል ሲል ከኒውዮርክ ፍርድ ቤት 3ኛ ችሎት ቀረበ ። ቁመ ናው ግዙፍ የሆነው አልማጭ ዳኛ ግን ምኞቱን አላሳካ ለትም ። ዳኛው ለይስሙላ ፊቱን በእብሪት በማጨፍገግ ወጣቶቹ በፈጸሙት ደባ ተቆጭቶ የአካል ቅጣት ሊፈጽ ምባቸው የተነሳ ይመስል ፣ የካባውን እጅጌ እየጠቀለለ ፣

"የመጨረሻውን ደባ ፣ የጫካ ውስጥ አደገኛ አውሬ ተግባር ነው የፈጸማችሁት" ሲል ተቆጣ ። ጸጉራቸውን እንደ ባህረኞች ተቆርጠው ፣ ጥፋታቸውን ያመኑ በመ ምሰል ፊታቸውን በሚፈትጉት ወጣቶች ላይም ደነፋ። ይህ ሁኔታ ቦናሴራን ቢያጠራጥረውም ለጊዜው የዳ ኛው አንጋገር ልቡን ሰቀለው ። ዳኛው ንግግሩን ቀጠለ።

"ግን ይችን ምስኪን ልጃገረድ በፍትወተ ስጋ ልትደርሱባት ባለመቻላችሁ እድለኞች ናችሁ ። አለዚ ያማ ወህኒ ወርዳችሁ ሀያ አመት ሙሉ ትማቅቋት ነበር" የሚል የፍርድ ግለዘቢያ ጣል አድርጎ ከፊቱ ባለው የአመክሮ ዘገባ ቁልል ላይ ጉንበስ አለ ። ከእው ነተኛ ፍላጎቱ ውጭ ለመፍረድ የተገደደ በማስመሰል ፣

"ነገር ግን በወጣትነታችሁ ምክንያት ፣ ስለንጹህ ሪኮርዳችሁ ፣ ስለመልካም ቤተሰቦቻችሁ ፣ እናም ሀግ

t.me/OLDBOOKSPDF

በታላቅነቷ በቀልን ስለማትሻ ፥ የሶስት አመት እስራት ፈርጀባችኋለሁ ። እስራቱ ግን በገደብ ተነስቶላች ኋል" የሚል ፍርድ ሲሰጥ ፥ ባንድ በኩል የነረምሶች ወላጆች በዙሪያቸው ተሰግስገው በደስታ ሲፈነድቁ ፥ በሌላ በኩል ከንዴቱ የተነሳ ኮምጥጥ የመረረ ጥቁር አሞት በአሜሪጐ ቦናሴራ ጉሮሮ ሽቅብ ገንፍሎ እየወጣ በጥርሶቹ ዘለቀ ። ግና ለአርባ አመታት መተዳደሪያው የነበረው የአልቃሽነት ሙያው እውነተኛ ስሜቱን የመደበቅ ዘዴ ስላስተማረው ፥ የገነፈለው ተስፋ መቁረጥና ንዴቱ እንዳይታወቅበት ቢያግድለትም ፥ ይህ ቧልታይ ተውኔት አብቅቶ እነዚህ አውሬዎች በነጻ ተለቀው ፥ ከወላጆቻቸው ጋር በደስታ ሲጓዙ አፉን በመሀረቡ አብሶ ሲመለከት ትእግስቱ ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነበት ።

"እኔ እንዳለቀስኩ ታለቅሷታላችሁ ፥ ልጆቻችሁ እኔን እንዳስለቀሱ እኔም እናንተን አስለቅሳችኋለሁ" ብሎ ጮኸ ።

አሜሪጐ ቦናሴራ በአሜሪካ በቆየባቸው አመታት ሀብታም ይሁን እንጂ ተስፋ ያደረገበት ያገሪቱ ህግና ስርአት ትክክለኛ ፍርድን ሊያጎናጽፈው አልቻለም ። ቂሙን በቀጥታ መበቀል እንደማይቻለው አወቀ ። የጠየቀውን ይጠይቅ እንጂ በሌላ ዘዴ ፍትህን ለማግኘት ተንበርክኮ የጡት አባቱን ዶን ኮርሌዎኔን ለመማጠን ወሰነ ።

ጆኒ ፎንቴን የልጆቹ እናት ወደሆነችው ወደ መጀመሪያ ሚስቱ ደውሎ ስለጤንነታቸው እንዳያነሳ ሰአቱ አልፏል ። ቀድሞ በስልክ ሲጠራቸው ይፈነድቁ የነበሩትን ታላላቅ ተዋንያት ቁጣቸውንም የተዋናይነት ዝናው

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅ! በል ምስኪኑ ጅኒ ፣ ደህና ሁን" ብላ ወደ መኝታ
ክፍል ገብታ ቆለፈችበት ።

ጅኒን ከዚህ የውርደት ማቅ ፣ ከዚህ የተስፋ መቁ
ረጥ ስሜት ሊያድነው የሚችል ሙሉ በሙሉ የሚ
ተማመንበት የጡት አባቱ ኮርሌዎኔ ብቻ ነውና ወደሱ
ዘንድ ለመብረር መኪና እንዲመጣለት ስልክ ደወለ።

ዳቦ ጋጋሪው ናዞሪኔ ልጁ ካተሪን ያባቷ ረዳት
የሆነውን ኤንዞን ወዳ ልቧ ጠፍቷል ። ሳለመከዳት
ቃል ገብቶው በአሜሪካ ኢኮኖሚ ውስጥ እንዲሰሩ
እንደተፈቀደላቸው ብዙ መዶ ሺህ የጠር እስረኞች
ጣልያን ወገኖቹ ሁሉ ፣ ኤንዞም ያ ፈቃድ ይሰረዝና
እስር ቤት ወደ መዋል ይመልሱኛል የሚል የዘወትር
ስጋት አለበት ። የናዞሪኔ ሚስት ፌሎሚና የልጅዋን
በዚህ ጉረምሳ ፍቅር መናወዝ አውቃለች ። እሱ
ወዳገሩ እንዲባረር ከተደረገ ካተሪንም አብራው እንደ
ምትኮበልል በማስጠንቀቋ ይህን ልጅ ሉንግ አይ
ለንድ ከሚገኙት ዘመዶቻቸው ዘንድ ወስዶ እንዲደ
ብቀው ባሏን ጉተጉተችው ። ናዞሪኔ የልጁን ሙቀትና
ለኤንዞ ያላትን ፍቅር ከቀድሞ ሁኔታቸው ተረድቷል ።
በተለይም ኤንዞ አንድ ቀን የበሰለ ዳቦ ከመጋገሪያ
እያወጣ ወደ ማጠራቀሚያው ሊጨምር ሲሞላ ካተሪን
በቂጢ ስትታከከው ተመለከተ ። የዚህ ወመኔ ትዝ
ዳቦ በልጁ መጋገሪያ ውስጥ መግባቱ እንደማይቀርም
ተገንዝቦታል ። ከዚህም በላይ ኤንዞን የመሰለ ጉብል
ለሴት ልጁ ማግኘት ቀላል አለመሆኑን ናዞሪኔ አው
ጥቶ አውርዶ ፣ የኤንዞንም ለልጁ ታማኝነት ካረጋገጠ
በኋላ ይህ ልጅ በአሜሪካ መቆየት እንዳለበት ወሰነ ።
ይህን ማድረግ የሚችለው ደግሞ የጡት አባቱ ዶን
ኮርሌዎኔ ብቻ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እያሽቆለቆለ በመሄዱ እንደልቡ ሊያዛቸው እንደማይ ችል ተረድቶታል ። ያለመጠን ደምቆ ባጌጠው የሎስ አንጀሊስ ሆቴል ከፍሉ ውስጥ በቀይ ሶፋው ላይ ተቀምጦ ውስኪውን እየተጋተ በቅናት ሲያሰላስላት የነበረችውን ያችን ሀጅ ሚስቱን የትም ካያረችበት ምናልባት ከተ መለሰች ህይወቷን በመቅጨት ሊበቀላት በስካር ልቦ ናው እየተመኘ ሲጠባበቅ በመጨረሻ በሩን ስትከፍት ሰማት ። ያቺ ቆንጆ ፣ በቀላሉ ተሰባሪ መሳይ ፣ መልአክ ፊት ፤ ያቺ በመላው አለም የመቶ ሚሊዮን ወንዶችን ልብ የሰረቀች እና እሷን በሲኒማ ለማየት ብራቸውን የሚያፈሱላት ተዋናይ ማርጐ አሽተን ከፊቱ ስትቆም ፣

"የት አባሽ ነበርሽ?" ብሎ በቁጣ ገነፈለ ። እሷ ግን ስካሩን በወግ ስላልተገነዘበች ፣ "ስዘሙት" ብላ መለሰችለት ። ዘሎ ጉሮሮዋን አነቃት ። ነገር ግን ትክ ብሎ ቢያያት ውበቷ ጉልበት ስለነሳው የሚያደርገውን አጣ ። አሁንም ሁኔታውን ስላልተገነዘበች የንቀት ፈገግታ ጣል አረገችበት ። በቡጢ ሊላት እጁን ሲያዘጋጅ፣

"ጆኒ! ፊቴን አትምታኝ! ፊልም እየሰራሁ ነው" ብላ ጮኸች ። ሆዷን ጉስም ሲያደርጋት ከመሬት ተዘ ረረች ። እንደድሮ እንደ ልጅነት ድብድቡ ከቁንጭ ውም ከጉሰማውም በማድረግ ስብራትም ሆነ ጠባሳ የማይተው አሳማሚ ቅጣት ሲሰጣት ፣ ከዚያው ከወደቀች በት ሆና እጆቿን ዘርግታ በስስ ልብሷ ዘልቆ የሚታየውን ጭኗን እያሳየች በወሲብ ልትሸነግለው ሞከረች ። ጆኒ ፎንቴን ትቷት ተነሳ ። እሷም ከተጋደመችበት ተነስታ ፣

"ጆኒ አልጐዳኝም ፣ ምንም አልጐዳኝ!" እያ ለች በልጆች መበሻሸቂያ ዜማ አሳግጣበት ተመልሳ እንደማዘን አለች ።

"አንት ጅል! እንደ ትንሽ ልጅ ትቆነጥጠኝ! ፍቅ ርህም እንደትንሽ ልጅ ፣ ግብረ ስጋህም እንደ ትንሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጁ ተደብድባበት ፍርድ ያጣው ፣ ሚስቱ በድ ላው ቁጭት ያለበት ፣ የነዋሪነት ፈቃድ ለልጁ ወዳጅ የሚሻው እንዲሁም ሌሎች ብዙ እንግዶች ዛሬ የጡት አባታቸው ቤት ይሰበሰባሉ ። ለስብሰባቸው ምክ ንያት የሆናቸው በ1945 ነሀሴ ወር የመጨረሻ ቅዳሜ ላይ የዋለው የወይዘሪት ኮንስታንዚያ ኮርሌዮኔ ሰርግ ሲሆን ፣ በበአሉ ላይ እንዲገኙ ቀደም ሲል ጥሪ ደርሷ ቸዋል ። አሜሪካ ከጃፓን ጋር ታካሂድ የነበረው ጦር ነት በማብቃቱ ለፈንጠዝያ አመች ወቅት ነበር ። ዶን ቪቶ ኮርሌዮኔ ዛሬ ታላቅ ሰው ሆኖ ፣ ሎንግ አይለንድ ለሚገኘው ታላቅ ቤቱ በቅቷል ። ይሁን እንጂ የጥንት ወዳጆቹን አልረሳቸውም ። ሰርጉ በግቢው ውስጥ ቀኑን ሙሉ ይከበራል ። የኮርሌዮኔ ወዳጆችም በበኩላቸው ለሱ ያላቸውን ክብር ለማሳየት ኒውዮርክ ከተማ ፈሰ ዋል ። ወደሱ ሲቀርቡም ባዶ እጃቸውን አይደለም ፣ ለሙሽሪት የጥሬ ገንዘብ ገጸ በረከት ማንነታቸውን ከምትገልጽ ካርድ ጋር በሽሮ መልክ ፖስታ ውስጥ አሽገው ይዘው ነው ።

ማንም ሰው ተቸግሮ ወደ ዶን ኮርሌዮኔ ዘንድ መጥቶ ተስፋ የሚያስቆርጥ መልስ ይዞ አይመለስም ። ዶን ኮርሌ ዮኔ ባዶ ተስፋ ሰጥቶ ወይም እርዳታ እንዳይሰጥ የሚያግ ዱት ሀይሎች በመኖራቸውም ምክንያት ጉዳዩን ሊፈ ጽም እንደማይችል በፍራቻ ተናግሮ አያውቅም ። አገልግ ሎቱን ወዲያው በሚቀበለው ሰው ገንዘብ ለመክፈል አይሻም ። ለዛሬው ውለታ ወዳጅነት ነው የሚ ሻው ። ምናልባት ታላቅ ሰው መሆኑን ለማረጋገጥ ‘ዶን’ መባሉን ፣ ቢበዛም ‘የጡት አባት’ ተብሎ መጠራቱን ፣ ምናልባትም አራት ጠርሙስ በቤት ውስጥ የተጠመቀ ወይን ጠጅ ወይም ለገና በአል ገበታውን ግርማ እንዲሰጠው ለሱ ተብሎ በበርበሬ የተሰራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድፍ ዳቦ ለአክብሮት ያህል ከቀረበለት በቂው ነ
ዋናው ከፍያ ግን አንድ ሰው ወዳጅነቱን ባረጋገጠለ
መሰረት ዶኑ የጣለበትን ውለታ በትንሹ ምላሽ እንዲሰ
ሲጠየቅ መፈጸም መቻሉ ነው ።

መላው ተሳታፊ ፣ አስተባባሪና አሳላፊ ሳይቀር
የዶኑ ወይም የቤተሰቡ ወዳጆች ናቸው ። በዚያ የሰ
ርግ ስነ ስርአት ላይ ዶን ኮርሌዎኔ ከመግቢያው በር
ላይ ቆሞ ሀብታምና ደሀ ፣ ሀይለኛና ደካማ ሳይለይ
የተለመደ ባህሪው በሆነው እኩል ፍቅር ማሳየት ወዳ
ጆቹን ሁሉ ተቀበላቸው ። እንግዶቹም አለባበሱ እንዳ
ማረበትና እንዲያውም ያላወቀ ሰው እሱን እድለኛው
ሙሽራ ነው ብሎ እንደሚገምት በአድናቆት ገለጹለት ።
ዶን ኮርሌዎኔ እንግዶቹን ሲቀበል ሁለቱ ወንዶች ልጆቹ
ሶኒ እና ፍሬድ አብረውት ቆመዋል ። ታላቅ ልጁን
አባቱ በክርስትና ስሙ ሳንቲኖ እያለ ይጠራዋል ። ዘለግ
ያለው ግዙፉና መልከ መልካሙ ሶኒ ዝነኛ የሆነ
በት ባህርይና አቋም አለው ። በሰርጉም ላይ ከዳሌ
አቸው ሰፋ ሰፋ ያሉ ኮረዶች ሶኒን ለማሽኮርመም ቢጥ
ሩም ዛሬ ለነሱ ደንታ የለውም ። ይልቁንም የሚስቱና
የሶስት ልጆቹ መኖር እንኳን ሳያግደው ፣ በሰርጉ ዝግጅት
ሰሞን ሲያሽኮረምማት የሰነበተውና ዛሬ ጧትም በተስኪ
ያን ሳሉ እጁን ጨመቅ በማድረግ ጥሪ ያደረገችለት
ሉሲ ማንቺኒ ልቡን ሰርቃዋለች ። ደፋሩና ጉልበታሙ
ሶኒ አባቱን በአያሌው የሚረዳ ቢሆንም አባቱን ለመ
ተካት ያለው ብቃት ግን ብዙዎችን አጠራጥሯል ።

ፍሬድ የተባለው ሁለተኛው የዶን ኮርሌዎኔ ልጅ
መልከ ቀና ባይሆንም ማንኛውም ጣልያን እንዲያ
ያለ ልጅ ስጠኝ ብሎ የሚመኘው ትጉህ ፣ ታማኝና ላባቱ
ታዛዥ የሆነ ልጅ ነው ። ፍሬድ ከአባቱ ጋር የማይጣላ ፣
በአሳፋሪ የዝሙት ባህርይ አባቱን የማያስቀይም ፣ ያባቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምርኩዝ ነው ። ይሁን እንጂ ሰምችን ለመምራት የሚያ ስፈልገው ትእግስት ስለሌለው የቤተሰቡን አስተዳደር ተረክቦ ለመምራት ብቱ ነው ተብሎ አይገመትም ።

ሶስተኛውና የመጨረሻው ልጅ ሚካኤል ኮርሌ ዎኔ ከዚህ ሁሉ ትርኢት ርቆ አትክልቱ ውስጥ ወደ ዳር ካለው ሰዋራ ስፍራ ከሚገኘው ጠረጴዛ አጠገብ ቁጭ ቢልም የቤተሰቡ እንግዶች እይታ አልሳተውም። ካባቱ መመሪያ ውጭ በመሆን የሚታወቀው ይህ ወጣት ልዩ ባህሪው የፊቱ ቅርጽ እንደቤተሰቡ አለ መሆኑ ብቻ አይደለም ። በሴት ላይ ቢሆን ውብ የሚ ያሰኝ የቆዳው መለሳለስ ፣ ቡናማነትና መልከ ቀናነቱ ከቤተሰቡ ልዩ አድርጎታል ። እድሜው አስራ ሰባት ደርሶ ተባእትነቱ እስከተፈተሸ ድረስ የሚካኤል ወን ድነት አባቱን ሲያጠራጥረው ቆይቷል ።

ዛሬ ሚካኤል ከአባቱና ከቤተሰቡ ፈቃድ ውጭ መሆኑን በይፋ ያወጣበት እለት ይመስላል ። በወጉ ከቤ ተሰቡ ጋር ቢያስተዋውቃትም በቤተሰቡ ዘንድ ግን ተቃባይነት ያላገኘችው አሜሪካዊት ወዳጁ ኬይ አዳ ምስ ቅጥንጂም ፣ ውበቷም ፣ ንቁነቷም ፣ ስሟም ሁለመና ዋም የተለየ ነው ።

ዶን ኮርሌዎኔ የመጨረሻ ልጁን ሚካኤልን ችላ እንዳለው እዚያ የተሰበሰበው ሁሉ ተገንዝቦታል ። ሚካ ኤል በሁለተኛው አለም ጦርነት የዘመቻ ጥሪ ላይ የአባቱን ትእዛዝ ጥሶ በባህር ሀይል ተመዘገበ ። ቀድሞ ግን እንደ ታላቁ አባቱ ብልህ ፣ ሰምች ለሱ ከበሬታ ከመስጠት በስተቀር ሌላ ምርጫ ያልነበራቸው ፣ ያባ ቱን አድናቆት የተቀዳጀ ፣ ጊዜው ሲደርስም የስልጣኑ ተረካቢ እንደሚሆን ተስፋ የተጣለበት ነበር ። አባት ልጁ እንዳይዘምት ለዳሞች ጉቦ ሰጥቶ ከዘመቻው የሚ ቀርበትን ሁኔታ አደራጅቶለት ነበር ። እሱ ግን አሻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈረኝ ብሎ ዘመተ ። በዘመተባቸው የፓስፊክ ጦርነቱት ላይ ተዋግቶ ፣ ሻምበልነት ተሹሞ ፣ የመዳሊያ ተሸላሚም ለመሆን በቅቷል ። በ1944 'ላይፍ' በተባለው ዝነኛ መጽሄት ላይ ስለ ጀግንነቱ በመዘርዘር የወጣውን ጽሁፍና ፎቶግራፉን ቤተሰቡ አይቶ ዝም ቢልም የውጭ ዘመድ ላባቱ ወስዶ ቢያሳየው "ለዘመድ አይበሉት እንጂ ለባዳማ እንዲህ ያለ ተአምር ይሰራል" ሲል ተናግሯል ።

ሚካኤል ሳያውቅ በ1945 ላይ በከባድ ቁስሉ ሰበብ የጦር ጉዳተኛ ነው ተብሎ ከሰራዊቱ እንዲሰናበት አባቱ ባቀነባበረለት ዘዴ ወደ ቤቱ ቢመለስም ፣ ብዙም ከቤተሰቡ ጋር አልቆየም ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ዳርትሙስ ኮሌጅ ለመማር ጥሏቸው ሄደ ። ከዚያው ከኮሌጁ ከርሞ ሰርጉን ምክንያት በማድረግ ፣ ወዲያውም ዘመዶቹ ጣል ጣል ያደረጓት አሜሪካዊት ወጣት የወደፊት ሚስቱ መሆኗን ለማረጋገጥ ተመልሷል ።

ኬይ አዳምስ በሚካኤል ጨዋታና በሰርጉ ሁኔታ ተመስጣ ነበር ። ትኩረትዋን በተለይ የሳቡት ከወይን ጠጅ በርሜል ዙሪያ የተቀመጡት አሜሪጎ ቦናሴራ ፣ ናዞሬኔ ዳቦ ጋጋሪው ፣ አንቶኒ ኮፓላና ሉካ ብራሲ የተባሉ ሰዎች ሁኔታ ነበር ። ሰዎቹ ደስ ያላቸው አይመስሉም ። ሚካኤል ለአባቱ የሚያቀርቡት ጥብቅ ጉዳይ ስላላቸው ከሱ እርዳታ ሊሹ የሚጠባበቁ መሆናቸውን ገለጸላት ። እንዳለውም ዶን ኮርሌዎኔ ወደ ተንቀሳቀሰበት አቅጣጫ አይናቸው አብሮ ሲንከራተት ተመለከተች ።

ዶኑ እንግዶቹን ሲቀበል ሳለ ጥቁር ሼቭሮሌት አውቶሞቢል መጥታ ከመንገዱ ዳር ቆመች ። ከውስጡ የነበሩ ሰዎችም ማስታወሻ ደብተራቸውን አውጥተው ላሰርጉ መጥተው የቆሙትን መኪናዎች ታርጋ ቁጥር

t.me/OLDBOOKSPDF

መመገብ ጀመሩ ። ሶኒ ፖሊሶች እንደሆኑ በመግ
መት ተያናግሮ ሁኔታውን ላባቱ በነገረው ጊዜ ፣
''እኔ እነኑ የመንገዱ ባለቤት አይደለሁም !'' በማለት
መለሰለት ። ግንኙነታቸውን ተረድቶታል ። ቀደም ሲልም
ዶኑ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጓል ። የቅርብ ወዳጅቹ
የሆኑት ታርጋ በተለጠፈባቸው መኪኖች እንዲመጡ
ተነግሯቸዋል ። ሶኒ ኤፍ ቢ አይ የተሰኘው የአሜሪካ
የደህንነት ጥበቃ ድርጅት ሰራተኞች መሆናቸውን
በመገንዘቡ መደናገጡንና የማይረባ ቁጣ ማሳየቱን
አባቱ ባይፈልገውም ፣ በወቅቱ ለማስመሰል እንደሚጠ
ትም ይረዳዋል ። የስለላው ድርጅት አለመደናገጣቸውን
ከተገነዘበ ቀደም ሲል ተዘጋጅተውበታል በሚል ሌላ
ክትትል ከማድረግ እንደማይመለስ ዶኑ ስለሚያውቅ
የልጁ መናደድ ሰዎቹን በማርካቱ ግቡን እንደመታ
ተግንዝቦታል ። ሰው በሰው ላይ የሚያደርሰውን ውር
ደት ችሎ መቀበል ነው ። በዚህ አለም ላይ የመጨ
ረሻው ደካማ ሰው እንኳን ነቅቶ ከጠበቀ በመጨረ
ሻው ሀይለኛ ላይ ቁጭቱን መወጣት የሚችልበት
መቅት እንደሚመጣ የታወቀ በመሆኑ በዚህ መጽናናት
ይገባል ። ይህ ግንዛቤ ነው ዶኑን ያ ሰዎች የሚያደን
ቁለትን ትህትና እንዲቀዳጅ ያስቻለው ። በመሆኑም ፣
እንግዶቹ ሁሉ ስለመጡለት የደህንነት ሰራተኞቹን
ጉዳይ ችላ በማለት ልጆቹን አስከትሎ የሙዚቃ ቡድኑ
ጨዋታውን ወደ ጀመረበት የበአሉ ስፍራ አመራ ።

በሰፊው የአትክልት ስፍራ በተዘጋጀው ግብግ
ላይ ገሚሱ በአበባ ካጌጠው መድረክ ላይ ወጥቶ ሲጨ
ፍር የቀረው ደግሞ እቤት የተጠመቀ ጥቁር የወይን
ጠጅና በቅመም የተሰራ ምግብ በተደረደረባቸው ጠረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጌሣዎች ዙሪያ ተኮልኩሏል ። ሙሽሮቹና አጃቢዎቻ
ቸውም ከፍ ብሎ ባሸበረቀ መድረክ ላይ ሰፍራችውን
ይዘዋል ። ሙሽራይቱ ኮኒ ይህን በሽበሽ ሰርግ አባቷ
ሲያዘጋጅ ያልተቃወመችው በባል ምርጫ ላይ ያስቀ
የመችውን አባቷን ለመካስ ብላ ነው ።

መልከ ቀናው ሙሽራ ካርሎ ሪዘ. አባቱ የሲሲሊ
እናቱ ደግሞ የሰሜን አፓሊያ ተወላጆች ናቸው ። ወላ
ጆቹ ይኖሩበት ከነበረው ነቫዳ ሸሽቶ ወደ ኒውዮርክ
ሲመጣ ሶኒ ኮርሌዎኔን ፣ ኋላም እሀቱን ተዋወቀ ። የሙ
ሽሪት አባት ልጁ ካርሎ ሪዚን ለባልነት መምረጧን
ከተረዳ በኋላ የኋላ ታሪኩን ለማጥናት ወላጆቹ ከሚኖሩ
በት የነቫዳ ክፍለ ሀገር ሰዎች ላከ ። መልእክተኞቹ
ካርሎ ቀላል በሆነ የወጣትነት ህገወጥ መሳሪያ አጠ
ቃቀም ፣ እንዲያውም በቀላሉ የመረጃውን ደብዛ ማጥ
ፋት በሚቻል ጥፋት ከፖሊስ ጋር ግጭት ስለነበረው
ከፍለ ሀገሩን ለቆ መሔዱን የሚገልጽ መልስ ይዘው
መጡ ። በዚያውም ዶኑ ለብዙ ጊዜ ሲሻው የነበረውን
በነቫዳ ውስጥ ህጋዊ የቁማር ንግድ አመችነት በሚ
መለከት ዘገባም አሰሙት ። ከሁሉም ነገር ማትረፍ
ዶኑን ታላቅ ለመባል ያበቃው አንዱ ባህርይው ነው ።

ኮኒ ኮርሌዎኔ እስከዚህም ውብ ባትባልም ዛሬ
በነጭ የሙሽራ ልብሷ አሸብርቃ ቆንጆ ሆናለች ።
መልከ ቀናነቱ የማረካትን ባሏን ካርሎን ከጠረጴዛው
ስር እጅዋን በወጠምሻ ሞኑ ላይ አሳርፋ ደጋን ቅርጽ
ከንፈሯን አሞጥሙጣ በሩቁ ሳም አደረገችው ።

የካርሎ በልጅነቱ በገላጣ በረሃ የጉልበት ስራ ሲሰራ
ጀምሮ የዳበረ ክንድና ደረቱ በሙሽራ ኮቱ ዘልቆ
ያስታውቃል ። ሙሽሪት ለሱ ባላት አፍቃሪ እድናቆት
እየተዝናና ብርጭቆዋን ወይን ጠጅ ሞላበት ። ካርሎ
ለጊዜው ጥንቃቄ የተሞላበት ትህትና ለኮኒ እያሳያት

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ይሁን እንጂ ብዙ ገንዘብ ባዘሉ ፖስታዎች በተሞላ በቀኝ ትከሻዋ ላይ የተንጠላጠለ የሀር ቦርሳ ላይ አልፎ አልፎ አይኑን ተክሎ ማቁለሞለጩን አልተወም ። ምን ያህል ይሆን? አሰር ሺህ ብር ፣ ሀያ ሺህ? ፈገግ አለ ። ይህ ገና የመጀመሪያው ነው ። ምንስ ቢሆን ንጉሳው ያን ቢተሰብ ውስጥ ገብቶ የለ፣ ይንከባከቡት እንጂ ።

ከተሰበሰበው ሰው መሀል ሌላው የኮኒ ቦርሳ ያቋ መጠው ፖሊ ጋቶ የተባለ በቤተሰቡ የጥበቃ ስራ ላይ የተሰማራ ሽክ ያለ ልሙጥ እራስ ወጣት ነው ። ጋቶ ግንዘቡን እንዴት አድርጎ ከኮኒ ላይ እንደሚነጥቅ በአ እምሮው ሳያሰላስል አልቀረም ። ምኞቱ ከንቱ መሆኑ ታውቆታል ። ወደ ረኸርሙና ወፍራሙ አለቃው አይ ኑን አቀና ። እድሜው መካከለኛ ፣ ቁመቱ በጣም ረኸም ፣ አቋሙ እጅግ ግዙፍ የሆነው የፖሊ አለቃ ፒተር ክሌሜንዛ ከእንጨት በተሰራው መድረክ ላይ ታራቴላ በተባለ የጣልያን ባህላዊ ዳንስ ወጣት ልጃገ ረዶችን ይዞ ጠጣር ሆዱ ጡታቸውን መታከክ በሚያ ስችለው ጥበብ ሲያሽከረክራቸው ተመልካቹ በጭብ ጨባ ያስተጋባል ። እድሜአቸው ገፋ ያለ ሴቶች በሚ ቀጥለው ዘፈን አብረው ለመደነስ ሲጎትቱት ወጣቶች ወንዶች መድረኩን በከበሬታ ለቀቁለትና ያጨበጭ ቡለት ጀመር ። ክሎሜንዛ ከድካሙ የተነሳ ሶፋው ላይ ዘፍ ከማለቱ ፖሊ ጋቶ በጣም የቀዘቀዘ ጥቁር ወይን ጠጅ አቀብሎት ላቡን በሀር መሀረቡ ይጠርግለት ጀመር ። አለቃው ግን በምስጋና ፈንታ ፣

"ይልቅ የጭፈራ ዳኝነቱን ተወውና እየተዘዋወርክ የጥበቃ ስራህን ተከታተል" አለው ። ፖሊ ጋቶ ወዲ ያው ከተሰበሰበው ህዝብ መሀል ጠልቆ ተሰወረ ።

የሙዚቃው ቡድን እረፍት ሲያደርግ አንድ የመ ጠጥ ተጽእኖ በውብ ፊቱ ላይ የሚታይ ኒኖ ቫሌንቲ

t.me/OLDBOOKSPDF

የ·ነ·ባለ መጣት· የ·ኮ·ላለች· ማንያ·ሊ·ን አንስቶና እግሩን ወንበር ላይ ሰቅሎ የሲ·ሲ·ሊ·ን የጭቅር ዘፈን መጫወት ሲጀምር ሁ·ሉ·ም እየ·ተ·ቀበለ መሥሠሀ ቀጠለ ።

እንዲህ ያለውን ጉ·ዳይ አለመውደዱ የታ·ወቀው ዶ·ን ኮርሊዎኔ ፣ ሚስ·ቱ ሜሪ·ፊ·ራ·ው·ን እያያ·መቀች· ሳለች· በዘያ· ጥሎ ወጣ ። ሶ·ኒ ያነ·ቡን መወ·ጣት· ተመለከ·ተ ። ሚስ ·ቱም የሚቀር·በው· ኬክ ·ተ·ሟ·ል·ቶ እንደ·ሆነ ለማየት· ወደ ማደ·በ·ት· ገብታ·ለች· ። ሶ·ኒ ይህን ጊ·ዜ አመች· ሁኔታ· የ·ተ·ፈጠረለ·ት· መሆኑ·ን ስለገመ·ተ· የእህ·ቱ ሚዜ ከሆነ ች·ው· ሉ·ሲ· ማንቹ·ኒ ዘንድ ሄዶ ቁ·ጭ አለና በጆሮዋ አንሽካሽከ ። ሉ·ሲ· ሰሞ·ን የናወዘች·ለ·ት· ጥሪ መጣ ። የማፊ·ር ፊ·ግታ· የማይቀር ቢሆንም የሶስት· አመት ኮሌጅ ት·ምህር·ት·ዋ የጠራች· አሜሪካዊ·ት· አድርጓታ·ል ። ረዥም ጽጌረዳ ተ·ሚ·ሰ·ን ከባ· አድ·ር·ጋ ያ·ረጃ·ው·ን ከወጣች· በኋላ ወደ መታ·ጠቢ·ያ ቤ·ት· ገባች· ። ስት·ወጣም ሶ·ኒ ተ·ቀበላ·ት·ቱ ።

የሠግ መጸህፍ·ት· በ·ተ·ያ·ረ·ያ·ሩ·በ·ት· ከፍታ· ካለው ቢሮው ውስጥ ሆኖ የሶ·ኒ·ንና የሉ·ሲ·ን ሁኔታ· ሲከታ·ተ·ል የነበ ረው ቶ·ማስ ሄገ·ን የ·ተ·ባለው የዶ·ኑ ጠበቃና ተ·ጠባባቂ አማካሪ ጉ·ዳዮ·ን ለዶ·ኑ መንገር ያስፈ·ል·ግ እንደሆነ ካሰ ላሰለ በኋላ ች·ላ ብሎ·ት· ሌላ አቢይ ስራ መቀጠል እንዳ·ለ·በ·ት· ተ·ገ·ነ·ዘ·በ ። ዶ·ኑ·ና ዋናው ተ·ከታ·ዩ ሄገን ብዙ ው·ስ·ብ·ስ·ብ ች·ግሮች·ን በዚህ ቢሮ ውስጥ እልባት· አስ ይ·ዘ·ሞ·ል ። ዶ·ኑ· የበጎ·ሉ·ን ስፍራ ት·ቶ ወደ ቤ·ት· በመግ ባ·ቱ ሄገን በቢ·ሮ የሚሰራ ነገር እንዳ·ለ ገመ·ተ ። በግል ነ·ዶ·ኑ ጋር እንዲ·ነ·ጋገ·ሩ የመ·ዘ·ግ·ባ·ች·ው·ን ሰዎች· ስም ዝር·ዝር የያ·ዘ የእጅ ጽ·ሁ·ፍ ለዶ·ኑ አቀ·ረ·በ·ለ·ት· ። ዶ·ኑም ዝር·ዝ·ሩ·ን አየና ‘‘በ·ና·ሴ·ራ·ን በመ·ጨ·ረ·ሻ ታ·ቀ·ር·ብ·ል·ኛ ለህ’’ አለው ።

በት·ድ·ሚ·ያ የመግባ·ት· እድል የ·ተ·ሰ·ጠው ዳቦ ጋጋሪው ናዛሬኔ ንበርና ገና ሲገባ ዶ·ኑ በእቅፍ ሰላምታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀበለው ። ከሠጻንነቱ ጀምሮ በኢጣሊያ አገር አብሮ ደጉ የነበረው ናዞሪኔ ዛሬም አሜሪካ ከመጣ ወዲህ ምንኑ ወዳጅነት አላጓደለም ። ለትንሳኤ በአል ከአይብ ፣ ተፈተገ ስንዴ ፣ ውጪውን ከእንቁላሉ አስኳል ሁኖ የተጋጋረ የመኪና ጐማ የሚያህል ትኩስ ድፎ ዳቦ ለዶኑ ይልክለታል ። ለገና እና ለዶኑ ቤተሰብ ልደት በዓላት የሚላከው በበለጸገ ቅባት የተለጠለጠ ኬክ ናዞሪኔ ለዶኑ ያለውን ክብር መግለጫ ነው ። ዶኑ በወጣትነቱ ሳለ ላቋቋመው የዳቦ ጋጋሪዎች ማህበር ቢያጣም ቢያተርፍም ያለማሰለስ መዋጮውን ይከፍላል ። ከዚህ ማህበር ቢበዛ በጦርነቱ ወቅት የዋጋ ቁጥጥር አስተዳደር በስውር ገበያ የሚሸጠውን ዱስኳር ኩፖን ለመግዛት ከሚጠቀምበት በስተቀር ሌላ ውለታ ጠይቆ አያውቅም ነበር ። ዛሬ ግን የታማኝ ወዳጅነት ፍሬውን ለመቅመስ ዶኑ ዘንድ ቀርቧል ። ዶኑም ውለታውን ለመመለስ ወደ ኋላ አይልም ። ይልቁንም ሰውን ውለታ መጠየቅ እንደሚከብድ የተገነዘበው ዶን ናዞሪኔን ሲጋርና መጠጥ እየጋበዘ እንዲዝናናም ትከሻውን እየመታ ከመናገር ወደኋላ እንዳይል አደፋፈረው እንጂ ።

ናዞሪኔም የልጁን በኤንዞ ፍቅር መናወዝ ፣ የኤንዞን በጦር እስረኛነት አሜሪካ መጥቶ በይቅርታ መለቀቅና አሁን ግን ሰላም በመሆኑ ወደ ሀገሩ ኢጣልያ ለመመለስ እንደሚገደድና ልጁ ካተሪንም ፣ ኤንዞ ቢሄድ አንጀትዋ እርር ብሎ መሞቷ እንደማይቀር ፣ ከዚህ ችግርም የሚያወጣው የመጨረሻው ተስፋ ዶኑ ብቻ እንደሆነ አጫወተው ። ዶኑም ናዞሪኔ ጉዳዩን አውርቶ እስኪያበቃ ትከሻውን አቅፎ በክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደና ራሱን እየነቀነቀ በጽሞና ካዳመጠው በኋላ ፣

"ውድ ጓዴ ፣ ስጋትህን ሁሉ ወደ ጐን ተወው ።"

ት የሚደረገውን ያሸረዳው ጀመር ። "ዩአውራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጃው ምክር ቤት ተመካይ ለኤንዞ አሜሪካዊ ዜግነት የሚያሰጥ ልዩ የህግ ረቂቅ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት ። ረቂቁ እርስ በርሳቸው ውለታ በሚለዋወጡት የኮንግሬስ አባላት መጽደቁ አይቀርም ። ለዚሁ ስራ የሚመለከታቸውን ባለስልጣኖች ለመሸንገያ ሁለት ሺ ብር ያስፈልጋል" አለው ። ናዞሪኔ ይህን የመሰለ ውለታ በነጻ እንደማያገኝ ያውቀዋል ። ስለዚህ ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ እንደሆነ ዶኑ ሲጠይቀው በአምንታ መለሰለት ። ዶኑም ተገቢው ሁሉ እንደሚከናወን ባረጋገጠለት ጊዜ ከደስታው ብዛት የተነሳ እንባ እየተናነቀው ትከሻውን አቅፎ ስሞት ተሰናበተው ።

ሄገን ፈገግ አለና ፥ ይህ ሰው አማችና የእድሜ ልክ ረዳት በሌለት ሺህ ብር ብቻ ማግኘቱ ጥሩ ትርፍ ያለው ሥራ መሆኑን ለዶኑ ገለጸለት ። ቀጥሎም ከዚያ በኋላ ያለውን ጉዳይ የማስፈጸም ተግባር ለማን መሰጠት እንዳለበት ጠየቀው ።

"ስራው የሚሰጠው ላለንበት ወረዳ ባለስልጣን ሳይሆን በሌላው ወረዳ ለሚገኘው እስራኤላዊ ባለስልጣን ነው ። እንግዲህ ጦርነቱ ካበቃ ብዙ ተመሳሳይ ጉዳዮች መቅረባቸው ስለማይቀር ከቁጥር ውጭ እንዳይሆንና ዋጋውም እንዳይንር የሚጠብቁ ተጨማሪ ሰዎች በዋሽንግተን ሊያስፈልጉን ነው ። ለዚህ ስራ የምክር ቤት ተወካይ ሉቴኮን ተወውና ፊሸርን ምክር" በማለት ዶኑ መመሪያ ሰጠው ።

ተከታዩ ባለጉዳይ አንቶኒ ኮፓላ የሚባል ዶኑ በወጣትነቱ ዘመን በባቡር ጣቢያ አብሮት ይሰራ የነበረ ሰውዬ ልጅ ነው ። ወጣቱ ፒሳ መሸጫ ቤት ለመክፈት አስቦ የልዩ መጋገሪያና የሌሎች እቃዎችን ዋጋ ለመሸፈን የሚያስችል አምስት መቶ ብር ብድር ነው የመጣው ። ዶኑ ኪሱን ሲፈትሽ አራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብር ብቻ በግግኘቱ አንድ መቶ ብር ሄገን እንዲያበድረው ጠየቀው ። ዶኑን የመሰለ ሰው ሊበደር? ኮፖላ "አይሆንም! አራት መቶው ይበቃኛል" ቢልም ፥ ደግነት የግል መሆን አለበት የሚለው ዶን የጠያቂውን ትከሻ እየመታ ይኸ በሽበሽ ሰርግ ኪሱን እንዳራቆተው ገል ጸለት ብሩን ሞልቶ ሰጠው ።

ዶኑ እራሱን ቀና በማድረግ ተክታዩ ባለጉዳይ ማን እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ ። ሄገን ለእለቱ ከተዘጋጁት ሰዎች ውጭ ሉካ ብራሲ የተባለው በግል ዶኑን "እንኳን ደስ ያለህ" ለማለት የሚፈልገው መሆኑን ተናገረ ።

ዶኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅሬታ በማሳየት ፥ "ያስፈልጋል?" በማለት ሄገንን ጠየቀው ። ሄገንም ሰውየው ሳይጠብቀው በሰርጉ ላይ በመጠራቱ የተሰማውን ደስታ ለመግለጽ እንደሆነ በማግባባት ስላስረዳው እንዲገባ ፈቀደለት ።

በአትክልቱ ስፍራ በሉካ ብራሲ ፊት ላይ የሚታየው አውሬነት ያዘለ ቁጣ ኬይ አዳምስን አስደንቋታል ። ሚካኤል ቀድሞውንም ቢሆን እጮኛውን ኬይን ወደ ሰርጉ ስፍራ ያመጣት ያባቱን ማንነት እንድታውቅ ነበርና ሉካ ብራሲ ስለተባለው ሰው ስትጠይቀው በመጠኑ የሚያውቀውን ያህል ከመመለስ ወደ ኋላ አላለም ። ሉካ ብራሲ በአሜሪካ ምስራቅ ክፍል የወንጀል አለም ውስጥ እጅግ ከሚፈሩት ሰዎች አንዱ ነው ። የወንጀሉን ደብዛ ማጥፋትና የግድያ ወንጀልን ያለ ተባባሪ ብቻውን መፈጸም የሚችል ሰው መሆኑ ይታወቃል ። ብራሲ ሰራው የሚባለው ሁሉ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ሚካኤል እርግጠኛ ባይሆንም ይህ ሰው ያባቱ ወዳጅ እንደሆነ ፊቱን አጨፍግጎ ነገራት ። ኬይ አዳምስ እንዲህ ያለ አረመኔ ያባቱ ወዳጅ መሆኑ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስገረማት ። ሚካኤል "ከእንግዲህ ያበጠው ይፈንዳ ሁሉንም ትወቀውና የራሷን ውሳኔ ታድርግ" በሚል ቁርጥ ሀሳብ ወደኋላ መለስ ብሎ የሉካ ብራሲን ታሪክ ማውራቱን ቀጠለ ።

ከአሰራ አምስት አመታት በፊት የዶን ኮርሌዮኔን የዘይት አስመጪነት ንግድ ለመቆጣጠር ሲሉ የመገደል ሙከራ አካሄዱበት ። ዶኑ ግን በሉካ ብራሲ አማካይነት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የስድስቱንም ባላንጣዎቹን ህይወት በማጥፋት ዝነኛውን የወይራ ዘይት ጦርነት በድል አድራጊነት እንደተወጣ ሚካኤል ለእርኛው አጫወታት ። የእርኛዋ አባት በወረበሎች ሊገደል ሙከራ የተደረገበት መሆኑ ኬይን አስደነቃት ። ከዚያ ወዲህ ግን ነገሮች የተረጋጉ መሆናቸውን ሚካኤል ገለጸላት ።

"እንዳላገባህ እያስፈራራኸኝ ነው?" ስትል በፈገግታ ጠየቀችው ። እሱም ይህን ሁሉ የሚያጫውታት ሁሉንም ነገር ተረድታ እንድታስብበት መሆኑን ባስረዳት ጊዜ ትኩረቷን ወደሉካ ብራሲ በመመለስ ፥

"በእርግጥ ይህ ሰው ስድስት ሰዎች ገድሏል?" ብላ ሚካኤልን ጠየቀችው ። እንደ ሚካኤል አመላለስ ይህ ሁሉ ወሬ በጋዜጦች ላይ የተነገረ እንጂ ግንም ያረጋገጠው አይደለም ። ሉካ ከዚህ የባሰ አሰቃቂ ድርጊት እንደፈጸመ እንደሚነገርለትና እንዲያውም ዶኑ እንኳን ስለዚህ ሰው ሊያወራ እንደማይሻ አጫወታት ። ሚካኤል እራሱ የዚህ ሰው ሚስጥር እንዴት እንደሆነ ለማወቅ በመሻት በአንድ ወቅት ቶም ሄገን እንዲነግረው ቢጠይቀው "እድሜህ መቶ አመት ሲሆን ይነገርሀል" ብሎ እንደመለሰለት አጫወታት ።

በእርግጥም አጭሩ ድፋጩውና ትልቅ የራስ ቅል ያለው ሉካ ብራሲ ገሀነም ውስጥ ያለውን ሰይጣንንም ያስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈራል ። በአጭሙ ከአንድ ቦታ ላይ መገኘቱ ብቻ የአደጋ ምልክት ያስተላልፋል ። ፊቱ ቁጣ የታተመበት ፥ ቡናማ አይናቹ ሙቀትን ሳይሆን የሞትን መገርጣት የሚያ ሳዩ ፥ አፉ ጠባብ ሆኖ ላስቲክ የሚመስልና የብርንዶ ስጋ መልክ ያለው አስደንጋጭ ፍጡር ነው ።

ሉካ ብራሲ ፖሊስ አይፈራም ፥ ህብረተሰቡን አይ ፈራም ፥ ፈጣሪውንም ፥ ገሀነምንም አይፈራም ፥ መሰሉን የሰው ልጅንም አይፈራም ። ዶን ኮርሌዎኔን ግን መፍ ራትና መውደድን መርጧል ።

በአደገኛነቱ እጅግ የሚፈራው ብራሲ ለዶኑ የህ ይል መዋቅር አንዱ ዋልታ የሆነ ፥ ለዶኑ ያለው ታማ ኝነት አመጣጡ እንዴት እንደሆነ ለማወቅም ያዳገተ ልዩ ፍጡር ነው ።

በግንባር ለመነጋገር የነበረው ምኞት ተሳክቶለት ወደ ዶኑ እንዲገባ ባስተናገዱት ጊዜ አደገኛው ብራሲ ለዶኑ ካለው አክብሮት የተነሳ ደርቆ ቀረ ። ዶኑን እን ኳን ደስ ያለህ ለማለትና የመጀመሪያው የልጅ ልጅ ወንድ እንዲሆን መመኘቱን ለመግለጽ ተንተባተበ ። ቀጥሎም ለዶኑ ያለውን ታላቅ አክብሮት ለመግለጽ ሰው ሁሉ ከሚሰጠው ገንዘብ እንዲበልጥ አውጥቶ አው ርዶ ያዘጋጀውን ለሙሽራት ገጸ በረከት የሚሆን በብር የታጨቀ ፖስታ ለዶኑ አስረከበው ። ዶኑ የብራሲን ዘዴ አልባ ድርጊት በምስጋና አጸፋውን ሲመልስ ፥ አን ድ ንጉስ ታማኝ ሉሌውን በቤተሰባዊ ፍቅር ሳይሆን በን ጉሳዊ ወግ እንደሚቀበል በማስተናገድ በሱ ዘንድ አሁ ንም ብራሲ ዋጋ ያለው መሆኑን አረጋገጠለት ። ብራሲ ድንጋጤ ይታይበት የነበረው ፊቱ በደስታ ተለውጦ የዶ ኑን እጅ ስሞ ለሄገን ፈገግታም አጸፋውን ሰጥቶ ወጣ። ሉካ ብራሲ እንደፈንጂ በጥንቃቄ መያዝ ያለበትና ለቁ ጥጥር አስቸጋሪ የሆነ የተፈጥሮ ሀይል በመሆኑ በአ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለም ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ዶኑን ስለሚያስፈራው ይህን ሰው በመገላገሉ ከሰቃይ የመዳን ያህል ተነፈሰና "ቦናሴራ ብቻ ነው የቀረው?" ሲል ሄገንን ጠየቀው። ሄገን "አዎን" አለው። ዶኑም በሀሳብ ፈቱን ጨፈገገና ትልቁ ልጁ ሶኒ አንዳንድ ነገር መማር እንዲችል አስቀድሞ እንዲገኝ ለሄገን መመሪያ ሰጠው።

ሶኒ ከዚያች ልጅ ጋር ሲዳራ ቆይቶ ከሆነ ሚስቱ እና የልጅቷ ቤተሰቦች በሚያነሱት ግርግር ጉድ እንደ ሚፈላ በመገመት ሄገን ሰጋ።

ሚካኤል ቀድሞ ወንድሜ ነው ብሎ ለኬይ አዳምስ ያስተዋወቃት ቶም ሄገን የቤተሰብ ስሙ ከነሱ ሌላ በመሆኑ ስለማንነቱ ይበልጥ ለማወቅ እጮኛዋን ጠየቀችው። ወላጆቹ በመሞታቸው መሄጃ አጥቶ አይኑን ታሞ እየተሰቃየ በየመንገዱ ሲንከራተት ሶኒ አግኝቶት ወደ ቤታቸው እንዳመጣው፥ ከዚያም ከአስራ ሁለት አመት እድሜው ጀምሮ ሚስት እስካገባበት ጊዜ ድረስ አብሯቸው እንደኖረ አጫወታት። ኬይ አዳምስ እንዲህ የመሰለ ተቀባይነት፥ በተለይም የራሱ ልጆች ካሉት አባት፥ ሊደረግ መቻሉ እጅግ ስላስደነቃት ለምን የማደጎ ልጅ እንዳላደረጉት ጠየቀችው። ሚካኤል ሳቅ ብሎ አባቱ 'ልጅን በማደጎ ወስዶ ስሙን መቀየር ለልጁም ሆነ ለቤተሰቦቹ ክብርን መንፈግ ነው' የሚል ግምት እንዳለው አስረዳት።

ሄገን ሶኒን ወደ ዶኑ ቢሮ ካስገባ በኋላ አሜሪጎን በጣቱ ሲጠራው ኬይ ስለተመለከተች ለምን እንዲህ ባለው ቀን ዶኑን እንደሚያስቸግሩት ጠየቀችው።

ሚካኤል እንደገና ሳቅ አለና ምክንያቱን አስረዳት። ማንኛውም የሲሲሊ ተወላጅ ሴት ልጁን በሚድርበት እለት የሚጠየቀውን ሁሉ እምቢ እንደማይል የታወቀ በመሆኑ ይህን እድል ማንም ባለጉዳይ ሊያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳልፍ እንደግይሻ ገለጸላት ። በዚያ የበጋ ወቅት ለኮኒ ሰርግ ዝግጅት በሚደረግበት ሰሞን ሴቶች ለለሶኒ ብርታት ሲያወሩ ሉሲ ሰማች ። በኢጣሊያ ተወልዳ ከሠጓንነቷ ጀምሮ በአሜሪካ ያደገችው ደልዳላና የቀጭ የሶስት ልጆች እናት የሶኒ ባለቤት ሳንድራ ስለባሏ ሀይለኛነትና ሙቀት ስታወራ ሉሲ በጽሞና አዳም ጣታለች ።

"በመጀመሪያ ቀን በጫጉላ ቤት ባየሁት ጊዜ ገላው ከገላዬ ጋር እንደሚቀላቀል ሲታሰበኝ የሞትኩ ያህል እሪ ብዬ ጮኬያለሁ ። ከአንድ አመት በኋላ ግን ለአ ንድ ሰአት እንደተቀቀለ ማካሮኒ ሰውነቴ ላላ ። ሶኒ እን ዲህ ያለውን ነገር ሌሎች ልጃገረዶችም ላይ ፈጸመ ሲሉኝ 'ተመስገን' እልና በተስኪያን ሄጀ ሻማ አበ ራለሁ" በማለት ሳንድራ ሴቶቹን ስታስቃቸው ሉሲ ግን ከከፍተኛ ምኞት የተነሳ ሰውነቷን ሲነዝረው ተሰማት ።

የሶኒ ወይን ጠጅ መልኩና ክብ ቅርጽ ፊቱ ቢያ ስፈራትም በሰርጉ ሰሞን ስታጠምደው ከርማለች ። በኮ ሌጅ ውስጥ ባጋጠሟት ሁለት አጫጭር የፍቅር ወቅ ቶች ከወዳጆችዋ ጋር ተቀያይማ ተለያይታለች ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቀሪውን የኮሌጅ አመታት የጋበዟትን መጣ ቶች ሁሉ እምቢ ብላ አሳልፋለች ።

የዚያን እለቱን የሶኒ ጥሪ ተቀብላ ወደሱ በሮ ጠችበት ወቅት ከመጠን ያለፈ የስሜት ሙቀት በሰ ውነቷ እየተሠራጨ ነበር ። ስትደርስም ሶኒ ይዟት ወደ ባዶ ክፍል ከጎተታት በኋላ የተቃጠለ ሲጋራ ጣእም ያለውን ከንፈሩን አቀመሳት ። በሚዜ ቀሚሷ ያዘለቀው እጁ ገላዋን ሲዳስሰው ተሰማት ። ቀጥሎም ሱሪውን ሲፈታ አንገቱን አቅፋ በናፍቆት ተጠባበቀችው ። የስሜት መግ ለጫዎች ሁሉ ተጋጥመው ለተወሰነ ጊዜ በፈታደ ስጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲታ ውስጥ ኖሩ ። ዝናውን ከሰማችለት ሶኒ ጋር ፍቅር ለመለዋወጥ እድል ስለገጠማት በደስታ ፈነደቀች ። በመጨረሻም ሁለቱም በስሜት ጣሪያ ከደረሱ በኋላ ተዝ ለፈለፉ ። አንድ ሰው በሩን ባይቆረቁር ኖሮ እንደተደ ጋገፉ ለብዙ ጊዜ በቆዩ ነበር ። ሶኒ በቶሎ ተነስቶ ያልተቆለፈው በር እንዳይከፈት እየተከላከለ ሱሪውን ማጥበቅ ጀመረ ። ሶኒ ሱሪውን ሲቆልፍ ሉሲ ግን ያ ታላቅ ደስታ የለገሳት የሶኒ ገላ በጨርቅ ሲከፈን እያየች ተቁለጨለጨች ። እራሷን ስትገዛም የራሷንም ልብስ ማስ ተካከል ጀመረች ። በሩን የቆረቆረው ቶም ሄገን መሆኑን በተረዳ ጊዜ ሶኒ ከድንጋጤው ተንፈስ ብሎ ለምን እን ደሚፈልገው ጠየቀው ። ሄገንም አባቱ ቶሎ እንዲመጣ ማዘዙን በነገረው ጊዜ ሉሲን ስሞ ተለያት ። ሉሲም ልብሷንና ጸጉሯን አስተካክላ ከሙሽሮቹ ተቀላቀለች ።

አሜሪጐ ቦናሴራ መደ ዶኑ ሲገባ የተደረገለት አቀ ባበል ቀዝቀዝ ያለ ነበር ። ዶኑ አላቀፈውም ወይም እጁን አልጨበጠውም ። በቀብር አስፈጻሚነት የሚተዳደረው ግርጡ ፊት ቦናሴራ ግብግ የተደረገለት ስለሱ ሳይሆን በሚስቱና በዶኑ ሚስት መሀከል በነበረው ጓደኝነት ምክንያት ብቻ ነው ። ዶኑ በሱ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንደነበረበት ስለሚያውቅ አቀራረቡን በለሆሳስ አድ ርጎ እንዲህ ሲል ንግግሩን ጀመረ ።

"የባለቤትህ የክርስትና ልጅ የሆነችው ልጄ ዛሬ ስላልተገኘች ይቅርታ አድርግላት ። አሁንም ሀኪም ቤት ነው ያለችው" አለና በነሱ ፊት ለመናገር አለመ ፈለጉን ለማሳየት አይኑን ወደ ሶኒና ቶም አቃና ። ዶኑ ጉዳዩን መስማቱንና ልጁ የባለቤቱ የክርስትና ልጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

በመሆኗ እንዲያያዙርግለት የሚፈልገውን በግልጽ እን ዲጠይቀው ነገረው ። ቦናሴራ ፥ ወጉ እንደሚፈቅደው 'የጡት አባቴ' ብሎ ለመጥራት ያልፈለገውን ዶኑን ፥ ሶኒና ሄገን ክፍሉን ለቀው እንዲወጡና ብቻውን ሊያነ ጋግረው እንደሚፈልግ በአመዳም ፊቱ ሲግጠነው ዶኑ እንዲህ ሲል መለሰለት ፥

"እነዚህን ሰዎች ከማመኔ የተነሳ ነፍሴ በእጃ ቸው ናት ። ሁለት ቀኝ እጆቼ ስለሆኑ ውጡልኝ ብዬ አላስቀይማቸውም ።"

ቦናሴራ ምርጫ በማጣቱ ሀዘነተኞችን ሲያጽናና እንደሚናገረው በማስተዛዘን ንግግሩን ቀጠለ ። የአሜ ሪካ ዜጎች ለልጆቻቸው እንደሚያደርጉት ሁሉ እሱም ልጁ የቤተሰቧን ክብር ሳታዋርድ እንደልቧ እንድት ሆን አድርጎ ማሳደጉን መናገር ጀመረ ። ይህችው ልጅ ኢጣልያዊ ያልሆነ ወዳጅ አበጅታ ስታመሽ መከረ ሚን ፥ ይኸው ልጅ ትእቢተኛ እንደነበር ፥ አሜሪካም ይሀን ሁሉ ታግሶ መከረሙን ነገረው ። ከሁለት ወር በፊትም ከጓደኛው ጋር ወደ ውጭ በመኪና ሽርሽር ወስደዋት ዊስኪ አጠጥተው ሊደፍሯት ፈልገው እምቢ ስላለቻቸው እንደደበደቧት ፥ ሀኪም ቤት ሄዶ ሲያያትም አይናቿ ጠቁረው አፍንጫዋ ተሰብሮ ፥ የደቀቀው መን ጋጋዋን በሽቦ ተሰፍታ እንዳገኛት አይኖቹ እንባ አቅ ረው አወራለት ። ዶኑ ከፈቃዱ ውጭ በሚመስል ስሜት ራሱን በሀዘኔታ ነቀነቀ ። ቦናሴራም ሰብአዊ ሰቆቃን በሚገልጽ ስሜት ፥

"ለምንድነው ያለቀስኩት ? ተወዳጅዋ ልጄ ያይኔ ብርሀን ናት ። ቆንጅዬና ሰዎችን የምታምን ነበረች ። ከእንግዲህ ግን ደግማ አታምናቸውም ። እሷም ተመልሳ ቆንጆ አትሆን" በማለት ሲንቀጠቀጥ የገረጣ ፊቱ ወደ ብስል ቀይነት ተለወጠ ። ንግግሩን ቀጠለ ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደ ጥሩ አሜሪካዊ ወደ ፖሊስ ሄድኩ፥ ልጄ ቹም ታሰሩ። ለፍርድ ቀረቡ። የተረበባቸው መረጃ የተ ሟላ ነበር። እነሱም ጥፋታቸውን አመኑ። ዳኛው ግን ሶስት አመት እስር ፈርዶባቸው እስራቱንም በገደብ ስላነሳላ ቸው በነጻ ተለቀቁ። እኔም እንደቂል ቆሜ ሳለ በፈ ገግታቸው አላገጡብኝ። 'ፍትህ ከጡት አባታችን ማግ ኘት አለብን' ብዬ ለሚስቴ ነገርኳት" አለ።

ስለሰውዬው ሀዘን ዶኑ እራሱን ዝቅ ቢያደርግም ቀድሞውንስ ወደ ፖሊስ ለምን እንደሄደና ለምንሰ እሱ ዘንድ እንዳልመጣ በቅያሜ ጠየቀው።

ቦናሴራ በማጉረምረም፥ "ከኔ ምን ትሻለህ? የም ትፈልገውን ንገረኝ። የምለምንህን ግን ፈጽምልኝ" በማለት በድፍረት ተማጠነው።

ዶኑም ኮምጨጭ ብሎ "ምንድነው የማደርግልህ?" ብሎ ሲጠይቀው ፍላጎቱን ከመግለጹ በፊት አውንም ሄገንና ሶኒን ተመለከተ። ወደ ዶኑ ጸጉሯማ ጆሮ ጠጋ ብሎ በሚስጥር የሚሻውን ነገረው። ዶኑ በጽሞና ሙልሶ ተመለከተው። አድርግልኝ የሚለውም ከገደብ በላይ በሆነ የቁጣ ስሜት ተነሳስቶ የጠየቀው ስለሆነ ሊያደርግለት እንደማይችል መለሰለት።

ይህን ጊዜ "የፈለግከውን እከፍልሀለሁ" ብሎ ከፍ ባለ ድምጽ ቦናሴራ ተናገረ። የዚህ ሰውዬ ድፍረት ሄገንን አስበረገገው። መስኮቱ አጠገብ ቆሞ ወደ ውጭ ያይ የነበረው ሶኒም ወደ ክፍሉ ዞሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ላይ አተኮረ።

ዶኑ በቀዘቀዘ ስሜትና ለዘብ ባለ ድምጽ፥ ከቦና ሴራ ጋር ለብዙ አመታት በመተዋወቅ ቢኖርም ለም ክርም ሆነ ሴርዳታ እሱ ዘንድ መጥቶ እንደማያውቅ ገለጸለት። ሚስቱ የልጁ ክርስትና እናት ብትሆንም ሌላ ቀርቶ ቦናሴራ ቤት ቡና የተጋበዘበት እለት እን

t.me/OLDBOOKSPDF

ኳን ትዝ አንደማይለው ፡ ወዳጅነቱን የናቀበትና ውለታም ሊቀበል ሲፈራ የቆየ ሰው መሆኑን ሲነግረው ቦናሴራ በግጥሪምረም "ችግር ውስጥ መግባት አልፈለግኩም ነበር" ሲል መለሰለት ።

ዶኑ "ዝምበል ፡ ምንም አትናገር ። አሜሪካን ገነት ሆና አገኘሀት ። ጥሩ ገበያ ሰለ ነበረሀና ጥሩ ኑሮ ስላ በጀህ አለምም እንዳሻህ የምትደሰትባት ጉዳት አልባ ቦታ መሰለችህ ። እራስህን በመልካም ወዳጆች አላስ ታጠቀክም ። ከሁሉም በላይ ፡ ፖሊስ ስለሚጠብቅህና ህግ የሚያስፈጽሙ ፍርድ ቤቶችም ስላሉ አንተና መሰሎችህ አደጋ እንደማይደርስባችሁ ተማመናችሁ ። ስለዚህ ዶን ኮርሌዎኔን አልፈለግክውም ። ይሁን እንጂ ስሜቴ ቢቆስልም ለወዳጅነት ክብር ለማይሰጡና የሚንቁኝን ሰዎች በግድ ጓደኛዬ ሁኑ የምል ሰው አይደለሁም" አለ ።

ዶኑ አረፍ አለና ፖሽርደዳ ፈገግታ ካሳየው በኋላ ንግግሩን ቀጠለ ፡

"ዛሬ መጥተህ ፡ ዶን ኮርሌዎኔ ፍርድ ስጠኝ ትለኛለህ ። ስትጠይቅም በትህትና አይደለም ። በልጄ ሰርግ ቀን ቤቴ መጥተህ ሰው ግደልልኝና የፈለግኸውን እከፍልሀለሁ ትለኛለህ ። እንዲያው ለመሆኑ እንዲህ ክብር የምትነሳኝ ምን በድየሀለሁ ?" አለው ።

ቦናሴራ በስቃይና በፍርሀት እየጮኸ ፡ "አሜሪካ ለኔ ጥሩ ነበረች ። ጥሩ ዜጋ ለመሆን ፈልጌ ነበር ። ልጄም አሜሪካዊት እንድትሆን ፈልጌ ነበር" አለ ።

ዶኑ ሀሳቡን የደገፈለት ይመስል እያጨበጨበ ፡

"ግሩም ተናገርክ ። በጣም ረቂቅ ! ታዲያ የምታ ማርርበት ነገር ምንም የለማ ! ዳኛው ፈረደ ። አሜሪካ ፈረደች ። ልጅህን ልትጠይቅ ሀኪም ቤት ስትሄድ አበ ባና አንድ ቆርቆሮ ከረሜላ ውሰድላት ። ትጽናናለች ። አንተም በዚህ እርካ ። ደሞ እንጂ ፡ ይህኮ ከባድ ጉዳይ

t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም ። ልጆቹ ሰሜታቸው ትኩስ መሆኑን አት ዘንጋ ። አንዱም የሀይለኛ ፖለቲካ ሰው ልጅ ነው ። ውድ አሜሪካ ፡ ዘወትር የሞህነት ያጠቃህል ። ወዳጅ ነቴን የረገጥከው ቢሆንም የተናገርከውን ሁሉ እቀበ ለሞለሁ ። ቢሆንም ይህን እብደትህን ተው ። ይህ አሜሪካዊነት አይደለም ። ይቅር በል ። እርሳው ። ህይወት በመጥፎ ገጠመኞች የተመላች ናት ” ሲል አፈዘበት ።

የዱኑ ጥንቃቄ የተሞላበት ቁጣ ፡ ሜካኔና ጥላቻ ያዘለ ምጸት ፡ የቀብር አስፈጻሚ ባለሙያውን ቦናሴራን አርበተበተው ።

“ፍትህ ስጠኝ !” ሲል ቦናሴራ ዶኑን ተማጠነው ።

“ፍትህንማ ከፍርድ ቤት አግኝተሀል ።”

ቦናሴራ ድርቅ ብሎ እራሱን በመነቅነቅ “የለም ፡ እነሱ ለወጣቶቹ ነው የፈረዱት ። ለኔ ፍትህ አል ሰጡኝም ” አለ ።

እነዚህ ሁለት ነጥቦች በውል መለየታቸውን በማ ረጋገጥ ዶኑ እራሱን ነቀነቀና ፡

“ታዲያ የምትፈልገው ምንድነው?” ሲል ጠየቀው ።

“አይን ላጠፋ አይኑን ማጥፋት ።”

“አንተ የጠየቅኸው ከዚህ የበለጠ ነው ። ያንተ ልጅ እኮ በህይወት አለች ።”

“እሷ እንደተሰቃየች እነሱም ይሰቃዩ” አለ ቦና ሴራ ። ዶኑ ንግግሩን እስኪቀጥል ጠበቀው ። ቦናሴራ የመጨረሻ ድፍረቱን ፀማጠናከር አሁንም “ምን ያህል ልክፈልህ?” ሲል ተስፋ በመቁረጥ እያለቀሰ ጠየ ቀው ። ዶን ኮርሌዮኔ ይህን ሀሳቡን ባለመቀበል ጀር ባውን ሰጠው ። ቦናሴራ ግን ፍንክች አላለም ። ዶኑ በቦናሴራ ላይ ቅያሜ ቢኖርበትም ንቆት የነበረው ሰው ዛሬ እንዲህ ሲማጠነው በቁጣው መዝለቅ አልፈለገም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚገነዝ እረሳ ግርጥት ብሎ ወደ ቀጮው ቦናሴራ ፊቱን መልሶ እንዲህ አለው ፣

"ቀድሞውኑ ከኔ ጋር ወዳጅነት ለግጠበት ለምን ፈራህ? ፍርድ ቤት ሄደህ ፍትህ ለግኘት ብዙ መር ትጠብቃለህ ። ነሆለልነትህን በሚገባ የተገነዘቡ ጠበ ቆች ዘንድ ሄደህ ብርህን ታፈሳለህ ። እንደ መጥፎ ዝሙት አደር እራሱን ከሚሸጥ ዳኛ ፍትህን ትጠ ብቃለህ ። ቂመታት በፊት ገንዘብ ስትሻ ባንኮች ዘንድ ሄደህ ባርኔጣህን በእጅህ ይዘህ ስትጠባበቅ ፣ ዙሪያህን ሲያነፈንፉ ፣ ገንዘባቸውን ልትከፍላቸው የምትችል መሆ ንህን ለማረጋገጥ ውስጥህን ሲበረብሩ ቆይተው ካረ ጋገጡ በኋላ ድራሽህን በሚያጠፉ ወለድ ያበድሩሀል ። እኔ ዘንድ ብትመጣ ኖሮ ግን ቦርሳዬ ቦርሳህ ይሆን ነበር ። እኔ ዘንድ መጥተህ ቢሆን ኖሮ እነዚያ ልጅ ህን ያበላሿት ስድ አደጎች ዛሬ የደም እምባ ያለቅሱ ነበር ። በአንዳንድ መጥፎ አጋጣሚ አንተን የመሰለ የዋህ ሰው ጠላት ቢያበጅ ፤ ጠላቶቹ ጠላቶቼ ይሆናሉ ። እመነኝ ከዚያ በኋላ ጠላቶችህም ይፈሩሀል" በማለት አስረዳው ።

ቦናሴራ እራሱን ዝቅ አድርጎ ፣ "እባክህ ወዳጄ ሁን ። እኔም ከአሁን ጀምሮ ወዳጅነትህን እቀበላለሁ" ሲል ተማጠነው ።

ዶኑ ሰውየው ትከሻ ላይ እጁን አድርጎ ፣

"መልካም ። ፍትህን ታገኛታለህ ። እኔም አንድ ቀን—ያ ቀን ላይመጣም ይችላል—ብድሬን መልስ ብዬ አገልግሎት እጠይቅህ ይሆናል ። እስከዚያው ግን ዛሬ የግ ደርግልህን ውለታ ፣ የልጅህ የክርስትና እናት የሆ ነችው ሚስቴ ያደረገችልህ ውለታ እንደሆነ ቁጠረው" በማለት አሰናበተው ።

ቦናሴራ እንደወጣም ዶኑ ወደ ሄገን ሾሮ ለበቀል የሚያሰግራቸው ሰዎች በደም ሽታ ናውዘው ከልክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለፈ ጉዳት በነዚያ ወጣቶች ላይ እንዳይፈጽሙ መመሪያ ሰጠው ።

ሶኒ ከዚያ ሲደረግ የነበረውን መከታተል ትቶ በመስኮት በኩል የሰርጉን ሁኔታ ሲመለከት ዶኑ አጠናት ተስፋውን ቆረጠ ። ይህ ወጣት ቁምነገር መግር ካልቻለ የቤተሰቡን አጠቃላይ ሀላፊነት ለመረከብ ስለማይችል ዶኑ ሌላ ተተኪ በቶሎ ማዘጋጀት ይኖር በታል ። ማንም ሰው ቋሚ አይደለም መቸስ ።

ከግብግቡ ስፍራ ሶስቱንም ሰዎች ያስደነገጠ ጩኸት ተሰማ ። ሶኒ ወደ መስኮቱ ጠጋ ብሎ ወደ ውጭ ሲመለከት የአባቱ የክርስትና ልጅ ጆኒ ፎንቴን መሆኑን በማረጋገጡ እጅግ በጣም ደስ አለው ። ሄገንም "የክርስትና ልጅህን ወዳንተ ዘንድ እናምጣው?" በማለት ጠየቀው ። ዶኑም መጀመሪያ ሰዎቹ ከጠገቡት በኋላ ወደሱ እንዲመጣ ከነገረው በኋላ ፥ "አየኸው ጥሩ የክርስትና ልጅ ነው" በማለት ደስታውን አረጋገጠ ።

ሄገን ቅናት ጠቅ እያደረገው ፥ "ከመጣ ሁለት አመቱ ነው ። ምናልባት ችግር ላይ ስለወደቀ እርዳታ ሊጠይቅህ መጥቶ ይሆናል" አለ ።

ዶኑም "ታዲያ ችግር ሲገጥመው የክርስትና አባቱ ዘንድ ያልመጣ የት ሊሄድ ኖሯል ?" በማለት ጥያቄ ያዘለ መልስ ሰጠው ።

ጆኒ ፎንቴንን በቅድሚያ ያየችው ሙሽሪት ኮኒ ሄዳ ስትጠመጠምበት አፏን ሳማት ። ሌሎች የጥንት ወዳጆቹም ከበቡት ። ኮኒ ጆኒ ፎንቴንን ከሙሽራው ጋር ለማስተዋወቅ ጮትታ ወሰደችው ። ሙሽራው የእለቱ ኮከብነቱን ጆኒ የተሻማበት ስለመሰለው ቅሬታ ገብቶት ቢቀዘቅዝም ጆኒ እጁን በመጨበጥና ዋንጫውን አንስቶ ለጤናው በመጠጣት አግባባው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሙዚቃው መድረክ አካባቢ "ምናለ አንድ ዘፈን ብታሰማን ?" ሲል የድሮ የልብ ወዳጁ ኒና ቫሌንቲ ጠየቀው ። ጆኒ ሮጦ ሄደና ኒናን አቀፈው ። ጆኒ ለሆሊውድ ተዋናይነት እስከበቃበት ወቅት ድረስ ከኒና ጋር አብረው ልጃገረዶች የሚያወጡ ፣ አብረው የሚዘፍኑ ፣ የማይለያዩ ጓደኛሞች ነበሩ ። ጆኒ ሆሊውድ ከሄደም በኋላ በተግባር አያውለው እንጂ ለኒና በማታ ከበብ የዘፋኝነት ስራ እንደሚያገኝለት ቃል ገብቶለት ነበር ። ደጋግሞም ስልክ ደውሎለታል ። ኒናን ሲያየው የድሮ ትዝታው ተቀሰቀሰበት ።

ኒና ማንዶሊኑን ሲከረክር ጆኒ ትከሻውን አቅፎ ለሙሽሪት ክብር የጥንት የሲሲሊ ሙዚቃ ማዜም ጀመሩ ። ሰዉም ተቀበላቸው ። ይኸኛው ዘፈን ሲያልቅ ጆኒ ሌላ ዘፈን ቀጠለ ።

ጆኒ በዘፋኝነቱ ታውቆ በአለም ዝነኛ ከሆኑት የፊልም ተዋንያን ጋር መዳራት እና የሀምሳ ሚሊዮን ሴቶችን ልብ መማረክ ቢችልም የክርስትና አባቱን አልረሳውም ። ሶስት ሺህ ማይል አቋርጦ በሰርጉ ላይ ተገኝቷል ። የቀድሞ ወዳጆቹንም ቢሆን ይወዳቸዋል ።

ኮኒን መሀከላቸው አድርገው ፣ ኒኖ ማንዶሊኑን እየከረከረ የሲሲሊ ባህላዊ ዘፈናቸውን ቀጠሉ ። ጨዋታው 'እኔ ላግባሽ ፣ እኔ ላግባሽ' በማለት በሁለቱ ወንዶች መካከል የሚካሄድ የፌዝ ፍልሚያ ሲሆን ፣ ድምጻቸውን የጉራዴ ውጊያ በማስመሰል ተራ በተራ አዝማች እየተቀያየሩ የሚያዜሙት ነበር ። በዘፈኑ ላይ የኒኖ ድምጽ እንዲያይል ፣ ኒኖ ሙሽሪቱን እንዲቀማና ፣ የድል አድራጊነት ዜማ እንዲዘፍን በማድረግ ጆኒ በትህትና የራሱን ድምጽ አከሰመው ። በመጨረሻ ህዝቡ በደስታ ሲያጨበጭብ ሶስቱም ተቃቀፉ ። እንግዶቹም ጨዋታው ስለጣማቸው ሌላ ዘፈን እንዲዘፈንላቸው ጠየቁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶኑ ግን ማንም ሳይገነዘበው እንድ ነገር እንደ ጐደለ በመረዳቱ እንግዶቹ እንዳይቀየሙ በመጠንቀቅ ፣

“ክርስትና ልጄ ለኛ ክብር ሶስት ሺህ ግይል አቋ ርጠ ሲመጣ ማንም ጉረሮውን አያርሰው ?” ሲል ሙሆ ተናገረ ። ከመቅጽበት ደርዘን የሚሆኑ ወይን የተ ሞሉ ብርጭቆዎች ለጆኒ ፍንቴን ቀረቡለት ።

ከዋንጫዎቹ ሁሉ በተራ ተጎንጭቶ ሲያበቃ ፣ ሮጠ ክርስትና አባቱን አቅፎ ሳመው ። ወድያውም በጆ ሮው አንድ ነገር ሲነግረው የክርስትና አባቱ ይዘት ወደ ቤት ገባ ። መንገዱ ላይ ቶም ሄገን ለሰጠው ሰላ ምታ ጆኒ የሰጠው መልስ ቀዝቀዝ ያለ ነበር ። ጆኒ ለዶኑ “የሰርጉ ጥሪ ሲደርሰኝ የክርስትና አባቴ ቁጣው በር ዷል ብዬ አሰብኩ ። ነገር ግን አምስት ጊዜ ብደውልም ቶም ሰራ ይዟል እያለ ሲያገናኘን ስላልቻለ እንደተ ቆጣኸኝ ተገነዘብኩ” አለው ።

ዶኑ ግን ያለፈው ቁጣው ሁሉ የተረሳ መሆኑን ካረጋ ገጠለት በኋላ ምን እንዲያደርግለት እንደሚፈልግ ጠየ ቀው ። ጆኒ ዶኑ ከሚቀዳለት መጠጥ እየተጎነጨ የደረሰበትን ውድቀት አጫወተው ። ሀብቱም እሱም እያቆለቆሉ መሄዳቸውን ፣ ከሚስቱና ከልጆቹ ተለያ ይቶ ያቺን ዝሙተኛ ሴት በማግባቱ እጅግ እንደተሳ ሳተ ፣ በዚህም ዶኑ መቀየሙ ትክክል መሆኑን አረጋ ገጠለት ።

ክርስትና አባቱ ስለክርስትና ልጁ የሚያስብ መሆ ኑን ባረጋገጠለት ጊዜ ጆኒ ሁለተኛ ሚስቱ ያደረሰች በትን በደል መዘርዘር ጀመረ ።

“ለዚያች ውሻ አብጀላት ነበር ። የሆሊውድ እውቅ ኮከብ ነች ። መልአክ ትመስላለች ። አንድ ፊልም ከሰ ራች በኋላ ምን እንደምታደርግ ታውቃለህ፣ በኪስ ውስጥ የተገኙ ጥቂት ሳንቲሞች በጉርሻነት እንደሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወረዉ ሁሉ እሷም ገላዋን እንደዚያ ትሚወትበታ ለች ።"

ይህን የሚሰቀጥጥ ንግግር ዶኑ ማዳመጥ አልፈ ለገም ። ይልቁንም ስለቤተሰቡ ደህንነት እንዲያወ ራለት ጠየቀው ። ጆኒም ፍርድ ቤት ከወሰነው በላይ ለሚስቱና ለልጆቹ ተቆራጭ እንደሚሰጥ ፣ በየሳም ንቱ እየሄደ እንደሚጠይቃቸውና እንደሚናፍቃቸው በመግለጽ መለሰለት ። ጆኒ እንደገና ስለሁለተኛ ሚስቱ ማውራቱን ቀጠለ ። ሴትየዋ እንደምታላግጥበት ፣ ቅና ቱን እንደማትረዳለት ፣ "አስተሳሰብህ ኋላ ቀር ነው" እን ደምትለው ፣ በዘፈኑም እንደምታላግጥ ፣ ወደ ዶኑ ዘንድ ከመምጣቱ በፊትም እንደደበደባት ምርር ብሎ አስ ረዳው ።

ለዚህ ምሬቱ ዶኑ የሰጠው መልስ ፣ "እንዲህ ባሉት ችግሮች እኔ ልረዳህ አልችልም" የሚል ነበር ። ቀጥሎም ምን ነክቶት ድምጹ እንደተበላሸ ሲጠይቀው የችግሩን ሚስጥር ሀኪሞችም ሊረዱት ባለመቻላቸው መፍትሄ ስላልተገኘለት ከእንግዲህ ሊዘፍን እንደማይ ችል በተሰበረ አንደበት አስረዳው ። ያ ጠንካራ ኮከብ እንዲህ መፈታቱ ዶኑንና ሄገንን አስገረማቸው ።

"ቀድሞ የሰራኋቸው ሁለቱ ፊልሞቼ ብዙ ገን ዘብ አስገኙ ። ትልቅ ኮከብ ተዋናይ ለመሆን በቅቼም ነበር ። አሁን ግን ከሰራዬ ተባርሬአለሁ ። የፊልም ድር ጅቱ የበላይ ጠልቶኛል ። የተፈራረምነውን ውልም ሰር ዞታል" በማለት ጆኒ የደረሰበትን በደል ለክርስትና አባቱ አሜወተው ። ዶኑ ለምን ይህ ሰው እንደሚጠ ላው ጠየቀው ። ቀደም ሲል ዶኑ እንኳን የተቃወመ ውን የፖለቲካ ሽኩቻ ዘፈን መዝፈኑ በጽክ ዎልትዝ ባኩልም ጥላቻ ስላስከተለበት 'ኮሚኒስት' እያለ ይጠ ራው እንደነበር ገለጸ ። ከዚያ በኋላም ዎልትዝ ለራሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያስቀመጣትን አንዲት ቆንጆ ልጅ ቀምቶት ሳለ ልጅቷም ጀኒን የሙጥኝ በማለቷ ጃክ ምልትዝ ቂም መያዙን ጀኒ ፍንቴን አልደበቀም ።

ያቺ ዝሙተኛ ሚስቱ ስላባረረችው ፣ የቀድሞዋ ሚስቱ እና ልጆቹም ጀኒ በእጅና በእግሩ ድሆ ካልለመ ናቸው እንደገና ሊቀበሉት እንደማይፈቅዱ ስለሚያ ውቅ ፣ የዘፈን ችሎታውም ስለተናጋ ከዚህ በኋላ ምንም ሊያደርግ የሚችል መስሎ እንዳልታየው ለክ ርስትና አባቱ ተስፋ ቆርጦ ነገረው ። የክርስትና አባቱ ግን በማዘን ፋንታ በቁጣ ፣

"ጠንካራ ሰው በመሆን መነሳት ትችላለህ"

ሲል ጮኸበት ። ቀጥሎም ፣ "ጠንካራ ሰው!" ብሎ ጮኸ በትና ፣ ፍቅር በተሞላበት ንዴት ጸጉሩን ጨመደደው ። ያ ዝነኛ የሆሊውድ ተዋናይ ፣ እንዲህ በመሰለ ሁኔታ አድነኝ ብሎ ሲማጠንና እንደሴት ልጅ ሲያለቅስ ፣ "ምን ልሁን? ምን ላድርግ?" ብሎ ግራ ሲጋባ ማየት ዶኑን እጅግ አናደደው ።

ዶኑ "ምን ላድርግ? ምን ልሁን ?" እያለ የጀኒን አባባል አስመስሎ ሲያፌዝ ቶምና ጀኒንም አሳቃቸው ። ዶኑ ግን በልቡ ተደሰተ ። የወለዳቸውም ልጆች ቢሆኑ እንዲህ የመሰለ የምላስ ጅራፍ ቢጥልባቸው እንደ ሚያኮርፉትና በጸጋ እንደማይቀበሉት ያውቀዋል ።

ሳንቲኖ ቢሆን ለሳምንታት ያኮርፍ ፣ ሚካኤል ቢሆን ደግሞ ቤቱን ለቆ ይወጣ እንደነበር ዶኑ ያውቃል ። ነገር ግን ጀኒ የክርስትና አባቱን ቁጣ አላማ ተረድቶ በጽሞና ማዳመጡ ዶኑን አስደሰተው ።

ዶኑ ንግግሩን ቀጠለ ፤

"ካንተ ይበልጥ ሀይለኛ የሆነውን የአለቃህን ሴት ቀምተህ ስታበቃ 'ሊያግዘኝ አልፈቀደም' ብለህ ታማርረዋለህ ። ምን ያለ ፉይዳ ቢስነት ነው ? ለዝሙተኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት ብለህ ልጆችህን ያላባት ተውካቸው ። ትዳርህን ፈተህ ስታበቃ አሁን ደግሞ ለምን እሷቸውን ዘርግ ተው አልተቀበሉኝም ብለህ ታዝናለህ ። ዝሙተኛ ሚስ ትህ ስታስቀይምህ ፊልም ትሰራለች ብለህ ፊቷን አት መታም ። ለዚህም ስለሳቀችብህ ትገረማለህ ። የነሆለለ ህይወት በማሳለፍህ መጨረሻህ ጅል ሆነ" አለው ።

ዶኑ ጥቂት አረፍ አለና ፥ "አሁን ምክሬን ትሰ ማለህ ?" ሲል ጠየቀው ። ጆኒም ከስጋት የተነሳ ፥ እሺ በማለት ፋንታ ፥

"ጂኒን ታረቃት የምትለኝ ከሆነ እሷ በምትፈል ገው አይነት አልታረቃትም" አለው ። "እንደልቤ ቁማር መጫወት ፥ መጠጣትና ከጓደኞቼ ጋር መዝናናት እፈ ልጋለሁ ። ቆንጆዎች ሲያሳድዱኝ መከላከል አልችልም ። ከነሱ ጋር ውዬ ጂኒ ዘንድ ተመልሼ ስሄድ ወራዳ ስራ የሰራሁ ይመስለኛል ። ስለዚህ ወደ ተፋሁት ነገር አል መለስም" አለ ።

በዶኑ ላይ ያልተለመደ ቁጣ ገነፈለ ። "ሚስትህን ታረቃት አላልኩህም ። እንተ የምትሻውን ማድረግ ትች ላለህ ። ለልጆችህ ማሰብህ መልካም ነው ። የልጆቹ አባት መሆን ያልቻለ ሰው እውነተኛ ሰው አይደለም ። ነገር ግን የልጅህ እናት እንድትቀበልህ ማድረግ ይኖርብህል ። በቀን በቀን ልታያቸው አትችልም ያለህ ማነው ? አንድ ቤትስ አብራችሁ ልትኖሩ አትችሉም ያለው ማነው ? ህይወትህን መምራት በምትፈልገው አይነት ልትመራስ አትችልም ያለህ ማነው ?" አለ ዶኑ ።

ጆኒ ፎንቴን ሳቀና "የክርስትና አባቴ ፥ ሁሉም ሴቶች እንደ ድሮ የጣልያን ሚስቶች አይምሰሉህ ። ጂኒ ይህን አትቀበልም" ሲል መለሰለት ።

"የማትቀበልህ ሴታሴት ስለሆንክባት ነዋ ! ያል ጠበቀችውን ፥ ፍርድ ቤት ከወሰንላት በላይ ሰጠሀታ ! ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌላይቱ ሚስትህ ደግሞ ፊልም ስለምትሰራ ፊቷን አል መታህትማ! በጽሞና እንደተመለከትኩህ ሴቶችን የበ ላይ ገዥዎችህ አድርገሀቸዋል" አለው።

ቀጥሎም ልባዊ በሆነ አገላለጽ፥ "መልካም ክር ስትና ልጅ ነህ። ለኔ የሚገባኝን ክብር ሁሉ ሰጥተኸኛል። ግን ሌሎች የዱሮ ጓደኞችህ እንዴት ናቸው? አንዱን አመት ከዚያ፥ የሚቀጥለውን አመት ከሌላው ጋር እና እፍ እፍ ትላለህ። ያ በፊልም ላይ ይኮምክ የነበረው ኢጣ ሊያዊ ልጅ መጥፎ እድል ቢገጥመው አንተ ባለገዘና በመሆንህ ንቀኸው አይተኸውም አታውቅ አሉ። ድሮ አብረኸው ትዘፍን የነበረው የጥንት ጓደኛህን ኒኖንስ ምን አደረግህለት? ከዚያ ጠጠር የሚጭን መኪና የመ ንዳት አድካሚ ስራ የታለ የገላገልከው? ደህና መዝ ፈን ይችል ነበር" ሲለው ጆኒ ፎንቴን፥ ድምጹ ደህና ቢሆንም ኒኖ ለታላቅ ስራ የሚውል ችሎታ እንደሌ ለው ለማስረዳት ሞከረ። ዶኑ ግን አልተቀበለውም።

"እንግዲያውስ አንተም የድሮ የዘፋኝነት ችሎታህ ስላሽቆለቆለ ከኒኖ ጋር እንድትሰራ የጠጠር መኪና ሹፌርነት ልፈልግልህ?" በማለት ልብ የሚነካ ጥያቄ አቀረበለት። ጆኒ ይኸኔ መልስ ማግኘት አልቻለም። ዶኑም ጓደኛነት ከችሎታም ሆነ ከሁሉ ነገር በላይ መሆ ኑን እንዳይረሳ አስገንዝበው።

"የጓደኝነት መከታ አበጅተህ ቢሆን ኑሮ ዛሬ የኔን ድጋፍ አትጠይቅም ነበር። ለመሆኑ ለምን ልትዘፍን አልቻልክም? በአታክልቱ ስፍራ ጥሩ ዘፍነህ ነበር። ከኒኖም እኩል ዘፍነህል" ሲል ጆኒ ፎንቴን የኒኖን ችሎታ እንዲያጤን ግፊት አደረገበት። ይህን አሽሙር ሲሰሙ ቶም ጆኒ ፎንቴንም ፈገግ አሉ።

ጆኒና ድምጹ መድከሙን፥ ሁለት ወይም ሶስቱ ከዘፈነ በኋላ ለሰአታት፥ እንዲያውም ለቀናት መዝፈን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚያቅተው ፥ በዚህም የተነሳ በልምምድ ላይ ለመ
ሳተፍ እንዳዳገተው ለዶኑ ገለጸለት ።

ዶኑም የጆኒ ፎንቴንን ችግሮች እየደረደረ ፤

"በሴት ችግር ገጥሞህል ። ድምጽህ ታውኳል ። ደግሞስ ከዚያ የሆሊውድ ከባድ ሰው ነኝ ባይ ጋር ለመስ ራት ያጋጠመህ ችግር ምን ይሆን?" ሲል ጠየቀው ።

"እሱ አንተ ከምታዛቸው ከባድ ሰዎች የላቀ ነው። የፊልም ማቀናበሪያው ድርጅት ባለቤት ነው ። የአሜሪ ካንን ፕሬዚዳንት ጦርነቱን በሚመለከት ስለሚዘጋጅ የሲኒማ ፕሮፓጋንዳ ያማከረዋል ። ከአንድ ወር በፊት ለአመቱ ታላቅ ልቦወለድ የሲኒማ ባለመብትነቱን ገዝ ቷል ። በዚያ ፊልም የሚኖረው ዋና ባህርይ እንደኔው ያለ ጉብል ነው ። ይህን ፊልም ብሰራው ብዙ ሳልቸገር በት የአካዳሚ ተሸላሚ ለመሆን እበቃበት ነበር ። ለኔ ተስማሚ እንደሚሆን ሁሉም ይናገራል ። ነገር ግን ባነሰ ዋጋ እንዲያውም በነጻ ልስራልህ ብለውም ያ ምልትዝ የሚሉት ዲቃላ እምቢ አለኝ ። 'ምናልባት ስቱዲዮ መጥቶ ባደባባይ ጫማዬን ከሳመ አስብበት ይሆናል' ብሏል አሉ" በማለት ጆኒ ከምልትዝ የተሰጠውን ቁርጠኛ ውሳኔ ለዶኑ ገለጸለት ።

ዶኑ የጫማ መሳም ወሬ ሲነገረው ችላ በማለት እጁን አራገበ ። በአእምሮዋቸው በሚጠቀሙ ሰዎች መሀከል የስራ ችግሮች በድርድር ሊፈቱ እንደሚችሉ በማመን ፥ ጆኒ ስጋት እንዳይገባው አጽናናው ። ቀጥ ሎም ጆኒ በመጠጥ እና በሚዋጡ የእንቅልፍ እንክብ ሎች የተጎዳ ስለሆነ መፍትሄ ሊፈልግለት መወሰኑን ነገረው ። ይኸውም ለአንድ ወር ከዶኑ ግቢ ሳይወጣ በደንብ እየተመገበ እረፍት እንዲያደርግ ፥ ሳይለየው አብሮት እንዲከርምና ለወደፊት ኑሮው የሚጠቅመው ሀሳብ ከዶኑ እንዲቀስም ፤ ከዘፈን ፥ ከመጠጥና ከሴት

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈጽሞ እንዲቆጠብ ፥ ይህን ካደረገም ያ ከባድ ሰው ነኝ ባይ ሰራውን እንዲሰጠው እንደሚያዩርግ አረጋገ ጠለት ።

ዶኑ የነባለትን ቃል እንደሚፈጽም ጆኒ ቢያምንም ጃክ ዎልትዝ ኤድጋር ሁቨርን የመሰሉ ሀይለኛ ባለስ ልጣኖች የግል ወዳጅ በመሆኑ ፥ ሌላ ቀርቶ ዶኑን ፥ ሊያ ናግረው ፈቃደኛ እንደማይሆን ሲነግረው ፥ "ግድየለም ነጋዴ ነው ፤ እምቢ ሊል የማይችለው ድርድር አቀርብ ለታለሁ" በማለት ጆኒን ሊያረጋጋው ሞከረ ። ነገር ግን ጉዳዩ ተስፋ የሌለው መሆኑን ጆኒ ስለሚያውቅ ለዶኑ እንዲህ አለው ፥

"አሁንማ ለሁሉም ነገር ጊዜው አልፏል ። የስራ ውል ተፈራርመው ጨርሰው ከሚቀጥለው ሳምንት ጀም ረው ፊልም ማንሳት ይጀምራሉ ።"

ዶኑ ይህ የጆኒ አባባል አሳሰጋውም ። ይልቁንም በቅ ልታ ፥ "ወደ ግብሣው ሂድ ወዳጆችህ ይጠብቁሀል ። ሁሉንም ነገር ለኔ ተወው" በማለት ከክፍሉ ገፍቶ አስወጣው ።

ከዚህ በኋላ የቀረ ምን ነገር እንዳለ ዶኑ ሄገንን ሲጠይቀው ፥ ቨርጅል ሶሎዞ የተባለ የአደንዛዥ እጽ ነጋዴ ብዙ ጊዜ ዶኑን ለማየት እየፈለገ ሳይሳካለት ቀርቶ ዛሬም እየጠበቀ መሆኑን ነገረው ። ይህን ሰው ለማየት የሚችለው የሰርጉ ሰነ ሰርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ እንደሚሆን ሲገለጽለት ሄገን ለዚህ አባባል ሁለት ትርጉም ሰጠው ። አንዱ በዚያች ሰአት ዶኑ ሶሎዞን ለማየት አለመፍቀዱን ፥ በሌላም በኩል የልጁ ሰርግ ከግብቃቱ በፊት ለሶሎዞ ጥያቄ አይሆንም የሚል መልስ ሰጥቶ ውዝግብ እንዳይከተል መስጋቱን ነው ።

ሶሎዞ የሚያቀርበው ጥያቄ ዶኑ በማይቀበለው የወንጀል ድርጊት ላይ እንዲመሳጠሩ የሚጋብዝ መሆ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኑን ቀድሞ በመረዳቱ እምቢታውን በልጁ ሠርግ እለት ማሰማት ባለመፈለጉ ውሳኔውን ከሰርጉ በኋላ እንደሚያስታውቀው ለሄገን ገለጸለት ። ሄገን ግን ዶኑ ኋላ የሚሰጠው መልስ እምቢታ መሆኑን በመገንዘቡ ፣ ምናልባት ይህን ውሳኔውን ማስለወጥ እንዲቻል ቤተሰቡ እንዲ መክርበት አሳብ አቀረበለት ። ዶኑም "ከመሰለህ ይሁን" ካለው በኋላ ፣ ከዚያ በፊት ግን የጆኒ ፎንቴንን ጉዳይ ለመጨረስ ሄገን ወደ ካሊፎርኒያ እንዲበር ፣ ሶሎዞንም ሄገን ሲመለስ እንደሚያነጋግረው እንዲነግረው መመሪያ ሰጠው ።

ከዚያ በኋላ "ምን ቀረ?" አለው ዶኑ ። አባን ዳንዶ የተባለው የዶኑ የቀድሞ አማካሪ በካንሰር በሽታ ሲሰቃይ ከርሞ ከዚያ ምሽት በላይ ሊቆይ እንደማይችል ከሆስፒታል ተደውሎ እንደተነገረው ገለጸለት ።

አማካሪ ጆንኮ አባንዳንዶ ካንሰር ይዞት ላለፉት ሁለት አመታት ያልጋ ቁራኛ ከሆነ ጀምሮ ሄገን በተጠባባቂነት በምትኩ ሲሰራ ቆይቷል ። ዛሬ ይህ የአማካሪነት ስልጣን ሙሉ በሙሉ የሱ መሆኑን ከዶኑ አንደበት ለመስማት ቢጠብቅም ፣ ሁኔታዎች አልፈቀዱም ። በነበረው ልማድ መሰረት እንዲህ ያለውን ከፍተኛ ስልጣን ለማግኘት በእናትም በአባትም በኩል ጣልያን ከሆኑ ወላጆች መወለድን ይጠይቃል ። የሄገን እስካሁን በቦታው ላይ በተጠባባቂነት መሰራት እንኳን ችግር አስከትሏል ። ሌላው እንቅፋት ደግሞ ሄገን እድሜውና ሰላሳ አምስት አመት ብቻ በመሆኑ ፣ አንድ ብቁ አማካሪ ሊኖረው የሚገባውን ልምድና ብልህነት አዳብሯል ለማለት አያስደፍርም ። ስለዚህ ዶኑ ይህን ስልጣን እንደሚሰጠው ግረጋገጫ የለም ።

"መቸ ነው ሙሽሮቹ ወደቤታቸው የሚሄዱት?" አለ ዶኑ ። ሄገን ሰአቱን አይቶ በጥቂት ደቂቃዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ኬካቸውን ከቀረሱ በኋላ እኩል ሰአት ያህል ቆይተው እንደሚሄዱ ነገረው ።

ሄገን ከዚሁ ጋር በተዛመደ ለአዲሱ ሙሽራ ከበድ ያለ ሀላፊነት በቤተሰቡ የድብቅ አለም ተግባር ውስጥ ይሰጠው እንደሆነ ጠየቀው ።

"ፈጽሞ!" አለ ዶኑ "ለኑሮው የሚበቃ ደህና ገቢ የሚያስገኝ ስራ እንጂ የቤተሰቡን ተግባር ፈጽሞ እንዳያውቅ ። ሶኒንና ፍሬዲን ክሌሜንዛንም ይህንኑ ንገራቸው ።"

ዶን ኮርሌዎኔ ልጆቹ እና ጆኒ ፎንቴን እንዲያ ጅቡት አድርጉ ለአማካሪውና ለወዳጁ ለጄንኮ የመ ጨረሻውን የክብር ስንብት ለመፈጸም ወደ ሀኪም ቤት አመራ ።

ቶም ሄገን ግን በዚያው ምሽት ወደ ካሊፎርኒያ መሄድ ስላለበት አብሯቸው ሄዶ ጄንኮን ለመጠየቅ ጊዜ እንደማይኖረው ዶኑ ከገለጸለት በኋላ የሚያነጋግ ረው ስላለ እስኪመለስ እንዲጠብቀው አዘዘው ።

ይህን ጊዜ የምክር ቤቱ አባል መምጣት ባለመ ቻሉ ይቅርታ ጠይቆ በልዩ መልእክተኛ ስጦታ መላ ኩን ሄገን ለዶኑ ሲነግረው ዶኑ ስለ መቅረቱ እንደ ማያውቅ እራሱን ነቀነቀ ። ቀድሞውኑ እራሱ ዶኑ ክትትል በመፍራት የምክር ቤቱ አባል በሰርጉ ስነ ስርአት ላይ እንዳይገኝ የነገረው መሆኑን መናገር አልፈለገም ።

"ጥሩ ስጦታ ላከ?" ብሎ ዶኑ ሄገንን ጠየቀው ። የምክር ቤቱ አባል የላከው ስጦታ ከብር የተሰራ የጥ ንት እቃ ሲሆን ፥ ቢያንስ ሺህ ብር እንደሚያወጣ ሄገን ገለጸለት ። ይህ የምክር ቤት አባል እንደ ሉካ ብራሲ ሌላው የዶኑ የሀይል ዋልታ በመሆኑ ታማኝነቱን ስላ ረጋገጠለት ደስ አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ደኒ ፎንቴን ከአትክልቱ የግብዣ ስፍራ ሲደርስ ኬይ አዳምስ አይታው ተደነቀች ። የዶኑ ቤተሰብ ጆኒ ፎንቴንን ከመሰለ ስታደንቀው የነበረ ዝነኛ ዘፋኝ ጋር የሚተዋወቅ መሆኑን ለምን እርሳዋ እንዳልነገራት ቅሬታዋን ከነገረችው በኋላ "አሁንስ እንደግባህ እርግጠኛ ነኝ" አለችው ።

ጆኒ ዘፈኑን አብቅቶ ከዶኑ ጋር ወደ ቤት ሲገባ ኬይ ሌላ ጥያቄ ለሚካኤል አነሳችበት ።

"ጆኒ ፎንቴንን የመሰለ ትልቅ የፊልም ተዋናይ 'ካባቴ እርዳታ ይጠይቃል' እንዳትለኝ ብቻ!" አለች ።

"ያባቴ የክርስትና ልጅ ነው ። ያባቴ ጥረት ባይኖርበት ኖሮ ፤ ጆኒ ለዝነኛ የፊልም ተዋናይነት ባልበቃ ነበር" ሲል መለሰላት ።

ሚካኤል ታሪኩን ብዙ ጊዜ ሳይፈጅ አጫወታት ። ከስምንት አመት በፊት ጆኒ ፎንቴን ከአንድ ተወዳጅ የዳንኪራ ቡድን ጋር በመጫወት ዝናን አተረፈ ። የላቀ የሬዲዮ ዘፋኝ ሆነ ። ሌዝ ሀሊ የተባለ ታዋቂ የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅ ጆኒ ፎንቴንን ለግሉ እንዲሰራለት የአምስት አመት ውል አስፈርሞት ነበር ። ከዚያ በኋላ ጆኒን ለሌሎች እያከራየ ገቢውን እኪሱ ይከታል ። በዚህ ጉዳይ ላይ ዶን ኮርሌዎኔ ጣልቃ ገባ ። ለሌዝ ሀሊ ሀያ ሺህ ብር ከፍሎት ውሉን እንዲያቋርጥ ዶኑ ሌዝ ሀሊን ጠየቀው ። ሀሊ ግን አስተያየት ማድረግ የሚችለው ጆኒ ፎንቴን ከሚያስገኘው ገቢ ሀምሳ በመቶውን ብቻ በመውሰድ መሆኑን ለዶኑ ገለጸ ። ዶኑ ሀያ ሺህ ብር ለመክፈል ያቀረበውን ሀሳብ ትቶ ባስር ሺህ ብቻ እንዲስማማ ሀሊን ጠየቀው ። የዚህ ቅንሳ ትርጉም ፥ ከሙያው ውጭ ያለውን አለም በውል የማያውቀው ሀሊን ስላልገባው ፤ ጉዳዩን ሳያጤን እምቢ አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በተከታዩ ቀን ዶን ኮርሌዎኔ ሁለት መዳጆቹን ፣ ግለትም አማካሪውን ጀንኮ አባንዳንዶንና ሉካ ብራሲን አስከትሎ ሌዝ ሀሊን በግል ሊጐበኘው ሄደ ። ቀድሞ ያነሳውን ጥያቄ በመድገም ሌዝ ሀሊ ውለታውን ሰርዞ አስር ሺውን ብር እንዲቀበል ሽጉጥ ግንባሩ ላይ ደግኖ ጠየቀው ። ሌዝ ሀሊ በፍርሀት እሺ ብሎ ፈረመ ። ዶኑ ሽጉጡን ኪሱ ከትቶ የአስር ሺህ ብሩን ቼክ ሰጠው ።

ከዚያ በኋላ ጆኒ ታላቅ ዘፋኝ ሆኖ ባለ ብዙ ሚሊዮን ብር ሆነ ። የልጅነት ሚስቱን ፈትቶ ልጆቹንም ትቶ ዝነኛይቱን የፊልም ተዋናይ አገባ ። ሁለተኛዋ ሚስቱ ዝሙተኛ መሆንዋን በተረዳ ጊዜ መጠጣቱን ፣ መቆመሩንና ሴቶችን ማሳደዱን ተያያዘው ። ድምጹም ተቃወሰ ። የሙዚቃ ሽክላዎቹ መሸጥ አቆሙ ። የተዋዋለበት ስቱዲዮም ውሉን አላድስለት አለ ። ስለዚህ የክርስትና አባቱን ሊማጠን መጥቷል ።

ኬይ ይህን የጆኒን ታሪክ ካዳመጠች በኋላ ሚካኤልን "ባባትህ አትቀናም? የነገርከኝ ታሪኮች በሞላ አባትህ ለሰዎች በጎ አድራጎትን እንደሚፈፅም የሚገልጹ ናቸው ። በርግጥ አድራጎቱ በትክክል ህጋዊ ባይሆንም ርህሩህ ልብ ያለው ሰው መሆን አለበት" አለችው ።

ዶን ኮርሌዎኔ ይህን የሚያደርግበት ምክንያት እሱም የነሱን ውለታ በሚሻበት ወቅት ማግኘት የሚያስችለውን ውለታ ለመጣል እንደሆነ አስረዳት ።

ሁካታው ደርቶ ፣ የሰርጉ ኬክ ቀርቦ ፣ ተበልቶ ሲያበቃ ምሽት ተቃረበ ። ዳቦ ጋጋሪው ናዞሬኔ ለሰርጉ የጋገረው ኬክ ጥበብ በተሞላበት ሁናቴ በቅባት የተዋበና ጣፋጭ በመሆኑ ሙሽሪት ቋምጣ ስትቆነጥርለት ነበር ።

ሰነ ስርአቱም አብቅቶ እንግዶቹ ሲሰናበቱ የኤፍቢአይዋ መኪና ባካባቢው እንዳልነበረች ዶኑ አስተዋለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በፍሬዶ ሹፍርና ፥ ዶኑ ከፊት ፥ ሶኒ ፥ ሚካኤልና ጆኒ ፎንቴን ከኋላ ሆነው ሲጓዙ ፥ "ወዳጅህ ብቻዋን ወደ ከተማ መሄድ ትችል የለ?" በማለት ዶን ኮርሌ ዮኔ ልጁን ሚካኤልን ጠየቀው ። ልጁም ቶም ሄገን የምትመለስበትን ሁኔታ ያደራጀ መሆኑን ላባቱ በገለጸ ለት ጊዜ ዶኑ በቶም ቅልጥፍና ረካ ።

በጉዞው ላይ ዶኑ ከሚካኤልና ጆኒ ፎንቴን ጋር እያንዳንዳቸውን የሚመለከት ወሬ አወራ ። ሚካኤልን ስለትምህርቱ ሲጠይቀው መልካም መሆኑን ለማስረዳት አንገቱን ነቀነቀ ።

ቀጥሎ ጆኒ ፎንቴንን የሚመለከት ጥያቄ ሶኒ ለአባቱ አነሳ ። ጆኒ በሆሊውድ ያጋጠመውንም ችግር ዶኑ ሊያቃልልለት የያዘው መሆኑን እንደነገረው ገለጸለት ። ይህን ተልእኮ ለማሳካት አባቱ ይልከው እንደሆን ጠየቀው ። ዶን ኮርሌዎኔ ግን ጉዳዩ ለቶም ተሰጥቶት ይህንኑ ለመከታተል በዚያው ምሽት ወደ ካሊፎርኒያ እንደሚጓዝ ነግሮት ጉዳዩ ቀላል መሆኑን አስረዳው ።

ሶኒ ሳቀና "ጆኒ ፎንቴን ጉዳዩን ልትፈጽምለት የምትችል አልመሰለውም ። ለዚህ ነው እኔን ልትልክ ትፈልግ ይሆናል ብዬ ያሰብኩት አለው ።

ዶኑ ወደ ጆኒ ፎንቴን ዞር አለና ፥ "ለምንድነው የምትጠራጠረኝ? የጡት አባትህ አደርጋለሁ ብሎ ያለውን ነገር ሁሉ አላደረገም? ለመሆኑ እኔ እንደሞኝ ተቆጥሬስ አውቃለሁ?" ሲል ጠየቀው ።

ጆኒ በድንጋጤ ይቅርታ ጠየቀና ፣

"የጡት አባቴ ፥ ይህን ችግር የፈጠረው ባላጋራዬ ፈጽሞ ሊገፉት የማይቻል ነው ። ልታነቃንቀው አት ችልም ። ከታላላቅ ሰዎች ጋር ግንኙነት አለው ። ሌላ ቀርቶ በገንዘብም ሀሳቡን አታስቀይረውም ። እኔን ደግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይጠላኛል ። እንዴት አድርገህ ልታቃናው እንደምትችል አላውቅም ” አለው ።

ዶኑ ፍቅር በተሞላበት ሁናቴ “ብዬሀለሁ ፥ ታግ ኝዋለህ” በማለት ጆኒን አስደሰተው ። ወደ ሚካኤል ዞር ብሎ በክርኑ ጐሰም አደረገውና ፥ “የጡት ልጃችንን ተስፋ አናስቆርጠውም ፥ አይደል ሚካኤል?” አለው ። አባቱን ተጠራጥሮ የማያውቀው ሚካኤልም እራሱን በመነቅነቅ ስምምነቱን ገለጸለት ።

ወቅቱ ነዳጅ በእደላ የሚከፋፈልበት ወቅት ስለ ነበር በመንገዱ ላይ መኪኖች በብዛት ስለማይታዩ የፈረንሳይ ሆስፒታል ተብሎ ከሚጠራው ሀኪም ቤት ለመድረስ አንድ ሰአትም አልፈጀባቸው ።

ከመኪና እንደወረዱ ዶን ኮርሌዎኔ እጁን በልጁ በሚካኤል ትከሻ ላይ አድርጎ ወደ ኋላ አስቀረውና እንዲህ አለው ፤

“የኮሌጅ ትምህርትህን ስታበቃ ናና አነጋግረኝ ። አንተም የምትወደው አንድ እቅድ አዘጋጅቼልሀለሁ”

ሚካኤል ምንም መልስ ስላልሰጠው ዶን ኮርሌ ዎኔ በብሽቀት “እህ!” ካለ በኋላ በቁጣ “አመልህን ስለማ ውቅ የማትፈቅደውን ነገር እንድታደርግ አልጠይቅ ህም ። አሁን የምልህ የተለየ ነው ። ትልቅ ሰው ነህና እንዳሻህ መጓዝ ትችላለህ ። ነገር ግን ትምህርትህን ስታጠናቅቅ ልጄ እንደመሆንህ ወደኔ ዘንድ ና” ሲል ልጁን ነገረው ።

ሀኪም ቤት ሲደርሱም የጀንኮ አባንዳንዶ ቤተሰብ ፥ ሚስቱና ሶስት ሴቶች ልጆቹ በዚያ የሀኪም ቤቱ ነጭ ሸክላ ወለል ላይ ጥቁር ለብሰው የቁራ መንጋ መስለዋል ። ዶኑ ከሆስፒታሉ ሊፍት ሲወጣ አዩትና ከለላውን በመ ሻት ተማጠኑት ። የአባንዳንዶ ባለቤትም እያለቀሰችና የዶኑን ጉንጭ ሳም ሳም እያደረገች “ምን ያለህ ቅዱስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ነህ ፤ በዛሬው አለት በልጅህ ሰርግ ቀን መምጣ ትህ ?" አለችው ።

"ለሀያ አመታት ቀኝ እጄ ለነበረ ወዳጄ ባለእዳ አይደለሁም?" በማለት ወዳጁን መጠየቅ ግዴታው መሆ ኑን ገለጸላት ። ጄንኮ አባንዳንዶ በካንሰር በሽታ በዚህ ሆስፒታል ከተኛ አመት ሊሞላው ምንም አልቀረው ። የአባንዳንዶ ሚስት ግን የባሏ መሞት ቁርጥ መሆኑን ባለመረዳት ዶኑን እንዲህ አለችው ።

"ምስኪኑ ባሌ አንተን ስለሚሻ ግባና እየው ። ለል ጅህ ሰርግ በመምጣት ተገቢውን ክብር ሊሰጥህ ፈልጎ ነበር ። ሀኪሙ ግን አልፈቀደለትም ። ዛሬ መጥተህ እን ደምታየው እርግጠኛ ሆኖ ይናገር ነበር ። እኔ ግን አላመንኩም ። ይገርማል ፥ ወንዶች በጓደኝነት በጣም ይተ ማመናሉ ።"

አንዲት ነርስና አንድ ኮምጨጭ ያለ ወጣት ሀኪም ከሀመምተኛው የግል ክፍል ብቅ አሉ ። ከአባንዳንዶ ልጆች አንዷ በፍርሀት ፤

"ዶክተር ኬኔዲ ገብተን ልንጠይቀው እንችላለን?" አለችው ። የጠያቂዎቹ ብዛት ሀኪሙን ሰላበሸቀው ፥ "ሰውዬው በሰላም እንዲሞትበት ቢተዉት ምንቸገራቸው" በማለት አሰበና ፤

"የቅርብ ዘመዶች ብቻ ይበቃሉ መሰለኝ" አለ ።

ዶኑ እንግሊዝኛው የጣልያን ተወላጅ አጣጣል በት ንሹ ባለበት አነጋገር

"ተወዳጅ ሀኪም ፥ የዚህ ሰው መሞት ቁርጥ ነው?" ሲል ጠየቀው ። ሀኪሙም በአምንታ አረጋገጠለት ። ዶኑም ቀጠለና ፥

"እንግዲያስ ከዚህ በኋላ ምንም የምታደርግለት ነገር አይኖርም ። እኛ ሸክሙን እንችለዋለን ። እናጽና ናዋለን ። ሲሞት አይኑን እንጥምለታለን ። በሰነ ስርአት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንቀብረዋለን ። ቀብሩ ላይ እናለቅሳለን ። ኋላም ሚስ
ቱን እና ልጆቹን እንንከባከባለን" አለው ። ዶኑ እን
ዲህ ማለቱ የአባንዳንዶ ባለቤት የባሏን ቁርጠኛ ሞት
እንድትረዳው በማሰብ ነበር ። እንደታሰበውም ዶኑ ይህን
ሰናገር ለቅሶዋን ለቀቀችው ።

ሀኪሙ እነዚህን የህክምና ምስጢር የማይገባ
ችውን ምስኪኖች ማስረዳት አስቸጋሪ መሆኑን
አጤነ ። አገልግሎቱ ያበቃ መሆኑ ቢነገረውም ተወዳዳሪ
በሌለው ትህትና እንዲህ አላቸው ፣

"ለበሽተኛው የምታደርጋቸውን ነገሮች አጠናቃ
ኑርሷ እስታስገባችሁ እባካችሁ ውጭ ቆዩ" በማለት
ካሳሰባቸው በኋላ ፣ ነጭ የስራ ልብሱን እያውለበለበ
ቁልቁል ደረጃውን ወረደ ።

ጄንኮ አባንዳንዶ ከሞት ጋር ሲታገል ከርሞ አሁን
ስለተረታ ቀና በተደረገው አልጋው ላይ ድቅቅ ብሎ
ተጋድሟል ። ከአጽሙ በቀር ምንም አካል አልቀረውም ።
በዚያ ጥቁር ዞማ ጠጉሩ ምትክ ውሉ የጠፋ የሳር ብናኝ
የመሰለ ጸጉር ተተክቷል ። ዶን ኮርሌዎኔ በፈገግታ ፣

"ጄንኮ ፣ ውድ ወዳጄ ፣ ልጆቼ ሊጠይቁህ መጥተ
ዋል ። ተመልከት ጆኒ ፎንቴንም ያን ሁሉ ርቀት
አቋርጦ ከሆሊውድ መጥቷል" ሲል አጽናናው ።

ሊሞት የተቃረበው ሰውዬ የጐደጐዱ አይኖቹን
በምስጋና ቀና አደረገ ። አጽሙ የቀረ እጁን በሞቀ
እጆቹ እንዲጨብጡት ዘረጋላቸው ። ሚስቱና ልጆቹም
በአልጋው አካባ ተኮልኩለው ጉንጩን እየሳሙ ተራ
በተራ ጨበጡት ። ዶኑ የህመምተኛውን እጅ ጠበቅ
እያደረገ ፣

"ቶሎ ብለህ ዳንና ወደ ኢጣልያ ተጉዘን ተወ
ልደን ያደግንበትን ነጠር እንጎበኛለን ። ከዚያ ቀደም
ባቶቻችን ያደርጉ እንደነበረው ከወይን ጠጅ መሸጫዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት ደጃፍ ቦውሊንግ እንጫወታለን ፡'' አለው ።

ሊምት የተቃረበው አባንዳንዶ እራሱን ነቀነቀ ። ወጣቶቹንና ቤተሰቡን ከአልጋው አጠገብ እንዲርቁ ምል ክት ሰጣቸው ። በነዚያ የወፍ እግር በመሰሉ ጣቶቹ ዶኑን ይዞ ለመናገር ሞከረ ። ዶኑም አንገቱን ዝቅ አደርጎ ከአልጋው አጠገብ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠ ። ጀን ኮም ስለልጅነታቸው ሰማውራት ፈለጎ እየቀባጠረ አይኖቹን ሰኮለ ። ዶኑ እንባው ሲፈስ በማየታቸው በዚያ የነበሩት ሁሉ ተደነቁ ። የሚንቀጠቀጠው ድምጽ እየ ጎላ ከፍሉን ሞላው ። ጀንኮ ሲቃ በመላበትና ከአ ቅሙ በላይ በሆነ ጥረት እራሱን ከትራሱ ቀና አድ ርጎ እነዚያን አጽም ጣቶቹን ወደ ዶኑ አቃንቶ ፡

''የጡት አባቴ ፡ ከሞት እንድታድነኝ እማጠንህለሁ ። ሰጋዬ በአጥንቴ ተለበለበች ። ትሎች አንጎሌን ሲበ ሉት ይሰማኛል ። አድነኝ የጡት አባቴ ። ሀይል አለህ ፤ የምስኪኗን ባለቤቴን እንባ አድርቀው ። በሰራሁት ሀጢአት የሚገጥመኝን እየፈራሁ ወደ አስፈሪ ሞት ሰጓገ ዝም ትለኛለህ?'' በማለት ተማጠነው ። ዶኑ ጸጥ አለ ። ጀንኮ አባንዳንዶ ቀጠለ ፡

''የልጅህ ሰርግ እለት ነው ። የምለምንህን እምቢ አትለኝም'' አለው ። ዶኑ ይህን መቀባጠር ለማስቆም በማሰብ ፡ እንዲህ ያለ አትም የለውም እንጂ ቢኖረውማ ለብዙ ጊዜ ወዳጁ አባንዳንዶ ከማንም ይበልጥ ማን ኛውንም ነገር ሊያደርግለት ፈቃደኛ እንደነበር መለሰ ለት ። ይልቁንም ሞትን እንዳይፈራና ከሞተም በኋላ ሌት ተቀን የተሟላ ፍታት እና ጸሎት እንደሚደረግ ለት ፡ ፈጣሪም እንዲህ ይቅርታ እየተጠየቀ እንደማይ ቀጣው አረጋገጠለት ።

ጣእረ ሞት የመሰለው አባንዳንዶ አይኖች ውስጥ ብልጠት እየታየ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

“ሁሉንም ነገር በሚገባ አስተካክለህልኛል ማለት ነው?” አለ።

ዶኑም የማጽናናት ጥረቱን አብቅቶ ሰውየው መቀባጠሩን አቁሞ እረፍት እንዲያደርግ በቁጣ ተናገረው። ተስፋ የቆረጠው ጀንኮም ወደ ትራሱ ላይ የኋሊት ወደቀ። ነርሷ እንዲወጡ ጠቆመቻቸው። ዶኑ ሊነሳ ሲል አባንዳንዶ ጠርቶት፣

“የጡት አባቴ፣ ሞት ሲመጣ አብረኸኝ ሁን። ምናልባት አንተን ሲያይ ፈርቶህ ይተወኝ ይሆናል። ምናልባትም ጥቂት ቃላት ጣል አድርገህ ሚስጥራዊ ተጽእኖ ታደርግበት ይሆናል።” ካለው በኋላ በቁርጥ መማጠኑን አብቅቶ ፈገግ ሞከረ።

“ከሞት ጋር በደም የተሳሰራችሁ ናችሁ” በማለት ሊቀልድ ሞክሮ ዶኑ እንዳይቆጣ በመፍራት በእጁ ይዞት፣

“አብረኸኝ ቆይ እባክህ። እጅህን ልያዘውማ። ሌሎችን ድል እንዳደረግናቸው ያንን ዲቃላ ሞትንም እናሸንፈዋለን። የጡት አባቴ፣ አትክዳኝ” አለው።

ዶኑ ሌሎቹን እንዲወጡ ምልክት ሰጣቸው። የጀንኮን አጽም እጅ በሁለት ሰፋፊ እጆቹ ጨብጦ፣ ወዳጁን እያጽናናው፣ ከዚያ እርኩስ የሰዎች ደመኛ ከሞት ፈልቅቆ ሊያወጣው የሚችል ይመስል የሞትን መምጣት አብረው ጠበቁ።

የኮኒ ኮርሌዎኔ ሰርግ በጥሩ ሁኔታ ሲከናወን፣ ካርሎ ሪዚም ለሙሽሪቱ በተጠራቀመው የሀያ ሺ ብር ስጦታ ግፊት የሙሽራነቱን ሚና በወግ ፈጸመ። ሙሽራት ከገንዘቧ ይበልጥ በሙሉ ፈቃድ ያስከረከበችው ሀጎን ሲሆን፣ ገንዘቧን ለማግኘት ግን ጮሌው አንድ አይኗን በጥፊ ማጥቆር ነበረበት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሉሲ ማንቺኒም ከሶኒ ጋር መዝናናት በመሻት የሶኒን የስልክ ጥሪ ተጠባበቀች ። ሳይጠራት በመቅረቱ ቤቱ ስትደውል በስልኩ የሰማችው ድምጽ የሴት ነበር ። ስልኩን ዘጋችው ። የሰርጉ እለት አብራው መሰወሯ እንደተነቃባት ለማወቅ አልቻለችም ። ግራም ነፈሰቸኝ 'ሳንቲኖ ኮርሌዎኔ ከእህቱ ሚዜ ጋር ተዳርቷል' የሚል ወሬ ተዛመተ ።

አሜሪካ ቦናሴራ አሰቃቂ ቅዠት አጋጠመው ። ዶን ኮርሌዎኔ ሹል ቆብ አድርጎ ቱታ ደርቦ ፥ ወፍራም ጓንት አድርጎ ጥይት የዘነበባቸው እሬሳዎችን ከመኪና ላይ እያራገፈ 'ማንም ሰው ሳያይ በፍጥነት እንድትቀብራቸው' እያለ ትእዛዝ ሲሰጠው በህልሙ አየ ። በህልሙ ሲያጓራ ሚስቱ ቀስቅሳው ፤

"ምን ያለኸው ነህ ፥ ሰርግ ላይ ውለህ መጥተህ እንዲህ የምትቃዥው?" እያለች ተቆጣችው ።

ኬይ አዳምስም ሽንጣም መኪና ተሳፍራ በክሌሜንዛና በፖሊ ጋቶ ሽኝነት ወደ ሆቴሏ ተጓዘች ። እነዚህ ሰዎች ልዩ አይነት መሆናቸውን ፥ ለሚካኤ ልም ፍቅርና አክብሮት እንዳላቸው እሷንም እንዳከበሯት ተገነዘበች ። ዶኑ ሚካኤልን ከልጅቱ ሁሉ የላቀና የቤተሰቡን ስራ መረከብ የሚችል አድርጎ እንደሚገምተው ክሌሜንዛ ሲነግራት ፥

"የቤተሰቡ ስራ ምንድነው?" ብላ ጠየቀችው ።

ይህን ጊዜ ፖሊ ጋቶ መሪውን እየጠመዘዘ ቶሎ ብሎ ተመለከታት ። ክሌሜንዛ ጥያቄዋን ከመመለሱ በፊት።

"ሚካኤል አልነገረሽም?" ብሎ ጠየቃትና መልሱን በመቀጠል ፥ ዶኑ በጣልያን አገር የሚመረት የወይራ ዘይት ዋና አስመጪ እንደሆነ ፥ በተለይም በዚያን ወቅት ጦርነቱ ያበቃ በመሆኑ ንግዱ እንደሚበለጽግ ፥ ይህን ለመሰለው ታዳጊ ንግድም ሚካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኤልን የመሰለ ብልህ ሰው እንደሚያስፈልገው አጫ ወታት ።

ሆቴላቸው እንደደረሱም ክሌሜንዛ ክፍሏ ከአደ ረሳት በኋላ የክፍሏን በር መዝጋቷን አረጋገጠ ። በሆ ቴሉ መዝገብ ላይም 'ሚካኤልና ባለቤቱ' በሚል የተ መዘገቡ መሆኑን ተረዳ ። ፖሊ ጋቶም ኬይ አዳምስን 'ውብ ወይዘሮ' በማለት ብቻውን አስተያየቱን ሰጠ ።

"ጂት ቀደም ብለህ ቀስቅሰኝ ። ሄገን አስቸኳይ ስራ አዘጋጅቶልናል ፥" ሲል ክሌሜንዛ ፖሊ ጋቶን መመሪያ ሰጥቶ አሰናበተው ።

እሁድ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ቶም ሄገን ሚስቱን ተሰናብቶ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ተጓዘ ። ከዚህ ቀደም ሄገን ውለታ በዋለለት አንድ የፔንታጎን ሹም በተሰ ጠው የመጀመሪያ ደረጃ ቅድሚያ የማግኘት መብት ወደ ሎስ አንጀሊስ ለመሳፈር ችግር አላጋጠመውም ።

ውሎው ለቶም ሄገን አድካሚም ቢሆን የሚያ ረካ ነበር ። ጄንኮ አባንዳንዶ ስላረፈ የቤተሰቡ ሙሉ አማካሪ መሆኑን ዶኑ አፍ አውጥቶ ነግሮታል ። ከእንግዲህ ስልጣንም ሀብትም በእጁ መሆኑን አረጋ ግጧል ።

ቶም ሄገንን አማካሪው ሲያደርገው ዶኑ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የማፊያ ስርአት አፍርሶታል ። ቶም ሄገን በዶኑ ቤት ማደጉ ለአማካሪነት አያበቃውም። የዘር ጉዳይ ነው ። በአሜርታ ወይም አይቶ ሰምቶ ጭጭ ማለት ሀግ የታነጸ ሲሲሊያዊ ተወላጅ ብቻ ነው ለኮ ንሲልዮሪነት ወይም ለአማካሪነት የሚታጨው ።

የቤተሰቡ ቁንጮና ሁሉን ወሳኝ በሆነው በዶኑ እና መመሪያዎችን በተግባር በሚያውሉ የበታቾች መሀከል ፥ ኮንሲሊዮሪው ወይም አማካሪው አሳልፎ እስ ካልሰጠው ድረስ ፤ ሶስት መከላከያ ድንበሮች አሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ አይነት ምንም ፍንጭ የማይገኝለት ከለላ መፍጠር ይቻላል ። በዚያች እሁድ እለት ጧት ዶኑ የቦና ሴራን ልጅ በደበደቡት ወጣቶች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በወሰነበት እለት ውሳኔውን ያስተላለፈው ለቶም ሄገን ነበር—ብቻ ለብቻ ። ሄገን በበኩሉ ያለ እማኝ ትእዛዙን ለክሌሜንዛ አስተላለፈ ፣ ክሌሜንዛም ለፖሊ ጋቶ ለብቻው ። በዚህ አይነት ፖሊ ጋቶ ተፈላጊውን የሰው ሀይል አደራጅቶ ትእዛዙን በተግባር ይተረጎማል ። ስለዚህ ፖሊ ጋቶና ረዳቶቹ ይህ ትእዛዝ ለምን እና በማን እንደተሰጠ ማወቅ አይችሉም ። የመጀመሪያው ትእዛዝ ከማን እንደመነጨ ለማወቅ ተከታታይ ቢነሳም እንኳን ፣ በዚህ ሁሉ ብቻ ለብቻ የስልጣን ተዋረድ ውስጥ ከተካተቱት ሰዎች አንዱን ከመሀል በመሰወር ደብዛውን ማጥፋት ይቻላል ።

ኮንሲሊዮሪ ወይም አማካሪ ስሙ እንደሚያመለክተው የዶኑ የቅርብ አማካሪ ፣ ቀኝ እጁ ፣ ረዳት አንጎሉ እና የቅርብ ጓደኛው ነው ። ለታላላቅ ጉዳዮች ዶኑ ሲጓዝ የዶኑን መኪና የሚነዳው አማካሪው ነው ። በስብሰባ ላይ ለዶኑ የሚጠጣ ነገር ወይም ሳንድዊች ያቀርብለታል ። ዶኑ የሚያውቀውን ነገርና የሀይል መሰረቶች ያሉበትን ሁሉ ያውቃል ። በአለም ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ዶኑን ድምጥማጡን ማጥፋት የሚችል ሰው ኮንሲሊዮሪው ብቻ ነው ። ነገር ግን በአሜሪካ ከሚኖሩ የሲሲሊ ተወላጆች የቤተሰብ ታሪክ ትዝታ ውስጥ አንድ አማካሪ ዶኑን ለጥፋት ሲያጋልጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ ። ዶኑን በማጋለጥ አማካሪው የሚያጋጥመው ምንም በጎ ነገር አይኖርም ። ይልቁንም ለዶኑ መታመን ማንንም አማካሪ ለሀብትና ለክብር እንደሚያበቃው ይታወቃል ። ታማኝ አማካሪ መጥፎ ቢያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋጥመው ደግሞ ሚስቱና ልጆቹ የዶኑን ሙሉ እንክ ብካቤ ያገኛሉ ። በታማኝነቱ ከጸና ነው ይህ እንግዲህ ።

በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አማካሪው ዶኑ እንዳይነካ እየተጠነቀቀ ዶኑን በግልጽ ወከሎ ይሰራል ። የሄገንም የካሊፎርንያ ጉዞው ለዚህ አንድ ምሳሌ ነው ። የዚህ ተል እኮው ውጤት ለሄገን የአማካሪነት እድል መሳኝ እን ሚሆን ተገንዝቦታል ። ከቤተሰቡ መሰረታዊ ጉዳዮች አንጻር ጆኒ ፎንቴን በቋመጠለት የጦርነት ፊልም ላይ መሳተፉ አነስተኛ ጉዳይ ነው ። ይበልጡኑ አቢይ ጉዳይ ግን ሄገን ለተከታዩ አርብ ዶኑ ከሶሎዞ ጋር እንዲገናኝ ያዘጋጀው ስብሰባ ነበር ። ነገር ግን ሁለቱም ጉዳዮች ለዶኑ እኩል አበይት መሆናቸውን ሄገን ያውቃል ። ይህ በቂው ነው ።

ሄገን በሚንገዘበት አይሮፕላን ውስጥ ማርቲኒውን አዝዞ እየተጎነጨ ዶኑም ሆነ ጆኒ ፎንቴን ስለጃክ ዎል ትገ የሰጡትን መግለጫ ሲያሰላስል ይህን ሰው በቀ ላሉ ማሳመን እንደማይቻል ገመተ ። ያም ሆነ ይህ ዶኑ ቃሉን እንደሚፈጽም አይጠራጠርም ። የሄገን ሚና ያስማሚነትና የአገናኝነት ነው ። በአውሮፕላኑ ውስጥ መቀመጫውን ተደግፎ ስለዎልትዝ ያሰላስል ጀመር ።

ጃክ ዎልትዝ በሆሊውድ ከታወቁት ከፍተኛና ከባድ ከሚባሉት ሶስት የፊልም አሰሪዎች አንዱ ነው ። የራሱ ስቱዲዮ አለው ። ከአያሌ ዝነኛ ተዋንያን ጋር ኮንትራት ተፈራርሟል ። የጦርነት ኢንፎርሜሽንን በሚመለከት የአሜሪካንን ፕሬዚዳንት እንዲያማክር በተቋቋመው የአ ማካሪ ቡድን ውስጥ በመሳተፍ የፕሮፓጋንዳ ፊልም ያዘጋጃል ። በጓይት ሐውስ እራት ተጋብዟል ። ኤድጋር ሁቨርን በሆሊውድ ቤቱ ውስጥ ጋብዞታል ። እነዚህ ሁሉ የስራ ግንኙነቶች ስለሆኑ ሄገንን ላያስፈሩት ይችላሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ዎልትዝ የባሰበት እብሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተኛ በመሆኑና በራሱ የታላቅነት ትምክህት በመናወዙ በሁሉም ላይ ሀይሉን ማሳየት ስለሚሻ የጠላቶቹ እንደ አሸን መፍላት የግል የፖለቲካ ጉልበት አሳጥቶታል ።

ከአስር አመት በፊት አንስቶ የመረጠው የአማካሪነት ሥራ ባለ ሰላሳ አምስት ዓመት እድሜውን ሄገንን ቢያረካውም የዛሬውን ተልእኮውን የሚወጣው አልመሰለውም። በህግ ሙያ ተመርቆ ለሶስት አመታት በህግ ሙያ ላይ ይሰማራ እንጂ ከዚያ በኋላ ለዶን ኮርሌዎኔ ቤተሰብ በአንዳችም የህግ ስራ ላይ አልዋለም ።

ቶም ሄገን እናቱ ታውራ በአስራ አንድ አመት እድሚው ስትሞትበት አሳዳጊ አጥቶ ሲንገላወድ የእድሜ እኩያው የነበረው ሶኒ ኮርሌዎኔ ደረሰለት ። አባቱ በአናጢነት ሙያው ሀቅ አልባ ተግባር ፈጽሞ ባያውቅም ከባድ ጠጭ ስለነበር ራሱንም ቤተሰቡንም አጠፋቸው ። በመጨረሻም ሞተ ። የሄገን ታናሽ እህት እጓለ ማውታን ገባች ። በዚያ ወቅት የማህበራዊ ጉዳይ መስሪያ ቤት የሚረዳቸው ያጡ ወንዶች ወጣቶች ትተውት ሲጠፉ የነሱን ጉዳይ ችላ ይለው ነበር። የሄገንንም ጉዳይ እንደዚሁ ። በዚህ ላይ ሄገን አይኑን ታሞ ሲሰቃይ በሽታው ከናቱ የተጋባበት ስለሆነ ያጋ ባብናል በማለት መንደርተኛው ሁሉ አገለለው ። ደጉ የአስራ አንድ አመት ወጣት ሶኒ ኮርሌዎኔ ግን ሄገንን ቤቱ አምጥቶ ከቤተሰቡ ጋር እንዲኖር ወላጆቹን ጠየቀ። ቶም ሄገንም ሊረሳው የማይችለው ትኩስ ስፓጊቲ በላ፣ የታጣፊ አልጋ መኝታም ተሰጠው ።

ዶኑ ልጁ በቤቱ እንዲኖር ከፈቀደ በኋላ እራሱ ልዩ ሀኪም ዘንድ ወስዶ አይኑን አሳክሞ አዳነው ። ኮሌጅና ህግ ትምህርት ቤት አስገባው ። ይህን ሁሉ፣ ቢያደርግም የጠባቂ እንጂ የአባት ሚና ሳይጫወት የፍቅር ምልክት ሳያሳየው ቆይቶ ነበር ። ይልቁንም ከወ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለዳቸው ልጆቹ በበለጠ ትህትና አስተናገደው ። የህግ ትምህርት ለመማርም የወሰነው እራሱ ቶም ሄገን ነበር ።

ዶን ኮርሌዮኔ የጥብቅናን ስራ በማድነቅ ሲያወራ "መቶ ጠመንጃ ከያዙ ሰዎች አንድ የህግ ባለሙያ ምስክር ወረቀት የያዘ ጠበቃ ይበልጣል" ይላል ። ይሁን እንጂ ልጆቹ ሶኒና ፍሬዲ እንደአባታቸው ፍላጎት ሳይሆን በራሳቸው ምርጫ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደጨረሱ በቤተሰቡ የንግድ ስራ ውስጥ መግባትን መረጡ ።

ሚካኤል ብቻ ትምህርቱን በኮሌጅ ቀጠለ ። ፐርል ሀርበር ወደብ በጃፓኖች በተደበደበች ማግስት በጦር መርከበኛነት ተመዘገበ ።

ሄገን የህግ ባለሙያነት ማረጋገጫውን ፈተና ካለፈ በኋላ የኮሌጅ ምሩቅ የሆነች አጣልያዊት ልጃገረድ አግብቶ የራሱን ቤተሰብ መሰረተ ። ሰርጋቸው በዶኑ ቤት ከተከናወነ በኋላም ሄገን ባሻው ሙያ ቢሰማራ ዶኑ እንደሚረዳው ፣ ከቢሮ እቃ አንስቶ እስከ ሀንጻ አሰፈላጊውን ሁሉ እንደሚያሟላለትና ደምበኞችም እንደሚልክለት አረጋገጠለት ። ነገር ግን ቶም ሄገን ስለ ዶኑ ቅን ሀሳብ እጅ ከነሳ በኋላ ፍላጎቱ ሌላ መሆኑን ሲገልጽለት ፣

"የእኔ ምርጫ ላንተ መስራት ነው" አለው ።

ዶኑ ይህን ሲሰማ በልቡ ቢደሰትም ተደነቀ ።

"ለመሆኑ የእኔን ማንነት አውቀሀል?" ሲል ጠየቀው ።

ሄገንም በአዎንታ እራሱን ነቀነቀ ። በእርግጥ ግን የዶኑ ሀያልነት ገደብ እስከምን እንደሆነ አውቆ አልነበረም ። ለተከታዩ አስር አመታትም ጀንኮ የአልጋ ቁራኛ በመሆኑ ሄገን ተጠባቂ አማካሪ ተብሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

እስከ ተሾመ ድረስ ምንም ያህል ሳያውቅ ኖሯል ። ነገር ግን አይኑን ከዶኑ አይን በመግጠም ፈርጥሞ ፡

"ከልጆችህ እንደ አንዱ ሁኝ አገለግልሀለሁ" በማለት ምንም ይሁን ምን ዶኑን በመቀበል ታማኝ ሆኖ ሊያገለግለው ቃል ገባለት ። ዶኑ ይህን ሲሰማ ሄገን ቤቱ ከመጣ ጀምሮ ከባእድ አከብሮት በስተቀር አሳያቱት የማያውቀውን አባታዊ ፍቅር ለመጀመሪያ ጊዜ አሳየው ። ሄገንን ስቦ አቀፈው ። ከዚያም በኋላ አልፎ አልፎ ወላጆቹን እንዳይረሳ ከሚያሳስበው በስተቀር እንደ እውነተኛ ልጁ ቆጠረው ።

ሄገን የኋላ ታሪኩን የሚረሳበት ሁኔታ አልነበረም ። እናቱ ከመሞቷ በፊት ስለታወረች ቱምም እንደሚ ታወር እርግጠኛ ሆኖ ነበር ። አባቱ ሲሞት የአስራ አንድ አመቱ ሄገን በየመንገዱ ሲንከራተት የተለየ አጋጣሚ ደረሰለት ። ከእለታት አንድ ቀን በአንድ የህንጻ መተላለፊያ በስተጀርባ ተኝቶ አግኝቶት ሶኒ ወደ ቤቱ ወሰደው ። ከዚያ በኋላ የሆነው ሁሉ አስገራሚ ሆነበት ። ለብዙ ጊዜ ወጣቱ ሄገን በቅዠት ተሰቃየ ። በህልሙ አዋቂ ሰው ሆኖ ፡ አይኑን ታውሮ ፡ ልጆቹም አይነ ስውራን ሆነው ፡ ነጫጭ የአይነ ስራውን ዱላ ይዘው ፡ መንገዱን እየቆረቆሩ በየመንገዱ ሲለምኑ ይታየዋል ። ጧት ሲነቃ በአእምሮው ውስጥ የሚቀረጸው የዶኑ በጎ ገጽታ እፎይታ ይሰጠው ነበር ።

ሄገን ለዶኑ ቤተሰብ ከሚሰራው ስራ ጐን በአጠቃላይ የህግ ስራ ላይም እንዲሰማራ ዶኑ ተጽእኖ አድርጓል ። ይህም ውሳኔ በተከታዮቹ አመታት ተግባሮቹ ላይ ሄገንን ከመጥቀሙም በላይ ለዶኑ ስለ መስራቱ የነበረውን ጥርጣሬም አስወግዶለታል ። ቀጥሎም ለሁለት አመታት ከዶኑ ጋር አግባብ ያላቸው ዝነኛ የወንጀል ጠበቆች ከሚሰሩበት ድርጅት ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገብቶ በሰራበት ወቅት በወንጀል ህግ ላይ ልዩ ተሰጥዎ እንዳለው ታየ። ስለዚህ ሙሉ ጊዜውን ለዶኑ ቤተሰብ ሰራ ባዋለበት ወቅት በስድስት አመታት ውስጥ አንድም ቀን ተወቅሶ አያውቅም።

የአየርላንዱ ተወላጅ ሄገን ተጠባባቂ አማካሪ ሆኖ ሲሾም የዶኑ ተቀናቃኞች የዶኑን ቤተሰብ "የአየርላንድ የዘረፋ ቡድን" የሚል ቅጽል ስም ሰጡት። የቤተሰቡ ስም በሱ ዘር መጠራቱ ሄገንን ቢያስቀውም፣ በምንም አይነት ዶኑን ተክቶ የቤተሰቡን ስራ በሀላፊነት ለመረከብ እንደማይችል ተገነዘበ። ግን እሱም ቢሆን የወራሽነት አላማ አልነበረውም። እንዲህ ያለ ምኞት ባለውለታው የሆነው ዶኑን ክብር መንሳት ይሆናል።

ሄገን ሎስ አንጀሊስ ሲደርስ ገና በወግ አልነጋም ነበር። የሆቴል ክፍሉን ከተረከበ በኋላ ገላውን ታጥቦ ጺሙን ተላጭቶ፣ ቁርስና ጋዜጣ ክፍሉ ድረስ እንዲመጣለት አዘ ከጃክ ዎልትዝ የተቃጠረበት አራት ሰአት እስኪደርስ ተጠባባቀ።

በትላንትናው እለት የሲኒማ ሰራተኞች የመደያ ማህበር ሊቀመንበር የሆነውን ቢሊ ጐፍን አነጋግሯል። ይህ ሰው በዶኑ መመሪያ የሚሰራ በመሆኑ ሄገን ከዎልተዝ ጋር መነጋገር እንዲችል ቀጠሮ እንዲይዝለትና የንግግሩ ውጤት አመርቂ ሳይሆን ቢቀር የሲኒማ ስቱዲዮ የሰራተኞች የስራ ማቆም አድማ እንደሚደረግ እንዲያስጠነቅቀው ነግሮት ስለነበር፣ ያሰበው ቀጠሮ በቀላሉ ሊሳካ ችሏል። የዶን ኮርሌዎኔ ቤተሰብ የድብቅ አለም ግዛት ከኒውዮርክ አካባቢ አያልፍም። ነገር ግን ዶን ኮርሌዎኔ መጀመሪያ ወደ ሀያልነቱ የተንጠላጠለው የመደያ ማህበራት መሪዎችን በመርዳት ስለ ነበር ብዙዎቹ ባለውለታነቱን አልረሱም።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሄገንና የምልትዝ ቀጠሮ በአራት ሰአት መሆኑ መጥፎ ምልክት ነው ። ምክንያቱም በመጀመሪያው የቀጠሮ ዝርዝር ላይ ስለሚሆን ጉዳዩን በጪት ስለሚያጠናቅት ምሳ አይጋበዝም ። የሄገንን ጉዳይ ምልትዝ ክብደት አልሰጠውም ማለት ነው ።

የጃክ ምልትዝ የእንግዳ መቀበያው ክፍል እጅግ ያማረና ምቹ ነው ። ሄገን ከተቀመጠበት ፊት ለፊት አንዲት ለቁንጅናዋ ወደር የሌላት ከአስራ ሁለት አመት እድሜ የማትበልጥ ወጣት በደማቅ ቀለም በተዋበ ምቹ ሶፋ ላይ ተቀምጣለች ። ልጅቷ እንደ አዋቂ እጅግ ውድ ዋጋ ያለው ልብስ ለብሳለች ። ግሩም ወርቃማ ጸጉር ፣ ወተበ ሰማያዊ አይኖችና ትኩስ ደም የመሰለ ቀይ ከንፈር ያላት ይህች ወጣት እናቷ ደንገጡሯ ሆና አብራት ትገኛለች ። እናቲቱም የምታሳየው የእብሪት አመለካከት ሄገንን በጥፊ በላት አሰኝቶታል ። ‘መልአክ ልጅ እና ዘንዶ እናት’ አለ ሄገን በልቡ ።

በመጨረሻም አንዲት ግሩም አለባበስ ያላት መካከለኛ እድሜ ላይ የምትገኝ ወፈር ያለች ሴት መጥታ ሄገንን በአያሌ ቢሮዎች አቋርጣ ወደ ፊልም አዘጋጁ አቀረበችው ። ሄገን በቢሮዎቹ ውበት እና በሰዎቹ ሁኔታ በጣም ተደንቋል ። ፊገግ አለ ። ሁሉም ከሲኒማ ሙያ በር አንገታቸውን ለማስገባት ስራ ሳይመርጡ የጀመሩ ናቸው ።

ረዣዥሙ ፣ ግዙፉና ቦርጫሙ ምልትዝ በልኩ የተሰፋ ልብስ ለብሷል ። ሄገን የምልትዝን ታሪክ በውል ያውቃል ። ይህ ሰው በአስር አመት እድሜው ባዶ የወይን ጠጅ በርሜል ሲያንከባልልና ጋሪ ሲገፋ ነበር ። በሀያ አመቱ አባቱን በልብስ ስራ ላይ ሲረዳው ቆየ ። ሰላሳ ሲሞላው ኒውዮርክን ትቶ ወደ ምእራብ ዩናይትድ ስቴትስ በመጓዝ በዝቅተኛ ዋጋ ሲኒማ የሚታይበት ድርጅት ከፈተ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በአርባ ስምንት አመቱ በሆሊውድ ታላቅና ሀያል የሲኒማ ባለሙያ ለመሆን በቅቶ በምስኪን ወጣት ሴቶች የሲኒማ ተዋንያት መንጋ ላይ ሊገራ ያልተቻለ ኮርማ ሆነ ። ሀምሳ አመት ሲሞላው ግን የረቀቀ ህይወት መምራት ጀመረ ። ያልተገራው አን ደበቱ እንዲለዝብ የአነጋገር ዘይቤ ትምህርት ወሰደ ። የእንግሊዝ አልባሽ ቀጥሮ አለባበስ ተማረ ። አሁንም ሌላ የእንግሊዝ ባለሟል ቀጥሮ በአካባቢው ለሚያከ ከናውናቸው ማህበራዊ ተግባሮች ስነ ስርአትን ለመደ ። የመጀመሪያ ሚስቱ ስትሞት በአለም ዝነኛ ተዋናይ ብትሆንም ተዋናይነትን የጠላች ውብ ሴት አገባ ። ዎልትዝ በገንዘቡ ህይል በስድሳ አመቱ ታላላቅ ስእ ሎችን እየገዛ የሚሰበስብ ከበርቴ ፡ በፖለቲካ ረገድም የፕ ሬዚዳንቱ ፊልም አማካሪ ኮሚቴ አባል ሆነ ። በዚህ እድሜው የበቃ የፖለቲካ ሰው ፡ በብዙ ሚሊዮን ብር ወጪ የተመሰረተ የፊልም ኪነጥበብ የሚስፋፋበት ማእ ከል በስሙ ያቋቋመ ፡ ሴት ልጁን ለእንግሊዝ መኳ ንንት ዘር የዳረ ፡ ወንድ ልጁ የኢጣሊያን ልእልት ያገባ ታላቅ ሰው ሆኗል ።

ዘግየት ባሉት ጊዜያት ደግሞ ብዙ የፊልም አስ ተያየት ሰጪዎች እንደዘገቡት ትኩረቱ በፈረስ ግል ቢያ መዝናኛ ላይ በመሆኑ ባለፈው አመት ብቻ አስር ሚሊዮን ብር የፈጀ ምርጥ ፈረሶች እንክብካቤ የሚያ ገኙበት ጋጥ አሰርቷል ። የመገናኛ ዘዴዎች የወቅቱ አቢይ ርእስ የሆነው ዜና ደግሞ አንድ 'ካርቱም' የሚባል የእንግሊዝ ምርጥ ፈረስ ሊታመን በማይችል ዋጋ ፡ በስድስት መቶ ሺህ ብር መግዛቱ እና በውድድር ላይ ተሸንፎ የማያውቀውን ይህንን ፈረስ ውድድር አቁሞ ለዘር ብቻ በጋጡ እንዲቀመጥ መወሰኑ ነው ።

ዎልትዝ ሄገንን በትህትና ተቀበለው ። በጥንቃቄ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሳለው መልኩና ቀና ፊቱ በፈገግታ አስተናገደው ። ከእድሜው በታች ለመምሰል ብዙ ገንዘብ ቢያወጣም፣ በብዙ ባለሙያዎች ቢገለገልም እድሜው አጋልጦት ቆዳው እርስ በርሱ የተሰፋ ይመስላል ። ዶን ኮር ሌዎኔን ይመስል የሚኖርበትን አለም እቆጣጠራለሁ ባይ ነት በዎልትዝም ጠንካራ የሰውነት እንቅስቃሴ ላይ ይታያል ።

ሂገን ወዲያውኑ የመጣበትን ጉዳይ አነሳ ። እራሱንም ሲያስተዋውቅ የጆኒ ፎንቴን ወዳጅ የሆነ ሰው መልእክተኛ መሆኑን ፣ ይህም የላከው ሰው እጅግ ሀይለኛ እንደሆነ ፣ ሚስተር ዎልትዝ አንድ ትንሽ ውለታ ቢውልለት ብድሩን ለመመለስ እና ዘለአለማዊ ወዳጅነቱን ለማረጋገጥ ቃል እንደሚገባ ነገረው ። ይህም ትንሽ ውለታ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ በሚቀረጸው የጦርነት ፊልም ላይ ጆኒ ፎንቴን በተዋናይነት እንዲሰራ የሚጠይቅ ነበር ። በክር የተሰፋ የሚመስለው የዎልትዝ ፊት ጽሞናው አብቅቶ ሂገንን በትህትና መጠየቅ ፈለገ ።

"ወዳጅህ በምን አይነት ውለታውን ሊመልስ ይችላል ?" አለው በመዘባነን ።

ሂገን ይህን መዘባነን ችላ በማለት ማስረዳቱን ቀጠለ ።

"የሙያ ማህበራት እንቅስቃሴ እየተነሳብህ ነው ። የኔ ወዳጅ ይህን ችግር ያስወግድልሀል ። ፊልሙን እንዲሰራ የመረጥከው መሪ ተዋናይ ለስቱዲዮህ ብዙ ገንዘብ ቢያስገባልህም የአደንዛዥ እጽ ሱሰኛ ነው ። ከእንግዲህ አንዳችም እጽ እንዳያገኝ ለማድረግ ይጥላል። ከዚህ በተረፈ አንዳንድ ችግር ቢያጋጥምህ የስልክ ጥሪ ብታደርግልኝ ወዳጄ ችግርህን ይቃልልሀል" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጃክ ዎልትዝ የሄገንን ንግግር እንደ ትንሽ ልጅ ጉራ በመቁጠር ካዳመጠው በኋላ ያልተገራ አንደበቱን ለቀቀው ፣

"እኔን ማስፈራራትህ ነው?" ሲል ሄገን ላይ ደነ ፋበት ።

ሄገንም ሳይገነፍል ፣ "ፈጽሞ አይደለም ። የመጣሁት በወዳጅነት በጐ ፈቃድህን ለመጠየቅ ነው ። ይህን በማ ድረግም ላንተ የሚጎልብህ ነገር አይኖርም" ሲል ለማ ግባባት ጣረ ።

ዎልትዝ ግን በቁጣ አይኑን አፍጥጦ ወደ ሄገን ጋደል አለና ፣ "ይብቃህ ፣ አንተ ቅልስልስ የውሻ ልጅ ፣ ላንተና ላለቃህ አንድ ነገር ግልጽ ላድርግላችሁ ። ጆኒ ቮንቴን የፊልም ተዋናይነቷን ፈጽሞ አያገኙትም ። ምንም ያህል የማፊያ ሽፍታ ስብስብ ከሜካ ቢወጣ ከቁም ነገር አልቆጥራችሁም" ብሎ ወደ ኋላው ተለጠጠ ። ቀጥሎም "ይልቅስ ስማኝ ወንድም ። ስለ ኤድጋር ሁሰር ሰምተህ የምታውቅ ይመስለኛል ። የምትማመንበት ወዳጄ ነው ። እያስቸገሩኝ ነው ብዬ ብነግረው ምን በትር እንደመታችሁ ሳታውቁት ልበቀ ላችሁ እችላለሁ ፣" በማለት ሄገንን አስፈራራው ። ሄገን በትእግስት አዳመጠው ። ዎልትዝን ከመሰለ ሰው የጠበቀው ከዚህ የተሻለ አንጋገር ነበር ። ይህን የመሰለ ደደብ ፣ ምግባረ ብልሹ ሰው የዚህ ታላቅ ኩባንያ የበላይ እንዴት ሊሆን ቻለ? ቶም ሄገን የፊልም ኢንዱስትሪ ቁንጮ እንዲህ በመሰሉ ደናቁርት የሚ መራ ከሆነ ፣ ገንዘቡን በአዳዲስ የንግድ ስራዎች ላይ ለማዋል በመሻት ላይ ያለው ኮርሌዎኔም ገንዘቡን በፊልም ስራ ላይ ቢያውለው ሊያዋጣው እንደሚችል አሰበ ። ሄገን ከዶኑ የተማረው የመደራደር ጥበብ ትዝ አለው ። 'ፈጽሞ ሰውን አታስፈራራ ፣ በምክንያት

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማግባባት ሞክር እንጅ እያለ ይመክረው ነበር ። ያ ዶኑ ማግባባት የሚለው ጥበብ ስድብን ፥ ማስፈራራትን ችላ በማለት አንዱ ጉንጭ ሲመታ ሌላውን ማሳየትን ይመ ክራል ። ሄገን የዶኑን ትእግስት ሲያስታውስ በተለይ በአንድ ወቅት ለስምንት ሰአታት ያህል ከአንድ እርጉም ትምክህተኛ ጋር የስድብ ውርጅብኝን ችሎ ሲደራደር ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ትእግስቱ ሲያልቅ 'ከዚህ ሰው ጋር ማንም ምክንያት ደርድሮ ለመግባባት አይችልም' በማለት በስፍራው ለነበሩት ሰዎች ገልጾላቸው ስብሰባ ውን ረግጦ መውጣቱ ትዝ ይለዋል ። ይህ ሁኔታ ያን ትም ክህተኛ ሰው በፍርሀት አገረጣው ። ስብሰባውን እንደ ገና ለማካሄድ መልእተኞች ተልከው ስምምነት ላይ ቢደርሱም ፥ ከሁለት ወር በኋላ ያ ሰው ጸጉር ቤት እያለ ተገደለ ።

ስለዚህ ያን ከዶኑ የተማረውን ከፍተኛ ትእግስት በተግባር በማዋል ቶም ሄገን እንደገና በጽሞና ንግግ ሩን ቀጠለ ።

"መታወቂያዬን ተመልከት ። የህግ ባለሙያ ነኝ ። ከቶውን አንገቴን ብቅ ብቅ አድርጌአለሁ? አንድ የማሰፊ ራራት ቃልስ ተናገርሁ ? አድምጠኝ ፥ ይህችን ብቻ ልና ገር ። ለጆኒ ፎንቴን ያን የሲኒማ ስራ እንድትሰጠው ማናቸውንም ውለታ ለመደራደር ዝግጁ ነኝ ። ለዚች አነስተኛ ውለታ ላንተም የሚበጅህ ከፍተኛ መደራ ደሪያ ያቀረብኩልህ ይመስለኛል ። ችሎታ የሌለው ሰው ቢሆን ኖሮ ይህችን አነስተኛ ውለታም ብትሆን አት ጠየቅም ነበር ። እንደ እውነቱ ከሆነ ለፊልሙ ስራ ስለምታውለው ገንዘብ ስጋት ያለህ ከሆነ የኔ ወዳጅ አስፈላጊውን ወጪ ሊሸፍን ይችላል ። ነገር ግን እባክ ህን እራሴን ግልጽ ላድርግልህ ። ያንተ እምቢታ እምቢታ ነው ። ማንም ሰው አያስገድድህም ። ወይም ለያስገድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድህ አይሞክርም ። ከሚስተር ሁቨር ጋር ያለህን ግን ኙነትም እናውቃለን ። ለዚህም የኔ አለቃ ያከብርሀል።''

ዎልትዝ ትልቅ ቀይ ላባ ያለው ብእር ይዞ ይሞ ነጫጭራል ። የገንዘብ ነገር ሲነሳ መሞነጫጨሩን ቆም አድርጎ ነቃ አለ ። ''ይህ ፊልም እኮ የአምስት ሚሊ ዮን ብር በጀት ነው የተያዘለት'' አለ ።

ሄገን የገንዘቡን ከፍተኛነት ማድነቁን ለማሳ የት አፋጨና ''የኔ አለቃ ፍላጎቱን የሚያሟሉለት እጅግ ብዙ ወዳጆች አሉት'' በማለት በገንዘቡ ረገድ ችግር እንደማይኖር ገለጸለት ።

ዎልትዝ ለመጀመሪያ ጊዜ ጉዳዩን በጽሞና ተመለ ከተው ። የሄገንን ማንነት የምትገልጸውን ካርድ አጤነና ፣

''ስላንተ ሰምቼም አላወቅ ። የኒውዮርክን የታወቁ የህግ ባለሙያዎች አውቃቸዋለሁ ። ታዲያ አንተ ደግሞ ከየት የመጣህ ነህ?'' አለው በንቀት ።

''እኔም ከነዚያ ከተከበሩ ኩባንያዎች በአንዱ የህግ ሙያ አከናውናለሁ ። ይህን የዛሬውን ጉዳይም እራሴ ነኝ መርጬ የያዝኩት'' ካለ በኋላ ከተቀመጠበት ተነሳ ። ''ከዚህ በላይ ጊዜህን አላጠፋብህም'' ብሎ ሊጨብጠው እጁን ሲዘረጋለት ዎልትዝም ጨበጠው ። ሄገን ወደ በሩ ጥቂት ከተራመደ በኋላ ወደ ዎልትዝ መለስ ብሎ ፡

''ከማንነታቸው ይበልጥ ታላላቆች መስለው ከሚ ታዩ አያሌ ሰዎች ጋር ብዙ ሳትዋዋል እንዳልቀረህ እገ ምታለሁ ። የኔ ሁኔታ ግን ተቃራኒው ነው ። ቢጋራ ወዳ ጆችን በኩል ማንነቴን ለምን አትረዳውም? አሳብህን የም ትለውጥ ከሆነ ካለህበት ሆቴል ደውልልኝ ። የኔ ደምበኛ ከሁቨርም ክልል በላይ የሆነ ውለታ ሊፈጽምልህ የሚ ችል በመሆኑ ውሳኔህ በበጎ ነገር ላይ የፈጸምከው ድፍ ረት እንዳይሆንብህ'' አለው ። ይህን ጊዜ የፊልም አዘ ጋጁ አይን እየጠበበ ሲሄድ ቶም ተመለከተ ። ዎልትዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻ መልእክቱ ደርሶታል ማለት ነው።

"በነገራችን ላይ፣ ፊልሞችህን በጣም አደንቃቸዋለሁ። ይህን መልካም ስራህን መቀጠል አለብህ። አገራችን ትፈልገዋለች" በማለት በተቻለ መጠን በለዘበ አንደበት ሸረደደው።

ከሰአት በኋላ ላይ ዘግየት ብሎ ሄገን ከዎልትዝ ጸሐፊ ጥሪ ደረሰው። በዎልትዝ የንጠር ቤት እራት ስለተጋበዘ መኪና እንደሚላክለት፣ ወደ ገጠሩ ቤት ለመድረስ የሶስት ሰአት ጉዞ እንደሚፈጅና በመኪናው ውስጥ መጠጥና ምግብ የሉሚላ እንደሚሆን ተገለጸለት። በተጨማሪም ጸሐፊዋ ትህትና በተሞላበት አነጋገር ለምሽት የሚያገለግል ልብስ የያዘ ሻንጣ እንዲይዝና ጧት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ እራሱ ዎልትዝ እንደሚያደርሰው ነገረችው።

እንግዲህ ሄገን የዶን ኮርሌዎኔ መልእክተኛ መሆኑን ዎልትዝ ተረድቶታል። ስለዚህ ስለዶኑ ማንነትም ስለሚረዳ ነገሮችን በምር ይመለከታቸዋል ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ዎልትዝ ጧት ከነበረው ሁኔታ የተሻለ ብስለት ያሳይና አንድ ውል ያለው ነገር ያደርጋል ብሎ ሄገን ገመተ።

የጀክ ዎልትዝ ቤት ውሉ የጠፋ የሲኒማ ድርጅት ይመስላል። ለመዘዋወር በሚያመቹ መንገዶች የተከበበው ሰፊ ግቢ፣ ትላልቅ ዛፎች፣ የፈረሶች ጋጥና ለፈረሶች ማሰማሪያ የሚሆን የጣለሽ መስክ ያለው ግቢ ነው። የግቢው ዛፎች፣ የአበቦችና የሳሩ አቆራረጥ እንደ ፊልም ተሞናይ ጥፍር ጥንቃቄ የተሞላበት ነው።

ዎልትዝ ሄገንን በመስታወት በተከበበ የአየር ሙቀትና ቅዝቃዜ ማስተካከያ ባለው በረንዳ ላይ ሆኖ ተቀበለው። የፊልም አዘጋጁ ክፍት ሰማያዊ የሀር ሸሚዝ፣ ብጫ ሰፊ ሱሪና ከለስላሳ ቆዳ የተሰራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነጠላ ጫማ ለብሷል ። ከቀረበው ትሪ ላይ አንድ ማር ቲኒ የተቀዳበት ብርጭቆ ለሄገን አቀብሎት አንድ ሌላ ለራሱ አነሳ ። ቅድም ከነበረበት ሁኔታ በጣም የተሻለ ወዳጅነት የተሞላበት ሁኔታ አሳየው ። እጁን ሄገን ትከሻ ላይ ጣል አደረገና "እራት እስኪቀርብ ጥቂት ጊዜ ስላለን ፣ ና ፈረሶቼን ላሳይህ" አለው ። ወደ ጋጡ ሲያመሩም ።

"ማንነትህን አወቅኩት ። አለቃህ ኮርሌዎኔ መሆኑን ልትነግረኝ ይገባህ ነበር ። ጆኒ እኔን ለማወናበድ የላከህ አንድ ዝቅተኛ ደረጃ አጭበርባሪ አድርጌ ገምቼህ ነበር ። እኔ በማስመሰል አልታለልም ። እንዲያም ሆኖ ፣ ጠላት በማፍራት አላምንም ። አሁንም ሁላችንም እንዝናና ፤ የሰራችንን ጉዳይ ኋላ እንነጋገርበታለን ።" በማለት አብሮት ተራመደ ።

ዎልትዝ በሚያስደንቅ ሁኔታ መልካም አስተናጋጅ ሆነ ። ጋጡን በአሜሪካ ከማናቸውም ጋጥ ይበልጥ ዝነኛ እንዲሆን ለማድረግ ያቀደውን ሀሳብና ዘዴ ለሄገን አስረዳው ። ጋጠቹ ሁሉ እሳት የማያጠቃቸው ፣ የጤና አጠባበቅ ሁኔታቸው በከፍተኛ ደረጃ የተሟላ ፣ ጥበቃቸውም በልዩ የግል የጥበቃ ኃይል የሚካሄድ ናቸው ። በመጨረሻም በመግቢያው በኩል ግድግዳ ላይ በነሀስ 'ካርቱም' የሚል ጽሁፍ እተለጠፈበት ጋጥ ወሰደው ። ሄገን ፈረሶችን የመለየት ልምድ የሌለው ቢሆንም በጋጡ ውስጥ ያለው ፈረስ ቁመናና መልክ በጣም ማርኮታል ። የ'ካርቱም' መልክ ግንባሩ ላይ ካለው የአልማዝ ቅርጽ ንጣት በስተቀር የኑግ ልጥልጥ የመሰለ ጥቁር ነው ። የፈረሱ ትላልቅ ቡናማ አይኖች እንደ ወርቅ እንከብል ያብረቀርቃሉ ። መላ ጸጉሩ ሀር ይመስላል ። ዎልትዝ እንደ ትንሽ ልጅ ጉራ ፣ "ይህን በአለም ታላቅ የእሽቅድምድም ፈረስ የገዛሁት ከእንግሊዝ አገር

t.me/OLDBOOKSPDF

በሰድስት መቶ ሺህ ብር ነው ። እንዲህ ያለ ከፍተኛ ገንዘብ የሩሲያ ነገስታት እንኳ ከፍለው አያውቁም ። ነገር ግን ይህን ፈረስ ውድድር ውስጥ አላስገባውም። ለዘር ብቻ ነው ። ይህች አገር አይታው የማታውቀው የፈረሶች ጋጥ ለማሰራት እቅድ አለኝ ፥ ”አለና ፥ የፈረሱን ጋማ አሻሸው በለሆሳስ ‘ካርቱም ፥ ካርቱም’ ብሎ ፍቅር በተሞላበት ድምጽ ሲጠራው እንሰሳው ተቁነጠ ነጠ ።

“ታውቃለህ ፥ ጥሩ ፈረሰኛ ነኝ ፥ ለመጀመሪያ ግዜ ፈረስ የጋለብኩት በሀምሳ አመት እድሜየ ነበር ”አለና ሳቀ ። ቀጥሎም “ምናልባት ከአያቶቼ አንዷ በኩሳክ ተወላጅ ፈረሰኛ ሳትደፈር አልቀረችም።የሱ ደም በውስጤ አለ፥” አለው።ዎልትዝ ካርቱምን ሆዱን ከኮረኮረው በኋላ ከልቡ በሆነ አድናቆት “እየው ስሜቱ እንደሚያቁነጠንጠው ። እኔም እንደዚህ ፈረስ የስሜት መቁነጥነጥ ሊኖረኝ ይገባል” እያለ ቀለደ ።

ወደ ቤቱ ሰራት ሲመለሱ በአንድ አለቃ የሚመሩ ሶስት አሳላፊዎች አስተናገዷቸው ። የጠረጴዛው ልብስ ወርቀዘቦ የተጠለፈበት ፥ የምግብ እቃዎቹ በወርቅና በብር የተንቆጠቆጡ ሲሆኑ ፥ ምግቡ ግን በጥንቃቄ የተዘጋጀ አይመስልም ። ዎልትዝ ለምግብ ግድየለሽ እንደሆነ ያስታውቃል ። ምግብ አብቅቶ ሁለቱም የሀሻና ሲጋር ማጨስ እስኪጀምሩ ጠበቀና ሄገን ፥

“ጆኒ ስራው ይሰጠዋል ወይስ አይሰጠውም?” ሲል ጠየቀ ።

“አልችልም ፥ ለተዋንያኑ ኮንትራት ተፈርሞ ፊልሙ የሚቀጥለው ሳምንት መነሳት ይጀምራል ። ይህን ስራ ልሰጠው ብፈልግ እንኳን ሁኔታዎቹን ለመለወጥ ስለማይቻል አልችልም”በማለት ዎልትዝ መለሰለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ትእግስቱ ተሟጠጠና ፡ "ሚስተር ዎልትዝ ፣ በአንድ ድርጅት አናት ላይ ካሉ ሰዎች ጋር የመደራደር ደግነቱ እንዲህ የመሰለው ሰበብ ነገሮችን ለመለወጥ በምክንያትነት ሊቀርብ አለመቻሉ ነው" ብሎ ሲጋራውን ካቦነነ በኋላ ፡ "የኔን ደምበኛ ቃሉን የሚጠብቅ ሰው አድርገህ አልገመትከውም ልበል?" ሲል ጠየቀው ።

ዎልትዝ ድርቅ ባለ አነጋገር ሲመልስ ፡

"የሙያ ማህበር ችግሮች እንደሚገጥሙኝ አላጣሁትም ። ያ የውሻ ልጅ ጮኩ ደውሎ ሲያነጋግረኝ የነበረው ሁኔታ በያመቱ ከኔ በድብቅ አንድ መቶ ሺህ ብር እንደሚቀበል ሰው አይነት አልነበረም ። ያንን የመረጥኩትን የግብረ ሰዶም አመለኛ የሆነ መሪ ተዋናይ ከአደንዛዥ እጽ ልታርቁት እንደምትችሉ አምናለሁ ። ግን ለዚህ ሁሉ ግድ የለኝም ። ፊልሞቹን እኔው እራሴ ማሰራት እችላለሁ ። በዚያ በዲቃላ በፎንቴን ላይ ጥላቻዬ ገደብ የለውም ። አለቃህን ይህን ውለታ ብቻ ላደር ግለት እንደማልችል ፡ ነገር ግን ከዚህ በስተቀር ሌላ ውለታ በጠይቀኝ ፈቃደኛ እንደምሆን ግለጽለት ። ማናቸውም ጉዳይ ይሁን" አለው ።

ሄገን 'አንት ወስላታ ዲቃላ! ታዲያ ለምን ይህን ሁሉ መንገድ አለፋኸኝ?' ሲል በልቡ ከአሰበ በኋላ ፡

"ሁኔታውን የተረዳህ አልመሰለኝም ። ሚስተር ኮርሌዮኔ የጆኒ ፎንቴን የክርስትና አባቱ ነው ። ይህም የተቀደሰ ሀይማኖታዊ የቅርብ ዝምድና ነው" ብሎ ሄገን ሲናገር ዎልትዝ በአክብሮት እጅ ነሳ ። ሄገን ንግግሩን ቀጠለ ፡ "ጣልያኖች አንድ አባባል አላቸው ። ይህም ፡ 'አለም በአንድ አባት ብቻ የማትበገር ስለሆነች የሰው ልጅ ሁለት አባቶች ሊኖሩት ይገባል ፡' የሚል ነው ። ለዚህ ነው ክርስትና አባት የሚኖራቸው ። የጆኒ አባት

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሞተ ወዲህ ፥ ሚስተር ኮርሌዎኔ ሀላፊነቱ እጅግ ይሰ ማዋል ። ሌላ ውለታ ይጠይቀኝ ላልከው ግን የላከኝ ሰው የመጀመሪያ ጥያቄውን ያላሟላለትን ሰው ሌላ ውለታ አይጠይቀውም ፥ ” አለው ። ዎልትዝ በምን ቸግ ረኝ ባይነት ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና “ አዝናለሁ መልሱ አሁንም ያው አይሆንም ነው ። ነገር ግን እዚህ ከመጣህ ስለ ሙያ ማህበራት ችግር ጉዳይ እናንሳና ፥ ይህን ችግር ምን ያህል በካ'ሽ ብከፍላችሁ ታስቆሙታ ላችሁ ። አሁኑኑ ልከፍላችሁ እችላለሁ” አለው ።

ሄገን ሌላ እንቆቅልሽ ተፈታለት ። ዎልትዝ በእም ቢታው ቢጸናም ይህን ያህል ጊዜ አብሮት ሊቆይ የቻ ለበትን ምክንያት ተረዳው ። ዎልትዝ ከዶን ኮርሌዎኔ ሀይል ከለላ እንዳለው ስለሚያምን አልፈራም ። በእ ርግጥ ዎልትዝ ባለው የፖለቲካ ግንኙነት ፥ ከኤፍ.ቢ. አይ ዋና ባለስልጣን ጋር ባለው ትውውቅ ፥ በታላቅ ሀብቱ ፥ በፊልም ኢንዱስትሪ ላይ ባለው ፍጹም ስል ጣን ፥ ለዶን ኮርሌዎኔ ማስፈራራት አይደነግጥም ። ዎልትዝ ስለራሱ የሰጠው ግምት ትክክል መሆኑን ሄገ ንም ያምናል ። የሰራተኞች አድማ ቢነሳበትም የሚደ ርስበትን ኪሳራ እችለዋለሁ ካለ ዶኑ ዘልቆ ሊገባበት የሚችልበት መንገድ አይኖርም ። ግን አንድ ችግር አለ ። ዶን ኮርሌዎኔ ለክርስትና ልጁ ስራውን እንደ ሚያሰጠው አረጋግጦለታል ። ሄገን እስከሚያውቀው ድረስ ደግሞ የዶኑ ቃል ታጥፎ አያውቅም ።

ሄገን በጽሞና እንዲህ አለ ፤

“ሆን ብለህ ያልተረዳኸኝ እየመሰልክ ነው ። መን ገድህን በማደናቀፍ ካንተ ገንዘብ የሚሹትን ሰዎች ህገ ወጥ በሆነ ዘዴ እንድከለክላቸው ልታደርገኝ ትሞክራ ለህ ። ሚስተር ኮርሌዎኔ ደምበኛውን ተቀብለህ በማን ጋገርህ ለወዳጅነት ማረጋገጫ ላንተ ቆሞ ፥ የሰራተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኞችን አድማ ጉዳይ ሊያነጋግርልህ ፈቃደኛ መሆኑን ቃል ገብቷል ። ወዳጃዊ መደጋገፍ እንጂ ከዚህ የተለየ አይደለም ። እንደማየው ግን ለጉዳዩ ትኩረት የሰጠኸው አልመሰለኝም ። በግሌ ስመለከተው ይህ ስህተት ነው ።''

ምልትዝ ይህን ወቅት ሲጠብቅ የቆየ ይመስል እሳት ሆነ ።

''በሚገባ ተረድቼዋለሁ ። ይህ የማፊያ ዘይቤ ነው ፣ አይደል? ሁሉም የወይራ ዘይት እና ጣፋጭ አነጋገር በውስጡ ማስፈራራት ያለበት ነው ። ስለዚህ ግልጽ ላድርግልህ ። ጆኒ ፎንቴን ለተዋናይነቱ ሙሉ በሙሉ ብቁ ቢሆንም ስራውን ፈጽሞ አያገኘውም ። ይህን ሚና ቢጫወት ታላቅና ዝነኛ ተዋናይ እንደሚወጣው አውቃለሁ ። ነገር ግን ያንን ያልበሰለ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ከሲኒማ ተዋናይነት ድራሹን አጠፋዋለሁ ። ለምን እንደሆነ ልንገርህ ። አንዲት ብዙ መቶ ሺህ ብር አፍስሼ ለአምስት አመታት ያህል በድምጻዊነት እያሰለጠንኩ ስንከባከባት የቆየች ልጅ ፣ እውቅ ተዋናይ አደርጋታለሁ ብዬ ሰደክም አስኮብልሎ አበላሽብኝ ። በግልጽ ልንገርህ ። ልበ ድንጋይ አይደለሁም ። የሳንቲም ጉዳይ ብቻ አይምሰልህ ። ልጅቷ ከቁንጅናዋም በላይ በዚህ አለም ካጋጠሙኝ ሴቶች እንደሷ የተደሰትኩባት የለችም ። ታዲያ ጆኒ ያንን የወይራ ዘይት ድምጹንና አሻንጉሊት ፊቱን ይዞ ሲቀርባት አዋርዳኝ ጥላኝ ኮበለለች ። ሚስተር ሄገን ፣ በኔ ደረጃ ያለ ሰው ውርደትን ለመቀበል አቅም የለውም ። ስለዚህ ጆኒን የሚገባውን ዋጋውን እሰጠዋለሁ'' ሲል ምልትዝ በምሬት ሲነግረው ፣ ሄገን ለመጀመሪያ ጊዜ በጉዳዩ ተገረመ ።

እንዲህ ያለ ትልቅ ሰው ዝሙትን የመሰለ ቀላል ነገር በስራው ላይ ገብቶ ተጽእኖ ሊያደርግበት መቻሉ ሄገንን ሲዋጥለት አልቻለም ። በሄገንና በዶን ኮርሌዎኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

አለም ፥ የገጽ ውበት ፥ የሴቶች ግብረ ስጋ ችሎታ ፥ በአ
ለም ውስጥ በሚያከናውኑት ተግባርና ውሳኔ ላይ አን
ዳችም ክብደት የለውም ። የቤተሰብን ክብር እስከማዋ
ረድ ካልደረሰ ፥ ወይም በጋብቻ ላይ ጣልቃ እስካል
ገባ ይህ የግል ጉዳይ ነው ። ሄገን አንድ የመጨረሻ
ሙከራ ለማድረግ ቆረጠ ።

"ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ነህ ፥ ሚስተር ዎልትዝ ። የደረሰብህ በደል ግን ያን ያህል አቢይ ነው? ይህ የም ጠይቅህ አነስተኛ ውለታ ለደምበኛዬ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ የተረዳኸው አልመሰለኝም ። ጆኒ ክርስትና ሲነሳ ሚስተር ኮርሌዎኔ ነው በእጁ ያቀፈው ። አባቱ ሲሞት ሚስተር ኮርሌዎኔ የወላጅነትን ሀላፊነት ተረ ከበ ። ዶኑ ላደረገላቸው ውለታ ክብርና ምስጋና የሚ ያቀርቡለት ሰዎች 'የጡት አባት' የሚል መጠሪያ ሰጥተውታል ። ሚስተር ኮርሌዎኔ ወዳጅነትን ፊጽሞ አያ ሳፍራቸውም "አለው ።

ዎልትዝ ድንገት ብድግ ብሎ ፥ "የሰማሁህ በቅ ቶኛል ። ማጅራት መቺዎች ለኔ ትእዛዝ አይሰጡኝም ። እኔ ነኝ ትእዛዝ የምሰጣቸው ። ይህን ስልክ ባነሳ አዳ ርሀ እስር ቤት ይሆናል ። ያ የማፊያ አለቃህም ጠን ከር ያለ ነገር ቢሞክር እኔ የእንድ ተራ ቡድን መሪ አለመሆኔን ይረዳዋል ። አዎን ፥ የምትለውን ታሪክ ሰም ቸዋለሁ ። ስማኝ ፥ ኋይት ሀውስ ያለኝን አግባብ ብጠ ቀምበት ያንተ ኮርሌዎኔ የመታውን ዱላ እንኳ ማወቅ አይችልም ፥ "አለው በእብሪት ።

'ይህ ደደብ የውሻ ልጅ በምን አባቱ እንዲህ ከባድ ሰው ለመሆን ቻለ?' በማለት ሄገን ተገረመ ። ዎልትዝን የመሰለ ሰው የፕሬዚዳንቱ አማካሪ ፥ የታላቁ ሲኒማ አዘ ጋጅ ድርጅት የበላይ ባለስልጣን ከሆነ ፥ ያለጥርጥር ዶኑ በፊልም ንግድ ስራ ውስጥ መግባት አለበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሰው የሚመራው በግልጽ በሚሰማው ስሜት ብቻ ስለሆነ የሄገን መልእክት አልደረሰውም ማለት ነው ።

"ስለ ተደረገልኝ ግብግ አመሰግናለሁ ። ወደ አውሮፕላን ማረፊያ የሚወስደኝ መጓጓዣ ታገኝልኛለህ፣ እዚህ አላድርም ። ሚስተር ኮርሌዎኔ መጥፎ ዜናን ወዲያውኑ መስማት የሚፈልግ ሰው ነው" አለው ።

ሄገን በመብራት ባሸበረቁት ቋሚዎች መሀል ሆኖ መኪና እንዲመጣለት ሲጠባበቅ ፣ ጪት ዎልትዝ ቢሮ ያያቸው ቆንጆይቱ ልጅና እናቷ ረዥም አውቶሞቢል ውስጥ ሲገቡ ተመለከተ ። የልጅቱ የተከረከመ የሚመስል ከንፈር ወፍሮ ፣ አይኗ ደብዝዞ ፣ ረዥም እግሮቿም መራመድ አቅቷቸው እንደ ሽባ ይዝለፈለፉ ነበር ። እናቲቱ በጆሮዋ ትእዛዝ እያንሾካሾከች ደጋግፋ ወደ መኪናው አስገባቻት ። ሄገንንም ዞራ አየት አድርጋው ድል አድራጊነት እንደተሰማት እየታየባት በመኪናው ውስጥ ገባች ። ዎልትዝ ሄገንን በአውሮፕላኑ አሳፍሮ ከሎስ አንጀሊስ ያላመጣው እነዚህን ሴቶች በመጫኑ ምክንያት መሆኑን ተረዳ ። ዎልትዝ ከሄገን ጋር ያለው ቀጠሮ ከመድረሱ በፊት ከዚች ጨቅላ ጋር ለመዝናናት ጊዜ አግኝቷል ማለት ነው ። ታዲያ ጆኒ ፎንቴን እንዲህ ካለው አለም ውስጥ ለመኖር ነው የሚፈልገው ። መልካም እድል ለጆኒም ለዎልትዝም ፣ እንዳሻቸው ይሁኑ!

ፖሊ ጋቶ በተለይ የጠብ ተልእኮ ሲሰጠው በሚገባ ማቀድ ስለሚፈልግ ችኮላ አይወድም ። ምንም እንኳ ለዚያን ምሽት የተሰጠው ስራ የአሜሪጎ ቦናሴራን ልጅ ከደበደቧት ልጆች ጋር የሚካሄድ ፍልሚያ ቢሆንም ከሰዎቹ መሀከል አንዱ ቢሳሳት አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ። ቢራውን እየጠጣ ፣ አካባቢውን እየቃኘ ፣ እነዚያ ሁለት ወጣቶች ቡና ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ካለት ሁለት ወጣት ሴቶች ጋር ሲዝናኑ ተመለ
ከተ ። ስለነዚህ ልጆች ግወቅ የሚገባውን መረጃ ሁሉ
ሰብስቧል ። ጀሪ ዋግነርና ኬቪን ሙናን የተሰኙት እነዚህ
የሀያ አመት ወጣቶች መልከ ቀናዎች እና ሎጋዎች
ናቸው ። ከሁለት ሳምንት በኋላ ከተግዋን ለቀው ወደ
ኮሌጃቸው ይመለሳሉ ። ሁለቱም ልጆች የፖለቲካ ሽግ
ምንት የሆኑ አባቶች ስላሏቸውና ኮሌጅ በመግባታ
ቸው ከውትድርና አገልግሎት ነጻ ሆነዋል ። ሁለቱም
የአሜሪካ ቦናሴራን ሴት ልጅ በመደብደባቸው በፍርድ
ገደብ ላይ ናቸው ።

'ቅማላም ዲቃሎች!' አለ ፖሊ ጋቶ በልቡ ።
እነዚህ የወላጆቻቸውን ስልጣን መከታ አድርገው
ከውትድርና አገልግሎት ያመለጡ ዋጋ ቢስ ወመኔዎች
የሰአት እላፊ ገደባቸውን ጥሰው ከእኩለ ሌሊት በኋላ
መጠጣትና ጽዳታቸውን የማይጠብቁ ሴትኛ አዳሪዎችን
ማሳደድ ነው ተግባራቸው ። ፖሊ ጋቶ ይህን ሁሉ እሰ
በና አእምሮው ታወከ ። ለእሱም ለራሱም ቢሆን
'የኤሌክትሪክ ሕክምና ተሰጥቶታል' የሚል ሀሰተኛ
መረጃ ቀርቦለት ከወታደራዊ አገልግሎት ነጻ እንዲሆን
ያመቻቸለት ክሌሜንዛ ነበር ። ይህም ቅንብር ሊደረግ
ለት የቻለው ፖሊ ጋቶ በኮርሌዎኔ ቤተሰብ ተግባር
ላይ ባሳየው ቆራጥነት ነው ።

የአሁኑን ተልእኮ ክሌሜንዛ ለፖሊ ጋቶ ሲነግረው
ልጆቹ ወደ ኮሌጃቸው ከመመለሳቸው በፊት በቶሎ መከ
ናወን እንዳለበት አስጠንቅቆታል ። ታዲያ ተልእኮው
ኒውዮርክ ውስጥ መፈጸም ያለበት መሆኑ ጋቶን አስ
ደንቆታል ። ክሌሜንዛ ሁልጊዜ መመሪያ ሲሰጠው ከዋ
ናው ተግባር ሌላ ተጨማሪ ስራ ይመድብለታል ። እነ
ዚያ ሁለት ምናምንቴዎች ከሴቶቹ ጋር አብረው ከወጡ
ተልእኮው ለሌላ ቀን መተላለፍ ሊኖርበት ስለሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤቶቹ የሚቀሩበትን መንገድ ፖሊ ጋቶ መቀየስ ያስ ፈልገዋል ። ግን አጋጣሚ ሆኖ ከልጆቹ ጋር ያለ ችው ወጣት እንዲህ ስትል ሰማት "አብደሀል ጂሪ ካንተ ጋር ፊጽሞ መኪና ውስጥ አልገባም ። እንደዚያች ምስኪን ልጅ መጨረሻዬ ሐኪም ቤት እንዲሆን አልፈልግም ።"

ልጅቷ ይህን ካለች ጥሩ የምስራች ነው ። አብራው አትሄድም ። ጋቶ ቢራውን ጨረሰና ወደ ሞለማው መንገድ አመራ ። እኩለ ሌሊት አልፏል ። አንድ ቡና ቤት ብቻ መብራት ከሚታይበት በስተቀር ሱቆች ሁሉ ተዘግተዋል ። የቀጣናው ጥበቃ መኪና በአካባ ቢው እንዳትገኝ ክሌሜንዛ አስፈላጊውን አደራጅ ቷል ። መኪናይቱ የሬዲዮ ጥሪ ካልተደረገላት አትመ ጣም ። ስትመጣም እያዘገመች ነው ።

ፖሊ ጋቶ አውቶሞቢሉን ተደገፈና ፥ እኋላ መቀ መጫው ላይ ለተደበቁት ሁለት ሰዎች "ልክ ከቡና ቤቱ ሲወጡ ይዛችሁ መኪና ውስጥ አስገቧቸው" ሲል መመሪያ ሰጣቸው ።

ጋቶ አሁንም ቢሆን ሁኔታዎች እንደተቻኮሉ ይገ ምታል ። ቀደም ሲል ክሌሜንዛ ፖሊስ ልጆቹን ያነ ሳቸውን ፊታቸውን በቅርበት የሚያሳይ ፎቶግራፍና ልጆቹ የሚያመሹበትን ቡና ቤት አድራሻ ለጋቶ ሰጥ ቶታል ። ጋቶ ሁለት የቤተሰቡን ወጠምሻ አሽከሮች መልምሎ ልጆቹን ካሳያቸው በኋላ መመሪያ ሲሰጣ ቸው ፥ ልጆቹ እንዳይሞቱ አናታቸውንና ማጅራታች ውን እንዳይመቱዋቸው ነግሮአቸዋል ። ከዚያ በተረፈ በደንብ እንዲደበድቧቸው ሲያዝ ፥

"እነዚያ ውሾች ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ከሀኪም ቤት ቢወጡ ፥ ወደ ጭነት መኪና ሹፌርነታችሁ እንደምትመለሱ እንድታውቁት" በማለት ድሮ ቦቅሰ ኞች የነበሩ ተከታዮቹን አስጠነቀቃቸው ። ተከታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዮቹ የክለባቸውን ውድድር ማሸነፍ ሲያቅታቸው ከው
ድድር መውጣት ግድ በሆነባቸው ጊዜ ሶኒ ኮርሌዮኔ
ደርሶላቸው ለመኖሪያ የሚሆን ገንዘብ በብድር ስም
ሰጥቷቸዋል ። ሰዎቹም ውለታውን ለመመለስ በቤተ
ሰቡ ተልእኮ ላይ ያለማወላወል ይሰማራሉ ። ሁለቱ ወጣ
ቶች አብረዋቸው ያመሹት ሴቶች ዘለፋና ወቀሳ እየ
ከነከናቸው በሞቅታ ከቡና ቤቱ ሲወጡ ለነፖሊ ጋቶ
ተልእኮ አመች ሆኖ ነበር ። ፖሊ መኪናውን ደገፍ
ብሎ ፤

"ስሙ እናንተ ሴት አመራረጥ እንኳን የማታውቁ
ወመኔዎች ፤ እነዚያ ሴቶች እንኳን ያባሯችሁ!" አላ
ቸው ። ወጣቶቹ ፈገግ ብለው ወደሱ ዞር አሉ ። ጋቶ
የሀፍረታቸው ማስወገጃ ስለመሰላቸው ዘለው ሊያን
ቋት ሲሉ ከበስተኋላቸው እጆቻቸው ተጠመዘዙ ። ጋቶ
እጅ ላይ የሚገባ የብረት መቦቀሻውን በቀኝ እጁ ላይ
ከመቅጽበት ካጠለቀ በኋላ ፤ በየሳምንቱ ሶስት ጊዜ የሚለ
ማመደውን ስፖርት በተግባር አዋለው ። ዋግነር
የተባለውን ወጣት አፍንጫውን ሰበረው ። ዋግ
ነርን ይዞለት የነበረው ሰውዬ ወደ ላይ ሲሸከምለት
ብሽሽቱን ደጋግሞ ጎሰመው ። ዋግነር ሲዝለፈለፍ የተ
ሸከመው ሰው አውርዶ ጣለው ። ይኸኛው ጉዳይ በስ
ድስት ሰኮንድ ተፈጸመ ። ሁለቱም ሰዎች ወደ ተከታዩ
ባለእጣ ኬቪን ሙናን ሲዞሩ ለመጮህ ሞከረ ። ከኋላው
ይዞት የነበረው ሰው በአንድ እጁ ጥብቅ አድርጎ ከያ
ዘው በኋላ ልጁ እንዳይጮህ በሌላው እጁ ጉሮሮውን
አነቀው ።

ፖሊ ጋቶ መኪናው ውስጥ ዘሎ ገባና ሞተ
ሩን አስነሳ ። ሁለቱ ወጠምቻዎች ሙናን እስኪዝለፈ
ለፍ ደጋግመው ጡጫ አጠገቡት ። ምታቸው ዝግ ያለ
ጥንቃቄ የተሞላበትና ጠንካራ ፣ እያንዳንዷም ቡጢ ስጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትቀረድድ ነበረች ። ጋቶ የሙናንን ፊት ሲመለከት ማንነቱን ለመለየት እንደሚያስቸግር ተገነዘበ ። ደብዳ ቢዎቹ ሙናንን ለቀቁና ወደ ዋግነር ተመለሱ ። ሙናን በመጮሁ ከቡና ቤት አንድ ሰው ብቅ ስላለ ተግባራቸ ውን ማፋጠን ነበረባቸው ። ዋግነር መረታቱ እስኪረጋ ገጥ ተቀጠቀጠ ። አንዱ እጁን ጠምዝዞ ጀርባውን ሲመ ታው የመሰበር ድምጽ ተሰማ ። የዋግነር የጣእር ጩኸት የተኛውን የሰፈሩን ሰው ሁሉ ቀሰቀሰው ። በመንገዱ ዳር ያሉ መስኮቶች ተከፈቱ ። ከነዚሁ ቅጥረኞች አንዱ የዋግነርን እራስ በሁለት እጁ ቆልፎ ከያዘው በኋላ ሌላው ደግሞ ግዙፍ እጁን ጨብጦ ደጋግሞ አሳረ ፊበት ይኸኔ በርከት ያሉ ሰዎች ከቡና ቤቱ እየወጡ መጡ ። ለመገላገል ወይም አጥፊውን ለመያዝ ግን አልደፈሩም ።

"ኑ ፣ በቃችሁ" አለ ፖሊ ጋቶ ። ሰዎቹ ዘለው መኪ ናዋ ውስጥ ሲገቡ ፖሊ ጋቶ መኪናዋን እንደ ጥይት አበረራት ።

ምእራፍ ሁለት

አርብ እለት ከቨርጂል ሶሎዞ ጋር ለሚደረገው ስብሰባ ቅድመ ዝግጅቱን ለማጠናቀቅ ሲል ሄገን ሀሙስ ጧት ከተማ ውስጥ ከሚገኘው የጠበቃ ቢሮው ገባ ። ሶሎዞ ለኮርሌዎኔ የሚያቀርበው ድርድር ስለ አደን ዛኧር እጽ ንግድ ጉዳይ መሆኑ በመታወቁ ቀደም ሲል በዚህ ጉዳይ ላይ ከዶኑ ጋር ለመወያየት አንድ ምሽት ሙሉ ፈጅቶበታል ።

ሄገን ከካሊፎርኒያ ተመልሶ ከዎልትዝ ጋር የነበ ረውን ንግግር ውጤት ሲያጫውተው ዶኑ ምንም አል

t.me/OLDBOOKSPDF

ተደነቀም ። ዶኑ ሄገን ያየውን የሰማውን ሁሉ እንዲ
ነግረው በጠየቀው ጊዜ ቆንጆዋን ልጅና እናቷን
በዚያ ማየቱን ሳይቀር ሲነግረው ዶኑ "ውጉዝ!" በማ
ለት ይህን በመሰለ ነገር ላይ ያለውን ጥላቻ ገለጸ ።
በመጨረሻም ዶኑ ጥያቄ አቀረበለት ።

"ይህ ሰው በእርግጥ ወዴ አለው?" ሄገን ዶኑ
ምን ማለቱ እንደሆነ አሰላሰለ ። ባለፉት ኣመታት ሄገን
ባገኘው ግንዛቤ ዶኑ ከሌሎች የተለየ እንደሆነ ሁሉ
ቃላቱም ልዩ ትርጉም ሊኖራቸው እንደሚችል ያው
ቃል ።

ዎልትዝ ከሰው የሚለይበት ባህርይ አለው? ፈቃዱ
የሚመራበት ጠንካራ ስሜት አለው ? እነዚህ ሊኖሩት
ይችላሉ ። ግን ዶኑ የጠየቀው ይህን አልነበረም ።
የፊልም አዘጋጁን በማስፈራራት ወይም በማታለል
አንድ ነገር እንዲፈጽም ማድረግ ይቻላል?ከፍ ያለ የግ
ንዘብ ኪሳራን ለመቋቋም ይችላል? የፊልሙን መዘግ
የት ፡ ቃላቱን ተዋናዩን የአደንዛዥ እጽ ጥገኛ መሆኑን
ማጋለጡ አያስደነግጠውም ? ለዚህ ሁሉ መልሱ አዎን
ይሆናል ። ግን የዶኑ ጥያቄ አሁንም ይህ እንዳልሆነ
ሄገን አውቋል ። ብዙ ካሰላሰለ በኋላ በመጨረሻ የዶ
ኑን ጥያቄ በአእምሮው ውስጥ ተረጎመ ። ጃክ ዎልትዝ
ለአሳማው ፡ ለክብሩ እና ለበቀል ሲል ማናቸውንም
ነገር መስዋእት ለማድረግ ወዴ አለው?

ሄገን ሁልጊዜም ባይሆን አልፎ አልፎ ከዶኑ ጋር
ይቀልዳል ። ዛሬም ሳቀና "ሲሲሊያዊ ነው ወይ
ማለትህ ነው ፡ አይደል?" ሲል ዶኑን ጠየቀው ። ዶኑ የሄ
ገንን ጮሌነት በማድነቅ ፈገግታ በተሞላበት ሁኔታ
እራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ሄገንም "አይደለም" ሲል
መለሰ ። ዶኑ መልሱ በቃው ። እስከሚቀጥለው ቀን
በጉዳዩ ላይ አሰበበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ረቡአ እለት ሄገንን ጠርቶት መመሪያ በሰጠው ጊዜ ፡ ሄገን የተቀበለው የዶኑ መመሪያ በጣም አስደ ነቀው ። በዚህ አይነት ዶኑ ጉዳዩን እንደፈጸመው ገመተ ። ዎልትዝ ዛሬ ጧት ደውሎ ጆኒ ፎንቴን ተዋና ይነቱን እንደሚያገኝ እንደሚያረጋግጥለት አልተጠራ ጠረም ።

እንዳሰበው ስልኩ ተደወለ ። የደወለው የእሬሳና የቀ ብር ዝግጅት ባለሙያ የሆነው አሜሪጎ ቦናሴራ ነበር።አሜ ሪጎ ሴት ልጁን የደበደቡበት ወጣቶች ተገቢውን ቅጣት በማግኘታቸው እጅግ ረክቶ ምስጋናውን በስልክ ባስተ ላለፈበት ወቅት ሲቃ ይዞት ነበር ። በአሜሪጎና በዶኑ መሀከል የማይሞት ወዳጅነት የተፈጠረ መሆኑንና ከእንግዲህ ህይወቱን ሳይቀር ለተከበረው ጡት አባት እንደሚሰጥ ገልጾ ምስጋናውን እንዲያስተላልፍለት ሄገንን ጠየቀው ። ሄገንም መልእክቱን እንደሚያደርስ አረጋገ ጠለት ።

"ዴይሊ ኒውስ" የተባለው ጋዜጣ በመሀል ገጹ ላይ ጀሪ ዋግነርና ኬቪን ሙናንን መንገድ ላይ ወድ ቀው ያነሳውን ፎቶግራፍ አውጥቷል ። ለማየት እጅግ የሚዘገንን ነበር ። የልጆቹ መልክ ሲታይ ሰብ አዊ ስነ ፍጥረታቸው ጠፍቶ ስጋ መስለዋል ። ጋዜጣው ስለጉዳታቸው ሲገልጽ መትረፋቸው ተአ ምር ቢሆንም ድነው ከመነሳታቸው በፊት ለወራት በሀኪም ቤት መቆየት እንደሚኖርባቸውና የፕላስቲክ ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው በዝርዝር አብራርቷል። ተልእኮው በታቀደው መሰረት በመከናወኑ ፡ ፖሊ ጋቶ የተፈለገውን ተግባር በመፈጸሙ አለቃው ከሌሜንዛ አንድ አይነት ማበረታቻ እንዲያደርግለት ሄገን መመ ሪያ ሲሰጠው ማስታወሻ ጻፈ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ሶስት ሰአት ለፈጀ ጊዜ ፡ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ፡ ማለትም ከመሬትና ከህንጻ ንግድ ፡ ከወይራ ዘይት ንግድ ፡ ከህንጻ ስራ ተቋራጭነት ስለ ተገኙት ገቢዎች ለዶኑ የሚቀርብ ዘገባ ሲያጠናቅር ቆየ ። በሁሉም አይነት ንግድ ጥሩ ውጤት ባይታይም በተለይ ጠርነቱ በማብቃቱ ይሻሻላሉ የሚል ግምት አደረበት ። ሄገን በሌሎች ስራዎች በመዋጡ የጆኒ ፎንቴንን ጉዳይ ረስቶት ሳለ አንድ የስልክ ጥሪ ከካሊ. ፎርኒያ ደረሰው ።

"ሄገን ነኝ" ሲል መለሰ

በስልኩ የሰማው ድምጽ ከፍተኛ ጥላቻ ያዘለ ነበር ።

"አንተ ምናምንቴ ዲኮላ ሶላቶ" ሲል ዎልትዝ ጮኸ ። ቀጥሎም "ለአንድ መቶ አመት ትታሰሯታላችሁ! ያለኝን ሀብት እንድ ሳንቲም ሳትቀር ከሰክሼ እበቀላችኋለሁ ። እናንተ ፋይዳ ቢስ ቅንዝረኞች ፡ ያን ጆኒ ፎንቴንን ካላስኮላሸሁት እኔ አይደለሁም" በማለት ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት ደነፋ ። ሄገን በትህትና "እኔ የጀር መንና የአየርላንድ ተወላጅ ነኝ" ሲል ዎልትዝ ጸጥ አለና ስልኩን በላዩ ላይ ዘጋው ። ዎልትዝ አንዴም እንኳን የዶን ኮርሌዎኔን ስም ጠርቶ ለመሳደብ አልደፈረም ። የዶኑ ብሩህ አእምሮ ክብሩን ታስጠብቅለታለች ።

ጃክ ዎልትዝ ከአንድ የሲኒማ ዝግጅት መገናኛ የማያንስ ስፋት ባለው መኝታ ቤቱ ውስጥ አስር ሰው ማስተኛት በሚችለው ሰፊ አልጋው ላይ ብቻውን ነው የሚተኛው ። ይህም ስለተባለ የመጀመሪያ ሚስቱ ከሞተች ወዲህ ብቻውን ቢተኛም ሴት መሄድ ትቷል ማለት አይደለም ። እድሜው ቢገፋም ጉልበቱ ጠንካራና ለሴስ ያለው ስሜቱም ሀያል ነው ። እንዲያም ሆኖ ፡ ስሜቱ የሚቀሰቀሰው ከጨቅላዎች ጋር በመዳራት ሲሆን ፡ ከነሱም ጋር ብዙ የሚያስቆይ አደብ የለውም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዛሬ ጧት በማይታወቅ ምክንያት ቀደም ብሎ ተነስቷል ። የማለዳ ብርሀን መኝታ ክፍሉን ሞጋግ አልብሶታል ። ከአልጋው ግርጌ የታየውን የፈረስ ራስ ቅርጽ ምንነት ለማጣራት በክርኑ ዳኽና የራስጊ መብራቱን አበራ ። ድንጋጤው በመላ ሰውነቱ ህመም አሰራጨበት ። በትልቅ መደሻ ደረቱን የተመታ ይመስል የልብ ትርታው እንጣጥ እንጣጥ እያለ አቅለሽለሸው ። ትውኪያው ውብ የወለል ምንጣፉን አዳረሰው ።

የተቆረጠው ጥቁር ሀር የመሰለው 'የካርቱም' ጭን ቅላት በያም ግግር ተጣብቋል ። ነጭ ቄጠማ መሰል ጅማቶቹ በግልጽ ይታያሉ ። አፍና አፍንጫው አረፋ ለብሷል ። እነዚያ ብርቱካን የሚያክሉት እንደወርቅ የሚያብረቀርቁ አይኖቹ ወይበው ፥ የበሰበሰ ፍሬ መስለው ፥ ደም ለብሰዋል ። ያ ዎልትዝ የሚወደውና የሚመካበት 'ካርቱም' ተብሎ ይጠራ የነበረው ታላቅ ፈረስ እራሱ ተቆርጦ በጌታው መኝታ ቤት እንደቀልድ ተጣለ !

ዎልትዝ ድንጋጤው ሀሊናውን አስቶት አውሬ ሆነ ። ድንጋጤው የሚሰራውን አሳጣው ። አሽከሮቹን ጠራና ጮኸ ፥ ሂገንን ጠራና ተሳደበ ። ሁኔታው ያስደነገጠው የዎልትዝ ባለሟል ልዩ ሀኪሙንና የፊልም ማእከሉን ምክትል ኃላፊ ጠራቸው ። ዎልትዝ ግን እነሱ ከመምጣታቸው በፊት ሀሊናውን ገዛ ። ሀሊናውን ቢገዛም ሁኔታው ከመጠን በላይ አስደንግጦታል ። ምን አይነት ሰው ነው ፤ ስድስት መቶ ሺህ ብርን ያህል ያወጣ ፈረስ የሚያጠፋ ? ይህን ውሳኔ ለመሰረዝ እንዳችም ድርድር ሳያቀርብ ፥ አንድም ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ይህን የመሰለ ትእዛዝ የሚያስተላልፍ ማነው ? ይህ ምህረት የሌለው ጭካኔና ከፍተኛ ግምት ለሚሰጠው ጉዳይ ደንታቢስነት ነው ። የሰውየውን ማንአህሎኝነት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያውም የራሱ ፈጣሪ ነኝ ባይነት ያሳያል ። ዎልትዝ የግል ስሜቱን ይጠብቅልኛል ብሎ የሚገምተውን አቅምና የጥበቃ ሀይል ቢያደራጅም ሰውየው ግን ከቁም ነገር አልጣፈለትም ።

የተገደለውን ፈረስ እንደተፈለገው እራሱን በመ ጥረቢያ ለመቁረጥ አስቀድመው የሆነ መርዝ ነገር አውጠውታል ። የሌሊት ተረኛ ዘበኞች ሌሊቱን ምንም አልሰማንም ባይ ናቸው ። ይህ ለዎልትዝ አልተዋጠለ ትም ። እንዲናገሩ ማድረግ ይቻላል ። ተገዝተው መሆን አለበት ። ማን እንደገዛቸው እንዲያወጡ ማድረግም ይቻላል ።

ዎልትዝ ገደብ የሌለው ራስ ወዳድ እንጂ ጅል አይደለም ። በአለም ላይ የጨበጠው ሀይል ከዶን ኮር ሌዎኔ ይበልጣል ብሎ መገመቱ ተሳስቷል ። ይህ እው ነት አለመሆኑን ለማረጋገጥ አንድ ጭብጥ ሲሻ ነበር ። መልእክቱ ደርሶታል ። የዚያ ሁሉ ሀብት ባለ ቤት ቢሆንም ፣ ከአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጋር ግንኙነት ቢኖረውም ፣ ከኤፍ ቢ አይ ዲሬክተር ጋር ወዳጅ ነኝ ብሎ ቢመካም ፣ አንድ ያልታወቀ የወይራ ዘይት አስ መጪ ሊያስገድለው ይችል ነበር ። በእርግጥ ሊያስ ገድለው ይችል ነበር ። ያውም ለጆኒ ፎንቴን የተዋናይነት ስራ ስላልሰጠው ብቻ ! ይህ ፈጽሞ የማይታመን ነው ። ሰዎች እንዲህ ያለ ድርጊት ለመፈጸም መብት የላቸውም ። ይህ እብደት ነው ። በዚህ አይነትማ አንድ ሰው በገንዘቡ ፣ በራሱ ኩባንያ ፣ ባለው ስልጣን የፈለገውን ማድረግ አይችልማ! ይህን የመሰለው ተግባር እሱ ባለበት አለም እንዲኖር ሊፈቀድለት ስለማይገባ መደምሰስ አለበት ።

ዎልትዝ ሀኪም ያዘዘለትን መድሀኒት ከወሰደ በኋላ በጥሞና ነገሮችን ማሰብ ጀምሯል ። ከሁሉም ያስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደነገጠው የዚህ ዶን ኮርሌዎኔ የተባለ ሰው ድንገተኛ በትር ስድስት መቶ ሺህ ብር የፈጀውን ፈረሱን እንደ ቀልድ ለማጥፋት መምረጡ ነው። ስድስት መቶ ሺህ ብር! ያውም እኮ ይህ ገና የበቀል መክፈቻው ነው። ዎልትዝ ተንቀጠቀጠ። ስለገነባው ህይወት ማጤን ጀመረ። ከበርቴ ነው፥ ምልክት በመስጠት እና ፊልም አሰራሻለሁ በማለት በአለም ውብ ነች ከተባለች ተዋናይ ጋር መዳራት ይችላል። የነገስታት እንግዳ ሆኖ ተቀብለውታል። ገንዘብና ህይል የሚገዛውን ህይ ወት በሙሉ ተቀዳጅቷል። እነዚህን ሁሉ በአጉል ፍላጎት ሊያበላሻቸው አይገባም። ኮርሌዎኔን በህግ ሊጠ ይቀው ቢችልስ የውድድር ፈረስ ማስገደል ቅጣት ምን ይሆን? ብቻውን የድንጋጤ ሳቅ ሲስቅ ሀኪሙና ባለሚሎቹ ተደናገጡ።

ሴላ አሳብ አእምሮው ውስጥ መጣ። ይህን ወሬ የካሊፎርኒያ ህዝብ ቢሰማ፥ አንድ የዎልትዝን ህያ ልነት የጠላ ሰው በንቀት ይህን ድርጊት የፈጸመበት መሆኑ ዎልትዝን መሳቂያና መዘባበቻ ያደርገዋል። ዎልትዝ ውሳኔ ላይ ደረሰ። እነዚህ ሰዎች ምናልባት አይገድሉት ይሆናልኮ። የሚበቀሉት ከመግደል በላይ ባለ በቀል፥ ስሜቱን በማቁሰል ሳይሆን አይቀርም። ለፈረሱ መሞት ምክንያት የሆነው ከእንግሊዝ አገር በመርከብ ሲጓጓዝ በተለከፈበት በሽታ መሆኑ ለህዝብ መግናኛዎች ተገለጸ። ይህን ጉዳይ የሚያውቁ ሰራ ተኞች በሙሉ እውነተኛውን ምክንያት በምስጢር እንዲጠብቁ አስማላቸው። የፈረሱ እሬሳም ሰዋራ ቦታ እንዲቀበር አዘዘ።

ከስድስት ሰአት በኋላ ጆኒ ፎንቴን በሚቀጥለው ሰኞ ስቱዲዮ ተገኝቶ የፊልም ተዋናይነቱን ስራ እን ዲጀምር ከፊልሙ ዋና አዘጋጅ የስልክ ጥሪ ደረሰው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን በዚያን እለት ምሽት ከቨርጂል ሶሎዞ ጋር በሚ ደረገው ስብሰባ ላይ ዶኑ እንዲዘጋጅበት ሊያነጋግረው ወደ ዶኑ ቤት ሄደ ። ዶኑ የበህር ልጁ ሶኒ ኮርሌ ዮኔ እንዲገኝ አስጠራው ። ሶኒ በድካም ስሜት የተነሳ ውሀ በብርጭቆ ቀስ እያለ ፉት ሲል ሄገን አይቶት አንድ ስጋት አደረበት ። ምናልባት ሶኒ ያቺን የእሀ ቱን ሚዜ እያሰላሰለ ይሆን?

ዶኑ ሄገን ካስቀመጠለት የሲጋር ቆርቆሮ ዲ ኖቢሊ የተሰኘውን ሲጋር አንስቶ እያጤሰ በምቹ ወንበር ላይ ተዝናንቷል ። እንደ ሄገን ፍላጎት ቢሆን ኖሮ ሃቫና ሲጋር ቢያጤስ ይመርጥ ነበር ። ዶኑ ጉረሮዉን ይከረ ከረኛል በማለት ዘወትር 'ዲ ኖቢሊ' ማጤስ ይመርጣል ።

"ማወቅ የሚገባንን ነገሮች ሁሉ ተረድተናል?" ሲል ጠየቀ ።

ሄገን ማስታወሻዎቹን ያሰቀመጠበትን ማህደር ከፍቶ ሶሎዞን በሚመለከት ሴላ ሰው ቢያነበው ሊገ ባው የማይችለውን ፣ ለራሳቸው ደህንነት የሚያስፈል ገውን ሚስጢራዊ ማስታወሻዎች ካገላበጠ በኋላ ፤

"ሶሎዞ የሚመጣው እንድንረዳው ፈልጎ ነው ። ለሚያቀርበው የንግድ ስራ የኛ ቤተሰብ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ብር በማዋጣት እና የህግ ከለላም በማስገ ኘት እንዲያግዘው ይፈልጋል ። ለዚህ ተሳትፎአችን መጠኑ ገና የማይታወቅ ጥቅም እናገኛለን ። ለሶሎዞ የታታሊያ ቤተሰብ ይዋሰዋል ። እነሱም ድርሻ ይኖራ ቸው ይሆናል ። የምንሳተፍበት ንግድ አደንዛዥ እጽ ይሆናል ። ሶሎዞ እጹን ከሚበቅልበት ከቱርክ አገር ለማስመጣት ተዋውሏል ። ከዚያ ያለችግር ወደ ሲሲሊ ያስመጣዋል ። እጹን በሄሮይን መልክ የሚቀምም ማምረ ቻም አደራጅቷል ። ወደ ሞርፊንነት የሚያለሰልስ ወይም ወደ ሄሮይን መልሶ የሚያጠነክር መሳሪያም አዘጋጅቷል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በስፍራው አስፈላጊው ጥበቃ ስላለ ችግር የለም ። ችግሩ እዚህ አገር ለማድረስ ያለው ሁኔታ ነው ። እሱም ብቻ ሳይሆን ስራውን በዚህ አገር ለማስፋፋት መንሻ ካፒታል ያስፈልገዋል ። አንድ ሚሊዮን ብር ካሽ ዛፍ ላይ አይበቅልም" ሲል ዶኑን አስረዳው ። የማይመስለው ንግድ ውስጥ መሳተፍ የሚጠላው ዶን ትከሻውን ነቀነቀ ።

ሄገን ፈጠን ብሎ ንግግሩን ቀጠለ ፥ "ሶሎዞን በሁለት ምክንያት ሶሎዞ ቱርክ ብለው ይጠሩታል ። ለረዥም ጊዜ ቱርክ አገር ሚስት አግብቶ ልጆች ወልዶ በዚያ ኖሯል ። አሁን እንጃ እንጂ ቀድሞ በስራም ሆነ በእንዳንድ ከርከር ላይ ጩቤውን መምዘዝ ይወዳል ። በቂ ችሎታ ያለው የራሱ አዛዥ የሆነ ሰው ነው ። የፖሊስ ሪኮርድ አለበት ። አንዴ በኢጣልያ ፥ አንዴ በአሜሪካ ፥ በድምሩ ሁለት ጊዜ ታስሯል ። የአሜሪካ ባለስልጣኖችም የአደንዛዥ እጽ ነጋዴ እንደሆነ በግልጽ ያውቁታል ። ስለዚህ ቢያዝ እኔ አይደለሁም ለማለት እንደማይችል ያውቀዋል ። በዚህ ላይ አሜሪካዊት ሚስት አግብቶ ሶስት ልጆች ወልዷል ። ቤተሰቡን ያፈቅራል ። ስለዚህ ምናልባት ቢያዝ ቤተሰቡ ገንዘብ እንደማይቸገር ካወቀ ማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ለመጥለቅ ወደ ኋላ አይልም"

ዶኑ ወደ ልጁ ዞሮ ፤

"ሶኒ ፥ ምን ይመስልሀል ?" ሲል ጠየቀው ።

ሄገን ሶኒ ምን እንደሚመልስ ያውቃል ። በዶኑ መዳፍ ስር መሆኑ ትእግስት የነሳው ሶኒ በራሱ ሀላፊነት የሚመራ ይህን የመሰለ ንግድ ይፈልጋል ። ዊስኪውን በረዥሙ ተጐነጨና ፥

"በዚያ በነጭ ዱቄት ላይ ብዙ ገንዘብ አለበት ። እርግጥ ጦሱ አደገኛ ነው ። ጥቂት ሰዎችን ለሀያ አመታት ሊያሳስራቸው ይችላል ። እንደሚመስለኝ በስራው ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳንገባበት ገንዘብ በማዋጣትና ከህግ ከለላ በመስጠት ብቻ ብንወሰን መጥፎ አይደለም" አለ ።

"ቶም ያንተስ ሀሳብ ምንድነው?" ሲል ዶኑ ሄገ ንንም ጠየቀው ።

ሄገንም ከዶኑ ሁኔታ እንደተረዳው በጉዳዩ እንደ ማይስማማ ገመተ ። እውነቱን ለመናገር ግን ተዘጋጀ ። ሄገን ቀድሞ ካጤነው ሁኔታ የተረዳው ዶኑ ካለው ሰፊ አመለካከት ሁሉ በአደንዛዥ እጽ ጉዳይ የመጣ አርቆ ማስተዋል አለመቻሉን ነው ።

"በል እንጂ ቶም" አለው ዶኑ በማበረታታት "ሲሲሊያዊ አማካሪም እኮ ሁልጊዜ ባለቃው ሀሳብ አይስማማም ።"

"እሺ ማለት የሚገባህ መሰለኝ ። ይህን ለማለት የሚያስችሉ ብዙ ምክንያቶች አሉ ። ከማናቸውም ንግድ የበለጠ ብዙ ትርፍ ከአደንዛዥ እጽ ንግድ ይገኛል ። እኛ 'አንገባም' ብንል ሌሎች የታታሊያን ቤተሰብ የመሰሉ ይገቡበታል ። እነሱ በዚህ ተግባር ውስጥ ገቡ ማለት ብዙ ትርፍ አገኙ ማለት ነው ። ብዙ ትርፍ አገኙ ማለትም ብዙ የፖለቲካ ስልጣን ሊገዙ ይችላሉ ማለት ይሆናል ። በዚህ ሁኔታ የነሱ ቤተሰብ ከኛ ቤተ ሰብ የበለጠ ሀይለኛ መሆኑ አይቀርም ። በመጨረሻ የእኛንም ለመውሰድ ወደኛ መምጣታቸው የማይቀር ነው ። ይህ ሁኔታ ልክ እንደሀገሮች ነው ። እነሱ ሲታ ጠቁ እኛም መታጠቅ አለብን ። በአሁኑ ወቅት ቁማርና የሙያ ማህበራት በኛ ትእዛዝ ስር መሆናቸው በጣም ጥሩ ነው ። ነገር ግን የአደንዛዥ እጽ ንግድ የወቅቱ ታዳጊ ንግድ መሆኑን መዘንጋት የለብንም ። ከዚህ ሲሳይ መቋደስ ካልቻልን ምናልባት አሁን ባይሆን እንኳን በአስር አመታት ጊዜ ውስጥ ያለንን ስራ ሁሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለአደጋ እናጋልጠዋለን" ሲል ሄገን የተቻለውን ያህል ዶኑን ለማግባባት ሞከረ ።

ዶኑ በንግግሩ ተመሰጠ ። በተለይም የቤተሰቡ ንግድ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ በማመን ፣

"ዋናው ነገር ይህ ያልከው ጉዳይ ነው" ሲል ዶኑ ካረጋገጠ በኋላ ከመቀመጫው ተነስቶ ፣

"ያንን አረመኔ ነገ በስንት ሰአት ነው የማነጋግረው?" ሲል ሄገንን ጠየቀው ።

ሄገንም ሶሎዞ በአራት ሰአት እንደሚመጣ ነገረው ።

"ሁለታችሁ እዚሁ ከኔ ጋር እንድትገኙ እፈልጋለሁ" አለ ዶኑ ተነስቶ ተንጠራራና ። ወደ ሶኒ ዞር ብሎም እጁን ያዘውና ፣

"ሳንቲኖ ፣ ሂድና ዛሬ ሌሊት በሚገባ ተኛ ። ሰይጣንን እራሱን ትመስላለህ ። እራስህን ጠብቅ ። ወጣት የምትሆነው ለዘለአለም አይደለም" አለው ።

ሶኒ ያባቱ ለሱ ማሰብ ስላበረታታው ሄገን ሊጠይቀው ያልደፈረውን ጥያቄ ፣

"አባዬ ፣ መልስህ ምን ይሆናል?" ሲል ጠየቀው ።

ዶኑ ፈገግ ብሎ "የድርሻየን መጠንና ሌሎቹንም ዝርዝሮች ሳልሰማ ምን እንደምል እንዴት አውቃለሁ? ዛሬ ማምሻየን ያላችሁኝን ሳሰላስል ልደር ። እንደምታውቁት ነገሮችን በችኮላ መፈጸም አልወድም" አለና መለሰለት ። ሊወጣ ሲል ወደ ሄገን ዞር አለና ፣

"ለመሆኑ ዛሬ የታታሊያ ቤተሰብ እንደሚያደርገው ሁሉ ያ ቱርክ ከጦርነቱ በፊት በሽርሙጥና ገቢ ይተዳደር እንደነበር በማስታወሻህ ላይ መዝግበህል? ሳትረሳ መዝግበው" ብሎ የፈዝ ሳቅ ሲስቅ ሄገን በሀፍረት ፊቱ ቀላ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ይህን ጉዳይ አጥቶት አይደለም ። ነገር ግን በገመት ጉዳዮች ላይ ጽኑ ተቃውሞ ያለው ዶን ይህን ከተረዳ ሶሎዞ ለሚያቀርበው ማናቸውም ድርድር መልሱ እምቢታ ይሆናል የሚል ፍራቻ ስላደረበት ነበር ።

ቱርክ እየተባለ የሚጠራው ጉልበታሙና ቁመቱ መሀከለኛ የሆነው ቨርጂል ሶሎዞ ከጠይም መልኩ ጋር እውነተኛ ቱርክ ይመስላል ። ሰይፍ የመሰለ አፍንጫ ፡ ጨካኝ ጥቁር አይኖችና ማራኪ ግርማ ሞገስ አለው ።

ሲገባ ከበሩ ላይ ሶኒ ኮርሌዎኔ ተቀብሎት ዶኑና ሄገን ከሚጠብቁበት ክፍል አደረሰው ። ሄገን ሲያየው 'ከሉካ ብራሲ በስተቀር ይህን ሰው የመሰለ አደገኛ ፍጡር አይኖርም' ሲል አሰበ ።

ሁሉም በትህትና ተጨባበጡ ። ሄገን አሁንም ሌላ አሳብ በልቡ መጣ ። 'ይህ ሰው ወኔ አለው ወይ?' ብሎ ዶኑ ቢጠይቀው ያለማመላወል ፡ 'አዎን' ብሎ እንደ ሚመልስለት ገመተ ። የሶሎዞን የመሰለ አስፈሪነት ዶኑ ላይ እንኳን አላየም ። በእርግጥም ዶኑ ዛሬ ከሶሎዞ ጋር ሲነጻጸር ተራ መሰለ ። ሰላምታ አሰጣጡም የገጠሬ ይመስላል ። በጠቅላላው ቆሌው ርቆት ነበር ።

ሶሎዞ ጊዜ ሳይፈጅ ወደ ጉዳዩ ገባ ። የንግዱ አይ ነት ሁሉም ነገር የተቀነባበረለት የአደንዛዥ እጽ ንግድ ነው ። በቱርክ የአደንዛዥ እጽ እርሻ ባለቤቶች የተወ ሰነ መጠን በአመት ሊያቀርቡለት ቃል ገብተዋል ። ሶሎዞ ይህንኑ እጽ በፈረንሳይ ወደ ሞርፊንና በሲሲሊ ወደ ሄሮይን የሚለውጡ ፍጹም ከለላ የተሰጣቸው ማምረቻ ዎች ከፍቷል ። ይህን እጽ ወደ ፈረንሳይም ሆነ ወደ ሲሲሊ ለማስገባት ምንም ችግር የለም ። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሲገባ ግን ሁለቱም እንደሚያውቁት ኤፍ ቢ አይን በአደንዛዥ እጽ የመጣ በጉቦ ለመሸንገል ስለማይ ቻል የተወሰነ ያህሉን (አምስት በመቶ) ማጣት ሊያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስከትል ይችላል ። ሶሎዞ ይህን ሁሉ ግግባቢያ ከነገረው በኋላ ፥ "ያም ሆኖ ትርፉ እጅግ ብዙ ፥ አደጋው ግን ፈጽሞ የሌለ ነው" ሲል ዶኑ እንዲገባበት አደፋፈረው ።

ዶኑ "ታዲያ እንዲህ ከሆነ ለምን እኔ ዘንድ መጣህ? ይህን ለጋስነትህን እንድቀዳጅስ እንዴት መረጥከኝ" በማለት በትህትና ጠየቀው ።

"ሁለት ሚሊዮን ብር በእጄ እፈልጋለሁ ። በዚህ ላይ ሀይል ያላቸው ባለስልጣናት ወዳጅ የሆነ ሰው ያስፈልገኛል ። ጥቂት መልእክተኞቼ መያዛቸው አይቀርም ። ነገር ግን ሪኮርድ የሌለባቸው እንደሚሆኑ ቃል እገባለሁ ። እንዲህ ያሉት ቢከሰሱም ቀለል ያለ ፍርድ ነው የሚሰጣቸው ። ሰዎቹ እጹን ይዘው ቢያዙ ዳኛው ከእንድ ቢበዛም ከሁለት አመት የበለጠ እስራት እንዳይ ፈርድባቸው የሚያደርግ ወዳጅ ያስፈልገኛል ። እንዲህ ከሆነ እነሱም አይለፈልፉም ። ነገር ግን አስር ወይም ሀያ አመት ከተፈረደባቸው አንዳንድ ደካሞች አይጠፉምና ፥ ሚስጥሩን አውጥተው ትላልቅ ሰዎችንም አጉል ያደርጋሉ ። ስለዚህ ከህግ ከለላ አስፈላጊ ነው ። ዶን ኮርሌዎኔ ፥ ብዙ ዳኞችን በጅህ ያደረግህ መሆንህን እሰማለሁ" ሲል ሶሎዞ ተናገረ ።

ዶን ኮርሌዎኔ ስለ ሙገሳው ምንም መልስ ለመስጠት ሳይፈልግ ፤

"ምን ያህል መቶኛ ነው ለቤተሰቤ የሚደርሰው ?" ሲል ጠየቀው ። ሶሎዞ አይኑ በራ ።

"ሀምሳ በመቶ !" ካለ በኋላ በሚያባብል ድምጽ "በመጀመሪያው አመት ድርሻህ ሶስት ወይም አራት ሚሊዮን ብር ይሆናል ። ከዚያም በኋላ እየጨመረ ይሄዳል" ሲል መለሰለት ።

ዶኑ "የታታሊያ ቤተሰብ ድርሻስ ስንት መቶኛ ይሆናል ?" በማለት ጠየቀው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጀመሪያ ጊዜ ሶሎዞ የደነገጠ መሰለ ። "እነሱ ከኔ ድርሻ ይካፈላሉ ። በእለት ተእለት ስራው ላይ እርዳታ እሻለሁ" ሲል መለሰለት ።

"እንግዲህ እኔ ገንዘብ በማዋጣቴና ከህግ ከለላ ስለማሰጥህ ብቻ ሀምሳ በመቶ አገኛለሁ ። በኔ በኩል ስለ እለት ተእለት ስራው ምንም ስጋት አይኖርብኝም ነው የምትለኝ?" አለ ዶኑ ። ሶሎዞ በአዎንታ እራሱን ነቀነቀ ።

"ተቀብዬ ላነጋግርህ የተሰማማሁት ለታታሊያ ቤተሰብ ያለኝን ክብር ለመግለጽ ነው ። አንተም ብትሆን በአክብሮት መስተናገድ የሚገባህ ቁምነገረኛ ሰው ነህ ሲሉ ሰምቻለሁ ። መልሴ እምቢታ ቢሆንም ምክንያቴን እነግርሀለሁ ። አንተ የምታካሂደው ንግድ ትርፉ ብዙ መዘዙም ያንኑ ያህል ብዙ ነው ። ባንተ ስራ ላይ ብካፈል ሌሎቹ ስራዎቼ ሁሉ አደጋ ላይ ይወድቃሉ ። እንዳልከው በፖለቲካው ውስጥ ብዙ ወዳጆች አሉኝ ። እነዚህ ወዳጆቼ አሁን በማካሂደው የቁማር ስራ ምትክ አደንዛዥ እጽን ብነግድ ወዳጅነታቸው ያበቃል ። በነሱ ግምት ቁማር እንደመጠጥ አደገኛ ያልሆነ ጥፋት ነው ። አደንዛዥ እጽ ግን ቁሻሻ ንግድ ነው ይላሉ ። በበኩሌ ሌላ ሰው ስለሚሰራው ንግድ አያገባኝም ። እኔ የምልህ ግን ይህ አንተ የተሰማራህበት ስራ እጅግ አደገኛ ነው ። መላው ቤተሰቤ ላለፉት አስር አመታት ያለምንም አደጋ ፣ ያላንዳች ጉዳት በደህና ኖሯል ። ስለሆነም ለትርፍ ተስገብግቤ ደህና ህይወታቸውን አላበላሸውም" በማለት ዶኑ አቋሙን ለሶሎዞ ገለጸለት ።

ሶሎዞ የዶኑን አቋም ከሰማ በኋላ ምናልባት ሌሎች ይደግፉት እንደሆን አይኑን አማተረና ፣ "ስለ ሁለት ሚሊዮን ብርህ ነው የሰጋኸው?" ሲል ዶኑን ጠየቀው ። "አይደለም" አለ ዶኑ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"የታታሊያ ቤተሰብ ለገንዘብህ ዋስትና ይሰጥሀል" አለ ሶሎዞ ። ይህን ጊዜ ሶኒ ኮርሌዎኔ በስነ ስርአትም ሆነ በአመዛዘን ይቅርታ የማይደረግለትን ስህተት ፈጸመ ።

"የታታሊያ ቤተሰብ አንዳችም መቶኛ ከኛ ሳይ ጠይቅ ገንዘባችንን ይመልስልናል" ሲል ሶሎዞን ጠየቀው ። ሄገን በሶኒ ጣልቃ ገብነት በጣም ደነገጠ። ዶኑ ልጁን በክፉ አይን ሲገላምጠው ልጁም ጥፋቱን ሳይረዳ ሲደነግጥ ተመለከተ ። ሶሎዞ ግን በሁኔታው በመርካት አይኑ በራ ። በዶኑ ድፍን ምሽግ ውስጥ ጭላንጭል ታየው ። ዶኑ ጉዳዩ ማብቃቱን በሚገልጽ ድምጽ ፡

"ወጣቶች ስግብግቦች ናቸው ። ዛሬ ደግሞ ስነ ስርአትም የላቸው ። ጣልቃ እየገቡ ታላላቆቻቸውን ያደናቅፋሉ ። ልጆቼን በጣም ስለምወድ እንደምታየው አበላሽቻቸዋለሁ ። ሚስተር ሶሎዞ ፡ እምቢታዬ የመጨረሻ ነው ። ከኔ ስራ ጋር በምንም የማይሻማ ስለሆነ በተሰማራህበት ስራ መልካም እድል እመኝልሀለሁ ። ባለመስማማቴ ግን አዝናለሁ" አለው ።

ሶሎዞ ተሰናብቶ ሲወጣ ፊቱ ላይ ምንም አይነት ስሜት አይታይም ነበር ።

ሄገን ሽኝቶት ሲመለስ "ስለ ሰውየው ምን ተሰማህ?" ሲል ዶኑ ጠየቀው ።

"ሲሲሊያዊ ነው" ሲል ሄገን ፈርጥሞ መለሰ ። ዶኑ ወደ ሶኒ ዞር ብሎ ፤

"ሳንቲኖ ፡ ከቤተሰባችን ውጭ የሆነ ሰው የምታስበውን እንዲያውቅብህ አታድርግ ። እንደ መሰለኝ በዚያች በምትዳራት ወጣት ልጃገረድ ምክንያት አእምሮህ ጨርቅ ሆኗል ። እሷ ትብቃህና ስለ ስራ አስብ ፡ አሁን ጥፋ ከፊቴ !" ሲል ገሰጸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶኑ ልጁ ክፍሉን ለቆ እስኪወጣ ጠበቀና መቀመጫው ላይ ተደላድሎ መጠጥ አዘዘ። ቶም ሄገንም አኒሴት ቀዳለት። ዶኑም ወደ ሄገን ቀና ብሎ "ሉካ ብራሲን ላክልኝ" አለው።

ከሶስት ወር በኋላ ሄገን ለገና በአል የሚሆኑ ስጦታዎችን ለቤተሰቡ ለመግዛት በቂ ጊዜ ማግኘት እንዲችል በቢሮ ስራው ላይ ይጣደፍ በነበረበት ወቅት የጆኒ ፎንቴን የስልክ ጥሪ አቋርጠው። በተዋናይነት የተካፈለበት ያ ፊልም ተነስቶ ፎንቴን ሞራሉ ሁሉ ከፍ ብሏል። ለክርስትና አባቱ ልብ የሚያጠፋ የገና ስጦታ መላኩን ተናገረ። ስጦታውን እራሱ ይዞ እንዳ ይመጣ የፊልሙን ስራ ለማጠናቀቅ ወደ ባህር ጠረፍ ስለሚጓዝ አለመቻሉን ለሄገን አስረዳው። የጆኒ ፎንቴን ተወዳጅነት ለሄገን አይዋጥለትም።

ከአስር ደቂቃ በኋላም ኮኒ ኮርሌዎኔ በስልክ ልታነጋግረው እንደምትፈልግ የሄገን ጸሀፊ ነገረችው። ኮኒ ከባሏ ጋር እየተጣላች አዋኪ መሆኗን ስለሚያውቅ ፥ ሄገን በረሸሙ ተነፈሰ። ኮኒ ከባሏ ጋር ትጣላና እያኮረፈች ለሁለት ሶስት ቀናት እናቷ ዘንድ ትከርማለች። ባሏ ካርሎ ሪዚም ለመተዳደሪያ የተሰጣቸውን መጠነኛ የንግድ ስራ ድቤ እያስጋጣት ነው። ይጠጣል ፥ አለሌነቱ ገደብ አጥቷል፤ ይቆምራል። ይህም አልበቃ ብሎት አልፎ አልፎ ሚስቱን ይደበድባታል። ኮኒ ይህን ሁሉ በደል ከወላጆችዋ ደብቃ ለሄገን ብቻ ትነግረው ነበር። ዛሬ ደግሞ ምን አዲስ ጣጣ ልታወራ ይሆን? በማለት አሰበ። ነገር ግን የዛሬው የኮኒ አመጣጥ ለአቤቱታ ሳይሆን ለአባቷና፤ ለወንድሞችዋ በምታቀርበው የገና ስጦታ ምርጫ ሄገንን ለማማከር ነበር።

ስልኩ አሁንም ጭርር ሲል ሄገን ተበሳጭቶ ወረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀቶቹን ሰብስቦ ወደ ትሪው መለሰና ከገና በአል መልስ ሊሰራ ወሰን ። የስልኩን ጥሪ ግን አለመመለሱ አልታ ሰበውም ። ስልኩን የደወለው ሚካኤል ኮርሌዮኔ መሆኑን ጸሀፊው ስትነግረው ጥሪውን በደስታ ተቀበለው ። ግይክን ከድሮ ጀምሮ ይወደዋል ።

"ቶም" አለው ሚካኤል ፥ "ነገ ከኬይ ጋር ከተማ እመጣለሁ ። ሽግግሌውን ከገና በፊት ልነግረው የም ፈልገው ጉዳይ አለኝ ። ነገ ማታ ቤት ይኖራል ?"

"በእርግጥ ይኖራል ። ከገና በፊት የትም አይ ሄድም ። የማደርግልህ ነገር አለ ?"

ሚካኤል እንደ አባቱ ዝግ ነው ። "አይ ፥ ምንም ነገር የለም ። ለገና እንገናኛለን ። ሁሉም ሰው ገናን በሉ ንግ ቢች ነው የሚያሳልፈው ፥ አይደል?" ብሎ ከጠየቀው በኋላ ሲሰናበተው ፥ ሄገን ጥቂት ስላላዋራው ተገረመ ።

ሄገን ቤቱ ዘግይቶ እንደሚደርስ እና እራት ብጤ እንዲዘጋጅለት ለሚስቱ ደውላ እንድትነግራት ጸሀፊ ውን ነገራት ። ህንጻውን ለቆ እንደወጣ 'መይሲዝ' ወደ ተባለው ትልቅ ሱቅ አቅጣጫ መንገዱን እቃንቶ እየፈጠነ ሲራመድ አንድ ሰው ወደ መንገድ ገባ ። ሶሎዞ መሆኑን ሲያይ ደነገጠ ።

ሶሎዞ ክንዱን ያዘውና "አይዞህ አትፍራ ፥ ላነጋግ ርህ ብቻ ነው" አለው ። ወዲያውኑ ከመንገድ ጠርዝ ላይ የቆመች መኪና በሮች ተከፈቱ ። "ግባ ፥ ላነጋግ ርህ እፈልጋለሁ" አለው ። ሄገን እጁን አስለቀቀና በፍ ርሀት ሳይሆን በንዴት ፥

"ጊዜ የለኝም!" አለው ። ይህን ሲል ሁለት ሰዎች ከኋላው መጡ ። ሄገን እግሩ ተንቀጠቀጠ ።

"ግባ ። ልገድልህ ብፈልግ ኖሮ ይኸኔ ሞተህ ነበር" አለው ሶሎዞ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄነን ሶሎዞን አምና ሳይሆን ተገደ መኪናው ውስጥ ገባ ።

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ሄነንን ዋሽቶታል ። ያኔ በደወለበት ወቅት እዚያው ኒውዮርክ ከተማ ሄነን ካለበት ህንጻ አስር መንገዶች ያህል ብቻ አቋርጦ ከሚገኝ ሆቴል ነበር ። ስልኩን ከደወለለት በኋላ ሲዘጋው ኬይ ሲጋራዋን እየኮሰተረች ፥ "ምን ያለህ ዋሾ ነህ" አለችው ። ሚካኤልም ከጐኗ ቁጭ ብሎ ፥

"ሁሉን ላንቺ ብዬ ነው ፍቅሬ ፥ ከተማ መጥቻለሁ ብዬ ብነግራቸው ዛሬውኑ ወደነሱ ዘንድ መሄድ ይኖርብናል ። ከዚያ በኋላ ለእራት ወይም ቲያትር ለማየት መውጣት አንችልም ። አብረንም ልናድር አንችልም ። እስካልተጋባን ድረስ በአባቴ ቤት አብረን መተኛት እንከለከላለን" ብሎ አቅፎ ከንፈሯን ሳማት ። በዝግታ ወደ አልጋው ጋደም ሲያደርጋት አይኗን ጨፍና የሚሰጣትን ደስታ ተጠባበቀች ። ሚካኤል በፓስፊክ ጦርነት ላይ በወታደርነት ሲያገለግል በሀሳቡ ይመኛት የነበረችውን ኬይ አዳምስን የመሰለች ቆንጆ ፥ ስሜትን የምትነዝር ፥ እንደ ወተት የነጣ ቆዳ ያላት ወጣት በእውን በማግኘቱ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶታል። አይኗን ከፍታ ቁልቁል ስባ ሳመችው ። የእራት ሰአት እስኪደርስም ፍቅር ሲለዋወጡ ቆዩ ።

እራታቸውን በልተው ካበቁ በኋላ ፥ ብዙ ሰው በሞላባቸው በመብራት ባሸበረቁ ሱቆች በኩል ወደ ቲያትር ቤት ሲያመሩ ሚካኤል ፥

"ለገና ምን ልግዛልሽ?" ሲል ኬይን ጠየቃት ።

ጥብቅ እያለችበት ፥ "አንተን ካገኘሁ ይበቃኛል" አለችው ። "አባትህ ከልቡ ይቀበለኝ ይመስልሀል?"

ሚካኤልም ጨዋነት በተሞላው አነጋገር ፥ "ያ አይደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለም ጥያቄው ። ያንቺ ወላጆች እኔን ይቀበሉኛል ወይ?''

ኬይ ትከሻዋን ነቀነቀችና ''ቢስማሙ ባይስማሙ ግድ የለኝም'' አለች ።

''እኔማ ስሜንም በህግ ላስለውጥ የሚል አሳብ ነበረኝ ። ነገር ግን ሳስብበት ፥ አንድ ነገር ቢደርስብኝ ጠቃሚ ሊሆን አይችልም ። አንቺ በእርግጥ የኮርሌዎኔ ቤተ ሰብ አባል መሆን ትፈልጊያለሽ?'' አላት በከፊል ቀልድ ።

''አዎን'' አለች ኑምጨጭ ብላ ። እርስ በርሳቸው ተጨማመቁ ። በገና ሰሞን ሁለት ጓደኞቻቸው ብቻ በእማኝነት በሚገኙበት በማዘጋጃ ቤት ጋብቻ ሊፈጽሙ ተስማምተዋል ። ነገር ግን ሚካኤል ለአባቱ መንገር እንዳለበት አጥብቆ ይነግራታል ። አባትየው በድብቅ እስካልተፈጸመ ድረስ በጭራሽ እንደማይቃወም አስረድቶታል ። ኬይ ተጠራጠረች ። በሷ በኩል ለወላጆችዋ የምትነግረው ጋብቻው ከተፈጸመ በኋላ እንደሆነ ስትገልጽለት ፥

''ያረገዝኩ ነው የሚመስላቸው መቸስ'' አለች ።

ሚካኤልም ፈገግ ብሎ ፥ ''የኔም ወላጆች'' አላት ። ጉዳዩ ሚካኤልን ከወላጆቹ የሚያራርቅ ነው ። ሁለቱም እንደተረዱት እስካሁንም ሚካኤል ከወላጆቹ በመጠኑም ቢሆን ተራርቋል ። ሁለቱም አጥፊነታቸው ተሰምቷቸው ቅር ብሏቸዋል ። በእቅዳቸው መሰረት የኮሌጅ ትምህርታቸውን እስኪጨርሱ በሳምንት መጨረሻ እና በዝግ ወቅት ብቻ አብረው ይሆናሉ ። ይህም የሚያስደስት ኑሮ መስሎ ተሰምቷቸዋል ።

በቲያትር ቤቱ ባዩት ትርኢት ተደስተው ወደ ሆቴላቸው ሲመለሱ ምግብ ትፈልግ እንደሆነ ጠየቃት ። እራሷን ነቅንቃ ፍላጎቷ ሌላ መሆኑን ስትነግረው የእሱም ስሜት ተቀሰቀሰና በዚያ ቀዝቃዛ መንገድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ሳማት ። ትንሽ ራብ ስላለው ሳንድዊች መሳይ መኝታ ክፍላቸው ድረስ እንዲመጣለት ለማዘዝ ወሰነ።

ሆቴላቸው መተላለፊያ ውስጥ እንዳሉ ፣

"እኔ የክፍላችንን ቁልፍ እስካመጣ አንቺ ጋዜጣ አምጪልኝ" አላት ።

ጦርነቱ ቢያበቃም አሁንም በየቦታው አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች የሰራተኞች እጥረት አለባቸው ። ሆቴሉን የተከራዩ ሰዎችም ቁልፍ ለማግኘት ትንሽ መሰለፍ ይኖርባቸዋል ። ሚካኤል ቁልፉን ካገኘ በኋላ የት እንዳለች በአይኑ ሲያማትር ጋዜጣውን ትመለከታለች ። ወደ እሷ ሲሄድ አይኗ እምባ አዝሎ ቀና ብላ አየችው ።

"ጉድ ነው! ማይክ ፣ ጉድ ነው !" አለች ። ሚካኤል ጋዜጣውን ከእጅዋ ወሰደው ። በመጀመሪያ የተመለከተው ፎቶግራፍ አባቱ ዶን ኮርሌዎኔ መንገድ ላይ ወድቆ በደም ርሶ ልጁ ፍሬዲም ካጠገቡ ተቀምጦ ሲያለቅስ የሚያሳይ ነበር ። ሚካኤል ኮርሌዎኔ ሰውነቱን ቅዝቅዝ አለው ። ሀዘንም ፣ ፍርሀትም ሳይሆን ቀዝቃዛ ቁጣ ተሰማው ። ኬይን "ወደ ክፍልሽ ሂጂ "አላትና ደግፎ ሊያስገባት ። ሚካኤል እክፍላቸው ቁጭ ብሎ ጋዜጣውን ገለጠና የዜናውን ርእሰ ጉዳይ አነበበ ።

"ቪቶ ኮርሌዎኔ ተተኮሰበት ። በህገወጥ ንግድ መሪነት የሚታማው ሰው በጸና ቆሰለ ። በከፍተኛ የፖሊስ ጥበቃ ሆኖ ቀዶ ጥገና ተደረገለት ። ብዙ ደም የሚፈስበት ብጥብጥ እንደሚነሳ ይፈራል ....." ይላል ።

ሚካኤል እግሩ እየተንቀጠቀጠ ፣

"አልሞተም ፣ እነዚያ ዲቃሎች ~ አልገደሉትም" አላት ። ጋዜጣው ላይ ያለውን ጽሁፍ ደግሞ አነበበው ። አባቱ ተተኩሶበት ወደሞት በተቃረበበት ወቅት

t.me/OLDBOOKSPDF

ኬይ አዳምስና ሚካኤል ተኝተው ይዳሩ ፥ እራታቸውን ይበሉና ፥ ቲያትር ያዩ የነበረበት ወቅት ነበር ። ሚካኤልን የሀሊና ጸጸት ተሰማው ። ኬይ አዳምስም "ወደ ሀኪም ቤት አሁኑኑ እንሂድ?" ብላ ጠየቀችው ።

"በመጀመሪያ ቤት ልደውል ። አባቴ በመትረፉ ሊገድሉት ያሰቡት ሰዎች በአሁኑ ወቅት እብድ ውሾች ናቸው ። ተስፋ በመቁረጥና በመያዳገጥ የሚያደርጉት አይታወቅም ። ቀጥለው ምን እንደሚያደርጉ አይታወቅም" አላት ። ሚካኤል ወደ ቤት ስልክ ሲደውል ሁለቱም ስልኮች ተይዘዋል ። ለሀያ ደቂቃ ደጋግሞ ከደወለ በኋላ ሶኒን በስልኩ ላይ አገኘው ።

"አቤት" አለው ሶኒ ።

"ሶኒ ፥ እኔ ነኝ" አለ ሚካኤል ።

ሶኒ በእፎይታ ተነፈሰና ፥

"አንተ ልጅ ስጋት ላይ ጣልከን እኮ ። ለመሆኑ የት ነው ያለኸው? እዚያች ገጠር ከተማችሁ ሰዎች ልኬ አጡህ" ሲለው ፥ ሚካኤል ፤

"ሽማግሌው እንዴት ነው? ምን ያህል ተጐድቷል?" በማለት ጠየቀው ።

"በጣም ተጐድቷል ። አምስት ቦታ ነው የመቱት፤ ግን ጠንካራ ሰው ነው ።" አለ ሶኒ በኩራት ፥ "ሀኪሞቹ ይተርፋል ብለዋል ። ስማ ፥ በጣም ስራ በዝቶብኛል ። ማውራት አልችልም ። የት ነው ያለኸው ?" ሲል ጠየቀው ።

"ኒውዮርክ ነኝ ። ቶም እንደምመጣ አልነገረህም እንዴ ?"

ሶኒ ዝቅ ባለ ድምጽ "ቶምን ጠልፈውታል ። ለዚህ ነው ላንተም የሰጋሁት ። ሚስቱ እዚህ ነች ። እሷም ሆነች ፖሊሶች ያለበትን ማወቅ አልቻሉም ። እንዲያውቁም አልፈልግም ። ይህን የፈጸሙት ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

አብደዋልና ምንም ሳትተነፍስ ወደ ቤት እንድትመጣ፣ እሺ ?"

"እሺ ፣ ግን ማን እንደፈጸመው ታውቃለህ ?"

"ይታወቃሉ ። ሉካ ብራሲ ሲመጣ የገማ ስጋ እንደምናደርጋቸው አትጠራጠር" አለ ሶኒ ። ሚካኤል በአንድ ሰአት ውስጥ በታክሲ እንደሚደርስ ነገሮት ስልኩን ዘጋው ። ጋዜጦች ዜናውን ካወጡት ሶስት ሰአት ሆኗቸዋል ። እስከአሁን ዜናው በሬዲዮ ሳይተላለፍ አይቀርም ። ሉካ ብራሲ ዜናውን አልሰማም ማለት ያዳግታል ። ሚካኤል ብራሲ የት እንዳለ ያሰላስል ነበር ። በዚያን ሰአት ሄገን እራሱ ይጠይቀው የነበረ ጥያቄ ነው ። ሶኒ ኮርሌዎኔንም ይሽው ጥያቄ አሳስቦታል ።

የዚያን እለት ከሰአት በኋላ ለአስራ አንድ እሩብ ጉዳይ ላይ ዶን ኮርሌዎኔ የወይራ ዘይት ኩባንያው ስራ አስኪያጅ ያቀረበለትን ሰነዶች ተመልክቶ አበቃ ። ኮቱን ለብሶ ልጁን ፍሬዲን ከጋዜጣው ላይ ቀና እንዲል እራሱን ኮረኮመውና ፣

"ፖሊ ጋቶን መኪናውን ከማቆሚያው እንዲያወጣ ንገረው ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ወደ ቤት እሄዳለሁ" አለው ።

"መኪናዋን እኔ ላውጣት ። ፖሊ ታሟል ። ጉንፋን እንደገና ይዞታል" አለ ፍሬድ ።

ዶኑ ጥቂት አሰበና "ይህ ሰው በዚህ ወር ለሶስተኛ ጊዜ መታመሙ ነው ። እንደሚመስለኝ ጤነኛ ሰው መተካት ይኖርባችኋል ። ይህንኑ ለሄገን እንድትነግረው ።"

"ፖሊ እኮ ጥሩ ልጅ ነው ። ታምሜአለው ካለ ታሟል ። እኔ መኪናዋን ባወጣት ምንም አይደል" አለና ቢሮውን ለቆ ወጣ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍሬዲ መንግዱን አቋርጦ መኪናዋ ወደ ቆመችበት ሲያመራ አባቱ በመስኮት ተመለከተው ። ዶኑ ሄገን ዘንድ ቢደውል መልስ አጣ ። ሎንጉ ቢች ወዳለው ቤትም ቢደውል ከዚያም መልስ የለም ። በሽቆ በመስኮት ተመ ለከተ ። መኪናው ከህንጻው ፊት ለፊት ካለው መንገድ ዳር ቆማለች ። ፍሬዲ መኪናዋን ተደግፎ ሰገና በአል ሸመታ የሚንጋጋውን ህዝብ ይመለከታል ። ዶኑ ኮቱን ለብሶ ካፖርቱንም በቢሮው ስራ አስኪያጅ ረዳትነት ደርቦ ሰውየውን አመስግኖ ደረጃውን መውረድ ጀመረ።

መንግዱ ሲታይ የከረምቱ ብርሀን እየደከመ ነው ። ፍሬዲ የአባቱን መምጣት ተመልክቶ ወደ መኪናው አመራና ከነጂው ቦታ ተቀመጠ ። ዶኑ ወደ መኪናው ውስጥ ለመግባት ከተጠጋ በኋላ አቅማማና ወደ አት ክልት መሸጫው ዞር አለ ። አዲሱ ልማዱ ያኔ ወቅታቸው ባልነበረው ፍራፍሬዎች ፥ ብጫ ኮክና ብርቱካን ላይ ያደረበት ፍቅር ነው ። አትክልት ሻጩ ትእዛዝ ሊቀበል ተነሳ ። ዶኑ ፍራፍሬዎቹን በማንሳት ፋንታ በጣቱ በማ መልከት ከመረጠ በኋላ ሻጩ በኪስ ወረቀት ውስጥ ከተተለት ። ፍሬ የተሞላበትን የኪስ ወረቀት አንስቶ አምስት ብር ሰጥቶ መልሱን ተቀብሎ ወደ መኪናው ሊሄድ ሲል ፥ ጥቁር ካፖርት ለብሰው አፍንጫቸው ላይ ባርኔጣ የደፉ ሁለት ሰዎች ከማእዘኑ አካባቢ ወደሱ ሲራመዱ አያቸው ። የሚሆነውን ነገር ወዲያውኑ ተረ ድቶ ለሱ ውፍረትና እድሜ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና በተሞላበት ሁኔታ ፍራፍሬውን ጣለና ወደ መኪናው ተወርውሮ ፥ 'ፍሬዶ' እያለ ጮኸ ። ያኔ ሁለቱ ሰዎች ተኩስ ከፈቱበት ። የመጀመሪያዋ ጥይት ጀርባውን ስትመታው መላ አቋሙን አናጋችው ። ቢሆንም ወደ መኪናው ከመሮጥ አላቆመችውም ። ተከታዮቹ ሁለት ጥይቶች መቀመጫው ላይ ሲመቱት መንግዱ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተዘረረ ። ሰዎቹ የተበተነው ፍራፍሬ እንዳያገኘራት ታቸው እየተጠነቀቁ ሊጨርሱት ተከተሉት ። ይኸኔ ፍሬዲ ከመኪናው ውስጥ በቁጣ ብቅ አለ ። በመ ጨረሻ የተተኮሱት ሁለት ጥይቶች ዶኑን አደገኛ ቦታ ላይ ባያገኙትም ፣ አንዷ ከንዱን ሌላይቱ ባቱን መታችው ። ዶኑ የተቃጣበት የመግደል ሙከራ ባይሳካም ብዙ ደም ስለፈሰሰው ህሊናውን ሳተ ።

ፍሬድ አባቱ በልጅነት ስሙ እየጠራው ሲጮህና ወዲያውም ሁለት የጥይት ድምጽ ሰምቶ ከመኪናው ውስጥ ሲወጣ እራሱ ተደናግጦ ስለነበር ሽጉጡን ለመም ዘዝ እንኳን አልቻለም ። ሁለቱ ነፍሰ ገዳዮች በቀላሉ ሊገ ድሉት ይችሉ ነበር ። ነገር ግን እነሱ እራሳቸው ተሸበሩ ። ፍሬድ ሽጉጥ መያዙን ሳያውቁ አልቀሩም ። ብዙ ጊዜ ስላለፈ ለተጨማሪ ተኩስ አልቆዩም ። ሸሹ ፣ ጠፉ ። በአካ ባቢው ከነበሩት ሰዎች ግማሹ ነፍሴ አውጪኝ ብሎ በየስርቻው ሲሸጉጥ ሌላው እዚህም እዚያም ተሰባስቦ ተፋፈገ ። ፍሬድ ባለበት ሆኖ አእምሮው ስለደነዘዘ አሁንም ሽጉጡን አላወጣም ። ቁልቁል ሲመለከት አባቱ ፊቱን አስፋልት የተነጠፈበት መንገድ ላይ ደፍቶ በጥቁር የደም ባህር ውስጥ ተጋድሟል ። ፍሬድ መላ ሰውነቱ ደነዘዘ ። ከከበቡት ሰዎች መሀል አንዱ ፍሬድ የሚሰራው ጠፍቶት ሲንከረፈፍ ስላየው ወደ መን ገዱ ጠርዝ ወስዶ አስቀመጠው ። የፖሊስ መኪና የአ ደጋ ምልክት ድምጽ እያሰማ ዶኑን ከቦ የቆመውን ህዝብ ጥሶ ወደተኛው ሰው ተጠጋ ። ከፖሊሱ መኪና ተከትላ 'ዴይሊ ኒውስ' የተባለው ጋዜጣ መኪና ተጠ ግታ ከመቆሟ በፊት ፎቶግራፍ አንሺው ዘሎ ወረ ደና በመድማት ላይ ያለውን ዶን ፎቶግራፍ ደጋግሞ አነ ሳው ። ከዚያ በኋላ ነበር አምቡላንስ የመጣው ። የጋ ዜጣው ፎቶግራፍ አንሺ ሌላ አስደናቂ ትርኢት ሆኖ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያገኘው ንፍጥና ለሀጭ ብቻ ሆኖ እየጮኸ ያለቅስ የነበረው የክብ ፊቱ ፍሬድ ሁኔታ ነበር ። የደህንነት ሰራተኞች በህዝቡ መሀል ተሰራጩ ። ተጨማሪ የፖሊስ መኪናዎች ብቅ አሉ ። አንዱ የደህንነት ሰራተኛ ወደ ፍሬድ ጠጋ ብሎ ጥያቄ ቢያቀርብለትም ከነበረበት ድንጋጤ የተነሳ መልስ መስጠት አልቻለም ። ሰውዬው የፍሬድን ኪስ ዳብሶ መታወቂያውን አውጥቶ ማንነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለጓደኛው ፉጨት አሰማ ። በጥቂት ጊዜ አያሌ ነጭ ለባሾች ፍሬድን ከበቡትና ከተሰበሰበው ህዝብ ነጠሉት ። የመጀመሪያው ነጭ ለባሽ የፍሬድን ሽጉጥ ከማ ሀደሩ አውጥቶ ወሰደው ። ከዚያም ፍሬድን አንስተው ምልክት ወደሌለው መኪና ውስጥ አስገቡት ። መኪናው ሲጓዝ የ'ዴይሊ ኒውስ' መኪናም ተከትሎት በረረ ። ፎቶ ግራፍ አንሺው አካባቢውን በሞላ ማንሳቱን አላቋረጠም።

አባቱ በተተኮሰበት በግማሽ ሰአት ውስጥ ሶኒ ኮርሌዎኔ አምስት ተከታታይ የስልክ ጥሪዎች ደረሱት። በመጀመሪያ ቤተሰቡ ልዩ የወር ክፍያ የሚሰጠው የደህንነት ባለሙያው ጆን ፊሊፕስ ደውሎ ዶኑ ተተኩሶበት በጠና መቁሰሉን ፣ ሆኖም ህይወቱ ተርፎ 'የፈረንሳይ ሀኪም ቤት' ተብሎ ወደሚጠራው ሀኪም ቤት መወሰዱን ፣ ወንድሙን ፍሬድንም ወደ ቼልሲ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዱት ነገረው ። ጆን ፊሊፕስ ቀጥሎም ፤

"ፖሊሶቹ ፍሬዲን ሲለቁት ሀኪም እንዲያየው ብታደርግ መልካም ነው ። እኔ ዶኑ መናገር ከቻለ ቃሉን እንዲሰጥ ለመርዳት ወደ ሀኪም ቤት እሄዳለሁ ። የሚሆነውን ሁሉ እየደወልኩ እነግርሀለሁ" አለው ።

ሶኒ አስደንጋጭ ነገር እንደተነገረው ከፊቱ መቅላት ስለገመተች ሚስቱ ስትጠይቀው ፣ ዝም እንድትል ምልክት ሰጣት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

‘ህይወቱ መትረፉን እርግጠኛ ነህ?’ ብሎ ሶኒ ፈሊፕስን ሲጠይቀው የነጭ ለባሽ ፖሊሱ ሹም ዶኑ አለመሞቱን አረጋገጠለት ። ቀጥሎም ጉዳዩን ፈጥኖ ስለነገረው በነገታው ሺህ ብር እንደሚከፍለው ነገረው ።

ሶኒ የስልኩን መናገሪያ ከቦታው መልሶ ቁጭ ብሎ ያስብ ጀመር ። የሱ ድክመት ግልፍተኛነቱ ነው ። ግን በአሁኑ ወቅት መናደድ አደገኛ ነው ። የመጀመሪያ ተግባሩ ቶም ሄገንን ማግኘት ይሆናል ። እሱ ከመደወሉ በፊት ስልኩ ጭርር አለ ። የተደወለው በዶኑ ፈቃድ በወረዳው ቁማር ከሚያጫውት ግለሰብ ሲሆን ፥ ሰውየው ስለዶኑ በጥይት ተመትቶ መሞት ለሶኒ አወራለት ። ሶኒ ሰውየው ሳያጣራ ያወራው ወሬ መሆኑን ስላወቀና በተለይም ያባቱን አለመሞት ከፈሊፕስ በማረጋገጡ አልተደናገጠም ። ሶስተኛው ጥሪ ከ‘ዴይሊ ኒውስ’ ጋዜጠኛ መሆኑን ሲሰማ ስልኩን ዘጋው ።

ሶኒ ሄገን ቤት ደውሎ የሄገን ሚስት ባሏ አለ መግባቱንና ከሀያ ደቂቃ በኋላ ለእራት እንደሚመጣ ነገረችው ። ሶኒም ‘‘እንደመጣ ይደውልልኝ’’ ብሏት ስልኩን ዘጋው ።

ሶኒ ነገሮችን ማሰብ ሞከረ ። አባቱ ቢሆን እንዲህ ባለ ሁናቴ ምን ያደርግ ነበር? ይህን አደጋ የጣለው ሶሎዞ መሆኑን ወዲያውኑ አውቆታል ። ነገር ግን ሶሎዞ ብቻውን ያለ ሀይለኛ ሰዎች ድጋፍ ዶኑን የመሰለ ታላቅ የድብቅ አለም መሪ ለማጥፋት አይደፍርም ። ይህን በግውጠንጠን ላይ እያለ ለአራተኛ ጊዜ የተደወለው ስልክ አሳቡን አቋረጠው ።

ለስለስና ለዘብ ያለ ድምጽ ፥

‘ሳንቲኖ ኮርሌዎኔ?’ ሲል ጠየቀው ።

‘አዎን’

t.me/OLDBOOKSPDF

“ቶም ሄገን እኛ ዘንድ ነው ። ከሶስት ሰአት በኋላ እንለቀዋለን ። የሚለውን ነገር ሳትሰሙ በችኮላ ጉዳት እንዳታደርሱና ብዙ ችግር እንዳይከተል ። ሁሉም ሰው አሁን በውል ማሰብ አለበት ። ያንን ዝነኛ የንዴት ችኮላህን እንዳታሳይ” ሲለው ፥ ይህ ድምጽ የሶሎዞ እንደ ሆነ ገመተ ። ሶኒም የተሰበረ በመሰለ አነጋገር “እጠብቃለሁ” በማለት ሲመልስለት ስልኩ ተዘጋ ። ባለወርቅ ማሰሪያ ሰአቱን ተመለከተና ጊዜውን መዘገበ።

ወጥቤቱ ጠረጴዛ ጋ ተቀምጦ ፊቱን አኩሳትሮ ሳለ ሚስቱ “ሶኒ ፥ ምንድነው ነገሩ?” ስትል ጠየቀችው ። የአባቱን በጥይት መመታት ሲነግራት በጣም ደነገጠች። አባቱ ስለአልሞተ እንዳትደነግጥ ነገራት ። ስለሄገን ግን ምንም ነገር አላነሳባትም ። ወዲያው አምስተኛው ስልክ ጮኸ ። ክሎሚንዛ ነበር ።

“ስላባትህ ሰምተሀል ?”

“አዎን ሰምቻለሁ ። ግን አልሞተም” አለ ሶኒ ። ክሌሚንዛ የሰማው ወሬ ዶኑ ሞቷል የሚል ስለነበር ፥ “እሰየው ተመስገን!” በማለት ከስቃይ የመገላገል ስሜት ተንፈሰ ። ልዩ ልዩ ባህርይ ማሳየት የሚችለው ወፍራሙ ክሌሚንዛ የቤተሰቡ ተግባር ያለመሪ እንዳይቀር መሪ ነቱን መያዝ እንዳለበት ሶኒን አሳሰበውና በበኩሉ ምን እንደሚያደርግ መመሪያ ጠየቀው ።

“ወደ አባቴ ቤት ና ። ፖሊ ጋቶንም አምጣው” አለ ሶኒ ።

“ይኸው ነው? ወደ ሀኪም ቤትና ወዳንተ ቤት የጥበቃ ሰዎች መላክ አያስፈልግኝም?”

“አያስፈልግም ። አንተና ፖሊ ጋቶን ብቻ ነው የምፈልገው” አለ ሶኒ ። ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሆነ ። ክሌሚንዛ መልእክቱ ደርሶታል ። ክሌሚንዛ እንዳይነቃበት የሁልጊዜው ሶኒ ለመምሰል ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ ያ ፖሊ የት ነው ያለው? ምናባቱ እየ ሰራ ነው?" ሲል ክሌሜንዛን ጠየቀው ።

"ፖሊ ጉንፋን አሞት ቤት ውሏል ። ክረምቱን እያመመው ነበር" ሲል መለሰለት ።

"ለመሆኑ ባለፉት ሁለት ወራት ብቻ ምን ያህል ጊዜ ታመመ?"

"ምናልባት ሶስት ወይም አራት ጊዜ ታሟል ። ፍሬዲን በፖሊ ፈንታ ሌላ ሰው ልመድብልህ ብለው እምቢ አለ" ሲል መለሰ ክሌሜንዛ ።

"መልካም ፥ አባቴ ቤት እንገናኝ ። ፖሊ እንዳይቀር በመኪናህ ሞነኸው ና ። የፈለገውን ያህል ቢታ መም ግድ የለኝም ። ገባህ?" ብሎ ሰልኩን ዘጋው። ሶኒ የምታለቅሰውን ሚስቱን ተመለከተና በቁጣ ተናገራት ።

"ከኛ ሰዎች ማናቸውም ቢደውል ባባቴ ልዩ ስልክ እንዲያነጋግሩኝ ንገሪያቸው ። ሌላ ሰው ከደወለ 'ምንም ነገር አላውቅም' በይ ። የቶም ሚስት ከደወለች ለጥቂት ጊዜ ለስራ እንደሚቆይ ንገሪያት ።"

ሚስቱ በፍርሀት ተውጣ ተመልከቷት ጥቂት አሰበና፥

"አትፍሪ ፥ የኛ ሰዎች መጥተው ይጠብቁሻል ። ያሉሽን ሁሉ አድርጊ ። ከፈለግሽ ባባቴ ልዩ ስልክ ደውይልኝ ። በጣም አስፈላጊ ካልሆነ አትደውይልኝ አይዞሽ አትስጊ" ብሏት ወጣ ።

ቀኑ ጨልሞ የታህሳስ ብርድ ይጋረፋል ። ሶኒ ወደ ሞለማው መሄድ አልፈራም ። ዙሪያውን ያሉት ስምንቱም ቤቶች ያባቱ ናቸው ።

ግራና ቀኝ ጫፍ ላይ ያሉትን ቤቶች የቤተሰቡ የቆዩ ባለሟሎች ከነቤተሰባቸው ፥ የምድር ቤቱን ደግሞ የታመኑ ወንደላጤዎች ተከራይተውታል ። ከቀሪዎቹ ስድስቱ ቤቶች አንዱን ቶም ሄገን ከነቤተሰቡ ፥ እን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዱን ሶኒ ፥ ሌላውን ደግሞ ዶኑ ይናሩበታል ። የቀሩት ሶስቱ ደግሞ በጡረታ የተገለሉ የዶኑ ወዳጆች በተፈለገ ጊዜ ሊለቱ ታል ገብተው ከኪራይ ነጻ ሆነው ይናሩበታል ። ይህቺ አካባቢ ሳይታወቅባት የዶኑና የቤተሰቡ የግትጣስ ምሽግ ነበረች ። ስምንቱም ቤቶች ለሰርጉ ገቦች እንዳያመቹ መብራታቸው በርቶ ጨረቃ መስለዋል ።

ሶኒ መንገዱን ተሻግሮ አባቱ ቤት ደረሰ ። በአምሳያ ቁልፍ በሩን ከፍቶ ገባና እናቱን ተጣራ ። እናቱ የተጣደ የፈረንጅ ቃርያ መአዛ አስከትላ ከወጥ ቤት ብቅ አለች ። ሶኒ እጅዋን ያዘና አስቀመጣት ።

"አንድ የስልክ ጥሪ ደረሰኝ ። አይዞሽ አትሰጊ ። አባዬ ትንሽ ተጎድቶ ሀኪም ቤት ገብቷል ። ለባብሺና ሄደሽ ታይዋለሽ ። መኪናና ሹፌር አዘጋጅልሻለሁ ፥ እሺ?" አላት ። እናቱ ልጅዋን ትክ ብላ ተመለከተችውና ፤

"ተከሱበት?" ብላ ስትጠይቀው ፥ እራሱን በመነቅነቅ አረጋገጠላት ። ለጥቂት ጊዜ እራሷን ደፍታ ከቆየች በኋላ ወደ ወጥ ቤቱ ተመልሳ ሄዳ በጣደችው በርበሬ ላይ የሚንቦገቦገውን የጋዝ እሳት አጠፋችው ። ሶኒ ዳቦ ከቅርጫቱ አውጥቶ ከመጥበሻው ላይ ቃርያ አንስቶ ሳንድዊች አበጀና የወይራ ዘይቱ እየተንጠባጠበ ይገምጥ ጀመር ። ከዚያም አባቱ ቢሮ ሄዶ የጠረጴዛውን ኪስ ከፍቶ በሀሰት ስምና አድራሻ የተመዘገበውን ያባቱን ልዩ ስልክ እወጣና ለሉካ ብራሲ ደወለ ። መልስ የለም ። ቀጥሎም ለዶኑ ያለው ታማኝነት ፈጽሞ ለግያጠራጥረውና ብሩክሊን ለሚገኘው የልዩ ቡድን ሹም ለሆነው ለቴስዮ ደወለለት ።

ሶኒ የደረሰውን ሁሉ ከነገረው በኋላ የሚፈልገውን ገለጸለት ። ለቴስዮ የተላለፈለት መመሪያ ሀምላ አስተማማኝ ግለሰቦች መልምሎ ግማሹ ሀኪም ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

አባቱን እንዲጠብቁ፣ የተሩት ሎንግ ቢች ዮናውን ቤት እንዲጠብቁ የሚል ነበር። ቴስዮም በመገረም፣

"ከሌሚንዛንም አደጋ ጣሉበት እንዴ!" ሲል ጠየቀ።

"ለጊዜው የክሌሚንዛን ሰዎች በጥበቃ ላይ ለማሰማራት አልፈለግኩም" ሲል መለሰለት። ቴስዮ ጉዳዩ ያሌውት ገባውና፣

"ይቅርታ አድርግልኝ ሶኒ፣ እንደአባትህ ሆኜ ልናገርና፣ ችኩለህ እርምጃ አትውሰድ። ክሌሚንዛ አሳልፎ ይሰጠናል ብዬ አሳምንም" አለው።

"አመሰግናለሁ። እኔም አልጠረጥረውም። ነገር ግን በጣም ጠንቃቃ መሆን አለብኝ ብዬ ነው። ሌላው ነገር" አለው ሶኒ፣ "ከቦስተን ሰዎች ልከህ ትንሹን መንድሜን ግይክን ከሚማርበት ኮሌጅ አስመጣው፣ እኔም ደውዬ እነግረዋለሁ። ለምናልባቱ ብዬ ነው።"

ቴስዮ ትእዛዙን በእሺታ ተቀበለው።

ሶኒ ከግድግዳው ላይ ያለች ካዝና ከፈተና በሰሚያዊ ቆዳ የተለበጠ የሰም ቅደም ተከተል ያለበት መዝገብ አወጣና የሬይ ፋረልን የስልክ ቁጥር ፈለገ። ሰሙ ባለበት ገጽ ላይ

'ሬይ ፋረል፣ 5,000 ብር ለገና ዋዜማ' ይላል። ሶኒ ለፋረል ሲደውልለት መዲያው አገኘው።

'ፋረል፣ ሶኒ ኮርሌዮኔ ነኝ። አንድ ቁም ነገር እንድትሰራልኝ እፈልጋለሁ። የምፈልገውም አሁኑኑ እንድታደርገው ነው። ሁለት ሰዎች አሉ። ባለፉት ሶስት ወራት ያደረጓቸውን የስልክ ጥሪዎች ቁጥር ትሰጠኛለህ" ብሎት የክሌሚንዛንና የፖሊ ጋቶን የቤት ቁጥር ሰጠው። "ከፍተኛ ጉዳይ ስለሆነ ከእኩለ ሌሊት በፊት እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ። አንተም ተጨማሪ የገና መደሰቻ ይኖርሀል" አለው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ብሎ ከማረፉ በፊት ሉካ ብራሲን ለማግኘት እንደገና ሞከረ ። አሁንም መልስ የለም ። ሉካን ባለመገኘቱ ቢሰጋም ከአእምሮው ወዲያውኑ አስወገደው ። ሉካ ብራሲ እንደሰማ ይመጣል ። ሶኒ በተሸከርካሪ ወንበሩ ላይ ተለጠጠ ። ከአንድ ሰአት በኋላ ለስብሰባ የሚመጡት የቤተሰቡ ባለሟሎች ቤቱን ሲሞሉት መመሪያ የሚሰጣቸው እሱ ነው ። ሁኔታው ምን ያህል የከፋ መሆኑን ተገነዘበ ። በአስር አመት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሀይል ላይ የተቃጣ ሙከራ ነው ። ድርጊቱን በሚስጢር ያቀነባበረው ሶሎዞ መሆኑ አያጠራጥርም ። ነገር ግን ከታወቁት ሶስት ታላላቅ የኒውዮርክ ቤተሰቦች አንዱ አይዞህ ሳይለው ይህን ድፍረት ከቶውንም ብቻውን አይሞክረውም ። 'አይዞህ' ያለውም የታታሊያ ቤተሰብ መሆን አለበት ። የዚህ ተልእኮ ትርጉምም ሶሎዞ ያቀረበውን ድርድር መቀበል ፥ አለበለዚያ ግን በመሀከላቸው ሙሉ ጦርነት ማወጅ ማለት ይሆናል ። ሶኒ የምሬት ፈገግ አለ ። ተንኮለኛው ቱርክ መልካም አቅዶ ነበር ። ዳሩ ምን ይሆናል ፥ ዶኑ ተረፈና የሚቀረው ጦርነት ብቻ ሆነ ። ዶኑ ባለው የገንዘብ ሀይልና ሉካ ብራሲ ባለው የግድያ ጥበብ ደግሞ አንድ ውጤት ብቻ ነው ሊገኝ የሚችለው ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ያሸንፋል ። ታዲያ ግን ሉካ ብራሲ የታለ ? ይህ ሲታሰበው ሶኒን ከነከነው ።

ምእራፍ ሶስት

ሾፌሩን ጨምሮ ከሄገን ጋር በመኪናው ውስጥ የነበሩት ሰዎች አራት ነበሩ ። ሶሎዞ ከፊት ለፊት ከሹፌሩ ጎን ፥ ቀደም ሲል ሄገንን ከመንገድ ላይ ጐትተው ያስገቡት ሁለት ሰዎች ሄገንን መሀከላቸው አድርገው ከኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀምጠዋል ። ከሄገን በስተቀኝ የተቀመጠው ሰው የሄገን ባርኔጣ አይኑን እንዲሸፍነው ወደታች ጐተተ በትና ግራና ቀኝ እንዳይመለከት አስጠነቀቀው ። ከሠያ ደቂቃ በላይ ያልፈጀው ጉዞ ሲያበቃ ጊዜውም እየመሸ በመሄዱ ሄገን ያለበትን አካባቢ ማወቅ አልቻለም። አፋኞቹ ሄገንን ወደ ምድር ቤት ወስደው ደረቅ የማድ ቤት ወንበር ላይ አስቀመጡት ። ሶሎዞ ከሄገን ባሻገር ቁጭ ብሎ ጩሉሌ አይኑን እያቁለጨለጨ ፣

"እንድትደነግጥ አልሻም ። በኮርሌዮኔ ቤተሰብ ውስጥ የጡንቻ ሰው እንዳልሆንክ አውቃለሁ ። የኮር ሌዮኔን ቤተሰብና እኔንም እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ" አለው ። ሄገን ሲጃራውን ወደ አፉ ሲያስጠጋ እጁ ይን ቀጠቀጥ ነበር ። ከአፋኞቹ አንዱ ዊስኪ አመጣና በቡና ሲኒ ቀዳለት ። ሄገን አመስግኖ ጠጣው ። መጠጡ የእጁን መንቀጥቀጥ አጸናለት ። የእግሩንም መዝለፍለፍ አጠናከረው ።

"አለቃህ ሞቷል" አለውና ሶሎዞ ዝም አለ ። የሄገን አይኖች እምባ ሲያፈሱ ተመልክቶ ተደነቀ ።

"መንገድ ላይ አገኘነው ። ዶኑን እንደገደሉት ሲነ ግሩኝ እኔም አንተን ከመንገድ ጠለፍኩህ ። አሁን ያንተ ሚና በኔና በሶኒ መሀከል ሰላም ማውረድ ይሆ ናል ።"

ሄገን አልመለሰም ። የዶኑን መሞት ስለሰማ ያን ያህል ማዘኑ እራሱን አስደነቀው ። ብቸኝነትና የሞት ፍራቻ ስሜቶች ተቀላቀሉበት ።

"ያን እለት ፣ ሶኒ ላቀረብኩት ድርድር የጋለ ስሜት ነበረው ። አይደለም? ይህ አስተዋይነቱን ያሳያል ። እደ ንዛኛ እጽ ነው ታዳጊው ነገር ። በዚያ ንግድ በጥቂት አመ ታት ከበርቴ መሆን ይቻላል ። ዶኑ ወቅቱ ያለፈበት ትምክህተኛ ሽማግሌ ነበር ። ቀኑ እንዳለፈበት ማወቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

አልቻለም ። አሁንማ ሞቷል ፤ ምንም ነገር አይመልሰ ውም ። እኔ አዲስ ድርድር ለማድረግ ዝግጁ ነኝ ። ሶኒን አነጋግረህ እንድታስማማን እፈልጋለሁ" አለው ።

ሄገንም ሲመልስ "ምንም እድል አይኖርህም ። ሶኒ ባለው ሀይል ሁሉ ያሳድድሀል" አለው ።

"የመጀመሪያው ሙከራውማ አጸፋ ይሆናል ። አንተ ግን በበቂ ምክንያት ማስረዳት አለብህ ። የታታሊያ ቤተሰብ ከኔ ጋር ናቸው ። ሌሎቹ የኒውዮርክ ቤተሰቦች በመሀከላችን ሙሉ ጦርነት ቢነሳ የነሱንም ጥቅም ስለ ሚያናጋ ጠቡን ለማቆም መጣራቸው አይቀርም ። እኔና ሶኒ ብንስማማ ግን የነሱን ምናቸውንም ስለማንነካ የዶኑ የቀድሞ ወዳጆች ሳይቀሩ ምንም አይሉንም" አለ ሶሎዞ ። ሄገን ምንም ሳይመልስ አጎንብሶ እጁን ይመለከት ነበር ። ሶሎዞም የማግባቢያ ንግግሩን ቀጠለ ።

"ዶኑ እየላላ ነበር ። ድሮ ቢሆን እሱን ልነካው አልችልም ነበር ። አንተን አማካሪ በማድረጉ ፥ አንተም ሲሲሊያዊ ባለመሆንህ ፥ ሌሎቹ ቤተሰቦች ዶኑን እምነት ነስተውታል ። በመሀከላችን ሙሉ ጦርነት ቢካሄድ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ይደመሰሳል ። ሁሉም ከኔ ጭምር ጥቅሙ ይነካል ። እኔ ከናንተ ጋር መተባበርን የምሻው ከገንዘቡ ይበልጥ ባላችሁ የፖለቲካ ግንኙነት ለመጠቀም ስል ነው ። ስለዚህ ሶኒን አነጋግረው፥ ሹሞቻችሁንም አነጋግራቸው ። ከብዙ ደም መፋሰስ ልታድነን ትችላለህ" አለው ።

ሄገን ተጨማሪ ዊስኪ በመሻት ሲኢውን አነሳና "እሞክራለሁ ። ግን ሶኒ እልኸኛ ነው ። ሉካ ብራሲ ደግሞ ሌላ ሰው ቀርቶ ሶኒም እንኳን እረፍ ብሎ ቢነግረው አይሰማም ። መስጋት ያለብህ ስለ ሉካ ነው ። ያንተን ድርድር ለማስፈጸም ብሞክር ደሞ እኔ ራሴ በሉካ ብራሲ በኩል የሚመጣው ያሰጋኛል" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶሎዞም በጽሞና እንዲህ ሲል መለሰለት ፥

“የሉካ ብራሲን ጉዳይ ለኔ ተወው ። ባንተ በኩል ከሶኒና ከወንድሞቹ ጋር አስማማኝ ። ስማ ፥ በዛሬው እለት ከኔ ትእዛዝ ባይሰጣቸው ኖሮ ፍሬዲንም ይገድሉት ነበር ። የግድ አስፈላጊ ከሆነው በላይ ቂም እንዲኖር አልፈልግም ። ፍሬዲ በህይወት መቆየት የቻለው በኔ ምክንያት መሆኑን ንገራቸው ።”

በመጨረሻ ሄገን አእምሮው መስራት ጀመረ ። ሶሎዞ ሄገንን የወሰደው ሊገድለው ወይም ያልኩትን ካላደረጋችሁ ሄገንን እገድለዋለሁ ለማለት አለመሆኑን ተገነዘበ ። ከወረረው ድንጋጤ ሲላቀቅ እፍረት ተሰማው ። ሁኔታውን የተመለከተው ሶሎዞ በፈገግታ ተመለከተው ። ሄገን በሶሎዞ ሀሳብ ካልተስማማ ሊገደል ይችላል ። ደግሞም ሶሎዞ ሄገንን የፈለገው ማንኛውም ሀላፊነት የሚሰማው አማካሪ እንደሚያደርገው ሁሉ የቀረበውን ድርድር ለአለቆቹ በሚገባ እንዲያስረዳለት ነው ። ጉዳዩን ከአሰላሰለ በኋላ ሶሎዞ ይህን ማድረጉ ትክክል ነው ሲል አሰበ ። በምንም አይነት በኮርሌዎኔና በታታሊያ ቤተሰቦች መሀከል ገደብ የለሽ ጦርነት እንዳይቀሰቀስ መከላከል አስፈላጊ ነው ። በአሁኑ ወቅት የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ‘የሆነው አንዴ ሆነ’ ብሎ ስምምነት ማድረግ አለበት ። ከዚያ በኋላ ወቅቱ ሲደርስና ጊዜው ሲፈቅድ ሶሎዞን ሊበቀሉት ይችላሉ ።

ሄገን ቀና ብሎ ሶሎዞን ሲመለከተው ሶሎዞ የሚያስበውን እንዳወቀበት ተረዳ ። ቱርኩ ፈገግ ሲል ሄገን አንድ ነገር ታሰበው ። ሶሎዞ ስለሉካ ብራሲ እንደዚህ ችላ ያለው ፥ ብራሲ ምን ሆኖ ይሆን ? ሉካ የኮርሌዎኔን ቤተሰብ ከዶ ከዶኑ ጠላቶች ጋር ስምምነት ፈጥሮ ይሆን ? ዶኑ ሶሎዞን እምቢ ባለበት ምሽት ሉካ ብራሲ ተጠርቶ ከዶኑ ጋር ቆይታ ይዞ እንደነበር ሄገን ትዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

አለው ። ብቻ አሁን ስለዚህ ዝርዝር ጉዳይ ማሰቢያ ጊዜ አይደለም ። በቅድሚያ አሁን ካለበት ወጥቶ ዶን ኮርሌዎኔ ምሽግ መግባት አለበት ።

"የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ" አለ ሄገን ።

"ልክ ነህ መሰለኝ ። ዶኑም ቢሆን በዚህ ሁኔታ ላይ ይህንኑ እንድናደርግ ነው የሚፈልገው ።"

ሶሎዞ እራሱን ነቀነቀና ፥ "መልካም ። እኔ ደም ማፍሰስ አልወድም ። የንግድ ሰው ነኝ ። ብዙ ደም ማፍሰስ ብዙ ገንዘብ ይፈጃል" ብሎ እንደተናገረ የስልክ ጥሪ ተሰማ ። ከሰዎቹ አንዱ ስልኩን አነሳና መልእክቱን ተቀበለ ።

"እሺ እንግረዋለሁ" ብሎ ስልኩን ዘጋ ። ወደ ሶሎዞ ጆሮ ተጠግቶ አንሾካሾከ ። ሄገን የሶሎዞ ፊት ሲገረጣና አይኑ በቁጣ ሲቀላ ተመልከቶ ፈራ ። ሶሎዞ በጥርጣሬ ሲመለከተው ሄገን እንደማይፈታ አወቀ ። የሆነው ነገር የሄገንን ሞት የሚያስከትል ሊሆን ይችላል ።

"አምስት ጥይት መትቶት ያ ሽማግሌ አልሞ ሞተም" አለ ሶሎዞ ። የመጣው ይምጣ በሚል ግድ የለሽነት ትከሻውን እየነቀነቀ ሄገንን እንዲህ አለው፡

"ለኔም ላንተም መጥፎ አጋጣሚ ተከሰተ ።"

ምእራፍ አራት

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ወደ አባቱ ቤት ሲመጣ መንገዱ በሙሉ መብራት በርቶ ፤ መኪኖች ተደርድረው አዳዲስ የጥበቃ ሰዎች ግቢውን ሞልተውት አገኘ ።

"ማነህ?" አለው አንዱ ጠባቂ ። ሰውየው የሚካኤልን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ እየመራው ሶኒ ወዳለበት ቤት ወሰደው ። ሚካኤል እንግዳ መቀበያው ክፍል

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲገባ የሄገን ሚስት ቴሬሳ ሲጋራ እና መጠጥ ይዛ ቁጭ ብላለች ። ፊቱ ላይ ምንም ስሜት የማይታይበት ክሌሜንዛ ተቀምጦ እያላበው ምራቅ ብቻ የሆነው ሲጋሩን ያቦናል ።

ክሌሜንዛ ሚካኤልን ለማጽናናት እጁን ጨምቆ ጨበጠና "እናትህ ሀኪም ቤት አባትህ ጋ ነች ። አይዞህ ይድናል" አለው ። ፖሊ ጋቶም ሊጨብጠው ሲነሳ ሚካኤል ገርሞት ተመለከተው ። ፖሊ ያባቱ ጠባቂ አጃቢ መሆኑን ይወቅ እንጂ በዚያን እለት ታሞ ቤቱ መዋሉን ሚካኤል አላወቀም ነበር ። ነገር ግን በጋቶ ፊት ላይ ጭንቀት አይቶበታል ። ፖሊ ታዳጊ ፤ ፈጣን እና ረቂቅ ተልእኮውን ያለ ውዝግብ መፈጸም የሚችል መሆኑን ያወቅለት የነበረው ሚካኤል ፥ ይህ ሰው ዛሬ ግን በተግባሩ ላይ እንደተሰናከለ ተገነዘበ ። ሚካኤል ብዙዎቹን ሰዎች ልብ ብሎ ሲመለከት ሊያስታውሳቸው አልቻለም ። የክሌሜንዛ ሰዎች አይደሉም ። ስለዚህ ክሌሜንዛና ጋቶ ተጠርጥረዋል ማለት ነው ። ፖሊ በአደጋው ስፍራ የነበረ መስሎት ፥ "ፍሬዲ እንዴት ነው?" ሲል ጠየቀው ።

"ሀኪሙ መርፌ ወግቶት ተኝቷል" ሲል ክሌሜንዛ መለሰለት ። ሚካኤል ሁልጊዜ ይግባባት የነበረችው የሄገን ሚስት ፥ ቴሬሳ ፥ በሀዘን ተጨብጣ ስላያት ወደሷ ሄዶ ፤ጐንበስ ብሎ ሳማትና በሹክሹክታ "አይዞሽ ቶም ምንም አይሆንም" አላት ።

ቴሬሳ ሚካኤል ላይ ለአፍታ ያህል ተጣበቀች ። እጅዋን ይዞ ከሶፋው ላይ አስነሳትና ሶኒ ወዳለበት ወደ አባቱ ቢሮ ወሰዳት ።

ሶኒ መቀመጫው ላይ ተንሰራፍቶ በአንድ እጁ እርሳስ በሌላው ደግሞ ቢጫ ደብተር ይዟል ። ሚካኤል

t.me/OLDBOOKSPDF

የቡድን አለቃ ቴስዮን አየና በግቢው ያያቸው ሰዎችም እሱ የሚመራቸው መሆናቸው ገባው ።

ሶኒ ሚካኤልንና ቴሬሳን ሲያያቸው ወደነሱ መጣና ቴሬሳን እቅፍ አድርጎ ፥

"አትሰጊ ቴሬሳ ፥ ቶም ደህና ነው ። እሱን ያቆዩት ሊያቀርቡልን የሚፈልጉት ድርድር ስላለ ነው ። ይፈቱታል ፥ እሱ ጠበቃችን እንጂ ውሳኔ ሰጪ ስላል ሆነ ግንም ሊጉዳው አይፈልግም" አላት ። እሷን ለቆ ሚካኤልን ጥብቅ አድርጉ አቅፎ ጉንጩን ሲሰመው ሚካኤል ፥ ሳቅ እያለ ፥ "ድሮ ድብደባህን ለምጂው ነበር አሁንም ደሞ ይህን መቀበል ሊኖርብኝ?" አለው በቀልድ ። በልጅነታቸው ብዙ ጊዜ ይደባደቡ ነበር ። ሶኒ ሚካኤልም አደጋ ይደርስበት ይሆን በሚል ሰግቶ እንደ ነበር ከገለጸለት በኋላ ፥ "እኔ እንኳ ቢደፋህ ስሜት አይሰጠኝም! ግን በኋላ ላሮጊቷ መንገር ስለሚኖርብኝ ነው ። የግዴን ስለ አባዩ ነገርኳት ።"

ሚካኤል እናቱ ያባቱን መመታት ስትሰማ እንዴት እንደሆነች ሶኒን ሲጠይቀው አሮጊቷ ብታዝንም ብዙም አለመሸበሯን ከገለጸለት በኋላ ፥ "ሶፖዳዋለች ። እኔም ለምጀዋለሁ ። አንተ ሀጻን ሳለህ ይህ ሁኔታ አጋጥሞን ነበር ። በመሀሉ ግን ነገሮች ሁሉ ቀና ሆነው ነበር ። አሁን ከሽሜ ጋር ሆስፒታል ነች ። ሊድን ነው ።"

"እኛስ እዚያ ብንሄድ?" ሲል ሚካኤል ሶኒን ጠየቀው ።

"ሁኔታዎች እስኪጠናቀቁ ድረስ እኔ ይህን ቤት ለቅቄ ልሄድ አልችልም" አለ ሶኒ ።

ስልክ ጭርር ሲል ሶኒ አነሳው ። ወንድሙ ስልኩ ላይ ሳለ ሚካኤል ወዲያ ወዲህ እያለ ሶኒ ይዞት በነበረው ብጫ ደብተር ላይ የተጻፈውን ሲቃኝ ሰባት

t.me/OLDBOOKSPDF

ስምች ተጽፈዋል ። የመጀመሪያዎቹ ሶስት ስሞች ሶሎዞ ፣ ፊሊፕ ታታሊያ ፣ እና ጆን ታታሊያ ናቸው ። ሶኒና ቴስዮ የሚገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ሲያወጡ እንዳቋረጣቸው በግልጽ ተረዳ ።

ሶኒ ስልኩን ከዘጋ በኋላ ቴሬሳንና ሚካኤልን ፣ "ከቴስዮ ጋር የምናጠናቅቀው ጉዳይ ስላለ እሳካችሁ ውጭ ቆዩ" ካላቸው በኋላ ፣ ቴሬሳን ትከሻዋን አቅፎ ሲያስወጣት ፣ "ቶም ምንም አይሆንም ። በኔ ይሁንብሽ!" አላትና በሩን ከዘጋው በኋላ ወደ ሚካኤል ዞሮ "ማይክ ፣ አንተ ከኛ ጋር ሁንና ልትሰማ የማትፈልገውን ነገር ስማ እሺ?" አለው ። ሚካኤልም አብሮት ቢሆን ሊያግዘው እንደሚችል አረጋገጠለት ።

"የለም እባክህ ፣ ልታግዝ አትችልም ። እዚህ ውስጥ ባስገባህ ሽማግሌው ይከፋዋል" አለ ሶኒ ።

ሚካኤል በንዴት ፣ "አንተ ብሽቅ ምናምንቴ! አባቴ እኮ ነው የተመታው ። እንዴት ላግዝ አልችልም እኔ? ሄጂ ሰዎችን ባልገድልም የበኩሌን የማደርግበት መንገድ ይኖረኛል ። እንደ ሀጻን የምትቆጥረኝን ተወኝ! ። ጦር ሜዳ ዘምቼ ጀብዱ ሰርቼ ቆስዬ የተመለስኩ መሆኔን አትዘንጋው" ሲል መለሰለት ።

ሶኒ በፈገግታ ፣ "ትንሽ ቆይተህ ትደበድበኛለህ! እሺ በቃ ፣ ትረዳኛለህ ። ስልኩን ተከታተል" አለው ። ሶኒ ወደ ቴስዮ ዞር ብሎም ፣ "ቅድም በተቀበልኩት ስልክ የምንፈልገውን ፍሬ ነገር ለማወቅ ችያለሁ" አለው ። ቀጥሎም ወደ ሚካኤል ዞረና ፣ ከክሌሜንዛ ወይም ዛሬ ታም ሚአለሁ ብሎ ከተኛው ፖሊ ጋቶ ከሁለቱ ለሶሎዞ እሳ ልፎ የሰጠን ማነው ብለህ ትገምታለህ?" ሲል ጠየቀው ።

ሚካኤል በመቀመጫው ላይ ተዝናንቶ ማሰብ ጀመረ ። ክሌሜንዛ በኮርሌዮኔ ቤተሰብ መዋቅር ውስጥ በሻምበልነት ደረጃ የሚገኝ ቁልአኮ ፈጸሚ ቡድን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሹም ነው ። የብዙ ሚሊዮን ብር ጌታ ለመሆን ከመ
ብቃቱም ሌላ ከዶኑ ጋር ከሀያ አመታት በላይ በቅርብ
ወዳጅነት ኖሯል ። ዶኑን አሳልፎ በመስጠት ምን ሊያ
ገኝ ይችላል? ተጨማሪ ገንዘብ? ክሎሚንዛ ድሮ ሀብ
ታም ሆኗል ። ግን ሰዎች ስግብግብ ናቸውና ምን ይታ
ወቃል? ይህ ሰው የበለጠ ስልጣን የማግኘት ምኞት
ይኖረው ይሆን? ወይስ አልፎ አልፎ ዶኑ ስላደረሰበት
ቁጣ ወይም ዘለፋ ለመበቀል አስቦ? ሄገን አማካሪነት
በመሾሙ ቅናት አሳርሮት ይሆን? የአንድ ነጋዴ አርቆ
አስተዋይነት የሌላውን ግለሰብ ታዳጊነት ማጤንም በመ
ሆኑ ሶሎዞ የማታ የማታ ያሸንፋል የሚል ጽኑ እም
ነት አድሮበት ከድቶ ይሆን? ፈጽሞ! ክሌሚንዛ ክሀዲ
ሊሆን አይችልም ። ሚካኤል በልጅነቱ ወፍራሙ ክሌ
ሚንዛ የሚያመጣለት ስጦታና አባቱ ስራ ሲበዛ
በት ያንሸራሽረው የነበረው ሁሉ ትዝ አለው ። ሚካ
ኤል ክሌሚንዛ ወዳጁን አሳልፎ ለሞት ይሰጣል ብሎ
ጨርሶ አይጠረጥረውም ። ይሁን እንጂ ፥ በሌላ በኩል
ሶሎዞ ከማንኛውም የኮርሌዎኔ ቤተሰብ አባል ይበልጥ
ክሌሚንዛን በጁ ሊያደርግ እንደሚሻ የታወቀ ነው ።

ሚካኤል ስለ ፖሊ ጋቶም አሰበ ። ፖሊ ገና ሀብ
ታም አልሆነም ። በቤተሰቡ ውስጥ ታዳጊነቱ ባይ
ካድም ትልቅ ለመሆን ጊዜውን መጠበቅ ይኖርበታል ።
ፖሊ ጋቶ ወጣት እንደመሆኑ ፥ ለስልጣን ያልተገራ
ጥማት አለው ። እንግዲያስ ዶኑን ለሶሎዞ አሳልፎ የሰ
ጠው ፖሊ ጋቶ መሆን አለበት ። ቢሆንም ሚካኤል
ስድስተኛ ክፍል ሳለ አብሮት ይማር የነበረው የክፍል
ጓደኛው ፖሊ ጋቶም ክሀዲ እንዲሆን አልፈለገም ።

አባታቸውን አሳልፎ የሰጠውን ሰው ሶኒ የደረ
ሰበት መሆኑን ስላወቀ ሚካኤል ራሱን ነቀነቀና ፥

"ሁለቱም አይደሉም" ሲል መለሰለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶኒ ሳቀበት ። "አይዞህ ፣ ከሌሜንዛ አይደለም ። ፖሊ ጋቶ ነው" አለው ። ቴስዮ በስራ ጓደኛው በከ ሌሜንዛ ነጻ መሆን ከነበረበት የሰጋት ስቃይ ተገላገለ።

"እንግዲያስ የኔን ሰዎች ነገ ወደ ቤታቸው ልላካ ቸው" አለ ቴስዮ ።

"ከነገ በስቲያ ነው የምትልካቸው ። ከዚያ በፊት ግንም ሰው ስለዚህ ጉዳይ መስማት የለበትም ። አሁን ከወንድሜ ጋር የቤተሰብ ጉዳይ ስለምነጋገር ውጭ ብት ቆየኝ የጀመርነውን የስም ዝርዝር ጓላ እንጨርሰዋለን ። ጉዳዩን ከከሌሜንዛ ጋር ሆናችሁ ታስፈጽማላችሁ" አለ ሶኒ ።

ቴስዮ ወጣ እንዳለ ሚካኤል ፣

"እንዴት እርግጠኛ ሆነህ ፖሊ ጋቶ ነው ለግለት ቻልክ ?" ሲል ሶኒን ጠየቀው ።

"የኛ የሆኑ ሰዎች ቴሌፎን ኩባንያ ውስጥ ይሰራሉ ። ወደ ፖሊ ጋቶና ከሌሜንዛ ቤቶች የተ ደወሉትን ጥሪዎችና እነሱ ወደ ውጭ የደወሏቸ ውን ቁጥሮች ሁሉ አስመዘገቡን ። ፖሊ ታመምኩ ባለ ባቸው ሶስት ቀናት ከህዝብ ስልክ መደወያ ጥሪ ሲደ ርሰው ነበር ። ዛሬም የሽማግሌው ሹፌር እሱ መሆ ኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሲሉ ይመስላል ደው ለውለት ነበር ። ምናልባት ለሌላም ነገር ሊሆን ይች ላል ። ፖሊ ጋቶ መሆኑ እድለኞች ነን ። በዚህ ቀውጢ ወቅት ከሌሜንዛ በጣም ያስፈልገናል"

ሚካኤል እያመነታ ሙሉ ጦርነት ሊከፈት ታስቦ እንደሆነ ጠየቀው ። የቶም መመለስ ከተረጋገጠ በኋላ፣ አባቱ ሌላ ትእዛዝ ካልሰጠው በስተቀር ቤተሰቡ ባለው ሙሉ ሀይል እንዲዋጋ ግቶዱን ሶኒ ገለጸለት ።

"ታዲያ ለምን የሽማግሌውን መመሪያ አትጠብ ቅም ?" አለ ሚካኤል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶኒ ሚካኤልን በመገረም ተመለከተው ።

"እነዚያን የተዋጊነት ሚዳሊያዎች እንዴት አባክ አድርገህ እንዳገኘሀቸው ይገርመኛል ። በጠመንጃ አፈ ሙዝ ላይ ያለን መሆናችንን አትዘንጋ ። መዋጋት ይኖ ርብናል ። እኔ የምሰጋው ቶምን አይለቁት እንደሆነ ብዬ ነው" አለ ።

ሶሎዞ ቶም ሄገንን የጠለፈው ዶኑ የሞተ መስ ሎት ስለአደንዛዥ እጽ ህገወጥ ንግድ ቶም ሄገን ከሶኒ ጋር ያስማማኛል የሚል ግምት አድሮበት ሲሆን ፣ አሁን ግን የሽግግሌውን ከሞት መትረፍ ስለሰሙ ቶምን ሊገድሉት እንደሚችሉ ሶኒ ለሚካኤል አስረዳው ።

"ከገደሉት እኛን ለማስፈራራት ነው" አለው ።

"ሶሎዞ ካንተ ጋር በድርድሩ እስማማለሁ የሚል ግምት እንዴት አደረበት?" በማለት ሚካኤል ሲጠ ይቀው ሶሎዞ በቤታቸው መጥቶ በነበረበት ወቅት የተነ ጋገሩትን ሁሉ ነገረው ።

"ሶሎዞ ሽግግሌውን ካስወገደ ከእኔ ጋር በሀሳብ የምንስማማ መሰለው ። ሽግግሌው ከሞተ የቤተሰቡ ሀይል ቢያንስ በግማሽ ተቀነሰ ማለት ነው ። ሽግግሌው ያቋቋመውን ንግድም እንዲቀጥል ለማድረግ የሞት የሽ ረት መዋጋት ይኖርብኛል ። አደንዛዥ እጽ ነው ነገ እያ ደገ የሚሄደው ንግድ ። ይህ ሰው በአባታችን ላይ የቃ ጣበት የመግደል ሙከራ ለስራው አመቺ እንዲሆነው ብቻ እንጂ ሌላ የግል ቂም ኖሮበት አይደለም ። ስለዚህ ከንግዱ አንጻር ብመለከተው ኖሮ ከሶሎዞ ጋር መስማ ማት ይኖርብኝ ነበር ። ይሁን እንጂ ፊት ለፊት ብን ገናኝ ይገድለኛል ብሎ ስለሚፈራ በጣም አያስጠጋኝም ። በሌላ በኩል ፣ አንድ ጊዜ ንግዱን ከተቀበልኩ በኋላ ጥቂት አመታት ቆይቼ የበቀል ጦርነት ልቀሰቅስ ብል ሌሎቹ ቤተሰቦች እንደማይፈቅዱልኝ ያውቃል ። በዚህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ የታታሊያ ቤተሰብ የሱ ደጋፊ ነው” በማለት ሶኒ አመለካከቱን ዘርዝሮ ለሚካኤል አስረዳው ።

“ሽግግሌውን ገድለውት ቢሆን ናሮስ ፥ ምን ታደርግ ነበር?” አለ ሚካኤል ።

“ያኔማ የፈለገውን መስዋእትነት ይጠይቅ እንጂ ሶሎዞን የግማ ሰጋ ከማድረግ ወደኋላ አልልም ። እንኳን ከሶሎዞ ጋር ብቻውን ቀርቶ ከአምስቱም ቤተሰቦች ጋር ብዋጋም ግድየለኝም ። የታታሊያ ቤተሰብ ሙልሙ ተደርጐ መጠረግ አለበት ። አብረን ብንጠፋም ግድየለኝም”

“አባዬ ቢሆን ግን እንዲህ አልነበረም የሚያደርገው”

ሶኒ በቁጣ ፥ “እኔ እሱን እንዳልሆንኩ አውቃለሁ” አለ ። “ግን አንድ ነገር ልንገርህ ፥ የወንድነት ጉዳይ ሲነሳ እንደማንም ሰው ፥ እንዲያውም በተሻለ መንገድ ፥ ተግባሬን በብቃት እንደምወጣ አባቴም ይመሰክራል ። ሶሎዞም ያውቀዋል ፥ ክሌሜንዛና ቴስዮም ። ቆራጥነቴን ያሳየሁት ገና በአስራ ዘጠኝ አመቴ ቤተሰቡ ጦርነት ላይ ሳለ ነበር ። ስለዚህ እንዲህ ባለ ውድድር ላይ አሸናፊው ቤተሰባችን ስለሚሆን ምንም ሲጋት የለኝም ። ያን ሉካ ብራሲን ቶሎ ባገኘሁት ብቻ።”

ሚካኤል በአድናቆት ፥ “ሉካ እንደሚወራለት ጉበዝና የሚደነቅ ሰው ነው?” ሲል ጠየቀ ።

ሶኒ እራሱን በአምንታ ነቀነቀና ፥ “እሱን የሚመስለው ሰው የለም ። ልዩ ነው ። ሶስቱንም ታታሊያ መንድግሞች ዋጋቸውን እንዲሰጣቸው እለቅባቸዋለሁ። ለሶሎዝ ግን እኔ አለሁለት” አለ ።

ሶኒ አልፎ አልፎ የሚያሳየው የአውሬነት ባህርይ ቢኖረውም ውስጡን ደግ መሆኑን ሚካኤል ያውቃል። ጥሩ ሰው ነው ። እንዲህ ያለ ንግግር የሱ ጠባይ አይ

t.me/OLDBOOKSPDF

መስልም ። እንዲገደሉ የጻፉቸው የሰዎች ስም ዝርዝር ደግሞ ሶኒን አዲስ የነገሰ የሮማ ቄሳር አስመሰለው ። ሚካኤል የዚህ ሁሉ ድርጊት ተካፋይ አለመሆኑ ደስ አለው ። በተለይም አባቱ በመትረፉ የበቀል ዘመቻ ውስጥ መሳተፍ አይኖርበትም ። በሱ በኩል የሚያበረ ከተው አስተዋጽኦ ስልክ መመለስ እና መልእክት ማድረስ ፥ ብቻ ይሆናል ። ሶኒና ሽማግሌው ግን በተ ለይ ሉካ ከጐናቸው ከቆመ እራሳቸውን መጠበቅ አያ ቅታቸውም ።

ይህን ጊዜ የሴት ጩኸት ተሰማ ። ጩኸቱ የደስታ ጩኸት ነበር ። ቶም ሄገን ከተያዘበት ተለቆ መጥቷል ። ሄገን እንደማፈር እያለ ሚስቱን ላፍታ ካባበለ በኋላ ወደ ቁም ነገር በመመለስ ወደ ቢሮው አመራ ።

ምእራፍ አምስት

ሶኒ ፥ ሚካኤል ፥ ቶም ሄገን ፥ ክሌሜንዛና ቴሰዮ ከሌሊቱ በአስር ሰአት ከቤቱ ዳር በሚገኘው ቢሮ ተሰባስበዋል ። ቴሬሳ ወደ ቤቷ እንድትሄድ ተደረገ ። ፖሊ ጋቶ ግን እዚያው እንግዳ መቀበያ ክፍል በአይነ ቁራኛ እየተጠበቀ መሆኑን ሳይገነዘበው ቁጭ ብሏል ።

ሄገን ሶሎዞ ያቀረበውን ድርድር በነገራቸው ወቅት እንዴት አድርጐ ሊለቀቅ እንደቻለም አወራላቸው ።

"አይጣልባችሁ ። ያንን እርጉም ቱርክ እንደለመን ኩት ብታዩ ፥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የምሀረት ጥያቄ ባቀርብ እንኳ እንዲህ አልግጠንም ። ሽማግሌው ቢተ ርፍም እናንተን በመዳፌ ስር እንደግስገባለት አሳመ ንኩት ። ሶኒ አትቀየመኝና ካንተ ጋር ከልጅነት ጀምሮ የነበረንን ጓደኝነት እንዲሁም ተተኪ እንደመሆንህ ባባ ትህ መመታት እንዳልተጸጸትክ ሁሉ ወተወትኩለት ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም ሲል ሄገን ሲመለስ ሶኒ እንዴት ዘሎ አቅፎ እንደሳመው ሚካኤል ትዝ አለውና ከሱ ይበልጥ ሁለቱ ሰዎች እንደሚቀራረቡ በመገንዘብ ትንሽ ቀና ።

ሶኒ ስራቸውን እንዲጀምሩ ጥሪ አድርጉ እሱና ቴስዮ የጻፏቸውን የሚገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር እንዲ መለከቱ አቀረበላቸው ።

ፍሬድ በመሀከላቸው እንዲገኝ የሚካኤል ምኞት ነበር ። ነገር ግን ፍሬድ አባቱ በተመታበት ወቅት ካጋጠ መው ድንጋጤ ገና ያላገገመና ሀኪሙ ሙሉ እረፍት ማድረግ አለበት ብሎ ያዘዘ ስለሆነ ሊገኝ እንደማይችል ሶኒ አስረዳው ።

ሄገን በችኮላ አነጋገር እንዲህ አለ፡ "ፍሬዲን ተዉትና ከሁሉም ነገር ነጻ አድርጉት ። ስማኝ ሶኒ ይህ ነገር እስኪ ያበቃ ድረስ ከዚህ ቤት እንዳትወጣ ፤ ሶሎዞን አትናቀው። ከባድ ሰው መሆኑን ለማሳየት መሞከሩ አይቀርም ። ለመሆኑ ሆስፒታሉ ተገቢው ጥበቃ እየተደረገለት ነው?"

"ፖሊሶቹ ዘግተውታል ። የኔ ሰዎች ያለማቋረጥ እንዲጐበኙት አድርጌአለሁ ። ለመሆኑ ስለነዚህ የሰዎች ስም ዝርዝር ምንድነው አስተያየትህ?"

"እግዚአ! በእርግጥ ይህን ጠብ የግል በማድረግ ላይ ነህ ። ዶኑ ቢሆን ሙሉ በሙሉ የንግድ ስራውን የሚመለከት ጉዳይ ብቻ አድርጉ ነበር የሚመለከተው ። ቁልፉ ሶሎዞ ነው ። እሱን ብቻ ማስወገድ እንጂ የታታሊያን ቤተሰብ መንካት የለብህም" በማለት ሄገን አስ ጠነቀቀው ።

ሶኒ የቡድን ሹሞቹን ክሌሜንዛንና ቴስዮን ተመለከተ ።

ቴስዮም "ይህ ጉዳይ አስቸጋሪ ነው" ሲል ፡ ክሌ ሜንዛ ግን ምንም ሀሳብ አልሰጠም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶኒ ወደ ከሌሜንዛ ዞረና "የፖሊ ጋቶን ጉዳይ ለውይይት ማትረቡ አስፈላጊ አይሆንም ። ከዚህ በኋላ ፖሊ እዚህ አካባቢ እንዲኖር አልፈልግም ። የስም ዝርዝርህ ላይ የመጀመሪያው አድርገው" ሲል መመሪያ ሰጠው ።

ወፍራሙ ሹም ፥ ከሌሜንዛም ፥ እራሱን በግንቃነት ትእዛዙን ተቀበለ ።

"የሉካ ብራሲስ ጉዳይ?" አለ ሄገን ። "ሶሎዞ ስለሱ ምንም ስጋት አልነበረውም ። የሱ አለመሲጋት እኔን አስግቶኛል ። ሉካ ሽጦን ከሆነ በእርግጥ ችግር ላይ ነን ። መጀመሪያ ማወቅ ያለብን ጉዳይ ይህ ነው ። ለመሆኑ ከሱ ጋር ለመገናኘት የቻለ ሰው አለ?"

"የለም" አለ ሶኒ ፥ "ሌሊቱን ሙሉ በስልክ ላነ ኘው ሞከርኩ ። ምናልባት አንዷ ጋ አድሮ ይሆናል ።"

ሄገን ቀበል አድርጐ ፥ "ፈጽሞ ከሌት ጋር አያድ ርም ። እመሱን ከከላ በኋላ ወደቤቱ ነው የሚሄደው ። ግይክ ፥ እስክታገኘው ድረስ ስልክ መደወልህን አታቋ ርጥ" አለ ።

ስልኩ የሚጠራ መሆኑ ቢሰማውም ሚካኤል ብራ ሲን ማግኘት አልቻለም ።

ሶኒ ወደ ሄገን ተመልከቶ አማካሪ እንደመሆኑ መጠን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ጠየቀው ።

ሄገን ጠረጴዛው ላይ ካለው ዊስኪ ቀዳና ፥ "አባ ትህ ተነስቶ እስኪመራን ድረስ ከሶሎዞ ጋር መደራደር ይኖርብናል ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ውለታ መግባት ይኖርብን ይሆናል ። አባትህ ሲድን ግን ያለ አንዳች ሞንቀት ጉዳዩን መልክ ያስይዘዋል ። ሌሎቹ ቤተሰቦ ችም ውሳኔውን ይቀበላሉ" ሲል ምክሩን ለገሰው ።

ሶኒ በቁጣ ፤

"ይህን ሶሎዞ የሚባል ሰው እኔ ልክ ላስገባው

t.me/OLDBOOKSPDF

አልችልም ግለትህ ነው?" አለ ። ቶም ሄገን ሶኒን አይን አይኑን እያየ ፡

"ሶሎዞን በጸብ ታሸንፈዋለህ ። የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ሀያልነቱ ጥርጥር የለውም ። ክሌሜንዛንና ቴሰዮን ከያ ዝክ ሺህ ጠላቶች ጦርነት ቢከፈቱብህ በቁጥጥርህ ስር ማዋል አያቅትህም ። ነገር ግን መላው የምስራቅ የባህር ዳርቻ በጥፋት ይጥለቀለቅና ሌሎቹ ቤተሰቦች የኮርሌዮኔን ቤተሰብ ማውገዛቸው የማይቀር ነው ። ብዙ ጠላቶች እናተርፋለን ። እንዲህ የመሰለውን ድርጊት አባትህ ፈጽሞ አይደግፈውም" አለው ።

ሶኒ ነገሩን የተቀበለው ይመስላል ። ነገር ግን ፡ "ሽማግሌው ቢሞትስ? ያኔ ምን ትመክረኝ ነበር ፡ ውድ አማካሪ?" በግለት ሄገንን ጠየቀው ።

ሄገንም በጽሞና ሲመልስለት ፡

"እንደማታደርገው አውቃለሁ ። ነገር ግን እኔ የም መክርህ አደንዛዥ እጽን በሚመለከት ከሶሎዞ ጋር ሰም ምንት እንድታደርግ ነው ። ያለአባትህ የፖለቲካ ግንኙነት እና የግል ተጽእኖ ቤተሰቡ ግማሽ ጉልበቱን ያጣል ። አባትህ ከሌለም ሌሎቹ ቤተሰቦች ሌላ የተራዘመ አጥፊ ጦርነት ባለመሻት ታታሊያን እና ሶሎዞን ይደግፋሉ ። አባትህ ከሞተ ከሶሎዞ ጋር ተስማሙ ። ከዚያ በኋላ ዝም ብለህ ጠብቅና የሚሆነውን ተመልከት" አለው ።

ሶኒ በቁጣ ፊቱ ቀላ ።

"ምንታደርግ?" አለ ፡ "የተገደለው አባትህ አይ ደል"

ሄገን ኩራ ብሎ ፈጠን ባለ አነጋገር እንዲህ ሲል መለሰለት ፡

"አንተና ማይክ ለዶኑ ልጆቹ የሆናችሁትን ያህል እኔም ለሱ ጥሩ ነኝ ። ምናልባትም እሻል ይሆናል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ የምሰጥህ የባለሙያ ምክር ነው ። እንደግል ስሜቴ ቢሆን እነዚያን ዲቃሎች እገድላቸው ነበር ።”

የቶም ሄገን ስሜትና አነጋገር ሶኒን አሳፈረውና ፥

“እግዚአ! ምን ነካህ ቶም? እኔኮ እንዲህ ማለቴ አልነበረም” አለው ። ይሁን እንጂ በደም የዶኑ ዘር ባለመሆኑ ከስጋ ዘመድ እኩል እንደማይሆን ሶኒ ያምናል ።

ሌሎቹ አፍረው እንደተቀመጡ ሶኒ ለጥቂት ጊዜ ዝም አለና ፥

“ደህና ። እንግዲያው ሽማግሌው ተነስቶ እስኪመራን በትእግስት እንጠብቃለን ። ቶም ፥ አንተም ከዚህ ግቢ እንዳትወጣ ። ለአደጋ እንዳትጋለጥ ። ማይክ ፥ ሶሎዞ ባንተ ላይ አደጋ ቢያደርስ በሁሉም እንደሚወገዝ ቢያውቅም አንተም ብትሆን መጠንቀቅ ይኖርብሀል ። ቴስዮ ያንተ ሰዎች በተጠባባቂነት ይቆዩ ፥ ግን ከተማዋን ያስሱ ። ክሌሜንዛ ፥ የፖሊ ጋቶን ጉዳይ ካከናወንክ በኋላ ሰዎችህ የቴስዮን ሰዎች ተክተው በቤቱና በቀዬው ተሰማርተው ይጠብቁ ። ቴስዮ ያንተ ሰዎች ከሀኪም ቤቱ እንዳይለቁ ። ቶም ፥ ከሶሎዞ እና ከታታሊያም ቤተ ሰቦች ጋር ከጧት ጀምረህ በስልክ ወይም በመልእክተኛ መደራደር ጀምር ። ማይክ ፥ ነገ አንድ ሁለት የክሌሜንዛን ሰዎች ይዘህ ሉካ ቤት ሂድና እስኪመለስ ጠብቀው ። ካልሆነም የት አባቱን እንዳለ ተከታትለህ ድረስበት ። ያ እብድ ዲቃላ ወሬውን ሰምቶ ከሆነ ሶሎዞን ማሳደድ ጀምሮ ይሆናል ። ከዚያ ሌላ ያ ቱርክ የፈለገውን ነገር ቢሰጠው ዶኑን ይከዳዋል ብዬ ፈጽም አልጠረጥረውም” በማለት ለሁሉም የስራ ድርሻውን ደለደለ ።

ሄገን እየተጠራጠረ ፥ “ሚካኤል በዚህ ውዝግብ ውስጥ በቀጥታ ባይሰማራ ይሻል ይሆናል” አለ ። ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

አባባል ሚካኤል ለቤተሰቡ ምን ያህል ባእድ እንደሆነ እዚያ ያሉት ክሌሜንዛና ቴስዮ ሞምር እንዲገምቱ ቢያደርጋቸውም ፡ ንቀታቸው እንዳይታወቅ አስተያየት ከመስጠት የተቆጠቡ መሆናቸው እየተሰማው ፡ ምንም ሳይናገር ሉካ ብራሲን ለማግኘት ስልክ መደወሉን ቀጠለ ።

ምእራፍ ስድስት

ፒተር ክሌሜንዛ ሌሊቱን ጥሩ እንቅልፍ ሳይተኛ ነበር ያደረው ። ጧት ተነስቶ ቁርሱን እምፖቲቶ ከበላ በኋላ አንድ ብርጭቆ ብራንዲ ጠጣበት ። ቀጥሎም በትልቅ መጠጫ ሙሉ ቡና ኮሬንቶ አከለበት ። ፒጃማውን ለብሶ ክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲል የእለቱን ስራውን በጽሞና ያሰላስል ነበር ። ትላንት ማታ ፖሊ ጋቶ መገደል እንዳለበት ሲወሰን ውሳኔው ባስቸኳይ እንዲፈጸም ትእዛዝ ደርሶታል ። ስለዚህ ዛሬ መሆን ሊኖርበት ነው ። ጋቶ ለክሌሜንዛ አብሮት የቆየ የቅርብ የበታቹ ሆኖ ሳለ ወደ ከሀዲነት በመለወጡ ምክንያት ሳይሆን የግድያው አፈጻጸም በቅንብር መመራት ያለበት በመሆኑ ክሌሜንዛ ተሸበረ ። የቅርብ ግንኙነቱ ወይም የከሀዲነቱ ጉዳይ ክሌሜንዛን የሰው ልክ አያውቅም አያሰኝም ። ፖሊ ጋቶ ከሲሲሊያዊ ቤተሰብ መወለዱ ፡ ከኮርሌዮኔ ልጆች ጋር በአንድ ሰፈር ማደጉ ፡ ከዶኑ ልጅ ጋር አንድ ትምህርት ቤት መማሩ ፡ በያንዳንዷ የእድገት አንጓ በስርአት ተኮትኩቶ ማደጉ ፡ ችሎታው ተፈትኖ ብቁ መሆኑ ፡ ኋላም ሲጠነክር በቤተሰቡ ተልእኮ ላይ ተሰማርቶ ለጥሩ ኑሮ የበቃ ደመወዝተኛ መሆኑ ፡ ከኢሰት ሳይድ ቁማር ንግድ ባለድርሻነቱ ፡ የሙያ ማህበሩ ድብቅ ደመወዝተኛ መሆኑ ፡ ይህ ሁሉ ታማኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊያደርገው ይገባ ነበር ። ከቤተሰቡ መመሪያ ውጭ ቢሆ
ንም ፖሊ ጋቶ በትርፍ ጊዜው በዝርፊያ ላይ እየተሰማራ
ገቢውን እንደሚያዳብር ቢታወቅም ፥ ይህ ጥፋት እራሱ
ልጓሙን ሊበጥስ እንደሚቃጣ መልካም ፈረስ እንደሚያስ
ቆጥረው ክሌሜንዛ ያውቃል ። በእርግጥ ፖሊ ጋቶ በዝ
ርፊያ ተግባር ላይ ቢሰማራም ፥ ዝርፊያዎችን በጥንቃቄና
በእቅድ ስለሚያካሂድ ፥ ሰዎችንም ስለማይጐዳ ፥ ችግር
አልተከሰተም ። በማንሀተን ልብስ መሸጫ ለደመወዝ
የተቀመጠ ሶስት ሺህ ብር ዘረፈ ፥ በብሩክሊን ጉራንጉር
ውስጥ የምትገኝ አነስተኛ የሸክላ እቃዎች ፋብሪካ
ውስጥ ለደመወዝ የተዘጋጀ ገንዘብ ዘረፈ ። እንደሚታ
ወቀው ማናቸውም ወጣት ተጨማሪ የኪስ ገንዘብ
ያስፈልገዋል ። ይህ ሁሉ ግልጽ እየሆነ ፥ ማን እሱን
ከሀዲ ይሆናል ብሎ ሊገምት ይችላል?

ክሌሜንዛን ያሳሰበው የጋቶ መሞት ሳይሆን ፥
ማነው የሱን ቁልፍ ቦታ የሚተካው የሚለው አስተዳ
ደር ነክ ጥያቄ ነበር ። ተተኪው ጮሌና ጠንካራ መሆን
ይኖርበታል ። በተልእኮው ላይ ፖሊስ ቢይዘው የማይለ
ፈልፍ ፥ 'አሜርታ' የተባለው ሲሲሊያዊ የዝምታ ህግ
የተዋሀደው ሊሆን ይገባል ። ያ ተተኪስ ምን ያህል
ነው ገቢው መሆን ያለበት? የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆ
ነው ዋናው ተልእኮ ፈጻሚ ሰው የሚከፈለው ማበረታቻ
ከፍ ማለት እንዳለበት ክሌሜንዛ ለዶኑ ቢያሳስብም ዶኑ
ጉዳዩን አዳፍኖታል ። ፖሊ ጋቶ ከዶኑ ብዙ ገንዘብ
ማግኘት ችሎ ቢሆን ኖሮ ምናልባት ለተንኮለኛው ሶሎዞ
ድለላ አይሸነገልም ነበር ።

ክሌሜንዛ ፖሊ ጋቶን የሚተኩ ሶስት ተወዳዳሪ
ዎች መረጠ ። የመጀመሪያው በጥቁሮች ሰፈር የቁማር
ቤት ውስጥ በአስገዳጅነት የሚሰራ ፥ በአጭሙ ግራኪ
የሆነ ፥ ተግባቢነትን የተቀዳጀ ፥ ሲያስፈልግም አስፈሪና

t.me/OLDBOOKSPDF

ጨካኝ መሆን የሚችል ወጠምሻ ነው ። ነገር ግን ሰው ዱው ከጥቁሮች ጋር በጣም ስለሚገባባ በባህርይው ላይ እንከን አያጣም በሚል ሰበብ ፥ እንዲሁም በያዘው ቦታ ላይ ሌላ ሰው ለመተካት ቀላል እንደማይሆን በመገመት ፥ ከሌሜንዛ ሰሙን ከዝርዝሩ ላይ ሰረዘው ።

ከሌሜንዛ ብቁ ነው ብሎ ሀሳቡን ሊያሳርፍበት የቃጣው ሁለተኛው እጩ በድርጅቱ ውስጥ በትጉህ ሰራተኝነትና በታማኝነት ያገለገለ ፥ በቤተሰቡ ፈቃድ አራጣ ከሚያበድሩ ሰዎች በወቅቱ ያልገባ ገንዘብ የሚ ሰበስብ ፥ ቀድሞ በውርርድ አካሂያጆች ዘንድ ተላላኪ በመሆን ስራውን የጀመረ ግለሰብ ነበር ። ይሁን እንጂ ይህ ሰው ከፖሊ ጋቶ ቦታ ላይ ለመድረስ ገና የሚቀ ረው እንደሆነ ገመተ ።

በመጨረሻ የክሌሜንዛ ምርጫ በሮኮ ላምፖኔ ላይ አረፈ ። ሮኮ ለአጭር ጊዜ ብቻ ያገለገለ ቢሆንም ፥ በዚሁ ወቅት ረዳት ሆኖ ሲሰራ የቤተሰቡን በጐ ስሜት ሊገርክ ችሏል ። በጦርነቱ ወቅት በአፍሪካ ዘምቶ በ1943 ቆስሏል ። አንካሳነቱ በግልጽ ታውቆ ሲንገላወድ እያየ ክሌሜንዛ ሮኮን የመረጠበት ምክንያት በወቅቱ በነበረው የልጅ እገሮች እጥረት ነበር ። ክሌሜንዛ ይህን ሰው የሚጠቀ ምበት በጨርቃ ጨርቅ ሱቆች ለሚካሄድ ኮንትሮባንድ ገበያ ፥ እንዲሁም የቁጥጥር አስተዳደር ሰራተኞች በም ገብ እደላ የቲኬት ቁጥጥር ሲያካሂዱ ፥ በአገናኝነት እንዲያገለግለው ነው ። ከዚህ ልምዱም ለእርቅ አስቸ ጋሪ የሆኑ ጉዳዮችን የመፍታታ ችሎታ አዳበረና የዚህ አይነት ጉዳዮች ፈቺ ሆነ ። ከሮኮ ባህርያት ክሌሜንዛ የሚወደው ጥሩ ግምቱን ነው ። ከበድ ያለ የገንዘብ ትጣት ወይም ስድስት ወር መታሰር ይደርስብኛል በማለት ኋላ የሚገኘውን ትልቅ ጥቅም በመርሳት ጉትር መሆን ምንም ጥቅም እንደማያስገኝ ያውቃል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀገ ወጥ ንግድ የሚያስፈራ አለመሆኑን የተገነዘበ ጠን
ካራ ልቡና ስላለው አጠቃላይ እንቅስቃሴውን ለመም
ራት የሚያስፈልገውን ቁልፍ ጨብጧል ።

ክሌሜንዛ የንዚህን ሰዎች ብቃት ተንትኖ ውሳኔ
ላይ ከደረሰ በኋላ ፥ ውስብስብ የሆነ የሰራተኛ ችግርን
መፍታት የቻለ ጥንቁቅ አስተዳዳሪ የሚሰማው የመ
ላገል ስሜት ተሰማው ። ስለዚህ ሮኮ ላምፖኔ ነው ረዳቱ
የሚሆነው ።

ክሌሜንዛ የፖሊ ጋቶን ጉዳይ የመፈጸሙን ተልእኮ
እራሱ ለማከናወን የሚፈልግበት ምክንያት ልምድ
አልባ የሆነው ሮኮ እራሱን ችሎ ለመስራት ድፍረት
እንዲያበጅ ለመርዳት ብቻ አይደለም ። ከፖሊ ጋቶ
የሚከፈለው እዳ አለ ። ፖሊ ለክሌሜንዛ የቅርብ ተከታ
ዩና ረዳቱ እንዲሆን ያሳደገው ከብዙ ታማኞች እና
እድገቱ ከሚገባቸው ሰዎች መሀል እሱን መርጠት
ነበር ። ፖሊ እራሱን እንዲችልና ወኔ እንዲያበጅ እንዲ
ሁም በተግባሩ እንዲበለጽግ ረድቶታል ። ስለዚህ ፖሊ
ቤተሰቡን ብቻ አይደለም የከዳው ። አለኝታውንና ለወግ
ያበቃውን ክሌሜንዛንም ጭምር ነው ። ይህ የሰውን
ክብር ማሳጣት ብድሩ መመለስ አለበት ።

ሁሉም ነገር ተደራጅቷል ። ፖሊ ጋቶ እንዳይነቃ
ክሌሜንዛን በራሱ መኪና ከሰአት በኋላ በዘጠኝ ሰአት
ላይ እንዲያጓጉዘው መመሪያ ተሰጥቶታል ። ክሌሜንዛ
ለሮኮ ላምፖኔ ደውሎ ፥

"እኔ ቤት እንድትመጣ ። የምልክህ አለኝ" አለው ።
ሮኮ በግለዳ ቢደወልለትም ድምጹ ውስጥ እንቅልፍ
የለም ። ሳይደናገጥ "እሺ" ሲል መለሰ ። ሮኮ ቁርሱንና
ምሳውን በልቶ ከስምንት ሰአት በፊት ክሌሜንዛ ቤት
እንዲደርስ አለቃው በተጨማሪ መመሪያ ሰጠው ።
በሶኒ ትእዛዝ መሰረት ፥ የክሌሜንዛ ሰዎች የቴስዮ ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥበቃ ያደርጉበት የነበረውን የዶኑን ቤትና አካባቢውን ተረክበው ለመጠበቅ እንዲዘጋጁ መመሪያ አስተላልፏል። ብቁ ረዳቶች ስላሉት ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት አያስፈልግም።

ክሌሜንዛ የሚወዳትንና በምኞት የምታጓጉዘውን ካዲላክ መኪናውን ለማጠብ ወሰነ። ከመቀመጫዎቹ ምቹነት የተነሳ፥ ከቤቱ ይልቅ መኪናው ውስጥ ቢቀመጥ ይመርጣል። ድሮ አባቱ በልጅነት አህያውን ይደባብስ እንደነበረው፥ እሱም መኪናውን ሲጠራርጋት ለማሰብ ይረዳዋል። መኪናውን ሙቀት ባለው ጋራዥ ውስጥ ሲያጣጥብ ዛሬ የሚሰራውን ማውጠንጠን ጀመረ። ስለ ፖሊ ጋቶ መጠንቀቅ አለበት። ፖሊ እንደ አይጥ አደጋ ማሽተት ይችላል። አሁን እንኳን፥ ምንም ጮሌ ቢሆን፥ ዶኑ በመትረፉ ሽንቱን በሱሪው ላይ ሳይለቅ አይቀርም። ፊንጢጣው ላይ ጉንዳን እንደወጣበት አህያ ይቁነጠነጣል። ነገር ግን ይህን በመሰለ ተልእኮ ላይ ምን ማድረግ እንዳለበት ክሌሜንዛ ጠንቅቆ ያውቃል። በመጀመሪያ ሮኮን ለማስከተል ጥሩ ምክንያት ማግኘት አለበት። ሁለተኛ፥ ሶስቱም የሚሳተፉበት አሳማኝ ተልእኮ ማዘጋጀት ይኖርበታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ፖሊ ጋቶ ያለ አንዳች ውጣ ውረድ ሊገደል ይቻላል። በር ተቆልፎበት በጥበቃ ላይ ያለ ስለሆነ ሊሸሽ አይችልም። ነገር ግን ክሌሜንዛ ጥሩ የስራ ልምድ ማዳበርና ከቶውንም በተልእኮው ላይ አንዳችም ለውጥ እንዳይታይ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለው። እንዲህ በመሰለ ተግባር ላይ ምን እንደሚመጣ ምን ይታወቃል? ተልእኮው የሞት ወይም የሽረት መሆኑ ቀረ?

ክሌሜንዛ መኪናውን ሲያጥብ ነገ የሚያደርጋቸውን ሁሉ በሀሳቡ ደረደረ። ፖሊ ጋቶ ያበሸቀው ይመስል ቆጣ ብሎ መናገር ነው። ተጠራጣሪውን ፖሊ ጋቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያዘናጋዋል መይም በእርግጠኛነት ይህ ነው ብሎ ግሰብ እንዳይችል ያደርገዋል ። ከተገቢው በላይ ወዳጅነት ቢያሳዩትም ሊነቃ ይችላል ። ስለዚህ ብሽቀቱ ልብ ያላሉት እንጂ ቁጣ የሞላበት እንዳይመስል መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ነገር ግን ሮኮ ላምፖኔስ ለምን አብሯቸው ይሄዳል? ፖሊ ይህ በጣም ያሸብረዋል ። በተለይም እሱ እየነዳ ሮኮ ከኋላው ተቀምጦ ሲሄድ የፈለገውን ሊያደርገው ስለሚችል በጣም ይቀፈዋል ። ክሌሚንዛ ይህን ጉዳይ ሲያጤን በቁጣ ተሞልቶ መኪናውን መፈተግ ጀመረ ። ሌላ ሰው መጨመር ያስፈልገው እንደሆንም ላፍታ አሰበ ። አሁን ይህን ቢያደርግ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ታየው ። በሚመጡት አመታት ከተባባሪዎቹ አንዱ በሱ ላይ መመስከር የሚጠቅመው ቢሆን ችግር ላይ ሊጥለው ይችላል ። እንዲህ የሚያደርግ ሰው አንድ ብቻ ከሆነ እዳው ገብስ ነው ። ነገር ግን ሁለት መስካሪዎች ከሆኑ ሚዛኑ ክሌሜንዛን ለመጉዳት ያጋድላል ። ስለዚህ ሮኮ ብቻ መሆን አለበት ።

የፖሊ ጋቶን መግደል ህዝቡ እንዲያውቀው ማድረጉ ግን ክሌሜንዛን አበሳጭቶታል ።

ክሌሜንዛን ያበሳጨው የፖሊ ጋቶ መግደል ሳይሆን አስከሬኑን ሰዎች እንዲያገኙትና ህዝቡ እንዲያውቀው ማድረጉ ነው ። እንደ ክሌሜንዛ ምርጫ ቢሆንማ ኖሮ በአቅራቢያው ካለው ባህር መይም የቤተሰቡ ወዳጅ የሆነ ባለእርስት ንብረት በሆነ ረግረግ ውስጥ መይም በሌላ ውስብስብ ዘዴ እሬሳውን ቢያጠፉ ደስ ባለው ነበር ። ነገር ግን ሌሎች ከሀዲዎች ብቅ ብቅ እንዳይሉ ለማስፈራራት እንዲሁም ከሀዲዎችን የሚመለምል ጠላትም የኮርሌዮኔን ቤተሰብ ንቁነት እንዲገነዘበው ለማድረግ የፖሊ ጋቶ መሞት ይፋ መሆን አለበት ። የሶሎዞ ሰላይ በመጋለጡ ፣ ሶሎዞ ሽማግሌውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመግደል ያደረገው ሙከራ ደደብነት እንደሆነ እንዲ ረዳው ማስገንዘቢያ የሚሆን የቤተሰቡን ክብር መጠበ ቂያ መሆን ይኖርበታል ።

ከሌሜንዛ መኪናውን አጥቦ ወልውሎ ጨረሰና በረሸሙ ተነፈሰ ። ለፖሊ ጋቶ የሚቀርብለት ጥሩ ምክንያት ስለአገኘ ደስ አለው ። በቤተሰቡና በጠላቶቹ መሀከል ጦርነት ከተከፈተ ቤተሰቡ አድራሻውን ቀይሮ የሚያደፍጥበት ሰዋራ ቤት ማዘጋጀት ስለሚያስፈልግ ፣ ለዚህ አገልግሎት የሚውል ቤት ለመምረጥ ሶስቱ እንደሚዘዋወሩ ለፖሊ ጋቶ ይነግረዋል ።

የቤተሰቦች ጠብ ሲነሳ ቤተሰቦች አድራሻቸውን ከነ በሩበት ስፍራ ይለውጡና የምስጢር ቦታ ያበጃሉ ። በዚህ ወቅት በአልጋ ላይ መተኛት ይቀርና የጦርነቱ ተካፋ ዮች ይፈርሻሉ—መኝታቸው መሬት ላይ ይሆናል ።

የፍረሻ አላማው በጠቡ ለማይሳተፉት ለቤተሰቡ አባላት ደህንነት ከለላ ለመስጠት አይደለም ። እነሱን የሚነካቸው የለም ። እንደዚህ ያለ ሙከራ ከተጀመረ ብድር መመላለስ ማስከተሉ ስለሚያስፈራ ፣ ማንኛውም ወገን ሴቶችን ፣ ልጆችን እና በበቀል እርምጃው ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፉትን የጠላት ቤተሰብ አባላት አይነ ካም ። ነገር ግን በጦርነቱ ውስጥ የሚሳተፈው አባል ወደ ቤተሰቡ መግባት መውጣቱ ስለማይቀር በተለመደ መኖ ሪያው ከቀጠለ ለአደጋ ስለሚጋለጥ ፣ ወይም ጣልቃ ለሚ ገባ ፖሊስ ክትትል ስለሚያመች ፣ እንዲህ ከመሰለው አደጋ ፍጹም የሆነ ከለላ እንዲኖረው ለማመቻቸት ነው ። ስለዚህ የቤተሰቡ ታማኝ ሹም ይመረጥና ለፍረሻ የሚ ሰማማ ቦታ ተከራይቶ ክፍሉን ወይም ክፍሎቹን በፍ ራሽ ይሞላል ። የፍረሻው ቤት ለፍልሚያው አስፈላጊ መመሪያ የሚወጣበት ማእከል ይሆናል ።

ከሌሜንዛ ይህን በመሰለ ተልእኮ መውጣቱ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲሄድም ፖሊ ጋቶንና ሮኮ ላምፖኔን ማስከተሉ የተለ መደ አሰራር ነው ። ክሌሜንዛን ሌላው ፈገግ ያሰ ኘው ጉዳይ ፡ ፖሊ ጋቶ ለዚህ ተልእኮ እንደሚወጡ ሲነገረው የሚሰማው ደስታ ነው ። ጋቶ የፍረሻውን ቦታ ለሶሎዞ ከጠቆመ ሶሎዞም ለዚህ እጅግ ጠቃሚ ጥቆማ የሚሰጠው ሽልማት ሲታሰበው ደስታው አናቱን ፈን ቅሎ መውጣቱ የማይቀር ነው ።

ሮኮ ቀደም ብሎ በተቃጠሩበት ሰአት ሲመጣ ስለ ተግባራቸውና ስለነሱ ሚና ማብራሪያ ሰጠው ። ሮኮ የፖሊ ጋቶ ቦታ እንደተሰጠው ሲነገረው በደስታ ሲቃ ተሞልቶ ፊቱ በራ ። ክሌሜንዛንም ስለሰጠው እድገት አመሰገነው ።

"ካዛሬ ጀምሮ ለመተዳደሪያህ የተሻለ ነገር ታገኛ ለህ ። እንደምታውቀው በአሁኑ ወቅት ቤተሰቡ በጣም አስጊ በሆነ ሁኔታ ላይ የተጠመደ ስለሆነ ያንተን ገቢ በሚመለከት ወደፊት ነው እምንነጋገረው" አለው ።

ላምፖኔ ከተሰጠው እድገት አንጻር የጥቅሙ መም ጣት የማይቀር መሆኑን በመረዳት ታግሶ የሚጠብቅ መሆኑን ለማረጋገጥ እራሱን ነቀነቀ ። ክሌሜንዛ በስውር ክፍሉ ውስጥ ካለው ካዝና ሽጉጥ አውጥቶ ለላምፖኔ ሰጠውና ፡

"በዚህ ተጠቀም ። የማን እንደሆነ ፈጽሞ ሊያገ ኙት አይችሉም ። ከፖሊ ጋር መኪናው ውስጥ ተወው ። ይህን ስራህን ካጠናቀቅክ በኋላ ሚስትህንና ልጆችህን ይዘህ ፍሎሪዳ ለእረፍት ሂድ ። በራስህ ገንዘብ ተጠቀ ምና ኋላ እተካልሀለሁ ። ሄደህ ተዝናና ፡ ጸሀይ ጥገብ ። ምናልባት የፈለግኩህ እንደሆነ ላገኝህ እንድችል ሚያሚ በሚገኘው የቤተሰቡ ሆቴል እረፍ" አለው ።

የክሌሜንዛ ባለቤት የድብቅ ክፍሉን በር አንኳኩታ ፖሊ ጋቶ መምጣቱን ነገረቻቸው ። ጋቶ መኪናውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ክሌሜንዛ ቤት መግቢያ መንገድ ላይ አቁሟታል ። ክሌሜንዛ ላምፖኔን እየመራው ተከታትለው በጋራዡ በኩል ወጡ ። መኪናውን ሲሳፈር የኩርፊያ ሰላምታ ሰጥቶት ገባ ። ምናልባት ጋቶ ዘግይቶ እንደሆነ ለማረ ጋገጥ ይመስል ሰአቱን ተመለከተ ። ጋቶ ስለ ሁኔታቸው ለመረዳት ምልክት ለማግኘት ክሌሜንዛን በጥንቃቄ ይመለከተው ነበር ። ላምፖኔ ከኋላው ሲቀመጥ ጋቶ ትንሽ ደንገጥ አለና ፡

"ሮኮ ፡ ከኔ ጀርባ በትክክል አትቀመጥ ። በኋላ መስታወት በኩል እንዳይታየኝ ትከልለኛለህ" አለው ። ሮኮ ላምፖኔም እንዳይነቃበት ምንም ሳይከራከረው ወደ ክሌሜንዛ በስተጀርባ ፈቀቅ አለ ።

ክሌሜንዛ በምሬት ወደ ፖሊ አቃንቶ ፡

"ያ ሶኒ በጣም ፈርቷል ። አፈር ይብላ! ካሁኑ መፈረሽ አለብን ነው የሚለው ። በምእራብ ክፍለ ከተማ ነው ቤት መፈለግ ያለብን ። ፖሊ እና ሮኮ አስፈላጊ ውን ሁሉ ማሟላት ይኖርባችኋል ። ለመሆኑ ተስማሚ ቦታ መጠቆም ትችላላችሁ?" በማለት ጠየቃቸው ። ክሌሜ ንዛ ቀድሞውኑ እንደገመተው ፖሊ ጋቶ ይህን ሲሰማ አይኑ በጉጉት ተቁለጨለጨ ። ፖሊ ተሸወደ ፡ ይህ ዜና ለሶሎዞ ምን ያህል ዋጋ ያለው እንደሆነ ሲያሰላስል ፡ እራሱ በአደጋ ላይ ይሁን አይሁን ማሰቡን ረሳ ። ሮኮ ላምፖኔ ጉዳዩን ፈጽሞ ያላጤነው ለማስመሰል እንደ ማይሰማ በመስኮት ውጭ ውጭ ይመለከታል ። የሮኮን ተዋናይነት ሲመለከት ክሌሜንዛ እሱን የፖሊ ጋቶ ተተኪ አድርጐ በመምረጡ ደስ አለው ።

ጋቶ ትከሻውን በመነቅነቅ "እስኪ ላስብበት" አለ ።

ክሌሜንዛ "እየነዳህ አስብ ፡ ዛሬውኑ ኒውዮርክ መድረስ አለብን" በማለት ጋቶ ላይ አጉረመረመ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በፖሊ ጋቶ ብቃት ያለው ሹፍርና፥ መንገዱም በትራፊክ ካለመጨናነቁ የተነሳ የከረምት ጭለማ ገና ሲጀምር ከተማ ደረሱ። በመኪናው ውስጥ ንግግር አልነበረም። ክሌሜንዛ ፖሊን ወደ ዋሽንግተን ሄይትስ እንዲነዳ አዘዘው። ጥቂት ፎቆችን ካማተረ በኋላ አርተር ጐዳና ተብሎ ከሚጠራው መንገድ ላይ መኪናውን እንዲያቆማት አዞት ሁለቱም መኪናው ውስጥ እንዲጠብቁት ነግሯቸው ወጣ። ቬራ ማርዮ ምግብ ቤት ገባና ከጥጃ ሲጋና ከአትክልት የተሰራ ቀለል ያለ እራት ተመገበ። ከአንድ ሰአት በኋላ ተመልሶ ቆማ ከምትጠብቀው መኪና ውስጥ ገባ። ጋቶ እና ሮኮ እንደታዘዙት ይጠብቁት ነበር።

"እንዲያው ወዲያ!" አለ ክሌሜንዛ የተበሳጨ ይመስል፤ "ሎንግ ቢች እንድንሄድ ይፈልጉናል ደግሞ። አሁን የተፈለግንበት ሌላ ስራ አለ ነው የሚሉት። ይህኛውን ኋላ ትቀጥላላችሁ ነው የሚለው ሶኒ። ሮኮ፥ አንተ እዚህ ከተማ ነው የምትኖረው። ስለዚህ እዚህ እናውርድህ?"

"መኪናዬን አንተ ቤት ትቻታለሁ። ሚስቴ ጧት ትፈልጋታለች" አለ ሮኮ።

"ደግ፥ እንግዲያስ አብረኸኝ ተመለስ" አለው ክሌሜንዛ።

ወደ ሎንግ ቢች የመልሱ ጉዞ ዝምታ የሰፈነበት ነበር። እከተማው ሊደርሱ ሲሉ፥

"ፖሊ፥ አቁም ሽንቴ መጠረኝ" አለው ክሌሜንዛ። ፖሊ አለቃው ፊኛው ብዙ መቋጠር እንደማይችልና ቀድሞም ቢሆን መንገድ ላይ አቁምልኝና ልሽና እንደሚል ያውቃል። ከመንገዱ ወጣ አድርጐ ወደ ረግረግ ከሚያመራው ደረቅ መሬት ላይ አቆመለት። ክሌሜንዛ ጥቂት ራመድ ብሎ ከቁጥቋጦው ላይ እንዳለው ሽንቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሸና ። ሲመለስም መኪናውን እየከፈተ ከፊትም ሆነ ከኋላ መኪና አለመኖሩን ቶሎ አየት አደረገ ። መብራት አይታይም ፥ መንገዱ ሙሉ ጭለማ ነው ።

"በል ቀጥል" አለ ከሌሜንዛ ።

ከሴኮንድ በኋላ መኪናዋ በጥይት ድምጽ አስተጋባች ። ፖሊ ጋቶ ወደፊት የዘለለ ይመስል ሰውነቱ ወደ መሪው ተወረወረ ። ከዚያም ተዝለፍልፎ ወንበሩ ላይ ዘቀጠ ። ክሌሜንዛ የፈነዳው የፖሊ አንጐል አጥንት ፍንጣሪ እና ደሙ እንዳይነካው ቶሎ ወደ ኋላ ፈቀቅ አለ ። ሮኮም ከኋላው መቀመጫ ዘሎ ለመውጣት ተጣ ደፈ ። ይዞት የነበረውን ሽጉጥ ረግረጉ ውስጥ ጣለው ። እሱና ክሌሜንዛ ራመድ ራመድ አሉና በአቅራቢያው ይጠብቃቸው የነበረ መኪና ውስጥ ገቡ ። ሮኮ መኪናውን አስነሰቶ ክሌሜንዛን ወደ ቤቱ አደረሰው ። በመጣበት መንገድ በመሄድ ፋንታ ሌላ መንገድ ተከትሎ በሌሎች ከተሞችና መንደሮች አቋርጦ ቤቱ ከሚገኝበት ከማን ሀተን ደረሰ ።

ምእራፍ ሰባት

ዶን ኮርሌዎኔ በተተኩሰበት እለት ዋዜማ ፥ በጉብዝናው ፥ በታማኝነቱና በአስፈሪነቱ የታወቀው የዶኑ ዋና አሽከር ሉካ ብራሲ ከጠላት ጋር ሊገናኝ ተዘጋጀ ። ሉካ ብራሲ በዶኑ ትእዛዝ የሶሎዞን ሰዎች ማነጋገር ከጀመረ ወራት አልፈዋል ። ይህ ሰው የተሰጠውን ተል እኮ ለመወጣት እንዲያስችለው የታታሊያ ቤተሰብ ንብረት በሆነ ሆቴል ውስጥ አንዲት ሴት ጋ መመላለስ አዘወተረ ። ከሴትየዋ ጋር በሚተኛበት ወቅት የኮርሌዎኔ ቤተሰብ የአገልግሎቱን ትክክለኛ ዋጋ ሳይገነዘብ ጨቁኖት እንዳለ ያወራላታል ። ለአንድ ሳምንት ያህል በኮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ርሌዎኔ ቤተሰብ ላይ ያለውን ቅሬታ ሲያወራ ከሰነበተ በኋላ ፥ አንድ ቀን የሆቴሉ ስራ አስኪያጅ የሆነው ብሩኖ ታታሊያ አነጋገረው ። የታታሊያ የመጨረሻ ልጅ የሆነው ብሩኖ ህብረተሰቡ በሽርሙጥና ንግድ ላይ የማይካፈል መሆኑን እንዲረዳለት ጥረት ያደርጋል ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን በመለሎ ወጣቶች የተሞላው ዝነኛ የማታ ክበቡ በከተማው ለሚሰማሩ ሴተኛ አዳሪዎች መመረቂያ ትምህርት ቤት ነው ።

ለመጀመሪያ ቀን ብሩኖ ሉካን ሲያነጋግረው በታታሊያ ቤተሰብ ተግባር ውስጥ በስነ ስርአት አስከባሪነትና በአስገዳጅነት እንዲያገለግል ለብራሲ ስራ የሚሰጠው መሆኑን ገለጸለት ። ሉካ ብራሲ ለተልእኮው ፥ ብሩኖም ለዘዴው አንዱ ሌላውን ሊያታልል ሲሞክር ፥ በዚህ ሁኔታ ይሽው መላላጥ ለወር ያህል ቀጠለ ። ሉካም በአንዲት ወጣት ፍቅር የናወዘ መስሎ ቀረበ ። ብሩኖ በዚሁ አጋጣሚ ተጠቅሞ አንድ ጠቃሚ የሆነ ተልእኮ ፈጸሚ ሰው ከተፎካካሪው ላይ ለማስኮብለል ጥረት የሚያደርግ መሰለ ። በአንድ ስብሰባ ላይ ሉካ ብራሲ እሺ ለማለት የጀመረ መሰለ ።

"አንድ ነገር ግልጽ መሆን አለበት ። ዶኑን በጣም አከብረዋለሁ ። በቤተሰቡ ተግባር ላይ ከኔ ይልቅ ልጆቹን ማስቀደም እንዳለበት ይገባኛል ። ስለዚህ እሱን አልቃወመውም" ሲል ሉካ ተናገረ ።

ብሩኖ ታታሊያ ፥ እንደ ብዙዎቹ ወጣቶች ፥ ሉካ ብራሲንና ዶን ኮርሌዎኔን ፥ ሌላ ቀርቶ የራሱንም አባት የመሰሉ ወግ አጥባቂዎችን በግልጽ ይንቃቸዋል ። ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት ዘዴኛ መሆኑን መርጧል ።

"አባቴም ቢሆን በኮርሌዎኔ ላይ ጉዳት እንድታደርስ አይፈልግም ። ለምንስ ይፈልግ? ሁሉም ሰው እርስ

t.me/OLDBOOKSPDF

በርሱ እየተሰማማ ነው ፥ የድሮው አይምሰልህ ። ምናባት አዲስ ስራ ትፈልግ እንደሆነ ላባቴ ልንገርልህ ብዬ ነው ። የኛ ንግድ ስራ ከባድ ስለሆነ ጠንካራ ሰዎች ያስፈልጉናል ። ስለዚህ ባንተ በኩል ስራውን የምትሻ ከሆነ ንገረኝ" አለው ።

ሉካ በግድ የለሽነት ትከሻውን ነቅንቀና ፥

"ያለሁበት ቦታ እስከዚህም መጥፎ አይደለም" አለው ። የዚያን እለቱ ንግግራቸው በዚሁ አበቃ ።

ሉካ ብራሲ የዶን ኮርሌዎኔ ቤተሰብ እንደሚበድለው ቀደም አድርጎ ለዚያች ከነገረ በኋላ ዛሬ ደግሞ ብሩኖ ታታሊያ ስራ ላሰጥህ ሲለው ሌላ አዲስ ስራ ለማግኘት ግድ እንደሌለው የገለጸለት ለብልሀቱ ነበር ። ሉካ ይህን ስራ አልቀበልም ካለ ብሩኖ በሌላ ዘዴ እጁ ውስጥ ለማስገባት መጣሩ አይቀርም ። ምናልባትም የአደንዛዥ እጽ ሀገ ወጥ ንግድ ጥቅም ስለሚያጓጓው በዚህ ስራ ላይ ያሰማራው ይሆናል ። በዚህ ዘዴ ሶሎዞ በአደንዛዥ እጽ ላይ ምን አይነት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳለ ወይም ተስፋ ቆርጦ ዶኑን ለማጥፋት እቅድ እንዳለው ለማወቅ ይችል ይሆናል ። ሉካ ሁኔታውን ለሁለት ወራት ያህል ቢከታተልም ምንም ፍንጭ አጣ ። ስለዚህ ዶኑ እምቢ ስላለው ሶሎዞ ቂም አድሮበት ክፉት ያስብ እንደሆን ለማወቅ ባደረገው ክትትል አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ። ሶሎዞ የዶኑን እምቢታ በጸጋ ተቀብሎታል ብሎ አመነ ። ይህንኑ ለዶኑ ሲነግረው ዶኑ አሁንም መከታተሉን እንዲቀጥል አዘዘው ።

ዶኑ በተተኮሰበት እለት ዋዜማ ምሽት ሉካ ብራሲ ከዚያች የማታ ክበብ ብቅ አለ ። ወዲያው ብሩኖ ታታሊያ ሉካ ከተቀመጠበት ወንበር አጠገብ መጥቶ ቁጭ አለና ፥

"ሊያነጋግርህ የሚፈልግ ወዳጅ አለኝ" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አምጣው እዚህ ። ያንተ ወዳጅ ከሆነ አነጋግረ ዋለሁ" ሲል ሉካ መለሰለት ።

"አይ ፥ ሰውዬው በግል ሊያነጋግርህ ነው እሚፈ ልገው"

"ማነው እሱ?"

"የኔ ወዳጅ የሆነ ሰው ነው ። አንድ ሀሳብ ሊያቀ ርብልህ ይፈልጋል ። ኋላ ዘግየት ብለህ ልታነጋግረው ትችላለህ?"

"በእርግጥ እችላለሁ ። በስንት ሰአት ፥ የትስ ነው የምንገናኘው?" ሲል ሉካ ጠየቀ ።

ብሩኖ ታታሊያም በለሆሳስ ፥ "ከበባችን ሊነጋጋ ሲል አስር ሰአት ላይ ነው የሚዘጋው ። ሰራተኞች ክፍሉን ሲያጸዱ እዚሁ ለምን አታነጋግረውም?" አለው ። የሉ ካን ልማድ ስለሚያውቁት ለሱ ተስማሚ ጊዜ ያደራጁ ለት መሰለው ። ሲከታተሉትና ሲያጠኑት ቆይተዋል ። ዘወትር ከሰአት በኋላ ወደ አስር ሰአት ላይ ከመኝታው ተነስቶ 'ቁርሱን' ይበላል ። ከዚያ በኋላ ከዶኑ ግቢ ካሉት የድሮ ወዳጆቹ ጋር ቁማር ሲጫወት ወይም ከሴት ጋር ሲደሰት ያመሻል ። አንዳንዴ እኩለ ሌሊት ላይ የሚታይ ሲኒማ ይመለከታል ። ከዚያም ካንዱ ክበብ ገብቶ ይጠጣል ። ሊነጋጋ ካላለ ወደ መኝታው አይሄድም ። ስለዚህ የተነገ ረው የቀጠሮ ሰአት ለሌላ ሰው አመች ባይመስልም ከሉካ ልማድ አንጻር ሲታይ ለሱ ይስማማዋል ።

"ደህና ። በአስር ሰአት ሊነጋጋ ሲል እመለሳለሁ" አለ ብራሲ ። ከክበቡ ወጣና በታክሲ ወደ ቤቱ ሄደ ። የሚኖረው በባቡር መስመር ዳርቻ ካሉ የሩቅ ዘመ ዶቹ ከሆኑ የጣሊያን ቤተሰቦች ጋር ነው ። ሁለቱ የሱ ክፍሎች በልዩ በር ከነሱ መኖሪያ ተለይቷል ። ይህን የመሰለ አኗኗር በአንድ በኩል የቤተሰብ ኑሮ መኖር ስለሚያስችለው ፥ በሌላም በኩል በቀላሉ ሊጉዳ የሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ችልበት ድንገተኛ አደጋ እንዳይጣልበት ምሽግ ስለ ሚሆነው ተስማምቶታል ።

ያ መልቲ ቀበሮ ፥ ሶሎዞ ጭራውን እንደሚቆላ ለሉካ ታየው ። በውይይታቸው ላይ ማወቅ የሚፈልገ ውን ሁሉ ሉካ ማወቅ ከቻለ ፥ ለዶኑ የሚያቀርበውን የገና ስጦታ አገኘ ማለት ነው ።

ሉካ ከቡና ቤቱ እንደወጣ በቀጥታ ወደ ቤቱ ሄዶ ፥ ጥይት የማያዘልቀው ኒናቴራ ከውስጥ ከለበሰ በኋላ ፥ ተራ ኒናቴራ ፥ ሸሚዝና ኮት ደረበበት ። ከዚህ በኋላ ሁኔታውን ለዶኑ ለማሳወቅ ፈልጐ ነበር ። ነገር ግን ዶኑ ማንንም በስልክ አያነጋግርም ። ለቶም ወይም ለሶ ኒም እንዳይነግር ፥ ይህ ጉዳይ ለሉ ብቻ በሚስጥር የተ ሰጠው ተልእኮ በመሆኑ ለማንም ሊነግር አልፈለገም ።

ሉካ ሁሌ ሽጉጥ ይይዛል ። የያዘው ህጋዊ የመሳሪያ ፈቃድም አስር ሺ ብር የተከፈለበትና ፖሊስ ቢይዘው ከእስር ነጻ የሚያደርገው ነው ። ለዛሬ ግን የሚይዘው ሽጉጥ ባለ ፈቃዱን ሳይሆን ሌላውን ነው ። ድንገት ሰዎቹን መግደል ቢያስፈልግ የእገሌ ነው ተብሎ ሊያ ጋልጥ የማይችል ሽጉጥ መያዝ አለበት ።

ሊያስብበት ግን በዚያን እለት የሚነገረውን ሀሳብ ሰምቶ ለዶኑ ከመንገር በስተቀር ጦርነት መክፈት አስ ፈላጊ መስሎ አልታየውም ።

በቀጠሮው መሰረት ወደ ክበቡ ሲሄድ ምንም ተጨማሪ መጠጥ አልጠጣም ። ይልቁንም ከሚያዘወት ርበት የጣልያን ምግብ ቤት ገብቶ ራቱን ከበላ በኋላ የቀጠሮው ሰአት ሲደርስ ወደ ክበቧ ጐራ አለ ። ሲገባ የበሩ ጠባቂ በቦታው የለም ። ክበቡ መግቢያ ላይ ባር ኔጣ ፥ ካፖርትና ጃንጥላ የመሳሰሉትን እቃዎች ተረክባ ደምበኞች እስኪወጡ አቆይታ ሲወጡ መልሳ የምታ ስረክበውም ልጅ ወጥታለች ። ብሩኖ ታታልያ ብቻ ተቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ ሰላምታ ሰጠውና የተወለወሉ ጠረጴዛዎች ብቻ ከተሞሉበት ባዶ ክፍል መራው ።

ሉካ መደርደሪያው አጠገብ ቁጭ ሲል ብሩናም ከመደገፊያው በስተጀርባ ሆኖ የሚፈልገውን መጠጥ ጠየቀው ። ሉካ መጠጥ እንደማይፈልግ ገልጾለት ሲጋራውን አቀጣጠለ ። 'ምናልባት ሌላ ጉዳይ ይሆን?' የሚል ጥርጣሬ የሉካ ብራሲን አእምሮ ለአፍታ ከነከነው ። ወዲያው ግን ሶሎዞ ራቅ ካለው የክፍሉ መጨረሻ አቅጣጫ ከሞለማው ብቅ አለ ።

ሶሎዞ ከጨበጠው በኋላ ከጐኑ ቁጭ ሲል ብሩናም መጠጥ ቀዳለት ።

"ማን እንደሆንኩ ታውቀኛለህ?" አለው ሶሎዞ ።

ሉካ አምን ለማለት እራሱን ነቀነቀ ።

"ትልቅ የምናካሂደው ንግድ ይኖራል ። ይህ ንግድ ከፍተኛ ቦታ ላይ ያለነውን ሁላችንንም ባለሚሊዮን ብር ነው የሚያደርገን ። የመጀመሪያው የመርከብ ጭነት ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ሀምሳ ሺህ ብር እንደሚደርስህ አረጋግጥልሀለሁ ። የምልህ እቃ አደንዛዥ እጽ ነው ። እሱ ነው ባሁኑ ጊዜ ታዳጊው ንግድ" አለው ሶሎዞ ።

"ለምን እኔን ፈለግከኝ? ዶኑን እንዳነጋገርልህ ነው?"

ሶሎዞ ፈገግ አለና ፥ "ዶኑንማ አነጋግሬዋለሁ ። እሱ በአደንዛዥ እጽ ንግድ ውስጥ ሊገባ አይፈልግም ። እኔም ግድ የለኝም ። ያለሱ መስራት እችላለሁ ። ነገር ግን ንግዱን የሚጠብቅ አንድ ጠንካራ ሰው እፈልጋለሁ ። ከዶኑ ቤተሰብ ተስማምቶህ የማትኖር መሆንህን ሰምቻለሁ ። ስለዚህ ወደዚህኛው ስራ ልትሰማራ ትችላለህ" ሲል ሊያግባባው ሞከረ ።

ሉካ አሁንም ምንቸገረኝ ለማለት ትከሻውን ነቀነቀና ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ድርሻዬ ደህና ከሆነ" ሲል መለሰለት ።

ሶሎዞ በጥንቃቄ ይመለከተው ነበር ። ወዲያውኑ ውሳኔ ላይ የደረሰ መሰለ ።

"አስብበትና እንደገና እንነጋገርበት" ብሎ ሶሎዞ ብራሲን ሊጨብጠው ሲል ፣ ብራሲ ያላየ ይመስል ሲጋራውን ወደ አፉ ጨመረ ። ብሩኖ ታታሊያ ከመቅጽበት የሲጋራ ማቀጣጠያ አወጣና ሊለኩሰለት ጠጋ ሲል አንድ አስደናቂ ተግባር ፈጸመ ። ብሩኖ ላይተሩን ጣለውና የሉካን ቀኝ እጅ ለቀም አድርጎ አጥብቆ ያዘው ።

ሉካ ወዲያው ከመቀመጫው ላይ ተነሳና የተጠመዘዘ እጁን ሊያስለቅቅ ሲል ሶሎዞ ሌላውን እጁን ያዘው ። ሉካ ለሁለቱም ሰዎች የሚበገር አልነበረም ። ነገር ግን አንድ ሌላ ሰው ከተደበቀበት ብቅ ብሎ በአንገቱ የሀር ሲባጎ አጠለቀበት ። ሰውዬው ጠንካራዋን ሲባጎ በሳባት ቁጥር የሉካን ትንፋሽ እያሳጠረችው ሄደች ። ፊቱ ወደ ሀምራዊ ቀለም ተለወጠ ። ትንፋሹ እያጠረ ሲሄድ የእጁ ጥንካሬም ላላ ። ታታሊያና ሶሎዞም አጥብቀው ይዘውት የነበሩትን እጆቻቸውን አላሉ ። ሉካ ባንገቱ ላይ ያለው ገመድ እየጠበቀ ሲሄድ ታችኛ ሰውነቱን መቆጣጠር አልቻለም ። የተቅጠነጠነ ሰገራ ወለሉን አዳረሰው ። እግሮቹ ተጣጥፈው ሰውነቱ ረገበ ። ሶሎዞና ብሩኖ እጆቹን ለቀቁ ። ብራሲ እየተዝለፈለፈ ዝግ ብሎ ወደ መሬት ሲወርድ አናቂው ተከትሎት ዝቅ እያለ ሲባጎውን ሲያጠብቅ ቆየ ። በመጨረሻም ሲባጐዋ ባንገቱ ዙሪያ ባለው ስጋ ውስጥ ጠለቀች ። የብራሲም አይን በመገረም ትክ ብሎ የሚያይ መስሎ አፍጥጦ ቀረ ።

"እሬሳው እንዳይገኝ ፣ ለጊዜው አለመታየቱ ይመረጣል" አለና ሶሎዞ ወጥቶ ወደ መጣበት ጭለማ ተመልሶ ገባ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ሰምንት

ዶን ኮርሌዎኔ የተተኰሰበት እለት ማግስት ቤተ ሰቡ ሲራወጠ ዋለ ። ሚካኤል ስልኩ አጠገብ ሆኖ መልእክት እየተቀበለ ለሶኒ ያስተላልፋል ። ቶም ሄገን ከሶሎዞ ጋር የሚያደራድር ሁለቱም ወገኖች የሚቀበሉት ሰው ለማግኘት ጥረት ሲያደርግ ዋለ ። ሶሎዞ ምና ልባት ክሌሜንዛና ቴስዮ ያለሁበትን ቦታ አሰሳ አድር ገው አጥምደው ይይዙኛል የሚል ፍራቻ ሳያድርበት አልቀረም ። እሱም ሆነ ከፍተኞቹ የታታሊያ ቤተሰብ አባላት ከተደበቁበት ስፍራ አልወጡም ። ሶኒ እንዲህ እንደሚሆን ገምቷል ።

ክሌሜንዛ በፖሊ ጋቶ ተልእኮ ተጠምዷል ። ቴስዮ ሉካ ብራሲ ያለበትን እንዲፈልግ ተመድቧል ። ካርሎ ሪዚም ፥ 'ምን ልርዳ' ብሎ ጠይቆ ነበር ። ነገር ግን ዶኑ ካቋቋመለት በማንሀተን የጣልያን ሰፈር ከሚገኘው የቁማር ቤቱ ተገኝቶ ስራውን እንዲያካሂድ ተነገረው ። ኮኒ አባቷን እየተመላለሰች ለመጠየቅ እንዲያመቻት ከእናቷ ጋር ነው ያለችው ።

ፍሬድ በወላጆቹ ቤት ተኝቶ የሚያረጋጋ መድሀኒት እየተሰጠው ነው ። ሶኒና ሚካኤል ጠይቀውት ሲወጡ የፍሬድ መገርጣት ሶኒን እጅግ አስደነቀው ። ሚካኤል ግን ጦር ሜዳ ላይ ይህን የመሰለ ሁኔታ አይቶ ስለነበር አዲስ አልሆነበትም ።

ከሰአት በኋላ ላይ ጆኒ ፎንቴን ደውሎ እንደሚመጣ ለሶኒ ሲነግረው "አይሆንም ጆኒ ፥ እዚህ ሽማግሌውን ለማየት መምጣትህ ዋጋ አይኖረውም ። በጣም ታሚል ። መምጣትህ እሱ የማይደግፈውን መጥፎ የሆነ የህዝብ እይታ ስለሚያስከትልብህ እስኪሻለውና ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤት እስክናመጣው ብትጠብቅ ይሻላል ። ሰላምታህን እነግረዋለሁ” ብሎ እንዳይመጣ ከለከለው ።

ከሰአት በኋላ ላይ ዘግየት ብሎ ኬይ ለሚካኤል ስልክ ደወለችለት ። ድምጿ ከተለመደው ለየት ብሏል ። ሚካኤል ፣ ኬይ ጋዜጦች አባቱን ሀይለኛ ወንጀል ሰሪ ነው እያሉ የሚያወሩትን ለማመን እንዳስቸገራት ያውቃል ።

“አባትህ ተሻለው?”

“ደህና ነው”

“ሐኪም ቤት ልትጠይቀው ስትሄድ አብሬህ ልምጣ?”

ሚካኤል የነገራት ትዝ አለውና ሳቀ ። ‘ከሽማግሌ ጣልያኖች ጋር ለመግባባት ከፈለግሽ ሲታመሙ መጠየቅ አስፈላጊ ነው’ ሲል ነገሯት ነበር ።

“ጋዜጦች ስምሽንና ማንነትሽን ካወቁ የ‘ዴይሊ ኒውስ?’ ጋዜጣ ቀዳሚ ገጽች ‘የታወቁ ያንኪ ወላጆች ያሏት ወጣት ከታላቅ የማፊያ ሹም ልጅ ጋር ተወዳጀች’ ብለው ያወጡሻል ። ወላጆችሽ ይህን ሲያነቡ ምን ይሰማቸዋል?”

“ወላጆቼ ዴይሊ ኒውስን አያነቡም” ብላው ትንሽ ዝም ካለች በኋላ “ግን አንተ ደህና ነህ ፣ ማይክ? አንተን የሚያሰጋ ነገር የለም ፣ አይደል?” አለችው ።

ሚካኤል አሁንም ሳቀና ፣ “እኔ እንደ ኮርሌዎኔ ቤተሰብ ወንድ አልቆጠርም ። ለማንም አደገኛ ስላይደለሁ በዚህ መንገድ የሚፈልገኝ አይኖርም ። ሁሉም ነገር ደህና ነው ። በተረፈ ስንገናኝ አጫውትሻለሁ” አላት ።

“መቼ ነው የምንገናኘው?”

ሚካኤል አትኩሮ አሰበና ፣ “ዛሬ ማታ ዘግየት ብሎ ቢሆንስ? አንቺ ካለሽበት ሆቴል መጥቼ ትንሽ ጠጥተን

t.me/OLDBOOKSPDF

እራታችንን እንበላለን ። ከዚያ ሽማግሌውን ልጠይቅ እሄዳለሁ ። እዚህ ቁጭ ብዬ ስልክ መቀበሉ ሰልችቶኛል። እሺ፣ ታድያ ለማንም እንዳትነግሪ ። ጋዜጠኞች አብረን ፎቶግራፍ እንዲያነሱን አልሻም ። እውነቴን ነው ፥ ኬይ ፥ በተለይ ላንቺ ቤተሰቦች አሳፋሪ ይሆናል" ሲል አስ ጠነቀቃት ።

"እሺ ተዘጋጅቼ እጠብቅሀለሁ ። ለገና የምገዛልህ ነገር ወይም ሌላ የምታዘኝ አለ?"

"ምንም የለም ። ተዘጋጅተሽ ብቻ ጠብቂኝ ።"

በደስታ ሳቀችና "ዝግጁ እሆናለሁ ። ሁልጊዜስ ቢሆን ዝግጁ አይደለሁም እንዴ?" አለች ።

"እዎን ነሽ ፤ ለዚህ ነው ከሁሉም በላይ የመረጥ ኩሽ"

"እወድሀለሁ" አለችው ፤ "አንተስ እወድሻለሁ ልትለኝ ትችላለህ?"

ሚካኤል ወጥ ቤት የተቀመጡትን አራት ጠባ ቂዎች ተመለከተና ፥ "አይ ፥ አሁን አልለውም ። ማታ እንገናኝ ፥ እሺ?" ሲላት በእሺታ ተሰናበተችው ።

ክሌሜንዛ የእለቱን ተግባሩን አጠናቆ ወጥ ቤት ውስጥ በትልቅ ድስት ፓስታ ጥዶ ይርመጠመጣል ። ሚካኤል 'ሰላም' ብሎት አልፎ ቶምና ሶኒ ከሚጠብቁት ክፍል ገባ ።

"ክሌሜንዛ እዚያ ነው ያለ?" ሲል ሶኒ ጠየቀ ።

"ልክ የጦር አባል ሳለሁ እናደርገው እንደነበር ስፓጌቲ ለሰዎቹ እየቀቀለ ነው" አለ ሚካኤል ።

ሶኒ ትእግስቱ አለቀና ፤ "ያን ምናምንቴውን ትቶ እንዲመጣ ንገረው ። እዚያ ከሚሰራው ስራ የበለጠ ተልእኮ አለለት ። ቴስዮም አብሮት ይምጣ" ሲል አዘዘ ።

በጥቂት ደቂቃ ሁሉም ቢሮው ውስጥ ተሰባሰቡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶኒ ወደ ክሌሜንዛ ዞሮ "የዚያን ሰውዬ ጉዳይ ጨረስክ?" አለው ።

"ከእንግዲህ አታየውም" ሲል መለሰለት ። ሁለቱ የተነጋገሩት ስለ ፖሊ ጋቶ መገደል መሆኑን ተገንዝቦ ሚካኤል ሰውነቱን ነዘረው ።

"ከሶሎዞ ጋር መገናኘት ቻልክ?" ሲል ሶኒ ሂገንን ጠየቀው ።

"ምናልባት የኛ ሰዎች አዘናግተው እንዳያጠምዱት በመፍራት ጥንቃቄ እያደረገ ስለሆነ በእርቁ ጉዳይ ላይ ቀዝቀዝ ያለ ይመስላል ። ያም ሆነ ይህ እሱ የሚያምነው ትልቅ ሰው በአስታራቂነት ማግኘት አልቻልኩም ። ሽማግሌው በመትረፉ እድሉ ያመለጠችው መሆኑን ተረድቶ መታረቅ አለበት" አለ ሂገን ።

"ይህ ሰው ቤተሰባችንን ካጋጠሙት ጠላቶች ሁሉ ይበልጥ ብልህ ነው ። ሽማግሌው እስኪሻለው ወይም እሱ ኢላማችን ውስጥ እስኪገባ በመጠበቅ ዘግየት እያልን መሆናችንን ሳይገምት አልቀረም" አለ ሶኒ ።

ሂገን ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፣ "በእርግጥ ገምቷል ። ግን ምርጫ የለውም ። መደራደር ይኖርበታል ። በምንም አይነት ነገሮችን ነገ አመቻቻለሁ" ብሎ ሲናገር ከክሌሜንዛ ሰዎች አንዱ የቢሮውን በር አንኳኳና ገባ ።

ወደ ክሌሜንዛ ጠጋ ብሎ ፣ "ፖሊ ጋቶ ሞቶ መኪናው ውስጥ መገኘቱ በሬዲዮ ተሰማ" አለው ።

ክሌሜንዛ እራሱን ከነቀነቀ በኋላ "ስለዚህ ጉዳይ አታስብ" ሲለው ፣ ሰውዬው በመገረም ከተመለከተው በኋላ ነገሩ ገባውና ወደ ወጥ ቤቱ ተመለሰ ።

"በዶኑ ጤንነት ላይ ለውጥ አለ?" ሲል ሶኒ ሂገንን ጠየቀው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ደህና ነው ፥ ብቻ ለአንድ ሁለት ቀናት መናገር አይችልም ። ከቀዶ ጥገናው እያገገመ ነው ። ግን አሁንም እንደደከመ ነው ። እናትህና ኮኒ አብረውት ናቸው ። ድንገት አንድ ሁኔታ ቢፈጠር ፖሊሶችና የቴስዮ ሰዎች በአካባቢው ይገኛሉ ። ዶኑ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሲሻለው ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ እናውቃለን ። እስከዚያም ሶሎዞ ቸኩሎ ሌላ ጥፋት እንዳይፈጽም ማስታገስ አለብን ። ለዚህ ነው ከሱ ጋር መደራደር እንድትጀምር የምፈልገው" አለ ሄገን ።

"እስከዚያው ክሌሜንዛንና ቴስዮን እንዲፈልጉት አሰማርቻቸዋለሁ ። ምናልባት ቀንቶን ሁሉም ነገር ፍጻሜ ያገኝ ይሆናል ።"

"የሚቀናህ አይመስለኝም" አለ ሄገን ፥ "ሶሎዞ ቆቅ ነው ። በጠረጴዛ ዙሪያ ቀርቦ ድርድር ከጀመረ አብዛኛውን እኛ ባልነው መሄድ እንዳለበት ያውቃል ። ለዚህ ነው ወደ ኋላ የሚለው ። እኔ ስገምት ፥ የሽማግሌውን መመሪያ ተቀብለን እንዳናሳድደው የሌሎቹን የኒውዮርክ ቤተሰቦች ድጋፍ እያሰባሰበ ሳይሆን አይቀርም ።"

ሶኒ ፊቱን አጨፍግጎ ፥ "ለምን አባታቸው ነው ድጋፍ የሚሰጡት?" ሲል ጠየቀው ።

ሄገን በትእግስት እንዲህ ሲል መለሰለት ፥

"ሁሉንም የሚጐዳ ጦርነት ለማስወገድ እና ጋዜጠኞም ሆኑ መንግስት ጣልቃ እንዳይገቡብን ለማድረግ ነው ። በዚህ ላይ ለነዚህ ቤተሰቦች ሶሎዞ ከትርፉ ያጋራቸዋል ። እንደምታውቁት በአደንዛዥ እጽ ንግድ ላይ ትልቅ ጥቅም አለ ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ የናርኮቲክስ ትርፍ አያስፈልገውም ፥ ከሁሉም የበለጠው የቁማር ትርፍ በእጃችን ነው ። ሌሎቹ ቤተሰቦች ግን ረሀብተኞች ናቸው ። ሶሎዞ የአደንዛዥ እጽን ንግድ በከፍተኛ ደረጃ ለማካሄድ ብቃት እንዳለው የተረጋገጠ ነው ። በህይወት

t.me/OLDBOOKSPDF

ከኖረ በኪሳቸው ያለ ገንዘብ ነው ማለት ነው ። ከሞተ ግን ችግር ያስከትላል ።”

ሚካኤል የሶኒ ፊት እንዲህ ሆኖ አይቶ አያውቅም ። ከበድ ያለው ክብ አፉ እና ነህስ መልክ ፊቱ አመድ መሰለ ።

“ለነሱ ፍላጎት ደንታ የለኝም! በዚህ ጠብ ውስጥ ባይገቡ ይሻላቸዋል” አለ ።

አንድን በጠላት የተያዘ አስቸጋሪ ኮረብታ ማናቸውም መስዋእትነት ተከፍሎ በወገን ጦር ቁጥጥር ስር እንዲውል ትእዛዝ የሚሰጥ የጦር ጀኔራል በቁጣ ሲጮህ የሚሰሙ የበታች አለቆች እንደሚሆኑት አኳኋን ክሌሜንዛና ቴስዮም በተቀመጡበት ተቁነጠነጡ ።

ሄገንም የሶኒን መናደድ ተመለከተና ፥ “ተው እንጂ፥ ሶኒ ። አባትህ በዚህ መልክ እንድታስብ አይሻም ። እንዲህ ባለ ወቅት ደም ያሳበደው ልትሆን አይገባም ። ሌላ ቀርቶ ያባትህም መመታት የስራ ጉዳይ እንጂ የግል ጠብ አይደለም ። በአሁኑ ወቅት ይህን መረዳት መቻል አለብህ” ሲል ምክሩን ለገሰው ።

ሶኒ አይኑን አፍጥጦ ፥ “እሺ ፥ ይገባኛል ። ግን ሶሎዞን በምንሻበት ወቅት ማንም ሰው ጣልቃ እንዳይገባ” በማለት ለሄገን መለሰለትና ወደ ቴስዮ ዞር ብሎ ፥

“ሉካ ብራሲ የት እንዳለ ፍንጭ ተገኘ?” ሲል ጠየቀው ።

ቴስዮ እራሱን ነቀነቀና ፥ “ጨርሶ ምንም አልተገኘም ። ሶሎዞ ጠልፎት ሳይሆን አይቀርም ፥” አለ ሄገን በጽሞና ፥ “እኔንም ያኔ የገረመኝ ጉዳይ ሶሎዞ ስለ ሉካ ደንታ ቢስ መሆኑ ነበር ። እሱን የመሰለ ብልጥ ሰው ሉካን ስለመሰለ ሰው መስጋቱ አይቀርም ነበር ። እንደሚመስለኝ ሶሎዞ ሉካ ብራሲን በሆነ መንገድ አስወግዶታል” አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጉድ! ነው" አለ ሶኒ፥ "መቸም ሉካ በኛ ላይ እንደማይዞር ተስፋ አደርጋለሁ ። ይህን ብቻ ነው የም ፈራው ። ክሌሜንዛና ቴስዮ ፥ ምን ይመስላችኋል ?"

ክሌሜንዛ ከቶውንም ሉካ ብራሲ ይከዳል ብሎ እንደማይጠረጥር አረጋገጠለት ። ቴስዮ ግን በአጋጣሚ ከሀዲ ሊሆን እንደሚችል ያለውን ግምት ተናገረ ።

"ሶሎዞ የፖሊ ጋቶን መሞት በቅርቡ ሳይሰማ አይቀርም ። ያኔ ምን ይሰማው ይሆን?" ሲል ሁሉንም ጠየቃቸው ።

ክሌሜንዛ በፈገግታ ፥ "የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ጅል አለመሆኑን ይረዳዋል ። የትላንቱም የዶኑ መመታት የእጣ ጉዳይ ብቻ መሆኑን ይገነዘበዋል" ሲል መለሰ ።

"የእጣ ጉዳይ አይደለም እባክህ!" አለ ሶኒ፥ "ሶሎዞ ለሳምንታት ሲያቅደው የቆየው ጉዳይ ነው ። ሽማግሌውን ቢሮው ሲወጣና ሲገባ የእለት በእለት ተግባሩን ሲከታተሉት ሰንብተው ነበር ማለት ነው ። ከዚያም ፖሊን ፥ ምናልባትም ሉካን ፥ ገዟቸው ። ቶምን መሳኝ በሆነበት ወቅት ጠለፉት ። የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ አደረጉ ። ነገር ግን ዶኑን እንዲገድሉ ሶሎዞ የላካቸው ሰዎች ደካማ በመሆናቸውና ሽማግሌውም ቀልጣፋ በመሆኑ እቅዳቸው ሳይሳካ ቀረ ። ገድለውት ቢሆን ኖሮ ከሶሎዞ ጋር ተደራድሬ ሶሎዞ ለጊዜው ድል ያደርግ ነበር ። ከዚያም አምስትም ፥ አስርም አመት ጠብቄ አገኘው ነበር ።"

ከአሽከሮቻቸው አንዱ ሰፊ ሰሀን ሙሉ ስፓጌቲ ከሹካ ፥ ከማንኪያና ከሰሀኖች ጋር አቀረበላቸው ። እያ ወሩ ሲመገቡ ሚካኤል በመደነቅ ተመለከታቸው ። ቶምና ሚካኤል ግን አልበሉም ።

ክሌሜንዛ ፥ ሚካኤልም ሆነ ሶኒ ስለ ሶሎዞ ያላ ቸውን ጥርጣሬ ካዳመጠ በኋላ ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሶሎዞ ፈጽሞ እዚህ ቤት አይደርስም ፥ አለቃዬ ፥ ስለዚህ ጉዳይ አታስብ" አለው ሶኒን ። ሶኒ ለቅጽበት አጤነው ። ቀጥሎም ፥

"ለመሆኑ ሀኪም ቤቱ እንዴት ነው? ያንተ ሰዎች ተገቢውን ጥበቃ እያደረጉ ናቸው?" ሲል ቴስዮን ጠየቀው ።

ቴስዮ ስብሰባው ከተጀመረ አንስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በልበ ሙሉነት ተናገረ ፥ "በውጭም ሆነ በውስጥ ፥ ሀያ አራቱንም ሰአት እየተጠበቀ ነው ። ፖሊሶችም በሚገባ ከለላ ሰጥተዋል ። የሚያስቀው ግን የወንጀል ተከታታዮች የተባሉ ዶኑን ለማነጋገር በር ላይ ይጠባበቃሉ ። ዶኑ ገና የመርፌ ፈሳሽ በደም ስሩ እየተደረገለት ነው ። ስለዚህ በሶሎዞ ሰዎች የምግብ መመረዝ አያሰጋውም ። ዶኑን በምንም አይነት አያገኙትም ።"

ሶኒ እንደተቀመጠ ወደ ኋላ አዘነበለና ፥

"የቤተሰቡን አንቀሳቃሽ ሀይል ስለሚሹ እኔን አይነኩኝም ። ከኔ ጋር መደራደር አለባቸው" አለና ወደ ሚካኤል ዞሮ ሳቅ እያለ ፥ "እንተ ትሆን ሚካኤል? ምናልባት ሶሎዞ አንተን በመያዣነት ጠልፎ ወስዶ ለመደራደር ያስብ ይሆናል" አለ ።

ሚካኤል ከኬይ ጋር ያለው ቀጠሮ ትዝ ብሎት ቅር አለው ። በዚህ አይነት ሶኒ ከቤት አያስወጣውም ማለት ነው ።

"የለም ፥" አለ ሄገን ፥ "ሶሎዞ ዋስትና ቢሻ ኖሮ ሚካኤልን በማናቸውም ሰአት ሊጠልፈው ይችል ነበር ። ነገር ግን በቤተሰቡ የንግድ ተግባር ውስጥ ሚካኤል እንደሌለበት ሁሉም ሰው ያውቃል ። ሶሎዞ ይህን በውጊያው ውስጥ የሌለበትን ልጅ ቢጠልፈው የሁሉንም ቤተሰቦች ድጋፍ ያጣል ። ሌላ ቀርቶ የታ ታሊያ ቤተሰቦች እንኳ ያሳድዱታል ። ስለዚህ ቀላል

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ጉዳዩ ። ነገ ከዚያ ቱርክ ጋር ተባብረን እንድን ሰራ የሚጠይቀን ፥ ሁሉንም ቤተሰቦች የሚወክል ሰው እናገኛለን ። ሶሎዞም ይህንኑ ነው የሚጠብቀው ።"

ሚካኤል የተሰቀለው ልቡ መለስ አለና በረኸሙ ተነፈሰ ።

"መልካም" አለ ሚካኤል "ዛሬ ማታ ወደ ከተማ መሄድ ይኖርብኛል ።"

"ለምን ?" አለ ሶኒ ።

ሚካኤል ፈገግ አለና "ሆስፒታል ብቅ ብዬ ሽማ ግሌውን ጠይቄ ፥ እማዬንና ኮኒንም አይቼ ለመምጣት አስባለሁ ። ሌላ ሌላም የማደርገው አለኝ" አለው ።

ዶኑን ይመስል ሚካኤል እውነተኛ አላማውን አይ ናገርም ። ኬይ አዳምስን ማታውን እንደሚጐበኛትም ለወንድሙ አልገለጸለትም ። ሲነግረው የማይችልበት ምንም ምክንያት አልነበረውም ፥ አመል ሆኖበት እንጂ ።

ከወጥ ቤቱ ከፍ ያለ የማጉረምረም ድምጽ ተሰማ። ክሌሜንዛ ምን እንደሆነ ለማየት ሄደ ። ሲመለስ የሉካ ብራሲን ጥይት የማይበሳው ካናቴራ የሞተ አሳ ተጠ ቅልሎበት በጁ ይዞ መጣ ።

"ያ ቱርክ ወሬ አቀባዩ ፖሊ ጋቶ መሞቱን ሰም ቷል ማለት ነው" አለ ክሌሜንዛ ።

"እኛም ስለብራሲ ተረድተናል ማለት ነው" አለ ቴስዮ ።

ሶኒ ሲጋሩን አቀጣጠለና ውስኪውን ተጎነጨ ።

ሚካኤል ግራ ተጋብቶ "የአሳው ትርጉም ምንድነው?" ሲል ጠየቀ ። አማካሪ ሄገን የአየርላንድ ዝርያ ቢሆንም የሲሲሊያውያንን ዘይቤ ስላጠና እንዲህ ብሎ መለሰለት፥

"የአሳው ትርጉም ፥ ሉካ ብራሲ ከውቅያኖስ ስር ተኝ ቷል የሚል የጥንት የሲሲሊያውያን መልእክት ነው ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ዘጠኝ

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ከኬይ አዳምስ ጋር ለመገናኘት ከተማ ሲወጣ ስሜቱን ከብዶት ነበር ። በቤተሰቡ ውዝግብ ገብቶ መቆላለፉ ፥ የስልክ ጥሪ በመመለስ ተግባር ላይ መሰማራቱ እና ስለግድያ እቅድና ውሳኔ ሁሉ መሰማቱ ቅር አሰኝቶታል ።

እንደባለቀለም ፊልም ቀባብቶ ላይ ላዩን በቀልድ እያስመሰለ ካልሆነ በስተቀር ሙሉ በሙሉ የቤተሰቡን ሚስጥር ለኬይ ስላልነገራትም ጥፋተኛነት ተሰማው ። አሁን ግን አባቱ የመግደል ሙከራ ተደርጉበት ፥ ታሳቅ ወንድሙም ለበቀል እየተዘጋጀ ነው ። ይህን በግልጽ ያለ እውነታ ግን ሚካኤል ለኬይ በዚህ መልክ አይነግራትም። አባቱ የተተኩሰበት በድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ እና ከእንግዲህ ችግሩም ያበቃ መሆኑን አስቀድሞ ነግሯታል። ውዝግቡ ግን ገና መጀመሩ ነው ። ሶኒና ሄገን ሶሎዞ ፥ አደጋ ሊጥል እንደሚችል እያወቁም ሰውየውን ንቀውታል ። ሚካኤል 'ይህ ሶሎዞ የሚባል ሰው በጉያው ምን ደብቆ ይሆን' ሲል አሰበ ። ሶሎዞ ፥ ጮሌ እና የላቀ ሀይል ያለው ሰው ስለሆነ ያልታሰበ አደጋ መጣሉ አይቀርም ። እንዲያም ሆኖ ግን ቶም ፥ ክሌሜንዛና ቴስዮ ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ስላለ የሚያሰጋ ነገር የለም ብለዋል ። እነሱ ደሞ ይህን በመሰለው ነገር ላይ ከሱ የበለጠ ልምድ አላቸው ። በዚህ ጦርነታቸው ውስጥ ሚካኤል እንዲሳተፍ ከፈለጉ ይሁለተኛው አለም ጦርነት ዘምቶ ካገኘው እጅግ የላቀ ሚዳሊያ ሊሰጡት ይገባቸዋል ።

ይህ ሁሉ ሲታሰበው ሚካኤል ያባቱን ደም ለመበቀል ስለመሻቱ ጥፋተኛነት ተሰማው ። አባቱ በጥይት ተበሳስቶ ቢያይም ፥ 'ይህ ሁኔታ የስራ ጉዳይ እንጂ የግል ጠብ አይደለም' ሲል ቶም ሄገን የተናገረው ከማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንም ይበልጥ ሚካኤልን ሊገባው ችሏል ። ስለዚህ አባቱ ይሆን ከመሰለ ሁኔታ ላይ መውደቁ ለስልጣኑና ክብሩ የከፈለው መስዋእትነት ነው ።

ሚካኤል ከዚህ ሁሉ ውዝግብ ነጻ ወጥቶ የራሱን ሀይወት መምራት ነበር የሚፈልገው ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ግርግር እስኪያበቃ በዚህ ውሳኔው መጽናት አይ ችልም ። በጦርነቱ ባይሳተፍ እንኳን በሰላማዊ ሰውነት በቤተሰቡ ተግባር ላይ ግገልገል ይኖርበታል ። እምነቱን ለመጠበቅ ሲባል በጦርነት ከመሳተፍ ነጻ ሆኖ የሰላማዊ ሰው ተልእኮ ስለተሰጠውም ተቆጨ ።

ለዚህ ነው ሰላማዊ ሰው የሚለው ቃል በአእምሮው ውስጥ እየባረቀ ያበሳጨው ።

የክሌሜንዛ ሰዎች ሚካኤልን አጅበው ኬይ አዳምስ ካለችበት ሆቴል አካባቢ ካደረሱት በኋላ የሚከታተላቸው አለመኖሩን አረጋግጠው አወረዱት ። ሚካኤል ከሆቴሉ ሲደርስ ኬይ አዳምስ ከእንግዳ መቀበያው ከፍል ቁጭ ብላ ጠበቀችው ።

እራታቸውን በልተው መጠጥም ከጠጡ በኋላ ፣ አባቱን መቼ ሄዶ እንደሚጐበኝ ጠየቀችው ። አባቱን ለማየት ሴሎች ጠያቂዎች ሲወጡ እንደሚሄድና ለመጣባትም እንደማይከለከል ነገራት ።

ኬይ በዶኑ መመታት ማዘኗን ከገለጸችለት በኋላ በሰርጉ ላይ ከተመለከተችው ወዲህ ጥሩ ሰው ነው ብላ እንደገመተች ለሚካኤል ነገረችው ። ጋዜጠኞች የሚያወሩትን ወሬም ለማመን እንዳቃታትና ሀሰት ነው የሚል ግምት ያላት መሆኑንም ገለጸችለት ።

ለሚያፈቅራትና ለሚያምናት ኬይ የቤተሰቡን ሚስጥር መደበቁ ሚካኤልን አስገረመው ። ባዳነቷ ስለሚሰማው አልነገራትም ። ይልቁንም እሱ ራሱ የሚወራውን ሁሉ እውነት ነው ብሎ እንደማይገምት አስረዳት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንተስ፣ በዚህ ጋዜጦች በሚያወሱለት የቡድን ጦርነት ውዝግብ ውስጥ ትገባበታለህ?" ስትል ኬይ ጠየቀችው ።

ሚካኤል ፈገግ ብሎ የኩቱን ቁልፍ ፈታና ኩቱን ከፍቶ "ያውልሽ ሽጉጥ አልታጠቅኩም" አላት ።

ጊዜው እየመሸ በመሄዱ ወደ መኝታ ክፍል ገቡ ። ከየአይነቱ መጠጥ ቀላቅላ ለሁለቱም በብርጭቆ ቀድታ ጭኑ ላይ ተቀመጠች ። ከቀሚሷ በታች ያለውን ሀር ዘልቆ በእጁ ሲዳስሳት ጭኗ በስሜት ግሎ ሞቀው ። ከነልብሳቸው እንዳሉ ተያይዘው አልጋ ላይ ወድቀው ፍቅር ተለዋወጡ ። እንዳበቁም የሰውነታቸው ግለት እየተሰማቸው በጸጥታ ቆዩ ።

እንቅልፍ ሽልብ አድርጓቸው ከቆዩ በኋላ ሚካኤል ከመኝታው ላይ ደንብሮ ሰአቱን ተመለከተ ።

"ወቸው ጉድ! አራት ሰአት ሊሆን እኮ ነው ። ሀኪም ቤት መሄድ አለብኝ" አላትና ተጣጠበ ። ጸጉሩን ሲያበጥር ወደ መታጠቢያ ቤት ገብታ ወገቡን አቅፋ ፥

"መቸ ነው የምንጋባው?" አለችው ።

"ይህ የቤተሰብ ውዝግብ ጋብ ሲልና አባቴ ሲሻለው ባልሽበት ቀን እንጋባለን ። እንደሚመስለኝ ሁኔታውን ለወላጆችሽ ማሳወቅ ይኖርብሻል ።"

"ምንድነው የማሳውቀው?"

"ካንድ ጉበዝ መልክ ቀና የጣልያን ተወላጅ ጋር መተዋወቅሽን ነዋ! ዳርትስሙት ኮሌጅ ሲማር ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ፣ 'የላቀ አገልግሎት' የጀግንነት ሜዳሊያ ዎች የተሸለመ ፥ ታማኝ ፥ ትጉህ ሰራተኛ ነው በያቸው ። ነገር ግን አባቴ መጥፎ ሰዎችን የሚገድል ፥ አንዳንዴ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖችን በጉቦ የሚገዛ ፥ በስራው ምክንያት ጠላቶቹ ጥይት የረጩበት ነው ብለሽ ንገሪያቸው ። ነገር ግን ባባቴ ውዝግብ ውስጥ ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅ የለበትም ሳትይ እንዳትቀሪ ። ይሆን ሁሉ ግስታወስ የምትችይ ይመስልሻል?"

ኬይ አቅፋው የነበረውን ወገቡን ለቀቀችና የመታጠቢያ ቤቱን በር ተደገፋ፥ "በእርግጥ ስለአባትህ ሰዎች የሚያወሩት እውነት ነው? ሰው ይገድላል?" ስትል ጠየቀችው።

ሚካኤል ጸጉሩን አበጥሮ ጨረሰና ፣

"በእርግጥ አላውቅም ። ማንም በእርግጥ አያውቅም። ነገር ግን እውነት ቢሆንም አይገርመኝም" አላት ። ሊወጣ ሲል ፥ "መቼ ነው የምንገናኘው?" ስትል ጠየቀችው ። ሚካኤል ሳማትና ፥

"ወደ ገጠር ከተማሽ ሂጅና ቤትሽ ሆነሽ አስቢበት ። እንዲህ ባለ ውዝግብ ውስጥ እንድትገቢ አልሻም ። ከዛና እረፍት በኋላ ትምህርት ቤቴ ስመለስ አብረን እንሆናለን ። እሺ?" አላት ።

"እሺ" ብላው ሲወጣ በሊፍቱ ውስጥ ገብቶ ከአይኗ እስኪሰወር ተመለከተችው ። ይሀን የመሰለ የመቀራረብ ፥ የማፍቀር ስሜት ተሰምቷት አያውቅም ። አንድ ሰው ከእንግዲህ ፥ ሚካኤልን ሁለት አመት እስኪያልፍ አታይውም ቢላት ሀዘን አትችለውም ነበር ።

ሚካኤል ፈረንሳይ ሀኪም ቤት ደርሶ ከታክሲው ሲወርድ በመንገዱ ጭር ማለት ተደነቀ ። በኮሪደሩ ሲዘልቅ ባዶ መሆኑ ይበልጥ አስደነቀው ። ምናባታቸው ውንስ ፥ ከሌሚንዛና ቴስዮ ምን ማድረጋቸው ነው? በርግጥ ወታደር ማሰልጠኛ ገብተው ባይሰለጥኑም ስለጥበቃ በሚገባ ማወቅ አለባቸው ። ቢያንስ አንድ ሁለት ሰው መግቢያው ላይ መጠበቅ ነበረበት ። ሰአቱ ከምሽቱ አራት ሰአት ተኩል ሆኖ የዘገዩ ጠያቂዎች ሳይቀሩ ሄደዋል ። ሚካኤል ይሀን ጊዜ ደነገጠና መጠንቀቅ ጀመረ ። ያባቱን ክፍል ያውቀው ስለነበር ከመግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባቱ በፊት ነርሷን ሳያነጋግር አልፎ ሊፍት ውስጥ ገባ ። የሚገርመው ነርሷ ካለችበት አራተኛ ፎቅ እስኪ ደርስ ድረስ ያስቆመው የለም ። አልፎ አባቱ ካሉበት ክፍል ገባ ። ከውጭ ማንም ሰው አልቆመም ። አባቱን የሚጠብቁ ሁለት የደህንነት ሰራተኞችስ የት ደረሱ? የክሌሚንዛንና የቴስዩን ሰዎችስ ምን በላቸው? ሰው ክፍሉ ውስጥ ይኖር ይሆን? በሩ ግን ክፍት ነው ። ሚካኤል ወደ ውስጥ ገባ ። አንድ ነገር አልጋው ላይ አለ ። በመሰኩቱ በዘለቀው የታህሳስ ጨረቃ ብርሃን ያባቱ ፊት ታየው ። አይንቀሳቀስም ። በተቆራረጠ ትን ፋሽ ደረቱ በትንሹ ከፍ ዝቅ ይላል ። ከብረት መስቀያ ላይ ከተንጠለጠለ ፈሳሽ የላስቲክ ክረጢት ጋር የተያያዘ የላስቲክ ቱቦ አፍንጫው ውስጥ ተሰክቷል ። ከሆድቃው የሚወጣው መርዝ የሚጋባበት በመስታወት የተሰራ ጆግ ወለሉ ላይ ተቀምጧል ። ሚካኤል አባቱ ደህና መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ተመልሶ ነርሷ ካለችበት ሄደና ፥

"ስሜ ሚካኤል ኮርሌዎኔ ይባላል ። ካባቴ ክፍል ውስጥ መቀመጥ እፈልጋለሁ ። የሚጠብቁት የደህንነት ሰራተኞችስ የት ደረሱ?" ሲል ጠየቃት ።

ወጣቷ ነርስ በቢሮዋ ስልጣን በመተማመን "አባትህ ጉብኝዎች ስለበዙበት ፖሊስ ከአስር ደቂቃ በፊት መጥቶ አስወጣቸው ። የደህንነት ሰራተኞችም ድንገተኛ ጉዳይ በማጋጠሙ ወደ መስሪያ ቤታቸው እንዲ ሮጡ ትእዛዝ ስለደረሳቸው እነሱም ከአምስት ደቂቃ በፊት ሄዱ ። ግን አትስጋ ። አባትህን ቶሎ ቶሎ እየጐበኘሁት ነው ። ማናቸውንም ድምጽ ከዚህ ሆኜ መስማት እችላለሁ" ስትል መለሰችለት ።

"አመሰግንሻለሁ ። ለጥቂት ጊዜ ከሱ ጋር ልቀመጥ ፥ እሺ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈገግ አለችና ፥ "ይሁን እሺ ፥ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ልትቆይ ትችላለህ ። እንደምታውቀው የሀኪም ቤቱ ህግ ጠያቂዎች እንዲቆዩ ስለማይፈቅድ ብዙ ላቆይህ አል ችልም"

ሚካኤል አባቱ ከተኛበት ክፍል ተመልሶ በሆስ ፒታሉ ስልክ ማዞሪያ አማካይነት ወደ ቤቱ ሲደውል ሶኒ አነሳ ። ሚካኤል በሹክሹክታ ፥

"ሶኒ ፣ ሀኪም ቤት ሆኜ ነው የምደውልልህ" እዚህ የደረስኩት ዘግይቼ ነው ። አባቦን የሚጠብቅ ማንም ሰው የለም ። ከቴስዮ ሰዎችም ሆነ ከደህንነት ሰራተኞቹ በክፍሉ ማንንም አላገኘሁም" ሲል ድምጹ እየተንቀጠ ቀጠ ነገረው ።

ሶኒ ጸጥ ብሎ ቆየና በዝግታ መናገር ጀመረ ፥ "ይህን ያደረገው ያ ሶሎዞ መሆን አለበት"

ሚካኤልም "እንኔም የመሰለኝ ይኸው ነው" አለ ። "ለመሆኑ እንዴት አድርጉ ፖሊሶቹ ሰውን ሁሉ እንዲ ያስወጡ ማድረግ ቻለ ። የትስ ሄዱ? የቴስዮ ሰዎችስ ምን ሆኑ? እግዚአ ፣ያ ሶሎዞ የሚባል ዲቃላ የኒውዮርክን ፖሊስ መስሪያ ቤት አባሎች በሙሉ በመዳፉ ውስጥ አስገብቷቸዋል ማለት ነው?"

"ግድ የለህም ። አንተ ዘግይተህ ሀኪም ቤት መሄ ድህ እድለኞች ነን ። ክፍል ውስጥ ቆይ ። ከውስጥ ቆል ፈው ። በሩብ ሰአት ውስጥ ሰዎች እንዲደርሱልህ አደ ርጋለሁ ። ዝም ብለህ ቁጭ በል ። አይዞህ አትፍራ ።"

"አልፈራም" ሲል ሚካኤል መለሰ ።

ሚካኤል ይህ ውዝግብ ከተጀመረ አንስቶ ለመጀመ ሪያ ጊዜ በአባቱ ጠላቶች ላይ ቁጣና ጥላቻ ተቀሰቀሰበት ።

ስልኩን ዘግቶ ለነርሷ የመጥሪያ ደወሉን ደወለ ። ሶኒ 'ባለህበት ሆነህ ቆልፈህ ተጠባበቅ' ቢለውም መመ ሪያውን ጥሶ ነርሷን ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"አይዞሽ አትፍሪ ። አባቴን ከዚህ ከፍል ማዛወር አለብን ። አልጋውን ወደ ሌላ ክፍል መውሰድ እንድንችል የተቀጣጠሉትን ላስቲኮች አንዴ ትነቅይልኛለሽ?" አላት ።

"ይህ ሊሆን የማይችል ነው ። በቅድሚያ ከሀኪሙ ፈቃድ ያስፈልጋል" ብላ መለሰችለት ።

ሚካኤል ቶሎ ቶሎ መናገሩን ቀጠለ ፥ "ስለ አባቴ በጋዜጣ ላይ ሳታነቢ አልቀረሽም ። ዛሬ ማታ ማንም የሚጠብቀው ሰው እንደሌለ እያየሽ ነው ። አሁን ወደዚህ ሆስፒታል ሰዎች ሊገድሉት እንደሚመጡ ተነግሮኛል ። እባክሽ እመኚኝና እርጂኝ" አላት ።

"የተያያዙትን ላስቲኮች መንቀል የለብንም ። ከአልጋው ጋር እንደተያያዙ ማንቀሳቀስ እንችላለን ።"

"ባዶ ክፍል አለ?" አለ ሚካኤል በሹክሹክታ ።

"በስተመጨረሻው በኩል ይኖራል"

ወዲያው ተቀላጥፈው ዶኑን ወደ ሌላ ክፍል አዛወሩት ።

"እርዳታ እስኪመጣ እዚሁ አብረሽው ቆዪ ። ውጭ ከሆንሽ ደመኞቻችን ጉዳት ሊያደርሱብሽ ይችላሉ" አላት ።

ይህን ጊዜ አባቱ ከአልጋ ላይ የሻከረ ድምጹን አሰማ ። "ሚካኤል ፥ አንተ ነህ? ምን ተፈጠረ? ምንድነው ነገሩ?" አለው ።

ሚካኤል ወደ መኝታው አዘንብሎ የአባቱን እጅ ያዘና ፥ "አዎን ሚካኤል ነኝ ፥ አትስጋ ፥ አድምጠኝ ፥ ምንም ድምጽ እንዳታሰማ ። ሰዎች ሊገድሉህ እየሞከሩ ስለሆነ ፥ በተለይ ሰው ስምህን ሲጣራ አቤት እንዳትል ።"

ዶን ኮርሌዮኔ ትላንት የሆነውን ነገር ለመረዳት ሙሉ በሙሉ ነፍሱን ባይዘራም ፥ ደግነት የተሞላው ፈገግታ ለልጁ በማሳየት ፣ አቅም አነሰው እንጂ እንዲህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊለው ፈለገ "ለምን እፈራለሁ? ከአስራ ሁለት አመቴ ጀምሮ ባእድ ሰዎች ሲገድሉኝ እንደ ምኸሩ ነው።"

ምእራፍ አስር

ሚካኤል አንድ መግቢያ ብቻ ባለው በዚህ አነስተኛ ሀኪም ቤት ውስጥ ሆኖ በመስኮቱ አቅጣጫ የመንገዱን አካባቢ ተመለከተ። መንገዱ ባዶ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሮጦ ወደ ውጭ ወጣ። የአምቡላንሱን መቆሚያ ሲመለከት ምንም መኪና የለም። ከእግረኛ መንገዱ ላይ ቆሞ ሲጋራውን አቀጣጠለ። መሳሪያ አለመያዙ እንዲታወቅ የኮቱን ቁልፍ ከፈታ በኋላ ማንነቱን መለየት እንዲቻልም ከመብራቱ አምድ ሰር ቆመ።

የውጊያ ጃኬት የለበሰ ችምችም ጸጉራም ወጣት፥ የሆነ እቃ ከጉያው ሸጉጦ በመንገዱ ቁልቁል አቅጣጫ በፍጥነት ይመጣል። ወጣቱ ወደ ሚካኤል ጠጋ ብሎ፥

"ዶን ሚካኤል፥ ታስታውሰኛለህ? የዳቦ ጋጋሪው የናዘሬኔ አማችና ረዳቱ ኤንዞ ነኝ። መንግስት በአሜሪካ እንድቆይ እንዲፈቅድልኝ በማድረግ ህይወቴን ያዳነው አባትህ ነው" አለው።

ሚካኤል አስታውሶት አንገቱን ነቀነቀ።

"የመጣሁት አባትህን ልጠይቅ ነው። ሰአት አልፏል ብለው አያስገቡኝ ይሆን?"

ሚካኤል ፈገግ ብሎ እንደማይፈቀድለት አስረዳው። ወጣቱ አባቱን ለመጠየቅ በመምጣቱ ካመሰገነው በኋላ ይህንኑ ላባቱ እንደሚነግርለት ነገረው። ይህን ጊዜ አንዲት መኪና እየጮኸች ስትበር ሚካኤል ነቃ አለ። ችግር መኖሩን ለኤንዞ ካስረዳው በኋላ ጣጣ ውስጥ እንዳይገባ ተሉ ከዚያ ሰፍራ እንዲሄድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገረው ። ከፖሊስ ጋር መጋጨት ከሀገር መውጣትን ስለ ሚያስከትልበት ኤንዞ ቢፈራም ወደ ሚካኤል ጠጋ ብሎ ፥

"ችግር ካለ ልቆይና ልርዳህ ። የጡት አባት ውለታ አለብኝ" ሲለው ሚካኤል ስሜቱ ተነካ ። ልጁን አሁ ንም እንዲሄድ ሊነግረው ፈልጐ ነበር ። ግን 'ለምን አይቆይም?' የሚል ሀሳብ አደረበት ። ደመኛቸው ሶሎዞ አደጋ ጣዮች ቢልክ በአካባቢው አንድ ሰው ቢያዩ ላይፈሩት ይችላሉ ። ሁለት ሰዎች ካገኙ ግን መስጋ ታቸው አይቀርም ። ስለዚህ ሚካኤል ለኤንዞ ሲጋራ ሰጥቶት ካቀጣጠለለት በኋላ ፥ በዚያ የታሀላስ ብርድ ውስጥ ከመብራቱ አምድ ስር አብረው ቆሙ ። የሆስ ፒታሉ ቢጫ መስኮቶች የገናን በአል ለማጌጥ ተብሎ በተዘጋጀ የቅጠል ሰብጥር አረንጓዴ ተውበው አብረ ቅርቀዋል ።

ሚካኤልና ኤንዞ ሲጋራቸውን ምገው ሊጨርሱ ሲሉ አንድ ጥቁር አውቶሞቢል ወደነሱ ዞራ መጣች ።

ሚካኤል ከውስጥ ያለውን ሰው ሲመለከት ፍር ሀት ወረረው ። መኪናዋ የምትቆም መስላ ወደ ፊት ገሰገሰች ። ከመኪናዋ ውስጥ ካሉት ሰዎች የሚካኤልን ማንነት ያወቀ ሰው ያለ ይመስላል ። ሚካኤል ለኤንዞ ሌላ ሲጋራ ሲሰጠው ኤንዞ እጁ ሲንቀጠቀጥ ተመለከተ። የራሱም እጅ አለመንቀጥቀጡ አስገረመው ።

አሰር ደቂቃ ያህል ከለፈ በኋላ ጮር ብሎ የነበ ረውን የሀኪም ቤቱን ጸጥታ የተዘዋዋሪ መኪና ጩኸት አደፈረሰው ። ሌሎች ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው ቡድና ችን የያዙ መኪኖች ተዘዋዋሪ መኪናዋን ተከትለው መጡ ። ሀኪም ቤቱ በፖሊሶችና በደህንነት ሰራተኞች ተሞላ ። ሶኒ የላካቸው ጠባቂዎች መሆናቸውን በመገ መት ሚካኤል ከስቃይ የመገላገል ስሜት ተነፈሰና ሊቀ በላቸው ወደነሱ ገሰገሰ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠጋ እንዳለ ሁለት ወጠምሻ ፖሊሶች እጆቹን ለቀም አደረጉት ። ሌላው ፖሊስ ፈተሸው ። አንድ ወፍራም ሻምበል ወደነሱ ሲጠጋ ወታደሮቹ መንገዱን ለቀቁለት ። ሻምበሉ ወደ ሚካኤል ጠጋ ብሎ በእብሪት "እናንት ወሮበሎች ፣ ሁላችሁንም ሰብስቤ የቆለፍኩ ባችሁ መስሎኝ ነበር ። ማን አባክ ነህ ደሞ አንተ ፣ ምን ትሰራለህ እዚህ?" ሲል ጮኸበት ። ይህን ጊዜ ከሚካኤል ጐን ቆሞ የነበረ ፖሊስ ፣

"እሱ መሳሪያ አልያዘም ሻምበል" ሲል ሊያስረዳው ሞከረ ። ሚካኤል ግራ ተጋብቶ መልስ በመስጠት ፋንታ የሻምበሉን ፊትና አዝማሚያ እያጤነ ሳለ አንድ የደህንነት ሰራተኛ ፣

"ይኸማ ፣ የዶኑ ልጅ ሚካኤል ኮርሌዮኔ ነው" አለው ።

"አባቴን እንዲጠብቁ የተመደቡትን ሰዎች ማን ከምድባቸው አነሳቸው?" ሲል ሚካኤል ሻምበሉን ጠየቀው ።

ሻምበሉ በቁጣ ፣

"አንተ ቅንዳሻም ! ምን አባክ ቆርጦህ ነው ስራዬን የምትነግረኝ? እኔ ነኝ ያነሳኋቸው ። ማንም ሶላቶ ወን በዴ እርስ በርሱ ቢጨራረስ እኔ ደንታ የለኝም ። እንደኔ ቢሆን ኖሮ አባትህ ላይ ሲተኮስበት ባይም እንኳን እሱን ለማዳን ጣቴንም አላነሳ ነበር ። የጉብኝት ሰአት አልፏል ። አሁን ጥፋ ከፊቴ አንተ ኩታራ!" ሲል ጮኸበት ።

ሚካኤል በመቆጣት ፋንታ ነገሮችን ማጤን ጀመረ። ቀድሞ እንደገመተው እነዚህ ሰዎች ሶኒ የላካቸው ጠባቂዎች እንዳልሆኑ ተገነዘበ ። ቅድም ባለፈው መኪና ውስጥ ውልብ ብሎ የታየው ሶሎዞ ይሆን? እነዚህ ሰዎችም የኮርሌዮኔን ሰዎች በአካባቢው እንዲያስወግዱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለት ሶሎዞ ገንዘብ የሸጦጠባቸው ሰዎች መሆን አለባ
ቸው ። ወይስ ሶኒ ሁሉም ነገር በጥንቃቄ ታቅዶ እንደ
ተደራጀ በገለጠለት መሰረት የተመደቡ ሰዎች ይሆኑ?
ስለዚህ ሚካኤል ለዘብ ባለ አነጋገር ፥

"አባቴ ባለበት አካባቢ ጠባቂዎች ማድረግህን
ሳላረጋግጥ ከዚህ ሀኪም ቤት ንቅንቅ አልልም" አለው ።

ሻምበሉ ከዚህ ኩታራ ጋር መነጋገር አላስፈለገ
ውም ። ከአጠገቡ ያለውን የደህንነት ሰራተኛ ፥

"ፊል ፥ ይህን ኩታራ ውሰድና እሰርልኝ" ብሎ
ሲያዘው የደህንነት ሰራተኛው ወዲያው ትእዛዙን
በመፈጸም ፈንታ ሊያስረዳው ሞከረ ።

"ሻምበሌ ፥ ይህ ልጅ መሳሪያ አልያዘም ፥ የጦር
ሜዳ ጀግናም ነው ። በህገወጥ ተግባር ውስጥ ፈጽሞ
ተሳትፎ አያውቅም ። ኋላ ጋዜጦች ስማችንን እንዳይበ
ክሉት" ሲል አሳሰበው ።

ሻምበሉ ወደ ደህንነት ሰራተኛው ዞሮ ፥

"አንት እርጉም ፥ እሰረው ነው የምልህ!" ሲል
ተቆጣው ።

ሚካኤል በመቆጣት ፋንታ ነገሮችን በጥንቃቄ
እያጤነ ሆን ብሎ ሻምበሉን በነገር ለመውጋት ፈለገ ።

"ሻምበል ፥ አባቴን ያለጠባቂ ብቻውን እንድት
ተወው ያ ቱርክ ምን ያህል ነው የከፈለህ?" አለው ።

የፖሊሱ ሻምበል ይህን ሲሰማ እሳት ለብሶ አጠ
ገቡ የቆሙትን ጠባቂዎች ፥ "ያዙልኝ!" አላቸው ።

ጠባቂዎቹ ሚካኤልን እጁን ከጉኑ ላይ አጣብቀው
ሲይዙለት ፥ የሻምበሉ ግዙፍ ቡጢ ወደሱ ሲወረወር
ታየው ። ለማምለጥ ይሞክር እንጂ የተሰነዘረበትን ጡጫ
ከጉንጩ አጥንት ላይ ከማረፍ አላዳነውም ። የራስ ቅሉ
በፈንጂ የተመታ ያህል አፉ በደምና በጥቃቅን የአጥ
ንት ስብርባሪዎች የተሞላ ስለመሰለው ጥርሱ የረገፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑ ገባው ። ጆሮ ግንዱ በአየር እንደተሞላ አበጠ ። ፖሊሶቹ ባይዙት ኖሮ ተዝለፍልፎ በወደቀ ነበር ። ሀሊናውን ግን አልሳተም ። ነጭ ለባሹ የደህንነት ሰራተኛ ለመገላገል ከመሀከላቸው ገብቶ ፥ "እግዚኦ ፥ ሻምበል ፥ በርግጥ ይህን ልጅ ጐድተኸዋል" አለው ።

ሻምበሉ ድምጹን ጐላ አድርጐ ፥ "ይግባህ! እኔ ንክችም አላደረግኩት ፥ አልታሰርም አሻፈረኝ ብሎ ሊደ በድበኝ ሲቃጣ ነው የወደቀው" ብሎ መለሰለት ።

ሚካኤል አይኑ በደም ጭጋግ እንደተጋረደ መኪ ናች ተከታትለው እየበረሩ መጡና ከመንገዱ ዳር ጠርዝ ላይ ሲደርሱ ተመለከተ ። ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ ። ከመሀከላቸው አንዱ የክሌሜንዛ ጠበቃ ነበርና ሻምበሉን በጽሞና እንዲህ ሲል ተናገረው ፥

"ሻምበል ፥ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ዶን ኮርሌዎኔን የሚጠብቅ የግል የደህንነት ሰራተኞች ቡድን አሰማር ርቷል ። እነዚህ ከኔ ጋር ያሉ ሰዎች ለያዙት መሳሪያ ፈቃድ አላቸው ። ካሰርካቸው ነገ ጧት ለምን እንዲህ እንዳደረግክ ለማስረዳት ዳኛ ፊት መቅረብ ይኖርብሀል"

ጠበቃው ወደ ሚካኤል ፊቱን አዞረና ፥

"ይህን ድብደባ በፈጸመብህ ግለሰብ ላይ ክስ ትመሰርታለህ?" ሲል ጠየቀው ።

ሚካኤል ሰመናገር አልቻለም ። መንጋጋዎቹ በመ ወላገዳቸው እየተንተባተበ ፥ "አዳልጦኝ ወድቄ ነው" ሲል ለጠበቃው መለሰለት ።

ሚካኤል ይህን የመሰለ መልስ በመስጠቱ ሻምበሉ የድል አድራጊነት ስሜት ሲሰማው ሚካኤልም ስሜቱን ደብቆ በፈገግታ ተቀበለው ። ይህ ሁሉ ጣፋጭ መልስ የሚካኤል ጥላቻና ቂም እንዳይታወቅበት ፥ ሻምበሉም እንዳይጠነቀቅ ከአባቱ የወረሳት የማዘናጊያ ዘዴ ናት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል በነገታው ጧት ከእንቅልፉ ሲነቃ መንጋጋው በሽቦ ተሰፍቶ አራት ጥርሶቹም መርገፋቸውን ተረዳ ። ከአጠገቡ ተቀምጦ የነበረውን ሄገንን ባለፈው ምሽት በሀኪም ቤት የተከናወነውን ሁኔታ እንዲያስረዳው በጠየቀው ጊዜ ፥ ከስጋው ውስጥ የተከሰከሱትን አጥንቶቹን ለማውጣት የተካሄደውን የሀኪሞች ጥረት አስረዳው ። ሀኪም ቤቱን ለቆ ሎንግ ቢች ከሚገኘው ቤታቸው እንዲሄድ ሶኒ ያቀደ መሆኑንም ሄገን ለሚካኤል ነገረው ።

ሚካኤል ስላባቱም ደህንነት ጠየቀ ። በግል የደህንነት ሰራተኞች አማካይነት አካባቢው በሙሉ በተሟላ ጥበቃ ላይ እንደሚገኝ ሄገን ለሚካኤል ካረጋገጠለት በኋላ የቀረውን መኪና ውስጥ ሲገቡ እንደሚነግረው ገለጸለት ።

ከሌሚንዛ እየነዳ ጉዟቸውን እንደ ጀመሩ ፥ ሚካኤል አሁንም ስላለፈው ምሽት ሁኔታ እንዲወራለት ፈለገ ። ሄገንም ያብራራለት ጀመር ። ሚካኤል በተመታበት ምሽት የተከናወነውን ሁሉ የቤተሰቡ ወሬ አቀባይ የሆነው ፊሊፕስ የተባለው የደህንነት ሰራተኛ በዝርዝር አስረድቷቸው ነበር ። ሚካኤልን የደበደበው ሻምበል ማክለስኪም ቢሆን የቤተሰቡ ድብቅ ደመወዝተኛ ነበር ። ኋላ ግን ሶሎዞ ይበልጥ ስላጐረሰው ይመስላል ፥ ከድቷቸዋል ። በሆስፒታሉ አካባቢ ታጥቀው ዶኑን ይጠብቁ የነበሩትን የቴስዮን ሰዎች ከጥበቃ ቦታቸው አንስቶ ወስዶ አስሯቸዋል ። የመንግስት ጠባቂዎችንም ለሌላ ተልእኮ እንደሚፈልጋቸውና በምትካቸው ሌሎች እንደሚልክ ዋሽቶ አንስቷቸዋል ። ይህ ሁሉ ተንኰል ማክለስኪ የተባለው የፖሊስ ሹም ብዙ ንዋይ ላፈሰሰለትና ኋላም ሊጨምርለት ቃል ለገባለት ለሶሎዞ ጥቃት ዶኑን በግላጭ ለመተው ነበር ። ሚካኤል የደረሰበት ጉዳት

t.me/OLDBOOKSPDF

ዜናው እንዲሰማ ፖሊሶችም ሆኑ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ስለማይሹ ጉዳዩ በድብቅ ተይዟል። በግርግሩ ወቅት ኤንዞ ውዝግብ ሳይበዛ ነው ሾልኮ ያመለጠው። ከሚካኤል ጋር በመቆየቱ ግን የቤተሰቡ በጐ አይን አይለየውም። ቶም ይህን ሁሉ ለሚካኤል ካወራለት በኋላ ፥ ማለዳ ላይ ብሩኖ ታታሊያ መገደሉን ገለጸለት።

አባታቸው እስኪድን ምንም የበቀል እርምጃ እንዳይወስዱ መስማማታቸውን ሚካኤል በማስታወስ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ጠየቀ።

"ሆስፒታል በተደረገው ሁናቴ ሶኒ እጅግ አመረረ። ትላንት ማታ የሚገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ወጥቶ ታማኝ ገዳዮች በመላው ኒውዮርክና ኒው ጀርሲ ተሰማር ተዋል። በበኩሌ ከዚህ ሁኔታው ቆጠብ እንዲል ጥረት እያደረግሁ ነው። አንተም ብታናግረው ጥሩ ነው። ጉዳዩ ያለ ጦርነት ሊቃለል ይችላል።"

"አነጋግረዋለሁ። ለመሆኑ ዛሬ ስብሰባ ይኖራል?"

"አዎን። ሶሎዞም ሰው ልኮብናል። ከኛ ጋር ተቀምጦ ለመደራደር ተስማምቷል። አደራዳሪ ተመርጦ ዝርዝሩን እያዘጋጀ ነው። ሶሎዞ ድል መሆኑ ታውቆታል። በህይወት ቢያመልጥ ይሻለዋል። ወኔ ቢሶች መስለነው ነበር። ከታታሊያ ልጆች አንዱ የሆነውን ብሩኖን ስንገድል ጊዜ ግን ማንነታችንን ሊረዳው ችሏል" በማለት ሄገን ለሚካኤል ገለጸለት።

ሎንግ ቢች በሚገኘው የዶኑ ቤት በተካሄደው ስብሰባ ላይ ሶኒ ፥ ሚካኤል ፥ ሄገን ፥ ክሌሜንዛና ቴስዮ ተገኝተዋል። ሶኒ ወንድሙ ሚካኤል በመትረፉ ተደስቶ እራሱን በሁለት እጁ ይዞ "አቤት እንዴት ነው ያሳመሩህ?" ሲል ቀለደበት። ሚካኤል ግን የሶኒን እጅ ከላዩ አላቆ የተሰፋውን መንጋጋውን ህመም እንዳይደነዝዝለት ከዊስኪው ቀድቶ ተጐነጨ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሶኒ የማመንታቱ ጊዜ አልፎለት በዚያን እለት ቆርጦ የተነሳበት ሁኔታ በመኖሩ ከሰሞኑ በተለየ ደስተኛ ሆኗል።

"ያ ቱርክ አሁን እንድንሰበሰብ ጥሪ እያደረገ ነው" አለ ሶኒ እየሳቀ፥ "ይገርማል የዚያ የውሻ ልጅ ወኔ! ትላንት ሰርቶልን ሲያበቃ ዛሬ ድርድር ይሻ ጀመር። እኛ በዚህ ወቅት እሱ የሰጠንን ሁሉ መቀበል እንዳለብን አምኗል። ወይ ድፍረት!"

ቶም በጥንቃቄ "ምን ብለህ መለስክለት?" አለው።

ሶኒም ፈገግ አለና፥ "ባላችሁት ሰአት ይቻላል ብያለሁ። ምንም የሚያስቸኩለኝ ነገር አይኖርም። ሶሎዞ አላርፍ ካለ ሚች ነው። መቶ ታዛዥ ገዳዮቼ በከተማዋ ተሰራጭተዋል" በማለት መለሰ።

ሄገን አሁንም፥ "ያቀረቡት መደራደሪያ ነጥብ አለ?" ሲል ጠየቀ።

"አዎን፥" አለ ሶኒ፥ "የሶሎዞ ፍላጐት በኮርሌዮኔ ቤተሰብ በኩል ሚካኤል በተደራዳሪነት እንዲገኝ ነው። ስለ ሚካኤል ደህንነት አደራዳሪው ማረጋገጫ ሰጥቷል። ሶሎዞ ለእራሱ ደህንነት ዋስትና አልጠየቀም። ሚካኤል የሶሎዞን ድርድር ካዳመጠ በኋላ ይለቁታል።"

ሄገንን ያሰጋው የብሩኖ ታታሊያ መገደል የሚያስከትለው መዘዝ ነበር።

"የብሩኖ ሞት በዶኑ ላይ ለተቃጣው የግድያ ሙከራ ክፍያ ነው። ነገሮች ተካክሰዋል ማለታቸው ነው። አይ የኛ ጮሌዎች!" በማለት ሶኒ ሳቀ።

የሶሎዞን ሃሳብ እንዲሰሙት ሄገን ምክር ቢያቀርብም ሶኒ አልተዋጠለትም። እራሱን በእምቢታ ነቀነቀና፥

"ከዚህ በኋላ ስብሰባ አንሻም። አደራዳሪውን ስታገኘው ምንም አይነት ውይይት እንደማናደርግ፥ ሶሎዞን ብቻ እንደምንፈልግ ንገረው። ይህ ካልሆነ ፍረሻችን እንገባና ጦርነቱ ይጀመራል። የሁሉም ንግድ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንትስታሴ ቢደናቀፍ ይደናቀፍ!" አለ ።

"ሌሎች ቤተሰቦች የጦርነት መቀስቀስን ፈጽሞ አይደግፉትም ። ሁሉንም ያስከፋቸዋል" በማለት ሄገን የሶኒን ሀሳብ ሊያስቀይረው ሞከረ ።

"ሌሎቹ ቤተሰቦችም ቢሆኑ ሶሎዞን አሳልፈው ከመስጠትና ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ጋር ጦርነት ከመክፈት ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ይኖርባቸዋል ። ተጨማሪ ምርጫ አልሻም ፤ ጉዳዩ ተወስኖበታል ። ያንተ ተግባር ድል እንዳደርግ መርዳት ብቻ ነው" አለ ሶኒ በቁርጥ ።

ሄገን እራሱን ዝቅ አድርጐ ጥቂት ካሰበ በኋላ ማክለስኪ የሶሎዞ ድብቅ ደመወዝተኛ መሆኑን ማረጋገጡን፣ እንዲያውም ከአደንዛዥ እጽ ገበያም ድርሻ የሚኖረው መሆኑንና የሶሎዞ ልዩ ጠባቂ ለመሆን መስማማቱን ለሶኒ ገለጸለት ።

"ስለዚህ ሶሎዞ ከሚካኤል ጋር ሲደራደር ማክለስኪን ከጐኑ አስቀምጦ ይሆናል ። ማክለስኪም የሲቪል ልብስ ለብሶ ይሁን እንጂ ሽጉጡን ታጥቆ ነው በስብሰባ ላይ የሚቀመጠው ። ሶሎዞን ለስብሰባ ጠርቶ አደጋ በሱ ላይ ለመጣል ያስቸግራል ። በዚህ ላይ ማን ደፋር ነው የፖሊስ ሻምበል ገድሎ የሚያመልጥ፣ በጋዜጦች ፣ በፖሊሱ ክፍል ፣ በሀይማኖት ድርጅቶች፣ ባጠቃላይ በመላ ከተማይቱ የሚነደውን እሳትስ ማን ሊያጠፋው ይችላል? የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ኩስ የነካው በትር ይሆናል ። በዚህ ሁኔታ ላይ የዶኑ የፖለቲካ ተገናኞች እንኳን ከኛ መራቃቸው የማይቀር ነው ። ስለዚህ ይህን ሁሉ አስብበት" ሲል ሄገን ሶኒን በአንክሮ አስገነዘበው ።

ሶኒ ምን ችገረኝ በማለት ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፣ "ሶሎዞ ለዘለአለም ማክለስኪ ጉያ ስር ተሸጉጦ አይኖር ። እኛም እንጠብቃለን" አለ ።

ከሌሜንዛና ቴስዩ ጦርነት ቢነሳ ከሌሎቹ ይበልጥ መከረኞቹ እነሱ መሆናቸውን በመገንዘብ በሲጋት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲጋራቸውን እያቦነኑ ያዳምጡ ነበር ። አልቢቸዋል ።

ሚካኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲናገር ያቀረበው ጥያቄ ሽማግሌውን ከሀኪም ቤት አውጥቶ ወደ ቤት ማምጣት ይቻል እንደሆን ነበር ። ይህን ጥያቄ ሄገንም እራሱ ቀደም ሲል አንስቶት እንደነበር ለሶኒ ከነገረው በኋላ ሽማግሌው ገና የሀኪሞች የቅርብ ክትትል ስለሚያስፈልገው ለማ ውጣት እንደማይቻል መለሰለት ።

"እንግዲያስ ሶሎዞን አሁኑኑ ማግኘት አለብን ። ሰውየው አደገኛ ነው ። አዲስ ዘዴ ሊቀይስ ይችላል ። 'የሽማግሌው መሞት ወሳኝ ነው' የሚል ግምት እንዳለው አትዘንጉ ። ተስፋ ከቆረጠ በዶኑ ላይ ሌላ የግድያ ሙከራ ለማድረግ ወደኋላ አይልም ። ያውም የፖሊስ ሻምበል ከሱ ጐን ሆኖ ምን እንደሚሆን ይታወቃል? አሁኑኑ ሶሎዞን መድፋት አለብን" አለ ሚካኤል ።

ማክለስኪ እያለ ምን አይነት እርምጃ መውሰድ እንደሚቻል ሄገን ጥያቄ አቀረበላቸው ። ሚካኤል አሁንም መልስ ጠቆመ ።

"እርግጥ ማክለስኪና ሶሎዞ አንድ ላይ እያሉ የመግደል ሙከራ ማድረግ ሊሆን የማይችል ይመስላል ። ነገር ግን ማክለስኪን ገድሎ ከሀገ ወጥ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር የሚሰራውን ደባ የዶኑ ደጋፊ በሆኑ ጋዜጦች አማካይነት መረጃ አቅርቦ በማጋለጥ የመገደሉን አስፈላጊነት ህዝቡ እንዲያምንና ቂጣውም ጋብ እንዲል ማድረግ እንደሚቻል ሚካኤል አስረዳ ። ቴስዮ እና ክሌሜንዛ ይህን ሀሳብ መቃወማቸውን ባይገልጹም ፊታቸውን ማጨፍገጋቸው አልቀረም ። ሶኒ ግን በፈገግታ "ቀጥል ማይክ ፣ አውራልን" አለው ።

ሚካኤል አፈር አለና ፣ "ደህና ፣ እነሱ የሚሹት ከሶሎዞ ጋር እንድደራደር ነው ። የምንሰበሰበው እኔ ፣ ሶሎዞና ማክለስኪ ብቻችንን ነው ። ስብሰባው ከሁለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀን በኋላ እንዲሆን አድርጉ ። የእኛ ጠቋሚዎች የስብሰ
ባው ቦታ የት እንደሚሆን እንዲነግሩን ይሁን ። ስብሰ
ባው መሆን ያለበት በህዝብ መዝናኛ ቦታዎች ነው ።
የግል ቤት እንዲወስዱኝ አልፈልግም ። በግልጽ ስፍራ
ከሆነ እኔም ሶሎዞም ደህንነታችን አስተማማኝ ይሆ
ናል ብለን እንገምታለን ። ከነሱ ጋር ስገናኝ መፈተሻ
ቸው ስለማይቀር መሳሪያ ሳልይዝ ባዶ እጄን መግባት
አለብኝ ። ነገር ግን ከነሱ ጋር ስብሰባ ከጀመርኩ በኋላ
መሳሪያ የማገኝበትን ዘዴ ቀይሱ ። ከዚያ የምሰራውን
እኔ አውቃለሁ'' ሲል ተናገረ ።

አራቱም ሰዎች ወደ ሚካኤል ዞር ብለው በአድ
ናቆት ተመለከቱት ። የክሌሜንዛና ቴስዮ አድናቆት
ድንጋጤ የተሞላበት ነበር ። ሄገን ግን ባይገርመውም
እንደ ማዘን ብሏል ። ሶኒ ሳቅ ፈንቅሎት እየተንከተከተ ፣

''አንተ ምርጥ የኮሌጅ ተማሪ! በቤተሰቡ ጉዳይ
ውስጥ መግባት አትሻም ነበር ። አሁን ግን ማክለስኪ
መንጋጭላህን ሲያቀምስህ ጊዜ እሱንም ሶሎዞንም
ካልገደልኩ ብለህ ትገለገላለህ ። የናንተ እኮ የስራ ግንኙነት
ግጭት ነው ። የግል ጠብ አድርገህ አትውሰደው'' አለው ።

ሚካኤል በክፍሉ ውስጥ ተቀምጠው የነበሩትን ሁሉ
ዞሮ ካያቸው በኋላ ሶኒን ትኩር ብሎ ተመለከተው ሶኒ ግን
አሁንም እየሳቀ ፣ ''ሁለቱንም መግደል ትሻለህ? ስማ አንተ
ልጅ ፣ እነሱን ብትገድል ሜዳሊያ የምትሸለም እንዳይመስ
ልህ ። ይልቁንም በኤሌክትሪክ ወንበር ላይ አስቀምጠ
መንግስት ይገድልሀል እንጂ ። ጦር ሜዳ ታደርገው
እንደ ነበር ራቅ ብለህ የምትተኩስም እንዳይመስልህ ።
የአይኑ ጥራት እስኪታይህ ጠጋ ብለህ እራሱን ስታፈነ
ዳው የአንጐሉ ፍንጣሪ የለበስከውን የዝነኛውን ኮሌጅህን
ልብስ እንደሚበክለው አትዘንጋ ። ታዲያ አንድ ሰው በጥ
ፊ መታኸኝ ብለህ እንዲህ ታደርጋለህ?'' ሲል አላገጠበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል ከመቀመጫው ተነሳና ፥ "ሳቁ ቢበቃህ ይሻልሀል!" አለ በቁጣ ። በሚካኤል ላይ ይታይ የነበረው ለውጥ ከተለመደው የተለየ በመሆኑ ይስቁ የነበሩት ሁሉ ፈገግታቸው ጠፋ ። ሚካኤል ግዙፍ ባይሆንም ግርማው አደጋን ይጠራ ነበር ። አባቱ በሱ ተመስሎ የመጣ መሰለ ። አይኑ ቀልቶ ፊቱ ገረጣ ። ታላቅ ወንድሙን ከአሁን አሁን ዘሎ ያንቀዋል የሚል ጥርጣሬ አሳደረ ። በዚያ ወቅት እንኳን መሳሪያ አልያዘ ብቻ ። ሶኒ ሁኔታውን ተመልክቶ መሳቁን ተወ ።

ሚካኤል ሞትን በሚጠራ ድምጽ ፥ "አንተ የውሻ ልጅ ፥ የማላደርገው ይመስልሀል?" በማለት ሶኒ ላይ አፈጠጠበት ።

ሶኒ ሳቁን ትቶ ልብ በሚነካ አነጋገር ፥ "እንደምታደርገው አውቃለሁ ። ባንተ አልነበረም የሳቅሁት ። ሁኔታዎች በዚህ መልክ መለወጣቸው ነው ያሳቀኝ ። ከመላ ቤተሰባችን ቆራጥነትህን ሁሌ ስናገረው የነበረ ነው ። ከዶኑም ይበልጥ ቆራጥ ነህ ። ያለሽማግሌው ከለላ መኖር የምትችል አንተ ብቻ ነህ ። በህጻንነታችን ካንተ ትልቅ ብሆንም እኔን ካልደበደብኩ ብለህ ትገለገል የነበረው ይታወሰኛል ። ፍሬዲ ብቻ ነበር ያንተ መድሀኒት ፥ ዋጋህን ይሰጥህ ነበር ። አሁን ደግሞ ሶሎዞ የዋህ ያገኘ መሰለው ። ምክንያቱም ማክለስኪ ሲደበድብህ አንዳችም ምላሽ ሳትሰጠው ዱላውን ተቀበልክ ። በቤተሰቡም ውዝግብ እንደማትገባ ይታወቃል ። ስለዚህ ሶሎዞ ከአንተ ጋር ፊት ለፊት ተቀምጠ መደራደር አላስፈራውም ። ማክለስኪም እንዲሁ የዋህ አድርጐህል ። ያም ሆነ ይህ አንተ ግን ኮርሌዎኔ ነህ ፥ አይደል? አንተ የውሻ ልጅ! አባታችን ከተመታበት ካለፉት ሶስት ቀናት ወዲህ የዚያን የዝነኛ ትምህርት ቤትህን ትምህርት ፥ የዚያን የጦር ሜዳ ጀግንነትህን ኩራት እርግፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

አድርገህ ከኛ ጋር እንድትሆን ስጠብት ቆይቻለሁ ። ቀኝ እጄ ሆነህ አባታችንና ቤተሰባችንን ሊያጠፉ የሚዙትን ሁሉ ድቤ እንድናስገጣቸው ተመኝቼ ስጠባበቅ ነበር ። መንጋጭላህ ጡጫ ሲቀምስ ሆነ የተመኘሁት ሊሆን የቻለው ፥ አይደል?" አለ ።

በከፍሉ ውስጥ የነበረው ውጥረት ሁሉ ላላ አለ ። ሚካኤል እራሱን ነቀነቀና ፥

"ሶኒ ፥ ያሰብኩትን የማደርገው ሊደረግ የሚቻለው ይኸው ብቻ ሆኖ ስለታየኝ ነው" አለ ። "ከእንግዲህ ሶሎዞ በሽግግሌው ላይ ጥፋት እንዲሰነዘር አንዳችም ቀዳዳ አልሰጠውም ። እንደሚመስለኝ አጠገቡ ሊደርስ የሚችል ሰው እኔ ብቻ ነኝ ። እንደግስበውም ሌላ ሰው ደፍሮ ሻምበል ማክለስኪ ላይ ሊተኩሰበት የሚቃጣ አይመስለኝም ። ምናልባት ፥ ሶኒ አንተ ትችል ይሆናል ። ነገር ግን አንተ ሚስትና ልጆች አሉህ ፥ አንተ ሽግግሌው ተሽሎት ሀላፊነቱን እስኪረከብ የቤተሰቡን ስራ መምራት ይኖርብሀል ። ስለዚህ ይህን የመሰለው ተልእኮ የሚቀረው ለኔና ለፍሬዲ ብቻ ይሆናል ። ፍሬዲ አሁን በድንጋጤ ህሊናውን ስቶ ይገኛል ። በመጨረሻም ለዚህ ተግባር የምቀረው እኔ ብቻ ነኝ ። ጉዳዩ የግንዛቤ እንጂ መንጋጭላዬን በጡጫ ስለተመታሁ ለመበቀል ብዬ አይደለም ።"

ሶኒ ወደ ሚካኤል ሄደና እቅፍ አደረገው ።

"አንተ ከኛ ጉን እስከሆንክ ድረስ ምክንያትህ የፈለገው ቢሆን ደንታ የለኝም ። እና አንድ ነገር ልንገርህ ፥ ተጀምሮ እስኪጨረስ ትከከል ነህ ። ቶም ምን ይመስልሀል?"

ሄገን በመስማማት ፥ "ምክንያቱ መሰረት ያለው ነው ፥" አለ ። "ያ ቱርክ ስለ ድርድር ያነሳው ከልቡ አልመሰለኝም ። ዶኑ ላይ ሌላ የመግደል ሙከራ ግድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረጉ የማይቀር ይመስለኛል ። ስለዚህ ሶሎዞን ለመምታት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይገባናል ። ከሻምበሉ ጋር ቢሆንም እንኳን ወደ ኋላ ማለት የለብንም ። ነገር ግን ማንም ያድርገው ማን ይህ ጉዳይ ትልቅ ውዝግብ ማን ሳቱ አይቀርም ። ታዲያ ሚካኤል ነው ይህን ተልእኮ መወጣት ያለበት?" አለ ።

"እኔ ላደርገው እችላለሁ?" አለ ሶኒ በለሆሳስ ። ሄነን ትእግስት አልባ ሆኖ እራሱን ነቀነቀና ፥ "ሶሎን አስር ፖሊሶች ቢያጅቡትም አንተ ካለህበት የአንድ ማይል ርቀት እንኳን አይጠጋህም" አለ ። "ከዚህም በላይ የቤተሰቡ ተጠባባቂ የበላይ ነህ ። አንተን ለአደጋ ማጋለጥ አይቻልም" አለና ወደ ክሌሜንዛና ቴስዮ ዞር ብሎ ፥ "ከሁለታችሁ ሰዎች መሀል ቁልፍ የሆነ ይህን ተልእኮ ሊፈጽም የሚችል ሰው አይኖርምን ይህን ማድረግ የሚችል ሰው ቢገኝ እድሜ ልኩን ስለ ገንዘብ እንዳያስብ ይደረግ ነበር ።"

"ሶሎዞ የማያውቀው ሰው የለም ። እኔና ቴስዮም ብንሞክር ባንዴ ይነቃብናል" አለ ክሌሜንዛ ። ሌላ ገና ያልታወቀ ፥ ሪኮርድ የሌለበት ገዳይ ሊያገኙ ይችሉም እንደሆነ ቢጠየቁ ሁለቱም እራሳቸውን በአሉታ ነቀነቁ ። ቴስዮ ፥ "ተራ ወሮበላ ልኮ ሶሎዞን ለማጥፋት መሞከር አንድ የሰፈር ቡድን ከአለም አቀፍ ተጫዋቾች ጋር ግጋጠም ይሆናል ፥" በማለት ይህን የመሰለ ሙከራ እንዳይደረግ አሳሰባቸው ።

"እንግዲያስ ማይክ ነው መሆን ያለበት" አለ ሶኒ ። "ይህን ለማለት ሚሊዮን ምክንያት ይኖራል ። ሞነኛው ምክንያት ጠላቶቻችን ሚካኤልን ቁም ነገር መስራት የማይችል እንከፍ አድርገው ገምተውታል ። ስለዚህ ያን ቱርክ መምታት የምንችለው በሚካኤል አማካይነት ብቻ ነው ። እንግዲህ በተልእኮው ላይ እን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዴት አድርገን ልንረዳው እንደምንችል መቀየስ አለ
ብን ። ቶም ፥ ክሌሜንዛና ቴስዮ ፥ ሶሎዞ ሚካኤልን
ለስብሰባ የት እንደሚወስደው ተከታትላችሁ ድረሱ
ልኝ።ይህን ሚስጥር ለማግኘት የሚፈጀውን ገንዘብ ይፍጅ።
ቦታውን ካወቅን ከዚያ ከደረሰ በኋላ መሳሪያ እንዲደርስ
ለት ዘዴ እንቀይሳለን ። ክሌሜንዛ ከሽጉጦችህ መሀከል
አድራሻው ያልተመዘገበና የአሻራ ደብዛውን ማጥፋት
የሚቻል ጥሩ ሽጉጥ መርጠህ አዘጋጅ ። ሀይለኛ ከሆነ
ስለማነጣጠሩ አትስጋ ። አናታቸው ላይ ሆኖ ነው
የሚተኩሰው ። ማይክ ፥ ሽጉጥህን ከተጠቀምክበት በኋላ
እዛው ወለል ላይ ጣለው ። በጅህ ላይ እንዳይታይ ። ክሌ
ሜንዛ በተለመደው ዘዴህ ፥ ሽጉጡ አሻራ እንዳያስቀር
የሆነ ነገር ጠምጥምበት ። ማይክ አስታውስ ፥ ሽጉጡ
በጅህ እስካልተያዘ ድረስ በሀሰት ምስክር ሁሉንም
ነገር ማስተካከል እንችላለን ። መጓጓዣ ይዘጋጅልህና
አገሩን ጥለህ ትሄዳለህ ። በዚያው ግርግሩ ጋብ እስኪል
ረጅም እረፍት ትወስዳለህ ። ነገር ግን ወዳጅህን እንዳት
ሰናበታት ፥ እንዲያውም እንዳትደውልላት ። አገሩን
ለቀህ በሰላም ከምትሄድበት ቦታ ከደረስክ በኋላ ደህ
ንነትህን እነግራታለሁ ። ይህ ትእዛዝ ነው ።”

ሚካኤልን ያ አደጋ ሲያንዣብብበት የሚመጣበት
ደስ የሚል ቅዝቅዝ ያለ ስሜት ሰውነቱን ወረረው ።

“ወዳጅህን አታናግራት ወይም እንዲህ አታድርግ
የሚለውን ፍሬቢስ አባባል ልትነግረኝ አይገባም ።
ደህና ሰንብች ለማለት የምደውልላት መስሎህ ኖሯል?”
ሲል ሚካኤል ተናገረ ።

ሶኒ በችኮላ አነጋገር ፥ “እሺ ይሁን ፥ ጅማሪ በመ
ሆንህ የምታደርገውን ሁሉ ልነግርህ ስለሚገባ ብቻ
ነው” አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤልም በፈገግታ ፥ "ምናባክ ማለትህ ነው ጀግሪ ስትለኝ? ሽማግሌው ሲናገራቸው የነበራቸውን ነጥቦች ሁሉ አንተ ትሰማ እንደነበረው እኔም በውል አዳምጫለሁ ። አለዚያ እንዴት እንዲህ ብልጥ ልሆን ቻልኩ ይመስልሀል?" አለው ። ሁለቱም ተሳሳቁ ።

ሄገን ለሁሉም መጠጥ ቀዳ ። የቀፈፈው ይመስላል ። ጠቢቡ መሪ የግዱን ወደ ጦርነት እንደሚዘምት ፥ የሀግ ባለሙያው የግዱን ወደ ክስ እንደሚያመራ አይነት ነበር ። "ደህና እንግዲህ ፥ ያም ሆነ ይህ ፥ ቢያንስ አሁን ምን እንደምናደርግ እናውቃለን ማለት ነው" አለ ሄገን ።

ምእራፍ አስራ አንድ

ሻምበል ማክለስኪ ከቢሮው ተቀምጦ ሶስት ያበጡ ኤንቬሎፖችን በጣቱ ይነካካቸዋል ። እነዚህ ኤንቬሎፖች ባለፈው ምሽት የሱ ፖሊሶች የኮርሌዎኔን ቤተሰብ ቁማር ቤት ወረው የሰበሰቧቸው የውርርድ ወረቀቶች ናቸው ። ኤንቬሎፖቹ የተዘረፉባቸው የቁማር ቤቱ ባለ ቤቶች እነዚህ የውርርድ ኤንቬሎፖች ካልተመለሱላቸው ፥ ቁማርተኞቹ በሀሰት አሸንፈናል ብለው በርካታ ገንዘብ ክፈሉን ሊሏቸው ይችላሉ ። ማክለስኪ በኤንቬሎፖቹ ውስጥ የተመዘገቡትን ቁጥሮች ትርጉማቸውን ለማወቅ በመሻት ቁጭ ብሎ በሀሳብ ፈቱን ያኮማትራል ። በውርርድ ወረቀቶቹ ላይ የተመዘገቡትን ቁጥሮች ትርጉም ማወቅ ለማክለስኪ ከፍተኛ ጥቅም አለው ። ለምሳሌ የሀምሳ ሺህ ብር አሸናፊ የሆነ ቁጥር ካለበት እሱ ለባለቁማር ቤቶቹ በአምስት ሺህ ብር መልሶ ቢሸጥላቸው ግድ የለውም ። ነገር ግን ያ ወረቀት የመቶ ሺህ ብር ወይም የሁለት መቶ ሺህ ብር አሸናፊ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢሆንስ? እንዲህ ከሆነ የሚሸጥበት ዋጋ ከፍ ማለቱ አይቀርም ። ማክለስኪ ለጥቂት ጊዜ ኤንቬሎፖቹን አገላበጠና ፣ ባለቱግር ቤቱን ጥቂት ካቋነጠነጠው በኋላ የሚከፍለውን እስኪነግረው ለመቆየት ወሰነ ። ሰውየው ከሚቀርብለት ገንዘብ መጠን የወረቀቶቹን ዋጋ ሊገ ነዘብ ይችላል ።

ማክለስኪ የጣቢያውን ሰአት ቀና ብሎ ሲመለከት ያን ቀፋፊ ሶሎዞን በመኪናው ጭኖ ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ጋር ለስብሰባ የሚወስድበት ሰአት መድረሱን ተረዳ ። ልብሱን ከሚያስቀምጥበት ቁምሳጥን አመራና የሲቪል ልብሱን ለበሰ ። ለሚስቱ ደውሎ ለስራ ስለሚያመሽ ለእራት እንደማይመጣ ነገራት ። የልቡን ስለማያጫው ታት የሚሰራውን ሁሉ አታውቅም ። እሷ በፖሊስነት ስራው የሚገኘው ደመወዝ ብቻ የሚያስተዳድራት ይመስላታል ። እናቱም ስላባቱ ገቢ እንዲሁ ታስብ ነበር ። ነገር ግን ይህን ጮሌነቱን ካገኘው ቆይቷል ። እድሜ ለአባቱ ፣ ዘዴዎችን አስተምሮታል ።

ድሮ አባቱ አምሳ አለቃ ሳለ በየሳምንቱ የስድስት አመት ልጁን ማክለስኪን ይዞ በየሰፈሩ ይዞር ነበር ። ወደ ባለሱቆች ጐራ ይልና ፣ 'ይሸውላችሁ ይሄ ነው ልጄ ፣' ይላቸዋል ።

ባለሱቆቹ ልጁን ይጨብጡትና በከንቱ ውዳሴ ከምካሹት በኋላ የገንዘብ ማስቀመጫ ሳጥናቸውን ከፊት አድርገው የአምስት ወይም የአስር ብር ስጦታ ይለግ ሱታል ። በእለቱ አመሻሽ ላይ ትንሹ ማክለስኪ ኪሶቹ በሙሉ በብር ይታጨቃሉ ። ትንሹ ማክለስኪ አባቱ በየወሩ ልጁን አስከትሎ መንደር ለመንደር በዞረ ቁጥር ሰዎች ብር የሚያሳቅፉት አባቱ የሰው መውደድን በመጐናጸፉ እየመሰለው ልቡ በኩራት ይሞላ ነበር ። አባቱ በርግጥ በዚህ ሁኔታ የሰበሰበውን ገንዘብ ልጁ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲያድግ ለኮሌጅ ትምህርቱ ወጪ እንዲሆነው እባንክ ያስቀምጥለታል ። በመጨረሻ ለትንሹ ማርክ የሚደር ሰው ሀምሳ ሳንቲም ብቻ ነው ። ታዲያ የማርክ አጎቶች ቤት መጥተው ፥ "ማሙሽ ፥ ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋ ለህ?" ሲሉት እየተኩላተፈ ፥ "ፖሊስ" ሲላቸው ብዙ ይስቁ ነበር ። ይህ ልጅ ሲያድግ አባቱ ወደ ኮሌጅ ገብቶ እን ዲማር ቢፈልግም ወጣቱ ማክለስኪ ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንደጨረሰ ወደ ፖሊስ ትምህርት ቤት ገባ ።

ማክለስኪ በስራ ላይ ሲሰማራ ወረበሎችን በጥ ጫው ልክ ያስገባ ፥ ሀቀኛና ጐበዝ ፖሊስ ነበር ። እሱ ግን አባቱን ይመስል ልጁን አስከትሎ የጽዳትና የት ራፊክ ህግ የመሳሰሉትን ቀላል ጥፋቶች ከጣሱ ባለ ሱቆች ቤት በመዞር ገንዘብ አይሰበስብም ። እነዚህ ሰዎች የሚሸጡሉትን ገንዘብ እንደ ልፋቱ ዋጋ ስለሚ ቆጥረው እራሱ ነበር የሚቀበላቸው ። የስራ ባልደ ረቦቹ በተለይ በክረምት ወራት እንደሚያደርጉት በእግር የመዘዋወር ስራውን ትቶ ወደሲኒማ ቤት ወይም ምግብ ቤት ጐራ አይልም ። እየተዘዋወረ የሚያ ደርገውን ጥበቃ በጥንቃቄ ያካሂዳል ። ለሱቆቹም ከፍ ተኛ ከለላ ይደረግላቸዋል ። ሱሰኛ ጠጪዎች የሚጋ ብዛቸው ፍለጋ ወደ ጥበቃ ክልሉ ሲመጡ በሚሰጣ ቸው ቅጣት ሁለተኛ እዚያ አካባቢ እንዳይደርሱ ያደ ርጋቸው ነበር ። ነጋዴዎቹ ለዚህ ጉብዝናው ባለውለታው ነበሩ ። ውለታውንም አይረሱም ።

ማክለስኪ የስርአቱም ታዛዥ ነው ። በክልሉ የሚ ገኙ የቁማር ቤት ባለቤቶችም እነሱ ከሚሰጡት ድርሻ በላይ ለማስጨመር ሲል ውዝግብ እንደማይፈጥር ያው ቁታል ። በስርአቱ ሀቀኛ ፖሊስ ተብሎ ስለሚቆጠር በሚያስደንቅ ፍጥነት አደገ ባይባልም ወቅቱን ጠብቆ ሳይቋረጥ ነው እድገቱን ያገኘው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ጊዜ የማክለስኪ ቤተሰብ እየጨመረ መጣ። የአራት ልጆች አባት ሆነ። ከልጆቹ አንዳቸውም ፖሊስ የሆነ የለም። ሁሉም ዝነኛው ፎርድሀም ዩኒቨርሲቲ ገቡ። ማክለስኪም ከአምሳ አለቃ መቶ አለቃ፥ ከዚያም ሻም በል ለመሆን በቃ። የሚጐድላቸው ነገር አልነበረም። በዚሁ ወቅት ነበር ማክለስኪም ጥቅሙን በሚመለከት ቁላል ተደራዳሪ አለመሆኑ የተከሰተው። የሱ ክልል ቁማር ቤቶች ከሌላው ሰፈር ቁማር ቤቶች የበለ ለጠ ነው ይከፍሉት የነበር። ምናልባትም ይህ ክፍያ ከፍ ያለው ማክለስኪ አራት ልጆቹን ኮሌጅ ልኮ ስለ ሚያስተምር ይሆናል።

ማክለስኪ እራሱ ንጹህ የሆነ ጉቦ መብላት ትክክል ነው ብሎ ያምናል። ገና ለገና መስሪያ ቤቱ በቂ ደመ ወዝ አይከፍለውምና ልጆቹ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው ኮሌጆች ሄደው ለምን ይማራሉ? ያን ሁሉ ሰው ነፍ ሱን ሽጦ ይጠብቀዋል። ሊያስፈራሩ መሳሪያ የመዘ ዙትን ወሮበሎች ድባቅ እንደመታቸው ማህደሩ ያረ ጋግጥለታል። ስለዚህ በሳምንት ከባለ አንድ መቶ ብር ደመወዙ በላይ ሊከፍል ይገባዋል። በደመወዙ ማነስ አይማረርም። ይልቁንም ማንም ሰው በዘዴ እራሱን መጠበቅ እንዳለበት ይገምት ነበር እንጅ።

ብሩኖ ታታሊያ የቆየ ወዳጁ ነው። ብሩኖ ከማክ ለስኪ ልጅ ጋር ፎርድሀም ዩኒቨርሲቲ ይማር ነበር። ከዚያም የማታ ክበቡን ከፈተ። አልፎ አልፎ የማክለስኪ ቤተሰብ ሊዝናና ሲሻ የሙዚቃ፥ የምግብና የመጥ ጅማስ በተሟላበት በዚሁ ቤት ምሽቱን ያሳልፋል። ከፍሎ ሳይሆን ተስተናግዶ ለአዲሱ አመት ዋዜማም ቤተሰቡ በዚህ ቤት እንዲዝናና ያማረ የግብዣ ወረቀት ይላክለታል። እንዲህ በሚጋበዙበት ጊዜ ብሩኖ የማክለ ስኪን ቤተሰብ አባላት ከዝነኛ ተዋንያንና የኪነት ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋር ያስተዋውቃቸዋል ። ብሩኖ ይህን ሁሉ ሲያደርግ አልፎ አልፎ አነስተኛ የውለታ ምላሽ መጠየቁ አልቀረም ። ለምሳሌ በአጭበርባሪነት የፖሊስ ሪኮርድ ያላቸው ቆንጆዎች ከመዝናኛ ቤቱ ገብተው መስራት እንዲችሉ ከተመዘገቡበት ወንጀል እንዲፋቅላቸው ብሩኖ መጠየቁና ማክለስኪም በደስታ እሺ ማለቱ አልቀረም ።

ማክለስኪ ሌሎች ሰዎች አንድ ውለታ ሲጠይቁት ከኋላ ምን እቅድ እንዳላቸው የተረዳባቸው መሆኑን እንዲያውቁበት አይሻም ። ለምሳሌ ሶሎዞ ዶን ኮርሌዎኔ የተኛበትን ሀኪም ቤት የሚጠብቁትን ዘቦች እንዲያስወግድለት በጠየቀው ጊዜ ለምን ብሎ አልጠየቀም ። የጠየቀው ምን ያህል እንደሚከፈለው ብቻ ነበር ። ሶሎዞ አስር ሺህ ብር እሰጥሀለሁ ሲለው ምክንያቱ ገባው ። አላንገራገረም ። ኮርሌዎኔ በአሜሪካ ካሉት ዝነኛ የማፊያ ወንበዴዎች ሁሉ ይበልጥ ብዙ የፖለቲካ ግንኙነትና ድጋፍ ያለው ሰው ነው ። እሱን የገደለ ሰው ለሀገሪቱ ትልቅ ውለታ እንደዋለላት ይቆጠራል ። ማክለስኪ ገንዘቡን በቅድሚያ ተቀብሎ ስራውን ፈጸመ ። የዚያን እለት ሚካኤል በተመታበት ምሽት ፣ ሶሎዞ ደውሎ በሆስፒታሉ አካባቢ ሁለት የኮርሌዎኔ ሰዎች መታየታቸውን በነገረው ጊዜ በቁጣ ነበር ወደ ሀኪም ቤት የገሰገሰው ። ማክለስኪ ቀደም ብሎ ሀኪም ቤቱ የነበሩትን የቴስዮን ሰዎች ወስዶ አስሯቸዋል ። የደህንነት ጠባቂ ዘቦቹንም ዶኑ ከተኛበት ክፍል በራፍ አስነስቶ ወደ ሌላ ቦታ አዛውሯቸዋል ። ይህን ሁሉ አድርጎም አካባቢው አሁንም እንደሶሎዞ ፍላጎት ከኮርሌዎኔ ሰዎች አልጸዳም ። ስለዚህ ተልእኮውን ባለመወጣቱ የልጅ ልጆቹን አስተምርበታለሁ ብሎ አቅዶ የነበረውን ከሶሎዞ የተቀበለውን አስር ሺህ ብር ለሶሎዞ ሊመልስለት ከብሩ ያስገድደዋል ። ይህ ሲታሰበው

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ንዴቱ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ወደ ሀኪም ቤቱ ገስግሶ ሚካኤልን ሊደበድበው የበቃው ።

ይሁን እንጂ ነገሮች ዞሮ ዞሮ ከበፊቱም የበለጠ ተመቻችተዋል ። በታታሊያ የማታ ክበብ ከሶሎዞ ጋር ተገናኝቶ እንዲያውም የተሻለ ሴላ ውለታ ተደራድሯል። አሁንም ማክለስኪ ለምን ብሎ አልጠየቀም ። መልሱን ያውቀዋል ። ያሁኑ ውለታዬ አደጋ ሊያደርስብኝ ይችል ይሆን? የሚል ሀሳብ ጨርሶ አልመጣለትም ። የኒውዮርክ ከተማ ፖሊስ ሻምበልን ለመግደል ማን ይቃጣል ብሎ ያስብ ። አገር ያሸነፈ የማፊያ ወንበዴ እንኳን ቢሆን ዝቅተኛው ሮንድ በጥፊ ቢወለውለው በጸጋ ነው የሚቀበለው ። ፖሊስን መግደል በጭራሽ አያዋጣም ። እንዲህ ያለው ሙከራ ቢደረግ አጸፋው ገደብ የለሽ ይሆናል ። አያሌ ወረበሎች አልታሰር ብለው ሲሸሹ ወይም ወንጀል ሰርተው ሲያመልጡ ተገደሉ ቢባል ምን ሊደረግ ይቻላል ?

ማክለስኪ በረሾሙ ተነፈሰና ጣቢያውን ለቆ ለመሄድ ተነሳ ። ችግር ፥ ሁልጊዜም ችግር፣ አየርላንድ ትናር የነበረችው የሚስቱ እህት በካንሰር ስትሰቃይ ኖራ ከመሞቷ በፊት እሷን ለማሳከም ብዙ አውጥቷል። አሁን ደግሞ የቀብሯም ወጪ አለበት ። በዚያው አገር ለሚኖሩ አጐቶቹና አክስቶቹም አፈሩ የተሟጠጠ የድንች እርሻቸውን ለማልማት ገንዘብ ይልካል ። በዚህ እንኳን አይከፋም ። ሚስቱና እሱ ወደ አየርላንድ በሚሄዱ ጊዜ ንጉሳዊ አቀባበል ይደረግላቸዋል ። ስለዚህ አሁንም ቢሆን የማክለስኪ ኪስ በዚህ አይነት ከደለበ፣ በተለይም እንግዲህ ጦርነቱ ካበቃ በተከታዩ በጋ ወቅትም ቤተሰቡን ይዞ መሄዱ የማይቀር ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማከለስነኒ የጥበቃ ጸሐፊውን ፖሊስ ከተፈለገ የት እንደሚገኝ ነገረው ። ቢያስፈልግ ሶሎዞ በየወቅቱ ወሬ የሚያቀብለኝ ጠቋሚዬ ነው ለማለት ስለሚችል ከሶሎዞ ጋር የሚገኝ መሆኑን መደበቁ አስፈላጊ መስሎ አልታየውም ። ስለዚህ ከፖሊስ ጣቢያው ትንሽ በእ ግሩ ራቅ ብሎ ከተጓዘ በኋላ ከሶሎዞ ጋር ከተቃጠረ በት ቦታ ለመሄድ ታክሲ ተሳፈረ ።

ሁሉንም ጉዳይ ፡ ማለትም አገሩን ለቆ የሚሄድበ ትን ፡ የውሸት ፓስፖርቱን ፡ የመርከበኛነት መታወቂያ ውን ፡ ሲሲሊ ላይ ጐራ የምትል የጣልያን መርከብ መሳፈሪያውን ሁሉ ለሚካኤል ያደራጀለት ቶም ሄገን ነበር ። ሶኒም በበኩሉ ሚካኤል ተልእኮውን ሲያጠና ቅቅ የሚያመልጥበት መኪናና ቴስዮን የመሰለ አስተ ማማኝ ሹፌር አዘጋጅቶለታል ። መኪናዋም ሞተሯ አስ ተማማኝ የሆነ ፡ ከላይ የተገጫጨችና የሀሰት ታርጋ የተለጠፈባት ፤ አድራሻዋን ለማግኘት የማይቻል ፡ ይህን ለመሰለ ስራ ተቀምጣ የቆየች ናት ።

የዚያኑ እለት በሲሲሊ ተራራማ ገጠር ውስጥ ለሚካኤል መደበቂያ የሚሆን ቦታ የሚያዘጋጅ መልእ ክተኛ ወደ አንድ በሲሲሊ ደሴት የሚኖር የማፊያ ሹም ዘንድ ተላከ ።

ሚካኤል እለቱን ኋላ የሚጠቀምበትን ባለነጥብ 22 ካሊበር ሽጉጥን አተኳኮስ በክሌሜንዛ አሰልጣ ኝነት ሲለማመድ ዋለ ። ክሌሜንዛ የሽጉጡ ቃታ ጠበቅ ስላለ አላላው ። የመሳሪያው ጩኸት ግን እንዲቀንስ አልተፈለገም ። ጉዳዩን የማያውቅ ሰው በጉዳዩ ጣልቃ እንዳይገባ ከሩቅ እንዲሸሽ ድምጹ አስፈላጊ ነበር ።

“ሽጉጡን ከተጠቀምክበት በኋላ ጣለው ። እጅ ህን ወደታች አውርድና ቀስ ብለህ ልቀቀው ። ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

መላሪያ የያዝክ ይመስላቸዋል ። አይን አይንህን ስለ ሚያዩ አትኩረህ አትመልከታቸው ። ነገር ግን አይንህ ከሰዎች አቅጣጫ መለየት የለበትም ። ከቤቱ እንደ ወጣህ ቴስዮ ይጠብቅሀል ። መኪና ውስጥ ዘለህ ግባ ። ከዚያ በኋላ ያለውን ለሱ ተወው ። ማንነትህን ለመለየት ስለ ማያስችል ይህን ባርኔጣ አድርግ" አለና ክሌሜንዛ ባርኔጣውን ሚካኤል እራስ ላይ ጫነው ። ሚካኤል የክሌሜንዛን ምክር ካዳመጠ በኋላ ፥

"ለመሆኑ ሶሎዞ የት እንደሚወስደኝ ሶኒ አውቋል?" ሲል ጠየቀው ።

"ገና አልታወቀም ። ሶሎዞ ከፍተኛ ጥንቃቄ እያ ደረገ ነው ። ነገር ግን ስለ ደህንነትህ ምንም ስጋት አይ ግባህ ። አስታራቂው አንተ እስክትመለስ ከኛ ጋር ይቆ ያል ። አንተ አንድ ነገር ብትሆን አስራቂው በህይወቱ ይከፍላታል"

"አስታራቂው ይህን በመሰለ ውዝግብ ውስጥ ለምን አንገቱን ያስገባል?"

"የሚከፈለው ጠቃሚ ገንዘብ ስላለ ነዋ ። ሶሎዞ አስታራቂው ክፉ ነገር እንዲደርስበት አይሻም ። በሶ ሎዞ ዘንድ ያንተ ህይወት ያስታራቂውን ያህል ክብደት የላትም ። ስለዚህ ያንተ ደህንነት ምንም አያሰጋም ። ኋላ መከራ ውስጥ የምንገባው እኛ ነን" አለ ክሌ ሜንዛ ።

"ምን ያህል ውዝግብ የሚነሳ ይመስልሀል?"

"በጣም መጥፎ ይሆናል ። የታታሊያ ቤተሰብ በኮ ርሌዮኔ ቤተሰብ ላይ ጦርነት ማወጁ አይቀርም ። ሌሎቹ ቤተሰቦች አብዛኛዎቹ ለታታሊያ ቤተሰብ ነው የሚያ ግዙት ። የከተማው ጽዳት መስሪያ ቤት በዚህ ክረ ምት ዋናው ስራው ሬሳ ከየመንገዱ ማንሳት ይሆ ናል ። ይህን የመሰለው ሁኔታ በየአስር አመቱ ያጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥላል ። የተጠራቀመ ቂም ማስወገጃ ወቅት ይሆናል ። ለጠላቶቻችን ስንዝር ብንሰጣቸው ጋት ይጨምሩና ሁሉን በቁጥጥራቸው ስር ከማድረግ ወደኋላ አይሉም ። ሂት ለርን ሙኒክ ላይ ማቆም ሲገባቸው ባለማቆማቸው መዘዙ የከፋ መሆኑን ስናስታውስ ፣ እኛም ጠላቶቻችንን መቋቋም ያለብን ገና ከመጀመሪያው ላይ መሆን አለበት እንላለን ።"

ስለ ሂትለር ሲወራ ሚካኤል አባቱ ገና ጦርነቱ ሳይነሳ ይህንኑ ይናገር እንደነበር ትዝ አለው ። "እነ ዚህ የማፊያ ቤተሰቦች የአገር አስተዳደር ሚኒስቴርን የመምራት ስልጣን ቢኖራቸው ኖሮ ሁለተኛው የአ ለም ጦርነት አይነሳም ነበር ፣" በማለት እያሰበ ፈገግ አለ ።

የተኩሱ ልምምድ ሲያበቃ ወደ ቤታቸው ተመ ልሰው ሶኒ ከሚገኝበት ቢሮ አመሩ ። ሶኒ ከጠላቶች በትር እራሱን በከለለበት የአባቱ ቢሮ ከሶፋው ላይ ጋደም ብሎ አገኙት ። ጽዳቱ ያማረ የነበረው የዶኑ ቢሮ እንዲህ ተመሰቃቅሎ መመልከቱ ስላላስቻለው ሶኒ ይህን ፋይዳ ቢስ ሁኔታ ትቶ ቢሮውን እንዲያጸዳ ሚካኤል ነገረው ።

"የወታደር ካምፕ የምትጐበኝ መሰለህ እንዴ?" አለው ሶኒ አዛጋና ። "ማይክ ፣ ሶሎዞና ማክለስኪ የት ሊወስዱህ እንዳቀዱ ገና አላወቅንም ። ቦታውን ካላወ ቅን እንዴት አድርገን ነው መሳሪያ የምናቀብልህ?"

"መሳሪያውን ይዤው ልሄድ አልችልም? ላይፈ ትሹኝ ይችላሉ ። ቢፈትሹኝም ዘዴኞች ከሆን ላያገኙት ይችላሉ ። ደግሞስ ቢያገኙትስ ? ቢበዛ ሽጉጡን መው ሰድ ነው ፣ ሌላ ጉዳት አይደርስብኝ"

ሶኒ እራሱን ነቀነቀና "አይሆንም ፣ ይህ እድል በዚያ ሶሎዞ በሚሉት ዲቃላ ላይ የማያወላዳ ዱላ የም ናሳርፍበት ወቅት መሆን አለበት ። አስታውስ ፣ ከሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

ልህ መጀመሪያ የምትመታው እሱን ነው ። ማክለስኪ ቀስስተኛና ደደብ ስለሆነ እሱን ለመምታት በቂ ጊዜ ይኖርህል ። ለመሆኑ ሽጉጡን ከተጠቀምክበት በኋላ እንድትጥለው ከሌሜንዛ ነግሮህል"

"ሚሊዮን ጊዜ ነግሮኛል"

ሶኒ የሚካኤል መንጋጋ ተሸሎት እንደሆን ሲጠ ይቀው ፣ ሽቦ የተሰፋበት እንደሚጠዘጥዘው ገለጸለት ። ሚካኤል ዊስኪውን ከጠርሙሱ ላይ በቀጥታ ተጉ ነጨ ።

"ቀስ በል" አለው ሶኒ ። ሰክሮ በተግባሩ ላይ መቀላጠፍ እንዳያቅተውም አስጠነቀቀው ።

"ሶኒ ፣ ይህን ታላቅ ወንድምነትህን ተወኝ ። ከሶሎዞ ከሚበልጡ ጠንካራ ሰዎች ጋር ከዚህ በባሰ ሁኔታ ተጋጥሜአለሁ ። ሶሎዞ የታለ መድፉ? በአየር ላይ የጦር አውሮፕላን ድጋፍ አለው? ከባድ መሳሪያስ? ሶሎዞ አንድ የፖሊስ ሹም ከጐኑ ያስቀመጠ ወስላታ ነው ። እነሱን ለመግደል ቆርጦ ለተነሳ ሰው ምንም የሚያስቸግረው ጉዳይ አይኖርም ። አስቸጋሪው ነገር መቁረጡ ነው ። ከዚያ በኋላ ምን እንደመታቸው እንኳን ማወቅ አይችሉም"

ቶም ሄገን መዳሉበት ክፍል ገባና በተሳሳተ ስም የተመዘገበውን ስልክ አነሳ ።

"ምንም ወሬ የለም" አላቸው ሲጨርስ ። "ሶሎዞ እስከመጨረሻው ዝም ማለቱ ነው ።" ጥቂት ቆይቶ ስልኩ ሲጮህ ሶኒ አንሰቶ ከዚያ ለሚተላለፍለት መልእክት ፣

"እሺ ፣ እዚያው ይመጣል" የሚል መልስ ሰጠና ስልኩን ዘጋው ። ከት ብሎ ሳቀና ሚካኤልና ሶሎዞ ስለሚያካሂዱት ድርድር ከሶሎዞ ጋር ያደረጉትን ስምምነት ገለጸላቸው ። በዚያን እለት ከምሽቱ ሁለት ሰአት ላይ ሶሎዞና ማክለስኪ ሚካኤልን ከጃክ ዴምሲ ቡና ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ፊት ለፊት ያሳፍሩትና ወደ አንድ ስፍራ አብረው ይሄዳሉ ። የሶሎዞና የሚካኤልን ድርድር ማክለስኪ እን ዳይሰማ በጣልያንኛ ይካሄዳል ። ማክለስኪ 'ሶልዲ' ከምትለው ቃል በስተቀር ጣልያንኛ እንደማይችል ሶሎዞ አረጋግጧል ። ሚካኤል የሲሲሊን የህገረሰብ ቋንቋ እንደ ሚያውቅም ሶሎዞ የደረሰበት መሆኑን ሶኒ ነገራቸው ።

"ጣልያንኛውን እንኳን እንደ መርሳት ብያለሁ ። ደግነቱ ብዙ አናወራም ።"

"አደራዳሪው እጃችን ሳይገባ ሚካኤልን አንል ከውም" አለ ሄገን ።

ክሌሜንዛ በሀሳቡ በመሰማማት እራሱን ነቀነቀና፥ "አደራዳሪው በሶስት ዘቦች እየተጠበቀ አብሯቸው እኔ ቤት ካርታ እየተጫወተ ነው ። እሱን ከመልቀቃቸው በፊት ከኔ ትእዛዝ ይጠብቃሉ" አለው ። ሶሎዞ ሚካ ኤልን የሚወስድበትን ቦታ አለማወቃቸው ሁሉንም አሰጋቸው ። ማንም ይሁን ማን ሊያሳፍሩት የሚመጡትን ሰዎች መኪና ውስጥ እንዳሉ ሚካኤል እንዲያዳፍንባ ቸው ሶኒ ሀሳብ አቀረበ ። ሄገን በዚህ አልተስማማም ። ሶሎዞ መኪናው ውስጥ ባይኖርስ? በከንቱ ጣጣ ውስጥ መግባት ይሆናል ።

"ሶኒ ለምን ያን ፊሊፕስ የተባለ የደህንነት ሰራተኛ ደውለህ ማክለስኪ ወዴት እንደሚሄድ እንዲደርስበት አትነግረውም?" አለ ሄገን ። ሶኒ ፊልፕስን ደውሎ ባዘዘው መሰረት በግማሽ ሰአት ውስጥ የተፈለገውን መልስ አገኘላቸው ።

ሻምበል ማክለስኪ የት እንደሚገኝ መልእክት እየተወ ነው የሚሄደው ። የዚያን እለት ማታ ከሁለት እስከ አራት ሰአት ላይ ሉና አዙሬ ከተባለው ጸጥ ባለ አካባቢ ከሚገኝ ምግብ ቤት እንደሚያመሽ ፊሊፕስ በስልክ ለሶኒ ነገረው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምግብ ቤቱ የት እንደሚገኝ ሶኒ ሲጠይቅ ቴስዮ የሚያውቀው መሆኑን ገለጸለት ። የቦታውን አቀማመጥ በሲጋራ ቁራጮች ካርታ እየሰራ ሊያስረዳው ሞከረ ። ቀጥሎም ሚካኤል ተልእኮውን ከፈጸመ በኋላ የት እንደ ሚጠብቀውና የመኪና መብራት ምልክት እንደሚያሳ የው ፥ ችግር ገጥሞት ቢጮህም እንደሚደርስለት አስረ ዳው ። ቴስዮ ወደ ክሌሜንዛ ዞሮ ለሚካኤል የሚያቀብሉ ትን ሽጉጥ ከመጸዳጃ ክፍሏ ውስጥ ከምትገኝ አሮጌ የሽንት ቤት ውሀ ማጠራቀሚያ ከበስተኋላዋ በማጣበቂያ ቴፕ ለጥፈው እንደሚያኖሩለት የቦታውን አቀማመጥ ነገረው ።

"ማይክ" አለ ቴስዮ "ከፈተሹህ በኋላ ጥርጣሬ ያቸው ያበቃል ። ምግብ ቤቱ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ቆይ። ከዚያም ይቅርታ ጠይቅና ወደሽንት ቤት አምራ ። ከተ መለስክ በኋላ በፍጥነት ተልእኮህን ቀጥል" ።

ሶኒ ሚካኤልን እንዲህ በማለት አሰናበተው ፥

"በል እንግዲህ ፥ አንተ ልጅ ፥ ስራህን ጀምር ፥ ለእናታችን ሳትሰናበታት ለምን እንደሄድክ አስረዳታ ለሁ ። ጊዜው ሲደርስ ለወዳጅህ መልእክት እንዲደ ርሳት አደርጋለሁ"

"እሺ ፥ ለመሆኑ መቼ እምመለስ ይመስልሀል ?"

"ቢያንስ አንድ አመት ትቆያለህ"

ቶም ሄገን ጣልቃ ገባና ፥ "ዶኑ ምናልባት ጊዜው እንዲያጥር ሊያደርግ ይችላል ። በህዝብ መገናኛዎች የምንነዛው ወሬ ፥ የፖሊሱ ክፍል ጉዳዩን ለመደበቅ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ፥ የሌሎቹ ቤተሰቦች ቁጣ መጠን ፥ ይሄ ይሄ ጊዜውን ለማሳጠር የምናደርገውን ጥረት ይወስነዋል ። ያም ሆነ ይህ ከብዙ አካባቢ ቁጣ ማስነሳቱ የማይቀር ነው" ብሎ እንደተናገረ ፥ ሚካኤል እየጨበጠው ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"የሚቻልሆን አድርግ፣ በድጋሚ ለሌላ ሶስት አመት ከቤት ርቄ መቆየት አልሻም" አለው።

ሄገን ሚካኤል ሀሳቡን ቢለውጥም አይጠላም። ሌላውን አማራጭ ተቀብሎ ሶሎዞንም ሆነ ማክለስኪን ላለመግደል እንደሚቻል አንስቶ ነበር። ሚካኤል ግን እንዲህ ሲል ነበር የመለሰለት፣

"በቅድሚያ ውሳኔያችንን ትክክል አድርገን ተቀብለናል። እስካሁን ቁጭ ብዬ ስበላ ኖሬአለሁ። አሁን ግን ውለታዬን መመለስ አለብኝ።"

"የመንጋጋህ መሰበር እንዲህ አመለካከትህን ወደ በቀል ሊያዘነብለው አይገባም። ማክለስኪ እንደሆነ ጅል ነው። ጠባችሁ ከስራ ጋር የተያያዘ እንጂ የግል አይደለም" አለው ሄገን።

በዚህን ጊዜ የሚካኤል ኮርሌዎኔ ፊት ፍጹም ያባቱን ገጽታ ሲላበስ ለቶም ሄገን ታየው።

"ቶም ማንም እንዲያታልልህ እድል አትስጠው። ሁሉም የስራ ግንኙነት የግል ነው። እያንዳንዱ ሰው በህይወቱ ዘመን በየእለቱ የሚያጋጥመው መከራ ሁሉ የግል ነው። ታዲያ ይህን ሁሉ የስራ ግንኙነት ይሉታል። ይህን ያስተማረኝ የኔው ሽማግሌ አባቴ ዶኑ ነው። ዶኑ 'የጡት አባት' ምን እንደሚሰማው ታውቃለህ? መብረቅ ወዳጁን ቢመታው በግል እንደተደረገበት ይሰማዋል። የኔን ባህር ሀይል ተመዝግቦ መዝመት በሱ ላይ እንደተፈጸመ በደል አድርጎ ነው የተሰማው። ያ ነው ዶኑን ታላቅ የሚያደርገው። ታላቁ ዶን ሁሉን ነገር ከራሱ ጋር ነው የሚያያይዘው። እንደ አምላክ ነው። ከያንዳንዷ ወፍ ላይ የምትረግፈውን ላባ የት እንደም ትወድቅ ለይቶ ያውቃል፣ አይደል? እና አንድ ነገር ታውቃለህ? ድንገተኛ አደጋን በግል እንደተፈጸመ አድርገው በሚመለከቱ ሰዎች ላይ አደጋም አይደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ርስባቸው ። ጉዳዩን ዘግይቼ የገባሁበት ቢሆንም ፥ እስከመጨረሻው ነው እምገባበት ። የመንጋጋዩን መሰበር በግል ቲም ነው የምመለከተው ። ሶሎዞ አባቴን ለመግደል ያደረገውን ሙከራም በግል ቲም ይዠዋለሁ" አለና ሚካኤል ሳቀ ።

ቀጥሎም "ሽማግሌውን ንገሩት ፤ ሁሉንም ነገር ከሱ የተማርኩ መሆኔን ፥ ላደረገልኝ ሁሉ ውለታውን ልከፍል በመቻሌ መደሰቴን ንገሩት ። መልካም አባት ነበር ። በልጅነታችን እኔንም ሆነ ሶኒን ወይም ፍሬዲን የመታን እለት ትዝ አይለኝም ። ኮኒንግ ሙሆባት እንኳን አያውቅም ። ሄገን እውነቱን ንገረኝ እስቲ ፥ አባቴ እራሱ የገደላቸውና ያስገደላቸው ሰዎች ቁጥር ምን ያህል ይደርሳል?" አለ ሚካኤል ።

ቶም ሄገን ፊቱን ወደዚያ አዞረና ፥ "ካባትህ ያል ተማርከው ምን እንደሆነ ልንገርህ? ያሁኑ አንጋገርሆን አባትህ ቢሆን አይናገረውም ። ግድረግ ስላለብህ የምታደርጋቸው እንጂ የማታወራቸው ጉዳዮች አሉ ። ግላ መኛ ሊቀርብባቸው ስለማይችሉም ምክንያት አትፈል ግላቸውም ። ብቻ ትፈጽማቸዋለህ ። ከፈጸምክ በኋላ ትረሳ ቸዋለህ" አለው ።

ሚካኤል ኮስተር አለና በጽሞና ፥ "አማካሪ እንደ መሆንህ መጠን ፥ ሶሎዞን ያለመግደል ለዶኑም ሆነ ለቤ ተሰቡ አደጋ መሆኑን ታምንበታለህ?" ሲል ጠየቀው ።

"አምን"

"መልካም ። እንግዲያስ እገድለዋለሁ" አለ ሚካኤል ።

ሚካኤል ከሶሎዞ ጋር በነበረው ቀጠሮ ላይ ለማገኝት በመጓዝ ላይ ሳለ ለቶም ሄገን የተናገረውን ሁሉ ለመርሳትና በወቅቱ ባለው ተግባሩ ላይ ብቻ ለማተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኮር ሞከረ ። ሶሎዞ ሞኝ ፥ ማክለስኪም ቀላል ሰው አይ ደሉም ። የመንጋጋው መጠዝጠዝ ቆራጥነቱን ስለሚያ ጠናክርለት በጸጋ ተቀበለው ።

ቀጠሮ ከተደረገበት ከጃክ ዴምሲ ቡና ቤት ፊት ለፊት ቀደም ብሎ ደረሰ ። በዚያ ቀዝቃዛ የክረምት ምሽት ቡና ቤቷ የምትገኝበት አካባቢ በወቅቱ የቲያ ትር መግቢያ ሰአት ቢሆንም ሰው አልበዛባትም ። ጥቁር ሽንጣም መኪና አጠገቡ መጥታ ቆም እንዳለች አንድ ሚካኤል አይቶት የማያውቀው ልጅግር ሹፌር ጎንበስ ብሎ "ግባ ማይክ" ብሎ ጋበዘው ። ከበስተኋለ ኛው መቀመጫ ላይ ማክለስኪና ሶሎዞ ተቀምጠዋል ። ሶሎዞ እጁን ዘርግቶ ሚካኤልን ሞቅ ባለ ስሜት ጨበ ጠውና ፥

"በመምጣትህ ደስ ብሎኛል ፥ ማይክ" አለው ። "ነገሮችን እንደምናስተካክላቸው ተስፋ አለኝ ። እነ ዚህን ሁሉ አስከፊ ነገሮች አልፈለግኳቸውም ነበር ። መሆንም አይገባቸውም ነበር ።"

ሚካኤልም ፥ "ዛሬ ማታ እልባት እንደምናስይዛቸው ተስፋ አለኝ ። አባቴ ከእንግዲህ ወዲያ በስጋት እንዲ ኖር አልሻም" ሲል መለሰለት ።

"ግድ የለህም በልጆቼ እምልልሀለሁ ፥ ከእንግዲህ የሚሰጋበት ነገር አይኖርም ። ብቻ በዛሬው ንግግራ ችን ላይ እንደወንድምህ እንደሶኒ ግንፍል ሳትሆን አእምሮህን ክፍት አድርገህ አድምጠኝ ። ከወንድምህ ጋር ስለ ስራ ጉዳይ መነጋገር ያስችግራል ።"

ሻምበል ማክለስኪም ሚካኤል ጥሩ ልጅ ስለሆነ ችግሮቹ እንደሚፈቱ ያለውን ተስፋ ገለጠላቸውና የሚካ ኤልን ጀርባ መታ መታ አደረገው ።

"ግይክ ፥ ስላለፈው ምሽት አዝናለሁ ። እያረጀሁና ብስጩ እየሆንኩ መሄዴ ይሰማኛል ። ምናልባት ጡረታ

t.me/OLDBOOKSPDF

መውጣት ሳይኖርብኝ አይቀርም ። በየቀኑ የሚያጋጥ ሙኝን ውጥረቶች መወጣት አልቻልኩም›› በማለት ግከለስኪ ሚካኤልን ካግባባው በኋላ የሀዘን ሲቃ እንደያዘው ተነፈሰና ምናልባት ሽጉጥ ታጥቆ እንደሆን ለማወቅ በጥንቃቄ ፈተሸው ።

የተሳፈሩበት መኪና ክትትል ቢደረግበት ግድ የሌለው ይመስል በቀጥታ ተጓዘ ። ጉዟቸው ጠቋሚው ከነገራቸው ቦታ ውጭ መሆኑን ሲረዳ ሚካኤል ተስፋ ቆረጠ ። ከተማውን ከኋላቸው ትተው ወደ አንድ ድል ድይ አካባቢ ሲደርሱ ሚካኤል ስጋቱ የጨመረ ቢሆ ንም በፊቱ ላይ እንዳይታወቅ ግዴለሽ ለመምሰል ሞከረ። ከዚያ ድልድይ አጠገብ ካለው ረግረግ ሊጨምሩት ይሆን? ወይስ ጮሌው ሶሎዞ በመጨረሻው ደቂቃ ላይ ስለ ስብሰባው ቦታ ሀሳቡን ለወጠ?

መኪናይቱ መንገዷን ልታግባድድ ጥቂት ሲቀራት በድንገት አቅጣጫዋን ለውጣ ተመልሳ ወደ ኒውዮርክ ከተማ አቃናች ። የሚከታተላቸው ሰው አለ እንደሆን ለማወቅ ማክለስኪና ሶሎዞ ወደኋላቸው ተመለከቱ ። በዚህ ሁኔታ ከአንዱ መንገድ ወደ ሌላው ፥ ከአንዱ አቅጣጫ ወደ ሌላው ፥ ከአንዱ ሰፈር ወደ ሌላው እያሰ ባበሩ ደብዛቸውን ካጠፉ በኋላ ማንም የሚከተላቸው አለመኖሩን አረጋገጡ ።

‘‘ጥሩ ስራ ነው ። ይህን ተግባርህን አስታውሰዋ ለሁ›› አለው ሶሎዞ ሹፌሩን ።

ቀድሞውኑ ከታቀደው ምግብ ቤት ሲደርሱ ሰአቱ መሸት በማለቱ ባካባቢው ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ ። ሚካኤል ሹፌሩ አብሯቸው ይግባ ይሆን የሚል ስጋት አደረበት ። ሹፌሩ ግን ከውጭ ቆየ ። ስለስብሰባው ዝግ ጅት በተነጋገሩበት ወቅት ሹፌሩ አብሯቸው እንደሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዝ አለመነገሩ ቢያበሳጨውም ሚካኤል ሊያነሳውና ሊያነቃቸው አልፈለገም ።

ሶስቱም አንድ ክብ ጠረጴዛ ጋ ለብቻቸው ተቀመጡ ። በምግብ ቤቷ ውስጥ ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል ። ምናልባት የሶሎዞ ሰዎች ይሆኑ? ቢሆኑም ምንም አይደል ፥ እነሱ ጣልቃ ከመግባታቸው በፊት ሚካኤል ተልእኮውን ያጠናቅቃል ።

ማክለስኪ እውነተኛ ፍላጐቱን ሳይደብቅ ፥

"እዚህ ቤት የጣልያን ምግባቸው ጥሩ ነው?" ሲል ጠየቀ ።

"የጥጃ ስጋ ሞክር ። በመላ ኒውዮርክ የሚስተካከለው የለም" አለው ሶሎዞ ።

አሳላፊው ያመጣውን ወይን ጠጅ ከፍቶ በሶስት ብርጭቆዎች ሞላ ። ማክለስኪ ሊጠጣ አልፈለገም ።

"የማይጠጣ የአየርላንድ ተወላጅ እኔ ብቻ መሆን አለብኝ ። ብዙ መልካም ሰዎች በመጠጥ የተነሳ ችግር ላይ ሲወድቁ አይቻለሁ" አለ ።

ሶሎዞ ወደ ስብሰባው አላማ ቶሎ ለመግባት በመሻት ፥ ማክለስኪን እንዲህ አለው ፥

"እኔ እንግዲህ ከማይክ ጋር የምነጋገረው በጣልያንኛ ነው ። እንዲህ የማደርገውም አንተን ባለማመኔ ሳይሆን ፥ በእንግሊዝኛ በሚገባ ለማስረዳት ስለሚያዳግተኝ ነው ። እናም ያሰብኩትን በጎ ሀሳብ ለማይክ በጣልያንኛ በማስረዳት ስምምነታችን ለሁላችንም እንደሚበጅ ላግባባው እፈልጋለሁ ። በዚህ አይክፋህ ፥ ሳላምንህ ቀርቼ አይደለም ።"

ማክለስኪም "ግድ የለም ፥ እናንተ ቀጥሉ ። የእኔ ትኩረት በጥጃ ስጋውና በስፓጌቲው ላይ ይሆናል" ሲል በውስጠ ፌዝ ፈገግታ መለሰ ።

ሶሎዞ ንግግሩን በሲሲሊ ቋንቋ ቀጠለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በእኔና በአባትህ መካከል የደረሰውን አለመግባባት በስራ ግንኙነት የተነሳ ጠብ ብቻ አድርገህ ተመልከተው ። ለዶን ኮርሌዮኔ ታላቅ አክብሮት አለኝ። እድሉን ባገኝ የሱ ታዛዥና ተከታይ ብሆን ደስ ይለኛል ። ነገር ግን አባትህን ጊዜ ያለፈበት አስተሳሰብ ስለሚያጠቃው በእድገት ጉዳና ላይ እንቅፋት ይሆናል ። እኔ ልገባበት የምለው ንግድ ለሁሉም ሰው ተነግሮ የማያበቃ ብዙ ሚሊዮን ብር የሚያስገኝ ታዳጊው የወደፊቱ ዋና ንግድ ነው ። አባትህ ግን ተጨባጭ ባልሆነ የህሊና ጥያቄ ምክንያት የዚህን ታዳጊ ንግድ ገበያ ያደናቅፋል ። ይህ አመለካከቱ በሌሎቹ ላይ ተጽእኖ ያስከትላል ። ስለዚህ ጉዳይ ሲያነሱለት ፣ 'አንተ ቀጥል የራስህ ጉዳይ ነው ፣' በማለት ይናገራል ። ነገር ግን ይህ አባባል ተጨባጩን ሁኔታ የሳተ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን ። እርስ በርሳችን ለመጉዳዳት እንገደዳለን ። ምክንያቱም አባባሉ በርግጥ ንግዴን እንዳላንቀሳቅስ የሚገድብ ነው ። እኔ እራሴን የማከብርና ሰው ተጽእኖ እንዲያደርግብኝ የማልሻ ሰው በመሆኔ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሊከተል ቻለ ። ልንገርህ ፣ የመላው ኒውዮርክ ቤተሰብ ስውር ድጋፍ አለኝ ። ከታታሊያ ቤተሰብም ጋር ሽርክና አለኝ ። ታዲያ በመሀከላችን የተፈጠረው አለመግባባት ከቀጠለ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ብቻውን ሆኖ ከነዚህ ሁሉ ቤተሰቦች ጋር ደመኛ ይሆናል ማለት ነው ። ምናልባት አባትህ ደህና ቢሆን ኖሮ ሊያሸንፍ ይችል ነበር ። ወንድምህ ግን ደፈርከው አትበለኝና ፣ ያባትህን ባህርይ የተቀዳጀ አይደለም ። ያ ሄገን የተባለ የአየርላንድ ተወላጅ አማካሪያችሁም ጀንኮ አባንዳንዶን የሚተካ ሰው አይደለም ። ስለዚህ የእርቅ ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ ። ግናቸውንም በክፉ መፈላለግ አቁመን አባታችሁ ድኖ መደራደር እስኪችል ድረስ እንጠባበቅ ። የታታሊያን

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተሰብ በመግባትና ካሳ በመክፈል ለልጃቸው ሰብ
ሩና ሞት በቀል እንዳይፈልጓችሁ እሺ አሰኝቻቸዋለሁ።
ሰላም ይወርዳል። እኔም እስከዚያው ንግዴን በመጠኑ
ላካሂድ። በንግዱ ላይ ትብብራችሁን አልጠይቅም።
ነገር ግን የኮርሌዎኔ ቤተሰብስ ጣልቃ እንዳይገባ እጠይ
ቃለሁ። ይህ ነው እንግዲህ የማቀርበው ሀሳብ። እንደ
ምገምተው፣ አንተ ተደራድረህ ለመስማማት ስልጣን
ያለህ ይመስለኛል።"

ሚካኤል በሲሲሊያንኛ መለሰለት።

"እስኪ እንዴት አድርገህ ንግድህን ልትጀምር
እንዳሰብክ ንገረኝ። የኛ ቤተሰብስ የሚሳተፈው እንዴት
ነው፣ ከዚህ ንግድስ ምን ያህል ሊያገኝ ይችላል?"

"ሁሉንም በዝርዝር እንድገልጽልህ ትፈልጋለህ?"
ሲል ሶሎዞ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት።

ሚካኤል ኮስተር ብሎ "ከሁሉ በላይ ከእንግዲህ
ለንዳችም የግድያ ሙከራ በአባቴ ላይ እንደማይደረግበት
መተማመኛ ያስፈልገኛል" አለው።

ሶሎዞ እጁን ዘርግቶ፣ "ምን ዋስትና ልሰጥህ እች
ላለሁ? ከእንግዲህ የምታደነው እኔ፣ እድል እንደሆነ
አምልጦኛል። ከአቅሜ በላይ ገምተሽኛል። ያን ያህል
ጮሌ እንዳልመስልህ" አለው።

ይህ ሁሉ የሶሎዞ ብልጣብልጥነትና የስብሰባ መጥ
ራት አላማ ለጥቂት ቀናት ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ አደጋ
ሳይጣልበት ለመቆየትና በዶኑ ላይ የጀመረውን የመ
ግደል ሙከራ ከግብ ለማድረስ እንደሆነ ሚካኤል አሳ
ምሮ ገባው። በተለይም ሚካኤልን የዋህ አድርጎ ሊያታል
ለው በመሞከሩ ሚካኤል ደስ አለው። የተጨነቀ ፊት በግ
ሳየት የጠጣው ወይን ጠጅ ፊኛውን ስለሞላው መሽናት
ይፈቀድለት እንደሆነ ጠየቀ። ሶሎዞ በጥርጣሬ አይኑን

t.me/OLDBOOKSPDF

እያቁለጨለጨ ተመለከተውና መሳሪያ ይዞ እንደሆነ በግለት ዳበስ ዳበስ አደረገው ። ሚካኤል በዚህ ጥርጣሬ የተበሳጨ መሰለ ። ማክለስኪም ኮስተር ብሎ ፥ "ፈትሼ ዋለሁ እባክህ ። ብዙ ሺህ ጐረምሶችን ፈትሻለሁ ። ምንም አልታጠቀም" አለ ።

ሶሎዞ ምክንያት ባይኖረውም ይህ ሁኔታ ደስ አላለውም ። እነሱ ከተቀመጡበት ባሻገር ካለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን የራሱን ሰው በአይኑ ጠቀሰው ። ሰውየው ሶሎዞ ያለው ስለገባው መጸዳጃ ቤቱን የፈተሸው መሆኑንና ከዚያ ማንም ሰው እንደሌለ አረጋገጠለት ። ሶሎዞ እያንገራገረ ሚካኤልን ፥ "ብዙ እንዳትቆይ" አለው ። ሶሎዞ የሚያስደንቅ አንቴና አለው ፥ ጠርጥሯል ።

ሚካኤል ተነስቶ ወደ መጸዳጃ ቤት አመራ ። በርግጥም ፈኛውን ወጥሮት ስለ ነበር ገብቶ ሸና ። ከዚያም ከሸክላው የውሀ መቋጠሪያ በስተጀርባ እጁን ልኮ ሲዳብስ ባለ ዱልዱም አፈሙዝ ሽጉጥ አገኘ ። ከሌሚንዛ ስለአሻራ አትስጋ ሲል የነገረውን እያስታወሰ ሽጉጡ የተጠለፈበትን ማጣበቂያ ሸለቀቀው ። ወዲያው ሽጉጡን ከቀበቶው ስር ሸጠ እንዳይታይበት ኮቱን ቆለፈው ። እጁን ታጥቦ ጸጉሩን አራሰው ። ከመታጠቢያው ቧንቧ ላይ አሻራ እንዳይቀር በመሀረቡ ጠራርጐ ወደ ስብሰባው ተመለሰ ።

ሶሎዞ የመጸዳጃ ቤቱን በራፍ እየተመለከተ ሚካኤልን ይጠብቅ ነበር ። ሚካኤል ፈገግ አለና ፥ "አሁን ንግግራችንን መቀጠል እንችላለን ፥" አለ ፥ ከስቃይ የመገላገል እፎይታ በመተንፈስ ።

ማክለስኪ የቀረበለትን ስጋና ፓስታ እየበላ ነው ። ከዳር ሆኖ በተጠንቀቅ ይጠባበቅ የነበረው የሶሎዞ ጠባቂ የሚካኤልን ሁኔታ ተመለከተና ዘና አለ ። ሚካኤል ከመጸዳጃ ቤት እንደተመለሰ ወዲያውኑ እንዲ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተኩሰ ክሌሜንዛ ነገሮት የነበረው ምክር ትዝ ብሎ ታል ። ነገር ግን ውቃቢው ይንገረው ወይም ከፍርሀት የተነሳ ይሁን አይታወቅም ፥ እንደተመከረው አላደረ ገም ። አንድ አይነት ፈጣን እንቅስቃሴ ቢያደርግ ሊቀ ልቡት እንደተዘጋጁ ተሰምቶታል ። አሁን ግን ቁጭ በማለቱ ከዚያ አደጋ ነጻ መሆኑና ፥ የእግሩም በፍርሀት መንቀጥቀጥ አለመታየቱ አስደስቶታል ።

ሚካኤል ጠረጴዛው ሆዱን ስለከለለለት ኩቱን ከፍቶ ሶሎዞ የሚያወራለትን መስማት ጀመረ ። ሶሎዞ ወደሱ ዘንበል ብሎ የሚያወራውን አንዱንም ቃል አል ሰማውም ። ጆሮውን የልቡ ድውድውታ ሞልቶታል ። ቀኝ እጁን በጠረጴዛው ስር ወደ ቀበቶው ልኮ እዚያ የተሻጠውን ሽጉጥ መዘዘው ። በዚያች ደቂቃ ሶሎዞ ፊቱን አዙሮ ትእዛዝ ሊቀበል የመጣውን አሳላፊ ያነ ጋግረው ነበር ። ሚካኤል በግራ እጁ ጠረጴዛውን ገፋና ከፊቱ አስወገደው ። ሽጉጡን ሶሎዞ እራስ ላይ አስጠ ጋው ። ሶሎዞ ከመቅጽበት የነቃ ቢሆንም ከሚካኤል ወጣትነትና ንቁነት ጋር ሊመጣጠን አልቻለም ። ሚካ ኤል ሶሎዞ ጆሮ ንግድ ላይ አስተካክሎ ቃታውን ሳበ ። ጥይቷ የሶሎዞን አናት በርቅሳ ስትወጣ የደም ፍን ጣሪና የአንጐል ፍርክስካሽ በአሳላፊው ኮት ላይ ረጨ ችበት ። ከዚያ በኋላ ለሶሎዞ ሌላ ጥይት ማባከን አስ ፈላጊ ሆኖ አልታየውም ። ሶሎዞ ፊቱን ወደሱ ዞር አድ ርጎ ስለነበረ የህይወት ብርሀን ከአይኑ እንደሻማ ብር ሀን ስትጠፋ ታየው ። በአንድ ሰኮንድ ጊዜ ውስጥ ተሽከርክሮ ሽጉጡን ማክለስኪ ላይ ደገነው ። ማክ ለስኪ ሁኔታው እሱን የማይመለከተው ይመስል ፥ ይህ አደጋ ወደሱም የሚመጣ መሆኑን ሳይገነዘብ ፥ ሚካኤልን ባልተረበሸ መገረም አፍጠ አየው ። ስጋ የያዘውን ሹካ እንዳንጠለጠለ እብሪት በተሞላበት ቁጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

አይኑን ወደ ሚካኤል አቃንቶ የሚካኤልን እጅ መስ
ጠት ወይ መሸሽ የሚጠባበቅ መሰለ ። ሚካኤል ፈገግ
አለና ቃታውን ሳበበት ። ይህ ተኩስ መጥፎ ነበር ፣
ግክለስኪ ወዲያው አልሞተም ። ጥይቷ በደንዳና ጉሮ
ሮው ዘልቃ ስለገባች ሙዳ ስጋ ያነቀው ይመስል ፈጥ
ርቃ ያዘችው ። ሲስል ከተበሳሳ ሳምባው የሚወጣው
ደም አየሩን የደም ጉም የተረጨበት አስመሰለው ።
ሚካኤል ሳይቸኩል በዝግታ ሁለተኛዋን ጥይት ሽበት
በወረረው የማክለስኪ አናት ላይ ለቀቀበት ።

አየሩ ቀይ ጭጋግ የተሞላ መሰለ ። ሚካኤል ግድ
ግዳውን ተደግፎ ወደ ተቀመጠው ሰውዬ ዞረ ። ሰውየው ደን
ዝዞ አልተንቀሳቀሰም ። ሁለት እጁን ጠረጴዛው ላይ
አደረገና ወደ ሌላ ተመለከተ ። አሳላፊው በድንጋጤ
እየተንገዳገደ ወደ ማድቤት አፈገፈገ ። ሶሎዞ አሁንም
መቀመጫው ላይ እንዳለ ጠረጴዛውን ተደግፏል ። የማ
ክለስኪ ግዙፍ ሰውነት ወለሉ ላይ ተዘርሯል ። ሚካ
ኤል ማንም ሰው ሳያጤነው ሽጉጡን ማክለስኪ ላይ
ጣለው ። ኳኳታ ሳይሰማ ሽጉጡ ከማክለስኪ ወደ ወለሉ
ወረደ ። ሚካኤል በረጅሙ ራመድ ብሎ ወደ በሩ ተጠ
ጋና ከፈተው ። የሶሎዞ መኪና ከመንገድ ጠርዝ ላይ
ቆማለች ። ሹፌሩ ግን የለም ። ሚካኤል ወደ ግራ ታጥፎ
ማእዘኑን ዞረ ። የመኪና የፊት መብራት ምልክት ታየው ።
ምልክቱን ወዳየበት መኪና ሲያመራ የመኪናው በር
ተከፈተለት ። ዘሎ ገባና ጉዞውን ቀጠለ ። የዚያች የተ
ጨረማመተች መኪና ሹፌር ቴስዮ ነበር ።

"ሶሎዞን አደረግከው ?" ሲል ጠየቀው ቴስዮ ።
ይህን የመሰለ አባባል ሴት ግባበልን የሚገልጽ በመ
ሆኑ ሚካኤልን አስገረመው ።

"ሁለቱንም ነዋ!" ሲል መለሰለት ።

"እውነት ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንጎላቸው ፈሶ አይቼዋለሁ" በማለት አረጋገጠ ለት ።

ሚካኤል ከመኪናው ውስጥ ተቀምጦለት የነበረ ውን ልብስ ቀይሮ ወደ ሲሲሊ በምትጓዝ የጣሊያን የጭ ነት መርከብ ላይ ተሳፈረ ። ከሁለት ሰአትም በኋላ መር ከቧ ጉዞዋን ስትቀጥል እንደገሀነም እሳት የሚን ቀለቀለውን የኒውዮርክን መብራት እያየ ከስቃይ የመ ገላገል እፎይታ ተሰማው ። ይህ ስሜት ለሚካኤል አዲስ አልነበረም ። ካሁን ቀደም በዘመቻ ላይ ሳለ የአገሩ ጦር በወረረው ደሴት ባህር ዳርቻ ሲጓዝ የነ በረው ሁኔታ ለአፍታ ትዝ አለው ።

ሶሎዞና ማክለስኪ በተገደሉ ማግስት ፥ በየጣቢያው ያሉ መኰንኖች ከእንግዲህ የሻምበል ማክለስኪ ገዳይ እስከተያዘ ድረስ እንድም ቁማር ፥ ሽርሙጥና ወይም መዋዋል እንዳይኖር ሲሉ አስታወቁ ። ከተማዋ በሰፊው ተወረረች ። ህገወጥ ንግድም ለጊዜው ቀጥ አለ ።

የዚያኑ እለት የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ገዳዩን አሳልፎ እንዲሰጥ ከድብቅ አለም ቤተሰቦች ቢጠየቅም ጉዳዩ አይመለከተኝም ሲል መለሰ ። በዚያው ምሽት ደግሞ በኮርሌዎኔ ግቢ ከመኪና ላይ የተወረወረ ቦምብ ፍንዳታ ደረሰ ። ሁለት የቤተሰቡ ታዛዥ ገዳዮች በሰላም እረፍ ታቸውን ሲበሉ ተገደሉ ። በዚህ አይነት የ1946ቱ የአም ስት ቤተሰብ ጦርነት ተከፈተ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ ሁለት

ምእራፍ አስራ ሁለት

ጆኒ ፍንቴን በቅርቡ ከተዋወቃት ወጣት ተዋናይት ጋር ለመዳራት ስለተቃጠረ አሽከሩን አሰናብቶታል ። በቅርቡ በጃክ ዎልትዝ ስቱዲዮ ተዋናይ ሳለ ጀምሮ ተዋ ውቀው የነበረች ይህች ወጣት ሻረን ሞር ትባላለች። ጆኒ ሲጋብዛት የብርቱነት ዝናው እየታሰባት ጥሪውን ተቀብላ መጥታለች ። ጆኒ ካልሰከረ በስተቀር የሆሊዉድ ሰዎች ለመዳራት ያህል የሚሉት ስሜት አልባ የሆነ የፈቃደ ስጋ ፈሊጥ የለበትም ። ዛሬም የጋብቻ ፍቺ የተደጋገመበት የ35 ዓመት ባለእድሜው ጆኒ በቀላሉ ለፍ ትወት የሚቋምጥ አልሆነም ። እንደ ሻረን ሞር ካሉት ጋር ለመዳራት ስሜቱን የሚጭርለት የደስ ደስ እንዲ ኖራቸው ያስፈልጋል ። እሱ ለራሱ ብዙ የመብላት ፍላ ጎት የለውም ። ወጣት ቆነጃጅት ግን ልብስ እንዲያም ርባቸው ፎርማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ይራቡ እንጂ በቀጠሮ ቀን ከወዳጆቻቸው ጋር ሲገናኙ ግን ብዙ እን ደሚመገቡ ሶኒ ስለሚያውቅ ገበታውን በምግብና በመ ጠጥ እንዲበለጽግ አድርጎታል ። የቀረበውን ምግብ ተቋድሰው እንዳበቁ ምግብ ቤቱን ለቀው ፓስፊክ ውቅያኖስ ከመስተዋት በተሰራው ግድግዳ ወለል ብሎ ወደሚታይበት ሳሎን ይዟት ገባ ። ጥቂት እንዳወሩም ስላስተዳደጓ አስወራት ። ከሶፋው ተዝናንተው እንደተቀመጡ ዘና ያለ ይልቁንም ወንድማዊ የመሰለ አሳሳም ሲስማት አጸፋውን እሷም ዘና ብላ መለሰችለት ።

"እስኪ ሸክላህን ወይም ድምጽህን ልስማው ። በሰራሀቸው ፊልሞች ላይ እንዚያ ውብ ተዋንያት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚያደርጉት እኔም በስሜት ልጋልና በላይህ ላይ ልቅለጥ" ብላ ስታሾፍበት ከት ብሎ ሳቀ ።

ጀኒ ለብዙ ወራት ስላልዘፈነ በድምጹ አይተማመንም ። ወትሮስ ቢሆን የዘፈን ሙያተኞች አድናቆት የሚያስገኝላቸው ድምጻቸው ብቻ ሳይሆን የሙዚቃ መሳሪያዎችና የቴክኒክ ድጋፍ ጭምር እንደሆነ ብዙ ሰዎች መች ያውቁትና !

"ድምጼ ትክክል አይደለም ። ደሞ እውነቱን ልን ገርሽ አይደል? ድምጼን መስማት ስልችት ብሎኛል" አላት ።

ሻረን ሁኔታውን ተረድታ ጨዋታ ለወጠች ።

"ባሁኑ ፊልምህ ድንቅ እንደተጫወትክ ሰምቻለሁ ። ለመሆኑ በነጻ ነው የሰራኸው የሚባለው እውነት ነው?" አለችው ። እሱም ምንም ያህል እንዳልተከፈለው ነገራት ። ሲጋራቸውን እያጤሱና ብራንዲያቸውን እየተጎነጩ የስሜታቸውን ጉዞ ተጠባበቁ ።

የጀኒ አዲሱ ፊሊጡ ፣ ያሰኘችውን ወጣት ለአንድ ቀን አብሯት አድሮ ፣ ጥቂት ቀናት እራት ጋብዟት ፣ ውድ ስጦታ ያበረክትላትና ፣ ስሜቷን ሳይጐዳ በዘዴ ያሰናብታታል ። በዚህ ሁኔታ የሚለያቸው ወጣቶች የጀኒ ትዝታ ከልባቸው አይጠፋም ። እሱ የሚጠላው እንደ ጨጐጐት አንለቅም የሚሉትንና በገቡበትና በወጡበት ሁሉ ስሙን የሚያነሱትን እንጂ ፣ ቆንጆዎችንማ ለቅጽበት ወዶ ቶሎ የሚያልፍ ፍቅር እንዴት ይከልከላቸው? እሱ ከሚስቶቻቸው ጋር ቢዳራም ይቅርታ እንደሚያደርጉለት የሚገልጹለትን ነሆለል ባሎች ግን በጣም ይታዘባቸዋል ። ግራማፎን የሚያሰማውን የሌላ ዘፋኝ ድምጽ ታክኮ በሻረን ፊት ለማንሳራጋር እንኳን አልደፈረም ። አንዱን እጁን በሻረን ጭን ላይ አድርጎ መጠጡን ወሳሰደለት ። ብርድ ተሰምቶት ልብስ እንደሚሻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀጻን ልብሷን ገለበው ። ነገር ግን እንዲህ ድምጹ እንደ ነዳው ስሜቱስ ቢከዳው ?

ለነገሩስ የራሱ ስሜት ደህና ተቀስቅሷል ፣ ብቻ የሻረ ንን መኮርነር አቃተው እንጂ ። የሷም አሳሳም ይሉኝታ የተሞላበት ሆነ ። እንዲህ ያለውን አጸፋ ይወደዋል። እንደሞተር ወዲያው የሚሞቁትን ይጠላቸዋል ።

የመጻራት ዘይቤዎቹን አንዳንዶቹ በጸጋ ሌሎቹ በጥፊ ይቀበሉታል ። የሻረን ግን ለየት ያለ ሆነ ። ሁሉንም አድራጎቱን ተቀበለችው—ንክኪውንም ፣ መሳሠሙንም ። ቀጥላም በዝግታ ቀና ብላ ብርጭቆዋን አነሳች ። በጽሞና ቁርጠኛ እምቢታዋን ገለጸች ። ጆኒም መጠጡን አነሳና ሲጃራውን ለኮሰ ።

"ጠልቼሀ እንዳይመስልህ ጆኒ ፣ ከጠበቅኩህ በላይ ጥሩ ሰው ነህ ። እኔም ፍቅር የምጠላ ሆኜ አይደለም ። ነገር ግን ስሜቴ አልቀሰቀስ አለኝ ። "

ጆኒ ፈገግ አለና ፣ "ታዲያ እኔ ስሜትሽን መቀ ስቀስ አልቻልኩም ማለት ነው?" ሲል ጠየቃት ።

ሻረን እንደማፈር ብላ ፣

"እንደምታውቀው ያኔ ስትዘፍንና ታላቅ ተዋናይ በነበርክበት ጊዜ ትንሽ ልጅ ነበርኩ ። እኔ ኩተኩታዩ ትውልድ በመሆኔ አመለጥከኝ ። አንተ ጀምስ ዲንን ወይም ሌላ እኩያዬን ብትሆን ኖሮ ስሜቴ ለመቀስቀስ አንዲት ሴኮንድም ባልፈጀበት ነበር ፣" ስትል መለሰችለት ።

ሻረን ጥሩ ፣ ዘዴኛና ብልህ ወጣት ነች ። ጆኒ ከብዙ ሰዎች ጋር ባለው የስራ ግንኙነት ይጠቅመኛል ብላም ልትጻራው አልፈለገችም ። ጆኒ ግን የተረዳው አንዳንድ ሴቶች እሱን የመሰሉ ዝነኛ ሰዎችን ምንም ያህል ቢወዷቸው ከመጻራቱ ይበልጥ የሚሹት እገሌ ጠይቆኝ እምቢ አለኩት ማለቱን ስለሆነ በዚያው በእምቢታቸው እንደሚጸኑ ስለሚያውቅ አልተናደደም ። በበኩሉም

t.me/OLDBOOKSPDF

ግለቱ ስላለፈለት ተዝናና ። ከፊት ለፊት በመስኮት ዘልቆ የሚታየውን የፓስፊክ ውቅያኖስ እየተመለከተ ይጠጣ ጀመር ።

"እንዳልተቀየምከኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። እንደ ሆሊዉድ ልጆች ገና ጮሌነትን አልለመድኩትም" አለች ።ጆኒ ፈገግ አለና ጉንጯን መታ አድርጎ ልብሷን አስተካከለላት ። በፊልም ላይ እንደጣአት ይመለከበት የነበረውን ያህል የተሳካለት ወዳጅ ሊሆን ባለመቻሉ መቆጨቱ ባይቀርም ስሜቱን ደብቆ ፣

"እረ በጭራሽ አልተቀየምኩም ። አንዳንዴ እኮ የጥንቱን ለማስታወስ የአሁኑን አይነት ፍቅር መለዋወጥ አይከፋም ፥" በማለት መለሰላት ።

መጠጣቸውን እየደጋገሙ ፥ ስሜታዊ ሙቀት የጮ ደለው መሳሳም ሲለዋወጡ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ሻረን ለመሄድ ተነሳች ።

"ደግሞ ሌላ ቀን እራት ልጋብዝሽ?" አላት ።

ስሜትዋን ሳትደብቅ

"ጊዜህን አጥፍተህ ተስፋ መቁረጥ እንደማትሻ አውቃለሁ ። አብረን ላመሽነው አመሰግናለሁ ። አንድ ቀን ዝነኛው ጆኒ እራት ጋብዞኝ ብቻችንን ሆነን ነበር ብዬ ለልጆቼ እነግራቸዋለሁ" አለችው ።

ጆኒ ፈገግ አለና ፣

"እጅ እንዳልሰጠሽም ትነግሪያቸዋለሽ" ሲላት ሁለቱም ሳቁ ።

"እንዲህ ብላቸውስ አያምኑኝም" አለች ሻረን ።

"እንግዲያውስ በጽሁፍ ላረጋግጥልሽ" ሲላት ሻረን የማያስፈልግ መሆኑን ለመግለጽ እራሷን ነቀነቀች ።

"እንዲህ ብለሽው አላምንሽ የሚል ካለ ደውይልኝ፥ እኔ አረጋግጥለታለሁ ። እንዴት እንደተፈታተንኩሽና

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳላደድኩሽ ፥ አንቺ ግን ከብርሽን ጠብቂሽ እምቢ እንዳልሽኝ ሞምር እነግረዋለሁ ።"

ጆኒ ፍንቴን ይህን የተናገረው ሻረን ሞር እምቢ ያለችው ስሜቱን ለመቀስቀስ ባለመቻሏ እና እሱም ብዙ ግፊት ባለማድረጉ እንደሆነ እንዲሰማትና የተቀዳ ጀችውን ድል ለመቀማት እንደሆነ ተሰምቷታል ።

"ብቸኝነት ወይም ብስጭት ሲሰማሽ ደውይልኝ ። እንደምታውቂው ከተዋወቅኳት ሴት ሁሉ ጋር መዳራት አይኖርብኝም" አላት ።

"እሺ" ብላ ሻረን ቤቱን ለቃ ወጣች ።

ረሹሙ ሌሊት ከፊቱ የተጋረጠበት ጆኒ ፍንቴን እሽታ የተሞላበት ተዋንያት ጋጣ ወይም ጃክ ዎል ትዝ እንደሚለው 'የሰጋ ፋብሪካ' ትዝ ቢለውም ፥ በእለቱ ያሰኘው ሰብአዊ ወዳጅነት ነበር ። ዛሬ በሰብአዊ ቋንቋ መነጋገርን ይሻል ። ስራውን ስላጠናቀቀ ክብሯን ጠባቂዋን የመጀመሪያ ሚስቱ ቨርጂኒያን አሰባት ። መቼም ከሷ ጋር ተዳራሁ ብሎ የሚወሽክትለት ጮሌ እንደማይኖር ይገምታል ። እርግጥ ስለ ሁለተኛይቱ ሚስቱ ማንም ምንም ለማለት እንደሚችል ያውቃል ። ሰልኩን አንስቶ ወደ ቨርጂኒያ ደወለ ። እድሜው አስር አመት ሳለ አራተኛ ክፍል አብረው ሲማሩ ጀምሮ የሚ ያውቀውን ድምጿን ወዲያው ለየው ።

"ታዲያስ ጂኒ ፥ ዛሬ ሌላ ጉዳይ አለሽ ? እናንተ ዘንድ ልመጣ እችላለሁ ?" ሲል ጠየቃት ።

"እሺ ፥ ልጆቹ ተኝተዋል ። ልቀሰቅሳቸው አል ሻም" አለችው ።

"ግድ የለም ካንቺ ጋር ለማውራት ነው የምፈልገው አላት ።"

"ምነው ደህና ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እረ ደህና ነኝ ። የፊልሙን ስራዬን ስለጨረስኩ ልጠይቅሽ ብዬ ነው ። ምናልባትም ልጆቹንም እንደ ተኙ አያቸዋለሁ ።"

"እሺ እንግዲያው ና ፣ የፈለግኸውን የፊልም ስራ በማግኘትህ ደስ ብሎኛል ።"

ጆኒ ከድሮ ሚስቱ ቤት ደርሶ ወደቤት ከመዝለቁ በፊት ክርስትና አባቱ 'ህይወትህን እንደምትሻው መምራት ትችላለህ' ሲል የተናገረው ትዝ አለው ።

ውዲቷ ኢጣሊያዊት የድሮ ሚስቱ ጂኒ በሩ ላይ ቆማ ትጠብቀዋለች ። ጆኒ እንዲያው ይህችን ሴት በፈቃደ ስጋ ይሻት እንደሆን እራሱን ጠየቀ ። ፍቅራ ቸው ያበቃ ስለሆነ ለዚህ ጥያቄ መልሱ አይሻትም ነው። ከዚህም በላይ ፣ እሷም ብትሆን ይቅርታ አታደርግለ ትም ። ነገር ግን በመካከላቸው የቂም ጉዳይ አብቅቶ የጠላትነት ስሜት ጠፍቷል ።

ቡና አፍልታ ፣ ራሷ ከጋገረችው ብስኩት ጋር አቀረበችለትና ፣ "ሶፋው ላይ ጋደም በል ። የደከመህ ትመስላለህ ፣" አለችው ።

ጆኒ ኮቱንና ጫማውን አውልቆ ከራባቱን አላልቶ እንደተዝናና ፤

"ይገርማል ?" አለች ጂኒ ።

"ምኑ ነው የሚገርመው?" አላት ቡናውን እየጠጣ ።

"ታላቁ ጆኒ ፎንቴን ያለ ሴት ማምሸቱ አያስገር ምም ?"

"ከዚህ በኋላ መቸም አይሳካለት !" ሲል መለሰላት ።

ቀጥታ መልስ መስጠት የጆኒ የወትሮ ጸባዩ እንዳ ልሆነ የምታውቀው ጂኒ በመገረም ምን እንደገጠመው ጠየቀችው ።

ጆኒ ሳቅ ብሎ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዲን ወጣት ቤቴ ጋብቻ ከመጣች በኋላ እምቢ አለችኝ ። እኔም ከስታይ የመግላገል ስሜት ተሰማኝ" አላት ።

ጂኒ ባልጠበቀው ሁኔታ ብስጭት ብላ ፣
"እባክህን ለማንም ኩታራ ደንታ አይኑርህ ። ምና ልባት በዚህ ዘዴዋ የምትለማመጣት መስሏት ይሆናል፣" በማለት ልታጽናናው ሞከረች ።

ጂኒ ባሏን የናቀችባት ሴት እንዳናደደቻት ውስጡን ሳቅ እያለ ተገነዘበ ። ጅኒ ከእንግዲህ አኪሩ ስላለ ፈበት መጨመት እንደሚኖርበት ሲነግራት ጂኒ አልተቀበለችውም ። ይልቁንም ከመቸውም ይበልጥ እንዳማረበት በመግለጽ አጽናናችው ።

"እየወፈርኩና ጸጉሬም እየተመለጠ ነው ። ያሁኑ ፊልም ካልተዋጣልኝ ከእንግዲህ ፒሳ መጋገር መማር ይኖርብኛል ። ወይም ውበትሽ እየጨመረ የሄደውን አንቺን ተዋናይ ማድረግ ነው" አላት ።

ጂኒ ለሰላሳ አምስት አመት እድሜዋ ተስማሚ ነው የሚባል አቋም ይዛለች ። እዚህ ሆሊውድ ከተማ ግን ይህን የመሰለ አቋም የመቶ አመት ባለእድሜ አቋም ሊሆን ይችላል ። ወጣት ልጃገረዶች ወቅት ጠብቆ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደሚዘምት የፍልፈል ሰራዊት ለአንድ አመት ቢበዛም ለሁለት አመታት በየመንገዱ ላይ ሲኮለኩሉ ይታያሉ ። የአንዳንዶቹ ሴቶች ውበት የወንዱን ልብ ትርታ ሊያቆመው ይደርሳል ። ተራዎቹ ሴቶች በገጽታ ደረጃ ሊወዳደሯቸው ከቶም ተስፋ አያደረጉም ። ማንም ሰው እንደሚያወራው ስለ ማራኪነታቸው ፣ ስለንቁነታቸው ፣ ሽክ ስለማለታቸው ፣ ስለተስተካከለው አቋማቸው ፣ የነዚህ ወጣት ልጃገረዶች የተፈጥሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውበት ከማንም የሚልቅ ነው ። ምናልባት እነሱ በሌሉበት የተራዋ ቆንጆ መሳይ ሴት ውበት ለመከሰት ተስፋ ይኖረው ይሆናል ። እናም ጆኒ ፎንቴን እነዚህን ሁሉ ቆነጃጅት ካልሆነም አብዛኛውን ሊያገኛቸው እንደሚችል ጂኒ ስለምታውቅ ጆኒ ይህን ሁሉ ማለቱ ለከንቱ ውዳሴ እንደሆነ አውቃለች ። ጆኒ ምንጊዜም ቢሆን ደግ ነው ። በዚያ ዝናው ጣሪያ በደረሰበት ወቅት እንኳን ፥ መልካም ምኞቱን በመግለጽ ሲጻራ ሊያጨሱ ሲሉ እሳት በማቀጣጠል ፥ ሲወጡም ሆነ ሲገቡ በር በመክፈት ለሴቶች ትህትናውን ይገልጽ ነበር ። ይህ አድራጎቱ አብሯቸው የሚወጣቸውን ቆነጃጅት ይበልጥ ሊማርክ ችሏል ። ይህን ትህትናውን ለሁሉም ሴቶች ፥ ማለትም ለአንድ ሌሊት አብረውት ለሚቆዩትና ስማቸውን ለማወቅ እንኳን ደንታ ለሌለው ሳይቀር ይለግሳል ።

ጂኒ ወዳጅነት የተመላበት ፈገግታ አሳየችው ።

"ድሮውንም ቢሆን የጨዋነት ወግ አሳይተኸኛል ። ጆኒ እስኪ ታስታውሳለህ? አስራ ሁለት አመት ሆኖናል ። አላማህን ለኔ ስትል ማዛባት የለብህም" አለች ።

ጆኒ በረዥሙ ተነፈሰና ሶፋው ላይ እንዳለ ተንጠራራ ።

"ቀልዴን አይደለም ጂኒ ። በጣም ጥሩ ቁመና አለሽ እኔም እንዳንቺ የመሰለ አቋም እንዲኖረኝ እመኛለሁ ።" አላት ።

መልስ አልሰጠችውም ። ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንደተቀረጸበት ተመለከተች ።

"ለመሆኑ በተዋናይነት የሰራህበት ፊልም ጥሩ ሆነ? ጥቂት በጐ ነገር ሊፈጥርልህ አይችልም?" ስትል ጠየቀችው ።

ጆኒ እራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አዎን ። ጥንት ወደነበረኝ ሁኔታ ሊመልሰኝ ይች ላል ። የአካዳሚውን ሽልማት ተቀዳጅቼ እጣዬን በሚገባ ብሞክር ያለዘፋኝነትም የተሳካ ህይወት መምራት እች ላለሁ ። ከዚያ በኋላም ላንቺም ሆነ ለልጆቹ የበለጠ ዳቦ ልሰጣችሁ እችላለሁ"

"አሁንም ቢሆን ከሚያስፈልገን በላይ አለን ።" አለች ጂኒ ።

"ልጆቼን ከአሁኑ የበለጠ እንዳናኖራቸው እሻለሁ ።" አለ ጆኒ ። "ጥቂት አረፍ ማለት እፈልጋለሁ ። ለምን ዘወ ትር አርብ ለእራት እናንተ ዘንድ አልመጣም?"

"የፈለገው ሩቅ ቦታ ብሆን ወይም ምን ስራ ቢበዛብኝ_ ዘወትር አርብ ከእናንተ ጋር ከመሆን እንደ ግልቀር እምልልሻለሁ ። ከዚያ በኋላ ደግሞ በሳምንቱን መጨረሻ ሳርፍ ልጆቹም ከኔ ጋር አልፎ አልፎ እረፍታቸውን ያሳልፋሉ ።"

ጂኒ ሲጋራ መኮስተሪያ ደረቱ ላይ አስቀመጠች ለትና ፡

"ያልከው ለኔ ይስማማኛል ። ሌላ ባል ያላገባሁት የአንተ አባትነት እንዳይቋረጥባቸው ስለፈለግሁ ነው ።" አለች ።

ይህን ስትል ያላንዳች የተለየ ስሜት ነበር ። ጆኒ ግን ጣሪያውን እየተመለከተ ይህን ማለቷ ትዳራቸው ሲፈ ርስ እና ዝናው ሲያሽቆለቁል ተናግራው የነበረውን ጭካኔ የተሞላበት ንግግር ለማካካስ መሆኑን ተረዳ ።

"በነገራችን ላይ ማን እንደደወለልኝ ታውቃለህ?" አለች ።

ጆኒ ማን እንደሆነ ለመገመት አልሞከረም ። አድር ጐትም አያውቅ ።

"ማነው?" ሲል ጠየቃት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቢያንስ ብዙ ሳትጨነቅ አንድ የምትገምተውን ሰው ስም ተናገረ" አለች ።

ጆኒ ግን አልመለሰላትም ።

"የጡት አባትህ ነበር ።" አለች ።

በእርግጥ ጆኒ በጣም ተደነቀ ።

"ማንንም ሰው በስልክ አያነጋግርም ። ምን አለሽ?"

"እንድረዳህ ነገረኝ ።" አለች ጂኒ ። "ወደቀድሞ ታላቅነትህ መመለስ እንደምትችል ፥ ትልቅ ለመሆንም ፈር መያዝህን ፥ ነገር ግን የሚያምኑብህ ሰዎች እንደ ሚያስፈልጉህ ገለጸልኝ ። ታዲያ እኔ ለምን ለዚህ ተግባር ተፈለግሁ ብዬ ጠየቅሁት ። እሱም አንተ የኔ የልጆቼ አባት በመሆንህ እንደሆነ መለሰልኝ ። በጣም ደስ የሚል ሽማግሌ ነው ። ሰዎች ግን ስለሱ አሰቃቂ ወሬ ያወራሉ ።"

ቨርጂኒያ ስልክ ትጠላለች ። እቤቷ ውስጥ በየክ ፍሎቹ ከተዘረጉት ስልኮች ሁሉ የመኝታ ቤቷንና የማድ ቤቷን ብቻ አስቀርታ ሌሎቹን አስቆርጣቸዋለች ።

ጆኒና ጂኒ እያወሩ ሳለ የማድ ቤቱ ስልክ ጭርር ሲል ተሰማቸው ። ስልኩን ለማንሳት ሄደች ። ተመልሳ ስትመጣ በፊቷ ላይ የሆነ መገረም ይታይ ነበር ።

"ስልኩ ላንተ ነው ጆኒ" አለች ። "ቶም ሄገን ነው የፈለገህ ፥ በጣም ብርቱ ለሆነ ጉዳይ እንደሆነ ነገረኝ ።"

ጆኒ ወደ ማድቤቱ ሄደና ስልኩን አንስቶ ፥ "አቤት ቶም" አለ ።

የቶም ሄገን ድምጽ የቀዘቀዘ ነበር ።

"ጆኒ ፥ የምትሰራው ፊልም በመጠናቀቁ ወዳንተ ዘንድ መጥቼ አንዳንድ ነገሮችን እንድፈጽም የጡት አባት አዘኖል ። ነገ ጧት አውሮፕላን ተሳፍሬ እንድ መጣ ይፈልጋል ። ሎስ አንጀሊስ ከተማ ላይ ብንገናኝስ?

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያው እለት ማታውን ወደ ኒውዮርክ መመለስ ይኖር ብኛል ። ስለዚህ ሌሊቱን ከኔ ጋር አሳልፉለሁ ብለህ አትስጋ ።" አለው ቶም ።

"ደህና ቶም" አለ ጆኒ ፥ "ከኔ ጋር ያሳለፈው ሌሊት ጊዜ ይባክንበታል ብለህ አትስጋ ። እዚህ ቆይተህ ትንሽ ተዝናና ። ግብግ መሳይ አዘጋጅና ከአንዳንድ የፊልም ሰዎች ጋርም ትተዋወቃለህ ።"

ጆኒ ፍንቴን ሁልጊዜም ቢሆን እንዲህ የመሰለ ዝግጅት አድርጐ ሊቀበላቸው እንደሚፈልግ ይገልጽላቸዋል ። ከድብቅ አለም ቤተሰብ ጋር ዝምድና ያለው መሆኑ የሚያሳፍረው ጉዳይ እንዳልሆነ የአካባቢው ህብረተሰብ እንዲያውቅለት ይሻል ።

"አመሰግናለሁ ፥" አለ ቶም ፥ "እሺ ይሁን ፥ ግን በተከታዩ ጧት በሚነሳው አውሮፕላን መሳፈር አለ ብኝ ። በአምስት ሰአት ተኩል ከኒውዮርክ በሚነሳው አውሮፕላን ስለምሳፈር ልትጠብቀኝ ትችላለህ?"

"በርግጥ እጠብቅለሀለሁ" አለ ጆኒ ።

"መኪናህ ውስጥ ቆይ ፥" አለ ሄገን ። "ከሰዎችህ አንዱን ወደኔ ላከውና ከአውሮፕላን ስወርድ ተቀብሎኝ መዳንተ ዘንድ ያምጣኝ ።"

"እሺ" አለ ጆኒ ።

ጆኒ ስልኩን እንዳዘጋ ወደ ሳሎን ሲመለስ ጂኒ ጥያቄ በተመላበት ገጽታ ተመለከተችው ።

"የጡት አባቴ እኔን ለመርዳት እቅድ አዘጋጅቷል ፣" አለ ጆኒ ። "በፊልሙ ላይ በተዋናይነት ለመስራት እንድበቃ ያደረገኝ እሱ ነው ። እንዴት እንደሆነ ግን አላውቅም ። ነገር ግን ከዚህ በኋላ የቀረውን ቢተወው ደስ ይለኝ ነበር ።

ወደ ሶፋው ተመልሶ ሄደ ። በጣም ድካም ተሰምቶታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወደ ቤትህ ከመሄድ ለምን እንግዳ ቤቱ ውስጥ አትተኛም ። በምሽት መኪና ከመንዳትም ትድናለህ ። ጧት ደግሞ ከልጆቹ ጋር ቁርስህን ትበላለህ ። ከእዚያ ካንተ ቤት ውስጥ ብቻህን መሆንህ ያስጠላኛል ። ብቸኝነት አይሰማህም?" አለች ጂኒ ።

"ቤት ብዙ አልቆይም ፥" አለ ጆኒ ።

"ታዲያ ምንም አልተለወጥክማ ?" አለችው ። ጥቂት ዝም አለችና "ሌላውን የመኝታ ክፍል ላዘጋጅልህ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ለምን ካንቺ መኝታ ቤት አላድርም?"

"አይሆንም" ስትል አፈር ብላ ፈገግ አለች ። ተግባቡ ። ጆኒ ጧት ሲነሳ ረፈድ ብሏል ።

ቁርሱ ግን ተዘጋጅቶለታል ። መኝታ ክፍሉ ሲከፈት የቁርሱን ማቅረቢያ ጋሪ እየገፉ የገቡት ሁለቱ ሴት ልጆቹ ነበሩ ።

ልቡ ተነካ ። ፊታቸው የጠራና የሚያብረቀርቅ ቆንጆዎች ሆነዋል ። ወደሱ ሮጠው መጡና አቀፉት ። ጉንጫቸውን በሻካራ ጺሙ እያሻሸ አስጮሀቸው ። አባታቸው ቁርሱን ሲበላ በናፍቆት ይመለከቱታል ። ድሮ ዘግይቶ ገብቶ ምግቡን ሲበላ ያገ ርሳቸው እንደነበረው ፥ ዛሬም ቡናውን እያስገ ነጨ ከዳቦው አጐረሳቸው ። ጆኒ ለልጆቹ ያለው ፍቅር ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ የሚያውቁት ጂኒና ጥቂት የቅርብ ወዳጆቹ ብቻ ናቸው ። በፍቺው የተነሳ ከልጆቹ መራቁ ይቆጨዋል ። ጂኒ ከፍቺ በኋላ ሌላ ወንድ የቤቷ ተቆጣጣሪ ባለማድረጓም ጆኒ ፎንቴን ይመካባታል ። እሱም በገንዘብ ማነስ ምክንያት ሌላ ባል ለማግባት እንዳትገደድ በቂ ገንዘብ ቆርጦላታል ። ያም ሆነ ይህ እሱም የማይፈልገውን የመታረቅ ጥያቄ ታነሳብኛለች ብሎ አይጠራጠርም ። ስለዚህ ግንኙነታቸው በዚህ አይነት ለመቀጠል አያሰጋውም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቶም ሄገንን የመቀበያ ቀጠሮው የደረሰ በመሆኑ ልብሱን ለባብሶ በጊዜ እንዲነሳ ጂኒ አሳሰበችው ። ሁለተኛ ሚስቱን ማርጎ አሽተንን ሊፈታ እንደሆነ ገለጸላት ። ጂኒ ለገና ሰሞን አብሯቸው ሊሰነብት ይችል እንደሆነ ጠየቀችው ። ለመጀመሪያ ጊዜ አላበት ታወሱት ። ድምጹ ደህና በነበረበት ወቅት በአላት ዘፍኖ ደህና ጥቅም የሚያገኝባቸው ቀናት ይሁኑ እንጂ የተቀደሱ ቀናት መሆናቸውን ያምናል ። የአምናን ገና ማርጎ አሽተን እንድታገባው ሊያግባባት አብሯት ስፔይን ነበር ያሳለፈው ።

"አዎን የገናን ዋዜማና የገናን እለት አብሬአችሁ ነው የማሳልፈው ፡" አላት ።

ጆኒ ቶም ሄገንን ለመቀበል ሲወጣ ሁለቱ ልጆቹ ግራና ቀኝ እጁን ይዘው ፣ ጂኒ ከጫላቸው እየተከተለች እስከ መኪናው ሸኙት ። ሶስቱንም ስሟቸው ወደ መኪናው ገባ ።

ጆኒ ፎንቴን አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሰ ቶምን ሲቀበል ማንም ሰው እንዳያየው ከቶም ጋር በተነጋገሩት መሰረት መኪናው ውስጥ ሆኖ ጠበቀው ። የህዝብ ግንኙነት ሰራተኛው ቶምን ከተቀበለው በኋላ ይዞት መጣ ። ሁለቱ ሲገናኙ ለጊዜው ቀዝቃዛ ስሜት ይታይባቸው ነበር ። ጆኒ ከዶኑ ጋር እንዳልገናኝ ቶም እንቅፋት ይሆንብኛል የሚል ቅሬታ አለው ።

"እንዳንድ ነገር እንድረዳህ ከርስትና አባትህ ልኮኛል" አለው ቶም ።

ፊልሙ ተሰርቶ አልቋል ። ምልትዝም ቢሆን ምንም ጆኒ ፎንቴንን ቢጠላው አሰር ሚሊዮን ብር የፈጀበትን ፊልም አያበላሸውም ። ታዲያ አሁን ደግሞ የምን እርዳታ ያስፈልገዋል? ጆኒ ይህን ሁሉ በአእምሮው አሰላሰለ።

"ለመሆኑ አሁን በሰራኸው ፊልም ተመዳድረህ

t.me/OLDBOOKSPDF

የዚህ አመት አንደኛ ተዋናይ ተብለህ መሸለምህ በሙያህ ላይ እጅግ ወሳኝነት ይኖረዋል? ወይስ እንዲያው ለውዳሴና ለዝና ነው? መቸስ ውዳሴና ዝናን ሁሉም ይወዳታል።"

"ከክርስትና አባቴና ካንተ በስተቀር ከንቱ ውዳሴና ዝና የማይወድ የለም። አንድ የአካዳሚ ሽልማት ማግኘት አንድን ተዋናይ ለአስር አመት ገናና እና በጣም ተፈላጊ ያደርገዋል።"

በድምጹ መበላሸት የደረሰበትን ውድቀት ለመካስ ሽልማቱ የሚኖረውን ጠቃሚነት ሁሉ ጆኒ ለሄገን አስረዳው።

"የክርስትና አባትህ እንደነገረኝ፥ ሁኔታዎች አሁን ባሉበት አያያዝ የውድድሩ አሸናፊ ልትሆን አትችልም፥" አለ ሄገን።

ጆኒ ፍንቴን የንዴት እንባ እየተናነቀው፥

"ምን ማለትህ ነው?" አለው። "ሌላ ቀርቶ ፊልሙ ገና በቅደም ተከተል እንኳን አልተገጣጠመም። ዶኑም ስለፊልም ስራ የሚያውቀው ነገር የለም። ታዲያ ለምንድ ነው ሶስት ሺህ ማይል በአይሮፕላን ተጉዘህ መጥተህ የማይረባ ነገር የምትነግረኝ?"

"ጆኒ፥ እኔ ስለፊልም ስራ የማውቀው ነገር የለም። እኔ የክርስትና አባትህ መልእክተኛ ብቻ ነኝ። ስላንተ ጉዳይ ግን ብዙ ተነጋግረናል። ስላንተ ብዙ ያስባል። ችግርህን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመወጣት አሁንም የሱ እርዳታ እንደሚያስፈልግህ ይገምታል። ለዚህ ነው እዚህ የመጣሁት። አንተም እንደ ዘፋኝና ተዋናይ ብቻ ማሰብህን ተውና እንደ አንድ ጠንካራ የድርጅት አንቀሳቃሽ አድርገህ እራስህን አስብ"

ጆኒ ፍንቴን ሳቀና፥ "ያችን ሽልማት ካላገኘኋት ጉልበቴ ዝሎ አቅሜ ከልጆቼም እንደማይሻል አትጠራጠር፥" አለው። "እንደምታውቀው ድምጼ ተበላሽቷል።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደቀደሞው ድምጼ ጥሩ ቢሆን ኖሮ ትንሽ ልንቀሳቀስ እችል ነበር ። ለመሆኑ ክርስትና አባቴ እንደማላሸንፍ እንዴት አድርጎ ሊያውቅ ቻለ? ብቻ ይሁን ፤ መጭም እሱ ተሳስቶ አያውቅምና ልጠራጠረው አልችልም ።''

''ጃክ ዎልትዝ ለአንተ መወዳደሪያ ገንዘብ ማውጣት አይሻም ። እንዲያውም መራጮች አንተን እንዳይመርጡ ነግሯቸዋል ። በጉቦ ፤ በቆነጃጅትና በሌሎች መደለያዎች መራጮችን ሸንግሏቸዋል ።''

ጆኒ ተበሳጭቶ ብርጭቆውን በውስኪ ሞልቶ ፊቤለጠና ፤ ''አልቆልኛል በለኛ!'' አለ ተስፋ በመቁረጥ ።

''መጠጣት እኮ ምንም አይረዳህም?'' አለው ሄገን ።

''ገደል ግባ!'' አለው ጆኒ ።

ሄገን ትእግስቱ አለቀ ። ነገር ግን ተልእኮውን በመገንዘብ ፤

''እንግዲያው ስለ ስራ ብቻ እናውራ'' አለው ።

ጆኒ ፎንቴን በተናገረው ብልግና ወዲያው ተጸጸተ ። አይኖቹ እምባ እንዳዘሉ ሄገንን ይቅርታ ጠየቀው ። በሁኔታው በመናደድም የሚጠጣበትን ብርጭቆ ከግድግዳ ጋር አላተመው ። የወረወረው ብርጭቆ ባለመሰበሩ ተደንቆ ለአፍታ በጽሞና ቆየና ፤ ለዘብ ባለ ድምጽ ሄገንን ከተማጠነው በኋላ ፤ ከእንግዲህ ድምጹ እስኪስተካከል ድረስ መጠጥ እንደማይቀምስ ቃል ገባለት ። ሄገንም ከልቡ ይቅርታ ከማድረጉም በላይ አዘነለት ።

''አይዞህ ፤ ይህን ያህል የሚያሰጋ ነገር አይኖርም ። ዎልትዝ የጠነሰሰብህን ሴራ ዶኑ እንደሚበጣጥሰው ቃል ገብቷል ። ነገር ግን አንተ ራስህ የፊልም አዘጋጅ ለመሆን አንኮልና ወኔ እንዳለህ ለማረጋገጥ ይፈልጋል ።''

''እንዴት አድርጎ ሽልማቱን እንዳገኝ ሊያደርግ ይችላል?''

t.me/OLDBOOKSPDF

“አትጠራጠር ፥ ክርስትና አባትህ ከጃክ ዎልትዝ የበለጠ ጉልበትም አንጐልም አለው ። ነገሮችን የሚቆጣጠሩ ሰዎች ፥ የሰራተኛ ማህበራት እና መራጮች ሁሉ በእጁ ናቸው ።”

“ይሁን እሺ ፥ ያልከኝን እቀበላለሁ ። ፊልም አዘጋጅ ለመሆን ችሎታውም ሆነ ቆራጥነቱ ይኖረኛል ። ግን ገንዘብ የለኝም ። የሚያበድረኝም ባንክ አይኖርም ። ፊልም ማዘጋጀት ብዙ ሚሊዮን ብር ይፈጃል ።”

“ሽልማቱን ካገኘህ በኋላ ሶስት የራስህን ፊልሞች አዘጋጅተህ ለማውጣት እቅድ አውጣ ። ከፍተኛ ባለ ሙያዎችን ቅጠር ፥ ከሶስት እስከ አምስት ፊልም ለማ ውጣት ተዘጋጅ”

“አብደሀል መሰለኝ ። ይህን ያህል ፊልም ለማዘጋጀ ሀያ ሚሊዮን ብር ይጠይቃል ።”

“ገንዘብ ሲያስፈልግህ አነጋግረኝ ። የሚያበድርህን ባንክ ስም እገልጽልሀለሁ ። ነገር ግን ቀደም ብለህ ፥ የምትጠይቀው ገንዘብ ለምን ለምን እንደሚውል በዝ ርዝር እንድትገልጽልኝ ። እሺ?”

ጆኒ ጸጥ ካለ በኋላ ለዚህ ውለታ ከሱ የሚጠበቅበት አጸፋ ይኖር እንደሆነ ቶምን ጠየቀው ። ምንም የሚጠበቅበት የውለታ ምላሽ አለመኖሩንና ፥ እንዲያውም ከቤተሰቡ ውዝግብ ውስጥ ጆኒን ፈጽሞ እንዳያስገቡት ለቶም ሄገንና ለሶኒ ዶኑ ጥብቅ መመሪያ የሰጣቸው መሆኑን ገለጸለት ።

ቶም ለጆኒ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ከባንኩ የሚያዝኘውን ብድር በቅብጠት እንዳያባክነው ብቻ ነበር ።

“ከርስትና አባቴን በዚህ አትስጋ በለው ። የፊልም ስራ ጃክ ዎልትዝን እንኳን ትልቅ ሰው አድርጐታል ፥ ለኔ አያቅተኝም ።”

t.me/OLDBOOKSPDF

ቶም ሄገን መልእክቱን አጠናቋል ። ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ጆኒ እንዲመልሰው ከጠየቀው በኋላ በመጨረሻ የሰጠው ማስገንዘቢያ ውለታ ሲደራደር የህግ አማካሪ እንዲቀጥር ነበር ። "ፈቃደኛ ከሆንክ ፥ ከመፈራረምህ በፊት ውሉን አሳየኝ ።"

"በፊልሙ ጽሑፍ ጉዳይና ተዋንያንን በመምረጥ ወይም ይህን በመሳሰለ ጉዳይስ ፥ ካንተ ጋር መመካከር አለብኝ?" ሲል ጆኒ ጠየቀው ። በዚህ ጉዳይ ላይ የመሰለውን ማድረግ እንደሚችል ቶም አረጋገጠለት ።

"መልካም ። እኔ ነኝ አውሮፕላን ማረፊያ የማደር ስህ ። ክርስትና አባቴን አመስግንልኝ ። ስልክ ደውዬ አመሰግነው ነበር ። ግን እሱ ሰው በስልክ የማያነጋግረው ለምንድነው?"

"ድምጹ እንዲቀዳ አይሻም ። ተንኰለኞች ቃላቱን ከቴፑ ቆራርጠው አገጣጥመው ያላለውን ከማስመሰል ወደ ኋላ አይሉም ።"

ጆኒ ሄገንን ወደ አውሮፕላን ማረፊያ እራሱ ይዞት በመሄዱ ከጠበቀው በላይ ሆኖ ስላገኘው አመሰገነው ። ሄገን ወትሮም ቢሆን የጆኒን ጠንካራ ጐን ያውቃል ። ሌላ ቀርቶ ዶኑን እንኳን የሚደፍሩ ጆኒና ሚካኤል ኮርሌዮኔ ብቻ መሆናቸውን አይክድም ።

ጆኒ ሄገንን አውሮፕላን ማረፊያ ካደረሰው በኋላ ወደ ጂኒ ቤት ተመለሰ ። ጂኒ ገረማት ። ጆኒ ስለ ወደፊቱ ፊልም አዘጋጅነቱ ስራ በጽሞና ማሰብ የሚችልበት አካባቢ የጂኒ ቤት ሆኖ ታየው ። ለጥቂት ሳምንታት ወይም ከዚያ በላይ ከጂኒ ጋር አብሮ መቆየት መልካም ነው ። ልጆቹን ለሽርሽር ያወጣቸዋል ። ምናልባት ጥቂት ወዳጆችም ይጋብዛል ። መጠጥ እና ማጤስ ያቆማል ። እራሱን በሚገባ ይጠብቃል ። ምናልባትም ድምጹ ይመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለስለት ይሆናል ። ይህ ከሆነማ የዶኑን ገንዘብ ከስራ ላይ ያውልና ተመልሶ ታላቅ ሰው ይሆናል ማለት ነው ።

ጂኒ የእንግዳ መኝታ ቤቱን አዘጋጅችለት ። እንደ ባልና ሚስት መኖርም ሆነ አንድ አልጋ ላይ መተኛት እንደማይሆን ተረድተውታል ። የዜና ማሰራጫዎች እንዳናፈሱት ለትዳራቸው መፍረስ ምክንያት የሆነው እሱ ነው ይባል እንጂ ፣ እሷ ከሱም የበለጠ አስተዋጽኦ አድርጋለች ።

ዝነኛ ተዋናይ ሆኖ ሳለ ትዳሩን ስለማፍረስ አስቦም አያውቅ ነበር ። በርግጥ የተሰማራበት ሙያ ስለሚያመቻችለት ለዝሙት መጋለጡ አልቀረም ፣ ቆነጃጅት ይሹት ነበር ። እሱም እንዲሁ ሲያሳድዳቸው ኖሯል ። እንዲያውም ደናግል ልጃገረዶችን በመሻቱ መሳቂያ ሆኖ ቆይቷል ። የተለያየ ቅርጽ ካላቸው ሴቶች ጋር የመጀመሪያውን ፍቅር መቅመስ ለሱ ታላቅ ድል ይመስለዋል ። ይህን ከመሳሰሉት ገጠመኞች በተለይ ከአንድ የጃዝ ሙዚቀኛ ልጅ ጋር የተዳራበት እለት ትዝ ይለዋል ። ከንፈሯ እንደማር እሸት ጥሞታል ። ድንግልናዋም ጣፋጭና ፍጹም ሆኖ ይታሰበዋል ። ጂኒ ኋላ ቀር ነው ብለው ያውሩበት እንጂ ፣ ምንም ቢሆን ከስርአት ውጭ የሆነ ግብረ ስጋን አይሻውም ። ሁለተኛ ሚስቱን የጠላበት አንዱም ቅጥ ያጣ ወሲብ ስለምትሻ ነበር ። ይህንኑ ባህሪውን ስላልወደደችለት ኋላ ቀር ነው በማለት አወራችበት ። ያም ሆነ ይህ ለፍቅር መለዋወጥ ይበጃሉ የሚላቸው ዘይቤዎች አሉት ።

ጂኒ ቡናና ኬክ እንዳመጣችለት ከሄገን ጋር ያወራውን አንስቶ ዶኑ ጂኒ የፊልም አዘጋጅ እንዲሆን እንደሚፈልግ ገለጸላት ። ጂኒ ነገሩ ደስ ቢላትም የዶኑ አቅም ምን ያህል እንደሆነ ስለማታውቀውና የሄገን

t.me/OLDBOOKSPDF

መምጣት ጠቃሚነቱም ምን ያህል እንደሆነ ስላልታ
ያት በውል መረዳት አልቻለችም ።

ቡናቸውን ሲጨርሱ ሌሊቱን ሲሰራና ስልክ ሲያውል እንደሚያመሽ ነገራት ።

"የማገኘውን ግማሹን በልጆቹ ስም ነው የማስመ ዘግበው" አላት ።

የምስጋና ፈገግታ አሳይታው "ደህና እደር" ብላ ስማው ወጣች ።

ሲጋራውን ከፊቱ አስቀምጦ አእምሮውን ማሰ ራት ጀመረ ። የአዲሱ ፊልም መሰረት የሆነውን ልቦለድ ታሪክ ለጻፈው ደራሲ ስልክ ደወለለት ። ደራሲው በስነ ጽሁፍ አለም ዝነኛ ቢሆንም ሆሊውድ መጥቶ ግን ተቀባይ አላገኘም ። አንድ ምሽት ከአንዲት ተዋናይ ጋር ወጥቶ ሳለ አንድ አይጥ የመሰለ የአስቂኝ ፊልም ተዋናይ ወጣቷን በጣቱ ምልክት ሲሰጣት ጥላው ሄዳለች።

ይህንን ደራሲ ጆኒ በመጀመሪያ በአድናቆት ሞቅ ካደረገው በኋላ ስለተከታዩ መጽሀፉ ጠየቀው ። ደራ ሲው መጽሀፉን ጽፎ ሲጨርስ አንድ ቅጂ እንዲሰ ጠው ሲጠይቀው ለጽሁፉ ከምልትዝ የተሻለ እንደሚ ከፍለው አረጋገጠለት ። ካሁን ቀደም ምልትዝ ለመጽ ሀፉ የሚረባ ገንዘብ ያልከፈለው ደራሲ ጆኒ የተሻለ ገንዘብ ሊያስከፍለው ቃል ሲገባለት ተደሰተ ። ጆኒ ከሰውዬው ጋር ከመሰነባበቱ በፊት ከገና በአል በኋላ ወደኒውዮርክ ስለሚሄድ እራት ጋበዘውና አብሯት የሚዝናናት ወዳጅም እንደሚያዘጋጅለት ነገረው ። ሰው የው ሳቀና ግብዣውን በእሺታ ተቀበለው ።

ጆኒ ቀጥሎ ለፊልሙ ዳይሬክተርና ለፊልም አንሺው ደውሎ ባለፈው ፊልም ላይ ጃክ ምልትዝ ባይደግፈውም እነሱ ስለረዱት የተሳካለት መሆኑን በመግለጽ አመሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገናቸው ። ይህን ካለም በኋላ ጆኒ እንዲያደርግላቸው የሚ
ሹት ነገር ቢኖር ከመጠየቅ ወደኋላ እንዳይሉ ነገራቸው ።
በመጨረሻም ከሁሉ አስቸጋሪውን የስልክ ጥሪ አደ
ረገ ። ጃክ ዎልትዝን ፊልሙን እንዲሰራ ስለፈቀደለት
ከአመሰገነው በኋላ ለወደፊት ከእሱ ጋር ለመስራት
በጣም እንደሚፈልግ ገለጸለት ። ጆኒ ይህን ያለው ከልቡ
ሳይሆን ፥ ጃክ ዎልትዝን ለማዘናጋት ፥ በመጨረሻም
እንደሱ የፊልም አዘጋጅ ሊሆን መብቃቱን ሲያውቅ
እንዲቃጠል ያቀደው በቀል ነበር ።

የስልክ ጥሪውን እንዳጠናቀቀ ፥ ላለማጤስ ቃል
የገባውን ረስቶ ሲጋራውን ማቡነን ጀመረ ። ከፊቱ ያለ
ውን ውስኪ ግን ላለመጠጣት በቃሉ ረጋ ።

ጸጥ ባለው ክፍሉ ውስጥ ልጆቹና የድሮ ሚስቱ
ትኝተው ሳለ ፤ ሙያውን ሁሉ ላበላሸችበት ለዚያች ውሻ
ብሎ ጥሏቸው መሄዱ ተሰማው ። ነገር ግን ማንንም ሴት
ላለመጥላትና በክፋት ላለመበቀል ያለው አቋም ስለሚ
ያጽናናው ለእርቅም ባይሆን ከቤቱ መመለሱ ደስ ብሎ
ታል ። በመሰረቱ ሚስቱንና ልጆቹን በቂ ገንዘብ ሰጥ
ቷቸዋል ። ከእያንዳንዱ የዘፈን ሽክላዎቹ እንኳን ለል
ጆቹ የተወሰነ ስጦታ በፈቃዱ ያደርግ ነበር ። ለሴቶች
በጐ ፈቃድ ቢያሳይም ፥ ስጦታ ቢለግሳቸውም ፥ ቢወዳ
ቸውም ዘላቂ ፍቅር አልነበረውም ። እነሱም በውድቀቱ
ጊዜ ስቀውበታል ። ስለዚህ ታማኝ አለመሆኑ አልጸጸ
ተውም ። ለልጆቹ ያለውን የአባትነት ሀላፊነት ግን
መቸም አልዘነጋም ።

ለቀድሞ ሚስቱ የነበረውን ክብርም አልቀነሰም ።
ዘመዶቿን ረድቷል ። ማን አክሎኝ ባይነትም አልነበረበ
ትም ። እህቶቿ ሰርግ ላይ ዘፍኗል ። እሷ ጠይቃው እምቢ
ያላት ነገርም የለም ። ስለዚህ ዛሬ ዝናውና ጥቅሙ ሲቀ
ነሱ ተቀባይ አላጣም ። ሚስቱ አስተናግደችው ። ተስፋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቆርጦ ዘፈኑ የተቀረጸበትን ዋናውን ሸክላ እስከመስበር በደረሰበት ጊዜ ያጽናናችው የልጆቹ እናት ነበረች ።

ጆኒ ለመተኛት ፈልጐ ነበር ። ነገር ግን ገና አንድ ሰልክ ጥሪ ይቀረዋል ። የድሮ አብሮ አደግ ጓደኛው ኒኖ ቫሌንቲ ዘንድ ደውሎ ፣

"ታዲያስ ኒኖ ፣ እንደምነህ ። እኔ ዘንድ መጥተህ መስራት ትፈልጋለህ ?" ሲል ጠየቀው ። ኒኖ እንደተ ለመደው በጠጣ አንደበቱ ፣

"ግሩም ነበር ፣ ብቻ እንጃ ። ባለትዳሮችን እያሳሳ ቅኩ እዚህ የጭነት መኪና ሹፌር ሆኜ በሳምንት የተ ጣራ መቶ ሀምሳ ብር አገኛለሁ ። አንተ ምን ያህል ትሰጠኛለህ ?" አለው ።

"እኔ በሳምንት አምስት መቶ ብር እሰጥሀለሁ ። በዚህ ላይ የፊልም ተዋንያት ኮረዶች ጋር አገጣጥ ምሀለሁ ።"

"እስቲ ላስብበትና የሚያማክሩኝንም ልጠይቅ ።"

"አትቀልድ ኒኖ ። እዚህ እንድትሰራልኝ እፈል ጋለሁ ። ነገ ጧት በአውሮፕላን በረሀ እኔጋ እንድትመ ጣና ኮንትራትህን ለአንድ አመት እንድትፈርም ። ሴቶ ቼን የቀማኸኝ እንደሆን ግን የአመት ደመወዝህን ከፍዬ አባርርሀለሁ ። ተስማማህ ?"

ኒኖ ጸጥ ብሎ ቆየና ፣ "ስማ ጆኒ ፣ እውነትህን ነው ወይስ ትቀልዳለህ ?" አለ ።

"በቁም ነገር ነው የማናግርህ ። ኒውዮርክ ከሚገ ኘው ወኪሌ ቢሮ ሂድና ቲኬትና ገንዘብ ተቀበል ። እኔ ጧት እደውልላቸዋለሁ ። ነገ አውሮፕላን ማረፊያ የሚቀበልህ ሰው እልካለሁ ።"

ኒኖ አሁንም ዝም አለና እጅ በሰጠ አንደበት "እሺ ፣ ጆኒ" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጆኒ በምሽቱ ስራው በጣም ረካ ። ክርስትና አባቱ የሚጠብቅበትን ወኔ ማሳየት ጀምሯል ። ኒናን በመር ዳቱ ክርስትና አባቱ እጅግ ደስ እንደሚለው ያውቃል ። የቀድሞ ዘፈኑ የተቀረጸበትን ሽክላ በብስጭት ከሰበረ በት እለት አንስቶ የተቀረጸበት የውድቀት ስሜት ለመ ጀመሪያ ጊዜ ተገፈፈለት ።

ምእራፍ አስራ ሶስት

ጆኒ ፍንቴን የፊልም አዘጋጅነት ስራውን የጀመረው ክርስትና አባቱን በሚያስደስት ስራ ነበር ። ውጥረት ከበዛበት ስራው መሀከል ለጆኒ ውሊታ ለመጣል ሲል የሙዚቃ አቀነባባሪው ኤዲ ኒልስ የጆኒን ሽክላ ለመቅ ረጽ ስቱዲዮ ገብቷል ።

ኒኖ ድምጹን ለማስቀረጽ መዘጋጀት ያለበት ቢሆ ንም መጠጡ ካጠገቡ አልተለየውም ። ኒኖ ቢጠጣም በወጉ መዝፈን ስለሚችል ጆኒ አልሰጋም ። የሚቀረጹት የጥንት የጣሊያንና የሲሲሊ ዘፈኖች ሲሆኑ ፥ አንደኛው ጆኒና ኒኖ ቀደም ሲል በኮኒ ኮርሌዎኔ ሰርግ ላይ ዘፍ ነውት የነበረ ነው ። እንዲህ የመሰለውን ዘፈን ዶን ኮርሌዎኔ ስለሚወደው ይህን ዘፈን በቅድሚያ በማው ጣቱ ጆኒ ደስ ብሎታል ። ሽክላዎቹ ብዙ ገዥ እንደሚያ ገኙም ገምቷል ። ዶኑ የኒኖም ክርስትና አባት በመሆኑ ፥ ኒኖ በዘፈኑ ላይ ሊካፈል መቻሉ ደስ ይለዋል ።

ዘፈኑ መቀረጽ ሊጀምር ሲል ጆኒ ፥

"ስማ ያገር ልጅ! በደንብ ከዘፈንክ የማመጣልህን ልጅ አታውቅም" በማለት ኒኖን አበረታታው ።

"ማንን? ላሲን ነው?" አለ ኒኖ ።

ጆኒ ሳቀና "አይደለም ። ዲያና ዳንን ነው" አለው ። ኒኖ ደስ ቢለውም "ላሲን ልታመጣልኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

አትችልም?" ሲል በከንቱ ተስፋ ከመጠይቅ ወደኋላ አላለም ። ዘፈን የሚቀረጽበት ሰአት ደረሰ ። አርኬስት ራው ሙዚቃውን ሲጀምር ሁለቱም ዘፈናቸውን ጀመሩ ። የጆኒ ድምጽ ብዙም ስለማያወላዳ በዘፈኑ ውስጥ አብዛኛው ድምጽ የኒኖ እንዲሆን ታቅዶ የተዘጋጀ ነበር ። ኒኖ ማንዶሊኑን ካልያዝኩ መዝፈን ያቅተኛል ስላለ ጆኒ የመጠጥ ብርጭቆውን እንዲይዝ ነገረው ። ሲዘፍን መጠጡን እየተጐነጨ ቢሆንም ዘፈኑ አልተበላሸም ። በዘፈኑ መጨረሻ ላይ የሙዚቃው ቡድን ባድናቆት አጨበጨበላቸው ። ሙዚቃው እንዳበቃም ኤዲ ኒልስ ወደ ጆኒ ጠጋ ብሎ ፣ "ድምጽህ በጣም ጥሩ ሆኗል ። ምናልባትም በራስህ ድምጽ ብቻ ሽክላ ማስቀረጽ የምትችል ይመስለኛል" አለው ።

"እባክህ አትቀልድብኝ ኤዲ ። በሁለት ሰአት ውስጥ ድምጼ ለመናገር እንኳን እስኪያቅተኝ እንደሚ ሸክር አትጠራጠር ። ለመሆኑ ከዚህ በኋላ ዛሬ የዘፈንነው ዘፈን የሚስተካከል ነገር ይኖረዋል?"

"ኒኖ አንዳንድ ስህተቶች ስላደረገ ነገ ስቱዲዮ መምጣት አለበት ። ግን ድምጹ ከጠበቅኩት በላይ ሆኖ ነው ያገኘሁት ።"

"እሺ እንግዲያስ ፣ መቼ እንሰማዋለን?"

"ነገ ማታ ፣ አንተ ቤት" አለ ኤዲ ።

ጆኒ ኤዲን ካመሰገነ በኋላ ኒኖን እጁን ይዞ ከስቱዲዮ ወጣ ። ወደ ጂኒ ቤት ሳይሆን ወደራሱ ቤት ይዞት ሄደ ። ቤቱ እንደደረሱም ማታ ትልቅ ግብግ ላይ ስለ ሚያመሹ ገላውን እንዲታጠብና ትንሽ እንዲተኛ ነገረው ። ኋላ የሚያመሹበት ግብግ ላይ ብዙ ጠጥቶ ሰርአት አልባ እንዳይሆንም አስጠነቀቀው ።

ኒኖ መጠጡን ሳያቋርጥ ከማን ጋር ሊያመሽ እንደሚችል በጉጉት ጆኒን ጠየቀው ። ከዝነኛዋ ተዋናይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዲያና ዳን ጋር እንደሚያዳራው ታል ሲገባለት ኒኖ ከመጠን በላይ ቋመጠ ።

"እባክህ ያን ያህል አትጓጓ ። ይህን ያህል የሚያ ቋምጥ ጉዳይ አይደለም" ሲል ጆኒ አስገነዘበው ።

ልጅ እግሮቹ 'የሆሊውድ ብቸኛ ልብ የተዋንያን ክበብ' እያሉ የሚሳለቁበት ክበብ ዘወትር አርብ ምሽት የዎልትዝ አለም አቀፍ ፊልም ኮርፖሬሽን የህዝብ ግንኙነት አማካሪ በሆነው በሮይ ማክኤልሮይ ውብ ቤት ይካሄዳል ። ይህ ክበብ የተቋቋመው ብዙ ላገለገሉ ሴት የፊልም ተዋንያት በረፋዱ እድሜያቸው ላይ የማፍቀርና የመፈቀር ጉልበታቸው ዝሎ እንደጥንቱ አሳዳጅ አልባ ሆነው ገንዘብና ዝና ብቻ ታቅፈው እንዳይነሆልሉ ፥ የሚሹትን ጐረምሳ ላንዴም ሆነ ረዘም ላለ ወቅት የሚመለምሉበት መድረክ እንዲሆን እራሱ ጃክ ዎልትዝ አስቦት ነው ። ክበቡ በሌላ ስፍራ ቢካሄድ የሚያስከትለው መዘዝ ቀድሞውኑ ለጃክ ዎልትዝ ታይቶታል ። የዚህ ማሽኮርመሚያ ገበያ ድንገት ቅጥ አጥቶ ጠብ ቢጫር ፖሊስ ጣልቃ ገብቶ ላደባባይ መጋለጣቸው አይቀርም ። በህዝብ ግንኙነት አማካሪው ቤት ከተካሄደ ግን ሁከት ቢነሳም ወሬው ውጭ እንዳይወጣ ፖሊሱንም ጋዜጠኛውንም በጉቦ አፉን ለማበት አመች ሆኖ ተገኝቷል ። ይሁን እንጂ ለክበቡ መቋቋም ሽፋን የሚሆን አላማ ላይ ላዩን ይወራለታል ። ክበቡ ገና ለዝነኛ ከዋክብትነት ያልበቁ ተዋንያንን በቅርቡ የተሰሩ ፊልሞችን ተመልከተው ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ታስቦ እንደተቋቋመ ተደርጐ ይወራል ። ስለዚህ "እገሌ የሰራውን አዲስ ፊልም ሂደን እንይ" ብለው መሄዳቸው አይቀርም ። ወጣት ወንዶች ተዋንያን፤ ኮረዳዎች ሞልተው ሳለ ከጐምቱዎች ጋር መጃጃሉ አይጥማቸውም ። ወጣት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሴት ተዋንያንን ግን አፍ አውጥቶ አትግቡ የሚላቸው ባይ ኖርም እንዲገቡ የሚያደፋፍራቸው የለም ። ለዚህ ነው ፥ "የብቸኛ ልብ ክበብ" የሚል ቅጽል ስም ያወጡለት ።

በዚህ ክበብ አዲስ ፊልም የሚታየው እኩለ ሌሊት ላይ ነው ። ጆኒና ኒኖ ከምሽቱ አምስት ሰአት ላይ ስፍራው ደረሱ ። በዚያ ስፍራ ጆኒን ማየቱ ማክኤልሮይን አስደንቆት ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገለት ። ጆኒም ያገሩን ልጅ አካባቢውን ሊያስጐበኘው ማምጣቱን ገለጸለት ። ማክኤልሮይ ኒኖን አትኩሮ ተመለከተውና ፣

"እነዚህ ሴቶች ዛሬ ይህን ሰውዬ በህይወቱ ይውጡታል" ሲል ከቀለደ በኋላ ፥ ሁለቱንም እየመራ ወደኋላ ከሚገኝ መዝናኛ ቦታ ወሰዳቸው ። የኋለኛው መዝናኛ ከአትክልትና ከተከተረ ኩሬ ጋር ትይዩ ሆኖ ልዩ ውበት የሚሰጡ መብራቶች የተተከሉበት የተያያዙ ክፍሎችን አቅፏል ። ኒኖ በአፍላ ወጣትነቱ ሳለ በጭለማ ክፍል ሆኖ በሲኒማ ቤት ግድግዳ ላይ እየተመለከተ ይነሆልልላቸው የነበሩ ተዋንያንን ዛሬ በአስደንጋጭ የውበት ቀለም ተጋጊጠው በአካል አያቸው ። የጉልበታቸውንና የመንፈሳቸውን መላሸቅ የሚደብቅላቸው ምንም ነገር አይኖርም ። እነዚህ ተዋንያት ሲያርፉም ሆነ ሲንቀሳቀሱ ግርማቸው አልተለያቸውም ። ነገር ግን በተድበለበለ ሰም የተቀረጸ የብርቱካን ተምሳሌት ስለመሰሉት ስሜቱን አልቀሰቀሱበትም ። ይልቁንም የሚወዳቸውን መጠጦች የያዙ ጠርሙሶች ከተኮለኮሉበት ጠረጴዛ ተጠጋ ። ጆኒም አብሮት ሆኖ ሲጠጡ ሳለ በድንገት ሙዚቃ መሳዩ የዲያና ዳን ድምጽ ከኋላቸው ተሰማ ።

ኒኖ ፥ እንደማናቸውም በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍቃሪዎች ፥ የሁለት አካዳሚ ሽልማት አሸናፊ የሆነችው የዲያና ዳን ድምጽ በአንጐሉ ውስጥ ተቀርጿል ። በሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራቻቸው እያሉ ፊልሞች ላይ ከቶውን ብላ የማታውቀውን ቃል ለጆኒ ስታሰማ ኒኖ አዳመጠ ፡

"ጆኒ ፡ አንተ ዲቃላ! ላንድ ምሽት ብቻ አብረኸኝ ወጥተህ ብትተወኝ ምን አይቶብኝ ነው ብዬ የስነ ልቦና ሀኪሜ ዘንድ ሄድኩ ። እንዴት ለድጋሚ ብቅ ሳትል ፡ እባክህ?"

ጆኒ ጉንጪን ሳም አደረገና ፡ "ለወር ያህል ከጥቅም ውጭ ስላደረገሽኝ ነዋ! ይልቅስ ወንድሜን ተዋወቂው ። ምናልባት እሱ ይችልሽ ይሆናል" አላት ።

ዲያና ኒኖን ቀብረር ባለ አስተያየት ተመለከተችውና ፡ "የምሽቱን ፊልም ማየት ይወዳል?" በማለት የግብዣ ጥያቄ አቀረበች ።

ጆኒ ሳቅ አለና ፡ "እስካሁን እድል አልገጠመውም ። ለምን አብረሽው አይታይም?" ሲል ጋበዛት ።

ኒኖ ከዲያና ጋር ብቻውን በመሆን ከመጠጡ በር ከት አድርጎ ተጐነጨ ። ምንም ያልተደናገጠ ለመምሰል ቢሞክርም አልቻለም ። የዲያናን ወደላይ መለስ ያለ አፍንጫና የውበቷን ማራኪነት ያውቀዋል ። በሲኒማ ላይ ልቧ ተሰብሮ ብቻዋን በመኝታ ቤት ሆና ልጇ ቿን ያላባት አስቀርቶ ለሞተው አውሮፕላን አብራሪ ባሏ ስታለቅስ ተመልክቷል ። ተናዳ ፡ ተበድላ ፡ ተዋርዳ ፡ ሆኖም ክብሯን ጠብቃ ፡ ባለጌው ክላርክ ጌብል ለዝሙት መውጫ እንደማትሆነው ተገንዝቦ ሲተዋት ኒኖ በፊልም ላይ አይቷታል ። በሌላ በኩል ለፍቅር መስዋእት ሁና ቢያንስ ስድስት ጊዜ ስትሞትም አይቷል ። ኒኖ በሲኒማ ግድግዳ ላይ ቢሆንም አይቷታል ፡ ሰምቷታል ፡ ስለሷም ሲያልም ኖሯል ። ይሁን እንጂ ፡ በአካል ቀርባ ከራሷ አንደበት ወጥቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ለብቻው ለምትና ገረው ቃል ግን ዝግጁ አልነበረም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በዚህ ከተማ ከሚገኙት ወኔ ካላቸው ጥቂት ግለሰቦች ጆኒ አንዱ ነው። ሌሎቹማ የማይረቡ ግብረ ሰዶማውያንና ደደብ በሽተኞች ናቸው። አንድ መኪና ሙሉ ተርብ ቢከተትባቸው እንኳ መንቃት አይችሉም" ብላው፥ ኒኖን እየመራች ትርምስና ውድድር ከማይኖር በት አንድ የክፍሉ ጥግ ወሰደቻው።

ቀጥላም ለዘብ ባለ ማራኪነት ኒኖ ስለ ራሱ እንዲ ያወጋት ጠየቀችው። ከትልቅ ቤተሰብ ነኝ የምትል የጨዋ ዘርነቷ የሚሰማት ሴት ለአንድ የፈረስ ጠባቂዋ ወይም ሹፌርዋ የምታደርገውን አይነት የደግነት ችሮታ ማሳየትዋ እንደሆነ ተሰማው። ይሁን እንጂ፥ የሱንም ጥላቻት የሷንም መናወዝ ተስፋ ማስቆረጥ አልታየ ውም። ስለዚህ ታሪኩን ያወራለት ጀመር። ጆኒና እሱ አብረው ማደጋቸውን፥ አብረው በትናንሽ ክበቦች መዝ ፈናቸውን ነገራት። ሲነግራትም የተማረከች መሰለችው። በንግግሩ ጣልቃ ገባችና፥

"ለመሆኑ፥ ያ ዲቃላ ዎልትዝ ጆኒ ያን ፊልም እንዲሰራ በምን ዘዴ እንደፈቀድለት ታውቃለህ?" ስትል ጠየቀችው።

ኒኖ ቀዝቀዝ አለና እራሱን ነቀነቀ። እሷም እንዲነ ግራት ግፊት አላደረገችም።

አዲሱ ዎልትዝ የሰራው ፊልም በቅድሚያ የሚታ ይበት ወቅት ደረሰ። ዲያና ዳንም በሞቀ እጅዋ እጁን አፍና ይዛ፥ መስኮት ከሌለው ሀምሳ የሚሆኑ ለጥንድ ሰዎች መቀመጫ እንዲያገለግሉ ራቅ ራቅ ብለው የተተ ከሉ መቀመጫዎች ካሉበት ክፍል ኒኖን ይዛው ገባች።

ከምቹ መቀመጫው ጐን የበረዶ ማስቀመጫ፥ ብርጭቆዎች፥ ልዩ ልዩ መጠጦችን የያዙ ጠርሙሶችና ሲጃራዎች የተቀመጠበት ትንሽ ጠረጴዛ ተመለከተ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚያው ጠረጴዛ ላይ ሲጋራ አንስቶ ዲያናን ከጋበዛት በኋላ ለኮሰላት ። ቀጥሎም መጠጥ ቀዳላት ።

ሁለቱም ጸጥ አሉ ። ከጥቂት ደቂቃም በኋላ መብራቱ ጠፋ ። ኂኖ ስለሆሊዉድ የሞራል ውድቀት ሰምቶ ነበር ። ነገር ግን የሲ የቅንዝር ስግብግብነት ለሚያስከትለው ድፍረት ዝግጁ አልነበረም ። መጠጡን እየተጎነጨ ፊልሙን ቢመለከትም ልብ ብሎ እየጣመው አልተመለከተም ። የጉርምስና ህልሙ ጣአት የነበረችው ዲያና ዳን አስተናጋጁ እንድትሆን በመብቃቱ በደስታ ተቅበጠበጠ ። ይሁን እንጂ በሆነ መንገድ ወንድነቱ ተደፍሯል ። የአለም ዝነኛዋ ተዋናይ ዲያና ዳን የኂኖ ነገር በቅቷት ገሸሽ ብታደርገውም እሱ ግን ቀዝቀዝ ብሎ በመዝናናት መጠጧን ሞልቶ ሲጋራዋን ከለኮሰላት በኋላ ፥

"በጣም ጥሩ ፊልም ይመስላል" አለ ። ንግግሩ ምንም እንዳልኮረኮራት ይልቁንም ደርቃ እንደተቀመጠች ተሰማው ። ምናልባት ከንቱ ውዳሴ ጠብቃ ይሆን? ኂኖ በጭለማው ውስጥ ካጋጠመው ካንዱ ጠርሙስ ላይ መጠጥ ብርጭቆው እስኪ ሞላ ቀዳ ። ገደል ትግባ! ምንስ ቢሆን አለሌ አድርጋ ገመተችው እንዴ? ለአፍታ በነዚያ ሁሉ ሴቶች ላይ ቁጣ አደረበት ። ፊልሙን ለተከታዩ ሩብ ሰአት ያህል ሲመለከቱ ሰውነታቸው እንዳይንካካ ከሲ ፈቀቅ ብሎ ተቀመጠ ።

በመጨረሻ ፥ ዝግ ባለ ሜካኔ የተሞላበት ሹክሹክታ ፥

"ንጥጣም ጎርባ አትሁን ! ሳትወደኝ አልቀረህም ። የቤት ያህል አብጠህ ነበር" አለችው ።

ኂኖ መጠጡን ጨለጠና በሚያቅበት ፈጣን መልስ አሰጣጥ ፥

"ለወትሮውማ እንዳልሽው ነበር ። ስሜቴ ሲመጣ ማየት አለብሽ" አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ትንሽ ሳቅ ብላ ፊልሙ እስኪያልቅ ጸጥ አለች ። በመጨረሻም ፊልሙ አልቆ መብራት በራ ። ኒኖ ዙሪ ያውን ተመለከተ ። ምንም እንኳን እሱ ሳይሰማው ቢያ ልፍም ፥ በዚያ ጭለማ ወቅት ፥ በዚያች ክፍል ውስጥ አያሌ እንቅስቃሴ መካሄዱን ተገነዘበ ። በክፍሏ ውስጥ የነበሩት ጐምቱ ተዋንያን ጥቂቶቹ ቀድሞ በጥንቃቄ ተኳኩለውና ተቀብተው የመጡበት መልካቸው አሁንም አልተቀነሰም ። አልቀናቸውም ማለት ነው ። ከፊልም መታያው አዳራሽ ተኮልኩለው ወጡ ። ዲያና ዳንም ኒኖን ጥላው ወደ አንድ የቆየ ዝነኛ ተዋናይ አመራች ። ኒኖ ይህን ተዋናይ በቅርብ ሲመለከት ግብረሰዶማዊ መሆኑን ተገነዘበና እያሰላሰለ መጠጡን ተጐነጨ ።

ጆኒ ፎንቴን መጣና "ታዲያስ ጓዴ ፥ ጥሩ ጊዜ አሳለፍክ?" ሲል ጠየቀው ።

ኒኖ ፈገግ አለና ፥ "እንጃ ፥ የተለየ ነገር ሆነብኝ ፥ እንግዲህ ወደ መንደሬ ስመለስ ዲያና ዳን አገኘችኝ ብዬ መናገር እችላለሁ" አለ ።

ጆኒ ሳቀና ፥ "ቤቷ ጋብዛህ ከሆነ ግን ከዚያም የበለጠ ማለት ትችላለህ ። ለመሆኑ ጋበዘችህ?" ሲል ጠየቀው ።

ኒኖ እራሱን ነቀነቀና ፥ "በፊልሙ በጣም ተማርኬ ነበር" ብሎ ሲመልስለት ፥ ጆኒ ፎንቴን አልሳቀም ።

"ቁም ነገረኛ ሁን እንጂ ፥ እንደሷ የመሰሉ ሴቶች ብዙ ሊያደርጉልህ ይችላሉ ።" አለው ጆኒ ፎንቴን ። ጆኒ ኒኖን ጥንት አገራቸው ሳሉ ኒኖ ከፉንጋ ሴቶች ጋር ሳይቀር ይዳራ እንደነበር ካስታወሰው በኋላ ፥ ይህችን ከመሰለች ጠቃሚ ሴት ጋር ያጋጠመውን እድል ኒኖ በከንቱ ማሳለፉ ያሳዘነው መሆኑን ገለጸለት ።

ኒኖ በሞቅታ መንፈስ ብርጭቆውን አነሳና ጮክ ብሎ ፥ "አዎን ፥ እነሱ ቆንጆ ባይሆኑም የሴት ወግ ነበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራቸው” ሲል መለሰለት ። ይኸን ጊዜ ዲያና ዳን ሰምታ ኖሮ ወደነሱ ዞር አለች ። ኒኖም ብርጭቆውን ወደሷ አቃንቶ በሰላምታ ከፍ አደረገው ።

ጆኒ ፎንቴን ተነፈሰና ፥ “በቃ ፥ አንተ ዋጋ ቢስ ገጠሬ ነህ” አለው ።

“ምንም ቢሆን መለወጥ አልሻም” ሲል ማራኪ ፈገግታውን አሳየው ።

ጆኒ የኒኖን ሁኔታ በውል ተረድቶታል ። ኒኖ እንዳ ስመሰለው ሰክሮ እንዳልሆነም ተገነዘበ ። በጽሞና ባለ በት ወቅት ቢናገረው አጉል ድፍረት የመሰለውን አቋ ሙን ለሆሊውድ አሳዳጊው ለጆኒ ፎንቴን ግልጽ ሊያደ ርግለት ሲል ሰክሮ የተናገረ ማስመሰሉ ነበር ። ጆኒ እጁን ኒኖ ትከሻ ላይ አድርጎ በፍቅር ስሜት ፥

“አንተ ጮሌ ያገር ልጅ ፥ የአመት ኮንትራት ከኔ ጋር ተፈራርመሀል ። የፈለግከውን ማለትና ማድረግ ትች ላለህ ፥ ላስወጣህም አልችልም” አለው ።

“ልታባርረኝ አትችልም?” ሲል የሞቅታ መን ፈስ እየተሰማው በዘዴ ጠየቀው ።

“ፈጽሞ”

“እንግዲያውስ ገደል ግባ!”

ጆኒ ለቅጽበት ንዴትና መገረም ተቀላቅሎበት ሳለ በኒኖ ፊት ላይ ደንታ ቢስ ፈገግታ ተመለከተ ። ይሁን እንጂ ካለፉት ጥቂት አመታት ወዲህ ጆኒ በሳልነት ይታይበታል ። ምናልባትም ኮከብ ተዋናይነቱ እየቀነሰ በመምጣቱ ነገሮችን ይበልጥ ያስተውላል ። በዚያ ወቅት የልጅነት ጓደኛው ኒኖ ለምን ማደግ እንዳልቻለና አሁንም ቢሆን ማናቸውንም የማደግ እድል ሊያበላሽ እንደሚሻ ጆኒ ተረዳው ።

ኒኖ ለድል የሚያበቁትን ጠቃሚ ጉዳዮች ሁሉ ያበላሻቸዋል ። ለሱ የሚደረግለትን በጐ ነገርም በጸጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደመቀበል እንደተሰደበ አድርጎ ይቆጥረዋል ። ለማ ደግ የሚከፈለውን መስዋእት ይሸሻል ።

ጆኒ ኒናን ይዞት ቤቱን ለቀው ወጡ ። ኒኖ በሞ ቅታ ብዛት መራመድ እንኳን አልቻለም ። ጆኒ በለሆ ላስ ፣ "እንደፈለገህ ሁን ፣ ብቻ ዝፈንልኝ" አለው ። "ባንተ አማካይነት ገንዘብ ማፍራት ነው የምፈልገው ። ህይወትህን እኔ ልምራ ብዬ አላስገድድህም ። ማድረግ የምትፈልገውን ሁሉ አድርግ ። ገባህ ፣ ያገር ልጅ ካንተ የምፈልገው እኔ ከእንግዲህ መዝፈን ስለማልችል አንተ ዘፍነህ ገንዘብ እንድናገኝ ነው? ገባህ ፣ የጥንቱ ጓደ?"

ኒኖ ቀጥ አለና ፣ በተገማመደ አንደበት "እዘፍንል ሀለሁ ። ጆኒ አሁን ካንተ የተሻልኩኝ ዘፋኝ ነኝ ። ድሮም ቢሆን ካንተ የተሻልኩ ድምጻዊ ነበርኩ ፣ ታውቃለህ?" በማለት መለሰለት ።

ጆኒ ቆም ብሎ አሰበ ። ድምጹ ጥሩ በነበረበት ወቅት ኒኖ እኩያው አይደለም ። ያኔ በልጅነታቸው አብረው ሲዘፍኑ በነበረበት ወቅትም ቢሆን እኩያው አልነበረም ። ኒኖ ለዚህ ንግግሩ ከጆኒ መልስ ይጠብቅ እንደነበር ጆኒ ያውቃል ። መልስ መስጠቱ አልታየውም ። ስለዚህ እሱም "ገደል ግባ!" ብሎ በመቀለድ ሲሰድበው ሁለቱም ሳቁ ።

ጆኒ ፎንቴን የዶን ኮርሌዎኔን በጥይት መቁሰል በሰማ ጊዜ ስጋቱ ለክርስትና አባቱ ህይወት ብቻ ሳይ ሆን ፣ ሊያወጣ ላቀደው አዲስ ፊልም ማሰሪያ ወጭ የማግኘቱ ተስፋ ምን ያህል እንደተጠበቀ ማወቁ ነበር ። ኒውዮርክ ሄዶ ክርስትና አባቱን ሊጠይቅ ቢፈልግም ፣ ዝነኛ ስሙ ከማፍያ ቤተሰብ ጋር ተመሳጥሯል በሚል እንዳይበከል ሲባል እንዳይሄድ ስለተከለከለ መቆየት ግዴታ ሆነበት ። ከሳምንት በኋላ ግን የፊልሙ ወጪ

t.me/OLDBOOKSPDF

መገኘት አሁንም የተረጋገጠ መሆኑን ፥ ሆኖም በቅደም ተከተል ፥ ማለትም በአንድ ወቅት አንድ ፊልም ብቻ እንዲያወጣ የሚል መልእክት ከቶም ሄገን ደረሰው ።

ጆኒ ፎንቴን ኒኖን አልፎ አልፎ አብሮት ከሚያ መሽ በስተቀር እንዳሻው ከተዋንያን ወጣቶች ጋር እንደልቡ እንዲጨፍር ተወው ። ስለ ዶኑ በጥይት መቁሰል ሲያወሩ ኒኖ ዶኑ ያለው ትዝ አለውና ለጆኒ ነገረው ።

"ታውቃለህ ፥ አንድ ጊዜ የጭነት መኪና ሹፌር ነት ሰለቸኝና ስራ ሰጠኝ ብዬ ጠየቅኩት ። ስራውን አልሰጠኝም ። ምን እንዳለኝ ታውቃለህ? እሱ ለሚመራው የማፊያ ተግባር እንደማልሆን ሲገልጽልኝ ፥ እያን ዳንዱ ሰው የራሱ እጣ እንዳለውና የኔም እጣ በኪነት ሙያ ብቻ መሆኑን ነገረኝ ።"

ጆኒም ይህን ጉዳይ መለስ ብሎ አሰበና ክርስትና አባቱ በጣም ብልህ ሰው መሆኑን ተገነዘበ ። ኒኖ ለድ ብቅ አለም ተግባር ተልእኮ መዋል የሚችል ሰው እን ዳልሆነና በዚህ ስራ ላይ ቢያሰማራው በአጉል ጮሌ ነት እንደሚጠፋ ዶኑ አውቋል ። ለመሆኑ እንዴትስ ኒኖ የኪነት ሰው መሆን እንደሚችል ገመተ? አንድ ቀን ጆኒ ኒኖን ረድቶት ለዚህ ሙያ እንደሚያበቃው ታይ ቶት ይሆን? ይህስ እንዴት ሊገለጥለት ቻለ? ዶኑ ለኒኖ እንዲደረግለት የሚሻውን ጆኒን ሲጠቁመው ጆኒ ክርስ ትና አባቱን ለማስደሰት ሲል የኒኖን እድል እንደሚከፍ ትለት አያጠራጥርም ። ጆኒ ፎንቴን ይህን ሁሉ አሰበና ተነፈሰ ።

ክርስትና አባቱ በጥይት ቆስሏል ። ጀክ ዎልትዝን የመሰለ ሀይለኛ ደመኛ ተጋርጦበት እያለ የአካዳሚ ሽልማቱን ከማግኘት የሚከለክሉት ጋሬጣዎች የሚያ ስወግድለት ዶኑ ብቻ ነበር ። ዛሬማ የዶኑ ቤተሰብ የተወጠረበት ጉዳይ ሌላ ነው ። ጆኒ በኮርሌዎኔ ቤተሰብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ችግር ውስጥ ገብቶ ለመካፈል ቢሻም ቶም ሄገን አይ ሆንም ብሎታል ።

ጆኒ በሚያሰራው አዲስ ፊልም ላይ ተጠምዷል ። በቅርቡ በኩክብ ተዋናይነት የሰራበትን ፊልም ታሪክ የጻፈውን ደራሲ ጣልቃ ገቦች ሳይኖሩ በቀጥታ ለመደራደር ጋብዞታል ። የዚህ ደራሲ ሁለተኛ ጽሁፍ ዘፈን የሌለበት ፣ ከብዙ ሴቶች ጋር የሚያዳራ ብቻ በመሆኑ ጆኒ በአሁኑ ወቅት ላለው ብቃት ተስማሚ ሆኖ አግኝቶታል ። በዚያው ታሪክም ላይ ለኒኖ ተለክቶ የተሰራ የሚመስል ክፍል አለበት ። ስለዚህ ኒኖ ብዙ ዝግጅት ሳያደርግ እራሱን ብቻ በመድረኩ ላይ ማቅረብ የሚችል በት ታሪክ ነው ።

ጆኒ በትጋት ሰራ ። ከጠበቀው በላይ የፊልም ዝግጅት ብቃት እንዳለው ማወቅ ቻለ ። ሌሎች ድርጅቶች በኮሚኒስትነት ስለሚጠረጠር ያገለሉት ብቁ የሆነ አዘጋጅ ማግኘት በመቻሉ ይህንኑ ሰው ቀጥሮ የሚገባውን ከፍሎት ችሎታውን እንዲያሳይ አደረገው ።

በሰራተኞች በኩል ችግር እንዳይገጥመው ሀምሳ ሺህ ብር ያህል ወጭ መድቦ የሰራተኛውን ማህበር መያዝ እንዳለበት ምክትል አዘጋጁ ጆኒን በመከረው ጊዜ ፣ ምናልባት ሊሸፍጥ እንዳይሆን በማለት የማህበሩን መሪ ወደሱ እንዲልከው ነገረው ።

ቢሊ ጐፍ የተባለውን የማህበር መሪ ባነጋገረው ወቅት ካሁን ቀደም በሰራተኞቹ በኩል የሚፈጠር ችግር እንደማይኖር የሱ ወዳጅ ያረጋገጠለት መሆኑን አነሳለት ። ቢሊ ጐፍ ግን የጆኒ ወዳጅ የሆነው ዶን ዛሬ ቁስለኛ ሆኖ ጉልበቱም የላላ ስለሆነ ድምጹ ወደዚያ አካባቢ ሊደርስ እንደማይችል ገለጸለት ።

"እንግዲያስ ከሁለት ቀናት በኋላ አነጋግረኝ" አለው ጆኒ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"መልካም ፡ ግን ኒውዮርክ ብትደውልም ምንም ጠቃሚ ውጤት እንደማታገኝ ካሁኑ ልንገርህ ፡" አለው ቢለ ጐፍ ።

ኒውዮርክ መደወል ግን በእርግጥ ውጤት አስገኘ ። ጆኒ ምንም ገንዘብ ለጐፍ እንዳይከፍል ሄገን ሲያስጠነቅቀው ፡ "ለዚያ ዲቃላ አንዲት ሳንቲም እንኳን ብትከፍል ክርስትና አባትህ ይቀየምሀል ። ይህን ካደረግህ በአሁኑ ጊዜ ሊያጣው የማይፈልገውን ክብሩን ማሳጣትነው" አለው ።

"ዶኑን ላነጋግረው እችላለሁ ? ወይም አንተ ታነጋግርልኛለህ ? ይኸ ችግር እልባት አግኝቶ ፊልሙን በቶሎ መጀመር አለብኝ ።"

ሄገንም ዶኑ በጣም ስለታመመ ከማንም ጋር እንደማይነጋገር ፡ ነገር ግን ሶኒ ኮርሌዎኔ እንደሚያነጋግርለት ገለጸለት ። ያም ሆነ ይህ ፡ ለጐፍ ሳንቲም እንዳይከፍል ከአስጠነቀቀው በኋላ ለውጥ ቢኖር ወዲያውኑ እንደሚያስታውቀው ነገረው ።

ጆኒ በሽቆ ስልኩን ዘጋው ። የሰራተኛ ማህበር ችግር በቆሰቆስ ብዙ ወጭ እንደሚያስከትልና ስራውን እንደሚያጓትት ጆኒ ያውቃል ። ማንም ሳይሰማ ሀምሳ ሺህ ብሩን ለጐፍ ሊወረውርለት አስቦ ነበር ። ነገር ግን ጥቂት ቀናት ጠብቄ ማየት አለብኝ ብሎ ወሰነ ።

በመጠበቁም ሀምሳ ሺህ ብር አዳነ ። ከሁለት ሌሊት በኋላ ጐፍ በቤቱ ውስጥ በጥይት ተገድሎ ተገኘ ። ከዚህ በኋላ የሰራተኛ ማህበር ችግር ወሬውም አልተነሳ ። ጆኒ በገደላው ትንሽ ተደናገጠ ። የዶኑ በትር በአጠገቡ ካለ ሰው ላይ ሲያርፍ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር ።

ጆኒ የፊልሙ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ ፡ ተዋንያን ተመድበው ፡ የዝግጅቱን ዝርዝር በማውጣት ተጠምዶ ሳለ የድምጹ መሻከር ትዝም አላለው ። ስሙ ለአመቱ ተሸ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላሚዎች ከቀረቡት ውስጥ ቢታከልም ፥ በበአሉም አለት እንዲዘፍን ባለመጋበዙ ቅር አለው ። በክርስትና አባቱ መቁሰል ምክንያት የማሸነፍ እድሉ መመንመኑን አወቀ ። ቢሆንም ፥ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙም ደንታ አልነበረውም ። ስሙ ከተወዳዳሪዎች ዝርዝር ውስጥ መጣቱም አንድ ነገር ነው ።

ከኒኖ ጋር ያስቀረጹት የጣልያንኛ ዘፈኖች ሽክላ በቅርቡ ካስቀረጻቸው ሽክላዎች የተሻለ ዋጋ እያወጣለት ቢሆንም ፥ ድሉ ከሱ ይልቅ የኒኖ መሆኑ ተሰማው ። ከእን ግዲህ ዘፋኝነቱ ማክተሙን ተረዳ ።

በሳምንት አንድ ቀን ከቀድሞ ሚስቱ ከጂኒና ከልጆቹ ጋር እራት ለመብላት የገባውን ቃል ምንም ስራ ቢበዛበት አልጣሰውም ። ከጂኒ ጋር ግን በስጋ ተገናኝቶ አያውቅም ። ሁለተኛዋ ሚስቱም ሜክሲኮ ሄዳ በዚያ አገር ህግ ፈትታዋለች ። ወደ ወንደላጤነቱ ተመልሷል ። የሚገርመው ፥ እንደወትሮው በቀላሉ የሚ ያገኛቸውን የፊልም ከዋክብት ለፈቃደ ስጋ አልፈለጋ ቸውም ። ከመጠን ላይ ጨዋ ሆኗል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማናቸውም ወጣት ተዋንያን እንዲያዋርዱት መንገድ አልሰጣቸውም ። ለዚህም የረዳው በስራ መጠመዱ ነበር ። አብዛኛውን ጊዜ ከስራ በኋላ ማታ ብቻውን ቤቱ ሄዶ የዱሮ ሽክላዎቹን እያዳመጠ በማንሮራነር መጠጡን ይጎነጫል ። አሁን ሲገነዘብ ለካስ የዘፈን ችሎታ ከሚታመን በላይ ኖሮታል ። እንዲህ የተካንኩ ነኝ ብሎ አስቦም አያውቅ ነበር ። ዛሬ ልብ ሲለው ለካስ መጠጥ ፥ ሲጋራና ሴት ማብዛት ነበር ድምጹን ያበላሸው ።

አልፎ አልፎ ኒኖ ጆኒ ቤት ይመጣና እየጠጡ የድሮ ሙዚቃውን ሲሰሙ ጆኒ ብሶት ሲሰማው ኒኖ ያጽናናዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻም አዲሱ ፊልሙ መነሳት ሊጀምር አንድ ሳምንት ሲቀረው የአካዳሚ ሽልማት ምሽት መጣ ። ጆኒ ኒኖን አብሮት እንዲሄድ ጋበዘው ። ኒኖ እምቢ አለ ።

"ጓደ ፥ ካሁን ቀደም ውለታ ጠይቂህ አላውቅም ። ዛሬ ለኔ ስትል አብረኸኝ አምሽ ። በውድድሩ ሳላሸንፍ ብቀር የሚያዝንልኝ ሰው አንተ ብቻ ነህ ።"

ለቅጽበት ኒኖ ደንገጥ አለና ፥ "በሚገባ ፥ አብሮ አደግ ጓዴ ፥ እመጣለሁ ። ደሞ ካላሸነፍክም እርሳውና ጣጥ ብለህ ስከር ። እኔ እጠብቅሀለሁ ። የዛሬን ላንተ ስል ሳልጠጣ አመሻለሁ ። ምን ትላለህ የልጅነት ጓዴ?"

"ጓደኝነት ይሉሀል ይኸ ነው!"

የአካዳሚ ሽልማቱ ወቅት ደረሰ ። ኒኖም በገባው ቃል መሰረት ሳይጠጣ ጆኒ ቤት መጣና አብረው ወደ ዚያው አመሩ ። ጆኒ የድሮ ሚስቶቹን ወይም ቁባቶቹን ባለመጋበዙ ኒኖ ደንቀው ። በተለይ የመጀመሪያ ሚስቱ ጄኒ ለሱ እንደምትቆረቆር ስለሚያውቅ አለመጠራቷ ገርሞታል ።

ኒኖ ሳይጠጣ ማምሸቱ ረዥም የሲቃ ምሽት ሆኖ በታል ። በተለይ የስነስርአቱ መራዘም ሰልችት ብሎ ታል ። ከወንድ ተዋንያን የአሸናፊው ስም ሲጠራ ፥ "ጆኒ ፎንቴን" ሲባል ኒኖ ዘለለና እያጨበጨበ ጮቤ ረገጠ ። ጆኒም እጁን ዘረጋና ጨበጠው ። ጆኒ ከኒኖ የተሻለ ተቆርቋሪ እንደሌለው በተረዳ ጊዜ አዘነለት ።

ከዚያ በኋላ የተፈጸመው ሁሉ ለኒኖ ሙሉ በሙሉ የቅዠት ያህል ሆነበት ። የጃክ ዎልትዝ ፊልም አበይት ሽልማቶቹን ሁሉ ተቀዳጀ ። በፊልም ስራው የተካ ፈሉት ሁሉ በጋዜጠኞች ተከበቡ ። ኒኖ ምንም መጠጥ ሳይቀምስ ጆኒን ይጠብቀው ነበር ። ነገር ግን የግብጣው

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሳታፊ ሴቶች ጅኒ ፎንቴንን መዲሀና መዲያ ሲጐትቱት በመጨረሻ ሰከረ ።

ከሴቶች በኩል በኮከብ ተዋናይነት የተመረጠች ውንም ሴት እንዲሁ ሲጎትቷት በዘዴ አስተናገደቻቸው ። ኒኖ ብቻ ከጐታቾች መሀከል ሳይታከል ንቋት ቀረ ።

በመጨረሻም አንድ ሰው አንድ ሀሳብ አመጣ ። በመድረክ ላይ ሁለቱ ሲዳሩ ለተመልካች እንዲታዩ የሚል ሀሳብ ነበር ። መዲያው ሴቷ ኮከብ ተዋናይ ልብሷ ከመቅጽበት ወለቀ ። ከዚያም ሴቶቹ የጅኒ ፎንቴንን ልብስ ማውለቅ ጀመሩ ። በዚያ አዳራሽ ውስጥ ያል ጠጣ ሰው ኒኖ ብቻ ነበርና ይህን ሁኔታ አልተቀበ ለውም ። ግማሽ እርቃኑን የሆነውን ጅኒን ለቀም አድ ርጎ ጐሸክሞ ይዞት ወጣና መኪናው ውስጥ አስገ ባው ። ኒኖ በመኪና ሲወስደው አንድ ነገር አሰላሰለ ። 'ድል' ማለት ይህ ከሆነ ኒኖ ድልን አይፈልገውም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ ሶስት

ምእራፍ አስራ አራት

ቁመቱ አጭር፥ መልኩ ድፍን ቀይ የሆነው ሎጋው ዶን በአስራ ሁለት አመቱ ሙሉ ሰው ነበር ። በሲሲሊ ከምትገኝ ኮርሌዎኔ ከተባለች መንደር ሲወለድ ስሙ ቪቶ አንዶሊኒ ነበር ። ነገር ግን አባቱን የገደሉበት ደመኞች ይህ ወጣት ይበቀለናል የሚል ፍራቻ ስላደረባቸው እሱንም ለማጥፋት አሳደዱት ። እናቱም አሜሪካ ከሚኖሩ ወዳጆችዋ ዘንድ ሄዶ ነፍሱን እንዲያድን አሸሸችው ። አሜሪካ ከገባ በኋላ ከተወለደባት ከተማ ጋር ያለውን የተቆራኘ ታሪክ ለማስታወስ ስሙን ወደ ኮርሌዎኔ ቀየረ ።

በምእተ አመቱ መግቢያ ላይ ማፊያ በሲሲሊ ውስጥ ሮም ካለው መንግስት ይበልጥ ሀይለኛ የሆነ ሁለተኛ መንግስት ነበር ። የቪቶ ኮርሌዎኔ አባት ካንድ ያካባቢው አለቃ ጋር የከረረ ጠብ ነበረው ። ሰውዬው የማፊያው ሹም ላይ ከሰሰው ። የቪቶ አባት እጁን አልሰጥም ብሎ ከሹሙ ጋር በአደባባይ ባደረጉት ግብግብ የማፊያውን ሹም ገደለው ።

ከሳምንት በኋላም እራሱ ሉፓራ በተባለ ጠመንጃ ተገድሎ ተገኘ ። ከወር በኋላ ፥ ደመኞቹ ትንሹ ቪቶ እየደረሰ በመሆኑ እንዳይበቀላቸው ስለፈሩት ሊፈልጉት መጡ ። የአስራ ሁለት አመቱ ቪቶ ዘመድ ቤት ተደብቆ አሳለፋቸውና ወደ አሜሪካ እንዲያመልጥ ተደረገ ። አሜሪካ ከመጣ በኋላ አባንዳንዶ በተባለ ቤተሰብ ዘንድ አርፎ በምግብ ሽቀጥ መሸጫ ቤታቸው ሰራተኛ ሆነ ። በአስራ ስምንት አመቱ ከሲሲሊ የመጣች ኢጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልያዊት አግብቶ በሁለተኛው አመት ትልቁን ልጁን ሶኒ ኮርሌዎኔን ወለደ ።

ቪቶ በሚናበርት ሰፈር ፋኑቺ የተባለ ዘረፋ እና በማስፈራራት በሚነጥቀው ገንዘብ የሚንደላቀቅ የማፊያ ብቃይ አለ ። አብዛኛዎቹ የሰፈሩ ሰዎች እንደፋኑቺ አምባ ጓሮች ባለመሆናቸው የፋኑቺ ጥቃት የወንድ ልጅ ተገን በሌላቸው አረጋውያን ላይ ብቻ ነበር ። ጥቂት ባለ ሱቆች ምጽታቸውን እንዳያናጋባቸው አነስተኛ ቋሚ ክፍያ ያደርጉለታል ። የዚህ ሰው የዘረፋ ጥም በደካሞችና በሰላም ፈላጊዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ፣ የሱ ቢጤ ቀማኞችና ህገወጥ ነጋዴዎች ላይም ጭምር ሆነ ። እስ ይዛችኋለሁ እያለ በማስፈራራት የጥቃታቸው ኢላማይ ሲሆን ኖሯል ። የአባንዳንዶ ግሮሰሪም ቢሆን ጥቂት ገንዘብ ይሰጠዋል ። ወጣቱ አባንዳንዶ አባቱን ምንም እንዳይሰጥ ቢነግረውም ፣ ሰላም ያገኘ መስሎት መስ ጠቱን አላቋረጠም ። ይህን ሁሉ ሁኔታ ወጣቱ ቪቶ ኮር ሌዎኔ ተመልክቶ በለዘብታ አልፎታል ።

አንድ ቀን ፋኑቺን ሶስት ጐረምሶች እንዲሞት ሳይሆን እንዲቀጣ ከአንዱ ጀርው እስከ ሌላው ጀርው እስኪደርስ አንገቱን በጩቤ ሲሸረክቱት እና የደም ዱካ ላለመተው ሲል የሚፈሰውን ደሙን በባርኔጣው እየተ ቀበለ እግሬ አውጭኝ ብሎ በፍርሀት ሲፈረጥጥ ወጣቱ ቪቶ ኮርሌዎኔ በትዝብት አይቶታል ። ይሁን እንጂ ፋኑቺ እነዚህን ሰዎች ሳይበቀል አልተዋቸውም ። በጩቤ የሸረከተው ሞቶ ሲገኝ ፣ ሌሎቹን ሁለት ወጣቶች እንዳ ይበቀላቸው ቤተሰቦቻቸው ካሳ ክሰውታል ። ፋኑቺ ከዚያ በኋላ ገቢው ከፍ በማለቱ ከባለቁማር ቤቶች ጋርም ሽርክና ገባ ።

በአንደኛው የአለም ጦርነት ጊዜ ፣ ከውጭ የሚገባ የወይራ ዘይት ውድ በሆነበት ወቅት ፣ ፋኑቺ ለነአባን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳንኤ ኢጣልያን አገር የመጀራ ዘይት በያይነቱ ፥ ያሳማ ሲጋ እና አይብ እያስገባላቸው የሱቁ ከፊል ባለቤት ሆነ ። በዚህ የስራ ግንኙነት በመጠቀም ቪቶን ከስራ አስወጥቶ ዘመዱን አስገባበት ። በዚህ ወቅት ሁለተኛ ልጁ ፊሬዲኮ ተወለደ ፥ ቪቶ አራት እራሱን መመገብ ነበረበት ። ቪቶ ጓደኛውን ጁንኮን አባቱ ለሰራው በደል ወቀሰው ። ጁንኮ አፈረና የጓደኛው ቤተሰብ እንዳይራብ ከሱቃቸው የምግብ ሸቀጥ እየሰረቀ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት ። ቪቶ ግን ልጁ አባቱ ሲሰርቅ አይገባውም በማለት እርዳታውን አልቀበልም አለ ።

ቪቶ ስራ ባሳጣው ፍኑኝ ላይ ታላቅ ቂም አደረበት ። በዚያ ስራ እንደ ልብ በማይገኝበት ወቅት የስራ ሀላፊዎች የነበሩ አይሪሾችና አሜሪካኖች ሰራተኞችን አስለያፊ [illegible] ሲያመርዱባቸው ፥ ቪቶ ልክ እንሚዝኛ ያልተባው ይመስል በዝምታ እየቻለ ፥ በወር ውስጥ [illegible] ጥቂት ቀናት በባቡር ሀዲድ ላይ ተሰማርቶ ሲሰራ ቆየ ።

አንድ ቀን ፥ ቪቶ ከቤተሰቡ ጋር እራቱን ሲበላ መስኩቱ ተንኳኳ ። መጋረጃውን ከፊት አድርጎ ሲመለከት ፒተር ክሊሜንዛ የተባለ ፖሊስ አባደውት ሳይሆን አይቀርም ።

አንድ በነጭ ጨርቅ የተሸፈነ ጥቅል አቀበለውና ፥ "ስማ ያገር ልጅ ፥ ይህን ነገር አስቀምጥልኝ ። ስጠይቅህ ትሰጠኛለህ ። ቶሎ በል ተቀበለኝ!" አለው ። ቪቶ የሰውዬውን በችግር ላይ መሆን ከንግግሩ ስለተረዳ ሳያንገራግር ሸክሙን ተቀበለው ። በኋላ ጨርቁን ፈትቶ የተጠቀለለውን ሲመለከት አምስት ዘይት የተቀቡ ሽጉጦች ናቸው ። እንዳሉ ጠቅልሎ ከቁምሳጥኑ አስቀመጠ ። ባለቤቱ እስኪጠይቀውም በሚስጥር አቆየለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ክሌሜንዛ ከሁለት ቀናት በኋላ መጣና ፥ "አንተ ዘንድ አስቀምጬው የነበረው እቃ አለ?" ሲል ጠየቀው ። ቪቶ ብዙ ሰለማይናገር በአምንታ እራሱን ነቀነቀ ። ክሌሜንዛ በቪቶ ቤት የወይን ጠጅ ተጋበዘ ። በአደራ አስቀምጦት የነበረውን ጥቅል ተረከበ ።

"የተጠቀለለው እቃ ምን እንደሆነ አየኸው?" ሲል ክሌሜንዛ ጠየቀው ።

ቪቶ በአሉታ እራሱን እየነቀነቀ ፥ "የማይመለከተኝን ነገር የማየት ፍላጐት የለኝም" አለው ።

ሁለቱም ምሽቱን በመግባባት ፥ ክሌሜንዛ በማውራት ፥ ቪቶም በማዳመጥ አሳለፉት ። ከዚያ ወዲህ ወዳጅ ብጤ ሆኑ ።

ከጥቂት ቀን በኋላ ክሌሜንዛ የቪቶን ሚስት ቆንጅዬ የወለል ምንጣፍ ትፈልግ እንደሆነ ጠየቃት ። ቪቶን አስከትሎ ሄዶ ቤቱን በቁልፍ ከከፈተ በኋላ ምንጣፉን ከወለሉ ላይ ሲጠቀልሉ የቤቱ ደወል ጮኸ ። ክሌሜንዛ ምንጣፉን ትቶ ወደ መስኮቱ ተጠጋ ። መጋረጃውን ገለጥ አድርጐ ሲመለከት ፥ ፖሊስ መሆኑን ስላየ ሽጉጡን መዘዘ ። ይኸን ጊዜ ነበር ቪቶ ኮርሌዎኔ ስርቆት ላይ መሆናቸውን የተገነዘበው ። ደግነቱ ፖሊሱ የበሩን ደወል ደጋግሞ ካሰማ በኋላ መልስ ሲያጣ ጥሎ ሄደ ። ሰፊውን ምንጣፍ ሰርቀው ካመጡ በኋላ ክሌሜንዛ በቪቶ ክፍሎች ልክ አስተካክሎ ቆረጠው ።

ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካ የነቪቶ ህይወት መሻሻል አልቻለም ። በስርቆት ያመጡትን ውብ ምንጣፍ አይበሉት ነገር ፥ ቤተሰቡ ተራበ ። ቪቶ አልፎ አልፎ ከጓደኛው ከጄንኮ ለቤተሰቡ የሚሆን ምግብ ይቀበል ገባ ።

ባመጨረሻ አንድ ቀን ለቪቶ አድናቆት የነበራቸው ክሌሜንዛና ቴሰዮ ፥ የተባለ ሌላ የሰፈሩ ጉልበተኛ ጐሪምሳ ቪቶን አነጋገሩት ። ሁለቱን ሰዎች ባቀፈ የቀማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞች ቡድን ቪቶ አባል ሆኖ የሀር ቀሚሶችን ከፋብሪካ ወደ ሱቆች የሚያጓጉዙ የጭነት መኪናዎችን አብረው እንዲዘርፉ ሀሳብ አቀረቡለት ። ይህ የዘረፋ ተግባር የሚ ያስከትለው አደጋ አልነበረም ። የመኪናዎቹ ሹፌሮች አደጋ እንዲወድቅባቸው ስለማይሹ መሳሪያ አሳይተው አቁም ሲሉዋቸው ከመኪናው ዘለው ይወጣሉ ። ከዚያ በኋላ ዘራፊዎቹ መኪናውን ወደፈለጉበት ይነዱና ጭነ ቱን ከአንድ ወዳጅ ሱቅ አራግፈው በጅምላም ሆነ በችርቻሮ በርካሽ እየሸጡ ያጣሩታል ። ቲስዮና ክሌሜ ንዛ ቪቶን ሊመለምሉት የፈለጉት ቀድሞ በአባንዳንዶ ግሮሰሪ በሹፌርነት ይሰራ እንደነበር ስላወቁ ለሚዘር ፉት መኪና ነጂ እንዲሆንላቸው ነው ። ይህን ሀሳብ ባቀረቡለት ጊዜ ካንድ ጭነት ዘረፋ ቢያንስ አንድ ሺህ ብር እንደሚያገኝ በማግባባት ገለጹለት ።

ቪቶ ቢቀርበት የተሻለ ቢመስለውም ፣ ከነበረው ችግር አንጻር ይህን ግብዣ እምቢ ማለት አልፈለገም ። በዘረፋው ላይ አብሯቸው ከተሰማራ በኋላ አሰራራቸው ዝርክርክና ችኮላ የነበረበት ሆኖ በስርአትና በእቅድ አለመካሄዱን አስተዋለ ። በሌላ በኩል ግን እነዚህ ሰዎች በዘረፋ በሚሰማሩበት ወቅት መሳሪያቸውን ሲመዙ በስሜት ተውጠው አደጋ በሹፌሩ ላይ አለመ ጣላቸው ፣ ይልቁንም ከሹፌሩ ጋር እየተቃለዱና ካላደና ቀፋቸው ለሚስቱ ጥቂት ቀሚሶች እንደሚልኩለት ተዝናንተው ማውራታቸው አድናቆት አሳድሮበታል ።

ቪቶ የዘረፋ ድርሻውን እያዞረ በችርቻሮ መሸጥ ስላላስደሰተው በጥቅል ሽጦ ሰባት መቶ ብር ብቻ ያግኝ እንጂ ፣ በዚያ ወቅት ይህ ገንዘብ ብዙ ነበር ።

በተከታዩ ቀን ፋኑቺ አምባገረኝነቱ ያስከተለበትን የጉ ሮሮ ዙርያ ጠባሳ እያሳየ ቪቶን ባቡር መንገድ አገኘውና ፣ እሱና ጓደኞቹ ስላካሄዱት ዘረፋ መስማቱን ገለጸለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመሆኑ በኔ ሰፈር ይህን የመሰለ ዘረፋ ስታካሂዱ እኔን የናቃችሁ አይመስላችሁም? የኔንም ጉረሮ አርጥቡት እንጂ" አለው ።

ቪቶ ወትሮውንም ብዙ ስለማይናገር ምንም ከፋ አልመለሰለትም ። ፋኑቺም የወርቅ ጥርሱን ብልጭ አደረገና የታጠቀውን ሽጉጥ ቪቶ ተመልከቶ እንዲፈራ ሲል የኮቱን ቁልፍ ፈታው ።

"አምስት መቶ ብር ስጡኝና ላሳያችሁኝ ንቀት ይቅርታ አደርጋለሁ ። ወትሮም ቢሆን ወጣቶች እኔን ለመሰለ ትልቅ ሰው የሚገባውን ክብር ሟስጠትን አያጤኑትም ።"

ቪቶ እንደማንኛውም ወጣት ግንፍል በመሆን ፋንታ ቀዝቀዝ ብሎ ፊገግታ አሳየው ። ይህ ሁኔታ ያጠራጠረው ፋኑቺ ከመሰናበቱ በፊት ፣

"እምቢ ካላችሁ ፖሊስ ይጐበኛችሁና ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁም ለውርደትና ለድህነት ይጋለጣሉ" አለው ። "አሁንም ቢሆን የዘረፋችሁት ንብረት በርከት ያለ መሆኑን ካረጋገጥኩ ጭማሪ ገንዘብ መጠየቄ አይቀርም ። እነስተኛ ከሆነም ከሶስት መቶ ብር ያነሰ አልጠይቃችሁም ። ስለዚህ ልታታልሉኝ ባትሞክሩ ይሻላችኋል ።"

ቪቶ በጸጥታ ካዳመጠው በኋላ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ትህትና በተሞላበት አንደበት ፣

"ድርሻዬ ጓደኞቼ ዘንድ ነው ። ላነጋግራቸው" ሲል በጽሞና መለሰላት ።

ፋኑቺ ዘና ብሎ ፣

"ጓደኞችህም ጉረሮዬን እንዲያረጥቡ እንደምሻ ንገራቸው ። ከለሜንዛና እኔ እንተዋወቃለን ። ከአንተ ይበልጥ ልምድ ስላለው የሚሰጥህን ምክር ስማው ።"

"እርግጥ ይህን የመሰለው ነገር ለኔ አዲስ ነው ። ስለ ምክርህ አመሰግናለሁ ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

ቪቶ ባሳየው ትህትና ፋኑቺ ተማረከና አደነቀው። እንዲያውም ወደፊት ዘረፋ ሲያቅዱ ምክር እንዲጠይቁት አስገንዝቦ ተሰናበተው።

ቪቶ ለህይወቱና ለንጹኑ ሳይሳሳ በዘረፋ ያገኘውን ብር ለማንም ሊሰጥ አይሻም። የፋኑቺ ጥያቄም አምቆ ይያዘው እንጂ ጥላቻና ቁጣ አሳድሮበታል። ነገር ግን የማይረሳው ትውስታ አለው። አባቱ ትእግስትና ዘዴ አልባ በመሆኑ ነው ከማፊያዎች ጋር ፊት ለፊት ተጋጭቶ ለመሞት የበቃው። ስለዚህ ይህን ታሪክ በራሱ ላይ ሊደግም አይሻም። ክሌሜንዛም ቢሆን ከዘረፈው ሀብት ላይ ሳንቲም ከሚሰጥ ሞቱን ይመርጣል። ለቪቶ ቤት ምንጣፍ ለመስረቅ በወጡበት እለት ፖሊስ በቤቱ አጠገብ ሲያልፍ አይቶ ምናልባት ድንገት ቢገባ ሊገድለው ክሌሜንዛ እንደተዘጋጀ ቪቶ አስታወሰ። ሎጋው ቴስዮም ቢሆን ድብን እንደሚያደርግ መርዘኛ እባብ አደገኛ ነው።

በዚያን እለት ምሽት ሶስቱ ጓደኞሞች ክሌሜንዛ ቤት አብረው ሳሉ ቪቶ ሌላ ትምህርት አገኘ። ክሌሜንዛ ከተራገመ፥ ቴስዮ ከተቆጣ በኋላ፥ ወደቁምነገሩ መለስ ብለው ሁለት ሁለት መቶ ብር ይቀበላቸው እንደሆነ መመካከር ጀመሩ። ነገር ግን ፋኑቺ ልብሱን ከሸጡበት ስፍራ ጠይቆ ያገኙትን ገንዘብ መጠን ሳይረዳ ስለማ ይቀር፥ ከሶስት መቶ ብር ቤሳ እንደማይቀንስ ክሌሜንዛ ገለጸላቸው።

ቪቶ እነሱ ሶስቱ በጉልበትም ሆነ በትጥቅ ስለሚ በልጡት ለዚህ ሰው ገንዘብ መስጠቱን አላመነበትም። ክሌሜንዛ ግን ሁኔታውን እንዲህ ሲል አስረድቶታል፥

"ፋኑቺ አረመኔ የሆኑ ወዳጆች አሉት። ከፖሊስ ጋር ግንኙነት አለው። ሚስጥራችሁን ንገሩኝ የሚለውም ለፖሊስ እኛን ጠቁሞ እሱ ባለ ውለታ ሆኖ ምስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋና ሊቀበል ነው። በዚህ ላይ፥ ጋዜጦች ብዙ ጊዜ ያተኩ
በት ዝነኛ የዘረፋና የወንጀል መሪ ማራንዛላ፥ ፋኑቺ
በዚህ ሰፊር ልዩ ልዩ ተግባር እንዲያከናውን ሊቼንሳ
ሰጥቶታል።"

ክሌሜንዛ እራሱ የጠመቀውን ወይን ጠጅ አቅር
ቦላቸው ቪቶ እየተጐነጨ ስለፋኑቺ ማውጠንጠን ጀመረ።
በተለይም የሱ ቢጤ ወሮበሎች አንድ ቀን ፋኑቺን
በጩቤ በወጉት እለት ይፈስ የነበረውን ደሙን በባር
ኔጣው እየተቀበለ እግሬ አውጪኝ ብሎ የፈረጠጠው
ትዝ አለው። በጩቤ የወጋው በበቀል ሲገደል ሌሎቹን
ሁለቱን ግን በጉማ መታረቁንም ቪቶ አስታወሰ። ይህ
ሰው ከፖሊስ ጋር የረባ ግንኙነት ያለው አያስመስለ
ውም። የማፊያ ወንበዴ ባህሪም የለውም። የማፊያ ወን
በዴ ቢሆን ኖሮ ሰዎቹን በደም ይበቀል ነበር። አንደኛ
ውን ጠላቱን ባጋጣሚ ቢገድለውም ሌሎቹ ስለተጠነ
ቀቁ ሊገድላቸው እንደማይችል ተገንዝቦ ጉማ በልቷ
ቸዋል። ባለሱቆችንም እያስፈራራ ክፍያ የሚቀበላቸው
ባለው የጭካኔ ቆራጥነት ብቻ ነው። ምንም አላቀምስ
ብሎት የሚኖር ባለቁማር ቤት እንዳለም ቪቶ ያውቃል።

ስለዚህ ፋኑቺ ምንም የረባ ግንኙነት የሌለው፥
ባጋጣሚ ከሌሎች ጋር ሲመሳጠርም በጊዜያዊ ጥቅም
ላይ ብቻ የተመሰረተ እንጂ ከዚያ ውጭ ያልሆነ ብቸኛ
ግለሰብ መሆኑን አመነ። ቪቶም ህይወቱን ፈር ሊያስ
ይዛት ቆረጠ። በቪቶ ግምት ሰው አንድ እጣ ነች ያለ
ችው። በዚያን ምሽት ቪቶ ለፋኑቺ እጅ መንሻውን
ሰጥቶ ወደተባረረበት የግሮሰሪ ጸሀፊነት ስራ ተመልሶ
ከጊዜ በኋላ የራሱ ሱቅ ባለቤት ይሆን ይሆናል። ነገር
ግን እጣው ዶን መሆን ነበርና ፋኑቺ የመንገዱ መጥረ
ጊያ ሊሆን ቀረበ።

የወይን ጠጃቸውን ጠጥተው ሲያበቁም ቪቶ በጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንቃቄ ፥ "ከፈለጋችሁ እያንዳንዳችሁ ሁለት ሁለት መቶ ብር ስጡኝና እኔ ልስጠው ። እንደሚቀበለኝ ላረጋግጥ ላችሁ ። ከዚያ በኋላ ይህን ጉዳይ ሁላችሁን በሚያረካ መንገድ እፈጽመዋለሁ" አላቸው ።

ክሌሜንዛ ባንድ ጊዜ ጥርጣሬ ስላደረበት ቪቶ ፥ "እኔ ፈጽሞ ወዳጆቼን አልዋሽም" አለው ፥ "እራስህ ነገ ፋኑቺን አነጋግረው ። ገንዘቡንም ሲጠይቅህ አትስጠው ። ጠብም አታንሳ ። ገንዘቡን በኔ እጅ እንደምትልክለት ንገረው ። ገንዘቡን እንደሚያገኝ አረጋግጥለት ። ቀንስ አትቀንስ በማለት ክርክር ውስጥም አትግባ ። በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ አነጋግረዋለሁ ። አደገኛ ነቱ እናንተ እንዳወራችሁት ከሆነ እሱን ማስቆጣት ጠቃሚ አይደለም ።"

ነገሩ በዚህ ቆመ ። በነገታው ክሌሜንዛ እንደተባለው ፋኑቺን ካነጋገረው በኋላ ፥ ሁለት መቶ ብሩን ይዞ ለት ቪቶ ቤት መጥቶ ሰጠውና ፥

"ፋኑቺ ከሶስት መቶ ብር በታች እንደማይቀበል ነገረኝ ። እንዴት አድርገህ ያነሰ ገንዘብ ልትሰጠው ትችላለህ?" ሲል የጮሪጥ እያየ ጠየቀው ።

"ይህ አንተን የሚያገባህ ጉዳይ አይደለም ። ይልቅ ውለታ የሰራሁልህ መሆኑን አስታውስ ።

ቴስዮም ዘግይቶ ከመጣ በኋላ ቪቶ ከፋኑቺ ጋር በሚያደርገው ድርድር ጉንቃቄ እንዲያደርግ መከረው ። እንዲያውም ቪቶ "ግድ የለም" ስላለው ተወው እንጂ ፥ ለምስክርነት እሱ ባለበት ገንዘብ እንዲሰጠው ጠይቆት ነበር ። በድርድሩ ላይ እንደነሱ ፍላጐት አምጡ ያላቸውን ለማስቀነስ ከቶውንም እንደማይችል ቴስዮ በተናገረው ወቅት ቪቶ ፥ "ሀሳብ ለሀሳብ እንድንግባባ አደርጋለሁ ፥" አለው ። ይህች አባባል ወደ ፊት ቪቶ የሚታወቅባት ልዩ ማስጠንቀቂያ ሆነች ። ቪቶ ዶን ከሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላም ከጠላቶቹ ጋር የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት "ሀሳብ ለሀሳብ እንግባባ" ሲላቸው ካልተግባቡት ፥ ከዚያ በኋላ ያ ጉዳይ በደም መፍሰስ ብቻ የማፈታ መሆኑን የምታስጠነቅቅ አባባል ሆነች ።

የዚያን እለት ማታ እራት ከተበላ በኋላ ሚስቱ ልጆቿን ፥ ሶኒንና ፍሬድን ፥ ይዛ እንድትወጣ ፥ እንዲያውም እሱ ምልክት እስከሚሰጣት ድረስ እንዳይመለሱ አስጠነቀቃት ። ከፉኑቺ ጋር የሚፈጽመው ጉዳይ ስላለ አካባቢውን መጠበቅ አለባት ። ቪቶ ፍርሀቷን ተመልከተና ተናድዶ ፥ "ጅል ባል ያገባሽ መሰለሽ?" ሲል ጠየቃት ። ሚስቱ ምንም አልመለሰችለትም ። መልስ ያልሰጠችው ፉኑቺ በባሏ ላይ አደጋ ያደርስበታል ብላ ፈርታ አልነበረም ፥ የእራሱን አደገኛነት ስለፈራች እንጂ ። ባሏን ስትመለከተው አደጋ ወደሚያመነጭ ሀይል ሲለዋወጥ በግልጽ ታያት ። ይህ ሰው ለወትሮው ጸባዩ በሲሲሊያውያን ጐረምሶች ላይ ያልተመለደ ፥ ዝምተኛ ፥ ብዙ የማይናገር ፥ ዘወትር ለአድራጎቱ ምክንያት የሚሻ ነበር ። ዛሬ ግን የወደፊት እጣውን ለመቀየስ ቁርጠኛ ሆኖ ፥ እራሱን ከመከላከል በስተቀር ማንንም የማይጐዳ የነበረ የምስኪንነት ገጽታውን እርግፍ አድርጎ የጣለ ሰው ሆነባት ። እድሜው ሀያ አምስት አመት በመሆኑ እጣውን ፈር ለማስያዝ ዘግይቶአል ። ይሁን እንጂ አጀማመሩ የተንበሸበሸ ነበር ።

ቪቶ ኮርሌዎኔ ፉኑቺን ለመግደል ወስኗል ። ይህን በማድረጉም ጓደኞቹ ያዋጡትን ፥ የራሱን መዋጮ ጨምሮ ሰባት መቶ ብር ያድናል ማለት ነው ። ሌላ ቀርቶ ፉኑቺን ከሞት ለማዳን የሰባት መቶ ብር የህክምና ወጪ ቢያስፈልግ እንኳን አይሰጥም ። የፉኑቺ ውለታ አላለፈበትም ፥ ዘመዱም አይደል ። ታዲያ ለምን ሰባት መቶ ብር ይገብርለታል ። ገንዘቡን አልሰጥም ብሎ እምቢ ሲል ፉኑቺ

t.me/OLDBOOKSPDF

በጉልበት ይቀማሞል ። ታዲያ ለምን አይገድለውምን እን ደእውነቱ ከሆነ አለም ያለፉኑቺ መኖር ትችላለች ። ቪቶ ፋኑቺን ቢገድለው ሊደርስበት የሚችለውም የሞት ቅጣት አልጠፋውም ። ግን ሞትን አልፎ ነው እዚህ የደረሰው ። ስለዚህ ከብዙ ማሰተዋል በኋላ ፣ እስካሁን በተግባር ያላዋለው ከሌሎቹ የላቀ ንቁነትና ወኔ እንዳ ለው ተሰምቶታል ።

ገንዘቡን በግራ ኪሱ ፣ ሽጉጡን ደግሞ በቀኙ ከትቶ የፋኑቺን መምጣት ተጠባበቀ ። ፋኑቺ ልክ በሰአቱ ደረሰ ። ቪቶ ክሌሜንዛ የለገሰውን የወይን ጠጅ አቀረ በለት ።

ፋኑቺ ባርኔጣውን አውልቆ ተዝናንቶ እንደተቀ መጠ ቪቶ ሰባት ሙቶ ብሩን አሰረከበው ። ገንዘቡን ቆጥሮ የረባ ገንዘብ ባልነበረበት ቦርሳው ውስጥ ከከተተ በኋላ ፣ "ሁለት ሙቶ ብር ይቀራል" አለው ። ለጊዜው ትንሽ የገንዘብ እጥረት ስላለበት ለጥቂት ሳምንታት እንዲታገሰው ቪቶ ጠየቀው ። ፋኑቺ በሀሳቡ ተስ ማማ ። እንዲያውም ይህን የመሰለ ጮሌ ሰው እስከዛሬ ሳያጤን መቆየቱ ገርሞት ፣ በቅርቡም ጠቃሚ ስራ እንደሚያገኝለት አረጋገጠለት ። ቪቶ በመስማማት እራ ሱን ከነቀነቀ በኋላ የወይን ጠጁን ሞላለት ። ፋኑቺ መጠ ጡን ጠጣና ተሰናበተ ። ደረጃውን ሲወርድ እና ህንጻ ውን ለቆ ሲወጣ በመስኮት ሆኖ ተመለከተው ። ያካባ ቢው ህዝብ ፋኑቺ ከቪቶ ቤት ለቆ ሲሄድ እንደሚ ያየው ቪቶ አረጋገጠ ። ፋኑቺ ወደ መንገዱ ከገባ በኋላ እስከ ማእዘኑ ተጉዞ ወደ ቤቱ መንገዱን አቃና ። የዘረ ፈውን ገንዘብና ሽጉጡን ከቤቱ አኑሮ እንደገና ሊወጣ ሳይሆን አይቀርም ።

ቪቶ ደረጃውን ወጣና ወደ ቤቱ ጣሪያ ዘለቀ ። የእሳት አደጋ ሲነሳ ለማምለጫ እንዲሆን በተሰራ

t.me/OLDBOOKSPDF

መውረጃ አድርጐ በቤቱ ጀርባ ወጣ ። የፋኑቺ ቤት ከመ
ንገዱ ባሻገር ይገኛል ። አብዛኛውን በዚህ መንገድ
የሚገኙ ባለአንስተኛ ዋጋ ቅጥልጥል ቤቶች የመንገዱን
ግራና ቀኝ ሞልተውታል ። ተከታዩ መንገድ ግን በባቡር
እቃዎችን የሚጭኑ ነጋዴዎች የተከራዩዋቸው የእቃ
መጋዘኖች ናቸው ። የፋኑቺ ቤት በነዚህ መሀል የሚገኝ
የባቡር ጣቢያ ወዛደሮችና ዝቅኛ ደረጃ ዝሙት አደ
ሮች መኖሪያ ነው ። ኗሪዎቹም እንደጤነኞች ጣልያኖች
ቁጭ ብሎ ማውራት የሚሹ ሳይሆኑ ፥ በየቢራ ቤቱ ተከ
ልኩሰው የሚጠጡ ናቸው ። ስለዚህ ቪቶ ማንም ሳያየው
መንገዱን አቋርጦ ወደ ፋኑቺ ቤት ሰመድረስ አልተቸ
ገረም ። ከቤቱ መግቢያ ላይ እውስጥ ቆሞ ተኩሰት
የማያውቀውን ሽጉጡን መዞ ጠበቀው ። ፋኑቺ እንደተ
ጠበቀው ወደቤቱ ሊገባ ሲል ተኮሰበት ። ደጋግሞ ተኩሰ
ነፍሱ መውጣቷን ሲያረጋግጥ ከሚቹ ኪስ ቦርሳውን
አውጥቶ ከራሱ ኪስ ከተተው ።

ያየው ሰው አለመኖሩን ለማረጋገጥ አካባቢውን
ቢቃኝ አልፎ አልፎ የሰው ጥላ ከሚታይባቸው ያንዳ
ንድ ሰዎች መስኮቶች በስተቀር ሜር ማለቱን ተረዳ ።

እሱ ሰዎቹን በጥላቸው መለየት እንደማይችል
ሁሉ ፥ እነሱም እንደማይለዩት ፥ እንዲያውም ማንም
ለፖሊስ ሊጠቁም እንደማይፈልግ ገመተ ።

ቦርሳውን ከፍቶ ገንዘቡን ከውስጡ ሲያወጣ ራሱ
ለፋኑቺ ሰጥቶት ከነበረው ገንዘብ ሌላ ጥቂት ብሮችና
ለመልካም እድል ሚልኪ ናት ብሎ ያምንባት የነበረ
ችው ያምስት ብር ዋጋ ያላት ጥንታዊ የወርቅ ገንዘብ
ብቻ ቦርሳው ውስጥ አየ ። በዚህን ጊዜ ፥ 'ይህ ሰው ሀብት
ያለው ከሆነ ሀብቱን በኪሱ ይዞ አይዞርም' ሲል አሰበ ።

ቦርሳውን በህንጻው የአየር ማስተላለፊያ ቱቦ
ውስጥ ወረወረው ። ሽጉጡን ከጣሪያው ድንጋይ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጥቅጦ ከሰበረው በኋላ ለያይቶ በተለያዩ የአየር ማስ ተላለፊያዎች ከአምስተኛው ፎቅ ቁልቁል ለቀቃቸው ። ከቁሻሻ ክምር ላይ ሰላረፉ አልተንኳኳኹም ። ጪትም ሌላ ቁሻሻ ስለሚከመርባቸው ደብዛቸው ይጠፋል ።

ቤቱ እንደደረሰ ድንገት የደም ፍንጣቂ እንዳይታ ይበት የለበሰውን ልብስ በሚገባ አጥቦ አዲስ ሸሚዝና ሱሪ ቀይሮ ከቤተሰቡ ጋር ተቀላቀለ ።

ይህ ሁሉ ጥንቃቄ አስፈላጊ አልነበረም ። ጪት ፖሊስ ሬሳውን ካገኘ በኋላ ስለፉኑቺ ሞት ቪቶን አልጠ የቀም ። ሌላ ቀርቶ ፉኑቺ ቪቶ ቤት መጥቶ መመለሱን እንኳን ያየ የለም ።

ይልቁንም ፉኑቺን የመሰለ ወሮበላ በመገደሉ ፖሊ ሶች ገዳዩን እንኳን ለመፈለግ ጥረት አላደረጉም ። ወሮ በሎች እርስ በርሳቸው ባደረጉት ግጭት የገደሉት ስለ መሰላቸው ጥቂት ሪኮርድ ያለባቸውን መስላቶች ቢጠ ይቁም ፥ ይህን የመሰለ ሪኮርድ ስላልነበረርት ቪቶን የጠየቀው የለም ።

ፖሊሶች ሊደርሱበት ባይችሉም ክሌሜንዛና ቴስዮ ግን አውቀውታል ። ለጥቂት ሳምንታት ራቁት። በኋላ ግን አንድ ምሽት ወደ ቤቱ መጥተው የአክብሮት ሰላምታ አቀረቡለት ። በትህትና ተቀብሎ የወይን ጠጅ ጋበዛቸው ።

ክሌሜንዛም ለቪቶ አንድ ሀሳብ በለሆሳስ አቀረበ ለት ፥

"ከባለሱቆች ላይ ማንም ገንዘብ የሚቀበል የለም። ካርታ ከሚያጫውቱትም ሆነ ከባለቁማር ቤቶችም ገንዘብ የሚቀበላቸው የለም ፥"

ቪቶ በጽሞና ተመለከታቸው ።

ቴስዮ ቀጠል አድርጎ ፥ "የፉኑቺን ደምበኞች እኛ ልንወርስ እንችላለን ፤ ይከፍሉናል" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቪቶ ትከሻውን ነቀነቀና ፥

"ታዲያ ወደኔ ለምን መጣችሁ? እኔ እንዲህ ባለ ተግባር ላይ ለመሰማራት አልሻም ፥" አላቸው ።

ክሌሜንዛ ከት ብሎ ሳቀና ፥

"ያኔ ልብስ ስንዘርፍ የሰጠሁህ ሽጉጥ የታለ? ከእንግዲህ የማያስፈልግህ ከሆነ መልስልኝ ፥" አለው ።

ቪቶ ቀስ ብሎ ረብጣ ከኪሱ አወጣና ከላዩ ላይ አምስት ባውንድ አንስቶ ፥ "ያውልህ ዋጋውን ልክፈልህ ፥ ዘረፋውን ከፊጸምን በኋላ ሽጉጡን ጥዬዋለሁ ፥" አለ በፈገግታ ።

በዚያ መቅጽበት ቪቶ የፈገግታውን ተጽእኖ አልተገነዘበም ። ይህ ሚስጥራዊ ፈገግታው ምንም ማስፈራራት ስላልታየበት አስደነገጣቸው ። ክሌሜንዛ እራሱን ነቀነቀና ፥

"አይ ገንዘቡን አልፈልግም ፥" አለው ። ቪቶም ገንዘቡን ከኪሱ ከመለሰው በኋላ ዝም ብሎ ጠበቃቸው ። ሁሉም እርስ በርሳቸው ተግባቡ ። ቪቶ ፋኑቺን እንደገ ደለው ቢረዱም ሰሰፈሩ ሰው አልነገሩም ። የሰፈሩ ሰው ግን የፋኑቺን ገዳይ አወቀው ። ቪቶ የተከበረ ሰው ሆነ ። ቢሆንም ፋኑቺ ያካሂድ የነበረውን አይነት ዘረፋ በሱ እግር ተተክቶ ለማካሄድ አልፈለገም ።

ተክታዩ ገዳይ የማይቀር ነበር ። አንድ ቀን ምሽት ላይ ፥ የቪቶ ሚስት አንዲት አከራይዋ ቤቴን ልቀቂ ያላትን ሴት ቪቶ እንዲያግልዳት አመጣቻት ።

ይህች ሴት በአነስተኛ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚያገኙትን ደመወዝ ቁጥረው ከሚያስረክቧት ልጅ ችዋ ር ሆና ኑሮዋን ለመግፋት ጥረት የምታደርግ ምስኪን ነበረች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስዝ ኮሎምቦ የተባለችው ይህቺ ሴት የገንዘብ እርዳታ የምትጠይቀው መስሎት ቪቶ ሊረዳት ፈቃደኛ ነበር ። ነገር ግን ሴትዮዋን አከራይዋ ውጪልኝ ያላት ኪራይ ኖሮባት ሳይሆን የምታሳድገውና ትንሹ ልጅዋ በጣም የሚወደው ውሻ ሴሲት ስለሚሙሀ ጉረቤቶቿ እሮሮ ስላሰሙባት ነው ።

ሴትዮዋ አከራዩ ውሻውን አስመግጂ ብሎ ባዘዘበት ጊዜ ታሱን ለመፈጸም ሰኒዜው ውሻውን የሰወረችው መሰለች ። አከራይዋ ውሻውን ሳታስመግደው ያታለለችው መሆኑን በኋላ ጊዜ ከቤቱ ውጪ አላት ። ውሻውም ለሌላ ዘመድ በተሰጠ ጊዜ ትንሹ ልጅ እሪ ብሎ ጮኸ ። ስለዚህ ውሻችውን አጥተው የኪራይ ቤታቸውንም ሊያጡ ሆነ ።

"ታዲያ እኔ እንድረዳሽ ለምን ጠየቅሽኝ?" ሲል ቪቶ ጠየቃት ።

"ሚስትህ እንድጠይቅህ መክራኝ ነው ።" ብላ መለሰችለት ።

ቪቶ ተገረመ ። ሚስቱ ያደረገውን ሁሉ የደረሰች በት ቢሆንም ጉዳዩን አንስታበት አታውቅም ። ፋኒቺን በገደለበት እለት ስላጠባቸው ልብሶቹ ጠይቃው አታውቅም ። የሚኖሩበትንም ገንዘብ ከየት እንዳመጣው አልጠየቀችውም ። አሁንም ቢሆን ፊትዋ ላይ ምንም ኩይነ በብም ።

"ቤቱን ለመልቀቅ የሚያስችል ገንዘብ እንድሰጥሽ ነው የምትፈልጊው?" አላት ።

ሴትዮዋ ራሷን በአሉታ ነቀነቀችና ፥ እያለቀሰች ፥ "አብሮ አደግ ጓደኞቼ ሁሉ እዚህ ሰፈር ናቸው ። ሌላ ሰፈር ሄጀ ከባእድ ሰዎች ጋር እንዴት እኖራለሁ? ባለ ቤቱ ከቤቱ እንዳያስወጣኝ ንገርልኝ" ስትል ተማጸነች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ" አላት፣ "ቤቱን አትለቂም። እኔ ነገ ጧት አነጋግረዋለሁ።"

"ለመሆኑ፣ እሺ የሚልህ ይመስልሀል?" አለች ሚስዝ ኮሎምቦ።

"እሺ ይላል እንጂ፣ ርህሩህ ሰው ነውኮ። ሁኔታሽን ሳስረዳው ያዘንልሻል። አይዞሽ፣ አትስጊ። ለልጆችሽ ስትይ ጤንነትሽን ጠብቂ፣" አላት ቪቶ።

የቤቱ ባለቤት ሚስተር ሮቤርቶ የጣልያን ወዝአደሮችን ከአገሩ እያስመጣ ለትላልቅ ኮርፖሬሽኖች ያስቀጥራል። በዚህ አይነት ካገኘው ትርፍ ነው እነዚህን የሚከራዩ ቤቶቹን ያሰራው። በሰሜን ኢጣልያ የተወለደውና የተማርኩ ነኝ የሚለው ይህ ግለሰብ ከናፖሊ እና ከሲሲሊ ፈልሰው የመጡት ወገኖቹ ለቤቱ የሚፈልገውን ጥንቃቄ ስለማያደርጉ በቤቱ ላይ እንደፈሰሰ የምስጥ ሰራዊት አድርጎ ስለሚቆጥራቸው ከፍተኛ ንቀት አለበት።

ቪቶ ሮቤርቶን መንገድ ላይ አግኝቶ ሊያነጋግረው እንደሚፈልግ ገለጸለት። ሰውዬው እብሪት ባያጣም ከደቡብ ኢጣሊያ የሚመጡ ሰዎች ለትንሹም ለትልቁም ጉዳይ ጩቤ መምዘዝ ይወዳሉ የሚል ግምት ስለነበረው በብልግና አነጋገር ሊመልስለት አልደፈረም።

ቪቶ የሴትዮዋን ችግር ለሮቤርቶ ካስረዳው በኋላ ይቅርታ እንዲያደርግላትና ከቤቱ እንዳያባርራት በጽሞና ጠየቀው። ሮቤርቶም የቪቶን አቋም ከላይ እስከታች አጠናና ቤቱን ለሌላ ሰው በተሻለ ዋጋ ሊያከራይ የተዋዋለ ስለሆነ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል መለሰለት።

"ምን ያህል ይበልጥ አከራየኸው?" ሲል ቪቶ ጠየቀው። "አምስት ብር" ሲል መለሰለት በዚያ የባቡር ጣቢያ አካባቢ የቤት ኪራይ ያን ያህል አያወጣም።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ያውልህ የሰድስት ወር ሞማሪ ። ለሴትዮዋ ግን ይህን አትንገራት ፥ ኩሩ ደሀ ናት ። ከሰድስት ወር በኋላ እንደገና እንገናኝ ። ታዲያ ውሻዋም አብሯት ይኖራል ።”

“ጀሀነብ ግባ! ለመሆኑ ማነህ አንተ ለኔ መመሪያ የምትሰጠኝ! አርመህ ተናገር! አለበለዚያ ድራሽህን ነው የማጠፋው!”

ቪቶ በመደነቅ እጆቹን አነሳ ። “በጐ አድራጐት እንድታደርግልኝ ነው የጠየቅኩህ ። ሰው የሌላውን ወዳጅነት የሚሻበትን ወቅት አያውቀውም ። ስለዚህ በበጎ ፈቃድ ገንዘቡን ውሰድና የራስህን ውሳኔ አድርግ ። ነገ ጧት ገንዘቡን ለመመለስና በቃልህ ለመጥናት ብትሻ ትችላለህ ። ሴትየዋንም ላስወጣት ብትል ፥ እንዴት ልከለክልህ እችላለሁ? ምንም ቢሆን ሀብትህ ነው ። ውሻውን በአካባቢው እንዳይኖር ብትሻ ይገባኛል ። እኔም እራሴ እንስሳት አልወድም ። ይህችን ውለታ ጣልብኝ ። ስለኔም የሰፈሩን ሰዎች ብትጠይቅ ውለታ እንደማልረሳ ይነግሩሀል ።” በማለት ብሩን በግድ ሰጠው ።

ሚስተር ሮቤርቶ የሰፈሩን ሰው ስለቪቶ ሲጠይቅ አምሽቶ ማንኑቱን ከጥሪዓ በኋላ እስኪነጋለትም ለመቆየት አልፈለገም ። ማታውኑ እቪቶ ቤት መጥቶ በሩን አንኳኳና ይቅርታ ጠየቀ ። ይህ ሁሉ ሁኔታ ከአለመግባባት የደረሰ መሆኑን ገልጾ ፥ ሚስስ ኮሎምቦን ከቤቱ እንደማያስወጣት አረጋገጠለት ። ጐረቤቶቿም ቢሆኑ ውሻዋ ይጮህብናል ብለው ቢያማርሩም አብሯት ሊኖር እንደሚችል ነገረው ። በመጨረሻም ሰላሳውን ብር ለቪቶ መልሶ ሰጠውና ፥ “ለዚች ሴት ያዘነላት ርህሩህ ልብህ እኔን አሳፍሮኛል ። ስለዚህ እኔም ርህራሄ ማሳየት አለብኝ ። የቤት ኪራይዋ አይጨምርም ፥ እንደነበረ ይቀጥላል ፥” አለው ።

ቪቶ ብስኩት እንዲቀርብ አዘዘ ። እጁን ጨምቆ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጨበጠውና አመሰገነው ። ሚስተር ሮቤርቶም ተነፈሰና ይህን የመሰለ በጎ ሰው መተዋወቁ በሰው ልጅ ላይ የነበረውን እምነት ያጠናከረለት መሆኑን ነገረው ። በዚህ ሁኔታ ሁለቱም ወገኖች የሚገባቸውን ከተጫወቱ በኋላ ተለያዩ ። ሮቤርቶም ሊያርስበት ከነበረው አደጋ ሲያመልጥ በፍርሀት አጥንቱ ፈሳሽ ልትሆን ምንም አልቀ ራት ። ከዚያ በኋላ በየቀኑ ይጐበኛቸው ከነበሩ ከሚያ ከራያቸው ቤቶች አካባቢ ለሶስት ቀናት አልታየም ።

እንግዲህ ቪቶ ኮርሌኦኔ በሰፈሩ የተከበረ ሰው ሆነ ። የሲሲሊ ማፊያ አባል እንደሆነ ተነገረለት ። አንድ ቀን አንድ ኪርታ የሚያጫውት ግለሰብ ቪቶ ዘንድ መጦ አልፎ አልፎ የድርጅቱን ደህንነት ቢጐበኝ ለት በየሳምንቱ ሀያ ብር ለመዳጅነታቸው እንደሚከፍ ለው ቃል ገባለት ። ወጣት ወሮበሎች የሚያስቸግሯቸው ባለ ሱቆች ቪቶ ቦታዩ ጣልቃ ገብቶ መፍትሄ እንዲሰጣቸው ይጠይቁታል ። ለዚህም ተገቢው ወሮታ ይከፈለዋል ። በዚያ ዘመን ሰፈር ከፍተኛ ገቢ ሊባል የሚቻል ሽያጭ መፍ ያገኝ ጀመር ። ያገኘውን ማንም ሰይጠይቀውና ሳያስገድደው ለክሌመንዛና ለቴ ስዮ ያካፍላቸው ነበር ።

በመጨረሻ ከልጅነት ጓደኛው ከጂንኮ አባንዳንዶ ጋር በወይራ ዘይት ንግድ ላይ ተሰማራ ። ጂንኮ ባለው ልምድ ስራውን ያካሂዳል ። ክሌመንዛና ቴስዮ በየሰዉ ሱቁ እየዞሩ ደላሎች ሆኑ ። ቪቶም ባለው ትሁትነት፣ ገንዘቡ የራሱ ቢሆንም ፣ ንግዱ በስሙ እንዲጠራ አል ፈለገም ። ስለዚህ በጓደኛው ስም 'ጂንኮ የተጣራ የወ ይራ ዘይት' ተብሎ እንዲጠራ አደረገ ። ቪቶ የድርጅቱ የበላይ ሆነ ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ላይ ብቻ ፣ ለም ሳሌ ባለሱቆች ከደላሎች ጋር ሳይግባቡ ሲቀሩና በመሳ ለት ሁናቴዎች ላይ መገኘቱን መረጠ ። እንዲህ ቁለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታ ላይ እሱ በሚገባበተ ወቅተ በውን ተግባሙን ልዩ ችሎታውን ይጠቀምበት ነበር ።

በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት ቪቶ አንድ መጠነኛ ንግድ እንደሚያካሂድ ነጋዴ የሚያረካ ኑሮ ከቤተሰቡ ጋር አሳለፈ ። "ጄንኮ የተጣራ የወይራ ዘይት" የተባለው ድርጅቱ ከጣሊያን አገር አስመጥቶ በአሜሪካ የሚሸጠው የወይራ ዘይት በከፍተኛ ደረጃ ስለሚሸጥ ንግዱ በጣም ተስፋፋ ። ቪቶ "ንጹ ገበያ ብኩንነት ነው" ይላል ። ሞኖፖሊ ግን በጣም ብቃት ያለው የንግድ ስራ እንደ ሆነ ይናገራል ። ስለሆነም የሚያስመጣውን ዘይት ዋጋ እየቀነሰ በመሸጡ ተፎካካሪዎቹ እሱ በሚሸጥበት ዋጋ ንግድ ለማካሄድ አልቻሉም ።

የነሱን ዘይት ባለሱቆች እንዳይወስዱት ተጽእኖ ስላደረገ ተወዳዳሪዎቹ በንግዱ ላይ ሊቆዩ አልቻሉም ። ስለዚህ ያላቸው እድል ንግዱን እርግፍ አድርጎ መተው ወይም ከሱ ጋር መቀላቀል ሆነ ። ቪቶ ንግዱን ለማስፋፋት በማስታወቂያ በመጠቀም ፋንታ በራሱ የተከበረ ስውነት ብቻ ይተማመን ነበር ። ይህ ሰው በልጅነቱም ቢሆን ሓድራነቱ በቂ ምክንያት መስጠት እንደሚችል ይታመቃል ። አያስፈራራም ። ዘወትር በቂ ምክንያት ያዘለ መከራከሪያ ነጥብ ያቀርባል ። የሌላውም ሰው ጥቅም እንዲነካበት አይፈልግም ። በከተማው ጥቂት ዘይት የሚያከፋፍሉ ነጋዴዎች ቁጡ ፡ ትምክህተኞች ምክንያት የማቅረብ ብቃት የሌላቸው ፡ አዙሪው ማየትና ማጤን የማይችሉ ፡ የቪቶን ያህል ግንዛቤ የሌላቸው ፡ እና በጉአ ግስት ሊያስረዳቸው ቢሞክርም የማይረዱ ደንቆሮዎች ነበሩ ። ቪቶ ተባብሩውን በቆረጠ ጊዜ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች የማያዳግም እርምጃ ይመሰድባቸዋል ። ቴስዮን ያስማራና ግምጃ ቤታቸውን ያቃጥላል ። የጫኑትን መኪና ሙሉ ዘይት ሚዳ ላይ ያፈስባቸዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ችኩል ጅምላ ሻጭ ነጋዴ ለሺህ አመታት የቆየውን 'የአሜርታ' ን አይቶና ሰምቶ ዝም ማለት ህግ ጥሶ ኢጣሊያዊ ወገኖቹን ለባለ ስልጣኖች ያጋልጥ ጀመር ። ይህ ሰው ብዙ ከመራመዱ በፊት ድንገት ጠፋ ፡ የት እንደደረሰ አልታወቀም ። ልጆቹና ሚስቱ ብቻቸውን ቀሩ ። ደግነቱ ልጆቹ የደረሱ ስለነበሩ ፡ የንግዱን ስራ ሲረከቡ ከጂንኮ የዘይት ኩባንያ ጋር ተስማሙ ።

ሰዎች ታላላቅ ሆነው አይወለዱም ፡ ወደ ታላቅነት ያድጋሉ እንጂ ። የቪቶ ህይወትም ከዚህ ውጭ አልነበረም ። የእገዳ ህግ ወጥቶ አልኮል እንዳይሸጥ በህግ በተከለከለ ጊዜ ፡ ቪቶ ከተራ ነጋዴነት ወጥቶ በድብቅ አለም ውስጥ ታላቅ የወንጀል ድርጅት የበላይ ሆነ ። ይህ በአንድ ቀን ወይም በአንድ አመት አልተገኘም ። ለማንኛውም የእገዳው ወቅት አብቅቶ ታላቁ የኢኮኖሚ ድቀት በደረሰበት ወቅት ቪቶ 'የጡት አባት' ተባለ ፤ ዶን ሆነ ፡ ዶን ኮርሌዎኔ ተባለ ። በዚያን ጊዜ የ'ጂንኮ የተጣራ ዘይት ኩባንያ' ጭነት መኪናዎች ቁጥር ሰድስት ደርሶ ነበር ።

አልኮል በህገወጥ መንገድ የሚነግዱ ሰዎች በከሌሜንዛ አማካይነት ቪቶን አነጋገሩት ። እነዚህ ሰዎች ከካናዳ በድብቅ ዘይ ያስገቡትን መጠጥ በኒውዮርክ ከተማ የሚያሰራጩላቸው መኪኖችና ቆራጥ ሹፌሮች ይሻሉ ። ጥቅሙ እጅግ ብዙ ስለነበር ቪቶ የዘይት ንግዱን በጣም ቀንሶ ከነዚህ ህገወጥ ነጋዴዎች ጋር ተመሳጠረ ። ይህንንም ያደረገው ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡትን ህገወጥ ነጋዴዎች ትብብር ቢነፍጋቸው አደጋ እንደሚደርስበት በእጅ አዙር ስላስፈራሩት አልነበረም ። ቪቶ ኮርሌዎኔ ለምን ተደፈርኩ በማለት ይህን የመሰለ ጥቅም ሊያጣ አይሻም ። የሚሰነዝሩት ዛቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከልብ አለመሆኑን ይመዝንና ፥ እነዚህ ሰዎች ዛቻ ሳያ ስፈልግ ስለዛቱ በከንቱነታቸው ዝቅ አድርጎ ይገም ታቸዋል ።

ቪቶ ከመከበሩም በላይ በእውቀት እየበለለ ፥ ግን ኑነቱም እየጠነከረ ሄደ ። አንድ ባንከኛ ለሀብቱ ማረጋ ገጫ ዋስትናዎችን እንደሚያደራጅ ሁሉ ፥ ቪቶም ውለታ የመጣል ተግባሩን ቀጠለ ። እንዲህ እያደረገም በተከታ ታዮቹ አመታት የብሩህ አእምሮ ባለቤትነቱን አረጋገጠ።

ቪቶ በቤታቸው አረቄ እያወጡ መለኪያውን በአ ስራ አምስት ሳንቲም ለወንደላጤ ወዛደሮች ለሚሸጡ ኢጣሊያዊ ወገኖቹ ተገን ሆነ ። ለሚስስ ኮሎምቦ ልጅ የክርስትና አባት ሲሆን የሀያ ብር የወርቅ ጌጥ ሰጠው።

በልዩ ልዩ ተግባር ላይ የተሰማሩ መኪኖቹን ፖሊስ በየወቅቱ ያስቆማቸዋል ። ጀንኮ ከፖሊስ ባለስ ልጣኖችና ከዳኞች ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ጠበቃ ቀጠረ ። እንደዚህ ለመሰሉ ባለስልጣኖች ድብቅ ደመ ወዝ የሚከፈልበትን ስርአት አበጀ ። በአጭር ጊዜ ውስጥ የደመወዝተኞቹ ዝርዝር እየጨመረ ሄደ ። ጠበ ቃው የወጪውን መብዛት በመፍራት ዝርዝሩን ለመቀነስ ሲሞክር ፥

"ፊጽሞ ፥ ፊጽሞ" ይለዋል ዶን ኮርሌዮኔ "ለጊዜው ባይጠቅሙንም ሁሉም በክፍያው ዝርዝር ላይ ይኑሩ ። እኔ በወዳጅነት አምናለሁ ። ወዳጅነቴን ቀድሜ ለማሳየትም ዝግጁ ነኝ ፥"

ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካ የዶን ኮርሌዮኔ ግዛት እየሰፋ ሄደ ። የጭነት መኪኖች ተጨመሩ ። የደመወዝ መዝገቡም እየረዘመ ሄደ ። የቴስዮኖ የክሌሜንዛ ረዳቶችም ቁጥራቸው ጨመረ ። በመጨረሻም ዶን ኮርሌ ዮኔ አንድ ድርጅታዊ ስርአት ቀየሰ ። ለክሌሜንዛና ለቴስዮ ለእያንዳንዳቸው የሻምበልነት ማእረግ ሰጥቶ በነሱስር

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚገኙ ተልእኮ ፈጻሚዎችንም በወታደርነት ደረጃ መደባቸው ። ጄንኮ አባንዶንዶን 'ኮንሲሊዮሪ' ወይም አማካሪ ብሎ ሰየመው ። በዚህ የስልጣን ተዋረድና መዋቅር መሰረት ዶኑ ትእዛዝ ሲያስተላልፍ ለአማካሪው ወይም ለሻምበሉ ለብቻው ነው ። ስለዚህ ማንም ይህን ተናገረ ብሎ ሊመሰክርበት የሚችል ሰው አይኖርም ።

ዶኑ ቀጥሎም የቴስዮንና የክሌሜንዛን ቡድኖች ለያያቸው ። ቴስዮ ከአምስቱ የኒውዮርክ ክፍለ ከተሞች ብሩክሊን የተባለው ቀጣና ሀላፊ ሆነ ። ቴስዮ እና ክሌሜንዛ ተገናኝተው እንዳይመሳጠሩ ዶኑ ግልጽ አቋም ወሰደ ። አቋሙን ይበልጥ ብልህ ለነበረው ለቴስዮ ባስረዳበት ወቅት ሁለቱን መለየት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ለጥንቃቄ ብሎ ነው በሚል ሽፋን ነበር ። ቴስዮ ምስጢሩን ቢረዳም በጽሞና ስለተቀበለው በብሩክሊን በሚያካሂደው ስራ ሙሉ ነጻነት ሰጠው ። በሌላ በኩል በዚያው በኒውዮርክ ከተማ ብሮንክስ ቤተ ባለው ቀጠና የተመደበው ክሌሜንዛ ጉበዝ ቢሆንም ጥንቃቄ አልባና ጭካኔው የበዛ በመሆኑ ልጓም አበጀለት ።

የኢኮኖሚው ድቀትና የስራ አጥነት መብዛት በየሰዉ አእምሮ መጥፎ ትዝታ በጣለበት በዚያ ወቅት የዶን ኮርሌዮኔ ሀያልነት ጨመረ ። 'ዶን ኮርሌዮኒ' ተብሎ የተጠራበት ወቅት በዚያ ዘመን ነበር ። በከተማው ላይ ሀቀኛ ግለሰቦች ስራ ፈለጋ ሲንገላቱ ፣ ኩሩ የነበሩ ግለሰቦች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሆነው ትእቢት የተመላባቸው ባለስልጣኖች ለሚጥሉላቸው ዳረጎት ክብራቸውን ሲያዋርዱ ፣ የዶን ኮርሌዮኔ ሰዎች ግን በኩራት እራሳቸውን አቅንተው ፣ ኪሳቸውንም በብር ሞልተው የስራ ማጣት ሳያሰጋቸው በመንገዱ ላይ ይዘባነኑ ነበር ። ትሁቱ ዶን እንኳን ሳይቀር ለተከታዮቹ የተሟላ ኑሮ በማስገኘቱ ፣ የፈጠራትን አለም በመንከባከብ ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ነጻነታቸውን ሰብዓዊነታቸውንና ሀይወታቸውን የሰጡት ተከታዮቹ ውድቀት ሳይገጥማቸው ተጠብቀው በመኖራቸው ኩራት ሳይሰማው አልቀረም ። ለምሳሌ ተከታዩ የሆነ ግለሰብ ቢታሰር ፥ እስኪፈታ ድረስ ቤተሰቡ የሰውዬውን ሙሉ ደመወዝ ያገኛል ። የታሰረው ግለሰብም በበኩሉ ምንም ቢሆን ሚስጥር አለማውጣት ይጠበቅበታል ። ይህ ሰው ለፖሊስ ምንም አለመንገሩ ከተረጋገጠ ሲፈታ የሞቀ አቀባበል እና ግብዣ ይጠብቀዋል ። በዚያው እለት ምሽት ላይ የዶኑ አማካሪ ወይም ዶኑ እራሱ ይህን ለመሰለው ቆራጥና መንፈሰ ጠንካራ አባላቸው ክብር ግብዣው ላይ ብቅ ይሉና ጠቀም ያለ ስጦታ ይለግሱታል ። ግለሰቡ ወደ አድካሚ ስራው ከመመለሱ በፊት በተሰጠው ገንዘብ ለአንድ ሁለት ሳምንት ከቤተሰቡ ጋር ሆኖ ከአንድ መዝናኛ ስፍራ ያሳልፋል ። ይህ ነበር የዶን ኮርሌዎኔ የማይረሳ በጎ አድራጎት ። በዚህ ወቅት እሱ የሚመራው ድብቅ የወንጀል አለም ጉዞውን የሚያደናቅፉት ጠላቶቹ ከሚመሩት የገሀዱ ህጋዊ አለም አመራር የጎሸለ እንደሆነ ዶኑ መገንዘብ ቻለ ። ይህንንም ያረጋገጠው መሰረታዊ እርዳታ ለማግኘት ለልጆቻቸው ስራ ለመሸጥ ፥ ልጆቻቸውን ለማስፈታት ገንዘብ ለመበደር ወይም ከአቅማቸው በላይ የሆነ ኪራይ ከጣሉባቸው ቤት አከራዮቹ እንዲያሸልዱቸው ለአቤቱታ ወደሱ ዘንድ የሚመጡትን የኔካባቢውን ሰዎች ሲመለከት ነበር ። ዶኑ እነዚህን ሰዎች ሁሉንም ረድቷቸዋል ። ይህ ብቻ አይደለም ። እርዳታው በጐ ፈቃድ ያለበት ሆኖ ፥ በጎ አድራጎት ተቀባዮችንም ከሚቆጠቁጣቸው ከባድ ስሜት በሚገላገሉ ቃላት አጽናንቶ ነው ። ስለዚህ እነዚያ ኢጣልያውያን ሌላ ቀርቶ ለሠማ ምክር ቤት ፥ ለማዘጋጃ ቤት ፥ ለምክር ቤት የሚመረጡትን ተመራጭ ለመለየት ሲችገሩ እንኳ የሚያማክሩት የጡት

t.me/OLDBOOKSPDF

አባታቸውን ፡ ዶኑን ነው ። በዚህ የተነሳ ይህ ሰው የፖ
ለቲካ ባለስልጣኖችም የሚያማክሩት ሀያል ሰው ሆነ ።

ዶን ኮርሌዮኔ አርቆ አስተዋይ ነበር ። ብሩህ አእ
ምሮ ያላቸውን የድሀ ቤተሰብ ልጆች ኮሌጅ እንዲማሩ
ያደርጋል ። እነዚህ ልጆች ተምረው አድገው የህግ
ባለሙያዎች ፡ ገዥዎችና ዳኞች ሲሆኑ የወደፊቱ ግዛቱ
ሀልውና ይበልጥ እየተረጋገጠ እንደሚሄድ በጥንቃቄ
አቅዷል ።

መንግስት ጸንቶ የቆየውን የመጠጥ እገዳ ባነሳበት
ወቅት የዶኑ አለም ተናግቶ ነበር ። እሱ ግን የጥንቃቄ
እርምጃ አዘጋጅቶ ነበር ። በ1933 ላይ የማንሀተን የቁማር
እንቅስቃሴዎችን ፡ የአራጣ ብድርንና ህገወጥ ተግባሮችን
በቁጥጥሩ ስር አውሎ ከነበረው ሳልቫቶሬ ማራንዛኖ
ከተባለው ፡ በወንጀል አለም ከባድ ተብሎ ከሚጠራው
ግለሰብ ዘንድ መልእክተኞች ላከ ። የቪቶ መልእክተ
ኞች ዶኑ በተመሳሳይ ተግባር ላይ ለመሰማራት እንደ
ሚሻ ለማራንዛኖ ገለጡለት ። ቪቶ በበኩሉ ከነድርጅቱ
ከፖሊስ እና ከባለስልጣኖች በሚያገኘው ከለላ በመ
ጠቀም ለማራንዛኖ ድጋፍ በመስጠት ሊያጠናክረውና
እንቅስቃሴውም በብሮንክስ እና በብሩክሊን መስፋፋት
እንዲችል ድጋፍ በመስጠት ከእንቅስቃሴው የሚገኘ
ውን ጥቅም በጋራ እንዲካፈሉ ሲሉ መልእክተኞቹ
ሀሳብ አቀረቡለት ። አርቆ ማስተዋል የተሳነው ማራን
ዛኖ ግን የኮርሌዮኔን ሀሳብ እንደማይቀበለው በእብሪትና
በጥላቻ ገለጸለት ። ታላቁ አልካፖኔ የማራንዛኖ ወዳጅ
ነው ።* በዚያ ላይ ፡ ማራንዛኖ የራሱ ድርጅትና ሰዎች

---

* አልፎንሶ ካፖኔ በአሜሪካ ብሩክሊን በ1899 ተወለደ ። ይህ ግለሰብ
ምናልባት በአሜሪካ ከነበሩት ወንበዴዎች ይበልጥ ዝነኛ ነበር ።
በ1920 የደብቅ መጠጥ ንግድ በአመት ከ20 ሚሊዮን ብር የበለጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያሉት ከመሆኑም በላይ ፥ አያሌ ትጥቅ አደራጅቷል ። እንደዱኑ ያለ ከእውነተኛ የማፊያ ባህርይ ይልቅ የፓርላማ ተሟጋች የመሰለ ግለሰብ ብቅ ብቅ ማለት ፈጽሞ ሊቀበል አይሻም ። የማራንዛኖ እምቢታ ታላቁን የ1933 ጦርነት አስነሰቶ የኒውዮርክን የወንጀል አለም መዋቅር ለወጠው ።

በመጀመሪያ ላይ ሲመለከቱት የተመጣጠነ ፍልሚያ አልመሰለም። ማራንዛኖ ሀይለኛ አስገዳጆች ያሉበት ድርጅት ባለቤት ነው ። ከራሱ ድርጅትም አልፎ የአልካፓኔንም እርዳታ ማግኘት ይችላል ። በተጨማሪ በከተማዋ የዝሙትንና የአደንዛዥ እጽ እንቅስቃሴን ከሚያካሂደው ከታማሊያ ቤተሰብ ጋር መልካም ግንኙነት አለው ። እንዲሁም የአይሁድ ሰራተኞች ማህበራት መሪዎችንና በህንጻ ስራ ላይ የተሰማሩ የጣልያን አናርኪስቶችን ፥ የማራንዛኖ አስገዳጆች ሰጥ ሲያደርጉላቸው የነበሩት የንግድ መሪዎች ፥ የሱ ውለታ ስላለባቸው ብድር መላሽ ከመሆን ወደኋላ አይሉም ። በዶኑ በኩል የክሌሜንዛና የቴስዮ ድንቅ ቡድኖች አሉ ። ዶን ኮርሌዮኔ የነበረው የፖለቲካ ግንኙነት ማራንዛኖ በነበረው የንግድ ግንኙነት ይጣጣል ። ነገር ግን እሱን የረዳው ጠላቶቹ ስለዶኑ ሀይል የነበራቸው ዝቅተኛ ግምት ነበር ። እንዲያውም በጠላቶቹ ግምት ቴስዮ በግሉ የሚሰራ

ያገኘበት ነበር ። በዚሁ አመት በሺካጐ የነበሩ የድብቅ አለም ወንበዴ ቤተሰቦች የእርስ በርስ ጦርነት ባካሄዱበት ወቅት ተቀናቃኞቹን በሙሉ ጨረሳቸው ። እንዲሁም በ1929 እሱ ያሰማራቸው ወንበዴዎች የፖሊስ ልብስ ለብሰው ሞራን የተባለውን የወንበዴ ቡድን አባላት ጨረሷቸው ። በመጨረሻም በ1931 የአገር ውስጥ ገቢ ግብር በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የ80 ሺህ ብር ቅጣትና የ11 አመት እስራት ተፈረደበት ። በ1939 በቂጥኝ በሽታ ተይዞ ከእስር ቤት ከተለቀቀ በኋላ ሞተ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንጂ ከዶኑ ጋር ግንኙነት ያለው መስሎ አልታያቸ ውም ።

ይህም ሆኖ ፥ ቪቶ የሀይል ሚዛኑን በአንድ ሀይለኛ በትር እስካስተካከለው ድረስ ያልተመጣጠነ ጦርነት ሆኖ ታይቶ ነበር ።

ማራንዛኖ ሁለት የታጠቁ የአል ካፖኔ ሰዎች እንዲ መጡለት እና ይህን መጤ እንዲደመሰሱት ጥሪ አደረገ ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ግን ወሬ የሚያቀብለው ዘመድ ሽካኑ ከተማ ላይ ስለነበረው እነዚህ ሰዎች በባቡር እንደሚ መጡ ቀድሞ ወሬ ደረሰው ። ቪቶ ኮርሌዎኔም አረመኔ ውን ሉካ ብራሲን የአውሬነት ባህርይውን እንዲወጣ ለቀቀባቸው ።

ሉካ ብራሲ ከረዳቶቹ ጋር አራት ሆኖ የሽካጎን ወመኔዎች ባቡር ጣቢያ ተቀበላቸው ። አንዱ የብራሲ ሰው ለዚህ ተልእኮ ሲባል ታክሲ ነጂ ሆነ ። እቃቸውን ያወረደው ወዛደር እቃቸውን ወስዶ ከተዘጋጀው ታክሲ ላይ ጫነላቸው ። ታክሲ ውስጥ ሲገቡ ብራሲና ረዳ ቶቹ ተከትለዋቸው ገቡ ። ሽጉጥ ደግነው ታክሲው ወለል ላይ እንዲተኙ አስገደዷቸው ። ታክሲዋም ወደ አንድ ለዚሁ ተግባር ብራሲ ወዳዘጋጀው የእቃ ግምጃ ቤት ይዛቸው ገባች ። ሁለቱ የካፖኔ ሰዎች እጃቸውንና እግራቸውን ታስረው እንዳይጮሁ ፎጣ አፋቸው ውስጥ ተጠቅጠቀ ።

ብራሲ ግድግዳ ላይ ተቀምጦ የነበረ አንድ መጥረ ቢያ አነሳና አንደኛውን የካፖኔ መልእክተኛ መፍለጥ ጀመረ ። እግሩን ፈልጦ ጨርሶ ወደ እግሩ ጡንቻ ከፍ አለ ። ከዚያም ወደ ጉልበቱ በመጨረሻም ወደ ጭኑ ዘልቆ ጨፈጨፈው ። ሰውየው ከሰቆቃው መብዛትና ከደሙ እንደጉርፍ መፍሰስ የተነሳ ወደ ሌላው አካሉ እስኪዘልቅ ሳይቆይ ጣእሩ አብቅቶ ፥ ህይወቱ አለፈች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ብራሲ ወደ ሁለተኛው ምርኮኛ ፊቱን ሲመልስ ሌላ ድካም አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም ። ሰውየው ከድንጋጤ ብዛት የተነሳ በአፉ ውስጥ የተጠቀጠቀውን ፎጣ ሊታመን በማይችል ሁኔታ ውጦ ትንፋሽ አጥሮት ነፍሱ ወጥታለች ። ፖሊስ ኋላ የዚህን ሰው ሞት ምክንያት ለማጣራት የሬሳ ምርመራ ሲያደርግ ሰውየው ሆድ ውስጥ ፎጣው ተገኘ ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሽካጎ ላይ የካፖኔ ቤተሰቦች ከቪቶ ኮርሌዎኔ መልእክት ደረሳቸው ።

'እንግዲህ አሁን ጠላቶቼን እንዴት እንደማደርግ የተረዳችሁ ይመስለኛል ። ለመሆኑ አንድ የናፖሊ ተወላጅ በሲሲሊያውያን መሀከል በተነሳ ጠብ ለምን ጣልቃ ይገባል? ለወዳጅነት እንድሻህ ከፈለግህ ይህን ለማድረግ ዝግጁ ነኝ ። አንተን የመሰለ ሰው እርዳታ አድርግልኝ በማለት ፋንታ በራሱ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ፣ እንዲያውም ወደፊት ችግር ቢገጥምህ ልረዳህ ዝግጁ ነኝ የሚል ወዳጅ ማግኘት ፣ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ሳይገባው አይቀርም ። ወዳጅነቱን አልፈልግም ካልክም እንዳልክ ይሁን ። ነገር ግን አንድ ነገር ልነግርህ ይገባል ። አየሩ እዚህ አካባቢ ጭጋጋም ስለሆነ ለናፖሊ ሰዎች አይስማማም ። ስለዚህ ሁለተኛ ይህን አካባቢ ለመጐብኘት እንዳትሞክር ተመከር ።'

ይህ እብሪት የተሞላበት መልእክት በእቅድ የተዘጋጀ ነበር ። ዶኑ ካፖኔዎችን ንቋቸዋል ። በእብሪታቸው ባካበቱት የወንጀል ሀብትና በትምክህታቸው የተነሳ የፖለቲካ ድጋፍ አጥተዋል ። እንደ እውነቱ ከሆነና ዶኑም እንደሚያምንበት አንድ ሰው የፖለቲካ ድጋፍ ካልያዘ ወይም ህብረተሰብ በጉያው ካልሰወረው በስተቀር ካፖኔም ሆነ እሱን መሰል ሁሉ በቀላሉ ሊጠፉ መቻሉን ዶኑ ተገንዝቧል ። ካፖኔ ወደ ውድቀት እያመራ እንደሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶኑ አውቆታል ። ወትሮም ቢሆን የካፖኔ ተጽእኖ ከሽካን አካባቢ የሚርቅ አልነበረም ። ስለዚህ ዶን ኮርሌዮኔ አቅዶት የፈጸመው ስልቱ ድል ሊያቀዳጀው ቻለ ። ካፖኔም የዶኑን ሀያልነት ለመቀበል ተገደደ ። የካፖኔ እንደዚህ መዋረድ ለዶን ኮርሌዮኔ በመላው የዩናይትድ ስቴትስ የወንጀል አለም ከፍተኛ ክብርን ማግኘት ዋና መነሻ ሆነ ።

በስድስት ወር ውስጥ ከማራንዛኖ ጋር በገጠመው ጦርነት ዶን ኮርሌዮኔ የበላይነትን ተቀዳጀ ። በማራንዛኖ ከለላ ስር የነበሩትን የቁማር ቤቶች በቁጥጥር ስር አዋለ ። ጠላቶቹን ከየቦታው ውጥረት ውስጥ ከተታቸው። ከሌሜንዛንና ረዳቶቹን ከጐናቸው እንዲቆሙ በማድረግ ልብስ መፈብረኪያና መሸጫ አካባቢ ያሉ የሰራተኛ ማህበራት መሪዎች የሱቆቹን ባለቤቶችና አስገዳጆቻቸውን እንዲፋለሙዋቸው አደረገ ። በሁሉም አቅጣጫ በብልሀነቱ በተለማቸው ፍልሚያዎች ድል አድራጊ ሊሆን ቻ ። የክሌሜንዛን የግዴለሽ አደገኛነት በዘዴ በመጠቀሙ የጦርነቱ ማእበል ለሱ እንዲያደላ አደረገ ። በመጨረሻም ለጊዜው አቆይቶት የነበረውን የቴስዮን ሀይል በማራንዛኖ በራሱ ላይ ለቀቀበት ።

በዚህ ወቅት ማራንዛኖ በሱና በዶኑ መሀከል ሰላም እንዲመሰረት መልእክተኞች ላከበት ። ቪቶ ኮርሌዮኔም ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠረ መልእክተኞቹን ሳያነጋግር ቀረ ። የማራንዛኖ ሰዎችም እድል ከከዳው አለቃቸው ጋር ሊሞቱ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ከዱት ። የቁማር ቤት ባለቤቶች እና አራጣ አበዳሪዎችም ለጠባቂነቱ ይከፍሉት የነበረውን ገንዘብ ለኮርሌዮኔ ድርጅት መስጠት ጀመሩ ።

በመጨረሻም በ1933 የአዲስ አመት ዋዜማ እለት ቴስዮ ከማራንዛኖ የጥበቃ ክልል ውስጥ ዘልቆ ገባ ። የማራንዛኖ ረዳቶች ለስምምነት ጓጉተው ስለነበር

t.me/OLDBOOKSPDF

አለቃቸውን ወደ] እርድ ለመምራት ተቻኮሉ ። ኮርሌዎኔ የሰላም ስብሰባ ለማድረግ እሺ ማለቱን ፥ ስብሰባውም በብሩክሊን በአንድ ምግብ ቤት እንዲሆን መታቀዱንና እነሱም አብረውት እንደሚሄዱ ለማራንዛኖ ገለጹለት ። ማራንዛኖ እንደተባለው ከምግብ ቤቷ ገብቶ ዳቦውን እያላመ እንደተከዘ ቴስዮ ከአራት ረዳቶቹ ጋር ሆኖ ሲገባ ፥ አጃቢዎቹ ማራንዛኖን ጥለውት ሸሹ ። ግድያው ፈጣን ነበር ። የጐረሰውን ዳቦ አላምጦ ሳይጨርስ በጥይት በሳሱት ። ጦርነቱም ተፈጸመ ።

የማራንዛኖ ይዘት ከዶን ኮርሌዎኔ ይዘት ጋር ተደባለቀ ። ዶኑ የቁማር ቤቶች ባለቤቶች ስራቸውን እንዲቀጥሉ ሆኖ ክፍያቸው በስርአት እንዲሰበሰብ ዘዴ ቀየሰ ። ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ወደሚሆነው ወደ ልብስ መሸጫ ሱቆች ማህበራት ውስጥም ዘልቆ ገባ ። በዚህ አይነት በውጭ ጠላቶቹ ላይ ይህን የመሰለ ድል ሲቀዳጅ ፥ በቤቱ ውስጥ ደግሞ ችግር ተፈጠረበት ።

በህር ልጁ ሳንቲኖ አስራ ስድስት አመት ሞልቶት ሎጋ ሆኖ ፥ ወንዳ ወንድ ባህሪው እያየለ መጣ ። ፍሬዶ ዝምተኛ ሳለ ፥ ሚካኤልም ገና ድክ ድክ በሚል በት ወቅት ፥ ሳንቲኖ ዘወትር ችግር ላይ ወዳቂ ሆነ ። ሶኒ ኮርሌዎኔ ወይም ሳንቲኖ ረብሻ ውስጥ ይገባል ። በት ምህርቱ ደካማ ነበር ። አንድ ቀን ፥ የሶኒ የክርስትና አባት የሆነው ክሌሜንዛ መጣና ሶኒ በመሳሪያ አስፈራርቶ ዝርፊያ ባካሄደ ቡድን መሪ ሆኖ መካፈሉንና በዚህም ምክንያት ትልቅ ችግር ላይ ሊወድቅ ይችል እንደነበር ለዶኑ ገለጸለት ።

ዶኑ ንዴቱ ከቍጥጥር ውጭ ከሆነባቸው በጣም ጥቂት ቀናት አንዱ የሶኒን ጥፋት በሰማበት እለት ያሳየው ንዴት ነበር ። ዶኑ የሚያሳድገው ሄገን የተባለው ወጣት በዚህ የብልግና ተግባር ላይ ተሰማርቶ እንደሆነ ክሌሜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንዛን ጠየቀው ። ክሌሚንዛ በአሉታ እራሱን ነቀነቀ ። ዶኑ መኪና ልኮ ሳንቲናን 'ጂንኮ የተጣራ ዘይት ኩባንያ' ቢሮ ድረስ አስመጣው ።

ልጁና ዶኑ ብቻቸውን ሆነው ሳለ ንዴቱን ለመግለጽ አመቺ ሆኖ ባገኘው የሲሲሊ ቋንቋ ገደብ የለሽ ስድብና እርግማን አወረደበት ። በመጨረሻም ፥ ሶኒ ተናዶ መልስ ሳይሰጥ እንደቆመ ቀረ ። ዶኑ በንቀት ፥

"እንዲህ ያለ የደደብ ሰራ ሰርተህ በዚያች ምሽት ውንብድናህ ምን ያህል አገኘህ? ሀምሳ ሀምሳ ብር ደረሳችሁ? ወይስ ሀያ ሀያ? ለህያ ብር ብለህ ህይወትህን ከአደጋ ላይ ጣልክ ፥ አይደል?" አለው ።

ሶኒ ዶኑ በመጨረሻ ያለውን ያልሰማ ይመስል በድፍረት ፥

"ፋኑቺን ስትገድል አይቼሀለሁ ፥" አለው ።

ዶኑ "እህህህ!" አለና ተዘርፍጦ ዝም ብሎ ጠበቀው።

"ፋኑቺ ከቤታችን ወጥቶ ሲሄድ ከእንግዲህ ቤት መግባት እንደምችል እማዬ ነገረችኝ ። በጣሪያ ላይ ስትሄድ አይቼ ተከተልኩህ ። እዚያ ሆኜ ያደረግከውን ሁሉ ተመለከትኩ ። እዚያ ጣሪያው ላይ ቆይቼ የገንዘብ ቦርሳውንና ሽጉጡን ስትወረውር አየሁህ ።"

ዶኑ ተነፈሰና ፥ "መልካም ፥ እንግዲያስ እንዲህ መሆን አለብህ ብዬ ልነግርህ አልችልም ፥" አለው ። "ትምህርትህን መጨረስ አትፈልግም? የህግ ባለሙያ አትሆንም? ቦርሳውን ብቻ ይዘ የሚሄደው የህግ አዋቂ የጦር መሳሪያ ከታጠቁ ሺህ ሰዎች የበለጠ ገንዘብ የመሰረቅ ችሎታ አለው ።"

ሶኒ በፈገግታና ጮሌነት በተሞላው አንጋገር ፥ "በቤተሰቡ ስራ ላይ መሰማራት ነው የምፈልገው ፥" ብሎ ሲናገር ዶኑ ምንም አለማለቱን ፥ አለመሰቁንና

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈገግታ አለግሳየቱን ሶኒ ተረዳና ፥ "የወይራ ዘይት መሸጥ መግር እችላለሁ" አለው በችኮላ አነጋገር ።

አሁንም ዶኑ ምንም ሳይናገር ቆየ ። በመጨረሻም ትከሻውን ከፍ ዝቅ አድርጎ ፥ "እያንዳንዱ ሰው አንድ እጣ አለው ፥" አለ ። ቪቶ ፋኑቺን ሲገድለው በመመልከቱ ልጁም ይህን የመሰለ እጣ ሳይ መውደቁን ግን አባትየው አልተናገረም ።

"እንግዲያስ ነገ ጧት በሶስት ሰአት ናና ጀንኮ ግድ ረግ ያለብህን ያስተምርሀል ፥" አለው ።

ጀንኮ አባንዳንዶ ግን አንድ አማካሪ ሲኖረው የሚገባውን እርቆ አስተዋይነት የተቀዳጀ ሰው በመ ሆኑ ፥ የዶኑን ፍላጐት ተረዳ ። ስለዚህ በቅድሚያ ለሶኒ የሰጠው ተግባር አባቱን ማጀብ ነበር ። በዚያውም ያባ ቱን ብልህነት ይማራል ። አባቱም ይህንኑ ተረድቶ ልጁ ሊያውቀው ይገባል የሚለውን ጥበብ ያስተምረው ገባ ።

ዘወትር ሶኒን ስለጤንነቱ ይወቅሰዋል ። ቁጡነት የመጨረሻው እራስን ማጋለጫ አደገኛ ባህርይ ነው ብሎ ዶኑ ያምናል ። ዶኑ ማንንም ሰው ሲያስፈራራ ወይም በቁጣ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ታይቶ አይታወቅም ። 'ጠላትህ ጉድለቶችህን ከሚገባ በላይ አጋንኖ ሲገምት ላንተ ትልቁ ጥቅምህ ነው ፥ ወዳጅህ ጥንካሬህን ከሚገባ በላይ አሳንሶ ሲገምትም እንደዚሁ ፥' ይላል ዶኑ ።

የሻምበል ጦር አዛዥ ከሌሜንዛ ሶኒን ተኩሰና በገመድ አንገትን አንቆ ማጥቃትን አስተማረው ። ዘመ ናዊው ሶኒ ግን ጥንታዊውን የገመድ አተናነቅ አልፈ ቀደም ። ከሌሜንዛ ቅር ቢለውም ወጣቱ ሶኒ ቀልጣፋውን ሽጉጥ ነበር የወደደው ። ሶኒ ያባቱ ሹፌር ፥ በአነስተኛ ጉዳዮች ላይም ረዳቱ ሆኖ ለሁለት አመታት ያህል ሰራ ። እጅግ ብሩህ አእምሮም ሳይኖረው እጅግም ጉጉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይሆን ፥ በመጠነኛ ስራው ረክቶ ባባቱ እግር ሊተካ የሚዘጋጅ መጣት መሰለ ።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ከፊል ጉዲፈቻ የሆነው የልጅ ነት ጓደኛው ቶም ሄገን የኮሌጅ ትምህርቱን ያካሂድ ነበር ። ፍሬዶ ሁለተኛ ደረጃ ፥ ሚካኤልም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይማራሉ ። ትንሿ እህታቸው ኮኒ ገና ድክ ድክ እያለች ነበረች ። ቤተሰቡ ለጊዜው በብሮ ንክስ በአንድ አፓርታማ ውስጥ በሚኖርበት ወቅት ዶኑ በሎንግ አይላንድ ቤት ገዝቶ ለመግባት ያለውን ፍላ ጐት ከሌሎቹ እቅዶች ጋር ለማጣጣም ፈለገ ።

በወቅቱ የአሜሪካ ታላላቅ ከተሞች በድብቁ የወ ንጀል አለም ብጥብጥ የተነሳ እየተናወጡ ናቸው ።የራሳ ቸውን የድብቅ አለም ግዛት ለመመስረት ከፍተኛ ምኞት ያሳበዳቸው ወሮበሎች በየቦታው የደፈጣ ውጊያ ያካሂዳሉ ። ኮርሌዎኔ እና መሰሎቹም ግዛታቸው እንዳ ይደፈር ይከላከላሉ ። ጋዜጦችና መንግስታዊ ክፍሎች በዚህ ሰርአት አልበኝነትና የህይወት መጥፋት ላይ ፖሊሳዊ ክትትል እንዲካሄድና ህጋዊ እርምጃ እንዲወ ሰድ በሰፊው ማሳሰብ ጀመሩ ። ዶኑ ይህ ሁሉ ህገ ወጥ ድርጊት በሰብአዊ መብት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን እገዳ ማስተዋል ጀመረ ። የውስጥ ግዛቱ ደህንነት አስተማማኝ ቢሆንም ከሱ ውጭ በእርስ በርስ ጦርነት ላይ በተሰማራው ድብቅ አለም መሀከል ሰላም እንዲሰፍን ፈለገ ። ይህ ተልእኮው አደገኛነቱ ሳይታየው ቀርቶ አይደለም ። እነዚያን ሁሉ ሊያስተባብ ርና ሰላም ለማስፈን ያመቻል ብሎ የገመተውን የማህ በራት ማህበር ጉባኤ እንዲመሰረት ሀሳብ አቀረበ ። ታዲያ አንጃዎቹ ብዙ ፍላጐታቸው የተለያየ ሆነበት ። ስለዚህ የእነዚህ አንጃዎች ብዛት ለቁጥጥር መደማያ መችበት መጠን መቀነስ አለበት ብሎ አመነ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አምስቱን ታላላቅ የኒውዮርክ ድብቅ አለም ቤተሰ
ቦች ለማጥፋት ሀይለኞች ስለሆኑ አይቻልም ። ነገር ግን
'ጥቁር መዳፍ' የሚባለው የኒውዮርክ አሸባሪዎች የሰፈር
ቡድን ፥ ከፍተኛ አራጣ አበዳሪዎች ፥ ከህግ አስፈጻሚዎች
ከለላ የሌላቸው ሀይለኛ ቁማር አጫዋቾች ፥ እነዚህ
እነዚህ መወገድ አለባቸው ። እነዚህን በመሳሰሉት ላይ
ዶኑ መላ ሀይሉን አሰማርቶ በሶስት አመት ውስጥ
ኒውዮርክን ጸጥ አደረጋት ። ዘመቻው በመጀመሪያ
አስደንጋጭ ነበር ። አንድ ቀን ዶኑ ድራሻቸውን ሲያ
ጠፉ አስቧቸው የነበሩ ወንበዴዎች አባል የሆነ ግለሰብ
ዶኑ ላይ ቢተኩስበት መከላከያውን ጥሶ ደረቱ ላይ
መቶ አቆሰለው ። ወዲያውኑ የዶኑ ሰዎች በዚህ ሰው ላይ
ተኩሰው ወንፊት ቢያደርጉትም ጉዳት ማድረሱ አልቀ
ረም ።

ዶኑ ቆስሎ በተኛበት ወቅት ሳንቲኖ በስልጣኑ
ተተክቶ እራሱን የጦር ሻምበል አድርጎ ከተማይቱን
ቆላት ። ከ1935 እስከ 1937 ባለው ጊዜ ዘዴኛ ፥ ደፋ
ርና ምህረት የለሽ አደገኛ ሰው ሆነ ። እንዲያም ሆኖ
ይበልጥ አደገኛ ከሆነው ከሉካ ብራሲ እኩል አልሆነም ።
ሉካ ብራሲ ዶኑን ያቆሰለውን የወንበዴዎች ቡድን
ብቻውን ድራሹን አጠፋው ። ለነዚህና ለሌሎች ግለኛ
ወንበዴዎች ከለላ ለመስጠት የሞከረ አንድ የወንጀል
አለም ቤተሰብ ከሉካ ብራሲ አንድ ከፍተኛ ማስጠንቀ
ቂያ ተሰጠው ። ይህም ማስጠንቀቂያ የቤተሰቡን መሪ
መግደል ነበር ። በመጨረሻ ግን ዶኑ ተሽሎት ሲነሳ
ከቤተሰቡ ጋር እርቅ መሰረተ ።

ዶኑ እንደ አንድ መሪ የአካባቢውን ሁኔታም ከግ
ጤን አልቦዘነም ። የሊትለርን ግናና መሆን ፥ የስፓኝን መው
ደቅና ጀርመን እንግሊዝን ሙኒክ ላይ ያደረሰችባትን
ጥቃት ተገንዘበ ። በሁኔታው ሳይደናገጥ ይህ ሁኔታ

t.me/OLDBOOKSPDF

የአለም ጦርነት እንደሚያስነሳ ታየው ። በጦርነት ወቅት እሱ የሚመራውን የመሰለ የወንጀልና የህገወጥ ንግድ አለም ይበልጥ እንደሚከብርም አስተዋለ ። ግን ለዚህ ለመብቃት የሱ አለም እውስጡ ከምንጊዜም የበለጠ ሰላም ያስፈልጋታል ።

ዶን ኮርሌዮኔ በመላው ዩናይትድ ስቴትስ እየተዘዋወረ ዝነኛ የሆኑትን የአገሩን ልጆች አነጋገረ ። በ1939 ላይ በድብቅ የወንጀል አለም ዝነኛ የሰላም ሀዋርያ ሆኖ ከአንድ ታላቅ የሀይማኖት መሪ የበለጠ ተደማጭነት በማግኘቱ ከአብዛኛዎቹ ዋና ዋና ቤተሰቦች ጋር መልካም የስራ ግንኙነት ፈጠረ ። በዚሁ ወቅት በወንጀል አለም ህብረተሰብ መሀከል የተደረገው ስምምነት አንድ ቤተሰብ የእራሱን የውስጥ አመራር በሚመለከት ሙሉ ነጻነት እንደሚኖረው ያረጋግጣል ።

በዚህ አይነት ዩናይትድ ስቴትስ በአለም ጦርነት ውስጥ በገባችበት ወቅት ዶን ኮርሌዮኔ ሙሉ ሰላም አግኝቶ መኸሩን ሊያጭድ ዝግጁ ሆነ ። የዶኑ ቤተሰብ የዋጋ አስተዳደር ቢሮ ያወጣውን የምግብ ሽቀጥና የነዳጅ ቴምብር በድብቅ በማደል እና የጉዞ ቅድሚያ በማስገኘት ረገድ እጁን አስገባ ። የጦር መሳሪያ ኮንትራት ለማስገኘት በመርዳት ፥ የተሰፉ ልብሶች የሚያዘጋጁ ድርጅቶች ያለባቸውን የጥሬ እቃ እጥረት ለማስወገድ ድብቅ ገበያ በማመቻቸት ፥ እንዲሁም በራሱ ድርጅት ውስጥ ያሉ ወጣት ሰራተኞች ወደ ጦር ሜዳ እንዳይዘምቱ ከሀኪሞች ጋር በመመሳጠር የፈለገውን ይሰራል ።

በህግና በስርአት የሚያምኑት ዜጎች በብዙ ሚሊዮን ሲያልቁ የዶኑ አለም ግን ደህንነቱ የተጠበቀ በመሆኑ በአመራሩ ኩራት ቢሰማውም ፥ ልጁ ሚካኤል ኮርሌዮኔ የአገር ጥሪ መቀበል አለብኝ ብሎ ጦር ሜዳ ተመዝግቦ መዝመቱ ደስታውን ቀንሶበታል ። በፍታዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቸው ወደ ጦር ሜዳ የዘመቱት የራሱ ልጅ ብቻ ሳይሆን በድርጅቱ ውስጥ የሚሰሩ ሌሎች ወጣቶችም ነበሩ ። ቪቶ ኮርሌዎኔ በነዚህ ሰዎች ሳይናደድ አልቀረም ። አስከፊ እርምጃ ሳይወስድባቸው የቀረው ግን ለልጁ ያደረገውን ይቅርታ ለነሱም ለመለገስ ስለተገደደ ነው ።

ሁለተኛው የአለም ጦርነት መጨረሻ ላይ የዶኑ ድብቅ አለም አሰራሩን በመለወጥ ከገሀዱ አለም ጋር መጣጣም እንዳለበት ተረዳ ። ይህንንም ምንም ትርፍ ሳይቀንሱ ማድረግ እንደሚቻል አምኗል ። ሁኔታውን የተረዳው ከራሱ ልምድ በመነሳት ነበር ። ትክክለኛውን መንገድ ያመላከቱትም ሁለት የግል ጉዳዮች ነበሩ ።

በመጀመሪያ ፣ አዲሱን የህይወት ጉዞ በጀመረበት ወቅት ፣ ዳቦ ጋጋሪው ናዞሪኔ ገና ወጣት ሆኖ በዳቦ ጋጋሪ ረዳትነት ሲሰራ ሳለ ፣ ሊያገባ የመረጣትን ወጣት ይዞ የቤት እቃ ሊመርጡ ጅምላ ሻጭ ቤት ገቡ ። በሶስት መቶ ብር ሙሉ የሳሎን እቃ አስመረጣቸው ። ጅምላ ሻጩም በወዛቸው ጭማቂ ያጠራቀሙትን ሶስት መቶ ብር ኪሱ ከቶ እቃው ቤታቸው ድረስ እንደሚመጣ ነገራቸው ። በተከታዩ ሳምንት ግን ድርጅቱ መክሰሩን አወጀ ። ሱቁም ታሸገ ። ባለሱቁም ከባለእዳዎቹ ቁጣ ለመሰወር ሲል ድራሹ ጠፋ ። ናዞሪኔም ጠበቆችን ምን ማድረግ እንደሚችል ቢያማክራቸው ሁኔታው ባለእዳዎቹን ሁሉ እስከሚያ ረካ ድረስና ይህም በፍርድ እስኪወሰን ምንም ማድረግ እንደማይቻል ገለጹለት ። ጉዳዩ በፍርድ እስኪወሰንም ሶስት አመት ያህል እንደሚፈጅና ምናልባትም ከአንዲ ብር ላይ አስር ሳንቲም እንኳን ቢመለስለት እድለኛ እንደ ሚሆን ጨምረው አሰረዱት ።

ቪቶ ይህን ሲሰማ ማመን እያቃተው ተደነቀ ። ይህን የመሰለ ሌብነት እንዴት በህግ ሊፈቀድ ቻለ ? ባለሱቁ ምን የመሰለ ቤት እያለው ፣ በጣም ምቹ በሆ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነች አውቶሞቢል እየፈሰሰ ፥ ልጆቹን ኮሌጅ እያስተማረ ተንደላቆ ይኖራል ። ታዲያ ለምን የደሀውን የናዞሬትን ሶስት መቶ ብር ወስዶ እቃውን ይከለክለዋል? ቪቶ ጀንኮ ንና ጠበቆቹን ልኮ ሁኔታውን ሲያጣራ እውነት ሆኖ አገኙት ። ባለቤቱ የግል ሀብቱን በሙሉ ያስመዘገበው በሚስቱ ስም ነበረ ። የቤት እቃ ድርጅቱም በህግ ተመዝግቦ በጋራ የሚያካሄደው ስለነበረ ሰውየው በግል ተጠያቂ መሆን አልቻለም ። ይህ ሰው ኪሳራ እንደሚያውጅ እያወቀ የነዚህን ድሆች ገንዘብ በመቀበሉ እምነት አጉድሏል ። ነገር ግን በህግ ረገድ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ስለዚህ ዶን ኮርሌዎኔ አማካሪውን ልኮ ሻጩን አነጋገረው ። በዚህ ጊዜ ቆቁ ነጋዴ የሁኔታዎችን አካሄድ ተመልክቶ ናዞሬት እቃውን እንዲያገኝ አደረገ ። እናም በዚህ ጉዳይ ላይ ወጣቱ ቪቶ ኮርሌዎኔ እጅግ ስሜቱን የነካው ትምህርት አገኘ ።

ሁለተኛው ድርጊት የበለጡ ጉዳዮችን የሚነካ ነበር ። በ1939 ላይ ዶኑ ቤተሰቡን በሎንግ ቢች አዲስ ከገዛው ቤት አዛወረ ። ግቢው አራት አዳዲስ ቤቶች የተሰሩበት ነበር ።

ሶኒ ሳንድራን ያጫት ስለሆነ በቅርብ ስለሚያገባ አንዱን ቤት ይይዛል ። ሌላው ቤት የዶኑ ይሆናል ። ሶስተኛውን ደግሞ ጀንኮ አባንዳንዶ ከቤተሰቡ ጋር ይኖርበታል ። አራተኛው ለጊዜው ነጻ ሆኖ ይቆያል ። ዶኑና ቤተሰቡ ከአዲሱ ቤት በገቡ በሳምንቱ ፥ በአትክልቱ ውስጥ በመዝናናት ላይ የነበረውን ዶኑን የሆኑ ሰዎች ወደ ውስጥ አስጠሩት ። ዶኑ ሲመጣም ክረምት ሲገባ መላውን ቤት ከሚያሞቀው ማሞቂያ ዙሪያ ሆነው ማሞቂያውን ፈታተው ጠበቁት ።

"ማሞቂያህ በጥሩ ሁኔታ ላይ አይደለም ። እንድና

t.me/OLDBOOKSPDF

ስተካከልልህ ከፈለግክ አንድ መቶ ሀምሳ ብር መክፈል ይኖርብሀል፣” አሉት ።

ዶኑ ተገረመና ፣ “አንድ መቶ ሀምሳ ብሩን ባልከ ፍልስ ማሞቂያዬ ምን ይሆናል?” ሲል ጠየቃቸው ።

የሰዎቹ መሪ ትከሻውን ነቀነቀና ፣ “እንደተፈታታ ትተንልህ እንሄዳለና!” አለው ።

ዶኑ በለሆሳስ ፣ “ቆዩኝ እማ ፣ ገንዘቡን እከፍላች ኋለሁ” ብሏቸው ሶኒ ከሚገኝበት አትክልት ስፍራ አመራ ።

“ስማኝ ሶኒ ፣ ሰዎች ማሞቂያችንን እንሰራላችኋለን ብለው መጥተዋል ። የሚፈልጉት ነገር አልገባኝም ። ሄደህ አንድ ነገር አድርግ ፣” አለው ።

ይህ ጉዳይ ቀልድ አልነበረም ። ለአንድ ታዳጊ የስ ውር ንግድ ድርጅት ሰራ አስኪያጅ የሚቀርብ ፈተና ነበር ።

የሶኒ መፍትሄ አባቱን አላስደሰተውም ። የአንድ ሲሲልያዊ ብልህነት የጎደለው ድርጊት ነበር ። በዳኝነት ሰይፍ ሳይሆን በጡንቻ ፍልጥ ጉዳዩን ፈታው ። በመሳ ሪያ አስፈራርቶ ማሞቂያውን እንዲጠግኑ ካደረጋቸው በኋላ ፣ ሁለተኛ አይናችሁን እንዳሳይ ብሎ አባረራቸው ።

የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ከአካባቢው የፖሊስ ሀይል ጋር የስራ ግንኙነት ከፈጠረ ወዲህ የህዝቡን አቤቱታ የመ ስማት እድል አጋጠመው ። አንድ አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሎንግ ቢች ከተማ ከወንጀል ነጻ ሆነች ። ማን ኛውም አጥፊ በመጀመሪያ ለሚያደርሰው ጥፋት ማስ ጠንቀቂያ ይሰጠዋል ። ጥፋቱን ከደገመ ግን ድራሹ ይጠ ፋል ። በራሳቸው ተማምነው ማስጠንቀቂያውን ችላ ያሉ ወንጀለኞች ከሞት አፋፍ እስኪደርሱ ይደባደባሉ ። በዚህ አይነት ሰላም ሰፈነ ። ዶኑ በልጅነቱ ሳያጤነው ኖሮ ዛሬ አንድ እውነት ታወቀው ። ስለሆነም እሱን ለመሰለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው በድብቱ አለም ውስጥ ተገቢ ስፍራ ስለሚኖረው ወደዚያው ለመግባት ተገቢውን እርምጃ ወሰደ ።

ዶን ኮርሌዮኔ ሎንግ ቢች በሚገኘው ግቢው ውስጥ ሆኖ ግዛቱን እያጠናከረና እያስፋፋ በደስታና በሰላም ኖረ ። አንድ ቀን ግን ሶሎዞ በተባለ 'ቱርክ' በተመረ ጠብ ሰላሙ ተናግቶ እሱም ቆሰለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ አራት

ምእራፍ አስራ አምስት

በኒው ሃምፕሻየር በምትገኘው መንደር ማናቸውም አዲስ ነገር በቀላሉ ይጤናል ። የኒውዮርክ ታርጋ የተጸፈባት ጥቁር አውቶሞቢል ከነሚስተር አዳምስ ቤት ስት ደርስ ቆመች ። የኮሌጅ ምሁር ብትሆንም የትንሽ ከተማ አደግነቷ ያልለቀቃት ኬይ አዳምስ ከመኝታዋ መስኮት አኳያ እንግዶቹን ተመለከተች ። እንግዶቹ የመጡበት ስአት ለፈተናዋ ስታጠና ቆይታ ምሳዋን ለመብላት ወደ ታችኛው ክፍል ለመሄድ የምትዘጋጅበት ጊዜ ነበር ። እነዚህ ሁለት ሰዎች በራፉ ላይ አቁመው ከመኪናዋ ወጥተው ወደነኬይ ቤት ሲያመሩ ፥ 'ከሚካኤል የተላኩ ይሆናሉ' ብላ በመጠርጠር አባቷን ከማነጋገራቸው በፊት ቀድማ ተቀበለቻቸው ። አንደኛው ሰው ማንነቱን ለማሳወቅ መታወቂያውን እያሳየ ፥

"ከኒውዮርክ ፖሊስ መስሪያ ቤት የመጣሁ ነኝ ። የመረጃ ሰራተኛ ጆን ፊሊፕስ እባላለሁ ። ይህም ሰው የስራ ጓደኛዬ ሲሪያኒ ይባላል ፥" ብሎ ማንነታቸውን ካስታወቀ በኋላ ፥

"ኬይ አዳምስ የምትባይው አንቺ ነሽ ?" ሲል ጠየቃት ።

ኬይ እራሷን በአምንታ ነቀነቀች ። ፊሊፕስ ቀጠለና ፥ "መግባት እንችላለን? ለጥቂት ደቂቃ ስለ ሚካኤል ኮርሌዎኔ ልንጠይቅሽ እንፈልጋለን ፥" አላት ።

አስገባቻቸው ። ይህን ጊዜ አባቷ ብቅ አለና "ኬይ ፥ ምንድን ነው ጉዳዩ ?" ብሎ ጠየቃት ።

ኬይ የሀይማኖት ምሁር የሆነውን አባቷን ብዙ ባታውቀውም ግልጽ መልስ ለመስጠት አልፈራችም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እነዚህ ሰዎች ከኒውዮርክ የመጡ የደህንነት ሰራተኞች ናቸው ። ስለ አንድ የማውቀው ልጅ ሊጠይቁኝ ይፈልጋሉ ፣" አለችው ።

ሚስተር አዳምስ በጉዳዩ አልተደነቀም ። "ለምን ወደ እኔ ቢሮ አንገባም?" ሲል ጠየቃቸው ።

የመረጃ ሰራተኛ ፊሊፕስ ግን በትህትና ፣ "እዚሁ ሆነን ልጅትዋን ለብቻዋ ለማነጋገር እንፈልጋለን ፣" ሲል መለሰለት ።

ሚስተር አዳምስም በትህትና "ይህ እንግዲህ በኬይ ፈቃድ የሚወሰን ይመስለኛል ። ውዴ ፣ እነዚህን ሰዎች ብቻሽን ታነጋግሪያቸዋለሽ ወይንስ የኔን ወይንም የናትሽን መኖር ትፈቅጃለሽ?" በማለት ጠየቃት ።

ኬይ እራሷን ነቀነቀችና ፣ "ብቻዬን ባነጋግራቸው እመርጣለሁ ፣" አለችው ።

"እንግዲያውስ የኔ ቢሮ ገብታችሁ መነጋገር ትችላላችሁ ። ለምሳ ከኛ ጋር ትቆያላችሁ?" ሲል ጠየቃቸው ። ሰዎቹ እንደማይቆዩ አረጋገጡለት ። በዚህ ጊዜ ኬይ ወደ አባቷ ቢሮ መራቻቸው ።

የመረጃ ሰራተኛው ፊሊፕስ በመጀመሪያ ያቀረበላት ጥያቄ ባለፉት ሶስት ሳምንታት ውስጥ ሚካኤል ኮርሌዎኔን አይታው እንደሆነ እንድትገልጽለት ነበር ። ይህ ጥያቄ እንድትጠነቀቅ የሚጠቁማት ነበር ። የመላ ጋዜጦች አቢይ ርእስ ሆኖ የከረመው የኒውዮርክ ፖሊስ ሻምበል ማክለስኪ እና የአደንዛዥ እጽ ድብቅ ነጋዴ የቪርጂል ሶሎዞ መገደል ስለነበር በሰፊው እንብባዋለች ። ጉዳዩ የኮርሌዎኔን ቤተሰብ የሚነካካ መሆኑን ከጋዜጦች ተረድታለች ።

ስለዚህ ለቀረበላት ጥያቄ እራሷን በአሉታ በመነቅነቅ ፣ ሚካኤልን ያየችው ከአንድ ወር በፊት አባቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊጠይቅ ወደ ሆስፒታል በሄደበት ወቅት እንደነበር ነገረቻቸው ። ሌላው የመረጃ ሰራተኛ ጠንከር ባለ ድምጽ ከዚያ ወዲህ አይታው እንደሆነ ጠየቃት ። ኬይም አላየሁትም ብላ መለሰች ።

የመረጃ ሰራተኛው ፊሊፕስ በትሁት አንደበት "ከሱ ጋር ከተገናኘሽ እንድታስውቂኝ ። ሚካኤል ኮር ሌዎኔን ማነጋገር ይኖርብናል ። ከሱ ጋር ግንኙነት ካለሽ ሁኔታው አደገኛ ነው ። ከተባበርሽው ደግሞ የበለጠ አደገኛ ይሆንብሻል ፡" ሲል አስጠነቀቃት ።

ኬይ ቀጥ ብላ ተቀመጠችና ፡ "ለምን አልረዳውም? ልንጋባ ነው ። የተጋቡ ሰዎች እርስ በርሳቸው ይረዳዳሉ ፡" ብላ መለሰችለት ።

"ከረዳሽውማ በግድያ ወንጀል ላይ ተባባሪ መሆንሽ ነው ። ወዳጅሽን የምንፈልገው አንድ የፖሊስ ሻምበል እና አንድ የፖሊስ ጠቋሚ በመግደሉ ነው ። ገዳዩ ሚካኤል ኮርሌዋኔ መሆኑን እናውቃለን ።"

ኬይ ከት ብላ በሳቀችበት ወቅት ሁኔታዋ የመረጃ ሰራተኞቹን አስገረማቸው ።

"ማይክ እንዲህ ያለ ነገር አይሰራም ፡" አለቻቸው ። "ቤተሰቡ ውዝግብ ውስጥም የለበትም ። አስታውሳለሁ ፡ ለእህቱ ሰርግ አብረን በሄድንበት እለት እንደባእድ ነበር የሚያዩት ። አሁን ቢደበቅም በቤተሰቡ ጉዳይ ውስጥ ስሙ ታክሎ እንዳይወጣ ብሎ ነው እንጂ ማይክ ወንበዴ አይደለም ። እናንተ ወይም ሌላ ሰው ከሚያውቀው በላይ አውቀዋለሁ ። ግድያን የመሰለ አስነዋሪ ተግባር አይፈጽምም ። ከማንም የበለጠ ህግ አክባሪ እንደሆነ አውቀዋለሁ ። ሲዋሽም ሰምቼው አላውቅም ።"

የመረጃ ሰራተኛው ፊሊፕስ በእርጋታ ፡ "ለመሆኑ ፡ ለምን ያህል ጊዜ ታውቂዋለሽ?" ሲል ጠየቃት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከአንድ አመት በላይ ፥" ብላ ስትመልስለት ሁለቱም ሰዎች ተያዩና ፈገግ አሉ ።

"እንደሚመስለኝ ልታውቂ የሚገባሽ ጥቂት ነገሮች አሉ ።" አለ መረጃ ሰራተኛ ፊሊፕስ ። "የዚያን እለት ከአንቺ ተለይቶ አባቱን ሊጠይቅ ወደ ሆስፒታል በሄደ ጊዜ ከፖሊሶች ጋር ግጭት ፈጥሮ ነበር ። የፖሊሱን መኩንን ተጣልቶት አጸፋውን ተቀብሏል ። መንጋጋው ተሰብሮ ጥቂት ጥርሶቹንም አጥቷል ። በተከታዩ እለት የፖሊሱ ሻምበል ተገድሎ ሚካኤል ኮርሌዮኔም ተሰ ወረ ። ጠቋሚዎቻችን እንደገለጹልን ፥ ገዳዩ ሚካኤል ኮርሌዮኔ መሆኑን ተረድተናል ። ነገር ግን ፍርድ ቤት ነምናቀርበው መረጃ የለንም ። የምግብ ቤት አሳላፊውም ሆነ የሶሎዞ ሾፌር ሚካኤል እስካልተያዘ ድረስ ሊመሰክ ኑበት አልደፈሩም ። በየቦታው ተከታታይ ቢሰማራም ሊያገኘው አልቻለም ። ምናልባት አንቺ ልትረጂን ትችያለሽ ብለን ገምተን ነበር ።"

ኬይም በቀዘቀዘ አንደበት ፥ "ከተናገራችሁት አን ዱንም ቃል አላምንም" አለቻቸው ።

የማይክ መንጋጋ መሰበሩ እውነት ሊሆን እንደ ሚችል ብታምንም ፥ ነፍስ ለማጥፋት በቂ ምክንያት ይሆነዋል ብላ አልተቀበለችውም ።

"ከማይክ ጋር ብትገናኙ ለኛ ትነግሪናለሽ?" ሲል ፊሊፕስ ጠየቃት ።

ኬይ እራሷን ነቀነቀች ። ሲሪያኒ ጠንከር ባለ አነ ጋገር ፥ "የሆቴል ሪኮርዳችሁን መርምረን አብራችሁ መተኛታችሁን አረጋግጠናል ። ይህን ዜና ለጋዜጦች ብናስተላልፍ አባትና እናትሽ በጣም ይናደዳሉ ። እነ ሱን የመሰሉ የተከበሩ ሰዎች ልጃቸውን ከወሮበላ ጋር ትማግጣለች ብለው አይገምቱም ። ስለዚህ አቋምሽን ካላስተካከልሽ አባትሽን መጥራቴ ነው" አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኬይ ሰውዬውን በመገረም ተመልከታ አባቷን ለመጥራት በሩን ከፈተች ። ፒፓውን እየሳበ ከመስኮት አጠገብ ቆሞ የነበረውን አባቷን ፥ "አባባ ፥ ከእኛ ጋር ልትቀላቀል ትችላለህ?" በማለት ጋበዘችው ።

አባቷም ኬይን ትከሻዋን አቅፎ ከመረጃ ሰራተኞቹ ፊት ቆመና ፥ "ታዲያስ ጌቶቼ?" ሲል ተጋፈጣቸው። የመረጃ ሰራተኞቹ ዝም ሲሉ ፥ "በቀጥታ ንገረው እንጂ ፥" ስትል ሲሪያኒን ጋበዘችው ። ሲሪያኔ አፈረ ።

"ሚስተር አዳምስ ፥ ይህን የምነግርህ ለልጅህ ደህንነት ብዬ ነው ። ልጅህ ከአንድ የፖሊስ መኮንን ገንዘብ ተበሎ ከተጠረጠረ ወሮበላ ጋር ግንኙነት አላት ። ስለዚህ ከኛ ጋር ትብብር ካላደረገች ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቋ ነው ። እሷ ግን የሚደርስባትን ችግር የተረዳች አትመስልም ። ምናልባት አንተ ልታስረዳት ትችላለህ ፥" ሲል ሲሪያኒ ተናገረ ።

"ይህማ ሊሆን አይችልም ፥" አለ ሚስተር አዳምስ ።

"ልጅህ ከሚካኤል ኮርሌዎኔ ጋር ስትወጣ ከአንድ አመት በላይ ሆኗታል ። በባልና በሚስትነት ተመዝግበው ሆቴል አድረዋል ። ሚካኤል ኮርሌዎኔ ስለግድያው ጉዳይ ለፖሊስ ጥያቄ ይፈልጋል ። ልጅህ ግን ሊረዳን የሚችል መረጃ ልትሰጠን ፈቃደኛ አይደለችም ። አንተ የማይታመን ነው ብትልም ሀቁ ይህ ነው ።"

ሚስተር አዳምስም ፥ "የተናገርከውን ሀሰት አለበት ብዬ አልተጠራጠርኩም ። ሊሆን አይችልም ብዬ ያልኩት ግን እሷ በከፍተኛ ችግር ላይ ትወድቃለች ስላልክ ነው ። ምናልባት ለወንጀለኞች የምስጢር ሰላይ ካልሆነች ?" አለው ።

ኬይ አባቷን በአድናቆት ተመለከተችው ። ነገሩን በቀላሉ መመልከቱ በጣም አስገረማት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስተር አዳምስ ፍርጥም ብሎ ፥ "ይሁንና ፥ ያላችሁት ወጣት ከታየ በቶሎ አስታውቃችኋለሁ ። ልጄም እንዲሁ ። አሁን እንግዲህ ይቅርታ ብታደርጉልን ፥ ምሳችን እየቀዘቀዘ ነው ፥" ብሏቸው ሰዎቹን ሸኛቸው ።

ሚስተር አዳምስ ልጁን እጅዋን ይዞ ፥ "ነይ ልጄ ፥ እናትሽ ለምሳ እየጠበቀችን ነው ፥" አላት ። ግድቤቱ ሲደርሱ ባባቷ ሁኔታ ከሜንቀት በመገላገሏ በዝምታ ታለቅስ ነበር ። እናቷ ማልቀሷን ባትመለከትም ኬይ አባቷ ስለሁኔታው ያስረዳት መሆኑን ተገንዘበች ። እናቷ በጸጥታ ምግቧን አቀረበችላት ።

"ኬይ ፥ ይህን ተዋናይነትሽን አቁሚ ። ይህ ሁሉ ሜንቀት ለማይረባ ነገር እንደሆነ ይሰማኛል ። ከሁሉም በላይ ፥ ልጁ የዳርትስሙት ተማሪ ሆኖ ይህን በመሰለ አሳፋሪ ስራ አይገባም ፥" ስትል ሁልጊዜ ጽዱ የሆነችው እናቷ ተናገረቻት ።

ኬይ በመገረም ቀና ብላ ተመለከተቻትና ፥ "ማይክ ዳርትስሙት ኮሌጅ መማሩን እንዴት አወቅሽ ?" ብላ ጠየቀቻት ።

እናቷም በቸልታ ፥ "እናንተ ወጣቶች ነገር በመደበቅ ዘዴኛ የሆናችሁ ይመስላችኋል ። ከመጀመሪያ ጀምሮ ስለእሱ ተረድተናል ፥" አለች ።

"እንዴት አድርጋችሁ ልታውቁ ቻላችሁ ?" ስትል ኬይ ጠየቀች ።

የመረጃ ሰራተኞቹ ለአባቷ በነገሩት ሚስጥር ስላፈረች አባቷን ቀና ብላ አላየችውም ። እሱም ኮምጨጭ ብሎ ፥ "ደብዳቤሽን ከፍተን እናይ ነበር" ሲል መለሰላት ። ኬይ ከመደናገጧም በላይ ተቆጣች ።

"አባዬ ፥ ይህን አላደረግከውም ። እንደዚህ ልታደርግ አትችልም" አለችው ።

ሚስተር አዳምስ ፈገግ አለና ፥ "ከራሴ ጋር የት

t.me/OLDBOOKSPDF

ኛው የባሰ ሀጢአት ይሆናል በሚል ብዙ መግት አድርጌ ነበር ። ደብዳቤ መክፈት ነው ፣ ወይስ አንዲ ልጂ ሊደርስባት ከሚችለው አደጋ ራሴን መሰወሬ ነው ኃጢአት? ምርጫው ቀላልና ትክክለኛም ነበር ።"

"ከሁሉም በላይ ፣ ውዲ ልጂ ፣ ለእድሜሽ ገና ምንም የማታውቂ ነበርሽ ። መጠንቀቅ ነበረብን ። አንቺ ምንም ገልጸሽልን አታውቂም ፣" አለቻት እናትዋ ።

ኬይ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ ሚካኤል በደብዳቤው ላይ የፍቅር ዝባዝንኪ አለማሰፈሩ ደስ አላት ። እሷ የምት ጽፍለትን አንዳንድ ደብዳቤዎቿን ባለማየታቸው አመሰ ገነች ።

"ስለ እሱ ያልነገርኳችሁ ስለቤተሰቡ ሰምታችሁ ትደነግጣላችሁ ብዬ ነው ።"

"እሱማ መደናገጣችን አልቀረም ። በነገራችን ላይ ፣ ከሚካኤል ጋር ትገናኛላችሁ?" ሲል አባቷ ጠየቃት ።

ኬይ በአሉታ ራሷን ነቀነቀችና ፣ "አንዳችም ወን ጀል ሰርቷል ብዬ አልጠረጥረውም ፣" አለች ።

አባትና እናቷ እርስ በርሳቸው ተያዩ ።

"ምንም ጥፋት ሳይኖርበት ከጠፋ አንድ ነገር ሆኗል ማለት ነው ፣" አለ ሚስተር አዳምስ ። በመጀመ ሪያ ኬይ አልገባትም ፣ ኋላ ግን ተነሳችና ወደ መኝታ ቤትዋ ሮጠች ።

ከሶስት ቀን በኋላ ኬይ ወደ ኮርሌዮኔ ግቢ ደውላ በታክሲ ወደዛው አመራች ። ቶም ሄገን በሩ ላይ ሲቀ በላት ምንም ነገር ስለማይከ እንደማይነግራት በመግ መት ተስፋ ቆረጠች ። የምትጠጣው ነገር ሰጥቷት ሳለ በቀጥታ ሄገንን እንዲህ ስትል ጠየቀችው ፣

"ግይከ ያለበትን ታውቃለህ? እንዴት አድርጌስ ላገኘው እንደምችል ትነግረኛለህ?"

ሄገን በለሰለሰ አንደበት ፣ "ስለ እሱ የምናውቀው

t.me/OLDBOOKSPDF

ደህና መሆኑን ብቻ ነው ። ለጊዜው የት እንዳለ አናውቅም ። የሻምበሉን መሞት በሰማ ጊዜ ገደልከው ይሉኛል ብሎ ፈራ ። ስለዚህ መጥፋት አለብኝ ብሎ ወሰነ ። በጥቂት ወራት ውስጥ አድራሻውን እንደሚገልጽልኝ ነግሮኛል ፥" አላት ።

"ሻምበሉ በእርግጥ መንጋጋውን ሰብሮታል?"

"ይህስ እውነት መሰለኝ ። ነገር ግን ግይክ በቀ ለኛ አይደለም ። ሆነ በተባለው ነገር ውስጥ ግይክ እንደሌለበት እርግጠኛ ነኝ ።"

ኬይ ቦርሳዋን ከፍታ አንድ ደብዳቤ አወጣችና ፥ "ከግይክ ጋር መገናኘት ከቻልክ ይህችን ደብዳቤ ትሰጥልኛለህ?" ብላ ጠየቀችው ።

ሄገን እራሱን ነቀነቀና ፥ "ይህን ደብዳቤ ብቀበልሽና ለፍርድ ቤት ደብዳቤውን መቀበሌን ብትነግሪ ፍርድ ቤቱ ግይክ ያለበትን ቦታ የማውቅ አድርጎ ይገምታል ። ለምን ለጥቂት ጊዜ አትቆዪም? ግይክ አድራሻውን እንደሚነግረን እርግጠኛ ነኝ ፥" አላት ።

ኬይ የቀረበላትን መጠጥ ጨርሳ ተነሳች ። ሄገን እስከ በሩ ሲሸኛት በሩ ላይ አንዲት አሮጊት አየች ። አጭር ፥ ወፍራምና ጥቁር የለበሰችው አሮጊት የሚካኤል እናት መሆኗን ተረዳች ። እጅዋን ዘረጋችና ፥ "ሚሲዝ ኮርሌዎኔ ፥ ጤና ይስጥልኝ" አለቻት ። የአሮጊቷ አይን ለጥቂት ቅጽበት አትኩሮ ተመለከታትና ፥ በፈገግታ ፥ "እህ! የግይክ ጓደኛ!" አለቻት ።

አሮጊትዋ እንደገና ፥ "ለመሆኑ ምናምን በላሽ?" ብላ ኬይን ጠየቀቻት ። ኬይ ምግብ ለመብላት አለመፈለጓን ራሷን በመነቅነቅ ገለጸችላት ። ይህን ጊዜ አሮጊቷ ወደ ቶም ሄገን ዞር ብላ ፥ 'ዲስግራዚያ' ወይም ወራዳ በማለት ተቆጣችው ። ኬይን እጅዋን ይዛ ወደ ማድቤት መሰደቻትና ፥ "ቡና ጠጥተሽ ምናምን ትበይና ሹፌር

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤትሽ ያደርሰሻል ። አንቺን የመሰለች ልጅ በባቡር መሄድ የለባትም ፡፡” ብላ ኬይን አስቀምጣ ተፍ ተፍ ማለት ጀመረች ። በጥቂት ሰኮንድ ውስጥ ዳቦ ፡ እይብ ስጋ ከቡና ጋር አቀረበችላት ።

ኬይ በማፈር ፡ “የመጣሁት ስለማይክ ለመጠየቅ ነበር ። ከሱ ሰምቼም አላውቅ ። ሚስተር ሄገን ‘ማንም ስለ እሱ የሚያውቅ የለም ፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይመለሳል ፡’ ሲል ነገረኝ ፡፡” አለች ።

ሄገን ቶሎ ጣልቃ ገባና ፡ “እማማ ፡ ለጊዜው ልንገ ልጽላት የምንችለው ይህንኑ ብቻ ነው ፡፡” አለ ።

ሚስዝ ኮርሌዎኔ በንቀት ዝቅ አድርጋ ተመለከተ ችውና “አሁን ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ልትነ ግረኝ ነው ማለት ነው ፧ እንኳን አንተ ባሌም እግዜር ይቅር ይበለውና ‘እንዲህ አርጊ’ ብሎ መመሪያ ሰጥቶኝ አያውቅም ፡፡” ብላ አማተበች ።

“ሚስተር ኮርሌዎኔ ደህና ነው ?” አለች ኬይ ።

“ደህና ነው ። እያረጀ ነው ፡ እንዲህ ያለ ጅል ነገር ሲደርስበት” አለች ራሷን በጣቷ መታ መታ እያደረገች ።

ለኬይ ቡናውን ቀዳችላትና ዳቦዋን ከአይቡ ጋር እንድትበላ ጋበዘቻት ። ቡናቸውን ከጠጡም በኋላ የኬ ይን እጅ በሁለት እጅዋ ይዛ እንዲህ አለቻት ። “ሚኪ አይጽፍልሽም ። ከእንግዲህ ከሱ ምንም ነገር አትሰሚም ። ለሁለት ለሶስት አመት ይሰወራል ። ምናልባትም ከዚያ የበለጠ ግዜም ሊሆን ይችላል ። አሁን ቤተሰቦችሽ ዘንድ ሂጂና ፡ ጥሩ ወጣት መርጠሽ አግቢ ፡፡” አለቻት ።

ኬይ ደብዳቤውን ከቦርሳዋ አውጥታ ፡ “ይህን ደብዳቤ ትልኪለታለሽ ?” ብላ ጠየቀቻት ። አሮጊቷ ደብዳቤውን ተቀብላ የኬይን ጉንጭ በፍቅር መታ መታ አደረገችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በእርግጥ እልክልሻለሁ" ስትላት ሄገን ለመቃወም ሞከረ ። ይህን ጊዜ አሮጊቷ በጣልያንኛ ጮኸች በት ።

ሚስዝ ኮርሌዎኔ ኬይን ሸኝቻትና ስትሰናበታት ጉንጯን ሰማ ፥ "ሚኪን እርሽው ፥ ከእንግዲህ ላንቺ የሚሆን ሰው አይደለም ፥" አለቻት ።

ኬይ ከቤቱ እንደወጣች ተዘጋጅቶ የሚጠብቃት ልዩ መኪና ላይ ተሳፈረች ። አብረዋት የነበሩት አጃቢዎችም ሆኑ እሷ አንድም ቃል ሳይተነፍሱ ሞቴሏ ደረሰች ። ነገር ግን አንድ ቁም ነገር ተረዳች ። ያፈቀረችው ሰው ነፍሰ ገዳይ ነው ። ይህን ድርጊቱን ከማትዋሽው እናቱ አንደበት ሰምታለች ።

ምእራፍ አስራ ሰድስት

ካርሎ ሪዚ ኮኒን ካገባ በኋላ የጠበቀውን ያህል ሳይሆን በትንሽ የቁማር ንግድ ላይ ብቻ ተወሰነ ። ሎንግ ቢች ከሚገኘው አዲሱ የዶኑ ግቢ ውስጥ አንድ ቤት ይሰጡኛል ብሎ ሲጠብቅ አልተሰጠውም ። ካርሎ በግቢው ውስጥ መኖርን የፈለገው ስለቤቱና ስለክብሩ ብቻ ሳይሆን በዶኑ ቤተሰብ የውስጥ እንቅስቃሴ ጠልቆ ለመግባት እንደሚያስችለው በመገመት ጭምር ነው ። ዶኑ ከተከታዮቹ ቤተሰቦች አንዱን ከግቢ አስወጥቶ ካርሎ ሪዚን በምትክ ማስገባት አላቃተውም ። ነገር ግን አልፈለገም ።

'የኛ ታላቅ ዶን!' አለ ካርሎ በሆዱ ፥ ፌዝና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት 'እንደ አንድ የማይረባ ተራ ወንበዴ መንገዱ ላይ በጥይት የሚደፋ ትምክህተኛ ወንበዴ! በሞተ!' ብሎ ተመኘ ። ሶኒ የካርሎ የድሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጓደኛው ስለሆነ ፥ ሽማግሌው ቢሞትለት ሶኒ በምትኩ ሀላፊነቱን ሲረከብ እንደሚያስጠጋው ተስፋ አደረገ ።

ካርሎ ሚስቱ ቡናውን ስትቀዳለት ተመለከታት ። ያንተ ያለህ! በአምስት ወር የጋብቻ ጊዜ ውስጥ እንዴት ሆና ተነፋፍታለች !

ወደ ኮኒ ጠጋ ብሎ ቂጢን አሸት አደረገ ። ፈገግ አለች ። "ከተኮላሸ አሳማ የበለጠ ሰብተሻል ።" አላት ። ፊቷ ተለዋውጦ ስታለቅስ ደስ አለው ። የ'ታላቁ ዶን' ልጅም ብትሆን ሚስቱ ናትና እንደፈለገው ሊያደርጋት እንደሚችል ተሰማው ። አንድ የኮርሌዎኔን ቤተሰብ አባል እንደበሩ ላይ ምንጣፍ ሊረጋግጥ በመቻሉ ሀያ ልነት ተሰማው ።

ካሁን በፊት በሙሽርነትዋ ጊዜ የተበረከተላትን ግንዘብ ለብቻዋ ልታደርግ ብትፈልግም ፥ አይኗ እስኪ ጠቁር ጥፊ አልሷት ቀምቷታል ። ሌላ ቀርቶ ግንዘቡን የት እንዳደረሰውም አልነገራትም ። ይህን ደባ ቤተሰቡ ቢሰማ ችግር ይፈጠርበት ነበር ። ነገር ግን ካርሎ ይህን በማድረጉ ከቶውንም አልተጸጸተም ። አስራ አምስት ሺህ ብሩን ያህል በአልባሌ ቦታ በቁማርና በዝሙት ሲያባክን ምንም አልተሰማውም ።

ካርሎ ለኮኒ ጀርባውን ሰጥቷት እየተዝናና ካቀረበ ችለት ጣፋጮች ለማንሳት ሲንጠራራ የሚያደርገውን እያጤነች መሆኑን ተሰማው ።

በቂ ቁርስ ቢበላም ትልቅ ሰውነት ስለሚሰማው ከበድ ያለ ቁርስ መብላት አለበት ። ዛሬ እሱ እንደድሮው በግራሶ የተጨማለቀ ሰው ሳይሆን ጽዱና የተደላደለ ውብ ሰው ነው ። እንዲያውም ለዶኑ ቤተሰብ በተልእኮ ከተሰማሩት ከነክሌሜንዛና ከነቴስዮ ፥ ከነሮኮ ላምፖኔ ወይም ከዚያ የት እንደደረሰ እንኳን ያልታወቀው ፖሊ ጋቶ የተሻለ ጉልበት እንዳለው ይሰማዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካርሎ ቀጥሎም ሶኒ አእምሮው ውስጥ መጣ ። ሶኒ ትንሽ ከሱ ይበልጥ ግዙፍ ቢሆንም 'አንድ ለአንድ እቋቋመዋለሁ' ብሎ አሰበ ። ነገር ግን ምንም እንኳን ከበጉ ነገር በስተቀር ያየበት ክፋት ባይኖርም ስለ ሶኒ የሰማው ሀይለኛነቱ አስፈራው ። ይሁን እንጂ ፥ ሶኒ የሱ ወዳጅ ስለሆነ ምናልባት ሽማግሌው ከሞተለት እድል ይከፈትለት ይሆናል ።

ቡናውን በዝግታ ጠጣ ። ያለበትን ቤት ጠላው ። ሰፋ ያለ ቤት ነው የለመደው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የምሽቱን ቁማር ሊያወራርድ ወደ ቁማር ቤቱ ይሄዳል ። በተለይም እለቱ እሁድ ስለነበረ የቤዝቦል ጨዋታ ውድድር የተፋፋመበት ፥ የቅርጫት ኳስ የመጨረሻ ውድድር የሚካሄድበት ፥ እንዲሁም የፈረስ እሽቅድምድም የሚጀምርበት እለት በመሆኑ ከሌሎች ቀናት ይበልጥ ስራ ይበዛበታል ። በመጨረሻም ከሀሳቡ መለሰ ሲል ኮኒን ከጀርባው ስትንደፋደፍ አያት ።

አለባበሷ ደስ አላለውም ። በሀር ቀሚስ ላይ ቀበቶ ታጥቃ እይታ የሚጋብዝ አምባርና የጆሮ ጌጥ አድርጋለች ።

"የት አባሽ ልትሄጅ ነው ?" ሲል ጠየቃት ።

"አባቴን ለማየት እሄዳለሁ ። አሁንም ከመኝታው መነሳት ስላልቻለ አብሮት የሚሆን ሰው ያስፈልገዋል ።"

ካርሎ ፥ "አሁንም አዛዥ ሶኒ ነው ?" ሲል ጠየቃት ።

ኮኒም በቸልታ "የምን ማዘዝ ?" አለችው ።

ካርሎ ተናደደና ፥ "አንቺ አስቀያሚ ውሻ ! እንዲህ እንድትመልሽልኝ አልፈልግም ። አለበለዚያ በሆድ እቃሽ ያለውን ልጅ እንዳልነርተው !" አላት ።

ኮኒ ሁኔታው አስፈራት ። እሱም ፍርሀቷን አይቶ አንበሳ ሆነ ። ዘሎ ተነስቶ ፊቷን ሰንበር እስኪያወጣ ድረስ ወለወላት ። አሁንም አላበቃም ። ሶስት ጊዜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደጋግሞ በጥፊ ሲመታት የላይኛው ከንፈሯ ተሰንጥቆ ከመድማቱም በላይ አበጠ ። ይህን ጊዜ ዱላውን አቆመ ። ጠባሳ ለመተው አልፈለገም ነበር ። ኮኒ ወደ መኝታ ቤቷ ሮጣ በሩን ስትቆልፍ ሰምቷት ሳቀ ።

መልበሻ ሰአት እስኪደርስ ድረስ ቁጭ ብሎ ሲጋራውን ሲምግ ቆየና ኮኒ ወዳለችበት መኝታ ክፍል አመራ ።

"በሩን ሳልሰብረው ክፈችው! ልብሴን ልልበስ በት !" ሲል ጮኸባት ። ይህን ግዜ ከመኝታዋ ተነስታ በሩን ስትከፍት ሰማት ። ሲገባ ጀርባዋን ሰጠችው ።

ልብሱን ቶሎ ከለባበሰ በኋላ ቢመለከታትም አሁንም በውስጥ ልብሷ ነች ። ዘመዶቿ ጋ ሄዳ ወሬ እንድ ታመጣለት ይፈልግ ነበር ።

"ምን ሆነሻል ? አንድ ሁለት ጥፊ ስለቀመስሽ ጉልበትሽ ሁሉ ጠፋ እንዴ ?" አላት ።

"መሄድ አልፈልግም ፡" አለች እያለቀሰች ።

ፊቷን በግድ አዙሮ ሲመለከታት ባለመሄዷ ተስማማ። ከገመተው በላይ መቷት ኖሯል ።

"እሺ እንግዲያው ። ዛሬ ስራ ስለሚበዛብኝ ቶሎ አልመለስም ፡" ብሏት ወጣ ።

ደስ ብሎታል ። ቀበጥባጣይቱን ሚስቱን ጥፊ ማቅመሱ ተሰምቶት ከነበረው የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ገላ ግሎታል ።

መጀመሪያ ደብድቧት ሰምበር የታየባት እለት ስጋት አድሮበት ነበር ። በቀጥታ ሎንግ ቢች ሄዳ የጠ ቆረውን አይኗን ለእናትና አባቷ አሳየች ። ነገር ግን ተመልሳ ስትመጣ በሚያስደንቅ አኳኋን ትሁትና ትጉህ አይነተኛ ሚስት ሆና ነበር ። እሱም በበኩሉ ለጥቂት ሳምንታት ፍጹም ጥሩ ባል ሆኖ ጧት ማታ ፍቅር ሊለዋወጡ ሰነበቱ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከእንግዲህ አይለምደውም መስሏት ኮኒ የዚያን እለት የሆነውን አጫወተችው ። ኮኒ ወላጆቿ ጋ ለአቤ ቱታ በሄደችበት ወቅት እንደጠበቀችው ሊያባብሏትና ሊቆጩላት አልፈለጉም ። እርግጥ እናቲቱ ሁኔታው አሳ ስቧት አባቷ ካርሎን እንዲያነጋግረው ፊልጋ ነበር ። አባቷ ግን "እርግጥ ልጄ ናት ፥ ነገር ግን አሁን ሀላፊዋ ባሏ ነው ። ተግባሩ ምን እንደሆነ ያውቃል ። ሌላ ቀርቶ የጣልያን ንጉስም በባልና ሚስት ጉዳይ ጣልቃ አልገ ባም ። ስለዚህ ቤትሽ ሂጂና ባልሽ እንዳይደበድብሽ ሆነሽ ኑሪ" አላት ።

ኮኒም በንዴት ፥ "አንተ ሚስትህን መትተህ ታው ቃለህ?" ስትል አባቷን ጠየቀችው ። አባቷ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወዳት ስለነበር ለመናገር አልፈራችም ።

አባቷም ፥ "እናትሽ የሚያስመታ ጥፋት ሰርታ አታውቅም" ብሎ መለሰላት ። እናቷም እራሷን ነቀነ ቀችና ፈገግ አለች ።

ኮኒ ቀጥላ ባሏ ለሰርጓ እለት የተሰጣትን ገንዘብ ሙልጭ አድርጎ ወስዶ የት እንዳደረሰው እንኳ እንደ ማታውቅ ለእናትና ለአባቷ ገለጸች ። አባቷም ትከሻውን ነቀነቀና ፥ "እኔም ብሆን ሚስቴ እንዳንቺ ጋጠወጥ ብትሆን ኖሮ እሱ እንዳደረገው አደርግ ነበር ፥" ብሎ መለሰላት ።

በዚህ ሁኔታ ኮኒ ተደናግጣ እና ግራ ገብቷት ወደ ቤቷ ተመለሰች ። አባቷ በጣም ይወዳት ነበር ። አሁን ግን ለምን ቀዝቀዝ እንዳለ አልገባትም ። ነገር ግን እሷ እንደገመተችው አባቷ ጉዳዩ ሳይከነክነው ቀርቶ አል ነበረም ። ካርሎ ገንዘቡን ወስዶ ምን እንዳደረገው ደር ሶበታል ። ዶኑ የካርሎን የቁማር ንግድ እንቅስቃሴ እየተከታተሉ ለቶም ሄገን ዘገባ እንዲያቀርቡ ሰዎችን መደበ ። ከዚህ በተረፈ ግን ጣልቃ መግባት አልፈለ ገም ። አንድ የሚስቱን ወላጆች የሚፈራ ባል የባልነት

t.me/OLDBOOKSPDF

ተልእኮውን በምን መልክ መወጣት ይችላል? አስቸጋሪ ጉዳይ ነው ። ኋላም ኮኒ ስታረግዝ ጣልቃ ባለመግባቱ ተደሰተ ። ይሁን እንጂ አቤቱታዋ ስላልቀረ እናትዋ እንደገና ጉዳዩን ለባሏ አንስታለት ነበር ። እንዲያውም ኮኒ ፍቺ መፈለጓን ስትጠቁመው አባቷ በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቆጣት ።

"የልጅሽ አባት እኮ ነው ። አባት የሌለው ልጅ ምን እንደሚደርስበት ታውቂያለሽ?" አላት ።

ይህን ሁሉ በማወቁ ካርሎ የልብ ልብ ተሰማው ። በቁማር ቤቱ ውስጥ የሚሰሩት ሁለት አወራራጆቹ ደፋርነቱን እንዲያምኑለት ሚስቱን ያደረጋትን በጉራ አወራላቸው ።

ነገር ግን ቁጡው ሶኒ ይህን ሁኔታ በሰማ ጊዜ በቁጣ ሊገድለው ተነስቶ አባቱ እንደከለከለው ቢያውቅ ኑሮ ይህን ያህልም ባልተዝናና ነበር ። ሶኒ ካርሎ ሪዚን የሚርቀው ንዴቱ ተቀስቅሶ አደጋ እንዳያደርስበት በመፍራት ነው ።

ካርሎ ምንም እንደማይደርስበት በመተማመን ወደ ቁማር ቤቱ ሲያመራ በሌላ በኩል ሶኒ ኮኒን ሊጠይቅ ወደ ቤታቸው ሲሄድ አላየውም ነበር ።

ሶኒ ኮርሌዎኔ ከሉሲ ማንቺኒ ጋር ለመዳራት በሚ ወጣበት ወቅት አስፈላጊው ጥበቃ ይደረጋልታል ። እንደ ወትሮው ሁሉ ዛሬም በተለያዩ መኪኖች ሁለት አጃቢ ዎች ከፊቱ አስቀድሞ ሌሎች ሁለት ከኋላ አስከትሎ ወደሉሲ ዘንድ ሲያመራ እህቱ ኮኒ ትዝ አለችው ። ያ ካርሎ የሚሉት ርካሽ ዲቃላ እለቱ እሁድ በመሆኑ ቁማር ቤቱ ስለሚውል እህቱ ብቸኝነት እንደሚሰማት ስለገመተ ይዟት ሊንሸራሸር ፈለገ ።

አጃቢዎቹ ቀድመውት ከገቡ በኋላ ተከትሏቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

እህቱ ከምትናርበት ሰምንተኛው ፎቅ ሲያመራ በሊ
ፍት አልተጠቀመም ። 'ሊፍት የሞት ወጥመድ ነው'
ብሎ ያምናል ።

በሩን ሲያንኳኳ አንድ በፍርሀት የተዋጠ ድምጽ
ከውስጥ ሆኖ "ማነው?" ብሎ ሲጠይቅ ተሰማው ።
እንደማንኛውም የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ጠንካራና ሀይለኛ
የነበረችው እህቱ ይህን የመሰለ የፍርሀት ድምጽ ስታሰ
ማው ግራ ተጋብቶ ደነገጠ ። ምን ሁና ይሆን?

"እኔ ሶኒ ነኝ" ሲላት መቀርቀርያውን ስባ በሩን
ከፍታለት እያለቀሰች እቅፉ ውስጥ ገባች ። ሶኒ በመገ
ረም እዚያው ቆሞ ቀረ ። ወደዚያ ገፋ አደረጋትና ፊቷን
ተመለከተ ። ፊቷ ማበጡን ሲያይ ምን እንደሆነች አወቀ ።
እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ ባሏ ካለበት ለመሄድ ሲመነ
ጭቃት ጥብቅ አድርጋ ያዘችው ። ኮኒ የወንድሟን ግንፍ
ልነት በማወቋ በጣም ስለፈራች ማልቀሷን ቀጠለች ።
ካሁን ቀደምም ቢሆን ንዴተኛነቱን ስለምታውቅ ባሏ
የበደላትን ለሶኒ ነግራው አታውቅም ። ወደቤቷ እንዲ
መለስ አድርጋው ፥ "የራሴ ጥፋት ነበር ። እራሴ ነኝ
ድብድብ የጀመርኩት ። ልመታው ስሞክር ጊዜ ነው
የመታኝ ። በርግጥ እሱ ሊመታኝ አልሞከረም ። እኔው
እራሴ ነኝ ድብድብ ውስጥ ያገባሁት" አለችው ።

ሶኒ ከበፊቱ ቁጣው መለስ አለ ። "ሽማግሌውን
ዛሬ አትጠይቂውም?" ሲል ጠየቃት ።

ምንም መልስ ሳትሰጠው ሲቀር ንግግሩን ቀጠል
በማድረግ "ትጠይቂዋለሽ ብዬ ገምቼ ነበር ። ወደ ከተማ
ብቅ ስላልኩ በዚያው ልወስድሽ ነበር የመጣሁት"
አላት ።

ኮኒ እራሷን ነቅንቃ ፥ "ዘመዶቼ እንዲህ ሆኜ እን
ዲያዩኝ አልፈልግም ። የሚቀጥለው ሳምንት እመጣ
ለሁ ፥" አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"መልካም ። ሀኪም ይምጣና ይይሽ! ለመሆኑ ለመ ውለድ ስንት ወር ነው የቀረሽ?"

"ሁለት ወር ነው የቀረኝ ። ግን አደራህን አንድም መጥፎ ነገር እንዳትስራ ። እባክህ ምንም አታድርግ" ብላ ተማጠነችው ።

ሶኒ ሳቅ አለና ፥ "አይዞሽ ፥ ልጅሽ ሳይወለድ ያለ አባት አላስቀረውም" ብሎ ፥ ቀስ ብሎ ባልቆሰለው ጉንጭ በኩል ሳማትና ወጣ ።

የካርሎ የቁማር ንግድ መስሪያ ቤት በመሆን ከሚያገለግለው የጣፋጭ መሸጫ ሱቅ ፊት ለፊት መኪ ኖች በጥንድ መስመር ተኮልኩለዋል ። ከሱቁ ፊት ለፊት የእግር መተላለፊያ መንገድ ላይ በእሁድ ውርርድ ላይ ለመካፈል የመጡ ወላጆች ይዘዋቸው የወጡትን ልጅ ቻቸውን ያጫውታሉ ። ካርሎ ሪዚ መምጣቱን ሲያዩ ጨዋታውን አቆሙና ልጆቻቸው እንዳይንጫጩ አይስ ክሪም ገዙላቸው ። ከዚያም የሚወራረዱበትን አሸናፊ ለመወሰን እንዲያመቻቸው ቀድሞ የቤዝቦል ኳስ ለጊዎች እነማን እንደሆኑ ከጋዜጦች ላይ መመልከት ጀመሩ ።

ካርሎ ከሱቁ በስተጀርባ ወደሚገኘው ሰፊ ክፍል አመራ ። ኮችና ሳሊ ራግስ የተባሉ ሁለቱ የውርርድ መዝጋቢዎች የውድድሩን መጀመር ተዘጋጅተው ይጠባበ ቃሉ ። ውርርድ መመዝገቢያ ወረቀቶችን ከፊታቸው ከምረዋል ። በእንጨት መቆሚያ ላይ በተሰቀለ ጥቁር ሰሌዳ ላይ የአስራ ስድስቱ ታላላቅ ተወዳዳሪ የቤዝ ቦል ቡድኖች ስም ዝርዝር ማን ከማን እንደሚጫወት ተግ ልጾ ተጽፏል ። ከጥንድ ተወዳዳሪዎቹ ስም አኳያ ባለ አራት ማእዘን ሳጥን ውስጥ አንዱ ከሌላው ያለውን የግሸንፍ እድል ወይም አሸናፊው የሚያገኘው ጥቅም አጠፌታ መጠን ተጠቅሷል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካርሎ ኮች የተባለውን መዝጋቢውን ፥ "የሱቁ ስልክ ተጠልፎአል?" ሲል ጠየቀው ።

ኮች እራሱን ነቀነቀና ፥ "አሁንም ዝግነው" አለው።

ካርሎ ከግድግዳ ላይ ከተተከለ ስልክ መደወያ ሄዶ አንድ ቁጥር ደወለ ። ይህን ጊዜ ልብ ያላሉ መስለው ንግግሩን የሚያዳምጡ መዝጋቢዎቹ ካርሎ የሚጽፈውን በጥንቃቄ ይመለከቱ ነበር ። ካሁን ቀደም ካርሎ የመወራረጃ ሰንጠረዡን ሳያደላድል ባደረገው ስህተት ስድስት ሺህ ብር ኪሳራ እንደደረሰበት ዶኑ ሰምቷል ። ከዚያ ወዲህ ዶኑ በአማቹ ስራ ባለመርካቱ ስራውን የሚቆጣጠሩለት ረዳቶች አብረውት እንዲሰሩ አደረገ ።

ብዙውን ጊዜ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ዝርዝር ስራ ውስጥ ጣልቃ መግባት አይፈልግም ። በወትሮው አሰራር ከነሱ ጀምሮ አምስት ደረጃ ያላቸው የስልጣን ተዋረዶች ነበሩ ። ነገር ግን ለካርሎ የተሰጠው የቁማር ንግድ ችሎታውን መፈተኛ ስለነበር ፥ የየእለቱ ዘገባዎች በቀጥታ ለቶም ሄገን እንዲዳረሱ ተደርጓል ።

እንግዲህ ለውርርዱ እመች የሆነው ዝርዝር ስለ ወጣ ተወራራጆች ከጣፋጭ መሸጫ ሱቁ በስተጀርባ ከሚገኘው ክፍል ተኮልኮሉ ። አንዱ ለመወራረጃ ብዙ ገንዘብ የከፈለ ግለሰብ ግራ ቢገባው ይዚት የነበረችውን ትንሽ ልጁን ፥

"ሚሚዬ ከባህር ወንበዴዎችና ከጭራቆች ማን ያሸንፋል?" ሲል ጠየቃት ።

ትንሿም ልጅ ስሞቹ ስላስደነቋት "ጭራቆች ፥ ከባህር ወንበዴዎች ይበልጣሉ?" ብላ እንደገና አባቷን መልሳ ስትጠይቀው ከት ብሎ ሳቀ ። ቀጥሎ መዝጋቢው ይመዘግብና ገንዘቡን ጠቅልሎ ለካርሎ ያቀብለዋል ።

በመዝናኛ ህጐች መመሪያ መሰረት አንዳቸውም የእሁድ ጨዋታዎች ከስምንት ሰአት ቀድመው ተጀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምረው አያውቁም ። ስለዚህ የመጀመሪያዎቹ ተወራራጆች ፣ ማለትም ቤተሰባቸውን ወደ መዝናኛ የባህር ዳር ቻዎች ለመውሰድ የሚቸኩሉ አባወራዎች ፣ ቶሎ ተወራርደው ሲመለሱ ፣ ወንደላጤዎቹና ለቤተሰባቸው ጨርሶ ግድ የሌላቸው ይከተላሉ ። እነዚህ ተወራራጆች በብዙ ገንዘብ ይወራረዱና ለሁለተኛ ውርርድ ተመልሰው ይመጣሉ ። እነዚህ ናቸው የካርሎን ስራ እስከምሽት እንዲራዘም የሚያደርጉት ።

ስለዚህ ሰባት ሰአት ተኩል ሲሆን የተወራራጆች መንጠባጠብ ስለአበቃ ካርሎና ሳሊ ወደ ጣፋጭ ሱቁ ዘልቀው አየር ይቀበሉ ጀመር ። የፖሊስ መኪና አለፈች ። ችላ አልዋት ። የቁማር ቤታቸው ተገቢውን ጥበቃ ከአጥቢያው ፖሊስ ስለሚያገኝ በመኪናዋ ማለፍ ምንም አልተጨነቁም ። ኮች መጣና ከአጠገባቸው ተቀመጠ ። እዚያው ተቀምጠው ሳለ ስለ ቤስቦል እና ስለ ሴቶች አወሩ ። ካርሎ እየሳቀ ፣ "ሚስቴን ዛሬም እንደገና መታኋት" ብሎ ነገራቸው ። በነፍሰ ጡርነቷ ምክንያት ስጋታቸውን ሲነግሩት ጥቂት ጥፊ ብቻ እንጂ ብዙ እንዳልጐዳት ነገራቸው ። ይህን ጊዜ ከፊት ለፊታቸው ይጫወቱ የነበሩት ትንንሽ ልጆች ድንገት ተበታተኑ ። አንዲት መኪና ስትገሰግስ መጥታ ሲጢጥ ብላ ቆመች ። መኪናዋ በደንብ ከመቆሟ በፊት አንድ ሰው ከሹፌሩ መቀመጫ ተመንጥቆ በወጣ ጊዜ እዚያ የነበሩት ቡድን ጋጤ ደነዘዙ ። ሰውየው ሶኒ ኮርሌዎኔ ነበር ። ፊቱ እጅግ ያስፈራል ። ከመቅጽበት ካርሎ ሪዚን ጉሮሮውን አነቀውና ከሰዎቹ መሀከል ለይቶ አወጣው ። ጎትቶ ከመንገድ ዳር ሊያወጣው ፈልጐ ነበር ። ነገር ግን ካርሎ ጡንቻማ እጆቹን በበረንዳው ብረት ላይ ጠምጥሞ አልለቅ አለ ። በፍርሀት ሞብጥ ብሎ ራሱንና ፊቱን በትከሻው ውስጥ ለመደበቅ ሞከረ ። ሶኒ ጉትቶ ሊያስለቅቀው ስላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልቻለ ሸሚዙ ተቀዶ እጁ ላይ ቀረ ። ከዚያ በኋላ የተ
ከተለው ሁኔታ ደስ አይልም ። ሶኒ እየተራገመ በቡጢ
ደጋግሞ መታው ። ካርሎ ጉልበተኛ ቢሆንም ለመከላከል
ም ሆነ ለመጮህ አልሞከረም ። በኮች እና ሳሊ ግምት
ካርሎን ሊገድለው ወስኖ የመጣ ስለመሰላቸው የእሱ
እድል እንዳይገጥማቸው ጣልቃ ለመግባት አልደፈሩም ።
መንገዱ ላይ ይጫወቱ የነበሩት ልጆች ጨዋታቸውን
አቋርጠ የበታተናቸውን ሹፌር ሊሰድቡ ተሰባስበው
መጥተው ነበር ። ነገር ግን የድብድቡን ሁኔታ ሲመለከቱ
ምንም አላሉም ። በመሀሉም አንዲት መኪና መጥታ
እንደቆመች የሶኒ አጃቢዎች ከውስጧ ብቅ አሉ ። እነ
ሱም ጣልቃ ገብተው በመገላገል ፋንታ በአለቃቸው ላይ
ከገላጋዮች እንዳችም ጉዳት እንዳይደርስ ይጠባበቁ
ነበር ። ከሁሉም ደስ የማይለው የካርሎ ሙሉ በሙሉ
እጅ መስጠት ነበር ። ምናልባትም ነፍሱን ያዳነው
እጅ መስጠቱ ሳይሆን አይቀርም ። ያ ሁሉ ቡጢ ሲዘን
ብበት በትእግስት ተቀበለ ። ሶኒ የቁጣ ማእበሉ ጋብ
ሲልለት ፥ ''አንተ ወሰክ ዲቃላ! ሁለተኛ እህቴን ብት
ነካት እገድልሀለሁ'' አለው ። እነዚህ ቃላት ፍራቻ
ውን ሁሉ አስወገዱት ። ሶኒ ሊገድለው ቢሻ ኖሮ ይህን
ማስፈራሪያ ባልተናገረ ነበር ። ሶኒ በወቅቱ ካርሎን
እንዳይገድለው የሚያግዱት ነገሮች ስለ ነበሩበት እርር
ብሏል ። ካርሎ ቀና ብሎም ሶኒን አላየው ። እጁን ብረቱ
ላይ እንደጠመጠመ እራሱን ዝቅ አድርጎ የሶኒ መኪና
መሄዷን እስካረጋገጠና ኮች እንሂድ ብሎ እስከጠራው
ድረስ ባለበት ቆየ ። ቀና ብሎ ሲያይ ልጆች ከበው ይመ
ለከቱታል ። አመለካከታቸው አንድ የተዋረደን ሰው
በትዝብት እና በእፍረት እንደሚመለከቱት ነበር ።
ካርሎ ብዙ ቡጢ ቢቀምስም በጣም አልተጐዳም ።
ነገር ግን ምድሩ ስለዞረበት ኮች አቅፎ እየመራ ወሰዶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቁስሉ ላይ በረዶ አደረገለት ። ፍርሀቱ ቢጠፋም የውር ደቱ ስሜት አገረሸበት ። ኮች እራሱ ላይ ውሀ አድርጎ ሲያስተኛው የሳሊ ራግስን መሰወር አላጤነውም ነበር ። ሳሊ ስለ ሁኔታው ለመናገር ወደ ሮኮ ላምፖኔ ሄደ ። ሮኮ ላምፖኔም ዜናውን ለሻምበል አዛዥ ለክሌሜንዛ ደውሎ ነገረው ። ክሌሜንዛ በሁኔታው አጉረመረመ ።

"ያንተ ያለህ! ያ እርጉም ሶኒ አመሉ ተነሳበት!" አለ ፣ ሮኮ እንዳይሰማ ስልኩን ዘግቶ ። ክሌሜንዛ ወዲያውኑ ቶም ሄገን ደውሎ ነገረው ። ቶም ሄገን ለጥቂት ጊዜ ዝም ካለ በኋላ ፣ ሶኒ ሲመለስ መንገድ ላይ አደጋ እንዳይጥሉበት አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያደራጅ መመሪያ ሰጠው ። ነገር ግን ጠላቶቹም ሳይነቁ ሶኒ ተመልሶ ወደ ግቢ ሲገባ አባቱ በሀይለኛ ቁጣ ተቀበለው ።

ምእራፍ አስራ ሰባት

በ1947 በኮርሌዎኔ ቤተሰብና ባንድ ላይ በተነሱባቸው አምስት ቤተሰቦች መሀከል የተነሳው ጦርነት መጠኑ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ወጪ አስከተለ ። የሻምበል ማክለስኪን ገዳይ እንዲያወጡ ፖሊስ ያደረገባቸው ተጽእኖ ውዝግቡን አሰፋው ። የፖሊሱ ክፍል ሰራተኞች ለቁማርና ሽርሙጥና ንግድ የሚሰጡትን ከለላ በማንሳታቸው ለጊዜውም ቢሆን ስርአት አልበኝነት ሰፈነ ። ይህን የመሰለው ህጋዊ ከለላ ማጣት የኮርሌዎኔን ጠላቶች የጐዳውን ያህል እራሱን ኮርሌዎኔን አልጐዳውም ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ይመካበት የነበረ ዋናው የግቢ ምንጭ ቁማር ነበር በተለይ ከሁሉም በላይ ኪሳራ የደረሰባቸው የተለያዩ ሎተሪ ማውጫ ቤቶች ነበሩ ። ቁማር አጫዋቾቹ በፖሊስ ቁጥጥር ስር በመዋላቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

የቁማር ቤቶቹ ባለቤቶች አቤቱታቸውን ለኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሹሞች ቢያቀርቡም ፥ የተሰጣቸው መልስ ምንም ሊደረግ እንደማይቻል ነበር ። ስለዚህ ስራቸውን ለማቆም ተገደዱ ። ዋና የገቢ ምንጭ የሆነው የሀርለም አካባቢ ጥቁሮች ስራውን እንዲያካሂዱ ሲደረግ ፥ እነሱም የተበታተኑ በመሆናቸው ለፖሊስ ክትትል አላ መቸም ነበር ።

ከማክለስኪ ሞት በኋላ አንዳንድ ጋዜጦች ሻም በሉ ከሶሎዞ ጋር ያለውን ግንኙነት አትመው አወጡ ። እንዲያውም ማክለስኪ ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ከሶሎዞ ከፍ ያለ ገንዘብ መቀበሉን ማረጋገጫ አቀረቡ ። ይህን ሁሉ ዜና የሚያቀርብላቸው ሄገን ነበር ። የፖሊሱ ክፍል ይህን ሁኔታ ለማረጋገጥም ሆነ ለማስተባበል አልፈቀደም ። ይልቁንም የፖሊሱ ክፍል በጠቋሚዎች አማካኝነት የማክለስኪን ወሰላታነት ማረጋገጥ ቻለ ። በተለይም ከነፍሱ ግድያና ከአደንዛዥ እጽ ጋራ በተያያዘ ጉቦ የተቀበለ ሰው ከማንም የባሰ ፥ ይቅርታ የማይደረግለት በደለኛ ሆኖ በፖሊሱ ክፍል ይቆጠራል ።

ማንኛውም ፖሊስ ከሌላው ዜጋ ይበልጥ በሀግና በስርአት እንደሚያምን ሄገን ያውቃል ። ሀግና ስርአትን የግል ሀይሉን የሚያመነጭለት አስማት አድርጎ ይገምታል ። ይሁን እንጂ በሚያገለግለው ህብረተሰብ ላይ ዘወትር ቁጭት አለው ። የህብረተሰቡን አባላት በአንድ በኩል ጠባቂ ሆኖ ይጠብቃቸዋል ፥ በሌላ በኩል ደግሞ አዳኝ ሆኖ ያድናቸዋል እንደ አውሬ ። ህብረተሰቡ በተጠባቂነቱ ውለታ ቢስ ፥ አጥፊና ብዙ አገልግሉኝ ባይ ይሆናል ። በታዳኝነቱ ደግሞ አሚላጭ አደገኛና መልቲ ነው ። አንድ ሰው በፖሊስ እጅ በሚወድቅበት ወቅት ህብረተሰቡ ግለሰቡን ለማስጣል የፈጠረው ልዩ ልዩ ዘዴ በስራ ላይ ይውላል ። ፖለቲከኞቹ በልዩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ትእዛዝ ወይም በጉቦ ያስፈቱታል ። ዳኞች የመጨረሻውን አጥፊ በገደብ ተነስቶልሀል ብለው ይፈርዱለታል ። የበላይ ባለስልጣኖች ለአጥፊ ሙሉ በሙሉ ምህረት ያደርጋሉ ። ከጊዜ በኋላ ፖሊስ ትምህርት ይወስዳል ። እነዚህ አጥፊዎች የሚያቀርቡትን ጥቅም እሱስ ለምን አይቋደስም? እንዲያውም ከእነሱ ይበልጥ ጥቅሙ የሚያስፈልገው ለሱ ነው ። ለምን ልጆቹ ኮሌጅ አይማሩም? ሚስቱስ ብትሆን ለምን ሂዳ ከውድ ሱቆች አትሸምትም? እሱስ ቢሆን ለምን በክረምት እረፍት ወስዶ ፍሎሪዳን በመሳሰሉ መዝናኛዎች ጸሀይ ሞቆ ተደስቶ አይመለስም ? ቢታሰብበት እኮ ህይወቱን ለአደጋ የሚያጋልጠው እርሱ ነው ።

ነገር ግን ጉቦም ቢሆን የረከሰና ንጹህ የሚል መለያ ተበጅቶለታል ። ፖሊስ ቁማር ቤቶች ቁማር እንዲያጫውቱ ይፈቅድና ገንዘብ ይቀበላቸዋል ። አጉል ቦታ ያቆመ ወይንም ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ መኪና የነዳ አሽከርካሪ እንዳይቀጣ ፈልጐ ገንዘብ ሲሰጠው ይቀበላል ። ዝሙት አደሮች መተዳደሪያቸውን ሲያሳድዱ አይቃወማቸውም ። እነዚህ ሁሉ የሰው ልጅ በተፈጥሮ የሚያደርጋቸው ጥፋቶች ናቸው ። ነገር ግን አደንዛዥ እጽ መሸጥን ፥ በመሳሪያ አስፈራርቶ መቀማትን ፥ ሴቶችን በጉልበት መድፈርን ፥ ነፍስ ማጥፋትን ፥ ከተፈጥሮ ህግ የወጣ ግብረስጋን ለመሳሰሉት ወንጀሎች ጉቦ ተቀብሎ አጥፊዎቹ ከህግ እንዲሰወሩ አያደርግም ። እነዚህ ወንጀሎች የገዛ ስልጣኑን የሚፈታተኑ በመሆናቸው ፈጽሞ አያልፋቸውም ።

አንድን የፖሊስ ሻምበል መግደል ንጉስን የመግደል ያህል የከፋ ነው ። ነገር ግን ማክለስኪ የተገደለው ከአደንዛዥ እጽ ነጋዴ ጋር ባለው ግንኙነት የተነሳ መሆኑ ሲታወቅ ፥ እንዲሁም ነፍስ ለማጥፋት በመዶለት ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደነበረ ሲረጋገጥ ፥ የፖሊሱ ክፍል ለብቀላ የነበረው ፍላጐት እየከሰመ ሄደ ። ስለዚህ ጠበቅ አድርገውት የነበረውን የወንጀሉን አለም እንቅስቃሴ በማላላት ከሞቀው እንቅስቃሴ ምርት ላይ ድርሻቸውን መቋደስ ጀመሩ ።

የዶኑ የሆስፒታል ክፍል በግል የደህንነት ሰራተኞች እንዲጠበቅ የሚለው ሀሳብ የመነጨው ከቶም ሄገን ነበር ። በእርግጥ የቴስዮም ሰዎች ተገቢውን የጥበቃ ድጋፍ ይሰጣሉ ። ይህ ሁሉ ሶኒን ስላላረካው የካቲት ወር አጋማሽ ላይ ዶኑ በአምቡላንስ ወደ ቤቱ ተወሰደ ። መኝታ ቤቱ በአስፈላጊ የህክምና መሳሪያዎች ተሞልቷል ። በዶኑ ቤት ውስጥ ነርሶችና ዶክተር ኬኔዲ የተባለ ሀኪም ከፍተኛ አበል እየተከፈላቸው የህክምና እርዳታ ያደርጉለት ነበር ። ግቢውን ዘልቆ በመግባት አደጋ ለመጣል የማይደፈር ነው ።

ተከራዮች ለእረፍት እንዲሄዱ ተደርገው በምትካቸው ጠባቂዎች ገቡበት ። ፍሬድ ኮርሌዮኔ እንዲያገግም በዚያውም አካባቢ ቤተሰቡ የቋማር መጫወቻ ያለበት ትልቅ ሆቴል ለመግዛት ወይም ለመሥራት ይችል እንደሆነ ያጠና ዘንድ ወደ ላስ ቬጋስ ተላከ ። የላስ ቬጋሱ ዶን ለፍሬድ ጥበቃ እንደሚያደርግለት አረጋግጧል ። የኒውዮርክ ድብቅ አለም ቤተሰቦችም በአካባቢያቸው ያለው ችግር ስለሚበቃቸው ክልላቸውን አልፈው በላስ ቬጋስ ሌላ ጠብ ሊጭሩ አይሹም ።

ከዶኑ ጋር ምንም አይነት ውይይት እንዳይካሄድ ዶክተር ኬኔዲ ቢያስጠነቅቅም ይህ መመሪያ ፈጽሞ ተጥሷል ። ዶኑ በክፍሉ ውስጥ ጉባኤ እንዲካሄድ ስለፈለገ ሶኒ ፥ ሄገን ፥ ክሌሜንዛና ቴስዮ ገና በመጀመሪያ ምሽት ስብሰባ ማካሄድ ጀመሩ ። ዶን ኮርሌዮኔ ብዙ ለመናገር እጅግ የደከመ ቢሆንም ውይይቱን አዳምጦ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምናልባት አንዳንዱን ውሳኔ በድምጽ ለመሻር ፈልጓል። ፍራዲ ወደ ላስ ቬጋስ መላኩ ሲነገረው ስምምነቱን ገለጸ። የብሩኖ ታታሊያን መገደል ሲሰማ ግን እራሱን በቅሬታ በመነቅነቅ ተነፈሰ። ከሁሉ በላይ ቅር ያለው ሚካኤል ሶሎዞንና ማክለስኪን ገድሎ ወደ ሲሲሊ እንዲሸሽ መደረጉ ነበር። ይህን ሲሰማ 'ውጡልኝ' ብሎ ምልክት ስለሰጣቸው ጥለውት ከወጡ በኋላ ስብሰባቸውን ሌላ ክፍል ውስጥ ቀጠሉ።

"እንደሚመስለኝ ሽማግሌውን ለአንድ ሁለት ሳምንት ያህል ሀኪሙ የስራ ጉዳይ መነጋገር ይችላል ብሎ እስኪነግረን ድረስ እንዲያርፍ ብንተወው ይሻላል" አለ ሶኒ። "እስከዚያው ነገሮች ይቀጥላሉ። ፖሊሶችም ስራችሁን ቀጥሉ ብለውናል። በመጀመሪያ ሀርለም ያሉ ትላልቅ ቁማር ማጫወቻ ባንኮች መከፈት አለባቸው። ለጥቁሮች ተሰጥተው የነበሩትን ቁማር ቤቶች መልሰን እንውሰዳቸው። እነሱ እንደሆኑ ስራውን አበላሽተውታል። እነሱ በካዲላክ እየተንሸራሸሩ የውርርድ አሸናፊዎችን ገንዘብ ለመክፈል ቆዩ ይሏቸዋል። ወይም ግማሹን ብቻ ይከፍሏቸዋል። ማናቸውም አወራራጅ ሀብታምነቱ በልብስና በአዲስ መኪናው እንዲታወቅ አልሻም። ማናቸውም የቁማርን ንግድ ስራዬ ብለው ያልያዙ ግለሰቦች በስራው ላይ እንዲሰማሩ አልፈልግም። ስማችንን ያጠፉታል። ስራው መከፈቱን ሁሉም ሲረዳ ነገሮች መስመር ስለሚይዙ፥ ቶም አንተ ይህን ጉዳይ እንድታስፈጽም።"

ቶም፥ "ዛሬ ሀርለም ውስጥ አያሌ ሀይለኛ ልጆች አሉ። የቁማር ንግድ ጥቅም ጥሟቸዋል። ከእንግዲህ የቁማር ቤት ሰራተኛ ወይም ረዳት ባለቤት ለመሆን አይሹም፥" አለው።

ሶኒ ትከሻውን ነቀነቀና፥ "አንተ ብቻ ስማቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለክለሜንዛ ስጥልኝ ። እሱ ልክ ያገባቸዋል ፥" ሲል ፥ አጠገባቸው የነበረው ክሌሜንዛ ፥ "ችግር የለም ፥" በማለት አረጋገጠላቸው ። ቴስዮ አንድ ትልቅ ቁም ነገር አነሳ ። "የንግድ እንቅስቃሴአችንን አንዴ ከጀመርን አምስቱም ቤተሰቦች በባለቁማር ቤቶችም ሆነ በኛ አወራራጆች ላይ በልብስ ሸቀጥ ሱቆችም ቢሆን አስቸጋሪ ሁኔታ መፍጠራቸው ስለማይቀር ይህ ጦርነት ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ ይሆናል "

"መልሰን ጥቃት እንደምናደርስባቸው ስለሚገምቱ አያደርጉትም ይሆናል" አለ ሶኒ ። "የሰላም አዝማሚያቸውን ማወቅ የሚያስችል ጥናት እየተደረገ ነው ። ምናልባትም ስለተገደለው ልጃቸው ለታታሊያ ቤተሰብ ካሳ ከፍለን እርቅ ማድረግ እንችል ይሆናል "

"ለእርቅ በምናደርገው ሙከራ ሌላው ወገን ቀዝቀዝ ያለ ስሜት እያሳየ ነው" አለ ሄገን ። "ለደረሰባቸው አያሌ ክስረት እኛን ተጠያቂ በማድረግ ላይ ናቸው ፥ ያውም በፍርድ ። እንደሚመስለኝ ቤተሰባችን በፖለቲካ ያለውን ድጋፍ ተጠቅሞ ከእነሱ ጋር በአደንዛዥ እጽ ንግድ ላይ እንዲሰማራ ይፈልጋሉ ። ይህም ከሶሎዞ ድርድር ላይ ሶሎዞን መቀነስ ማለት ነው ። ነገር ግን በግልጽ ፍልሚያ እስኪጐዱን ድረስ ውይይት ለመጀመር ፈቃደኛ አይሆኑም ። ከዚያ በኋላ የኛን መላላት ተመልክተው ስለ አደንዛዥ እጽ ንግድ የሚያቀርቡልንን ሀሳብ በወግ እናዳምጣቸዋለን ብለው ያስባሉ "

"በአደገኛ እጽ ላይ አንዳችም ድርድር አናደርግም ። ዶኑ አይሆንም ብሏል ። እኛም ሀሳቡን እስካልለወጠ ድረስ በእምቢታችን እንቀጥላለን " ሲል ሶኒ በቁርጥ ተናገረ ።

"እንግዲያማ ታክቲካዊ ችግር ተደቅኖብናል ማለት ነው" አለ ሄገን ። "በቁማር የምናገኘው ገንዘባችን ለአደጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተጋለጠ ስለሆነ ልንመታ እንችላለን ። ነገር ግን የታታሊያ ቤተሰብ ሽርሙጥናን እና የወደብ ሰራተኞች ማህበርን ፥ ሌሎቹ ደግሞ አብዛኛውን የኮንስትራክሽን ንግድ ፥ያራጣ ብድር ፥ማህበራትን መቆጣጠርን እና የመንግስት ኮንትራት ማግኘትን ይዘዋል ። ንጹህንን በማስገደድ ጥቅም አግኝተዋል ። ገንዘባቸው የተጋለጠ አይደለም ። የታታሊያ የምሽት ክበብ ዝነኛ በመሆኑ ብንነካው ብዙ ነገር ያግማማል ። የዶኑ አመራር በሌለበት በአሁኑ ወቅት የእነሱም የፖለቲካ ግንኙነት ከእኛ ጋር ይፎካከራል ። ስለዚህ ከፍተኛ ችግር አለብን ”

“ይህ የኔ ችግር ነው ፥ ቶም ። መልስ አግኝለታለሁ ። ድርድሩ እንዲጀመር ሞክር ። ወደ ንግዳችን ተመልሰን የሚሆነውን እንመለከትና ከዚያ የምናደርገውን እናደርጋለን ። ከሌሚንዛና ቴስዮ ብዙ ወታደሮች አሉዋቸው ። አምስቱም ቤተሰብ አንድ ላይ ሆነው ቢነሱብን እንኳን በትጥቅ ትግል እንቋቋማቸዋለን ። ቢበዛ ፍረሻ እናካሂዳለን ” ሲል ሶኒ ቆራጥ አቋሙን አሰገነዘባቸው ።

በወቅቱ በአሜሪካ በተንሰራፋው የዘር መድልዎ ምክንያት ጥቁሮች ጉቦም ሰጥተው በቁማር ንግዳቸው ውስጥ መቆየት ስለማይችሉ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ በጊዚያዊነት ያሰራቸው የነበሩ የቁማር ንጋዴዎች ስራቸውን እንዲያቆሙ ለማድረግ ምንም አላደገተም ።

ነገር ግን አምስቱ ቤተሰቦች የመጡት ባልተጠበቀ አቅጣጫ ነበር ። ሁለት የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ወገን የነበሩ የልብስ ማህበር መሪዎች ተገደሉ ። የኮርሌዮኔ ቤተሰብ አራጣ አበዳሪዎችና አወራራጆች በባህሩ አካባቢ ስራቸውን ከማከናወን ታገዱ ። የወደብ ሰራተኞች ማህበር ከአምስቱ ቤተሰቦች ጋር ተቀላቅሏል ። የኮርሌዮኔ አወራራጆች ሽርክናቸውን እንዲለውጡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል ። አንድ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ

t.me/OLDBOOKSPDF

የጥንት ወዳጅ የሆነ የቱግር ባንክኛ በአሲታቲ ሁኔታ ተገደለ ። ከዚያ በኋላ ምንም አግራጭ አልነበረም ። ሶኒ ሻምበሎቹን ከነተከታዮቻቸው እንዲፈርሹ አዘዘ ። ሁለት አፓርታማዎችን ተከራይተው ምግብና ግቱዝቱዣ ጠመንጃና ጥይት አስገብተው ፍራሽ ሞሉዋቸው ። በአንደኛው አፓርታማ የክሌሜንዛ ጦር በሌላው ደግሞ የቴስዮ ገባበት ። የቤተሰቡ ቱግር ቤቶች ጥበቃ ተደረገላቸው ። የሀርለም የቱግር ባንከኞች ከድተው መደጠላት ጉራ ቢገቡም ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ይህ ሁሉ ለኮርሌዎኔ ቤተሰብ ከፍተኛ ወጭ አስከተለ እንጅ ምንም ጥቅም አልተገኘበትም ። ተከታዮቹ ጥቂት ወራት እንደተገባደዱም ሌሎች ጉዳዮች ግልጽ ሆኑ ። ዋናውም ጉዳይ የዶኑ ቤተሰብ ሀይል አቅም ከመጠን በላይ መግመቱ ነበር ። ለዚህ ምክንያት ነበረው ። ዶኑ በፍልሚያ ውስጥ ገብቶ አመራር ለመስጠት ገና በመሆኑ የቤተሰቡ የፖለቲካ ድጋፍ ሳስቷል ። በተጨማሪም ያለፉት አስር የሰላም አመታት የክሌሜንዛንና የቴስዮን የውጊያ ብቃት አላሽቀውታል ። በዚሁ ላይ ቶም ሄገን ምንም እንኳን ብልህ ቢሆንም ለጦርነት ወቅት ብቁ አማካሪ መሆን አልቻለም ። ዋናው ጉድ ሲሲሊያዊ አለመሆኑ ነበር ።

ሶኒ ኮርሌዎኔ ይህን ሁሉ ድክመት ቢገነዘብም ችግሩን ለማስወገድ የሚያስችለው እርምጃ መውሰድ አልቻለም ። ሶኒ ዶኑን መሆን አልቻለም ። ዶኑ ብቻ ነበር ሻምበሎቹንም አማካሪውንም መቀየር የሚችል ። በሌላ መተካት የሚለው ሀሳብ ደግሞ በጣም አደገኛ ነበር ። መከዳትን ሊያስከትል ይችላል ። በመጀመሪያ ዶኑ ስልጣኑን እስኪረከብ ድረስ የነበረው ሁናቴ እንዳለ ተጠብቆ እንዲቆየው ሶኒ አስቦ ነበር ። ነገር ግን የቱግር ባንከኞች መክዳት ፥ በአመራራጆች ላይ የደረሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

ማስፈራራት የቤተሰቡን ህልውና ጥርጣሬ ላይ ጣለው ። ስለዚህ ሶኒ መልሶ ማጥቃት እንዲካሄድ ወሰነ ። ነገር ግን መልሶ የማጥቃቱ ኢላማ በቀጥታ በጠላቱ ልብ እንዲሆን ነበር ። ባንድ ታላቅ ዘመቻ የአምስቱም ቤተሰቦች መሪዎች እንዲገደሉ ሶኒ እቅድ አወጣ ። ስለዚህ በነ ዚህ ሰዎች ላይ ከትትል ተካሄደ ። ከአንድ ሳምንት በኃላ ግን ተፈላጊዎቹ ሰዎች በአደባባይ መታየታቸው ቀርቶ አደፈጡ ። በዚሁ ሁኔታ የአምስቱ ቤተሰቦችና የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሳይሸናነፉ እንደተጠፋፉ ቀሩ ።

ምእራፍ አስራ ሰምንት

የአሜሪጐ ቦናሴራ መኖሪያ አስከሬን ከሚገንዝበት መስሪያ ቤቱ የሚርቅ አልነበረም ። ስለዚህ እራቱን ቤቱ ከበላ በኃላ ወደ ስራው ይመለሳል ። ሰዎች ስለሙያው እያነሱ በሚናገሩት ፌዝ ቅር ይሰኛል ። በርግጥ የቅርብ ወዳጆቹ በሙያው አያላግጡም ። ማናቸውም ሙያ የሰ ዎች መተዳደሪያ በመሆኑ ሊከበር ይገባል ።

አሜሪጐና ሚስቱ ልጃቸውን ከድንጋጤዋ እና ከሀመምዋ እንድታገግም ወደ ቦስተን አክስቷ ዘንድ ልከዋት በአፓርታማ ውስጥ ብቻቸውን ይኖራሉ ።

እራታቸውን ሲበሉ ሳለ ሚስቱ ፣ "ዛሬ ማታ ወደ ስራህ ትመለሳለህ?" ስትል ጠየቀችው ። እራሱን በአ ምንታ ነቀነቀ ። ሚስቱ ስራውን ታክብርለት እንጂ ምን እንደሆነ በሚገባ አልተረዳችውም ። ብቻ ሙታን በሚገ ነዙበት ወቅት ህያው እንዲመስሉ ስለሚያደርገው ጥበብ ተገቢው ዋጋ እንደሚከፈለው ታውቃለች ። አሜሪጐ ሬሳውን አሳምሮ መገነዝ ብቻ ሳይሆን ፣ ቀብሩ ከመፈጸሙ አስቀድሞ ባለው ምሽት ከሟች ዘመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶች ጋር አብሮ በማምሸት ያጽናናቸዋል ። ሙትን በመሸኘት ችሎታው ጠንካራና አጽናኝ ቢሆንም ፥ ፈቱ መራራ ሀዘን ስለምታሳይ ፥ ድምጹም ዝቅ ብሎ በአንድ ስልት እንድትጓዝ የማድረግ ብቃት ስላለው የሀዘኑን ስነ ስርአት በወግ ይመራዋል ። በዚህ ተግባሩ ላይ እን ቅፋት የሚሆኑትን ያወግዛል ። ነገር ግን ደምበኞቹን በዚያ ከፍተኛ የሀዘን ምሽት ምንም ቢሆን አይከሳ ቸውም ።

እንደወትሮው ሁሉ አሜሪጐ ራቱን ከበላ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይተኛል ። ከዚያ በኋላ ይነሳና ጺሙን ቱላ ጭቶ ፥ አፉን ተጣጥቦና አዲስ ጥቁር ልብስ ለውጦ ወደ ስራው ይመለሳል ። አሜሪጐ ሽበቶ ጸጉር ቢኖረውም በቀለም አጥቁሮታል ። የሽበቱ ንጣት ለስራው ተስ ማሚ አልመሰለውም ።

ምግቡን እንዳበቃ ሲጀራውን እያጨሰ ቡናውን መጠጣት ጀመረ ። ቡናውን ገና ከማብቃቱ ስልክ ጭርር ሲል ተሰማው ።

አሜሪጐ ስልኩን አንስቶ "ሀሎ" አለ ።

"ዶም ሄገን ነኝ! የዶን ኮርሌዎኔን መልእክት ላስ ተላልፍልህ ነው የምደውለው" አለው ።

አሜሪጐ መልእክቱ የዶኑ መሆኑን ሲሰማ ሆዱ ተሸበረ ። ዶኑ ዘንድ ሄዶ ሴት ልጁን የደበደቡትን ወጣቶች እንዲበቀልለት አመልክቶ ፍትህን ካገኘ አመት አልፏል ። እነዚያ ባለጌ ወጣቶች በዶኑ ተልእኮ ፈጸሚ ዎች ተደብድበው ፊታቸው ደም ብቻ ሆኖ በማየቱ እጅግ ደስ ብሎት ለዶኑ ማናቸውንም ውለታ ለመክፈል ለራሱ ቃል ገብቶ ነበር ። ነገር ግን የጊዜ ብዛት ውበ ትን ከሚያከስማት በበለጠ ፍጥነት የውለታን ደብዛ ያጠ ፋል ። ቦናሴራ መአት የወረደበት ሰው ስሜት ተሰማው ። እየተርበተበተ ፥ "ገብቶኛል ፤ እያዳመጥኩ ነው" ሲል

t.me/OLDBOOKSPDF

መለሰ ። በቶም ሄገን ድምጽ መቅዝቀዝ ተደነቀ ለወ
ትሮው አማካሪው ትሁት ነበር ። ዛሬ ግን ድፍረትና
ቀጥተኝነት በተመላበት አነጋገር ፥

"የዶኑ ውለታ አለብህ ፥" አለ ቶም ሄገን ። "እሱም
ውለታውን እንደምትከፍለው አይጠራጠርም ። አንተም
ውለታውን ለመክፈል እድል በማግኘትህ ደስ ሊልህ
ይገባል ። ከአንድ ሰአት በኋላ ዶኑ ራሱ በአስከሬን
ማዘጋጃ አዳራሽህ ይገኛል ። ከዚያ ሆነህ ተቀብለህ ሰላም
በለው ። ማንም ሰው እንዳይናር ፥ ሰራተኞችህንም
አሰናብታቸው ። ለዚህ ተቃውሞ ካለህ አሁኑኑ ንገረ
ኝና ለዶኑ ልግለጽለት ። ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰ
ጡት ሌሎች ወዳጆች አሉት "

አሜሪጐ ከድንጋጤ የተነሳ ሊጮህ ምንም አልቀ
ረው ። "እንዴት የጡት አባትን እምቢ እለዋለሁ ብለህ
ታስባለህ? ዶኑ የሚሻውን ማናቸውንም ነገር አደርጋ
ለሁ ። እዳዬንም አልረሳሁትም ። አሁኑኑ ወደ ስራ ቦታዬ
በፍጥነት እሄዳለሁ " ሲል መለሰለት ።

ይህን ጊዜ የሄገን ድምጽ ለዘብ አለ ። "አመሰግና
ለሁ ። ቀድሞውንም ቢሆን ጥርጣሬው የዶኑ ሳይሆን
የኔ ነበር ። ዛሬ ትእዛዙን ፈጽመህ ከዚያ በኋላ ማናቸ
ውም ጉዳይ ቢገጥምህ ወደ እኔ መምጣት ትችላለህ ። የኔንም
የግል ወዳጅነት ታገኛለህ "

ይህ አባባል አሜሪጐ ቦናሴራን ይበልጥ አስፈራ
ራው ። እየተንተባተበ "ዶኑ ራሱ ነው ዛሬ የሚመጣው?"
ሲል በመሸበር ጠየቀ ።

"አዎን"

"እንግዲያስ ፈጽሞ ተሸሎታል በሽታው ። እሰየው፣
ለፈጣሪ ምስጋና ይግባው ።"

ሄገን አሁንም "አዎን" ብሎ ከመለሰለት በኋላ
ስልኩ ተዘጋ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቦናሴራ በላብ ተዘፈቀ ። መኝታ ቤቱ ሄዶ ልብሱን ቀያይሮ ፣ ጺሙንም ሳይላጭ ከራባትም ሳይቀይር አፉን አደራረቀና ወደ አስከሬን ማዘጋጃ አዳራሹ ደወለ ።

ረዳቱ ስልኩን ባነሳ ጊዜ ከፊት ለፊት ካለው የሀዘንተኞች ማረፊያ ክፍል ከሀዘንተኞቹ ጋር እንዲቆይ አዘዘው ። ይህን ሲነግረው አሜሪጐ በበኩሉ በሬሳ ማዘጋጃ ክፍል ብቻውን እንደሚቆይ አስረዳው ። ይህን ጊዜ ረዳቱ ጥያቄ ለመጠየቅ ሲሞክር ፣ "እንደታዘዝከው አድርግ" ብሎ ስልኩን ዘጋበት ።

ልብሱን ለባብሶ ፤ ሚስቱን ስራ አለኝ ብሏት ፣ ለብቻው ወደተከለለው አስከሬን ማዘጋጃና የሀዘንተኞች ማስተናገጃ ግቢ አመራ ። ወደዚያ ሲያመራ ለቅሶ የሚደርሱ ሰዎች አስከሬን ለመሰናበት ወደዚያው ሲጓዙ አየ ።

አሜሪጐ ቦናሴራ ይህን ህንጻ ከአንድ በእርጅና ምክንያት ስራውን ካቆመ የሬሳ አዘጋጅ ላይ ከገዛ በኋላ ለደምበኞቹ ምቾት እንደሚስማማ አድርጐ አዘጋጅቶታል ። የህንጻው የኋላ ክፍል አንድ ቢሮ ፣ የአስከሬን ማዘጋጃ ክፍል ፣ የሬሳ ማስቀመጫ ግምጃ ቤት ፣ እንዲሁም አንድ ሬሳ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ቅመሞችና የእጅ መሳሪያዎች የሚቀመጡበት ክፍል የያዘ ሲሆን ፣ ከእንግዶቹ ማስተናገጃ ፣ ከአስከሬኑ መታያና ከአልቃሾች ማስተናገጃ አዳራሽ በአንድ ድምጽ በማያስተላልፍ ትልቅ በር ተለይቷል ።

ቦናሴራ ወትሮ በቢሮው ውስጥ የማያደርገውን ሲጋራውን እያጤሰ ዶን ኮርሌዮኔን መጠባበቅ ጀመረ ።

አሜሪጐ ዶኑ እንዲፈጽምለት የሚጠይቀው ውለታ ምን ሊሆን እንደሚችል ተሰፋ በመቁረጥ አሰላሰለ ። አመቱን በሙሉ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ከአምስት የማፊያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤተሰቦች ጋራ በጦርነት ማሳለፉን ፥ ከሁለቱም ወገን አያሌ ሰዎች ማለቃቸውን ፥ ከበርካታ ጋዜጦች አንብቧል ። እንግዲህ ዛሬ የዶን ኮርሌዎኔ ጥሪ አንዱን ትልቅ የጠላት ወገን ገድሎ የሬሳውን ደብዛ በማጥፋት በአስከሬን አዘጋጅነት ከታወቀው ቦናሴራ ህጋዊ ማረጋገጫ ለማግኘት እንደሚሆን ቦናሴራ ገምቷል ።

ይህን በመስራትም ቦናሴራ የሚፈጽመውን ህገ ወጥነት በቅድሚያ ተገንዝቦ የነፍስ ግድያ ተባባሪ መሆኑ ሲታወቅበት እስር ቤት ለአመታት ይማቅቃል ። ልጁና ሚስቱ ይዋረዳሉ ። መልካም ስሙ ከማፍያ ጦርነት ጋር በተያያዘ ይበከላል ። ሌላ ሲጋራ አቀጣጥሎ ሲያሰላስል ሳለ የበለጠ አሰቃቂ ሀሳብ በአእምሮው ውስጥ መጣበት ። የዶን ኮርሌዎኔ ጠላቶች የአሜሪጎን ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ጋር መመሳጠር ሲገነዘቡት በጠላትነት ይመዘግቡትና ይገድሉታል ። ይህ ሲታሰበው የጡት አባት ዘንድ ሄዶ የልጁን ደብዳቢዎች እንዲበቀልለት የተማጠነበትን እለት ረገመ ። ሚስቱና የዶን ኮርሌዎኔ ባለቤት የተዋወቁበትን እለት ረገመ ። ልጁንም ፥ አሜሪካንንም ፥ የተቃና ስራውንም ፥ ሁሉንም ረገመ ። ቀጥሎ ደግሞ በጐ አመለካከት ብልጭ አለበት ። ነገሮች ሁሉ መልካም ሂደት እንደሚኖራቸው ተስፋ አደረገ ። ዶን ኮርሌዎኔ ብልህ ሰው ነው ። ሁሉ ነገር በሚስጥር እንዲያዝ ስለሚያደርግ ቦናሴራ የሚጠበቅበት ወሬ ብቻ ነው ። ከማናቸውም ነገር የከፋ የሚሆነው ዶኑን ማስከፋት ብቻ ነው ።

በኮረኮንች መንገድ ላይ የጐማ ድምጽ ሲሰማ የኋለኛውን በር ከፈተው ። ግዙፉና ወፍራሙ ክሌሜንዛ ሁለት ሰዎች አስከትሎ ገባ ። ሰዎቹ ክፍሉን በዝምታ ከፈታተሹ በኋላ ክሌሜንዛ ወጥቶ ሄደ ። ሁለቱ ሰዎች ግን እዚያው ቆዩ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አምቡላንስ

t.me/OLDBOOKSPDF

መኪና በጠባቡ መንገድ ገባ ። ይህን ጊዜ ክሌሚንሳ ቃሬዛ የተሸከሙ ሁለት ሰዎች አስከትሎ መጣ ። አሜሪጐ ቦናሴራ የፈራው ደረሰ ። በቃሬዛው ላይ በግራጫ ብርድ ልብስ የተሸፈነ ሬሳ ተጋድሞ ተመለከተ ። የተሸከሙትን ሰዎች ወደ ሬሳ ማዘጋጃ ክፍል እንዲወስዱት ክሌሚንሳ ምልክት ሰጣቸው ። በመጨረሻም ከኋላ በኩል አንድ ሰው ወደ ቢሮው ዘልቆ ገባ ። እሱም ዶን ኮርሌዮኔ ነበር ።

ዶን ኮርሌዮኔ በሕመም ምክንያት ሰውነቱ ቀንሷል ፣ አረማመዱም ዘና ያለ አልነበረም ። ባርኔጣውን በጆሮ ይዟል ። በትልቅ ጭንቅላቱ ላይ ጸጉሩ ሳስቷል ። ቦናሴራ ዶኑን በልጁ ሰርግ ላይ ካየው ወዲህ አርጅቷል ፣ ተጨማዷል ፣ ግን ሀያልነቱ አሁንም በግልጽ ይታያል ። ባርኔጣውን በደረቱ ላይ አስደግፎ ፣

“መልካም የጥንት ወዳጄ ፣ ዛሬ ውለታ ልታደርግልኝ ፈቃደኛ ነህ ?” ሲል ጠየቀው ።

ቦናሴራ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ። ዶን ኮርሌዮኔ ሰዎችን እንዲወጡ ምልክት ሰጣቸው ።

ቦናሴራም በሹክሹክታ ፣ “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?” ሲል ዶኑን ጠየቀው ።

ዶኑ ወደ ጠረጴዛው ተመለከተና ፣ “የምትወደኝን ያህል ፣ ያለህን ሁሉ እውቀትና ችሎታ ሰራበት ። እናቱ በዚህ ሁኔታ እንደታየው አልሻም ፣” አለውና ወደ አስከሬኑ ቀርቦ ግራጫውን ብርድልብስ ገለጠው ።

አሜሪጐ ደነገጠ ። በመገነጣጠል ጠረጴዛው ላይ በጥይት ተበሳስቶ መልኩ የጠፋውን የሶኒ ኮርሌዮኔን ፊት ተመለከተ ። ግራ አይኑ ተበስቶ ጉድጉዷል ። አፍንጫውና የጉን አጥንቱ ተሰባብሮ አብጧል ።

ዶኑ ለቅጽበት ቦናሴራ ላይ ደገፍ አለና ፣

“ልጄን ምን እንዳደረጉብኝ ታያለህ?” አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምእራፍ አስራ ዘጠኝ

ሶኒ ኮርሌዎኔን ለራሱ መጥፋት ያበቁት በዚያ የሁለት ቤተሰብ ወገኖች ጦርነት ወቅት የተሳተፈ ባቸው እነዚያ በደም መፋሰስ የተሞሉ ግጭቶች ነበሩ ። ምናልባትም የጠበኛነት ባህርይው ያለልጓም መለቀቁ ይሆናል ። ያም ሆነ ይህ በነዚያ ወቅቶች ጭካኔ የተሞ ላበት ወረራ በጠላት ወገኖች ላይ አካሂዶ ነበር ።

በሀርለም የነበሩ የታታሊያ ቤተሰብ አቃጣሪዎ ችና ተልእኮ ፈጻሚዎች በየሜዳው በጥይት ተገደሉ ። ከታታሊያ ቤተሰብ ጋር ግንኙነት የነበራቸው የማህበ ራት መሪዎች ግንኙነታቸውን እንዲያቋርጡ ማስጠንቀ ቂያ ተሰጣቸው ። ይህን ጊዜ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ቁማር ቤቶች እና አራጣ አበዳሪዎች ስራቸውን እንዳይሰሩ መሰናክል ሲፈጠርባቸው ሶኒ ክሌሜንዛና ረዳቶቹን የበቀል ጥፋት እንዲያደርሱ ያሰማራቸዋል ።

ይህን የመሰለው ትርጉም የለሽ ጭፍጨፋ ለጦር ነቱ ውጤት አንዳችም ልዩነት የሚያመጣ አልነበረም ። እርግጥ ሶኒ ጐበዝ ታክቲከኛ በመሆኑ ደማቅ ድሎችን ተቀዳጅቷል ። ነገር ግን ተፈላጊው ይህ ሳይሆን የዶኑ ረቂቅ ስትራቴጂ ነበር ። መላው እንቅስቃሴ ጥፋት የተ መላበት የደፈጣ ሽብር በመሆኑ ሁለቱም ወገኖች አያሌ ጥቅሞቻቸውን አጥተው ብዙ ህይወትም ያለአግባብ ጠፋ ። በመጨረሻም የኮርሌዎኔ ቤተሰብ አንዳንድ አትራፊ የቁማር ቤቶቹን ፥ ለካርሎ ሪዚ ተሰጥቶት የነበረውን ጭምር ፥ ለመዝጋት ተገደደ ። ካርሎ ሪዚ መጠጥና ሴቶችን ማሳደድን በሰፊው ተያያዘው ። ሚስቱንም መከራ አሳያት ። ሶኒ ከደበደበው ወዲህ ደብድቧት ባያውቅም ፥ ከዚያን እለት ጀምሮ አብሯት ተኝቶ አያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውቅም ። ኮኒ እግሩ ላይ ወድቃ ብትለምነውም ይቅር ርታ በማድረግ ፋንታ በስቃይዋ ይደሰት ነበር ።

“ሂደሽ ወንድምሽን ጥሪውና ‘ከኔ ጋር ግብረ ስጋ አልፈጽም አለኝ’ ብለሽ ንገሪው ! ምናልባት ይደበድበኝና ስሜቴን ይቀሰቅስልኝ ይሆናል ፡” አላት ።

ነገር ግን ከዚያ ወዲህ ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ቢለዋወጡም ካርሎ ሶኒን እጅግ ፈርቶታል ። በእርግጥ ሶኒ በተፈጥሮው ባለው የአውሬነት ባህርይ ሊገድለው እንደሚችል ተሰምቶታል ። ስለዚህ ይህን የመሰለው የሶኒ አስፈሪ አውሬነት ካርሎን እጅግ እንዲጠላው አድርጐት ነበር ።

ቶም ሄገን እንደ አንድ አማካሪ የሶኒን አድራጎት ባይደግፈውም ተከታትሎ ተቃውሞውን ለዶኑ ለመንገር አልፈቀደም ። አምስቱ ቤተሰቦች ድል የተመቱ መሰለ ። በመጨረሻም ግጭቱ እንደቀጠለ የመከላከል ምታቸው ተዳክሞ በጠቅላላው አቆመ ። ይህን ጸጥታ ሄገን አላመነውም ። ሶኒ ግን ከመጠን በላይ ተደሰተ ።

“አሁንም ይበልጥ በማፋፋም በላዩ ላይ ጨምር በታለሁ ። ያኔም እነዚያ ዲቃሎች ለእርቅ ድርድር ይጣጠኑናል ” ሲል ሶኒ ሄገንን ነገረው ።

ሶኒ ሌሎች ነገሮች ያሳስቡታል ። ሚስቱ ሉሲ ግን ቺኒ የተባለች ሴት የባሏን ልብ መስረቋ በሰፊው ሲወራ ሰምታ ተቆጥታለች ። ስለባሏ ገላና ተራክቦ ያለማፈር በግልጽ የምታወራው ሚስቱ ፣ ያ ተሰጥዎው ለረዥም ጊዜ የተለያት በመሆኑ እየነዘነዘች ሰላም ነስታዋለች ።

በዚህ ላይ የጠላቶች ኢላማ በመሆኑ ጭንቀት ፈጥሮበታል ። ከወትሮው በበለጠ ሲገባ ሲወጣ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ። ከሉሲ ማንቺኒ ጋር ያለውን ግንኙነትም የጠላት ወገን ደርሶበታል ። ለዚህ እንኳን

t.me/OLDBOOKSPDF

ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጓል ። ሉሲ ሳታውቀው ሀያ አራቱን ሰአት ሙሉ ክትትል ይደረግባታል ።

ዶኑ እየተሻለው በመሄዱ በቅርቡ ሰልጣኑን ይረከባል ። በዚያ ወቅት የጦርነቱ ግእበል ለኮርሌዮኔ ቤተሰብ እንደሚያመች ሶኒ እርግጠኛ ነበር ። እስከዚያው የቤተሰቡን ግዛት ይጠብቅና ያባቱን አድናቆት ይቀዳጃል ። ያኔም የሶኒ ታላቅነትና ለሰልጣን ወራሽነት ብቁነቱ ይረጋገጣል ።

ነገር ግን ጠላት የራሱን ዘዴ እየቀየሰ ነበር ። የጠላት ወገኖች ሁኔታውን ተንትነው የተሟላ ድል መቀዳጀት የሚቻለው ሶኒን በመግደል ብቻ መሆኑን አምነው ወስነዋል ። በምክንያትና በእርጋታ በመደራደሩ ከታወቀው ዶን ጋር በዚያ ወቅት እርቅ ማድረግ እንደሚቻል ገምተዋል ። ሶኒን ግን ደም የጠማው አረመኔ በመሆኑ ጠልተውታል ። ይህ ጥሩ የንግድ አቋም አይደለም ። በምንም ምክንያት የጥንቱ ውዝግብ እና ችግር ተመልሶ እንዲመጣ አይሹም ።

አንድ ቀን አንዲት ስሟን ያልጠቀሰች ሴት ስልክ ስትደውል ኮኒ አነሳች ። "ካርሎን እፈልገዋለሁ ፥" በማለት ሴትየዋ ስትናገር ፥ ኮኒም ማንነቷን ጠየቀቻት ።

ሴትየዋም ፥ "እኔ የካርሎ ወዳጅ ነኝ ። ዛሬ ማታ ከከተማ ውጭ ስለምሄድ ከሱ ጋር ልንገናኝ እንደማንችል ልነግረው ነው የደወልኩት " አለች እየገለፈጠች ።

ኮኒ ፥ "አንች ቅማላም ዱር አዳሪ ውሻ" ብላ ጮኸችባት ። ስልኩን በላይዋ ላይ ዘጋችባት ።

ካርሎ በፈረሰ እሽቅድምድም ውርርድ ላይ በመበላቱ ስለተበሳጨ ጠጥቶ ቤቱ ገባ ። ገና ከመግባቱ ኮኒ እሪ ብላ በመጮህ እርግማኗን አወረደችበት ። እሱ ግን ችላ ብሏት ገላውን ሊታጠብ ገባ ። ከመታጠቢያ ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ከወጣም በኋላ ወደ ውጭ ለመሄድ ይለባበስ ጀመር ።
ኮኒ ወገቧን ይዛ በንዴት ፥

"ዛሬ የትም አትሄዳትም ፥ ወዳጅህ ደውላ ዛሬ አልችልም ብላሀለች ። አንት ቅማላም ዲቃላ! ለውሽሞችህ ስልኬን መስጠት ጀመርክ ደግሞ? እገድልሀለሁ ዛሬ!" አለችና ወደሱ ሮጣ ድብድብና መቧጨር ቀጠለች ።

በአንዱ ጡንቻማ እጁ ያዛትና ፥ "አብደሻል ፥" አላት በቀዘቀዘ ስሜት ። ነገር ግን ይህች በፍቅር ያበደች ወዳጁ ስሜቱን ለመሳብ እንዲህ ማድረጓ እንደማይቀር በመጠርጠሩ ስጋት እንዳደረበት ኮኒ ተረዳች ።

"ዝም ብላ ነው ፥ የምታቸፈችፍ እብድ ናት" አለ ካርሎ ፥ ኮኒን ለማዘናጋት ። እሷ ግን ይበልጥ በመናደድ እጁ ላይ ተጠምጥማ ፊቱን በመቧጨር አቆሰለችው ። የኮኒን ነፍሰ ጡርነት በመገንዘብ እንዳይጎዳት ተጠነቀቀ ። ይህን በመረዳትዋ ስሜቷን መቆጣጠር አልቻለችም ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ፥ ማለትም ልትወልድ ሁለት ወራት ሲቀራት ጀምሮ ፥ ምንም ፍትወተ ስጋ መፈጸም እንደ ማይኖርባት ሀኪም አስጠንቅቋታል ። ስለዚህ ያ ሁለት ወር ከመጀመሩ በፊት ካርሎን ተመኝታዋለች ። ያም ሆኖ ከንዴቷ ብዛት የተነሳ በአካሉ ላይ ጉዳት ለማድረስ ስለፈለገች ተከትላው መኝታ ክፍል ገባች ።

ካርሎ እንደፈራ ስለተረዳች የንቀት ደስታ ተሰማት ፥

"ዛሬ ቤት ነው የምታመሸው ። ወደ ውጭ ልትሄድ አትችልም ፥" አለችው ።

"እሺ ፥ እሺ" አላት ።

አሁንም ልብሱን ሳይለብስ በውስጥ ሱሪው ነው ያለው ። ደረቱ ሰፊ እና ወገቡ ጠባብ በሆነው ሰውነቱ ስለሚኮራ ቤት ውስጥ እንደዚያ ሆኖ መዘዋወር ይወዳል ፥ ኮኒ በጉጉት ተመለከተችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳቀና ፥ "ምናለ የምበላው ነገር እንኳን ብትሰ ጭኝ!" አላት ።

ይህ አባባል አገልግሎቷን እንድታበረክት የሚጋ ብዝ በመሆኑ ቀዝቀዝ አለች ። እናቷ አስተምራት ምግብ ስትሰራ ባለሙያ ናት ።

ኮኒ ለባሏ ምግቡን ስትሰራለት እሱ ዊስኪውን ካጠገቡ ሞልቶ የነገታውን የፈረስ እሽቅድምድም መጫ ለጫ ያነብ ጀመረ ።

ኮኒ ምግቡን ካዘጋጀች በኋላ ስትጋብዘው ወደ አልጋው ለመጠጋት የፈራች ይመስል ከመኝታ ቤቱ በራፍ ላይ ቆማ ፥

"ምግብ ተዘጋጅቶ ከጠረጴዛው ላይ ተቀምጦል ሀል" አለችው ።

"ገና አልራበኝም ፥" ሲል መለሰላት ።

"ጠረጴዛው ላይ ቀርቧል ነው እኮ የምልህ" አለች ድርቅ ብላ ።

"ቂጥሽ ላይ ለጥፈው ፥" አላትና ዊስኪውን እንደገና ሞልቶ ዘጋት ።

ኮኒ ወደግድ ቤቱ ሄዳ ምግብ የተመላባቸውን ሳህ ኖች ከእቃ ማጠቢያ ጋር አላተመቻቸው ። ይህን ከፍ ተኛ ድምጽ ሲሰማ ወደ ግድ ቤት መጣ ። ግድግዳው ሁሉ በወጥ ተበክሎ ሲያይ ጥንቁቅ የሆነው የጽዳት ስሜቱ ተነካ ።

"አንቺ ቆሻሻ ብልሹ ሰድ አደግ! በይ አሁን ሙልጭ አድርገሽ አጽጅው ። አለበለዚያ አርሽን ነው ግበላሽ" አላት ።

"ጀሀነብ ግባ!" አለችና ኮኒ እጅጉን የአሞራ ጥፍር አስመስላ ራቁት ገላውን ለመቧጨር ተዘጋጀች ።

ካርሎ መኝታ ቤቱ ገባና ቀበቶውን አጥፎ ተመለሰ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"በይ አሁን አጽድው ፥" አላት በቁርጥ ። ዝም ብላ ስትቆም ዳሌዋ ላይ ቀበቶውን አሳረፈው ። ግርፊያዋ አትጉዳም ፥ ግን ታማለች ።

ኮኒ ከግድ ቤቱ አንድ የዳቦ ቢላዋ አውጥታ ወደ ካርሎ አቃናችው ።

ካርሎ ሳቀና ፥ "ለካስ የኮርሌዎኔ ሴቶችም ነፍሰ ገዳዮች ናችሁ" ብሏት ቀበቶውን አስቀምጦ ወደርሷ ተጠጋ ። በድንገት ልትወጋው ስትሞክር ሆዷ እንደልብ አላንቀሳቅስ አላት ። ቢላዋውን ቀማትና በጥፊ ወለወላት ። እንዳትደማና ጠባሳ እንዳይኖራት እየተጠነቀቀ ደጋግሞ ደበደባት ። ልትነክሰው ስትሞክርም ጸጉሯን ጐትቶ ቀና አደረጋት ።

በመጨረሻ እንደ ህጻን ልጅ መጮህ ጀመረች ። ያኔ አልጋው ላይ ወረወራትና ዊስኪውን ተጋተ ። መስ ከሩን ስትመለከት ኮኒ ፈራች ።

ካርሎ እግሩን አንፈራጦ ዊስኪውን ከተጋተ በኋላ ሯኗን በእፍኙ ጨመደደው ። ጨመቅ አድርጎ ሲያሰቃ ያት እንዲለቃት ተማጠነችው ።

"እንደአሳማ ጮማ ብቻ ሆነሻል" አላትና መኝታ ቤቱን ጥሎ ወጣ ። በፍርሀትና በውርደት ተውጣ ባሏ የሚሰራውን እንኳን ቀና ብላ ለመመልከት መድፈር አቅቷት መኝታዋ ላይ እንደተጋደመች ቀረች ።

በመጨረሻ ተነስታ በመኝታ ቤቱ በር ቀዳዳ ስት መለከት ባሏ ሳሎን ውስጥ አዲስ ዊስኪ ከፍቶ ሶፋው ላይ ተኮፍሷል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከስካሩ ብዛት የተነሳ እዚያው እንቅልፍ ይወስደውና ሲተኛላት ቀስ ብላ ወደ ዘመዶቿ ስልክ ትደውላለች ። እናቷ ሰው ልካ እንድታስወስዳት ትነግራታለች ። ሶኒ ስልኩን እንዳያነሳ ብቻ ፈራች ። ማንጋገር የፈለገችው ቶም ሄገንን ወይም እናቷን ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከምሽቱ አራት ሰአት ነበር ። የዶን ኮርሌዎኔ ቤት ስልክ ሲያንቃጭል ፥ ስልኩን ያነሳው የዶኑ ጠባቂ ለኮኒ እናት አቀበላት ። ኮኒ ከንፈርዋ አባብሎ በወግ ለመናገር ባለመቻሏ ፥ እንዲሁም ባሏ እንዳይሰማት ቀስ ብላና በፍርሀት ትንጋገር ስለነበር ፥ ሚስዝ ኮርሌዎኔ ልጅዋ የምትናገረውን ማዳመጥ አቃታት ። ስለዚህ የዶኑን ጠባቂ በምልክት ጠራችና ከሄገን ጋር ሳሎን ተቀምጦ የነበረውን ሶኒን እንዲጠራላት አዘዘችው ።

ሶኒ ስልኩን እንደተቀበለ ፥

"አቤት ፥ ኮኒ" አላት ።

ኮኒ ባንድ በኩል ባሏ እንዳይሰማት ፥ በሌላ በኩል ሶኒ ከባሏ ጋር መጣላቷን እንዳያውቅ በማሰብ በጣም ስለተጨነቀች ድምጿ እየተበላሸ ሄደ ።

"ሶኒ ፥ ወደናንተ ዘንድ የሚያመጣኝ መኪና ብቻ ላክልኝ ። እዚያ መጥቼ እንግርሀለሁ ። ምንም አይደል ። አንተ አትምጣ ። እባክህ ቶምን ላከው ፥ ሶኒዬ ። ምንም የሆነ ነገር የለም ። ብቻ እናንተ ጋ ለመምጣት ፈልጌ ነው ።"

ይህን ጊዜ ሄገን መጣ ። ዶኑ አሁንም ገና ስላል ተሻለው ሄገን የሶኒን እንቅስቃሴ ይቆጣጠር ነበር ። ሁለቱ ዘቦችም እዚያው ናቸው ። ሁሉም ሰው ሶኒ እህቱ በስልኩ ስታወራው የሚሆነውን ይመለከታል ።

በሶኒ ተፈጥሮ ላይ የሚታየው የጠበኛነት ባህርይ ከአንድ ጥልቅና ድብቅ አካላዊ ምንጭ እንደሚመነጭ አያጠያይቅም ። በዚያ የነበሩት ሶኒን ሲመለከቱት ደሙ የአንገቱን ደም ስር እየገፋ ሲሮጥ ፥ አይኑ ጥላቻ ሲለብስ ፥ የተለያዩ የፊቱ ገጾች ሲኮማተሩና ሲገተሩ ፥ ቀጥሎም ሞትን የሚታገል በሽተኛ ይመስል ፊቱ ሲገረጣ ፥ እና እጁ ላይ ባሉት ደምስሮች የሚተላለፈው ፈሳሽ እጁን ሲያንቀጠቅጠው አዩት ። እንደዚያም ሆኖ ድምጹን እየተቆጣጠረ ፥ ዝግ ባለ ድምጽ ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"እዚያው ቆዪኝ። እንቺ ብቻ እዚያው ቆዪኝ፥" ብሏት ስልኩን ዘጋው።

ከንዴቱ ብዛት በመደናበር ለአፍታ ያህል ካለበት ቆመና፥

"ያ የውሻ ልጅ! የተንፋ የውሻ ልጅ" ብሎ ቤቱን ለቆ ወጣ።

ሶኒ በመናደዱ የማሰብ ችሎታው እንደተቃወሰ ሄገን ተረዳ። ነገር ግን ከተማ እስኪደርስ ንዴቱ ይበር ድለትና ነገሮችን ማመዛዘን ይችላል ብሎ ገመተ። ያ ማመዛዘን ግን ለራሱ መከላከል የተሻለ ብቃት ይሰጠው እንደሆን እንጂ ጥፋቱን ከማድረስ የሚመልሰው አልነበረም።

ሄገን የሶኒን መኪና ድምጽ ሲሰማ ሁለቱን ጠባቂ ዎች፥ "ተከተሉት፥" ብሎ አዘዛቸው።

ቀጥሎም ከተማ ከሚገኙት የሶኒ ሰዎች ዘንድ ደውሎ ወደ ካርሎ ቤት ገስግሰው ካርሎን ከዚያ እንዲ ያርቁትና ሶኒ እዚያ እስኪደርስ ኮኒን እንዲጠብቁት አዘዛቸው። ሄገን የሶኒን እርምጃ ማደናቀፉ ቢሆንም ዶኑ እንደሚደግፈው እርግጠኛ ነበር። ሶኒ ካርሎን በእ ማኝ ፊት ይገድለዋል የሚል ስጋት ነበረው። ከጠላት አደጋ ይሰነዘራል ብሎ አላሰበም። ምክንያቱም አምስ ቱም ቤተሰቦች ለብዙ ጊዜ ጸጥ ብለው ከመቆየታቸውም በላይ፥ ሰላም ፈላጊ መሆናቸውን ሄገን ገምቷል።

ሶኒ አውቶሞቢሉ ውስጥ ገብቶ ጥቂት እንደገሰገሰ ሃሊናውን ሲገዛ አጃቢዎቹ የሚከተሉት መሆኑን ተገነዘበ። ስለዚህ በጉዞው ላይ የሚያስፈራ ነገር ይኖራል ብሎ አልተጠራጠረም።

የተሳፈረበት መኪና በረዳቶቹ ስም የተመዘገበች ስትሆን በስውር ኪሷ ውስጥ ሽጉጥ ስላለ ለሚደርሰው ነገር ሁሉ ህጋዊ ውገግብ ውስጥ እገባለሁ ብሎ አል

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈራም ። ነገር ግን የመሳሪያ አስፈላጊነትም አልታየውም ነበር። ካርሎንም ቢሆን የሚያደርገውን አያውቅም ። ስለዚህ አእምሮው መለስ ሲልለት በጥቂት አለ መግባባት ምክንያት የእህቱን ልጅ ያለ አባት ሊያስቀረው እንደማይሻ ተገንዝቦታል ። ይህ እንኳን እንደ አነስተኛ የውስጥ አለመግባባት ብቻ ሊታይ አይገባውም። ካርሎ መጥፎ ሰው ነው ። ከኮኒ ጋር ያስተዋወቀው ሶኒ ነው ። ስለዚህ ሶኒ ሀላፊነቱ ተሰማው ።

ከሶኒ ሁከተኛ ባህርይ የሚያስደንቀው ሴት ወይም ህጻን ወይም እጅ የሰጠ ሰው መምታት አለመሻቱ ነው ። ለምሳሌ ሶኒ ካርሎን በደበደበው እለት ካርሎ መልሶ ለመደብደብ ባለመሞከሩ ሶኒ ሊገድለው አልፈለገም ። በልጅነቱ ርህሩህ ነበር ። ኋላ ነፍሰ ገዳይ ለመሆን የበቃው እጣው በመሆኑ ብቻ ነው ።

ያም ሆነ ይህ ካርሎ የሚያደርሰውን ችግር ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ እንዳለበት በአቋራጭ መንገድ ወደነኮኒ ዘንድ ሲጓዝ ታሰበው ። እሷን ወደ ቤታቸው ይልካትና ከካርሎ ጋር ብቻውን ይሆናል ። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ግን አያውቅም ። ያ ዲቃላ እህቱን ጐድቷት ከሆነ አካለ ስንኩል ያደርገዋል ። ነገር ግን ከባህሩ የሚነፍሰው ንፋስ ከቁጣው አበረደው ።

ካለመው ሰፍራ ለመድረስ ብዙ ተሽከርካሪዎች በማይበዙበት በባህር ዳር መዝናኛ መንገድ ሲበር ተከታዮቹን ጥሏቸው ርቋል ። ይህ ረግረጉን ታኮ ከፍ ብሎ የተሰራ የባህር ዳር መዝናኛ መንገድ በቂ መብራትም የለበትም ። ከሩቅ ሾል ያለ ጣራ ባለው ጎጆ ውስጥ በመንገዱ ላይ ከሚነዱ ሰዎች ገንዘብ የሚቀበል ሰው ቆሞ አየ ። ባለተሽከርካሪዎች የሚበዙት ቀን ቀን ነው ። ሶኒ ባካባቢው ሲደርስ ፍጥነት ቀንሶ ዝርዝር ሳንቲሞች ከኪሱ ቢፈልግ ስላጣ ከገንዘብ ቦርሳው ብር አወጣ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመብራቱ ስር ሲደርስ እንዲት መኪና ከገንዘብ መቀ
በያው አጠገብ መንገዱን ዘግታ ቁማለች ። አሽከርካሪው
አቅጣጫ ተሳስቶ ገንዘብ ተቀባዩን የሚጠይቅ ይመስ
ላል ። ሶኒ ጥሩምባውን ሲያሰማ ከፊት ያለው መኪና
ትእዛዙን በመቀበል ወደፊት ሲያመራ የሶኒ መኪና
መኧለኪያው ውስጥ ተሽጋሸገች ።

ሶኒ ብሩን ለተቀባዩ ሰጥቶ መልስ ሲጠባበቅ ከእት
ላንቲክ ውቅያኖስ የሚነፍሰው ንፋስ ብርዳም በመሆኑ
የመኪናውን መስኮት ለመዝጋት ተጣደፈ ። ያ ደንቆሮ
ገንዘብ ተቀባይ ግን እየተንቀጠቀጠ መልሱን ሲቆጥር
ሳንቲሞች ወደቁበት ። ገንዘቡን ለማንሳት ወደ ጎጆው
ዝቅ አለ ።

የፊተኛው መኪና መንገዱን በመቀጠል ፋንታ
ቆሟል ። በዚያን ወቅት በጐኑ በኩል በጭለማው ጎጆ
ውስጥ አንድ ሰው ቆሞ ተመለከተ ። ይህን ሁሉ ለማስ
ላሰል ጊዜም አላገኘም ። ከፊተኛው መኪና ውስጥ
ሁለት ሰዎች ወደሱ ሲመጡ አየ ። ገንዘብ ተቀባዩ
አሁንም አልመጣም ። ሶኒ ወዲያው ሚች መሆኑን ተረዳ ።
የተደበቀው ፍርሀቱ ከአምባገሮኝነቱ ያጸዳው ይመስል
በዚያች ቅጽበት እእምሮው የጠራ ነበር ። እንዲያም ሆኖ
ለማምለጥ ባደረገው የቅጽበት እርምጃ ግዙፍ ሰውነቱ
በሩን ጣሰው ። በጭለማዋ ጎጆ መሰል ከለላ ውስጥ የነ
በረው ሰው የከፈተበት ተኩስ እናቱን እና አንገቱን
አገኘው ። ይህን ጊዜ ሚዳ ላይ እንደተዘረረ ሌሎች ከፊቱ
የነበሩ ሁለት ሰዎች ከተኩሱበት በኋላ ፣ መልኩን
ለማበላሸትና ዱላቸው የአንድ ታላቅ ሀይል በትር መሆ
ኑን ለማሳየት ፊቱን በእግራቸው ጨፈጨፉት ።

ከጥቂት ሰከንድ በኋላ የሀለት ገንዘብ ሰብሳቢውና
ሶስቱ ገዳዮችም መኪናቸው ውስጥ ገብተው አመለጡ ።
የሶኒ አጃቢዎች ሲደርሱ ሁሉ ነገር አብቅቷል ። ለማሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደድም እንዳይችሉ የሶኒ መኪናና እሬሳ መንገዳቸውን ዘግተውታል ። ስለዚህ ተስፋ በመቁረጥ አዙረው ተመለሱና አንደኛቸው ወደ ቶም ሄገን በመደወል ፥ "ሶኒ ተገድሏል። ጀንስ መዝናኛ ባህር ዳር መግቢያ ላይ ነው የገደሉት" ብሎ ነገረው ።

ሄገን ምንም መሸበር በሌለበት ድምጽ ፥ "ከሌሚ ንዛ ቤት ሄዳችሁ ቶሎ ወደዚህ እንዲመጣ ንገሩት ። ከዚያ ምን እንደምታደርጉ እሱ ይነግራችኋል " አላቸው ።

ሄገን እግድ ቤቱ ነበር ስልኩን የተቀበለው ። ሚስዝ ኮርሌዎኔ ለኮኒ የምትበላው ለማዘጋጀት ስትን ደፋደፍ ነበር ። ሄገን ጸጥ ቢልም ምን ሆኖ ነው ብላ አሮጊቷ ለመጠርጠር አልሞከረችም ። መጠርጠር አቅቷት ሳይሆን ከዶን ኮርሌዎኔ ጋር ባሳለፈችው ህይወቷ ነገሮችን አለማሰላሰል መልካም እንደሆነ ተምራለች ። አሰቃቂ ጉዳይም ቢኖር ጊዜው ሲደርስ ትሰማዋለች ። ልትሰማው የማይገባት አሰቃቂ ዜናም ከሆነ ባትሰማው ይሻላታል ። የወንዶችን ስቃይ ባለመካፈልዋ ቅሬታ የላትም ። እነሱስ ቢሆኑ የሴቶችን ስቃይ ተካፍለው ያውቃሉ? ስሜቷ ምንም ሳይነካ ቡናዋን አፍልታ ጠረጴዛውን ምግብ እንዲበላበት አዘጋጀችው ። አሮጊቷ ባላት ልምድ ስቃይና ፍርሀት አካላዊ ረሀብን አይቀንሰውም ፥ በሷ ልምድ ምግብ መውሰድ ስቃይን ያደበዝዘዋል እንጂ ። አንድ ሀኪም በመድሀኒት ስቃይዋን ሊያስታግሰው ቢሞክር ትናደዳለች ፥ ቡና እና ቁራሽ ዳቦ ግን ለሷ ሌላ ጉዳይ ነው ። ከኋላቀር ሀብረተሰብ የመነጨች ናትና ።

ስለዚህ ቶም ሄገን ምንም ሳይል ወደ ሳሎን ሲሄድ ጥያቄ አላቀረበችለትም ። ኩምትር ብሎ የተቀመጠው ሄገን ከፍተኛ መሸበር ደረሰበት ። በጦርነት ወቅት ለሚገኝ ቤተሰብ ብቁ አማካሪ አለመሆኑን ተረድቷል ። እነዚህ አምስት ቤተሰቦች ጸጥ ያሉ መስለው በግድፈጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

አቂለውታል ፥ አወናብደውታል ። ተግባራቸውን በጥን ቃቄ በማቀድ ፥ በደል ቢሰራባቸውም ደም የጠማቸው እጆቻቸውን ሰብስበው በጸጥታ ተጠባበቁ ። ለካስ ይህ ሁሉ ትእግስት አንድ ከባድ በትር ለመሰንዘር እስኪ ችሉ ኖሯል ። ጥንቃቄ የተሞላበት እቅዳቸውም ግቡን መታ ። ሽማግሌው አባንዳንዶ ቢሆን ኖሮ ግን ይህን የመሰለ ስህተት ውስጥ ሳይገባ ጥንቃቄውን እጥፍ ድርብ በማድረግ ቀበኛ አይጥ የማሽተት ፥ አሽትቶም በጢስ የማፈን ችሎታውን የማሳየት ብቃት ነበረው ። ሄገን ይህ ሁሉ የሀዘን ስሜት ፈጠረበት ። ሶኒ ከሞት ያዳነው እውነተኛ ወንድሙና በልጅነታቸው እጅግ የሚያደንቀው ጓደኛው ነበር ። ሶኒ አንድም ቀን በብልግና ወይም በድፍረት ሳያስቀይመው በፍቅር ነበር ያስተናገደው ። ሶሎዞ ሄገንን ከጠለፈው በኋላ ሲለቀው ፥ ልባዊ ፍቅር በተሞላበት ደስታ ነበር ሶኒ ዘሎ እቅፍ ያደረገው ። ሶኒ ካደገ በኋላ ጨካኝ ፥ አምባገሮኛና ደም የጠማው መሆኑ በሄገን አይን ሶኒን የሚለውጠው አይደለም ።

ሄገን ለሚስዝ ኮርሌዎኔ የልጅዋን መሞት ለመንገር አለመድፈሩን ተረድቶ ማድቤቱን ለቆ ወጣ ። ዶኑን እንደ አባቱ ወይም ሶኒን እንደ ወንድሙ የሚመለከታቸውን ያህል አሮጊቷን እንደ እናቱ ተመልክቷት አያውቅም ። ለእሷ ያለው ፍቅር ከፍሬድ ከሚካኤልና ከኮኒ የተለየ አይደለም ። ይህም ፍቅር ደግነት ላሳየን ሰው የሚሰማን እንጂ ፍቅር ላላሳየን ሰው የሚሰማን አይደለም ። ነገር ግን ሊነግራት አልቻለም ። አሮጊቷ በጥቂት ወራት ውስጥ ወንድ ልጆቿን ሁሉ አጥታለች ። ፍሬድ ወደ ነቫዳ ተሰዷል ። ሚካኤል ህይወቱን ለማዳን በሲ ሲሊ ተደብቋል ። አሁን ደግሞ ሳንቲኖ ሞተ ። ከእነዚህ ከሶስቱ ማንኛቸውን ይበልጥ እንደምትወድ አሳይታ አታውቅም ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሔገን ራሱን ተቆጣጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረና ስልኩን አነሳ ። ወደ ኮኒ ቤት ደወለ ። ባሏን ማነጋ ገር ስለሚፈልግ እንድትቀስቅሰው ነገራት ። ኮኒም ፍር ሀት በተሞላበት የቀስታ ድምጽ ፥ "ቶም ፥ ሶኒ ወደ እዚህ እየመጣ ነው!" ስትል ጠየቀችው ። "አይ ፥ ሶኒ ወደ አንቺ አይመጣም ። አትስጊ ፥ ይልቁንስ ካርሎን ቀስቅ ሺና ለብርቱ ጉዳይ እንደምፈልገው ንገሪው" አለት ።

"እባክህ ይመታኛል ። ቤት መደወሌን ካወቀ እንደገና ይመታኛል"

"አያደርገውም ። ካነጋገረኝ በኋላ እንዲታረም አስ ጠነ ቅቀዋለሁ ። ምንም አትስጊ ፥ ይልቁንስ እጅግ ብርቱ ለሆነ ጉዳይ ስለምፈልገው መደስልኩ ይቅረብ" አላት ።

አምስት ደቂቃ ሊሆን ምንም ባልቀረው ጊዜ ውስጥ ዊሲኪና እንቅልፍ ያጐረነነው የካርሎ ድምጽ በስልክ ውስጥ መናገር ጀመረ ።

"ስማ ካርሎ ፥ አሁን የምነግርህ በጣም የሚያስደ ነግጥ ዜና ነው ። በጽሞና ለማዳመጥ ተዘጋጅ ። ለኮኒም የምነግርህን ሳይሆን ሌላ ወሬ ንገራት ። ቤተሰቡ ለካርሎ ትልቅ ስራ ለመስጠትና እናንተንም በግቢው ውስጥ እንድትኖሩ መወሰኑን ንገራት ። በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ሰዎች ሊወስዱህ ይመጣሉ ። እንደመጡ ካንተጋ ሆነው በስልክ እንዲያነጋግሩኝ ንገራቸው ። ሌላ ምንም ነገር አትበላቸው ። እንዳይወስዱህ ፥ እዚያው እንዲተዉህ እነ ግራቸዋለሁ ። ገብቶሀል የምልህ?"

"አዎን ገብቶኛል ፥" አለ ካርሎ ። ከሄገን ውጥረት የሞላበት አነጋገር እንደተረዳው ቀጥሎ የሚነገረው ዜና ከበድ ያለ እንደሚሆን በመገመት ካርሎ በጉጉት ተጠ ባበቀ ። ሄገንም በቀጥታ ገለጸለት ።

"ሶኒን ዛሬ ማታ ገድለውታል ። አንድም ሳትናገር በጸጥታ አድምጠኝ ። አንተ እንቅልፍ ወስዶህ ሳለ ኮኒ ደውላለት ስለነበር ወደ እናንተ ጋ ሲመጣ ነበር ። የኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥፋት ነው የሚል ጸጸት እንዳይሰማት አብረሀት አምሽ እንጂ ምንም ነገር እንዳትነግራት ። ቢያንስ እስክትመ ልድ ድረስ መልካም ባህርይ አሳያት ። ነገ ጧት ዶኑ ወይም እናቷ የወንድሟን መሞት ይነግሯታል ። አብረ ሀት ከጐኗ እንድትሆን እፈልጋለሁ ። ይህን ብትፈጽምልኝ እኔም ወደፊት እንከባከብሀለሁ ። ገባህ?"

ካርሎ ድምጹ እየተንቀጠቀጠ ፣

"እሽ ቶም ፣ ግድየለም ። ስማ እኔና አንተ እኩ ድሮም እንግባባለን ። ውለታህን አልረሳውም ። ገባህ የምልህ?"

"አዎን ገብቶኛል ። ያንተና የኮኒ ግጭት የሶኒን ሞት አስከተለ ብሎ የሚወቅስህ አይኖርም ። ስለዚህ አሁን እንደነገርኩህ ለኮኒ እንክብካቤ አድርግላት "

ቶም ሄገን ማናቸውንም አይነት ማስፈራራት በሰው ላይ መፈጸም እንደሌለበት ዶኑ አስተምሮታል ። ያም ሆነ ይህ ካርሎ መልእክቱ ደርሶታል ። ከሞት ያለው ርቀት እጅግ የጠበበ ነው ።

ሄገን ወደ ቴስዮ ደውሎ ምክንያቱን ሳይነግረው በአስቸኳይ ወደ ግቢ እንዲመጣ አዘዘው ።

ዋናው አስፈሪ ጉዳይ ከዚህ በኋላ ያለው ነው ። ዶኑን በመድሀኒት ሀይል እንቅልፍ ከተኛበት ቀስቅሶ ፣ በአለም ላይ ካሉት ነገሮች ሁሉ ይበልጥ የሚወደው ልጁ በአማካሪው ተገቢው ጥበቃ ሳይደረግለት በመቅ ረቱ ለሞት መብቃቱን ሊያረዳው ነው ። ሀመምተኛው ሽማግሌ በአስቸኳይ ወደ አመራር ላይ ካልተመለሰ ሁሉ ነገር ሊወድም መሆኑን መንገር ይኖርበታል ። ሄገን ራሱን አልደለለም ፣ ዶኑ ብቻ ነው ይህን ጦርነት በድል አድ ራጊነት መወጣት የሚችል ። ስለዚህ ሄገን ዶኑን ለማ ነጋገር ሀኪሞቹንም ማማከር አስፈላጊ ሆኖ አልታየውም ። አሳዳጊ አባቱ ሊሞት ነው ቢሉት እንኳን የወቅቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታ በግልጽ ነግሮ አመራሩን መቀበል ይኖርበታል ። ዶኑ ምን እንደሚያደርግ ጥያቄ አይኖርም ። አንድም ዶኑ ሁሉ ነገር ተገልጾለት አመራሩን መቀበል ይኖርበታል። አሊያም የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ለአምስቱ ቤተሰቦች እጁን እንዲሰጥ መወሰን ይኖርበታል ።

ሄገን መዘጋጀት አለበት ። በዚህ ወቅት ስለራሱ ጥፋት ማንሳትና ራሱን መውቀስ የዶኑን ሽክም ከመ ጨመር ሌላ ፋይዳ አይኖረውም ። የጦር አማካሪ ለመ ሆን ብቃት የሚያጥረው ሰው መሆኑን በመጠቆም የራሱን ጉድለት ቢናገር ዶኑ ይህን የመሰለ ሰው ለአ ማካሪነት በመምረጡ ራሱን እንዲወቅስ ያደርገዋል ። ስለዚህ ሁሉን ነገር ለዶኑ በቀጥታ መግለጽ አለበት ። መወሰድ ስላለበት እርምጃም የራሱን ትንታኔ ካቀረበ በኋላ የዶኑን ውሳኔ መጠባበቅ ነው ያለበት ። ዶኑ ሁን እንዳለው ይሆናል ። ዶኑ ጥፋተኛነቱን እንዲያምን ከፈ ለገው ጥፋተኛነቱን ያረጋግጣል ። ዶኑ ሀዘን የሚሻም ከሆነ ከልብ የመነጨ ሀዘኑን ያቀርብለታል ።

ይህን ሁሉ ሲያሰላስል በግቢው ውስጥ የመኪና ዎች ድምጽ ሰማ ። የሻምበል አዛዦቹ እየመጡ ነው ። ስለዚህ በቅድሚያ ሁኔታውን ባጭሩ ለነሱ ከገለጸ በኋላ ወደ ዶኑ ሄዶ ይቀሰቅሰዋል ። ተኝሳና መጠጥ ከተቀመጠባቸው መደርደሪያዎች ብርጭቆና ጠርሙስ አወጣ ። ሀሳቦችና ስሜቶች አሸንፈውት ፣ እጆቹ መጠጡን መቅዳት አቅቷቸው ፣ ላፍታ ቆም ብሎ ቆየ ። በስተጀ ርባው ያለበት ክፍል በር በቀስታ ሲዘጋ ሰማ ። ዞር ብሎ ሲመለከት ከተመታ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ልብ ሱን አሚልቶ የለበሰውን ዶን ኮርሌዮኔን አየ ።

ዶኑ ወደ ክፍሉ ዘልቆ ከቆዳ ከተሰራው ምቹ ወንበር ላይ ቁጭ አለ ። እንቅስቃሴው በጥቂቱ ቅልጥ ፍና የጐደለው ፣ ልብሱም በጥቂቱ የሰፋበት የሚመስለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶን በሄገን አይን እንደ ወትሮው ግርማው የተሟላ ነበር። ዶኑ በተዳከመው አካሉ ያካባቢን ተጽእኖ በራሱ ፈቃድ ፈጽሞ ያስወገደ መስሎ፥ ፊቱ የጥንቱን ሀይልና ጉልበት ተቀዳጅቷል። ቀጥ ብሎ ከምቹ ወንበሩ ላይ እንደ ተቀመጠ ሄገንን፥

"እስቲ ጥቂት አረቄ ስጠኝ" አለው። አረቄው በቤት የተሰራ፥ አንድ የዶኑ ወዳጅ የሚያቀርብለት፥ ሱቅ ውስጥ ከሚሸጡት አረቄዎች ጠንከር ያለ አልኮል ነው። ሄገን ከዚህ መጠጥ ለሁለቱም ቀዳ።

"ባለቤቴ ከመተኛቷ በፊት ታለቅስ ነበር። የጦር አዛዦቼ እኩለ ሌሊት ላይ ተሰባስበዋል። ስለዚህ፥ የኔው አማካሪ፥ ሰዉ ሁሉ የሚያውቀውን ነገር ልትነግረኝ ይገባሀል" አለ ዶኑ።

ሄገንም በጽሞና፥ "እማማን ምንም ነገር አልነገርኳትም። አንተ ዘንድ መጥቼም ቀስቅሼህ ዜናውን ራሴ ልነግርህ ነበር። ይህን ጊዜ ቀስቅሼህ ነበር" አለው።

ዶኑ ያለአንዳች የተለየ ስሜት፥ "ታዲያ እኔን ከማ ነጋገርህ በፊት በቅድሚያ መጠጥ አስፈልጦህ ነበር" አለው።

"አዎን"

"እንግዲያስ አሁን መጠጥህን ጠጥተሀል። ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"ሶኒን አውራ ጐዳና ላይ ተኩሰው ገደሉት"

ዶን ኮርሌዎኔ አይኑን አርገበገበ። ለቅጽበት ያህል መላ ስሜቱ ተናጋ። አካላዊ ጉልበቱ ከውስጡ ሲጠፋ ከፊቱ ላይ በግልጽ ታየ። ከዚያ በኋላ ግን ወዲያውኑ መልሶ አገገመ።

በጠረጴዛው ላይ እጆቹን ቆላልፎ በቀጥታ የሄገንን አይኖች ተመለከተና፥

"በል የሆነውን ነገር ሁሉ ንገረኝ" ካለ በኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዱን እጁን አንስቶ ፥ "ቆይማ ፥ ከሌሚንዛና ቴስዮ ይግቡ ። የምትነግረኝን መልሰህ ከምትደግም እነሱ ባሉበት ንገረኝ" አለው ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለቱ ሰዎች እየተመሩ ገቡ ። ዶኑ የልጁን መሞት እንደሰማ በአንድ ጊዜ ተረዱ ። ለጥንት ወዳጆች እንደሚፈቀደው አቅፈው ሳሙት ። ሁሉም ሄገን ከቀዳላቸው አረቄ ከጠጡ በኋላ ታሪኩን ነገራቸው ።

መጨረሻ ላይ ዶን ኮርሌዮኔ አንድ ጥያቄ ጠየቀው ፥

"የልጄ መሞት እርግጥ ነው ?"

"አዎን ፥" አለ ክሌሜንዛ ፥ "አጃቢዎቹ የሶኒ ሰዎች ይሁኑ እንጂ እኔ ነኝ የመረጥኳቸው ። ወደኔ ቤት በመጡ ጊዜ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር ። በትኬት መቁረጫው ቤት መብራት ሰውነቱን ተመልክተዋል ። በደረሰበት ቁስል በህይወት ሊቆይ አይችልም "

ዶን ኮርሌዮኔ ያለአንዳች መሸበር ቃላቸውን ከተቀበለ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ጸጥ አለ ። ከዚያም ፥ "ማንኛችሁም በዚህ ጉዳይ ውስጥ እንዳትገቡ ፥" አለ ዶኑ ፥ "ማናችሁም ብትሆኑ የብቀላ እርምጃ እንዳትወስዱ ። እንዲሁም ማንኛችሁም ብትሆኑ ከእኔ ትእዛዝ እስከ ደረሳችሁ ድረስ የልጄን ገዳዮች ለማወቅ አንዳችም ጥያቄ እንዳታካሂዱ ። በአምስቱ ቤተሰቦች ላይ አንዳችም የጦርነት እርምጃ ያለእኔ ትእዛዝ እንዳትወስዱ ። የልጄ ቀብር ስነስርአት እስከተፈጸመ ድረስ ቤተሰባችን አንዳችም የንግድ እንቅስቃሴ ወይም የንግድ ከለላ አያደርግም ። ከዚያ በኋላ ምን እንደምናደርግ እዚሁ ተሰብስበን እንነጋገራለን ። ዛሬ ማታ ግን ለሳንቲኖ የሚደረግለትን አሟልተን በስርአት እንቀብረዋለን ። ወዳጆቼ ከፖሊስና ከሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ጋር ሁኔታዎችን እንዲያደራጁ አደርጋለሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ክሌሜንዛ ፣ ከሰዎችህ ጋር ሆነህ እኔን ትጠብቃለህ ። ቴስዮ ደግሞ ሌሎቹን የቤተሰቤን አባላት ትጠብቃለህ ። ቶም ፣ አሜሪጐ ቦናሴራን ደውልለትና ዛሬ ሌሊት የሱን አገልግሎት እንደምሻ ንገረው ። እስራው ቦታ ይጠብቀኝ ። በአንድ ወይም በሁለት ወይም በሶስት ሰአት ጊዜ እሱ ዘንድ እደርሳለሁ ። ሁላችሁም ገባችሁ ?”

ሶስቱም ሰዎች በእሺታ ራሳቸውን ነቀነቁ ። ዶኑ ቀጥሎ ፣ “ክሌሜንዛ ፣ ሰዎችና መኪኖች አዘጋጅና ጠብቀኝ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቼ እነሳለሁ ። ቶም ፣ መልካም አድርገሀል ። ኮንስታንዚያና እናቷን ነገ ጧት እፈልጋቸዋለሁ ። ከባልዋ ጋር ግቢያችን ውስጥ ካለው ቤት እንዲገቡ አድርግ ። የሳንድራ ጓደኞችም ቤቷ ሄደው ይቆዩ ። ባለቤቴን ካንጋገርኳት በኋላ እዚያው ለሳንድራ ይህን አሰቃቂ ዜና ትነግራታለች ። ሴቶቹም ያስተዛዝኗታል ።”

ዶኑ ተነሳ ። ሌሎቹም ተነሱ ። ክሌሜንዛና ቴስዮ እንደገና አቅፈው ሳሙት ። ዶኑ በሩን የከፈተለትን ሄገንን ለአፍታ ያህል ተመለከተው ። ከዚያም እጁን ሄገን ጉንጭ ላይ አሳረፈና እቅፍ አድርጎት በጣልያንኛ “መልካም ልጅ ነህ ። እጽናናብሀለሁ ” አለው ። ይህ አባባል ሄገን በዚያች ቀውጢ ወቅት የሚገባውን እንዳ ከናወነ የሚያበስር ነበር ።

ዶኑ ሚስቱን ለማንጋገር ወደ መኝታ ቤቱ ሲሄድ ፣ ሄገንም በበኩሉ የቀብር ስነስርአት አዘጋጅ ከሆነው ከአሜሪጐ ቦናሴራ ዘንድ ደውሎ የዶኑን መልእክት ነገረው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ አምስት

ምእራፍ ሀያ

የሳንቲኖ ኮርሌዎኔ መሞት መላውን ድብቅ አለም አሸበረው ። ዶን ኮርሌዎኔ ከሀመሙ ድኖ የቤተሰቡን ተግባር ማመምራት ላይ መሆኑ በታወቀ ጊዜ ፣ በተለይ በሳንቲኖ ቀብር ስነ ስርአት ላይ የተላኩ ቃፊሮች የዶኑን ሙሉ በሙሉ ማገገም ለአለቆቻቸው ተመልሰው ባስታወቁበት ወቅት ፣ ዶኑ የልጁን ሞት ለመበቀል ሊወሰድ የሚችለውን እርምጃ በመፍራት አምስቱም ቤተሰቦች መደናገር የተሞላበት የመከላከል ዝግጅት አካሄዱ ። ዶን ኮርሌዎኔ ገና ለገና መጥፎ አጋጣሚ ደርሶበታልና በቀላሉ ሊገመት ይችላል የሚል ማንም አልነበረም ። በተግባሮቹ ላይ ጥቂት ስህተቶችን የፈጸመ ቢሆንም ከየአንዳንዶቹ ትምህርት ወስዷል ። ወደ አምስቱ ቤተሰቦች መልእክተኛ ልኮ ሰላም እንደሚሻ በገለጸላቸው ወቅት አላማው ምን እንደነበር የተረዳው ሄገን ብቻ ነበር ። ለአምስቱ ቤተሰቦች የቀረበላቸው የሰላም ጥሪ ብቻ ሳይሆን ተሰብስበው በጋራ ቅራኔአቸውን እንዲፈቱ ነው ። በኒውዮርክ የሚገኙት ቤተሰቦች ከሁሉም በላይ ሀይለኛ በመሆናቸው የነሱ ደህንነት መነካት የአገሪቱ ደህንነት መነካት መሆኑ ግልጽ ነበር ።

በመጀመሪያ ጥርጣሬ ነበር ። ዶን ኮርሌዎኔ ወጥመድ ሊያጠምድ ይሆን ወይስ ጠላቶቹን ከጥበቃቸው ሊያዘናጋ? የልጁን ሞት ለመበቀል መላ ጠላቶቹን ሰብስቦ ሊፈጅ መሞከሩ ይሆን? ይህ ሁሉ ጥርጣሬ እንዲወገድ ሀቀኛነቱን ለጠላቶቹ አረጋገጠ ። በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የድብቅ አለም ቤተሰቦች በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ከማድረጉም በላይ ፣ አንዳችም የማሳደድም ሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

የመመሳጠር ተግባር በሱ ወገኖች በኩል እንዳይካሄድ መመሪያ ሰጠ ። ቀጥሎም ይህ አላማው ማታለል የሌለ በት መሆኑን ለማረጋገጥ የመጨረሻውን የማይለወጥ እርምጃ ወስዶ የሚሰበሰበውን ታላቅ ጉባኤ ደህንነት አስ ተማማኝ አደረገው ። ለዚህም የቦኪኪዮን ቤተሰብ ትብብር ጠየቀ ።

በአንድ ወቅት በሲሲሊ በጣም አስፈሪ የነበረው ይህ የማፊያ ቅርንጫፍ በአሜሪካ የሰላም መሳሪያ ሆኗል ። የቦኪኪዮ ቤተሰብ በስጋ ዝምድና የተሳሰሩ አባላትን ያቀፈ የቤተዘመድ ቡድን ነው ። በጥቂት ወፍ ጮዎች የሚገኘው ገቢ ሁለት መቶ ለሚያክሉ የሶስት ዝርያ ቤተሰቦች መተዳደሪያ ነበር ።

የቦኪኪዮ ቤተሰብ ቀደም ሲል በአገራቸው በሲሲሊ አንዳችም ተወዳዳሪ ወፍጮ ወይም ለጠላቶቻቸው የሀ ይል ምንጭ ወይም የመጠጥ ውሀ የሚያስገኝ አሊያም የውሀ መሸጥ ስራቸውን ሊያደናቅፍ የሚችል ግድብ እንዳይቋቋም ይከላከሉ ነበር ። አንድ ሀይለኛ ባለርስት ለግሉ የሚጠቀምበትን ወፍጮ ሲያቋቁም አቃጠ ሉበት ። ባለርስቱ ለባለስልጣኖች በመክሰሱ ከቦኪኪዮ ቤተሰቦች ሶስት ሰዎች ታሰሩ ። የታሰሩት ሰዎች ገና ለፍርድ እንኳን ሳይቀርቡ በመሀከሉ የሹሙ መኖሪያ ቤት ተቃጠለ ። ከሳሹ የመሰረተውን ክስ አነሳ ። ከጥ ቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ አንድ የኢጣሊያን መንግስት ባለስልጣን የሲሲሊን ቋሚ የውሀ ችግር ለማስወገድ ግድብ እንዲሰራ ሀሳብ አቀረበ ። መሀንዲሶች ከሮም መጥተው ጥናት በሚያካሂዱበት ጊዜ የቦኪኪዮ ተወላ ጆች በጥላቻ ተቀበሉት ። ይሁን እንጂ የዚህን ግድብ መሰራት ምንም የሚያግደው ሀይል ሊመጣ እንደማይ ችል ስለተገመተ ለግንባታ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች በሙሉ ወደስፍራው ተጓጓዙ ። ነገር ግን የዚህ ግድብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስራ እድገት ከዚህ በላይ እልፍ አላለም ። ቦኪኪዮዎቹ ከሌሎች የማፊያ ሹሞች እርዳታ ጠይቀው ከፍተኛ ጥፋት አደረሱ ። በከባድ መሳሪያዎች ላይ አሻጥር ተሰራ ። አነስተኛዎቹ መሳሪያዎች ተሰረቁ ። በኢጣሊያ ፓርላማ ውስጥ የሚገኙ የማፊያ ተወካዮች ይህን የልማት እቅድ ባወጡት ሰዎች ላይ ቢሮክራሲያዊ ተቃውሞ ዘረጉ ። ነገሩ ሲጓተት ብዙ አመት ፈጀ ። በመሀሉም ሙሶሊኒ ስልጣን ያዘ ። አምባገነኑ ሙሶሊኒም ግድቡ እንዲሰራ ትእዛዝ ሰጠ ። ነገር ግን ግድቡ አልተሰራም ። ሙሶሊኒ የማፊያ ቡድን ለስልጣኑ አስጊ መሆኑን ስለተረዳ አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ስነ ስርአት ለሚያስከብርለት ለአንድ ከፍተኛ የፖሊስ ባለስልጣን ሙሉ ሀላፊነት ሰጠው ። ይህም ባለስልጣን ማናቸውንም ሰው እስር ቤት እየከተተና የቅጣት ስራ ወደሚሰራባቸው ደሴቶች እየላከ ችግሩን በቅልጥፍና ተወጣው ። በአጭር ጊዜም የማፊያን ሀይል ሰባበረው ። ይህንንም ያደረገው ማናቸውንም በማፊያ ቡድን አባልነት የተጠረጠረ ግለሰብ ያለፍርድ በማሰር ሲሆን ፥ በዚህ ወቅት በብዙ ንጹህ ቤተሰቦችም ላይ ጥፋት አድርሷል ።

ቦኪኪዮዎች ይህን ገደብ የሌለው ሀይል ሊቋቋሙት አልቻሉም ። ግማሾቹ በትጥቅ ትግሉ ላይ ሞተዋል ። ቀሪዎቹ ደግሞ የቅኝ ግዛት ከሆኑት የቅጣት ደሴቶች ተልከዋል ። እፍኝ የማይሞሉ ብቻ ቀርተው እነዚሁ በሚስጥር ወደ አሜሪካ ሊያመልጡ ቻሉ ። ኒውዮርክ አጠገብ በሀድሰን ሸለቆ ላይ የሰፈሩት ሀያ የሚያክሉ ስደተኞች ከመጨረሻው ዝቅተኛ ስራ ጀምረው ቁሻሻ ከከተማው የሚያነሳ ድርጅት አቋቋሙ ። ስራቸው ተወዳዳሪ የሌለበት በመሆኑ በቀላሉ ከበሩ ። ተወዳዳሪዎች ብቅ ብቅ ባሉ ቁጥር መኪኖቻቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

በማቃጠልና አሻጥር በመፈጸም ያስወግዷቸው ነበር።
አንድ ግትር ተፎካካሪ በቅናሽ ዋጋ ቆሻሻ የማንሳት
ተግባር ላይ በመሰማራቱ ታፍኖ ከተገደለ በኋላ ራሱ
በሰበሰበው ቆሻሻ ውስጥ ተጥሎ ተገኘ።

ወንዶቹ ሲሲሊያዊ ልጃገረዶችን አግብተው ልጅ
አፈሩ። የቆሻሻ ማንሳቱ ስራ ለመተዳደሪያቸው የገቢ
ምንጭ መሆኑ ባይካድም በአካባቢያቸው ለሚያዩ
ዋቸው ነገሮች መግዣ በቂ አልነበረም። ስለዚህ የቦኪኪዮ
ጐሳ የማፊያ ቤተሰቦችን ጦርነት ለማቆም በሚደረገው
የእርቅ ጥረት ላይ እራሳቸውን እንደመያዣ በማቅረብ
እና በአስታራቂነት በማሰማራት አዲስ ስራ ፈጠሩ።
ምናልባት በኋላ ቀርነታቸው ሊሆን ይችላል፥ ግን የቦ
ኪኪዮ ጐሳ የዋህነት ያጠቃዋል። ያም ሆነ ይህ አቅማ
ቸውን በማወቃቸው ጠለቅ ባለው ንግድ ውስጥ ግለ
ትም በሽርሙጥና፥ በቁማር፥ በአደንዛዥ እጽ እና የመንግ
ስት ሀብት በማጭበርበር ተሰማርተው የማፊያ
ቤተሰቦችን ሊወዳደሩ እንደማይችሉ ተገንዝበውታል።
ነገር ግን እነዚህ ቦኪኪዮዎች በጥበቃ ላይ ለተሰማራ
ግለሰብ ስጦታ ማበርከት የሚያውቁበትን ያህል ለባለ
ስልጣኖች መሸንገያ ገንዘብ የሚያደርስላቸውን ሰው
እንዴት እንደሚቀርቡት አያውቁበትም። በተፈጥሯቸው
ያሏቸው ሁለት ጸጋዎች ክብራቸውን መጠበቃቸውና
አስፈሪነታቸው ናቸው።

አንድ የቦኪኪዮ አባል አይዋሽም ወይም አሳልፎ
አይሰጥም። ይህን የመሰለው ባህርይ የተወሳሰበ ነው።
በዚህ ላይ አንድ የቦኪኪዮ ሰው ቂሙን አይረሳም።
የመጣው ቢመጣ ሳይበቀል አይተውም። ስለዚህ በአጋ
ጣሚ ይህን በመሰለው ጠቃሚ ስራ ላይ ለመሰማራት
ቻሉ።

ጦርነት ላይ ያሉ ቤተሰቦች ሰላም ለመመስረት

t.me/OLDBOOKSPDF

የእርቅ ድርድር በሚፈልጉበት ወቅት ከቦኪኪዮ ጐሳ ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ ። የጐሳው መሪ የእርቅ ድርድሩን በማስተባበርና ተገቢውን መያዣ ማለትም ሰዎች በማቅረብ ሁኔታዎችን ለእርቅ ያመቻቻል ። ለምሳሌ ሚካኤል ከሶሎዞ ጋር እርቅ ሊደራደር በሄደበት ወቅት ፥ ለደህንነት መያዣ የሚሆን አንድ ቦኪኪዮ ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ዘንድ እንዲቆይ ተደርጎ ነበር ። ሚካኤል ቢገደል ኖሮ በኮርሌዎኔ ቤተሰብ ውስጥ በመያዣነት የተቀመጠው ቦኪኪዮ ይገደል ነበር ። እንዲህ ከሆነ ቦኪኪዮዎች በሶሎዞ ምክንያት ወገናቸው ስለተገደለባቸው በሶሎዞ ላይ በቀል ይወስዱበት ነበር ። ቦኪኪዮዎች ኋላ ቀር በመሆናቸው ማናቸውንም የብቀላ እርምጃቸውን የሚያደናቅፍ ነገር አይቀበሉም ። አምነው የሰጡትን ህይወት አሳልፎ ለሰጠባቸው ሰው ከለላ መስጠት የሚችል ምንም ሀይል አይኖርም ። የቦኪኪዮ መያዣ አስተማማኝ የሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ዋስትና ነው ።

ስለዚህ ዶን ኮርሌዎኔ ቦኪኪዮዎችን በአስታራቂነት ቀጥሮ ለየአንዳንዱ ቤተሰብ አንዳንድ የጐሳውን አባላት በመያዣነት በማቅረቡ ለእርቁ ከልብ መነሳቱ አጠያያቂ አልነበረም ። ከዚህ ውጭ የመከዳዳት ሁኔታ ስለማይኖር ስብሰባው የሰርግ ያህል አስተማማኝ ደህንነት ይኖረዋል ። በመያዣነት የተመለመሉ ሰዎች ለየቤተሰቡ ከታደሉ በኋላ ስብሰባው በአንድ የንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት ቢሮ እንዲካሄድ ተደረገ ። የባንኩ ፕሬዚዳንት የዶን ኮርሌዎኔ ውለታ አለበት ። ይህም ብቻ ሳይሆን በስሙ ያለው የገንዘብ ክምችትም ከፊሉ የዶን ኮርሌዎኔ ነው ። ፕሬዚዳንቱ ዶን ኮርሌዎኔ በባንኩ ገንዘብ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ መረጃ ሊሰጠው በፈለገበት ወቅት ዶኑ እንዲህ ብሎ መልሶለታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለመላ ህብቴም ቢሆን አንተን አምንሀለሁ ። በመላ ህይወቴ ፥ በልጆቼም ሞምር ፥ አንተን አምንሀለሁ ። አንተ እኔን ታታልለኛለህ ወይም ትከዳኛለህ ብዬ በህሳቤ ውስጥ ጥርጣሬ የለኝም ። ይህማ መላው የኔ አለምና በሰው ልጆች ባህርይ ላይም ያለኝ እምነት መደምሰሱ ነው ። በእርግጥ እኔ አንድ ነገር ብሆን ወራሾቼ ካንተ ዘንድ ገንዘብ እንዳለኝ እንዲረዱት ማስታወሻ ይጥለሁ ። ነገር ግን እኔ በዚች አለም በህይወት እንኳን ባልኖር የልጆቼ ፍላጐት እንዲጠበቅ ታማኝነትህ እንደሚቀጥል አምናለሁ"

የባንኩ ፕሬዚዳንት ሲሲሊያዊ ባይሆንም የሰው ሁኔታ ቶሎ የሚገባው አስተዋይ ሰው ነው ። ዶኑም በሚገባ ተረድቶታል ። አሁን የጡት አባት ያቀረበለት ጥያቄ ለባንኩ ፕሬዝዳንት የትእዛዝ ያህል የሚከበር ነበር። አንድ ቀን ከሰአት በኋላ ገለል ለማለት አመቺ በሆነ ሁኔታ ባንኩ ለድብቅ አለም ቤተሰብ ሹሞች መሰብሰቢያ እንዲሆን ተዘጋጀ ። በባንኩ አካባቢ ያለው የጸጥታ አጠባበቅ የተሟላ እንዲሆን ምርጥ ሰዎች የባንኩን ዘቦች ልብስ ለበሱ ። ቅዳሜ ጠዋት አራት ሰአት ላይ የስብሰባ አዳራሹ መሙላት ጀመረ ። ከአምስቱ የኒውዮርክ ቤተሰቦች ሌላ በመላ አገሪቱ ከሚገኘው የወንጀል አለም የአስር ቤተሰቦች ተወካዮች ተገኝተዋል ። ነገር ግን ከወንጀሉ አለም ቤተሰብ መሀል እንኳን የተወገዘው 'ጥቁር በግ' በመባል የታወቀው የሺካጎ ቤተሰብ ተወካይ አልተገኝም ። ሽካጐን ለማሰልጠን በተደረገው ሙከራ ተስፋ ቆርጠዋል ። ስለዚህ ይህን በመሰለው ጠቃሚ ስብሰባ ላይ የእነዚያን የሺካጎ እብድ ውሾች ተወካይ እንዲገኝ ግድረግ አስፈላጊ አልሆነም ።

መጠጥ ማደያ እና ብፌም ተዘጋጅቷል ። የእያንዳንዱ ቤተሰብ መሪ አንዳንድ ረዳት ይዞ እንዲገኝ ተፈቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶለታል ። አብዛኛዎቹ ዶኖች ይዘው የቀረቡት አማካሪዎቻቸውን ስለነበረ በስብሰባው ቦታ ጥቂት ልጅ እግሮች ብቻ ነበሩ ። ከነዚያም ጥቂት ወጣቶች አንዱ ፥ ሲሲሊያዊ ያልሆነው ቶም ሄገን ፥ ሌሎቹን ሳያስገርማቸው አልቀረም ።

ሄገን ምን ማድረግ እንዳለበት በውል ያውቃል ። አይናገርም ፥ ፈገግ አይልም ። እራሱን ያለወግ ሳያቀል እንደ አንድ የንጉስ ባለሟል ለአለቃው ታላቅ ክብር በመስጠት መጠጥ ሲቀዳለት ፥ ሲጋሩን ሲያያዝለት ፥ መኰስተሪያውን ሲያመቻችለት ብቻ ይታያል ።

በዚያ አዳራሽ ግድግዳ ላይ ምስላቸው የተሰቀለ ሰዎች እነማን እንደሆኑ የሚያውቀው ሄገን ብቻ ነበር ። በዘይት ቅብ ከተሳሉት ከነዚያ ከበርቴዎች መሀከል አንዱ የገንዘብ ሚኒስትሩ ሀሚልተን ነው ። 'ሀሚልተን ይህን ስብሰባ በባንኩ እንደሚካሄድ ቢያውቅም ኖሮ መፍቀዱ አይቀርም ነበር' ፥ ሲል ሄገን ለአፍታ አሰበ ። ምክንያቱም ከገንዘብ አካባቢ የበለጠ ጸጥታ የሚገኝ በትና ለድርድርም አመቺ የሆነ ስፍራ እንደማይኖር ስለሚረዳ ነው ።

የስብሰባው ተካፋዮች አመጣጥ ከ3፡30 ጀምሮ እስከ 4 ሰአት ድረስ ሲንጠባጠብ ቆየ ። በሰአት አክባሪነቱ የታወቀው ዶን ኮርሌዎኔ አስተናጋጅ በመሆኑ ቀድሞ ደረሰ ። ቀጥሎ የደረሰው ካርሎ ትራሞንቲ የተባለው ፥ የደቡብ ዩናይትድ ስቴትስ ድብቅ አለምን ግዛቱ ያደረገው እና በቁማር ንግዱ የታወቀው መልከ ቀና ሰው ነበር ። ትራሞንቲ በልጅነቱ ከሲሲሊ መጥቶ በፍሎሪዳ አዋቂ እስኪሆን ድረስ ኖረ ። የቁማር ንግድ በሚያካሂዱ የፖለቲካ ሰዎች ከተቀጠረ በኋላ ብዙ ደም መፋሰስ አካሂዶ የቁማር ንግዱን በቁጥጥሩ ስር አዋለ ። በኩባም የባቲስታ መንግስት ስልጣን ላይ በነበረበት

t.me/OLDBOOKSPDF

ወቅት በሀባና የቁማርና የዝሙት ቤቶችን አስፋፍቶ የአሜሪካ ቁማርተኞችን መሳብ ችሎ ነበር ። ትራምንቲ ዛሬ በማያሚ ባህር ዳር ምን የመሰለ ታላቅ ሆቴል ባለቤትና ባለብዙ ሚሊዮን ብር ከበርቴ ነው ። ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንደሱ ጠየም ያለ አማካሪውን አስከትሎ እንደገባ ዶኑን እቅፍ አድርጎ በልጁ ሞት ያዘነለት መሆኑን በፊቱ ገጽታ አሳየው ።

ሌሎቹም ዶኖች መግባታቸውን ቀጠሉ ። ሁሉም በስራም ሆነ በማህበራዊ ግንኙነት ለአመታት ይተዋወቃሉ ። በተገናኙም ቁጥር እርስ በርሳቸው አንዱ ለሌላው ትህትና ያሳያል ። እንዲያውም በልጅነታቸው እንደ ዛሬው ከመከበራቸው በፊት የውለታ ልውውጥ ያደረጉ ናቸው ። ቀጥሎ ከስብሰባው ቦታ የደረሰው ዛሉኪ የተባለው በዲትሮይት አካባቢ የአንድ የፈረስ እሽቅድድም እና የአብዛኛው የቁማር ንግድ ባለቤት ነው ። የደስደስ ያለውና ቅንጦት የተመላበት ህይወት የሚመራው ዛሉኪ ህይወቱ እንደ ዶን ኮርሌዎኔ ውስብስብ ነው ። ዛሉኪ የአደንዛዥ እጽ እንቅስቃሴ አጥብቆ ይቃወም ነበር ። ወደ ዶኑ ጠጋ ብሎ ፥

"ወደዚህ ስብሰባ ያመጣኝ የአንተ አንደበት ብቻ ነው " አለው ።

ዶኑም በምስጋና ራሱን ዝቅ አደረገ ። ዶኑ በሚፈልገው ጊዜ ዛሉኪ እንደሚደርስለት ይተማመንበታል ።

ቀጥሎ ከምእራብ ጠረፍ በአንድ መኪና ሆነው የመጡት ፍራንክ ፋልኔኮና አንቶኒ ሞሊናሪ የተባሉ ከሌሎቹ ዶኖች ወጣት የሚሆኑት ሁለት ዶኖች ናቸው ። እነዚህ ዶኖች የሆሊዉድ ስሜት የዳሰሳቸው ናቸው ። የመግባባት ችሎታቸውም ከሚጠበቀው በላይ ሆኖ ይታይ ነበር ። ፍራንክ ፋልኮኔ የፊልም ተዋንያን ማህበርን ፥ እና በስቱዲዮዎች አካባቢ የሚካሄደውን ቁማር በቁጥጥሩ ስር ከማዋሉም

t.me/OLDBOOKSPDF

በላይ ፥ ለምእራብ ክፍለ ሀገራት ሴቶችን በማቅረብ ይተዳደራል ። ፋልኮኔ ከአንድ ዶን የማይጠበቀው የት ርኢት ሞያ ስለሚነካካው የዶናቹን አመኔታ ማግኘት አልቻለም ።

አንቶኒ ሞሊናሪም ከባህሩ አንጻር የሚገኘውን የሳን ፍራንሲስኮን ክፍል ከመቆጣጠሩም በላይ በስፖርት ውር ርዶች ቁማር አለም ቀዳሚ ስፍራ ይዟል ። የኢጣልያ አሳ አጥማጆች ዝርያ በመሆኑ ከባህር ውስጥ ከሚገኙ ፍጡ ራን ምግብ የሚዘጋጅበት ዝነኛ ምግብ ቤት ባለቤት ነው ። ከዚህ ሌላ በሜክሲኮ ወሰን በኩል አደንዛዥ እጽ በድብቅ በማስገባት ላይም ተሰማርቷል ።

ተከታዩ የስብሰባ ተካፋይ የቦስቶንን ቤተሰብ የሚወክለው ፖንዛ የተባለውን ዶን ነበር ። ይህ ሰው የሌሎቹን ዶኖች ከበሬታ መቀዳጀት ያልቻለው በእታ ላይነቱ ብቻ ሳይሆን በክልሉ ውስጥ ስርአት ማስከበር ባለመቻሉም ነበር ። የቦስተን አካባቢ አያሌ ግድያዎችና እጅግ የበዙ የድብቅ አለም የስልጣን ሽኩቻዎች የሚ ካሄድበት ክልል ሆኖ ቆይቷል ። ፖንዛ አጭር ድፋጭ ያለ ሆኖ ፥ እንዱ ዶን እንዳለው 'ሌባ' የሚመስል መልክ ነበረው ።

በመላ ዩናይትድ ስቴትስ እጅግ ሀይለኛ እንደሆነ የሚታወቀው የክሊቭላንድ ድብቅ አለም መሪ ቪንሰንት ፎርሌንዛ ይሁዳዊ አማካሪ በመምረጡ ምክንያት 'ይሁዳዊው' እየተባለ ይጠራ እንጂ ፥ የድብቅ አለም ክልሉን በለስላሳ የፖለቲካ ጓንት በተሸፈነ የብረት ግዳፍ ጨብጦ ይዞታል ።

ከስብሰባው ተካፋዮች መሀከል በመጨረሻ የደረ ሱት አምስቱ የኒውዮርክ የድብቅ አለም ቤተሰብ ተወካ ዮች ናቸው ። ቶም ሄገን እነዚህ ሰዎች ከኒውዮርክ ከተማ ውጭ ከመጡት የድብቅ አለም መሪዎች የተሻለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግርማ ሞገስ እንዳላቸው ተሰማው ። ከነዚሁ ማራኪ ገጽታዎቻቸው ባህርያት አንዱ እንደ ጉንቱ የሲሲሊ ባህል ልበ ሙሉ እና አካለ ደንዳና መሆናቸው ነበር ።

ከነዚሁ የኒውዮርክ ቤተሰቦች አንዱ የኒው ጀርዚን አካባቢ እና የማንሀተንን የወደብ ክልል በቁጥጥሩ ስር ያደረገው አንቶኒ እስትራቺ የተባለው ሰው ነው ። የጀርዚን የቁማር ንግድ ከመምራቱም በላይ ፥ በፖለቲካው ስርአትም ውስጥ ልዩ ሚና አለው ። ከባህር ላይ የሚወርዱ እቃዎችን የሚያመላልሱ መኪኖቹ ከመጠን በላይ ተጭነው እንደልባቸው መንገዱን ሲያፈርሱት ይውላሉ። መንገዱ ሲበላሽለትም የጥገናውን ኮንትራት የሚወስደው እራሱ ነው ። አንዱ ንግድ ሌላ ንግድ ይፈጥርለታል ። እስትራቺ ወግ አጥባቂ በመሆኑ በሽርሙጥና ንግድ ላይ አልተሰማራም ። ይሁን እንጂ የንግድ ስራው በወደብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከአደንዛዥ እጽ ንግድ እንቅስቃሴ ላይ ከመሳተፍ ነጻ አይደለም ። ኮርሌዎኔን ከሚቃወሙት አምስት ቤተሰቦች መሀከል ደካማው እስትራቺ ቢሆንም ለኮርሌዎኔ ከሌሎቹ በላይ በጎ ፈቃድ ያለው እሱ ነበር ።

የላይኛውን ኒውዮርክ ግዛት በቁጥጥር ስር ያዋለው አቲሊዮ ኩኒዮ ይባላል ። ይህ ሰው የታወቀው የኢጣልያ ስደተኞችን በካናዳ በኩል በማስገባት ፥ የክልሉን ቁማር በመቆጣጠርና በእሽቅድምድም ስፖርት መንግስታዊ ፈቃድ ሲሰጥ ሊከለክል በመቻሉ ነው ። ሌላው የታወቀበት ባህሪው እምነት የሚያሳድር ገጽታውና ህጻናትን መውደዱ ፥ ምናልባትም ለልጅ ልጆቹ ወይም የሽርኮቹ ዝርያዎች ሊሆኑ ለሚችሉ ህጻናት የሚያደላውን ከረሜላ በኪሱ ይዞ መዞሩ ነው ። ኩኒዮ እውነተኛ ተግባሩ ሳይታወቅና እንደ ሌሎቹ ጓደኞቹ እስርም ሳይደርስበት ኖሯል ። እንዲያውም በህዝባዊ አገልግሎት

t.me/OLDBOOKSPDF

እና በበጐ አድራጐት አለሁ አለሁ በማለቱ በኒውዮርክ ክፍለ ሀገር የአመቱ ታዋቂ የንግድ ሰው ለመባል በቅቷል ።

ለታታሊያ ቤተሰብ እጅግ ቀራቢ የሆነው ዶን ባርዚኒ ነው ። የቁማር ንግድን በብሩክሊንና በኩዊንስ ያካሂዳል ። በጥቂቱም ከሽርሙጥና ንግድ ውስጥ አለበት። እስታተን ደሴት በቁጥጥሩ ስር ናት ። በብሮንክስና በዌስትቼስተር የስፖርት ውርርድ ያካሂዳል ። አደንዛዥ እጽ ንግድ ውስጥም አለበት ። በብዙ ከተሞችም ህገወጥ ንግድ ለማካሄድ እጁን አስገብቷል ። በዶን ኮርሌዮኔና በታታሊያ ቤተሰብ መሀከል ጦርነት ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ የታታሊያን ቤተሰብ በገንዘብም ሆነ በተጽእኖ ሲረዳ ቆይቷል ። ባርዚኒ ዶን ኮርሌዮኔን ከሀያልነቱ እና ከተከበረ የማፊያ መሪነቱ ነቅሎ ፣ በቦታው ለመተካትና ከፊሉን ግዛቱን ለመያዝ አልሞ ነበር ። ይህ ሰው ከዶን ኮርሌዮኔ ጋር በብዙ ይመሳሰላል ። ነገር ግን ይበልጥ ዘመናዊ ፣ ይበልጥ ውስብስብና ይበልጥ የንግድን ስርአት አጥባቂ ነው ። ወግ አጥባቂ ነው ብሎ የሚያንቋሽሸው የለም ። የታዳጊ መሪዎችን አመኔታ ጨብጧል ። እንደ ዶን ኮርሌዮኔ ሞቅ ያለ ሳይሆን ቀዝቀዝ ባለ ዘይቤ የግሉ የሆነ ታላቅ ሀይልን በመቀዳጀቱ በዚች ሰአት ምናልባት ከቡድኑ መሀል ይበልጥ 'የተከበረ' ሰው ነው ።

በመጨረሻ በስብሰባው ስፍራ የደረሰው ዶን ፊሊፕ ታታሊያ ነበር ። ይህ ሰው ሶሎዞን በመርዳት የኮርሌዎኔን ሀይል የተጋፈጠ ፣ እንዲያውም ሊያሸንፍ ተቃርቦ የነበረ ግለሰብ ነው ። ይሁን እንጂ በሌሎቹ ዶኖች ዘንድ ያተረፈው በአድናቆት ፋንታ ንቀትን ነበር ። ታታሊያ ለሶሎዞ የበላይነት ራሱን በመጣሉ ፣ ያ ቱርክ ባንፈንፈ በት አቅጣጫ ሲያመራ በመታየቱ በኒውዮርክ ለደረሰው ውዝግብም በሀላፊነት አስጠይቆታል ። በስድሳ አመት

t.me/OLDBOOKSPDF

እድሜው አጊጦ ለባሽና ሴት አሳዳጅ ሲሆን ለዚህ ድክመቱ ስራው ያመች ነበር ። የታታሊያ ቤተሰብ ዋናው ስራ የሽርሙጥና ንግድ ነው ። አብዛኛውን በዩ ናይትድ ስቴትስ የሚገኙት የማታ ክበቦች በቁጥጥሩ ስር ናቸው ። ፊሊፕ ታታሊያ ታዳጊ ዘፋኞችን እና ቀልደኞችን በቁጥጥሩ ስር በማዋልና በዘፈን ሽክላ ቀራጭ ድርጅቶች ላይ ጡንቻውን በማሳየት ባህሪው ይታ ወቅ እንጅ ፥ ዋናው ንግዱ ግን ዝሙትን ማስፋፋት ነው ።

ፊሊፕ ታታሊያና ዶን ኮርሌዎኔ በመሀከላቸው በተ ካሄደው ጦርነት ሁለቱም ወንዶች ልጆቻቸውን ያጡ በመሆናቸው የተለዋወጡት ሰላምታ በአንገት እጅ መን ሳት ብቻ ነበር ። በመጨረሻው ወቅት በደረሰበት አበሳ የተነሳ ዶን ኮርሌዎኔ ምን ድክመት እንደተከሰተበት ለመገንዘብ የስብሰባው ተካፋዮች በሞላ በጽሞና አጤ ኑት ። እንቆቅልሹ ግን ዶን ኮርሌዎኔ ልጁን አጥቶ እንደገና ሰላምን ለምን ፈለገ የሚለው ነጥብ ነበር ። በእርግጥ መሸነፉንና የሀይሉን መቀነስ የሚያረጋግጥ ሁኔታ ነው ። ለማንኛውም ሚስጥሩን አሁን በቅርቡ ይደር ሱበታል ።

ዶን ኮርሌዎኔ ንግግሩን ከመጀመሩ አስቀድሞ የሰላምታ ልውውጥና የመጠጥ መታደል ሲካሄድ ቆየ። ከዚያም ዶን ኮርሌዎኔ መቀመጫውን ሲይዝ ሄገንም ከበስተጀርባው በግራ በኩል ተጠግቶ ተቀመጠ ። ይህን ጊዜ ሌሎቹ ዶኖችም አማካሪዎቻቸውን አስከትለው ቦታቸውን ያዙ ። ዶን ኮርሌዎኔ የመጀመሪያው ተናጋሪ ሆነ ። ምንም እንዳልደረሰበት ፥ ህይወቱ በአደጋ ላይ ወድቃ እንዳልነበር ፥ ልጁ እንዳልተገደለበት ፥ ግዛቱ እንዳልተናጋበት ፥ ቤተሰቡ እንዳልተበተነ ሆኖ ቀረበ ።

“ሁላችሁም በዚህ ስብሰባ ላይ ስለተገኛችሁ አመ ሰግናለሁ ። ለኔ በግል ውለታ እንደጣችላሁብኝ እቆጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረዋለሁ ። ስለዚህ በቅድሚያ አላማዬ ጸብ ለመሻት ወይም ሀሳባችሁን ለማስለወጥ ሳይሆን ፥ ለሁላችንም በጐ የሆነውን በሚያሳምን ምክንያት እንድንቀይስ ላሳስባችሁ ነው ። በበኩሌ ለዚህ ጉዳይ ቃሌን እሰጣለሁ ። ቃሌንም እንደምጠብቅ ብዙዎቻችሁ ታውቃላችሁ ። ስለዚህ ሁላችንም ጨዋ ሰዎች ስለሆን መተማመኛ መሻት የለብንም ፥" ብሎ ዶን ኮርሌዮኔ ንግግሩን አቋረጠ ።

ሌሎች ጸጥ ብለዋል ። ሁሉም በጥሞና የሚያዳምጡ ናቸው ። እነዚህ ሰዎች የሚያመሳስላቸው ሌላም ነገር አለ ። የተደራጀ ህብረተሰብ በሚመራበት ስርአት ላይ ያመጹ ፥ የሌሎችን የበላይነት የማይቀበሉ ፥ ተራ ያልሆኑ ልዩ ግለሰቦች ናቸው ። እንዲያጐበድዱ የሚያደርጋቸው ሀይል ወይም ሰው አይኖርም ። ልጓም አልባ ፈቃዳቸውን በተንኰል ወይም በነፍስ ማጥፋት የሚያስከብሩ ናቸው ። ፈቃዳቸውን የሚቀለብሰው ሞት ብቻ ነው ። ከዚያ ሌላ 'የመጨረሻው በቂ ምክንያት' ፈቃዳቸውን ይገዛዋል ።

ዶን ኮርሌዮኔ ተነፈሰና "እስካሁን በነበረው ሁኔታ ብዙ የማይገባና መጥፎ አጋጣሚ ያስከተለ ድርጊት ተከናውኗል ። እስኪ እኔ እንደተገነዘብኩት እንድገልጽላችሁ ፍቀዱልኝ ፥" ብሎ የሰዎቹን ስምምነት ለማረጋገጥ ለአጭር ጊዜ ጸጥ አለ ።

"ፈጣሪ ምስጋና ይግባውና ፥ ጤንነቴ በመመለሱ ነገሮችን ለማስተካከል የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ እችል ይመስለኛል ። ምናልባት ልጄ ከሚያስፈልገው በላይ ችኩልና እልኸኛ ሆኖ ይሆናል ። ይሆን መካድ አልችልም ። ያም ሆነ ይህ ሶሎዞ ወደኔ ዘንድ መጥቶ በገንዘብና ከሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት እንድተባበረው ጠየቀኝ ። ይህን ሲለኝ ከታታሊያ ቤተሰብ ጋርም በዚህ ረገድ ትብብር ማግኘቱን ገልጾልኝ ነበር ። ጥያቄው በአደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንዛዥ እጽ ንግድ ላይ እንድሳተፍ የሚጋብዝ ስለነበር ከእኔ ፍላጐት ጋር ስለማይጣጣም ፥ አለመፈለጌን በትህትና ለሶሎዞ አስረዳሁት ። ይሁን እንጂ እኔ ባልሳተፍበትም ከእኔ ንግድ ጋር ተቃርኖ ስለሌለው እሱ እንዳሻው ማድረግ እንደሚችል አስረድቼዋለሁ ። ነገር ግን ይህን አባባሌን በመጥፎ ተርጉሞት በሁላችንም ላይ ጉዳት አመጣ። መቸስ ምን ይደረግ? ህይወት እንዲህ ነው ። ማንም እዚህ የሚገኝ ግለሰብ የራሱ ሀዘን ይኖረዋል" አለና ዶኑ ሄገን የሚጠጣው እንዲያቀብለው ምልክት ሰጠው ። ሄገን ወዲያውኑ ቀዝቃዛ መጠጥ ሲያቀርብለት አፉን አርሶ ንግግሩን ቀጠለ ።

"በበኩሌ ሰላምን ለመመስረት ፈቃደኛ ነኝ ። ታታሊያ ልጁን አጥቷል ። እኔም ልጄን አጥቻለሁ ። እኩል ለእኩል ነን ። ሰዎች የብቀላ ተግባራቸውን ሲቀጥሉ ቢኖሩ አለም ምን ልትሆን ነው? ያ ብቀላ በመሻት በሲሲሊ የሚካሄደው ውዝግብ በመጨረሻ ሰዎች ለቤተሰባቸው ዳቦ የሚያፈሩበትን ጊዜ እያሳጣቸው ነው ። ፍጹም ከንቱነት ነው ። ስለዚህ የማሳስባችሁ ያየነበረው ሰላም እንዲመለስ ነው ። በበኩሌ ልጄን ለሞት አሳልፈው የሰጡትን ሰዎች ለማወቅ ምንም እርምጃ አልወስድም ። ሰላም ከተመሰረተ ወደፊትም አላደርገውም ። ሸሽቶ የሄደውን ልጄን እንዲመለስ በማደርገው ጥረት ከባለስልጣኖች መሰናከል እንዳይገጥመኝ እሻለሁ ። ይህ ጉዳይ ከተቃለለ ሌሎች ሁላችንንም የሚጠቅሙ ጉዳዮችንም መወያየት እንችላለን ። እንግዲህ የኔ ፍላጐት ይህ ነው ፥" በማለት ዶን ኮርሌዮኔ ሀሳቡን በጥሞና አቀረበላቸው ።

ግሩም አቀራረብ ነበር ። የጥንቱ በምክንያት አማኝ ፥ ተግባቢና ልስልስ እንደበት ኮርሌዮኔ እንደገና ብቅ አለ ። ሁሉም ሰው ግን አንድ ነገር አጢኗል ። ዶን ኮርሌዮኔ ምንም እንኳን መጥፎ አጋጣሚ በራሱና በቤተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰቡ ላይ ቢደርስበትም ፥ በቀላሉ ሊገመት የማይቻልና ጤንነቱ የተሟላ መሆኑን ሁሉም ሰው ተረድቶታል ። ዶን ኮርሌዎኔ በንግግሩ ላይ ያነሳው የሰላም ጥያቄ ካልተመለሰ ሌላውን የስራ ጉዳይ መወያየት ፍሬ ቢስ እንደሚሆን በግልጽ አሳውቋል ። ባለፈው አመት ከሁሉም ይበልጥ ጉዳት እንደደረሰበት ባይካድም ፥ ቀድሞ ሰላም ቢወርድ ምንም የሚያጣው ነገር እንደማይኖር ለሁሉም ግልጽ ሆኗል ።

ይሁን እንጂ ፥ ለዶን ኮርሌዎኔ መልስ የሰጠው የተጠበቀው ታታሊያ ሳይሆን ኤሚሊዮ ባርዚኒ ነበር ። ባርዚኒ በብልግና ሳይሆን በግልጽ አነጋገር እንዲህ አለ ፥ "የተባለው ሁሉ እውነት ነው ። ነገር ግን ጥቂት ይቀራል ። ዶን ኮርሌዎኔ ትህትናው በዛ ። ሀቁ ግን ያለእሱ እርዳታ ሶሎዞም ሆነ ታታሊያ ባዲሱ ንግድ ስራቸው ሊሰማሩ አይችሉም ። በእርግጥ የሱ በሀሳባቸው አለመስማማት ጉዳት አድርሶባቸዋል ። ይሁን እንጂ ፥ የሱ ጥፋትም አልነበረም ። ነገር ግን በአደንዛዥ እጽ ጉዳይ ላይም እንኳን ቢሆን ዶን ኮርሌዎኔ ሊሸነግላቸው የሚችለው ዳኞችና የፖለቲካ ሰዎችን ሌላ ሰው ሊያሸንፋቸው አይችልም ። የሶሎዞ ረዳቶች በህግ በኩል ቀለል ባለ ሁኔታ ካልተያዙ የአደንዛዥ እጽ ንግዱን ማካሄድ አይችልም ። በተለይ በአሁኑ ወቅት በአደንዛዥ እጽ ነክ ጥፋት ላይ ዳኞች ቅጣቱን ጠበቅ ስላደረጉት ሰዎቻችን ቢያዙ ለመደራደሪያ የሚጠየቀው ሁሉ ጠበቅ ያለ ይሆናል ። 'በአሜርታ' የተካነ ሲሲሊያዊም ቢሆን ሀያ አመት ተፈርዶብሀል ሲሉት የሚያውቀውን ሁሉ ሊዘከዝክ ይችላል ። ይህ እንዳይሆን ለማድረግ የሚችለው ዶን ኮርሌዎኔ ብቻ ነው ። የሚችለውን እርዳታ እምቢ ማለት አንድ ወዳጅ የሚያደርገው አይደለም ። የቤተሰባችንን ጉሮሮ ዘጋው ማለት ነው ። ጊዜው ሌላ ሆኗል ። እንደ ጉንቴ እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንገድ የሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተልበት ወቅት አልፏል። ዶን ኮርሌዎኔ የኒውዮርክን ዳኞች በእጁ ካስገባ ለኛም ሊያጋራን ይገባል ። በእርግጥ ለዚህ አገልግሎቱ ዋጋ መጠየቅ ይችላል ። ግን እሱ ከሚቀዳበት ምንጭ መቅዳት መቻል አለብን ። ጉዳዩ ቀላል ነው።"

ባርዚኒ ንግግሩን እንዳበቃ በአዳራሹ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ። እንግዲህ መስመሩ ተሰምሯል ። ወደ ቀድሞው መመለስ አይቻልም ። ከሁሉም ይበልጥ ግልጽ የሆነው ፡ ስም ምኑት ላይ ካልተደረሰ ባርዚኒ ከታታሊያ ቤተሰብ ጐን ቆሞ ኮርሌዎኔን እንደሚዋጋ መናገሩ ነበር ። ህይወታቸውና እጣቸው ሊሳካ የሚችለው አንዱ ለሌላው በሚያደርግለት እርዳታ ነው ። ስለዚህ እርዳታ ሲጠየቅ እምቢ ማለት ጠብ መጫር ነው ። ውለታም መጠየቅ ቀላል እንዳልሆነ ሁሉ እምቢታም በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

ዶን ኮርሌዎኔ በመጨረሻ እንዲህ ሲል መለሰ ፡ "ወዳጆቼ ፡ እምቢታዬ ለክፋት አልነበረም ። ሁላችሁም ታውቁኛላችሁ ። እርዳታ ተጠይቄ መች እምቢ ብዬ አውቃለሁ? ይህ በተፈጥሮዬም የለ ። ነገር ግን አሁን እምቢ ማለት ነበረብኝ ። ለምን ቢባል ፡ በአደንዛዥ እጽ ላይ መሰማራት ሁላችንንም ከጊዜ በኋላ ያጠፋናል ። በዚህ አገር ላይ ህብረተሰቡ ስለ አደንዛዥ እጽ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጥላቻ አድሮበታል ። የቤተክርስቲያንና የመንግስት ባለስልጣኖች እንደሚያወግዙት ዝሙት ፡ ወይም እንደ ውስኪና ቁማር ንግድ የሚታይ አይደለም ። በአደንዛዥ እጽ ጉዳይ ላይ አንዳችም እርዳታ አይለግሱም ። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔን እርዳታ እንድሰጥ መጠየቅ እራሴን እንድጐዳ መጠየቅ ነው ። እንዲያም ሆኖ ግን ፡ ሁላችሁም የምታምኑበት ከሆነና ሌሎችንም ጉዳዮች ፈር ለማስያዝ ይረዳናል ብላችሁ ካሰባችሁ የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ ።"

ዶን ኮርሌዎኔ ንግግሩን ሲያበቃ በአዳራሹ የተሰበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰበው ሰው ሁሉ በመዝናናት እርስ በርሱ ይንሾካሾክ ጀመር ። ዶኑ በአቢይ ጉዳይ ላይ ፈቃዱን ለግሷል ። ማናቸውንም የተደራጀ የአደንዛዥ እጽ ንግድ እንቅስቃሴ ለመርዳት ከለላ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኗል ። እዚያ የተሰበሰበው መላ የድብቅ አለም ሹም ከደገፈው ያ ቀደም ሲል ሶሎዞን እምቢ ብሎት የነበረውን ጉዳይ ሊደግፍ ማረጋገጫ ሰጥቷል ። በእርግጥም እሱ ራሱ በተግባሩ ላይ መሳተፍ ወይም ገንዘቡን በንግዱ ላይ ማዋል እንደማይጠበቅበት ይታወቃል ። በህግ ከፍሎች በኩል ለሚያጋጥም ችግር ብቻ ከለላ ይሰጣል ። ቢሆንም ይህ በጣም ትልቅ እሺታ ነበር ።

ፍራንክ ፋልኮኔ የተባለው የሎስ አንጀሊስ ዶን ፣ "ሰዎቻችን በዚህ ንግድ ላይ እንዳይሰማሩ ማድረግ የሚቻልበት መንገድ አይኖርም ፣" አለ ። "በገዛ እጃቸው ገብተው ነው ችግር ውስጥ የሚወድቁት ። ይቅርብኝ ለማለት የማይቻል አያሌ ትርፍ አለበት ። ስለዚህ ይበልጥ አደገኛ የሚሆነው እኛ በውስጡ ሳንሳተፍ ብንቀር ነው ። ቢያንስ በቁጥጥራችን ስር ብናደርገው በተሻለ ሁኔታ ከለላ ለመስጠት ፣ በስርአት ለመምራት እና የሚያስከትለውንም ችግር ለመቀነስ እርግጠኛ መሆን እንችላለን ። በዚህ ንግድ ውስጥ መግባት መጥፎ አይደለም ፣ ቁጥጥር ፣ ከለላና ድርጅት ሊኖረው ይገባል እንጂ ። ሰዎችን ስርአት አልበኞች ይመስል ያሻቸውን በማድረግ እንዲሯሯጡ ልንፈቅድላቸው አንችልም ።"

ከሌሎች ይበልጥ የዶን ኮርሌዮኔ ወዳጅ የሆነው የዲትሮይት ዶን እንኳን የወዳጁን ሀሳብ በመቃወም ፣ "በበኩሌ በአደንዛዥ እጽ ንግድ አላምንም ፣" አለ ። ለብዙ አመታት የኔ ሰዎች በዚህ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ተጨማሪ ገንዘብ ከፍያቸዋለሁ ። ነገር ግን ይህ አልሰራም ። አንዱ ይመጣና ፣ 'ዱቄት ያለበትን አግኝቻለሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አንተ ሶስት አራት ሺህ ብር አውጥተህ ብንገዛው እኛ አሰራጭተን ሸጠን ሀምሳ ሺህ እናደርሰዋለን' ይላ ቸዋል ። ይህን የመሰለ ትርፍ ማን አልፈልግም ይላል? ስለዚህ ፥ እኔ ከፍዬ የማሰራቸውን ስራ ወደ ጐን ትተው በዚህ ተግባር ላይ ይጠመዳሉ ። አደንዛዥ እጽ ብዙ ገንዘብ አለበት ። ይበልጥ እያደገ ነው የሚሄደው ። ልናስቆመው ስለማንችል በቁጥጥራችን ስር አድርገን የተከበረ ስራ ማድረግ ይኖርብናል ። በበኩሌ በትምህርት ቤቶች ወይም በሀጻናት አካባቢ እንዲደርስ አልፈቅድም ። ይህ ውግዝ ነው ። በአለሁበት ከተማ ጥቁሮች አካባቢ ብቻ እንዲ ሰራጭ ለማድረግ እሞክራለሁ ። እነሱ የአደንዛዥ እጽ ጥሩ ደምበኞች ናቸው ። ብዙም አያስቸግሩም ። መቸም ቢሆን እነሱ እንስሳት ናቸው ። ለራሳቸውም ሆነ ለቤተ ሰቦቻቸው ግድ የላቸውም ። ነፍሳቸውን በአደንዛዥ እጽ ያጥፉት ። ለማንኛውም ፥ ያፈቀደው ሰው በዚህ ንግድ ላይ እየተሰማራ ሁሉንም እንዳይበክል አንድ ነገር መደረግ አለበት''

ይህን በተናገረ ጊዜ ሁሉም ሀሳቡን በመደገፍ ያጉረመርም ጀመር ። የዲትሮይት ዶን እቅጯን ነበር የተናገረው ። ሰዎች በዚህ ንግድ ላይ እንዳይሰማሩ ገን ዘብ ቢከፈላቸው እንኳ ንግዱን ለማስቀረት አይቻልም ። ስለ ሀጻናት የሰጠውም አስተያየት ቀድሞውን የታወቀ ባህሪው ነው ። ምንስ ቢሆን ማን ለሀጻናት አደንዛዥ እጽ ይሸጥ ብሎ ያስባል? ገንዘቡንስ ቢሆን ሀጻናት ከየት ያመጡታል ። ስለጥቁሮች የተናገረው ማንንም አላሳሰበ ውም ። ጥቁሮች ቁጥር ውስጥ የሚገቡ አይደሉም ። ሀይል የሚባል ነገርም የላቸውም ። እነዚህ ወገኖች ፤ ህብረተሰቡ ፈጭቶ የዱቄት ብናኝ እንዲያደርጋቸው የፈ ቀዱ ስለሆነ ከመጤፍ አይቆጠሩም ። ስለዚህ የዲትሮይት ዶን ወትሮ እንደሚያደርገው ሊተኮርባቸው የማያስፈልጉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቃቅን ነገሮችን በንግግሩ ጣልቃ እንደሚያስገባ ሁሉ ፣ ዛሬም ስለጥቂሮች ያነሳው ነጥብ ከዚያ ተለይቶ አልታየም ።

ዶኖቹም ሁሉም በየተራ ተናገሩ ። ሁሉም የአደን ዛሹ እጽን እንቅስቃሴ ቢያወግዙም ፣ ተቆጣጥረው ማስቀረት የሚቻልበት ዘዴ አይኖርም የሚል ተመሳሳይ ሀሳብ ነበራቸው ። ስለዚህ በዚህ የሚያጓጓ ትርፍ በሚያስገኝ ንግድ ላይ ሰዎች እንዳይሰማሩ ማድረግ እንደማ ይቻልም ተገንዝበዋል ። በመጨረሻም ስምምነት ላይ የተደረሰው ዶን ኮርሌዎኔ ከለላ እንዲሰጥ ነው ። የባር ዚኒና የታታሊያ ቤተሰቦች አብዛኛውን የእጹን ንግድ እንደሚያንቀሳቅሱ ታውቋል ።

ይህ ጉዳይ ፈር ከያዘ በኋላ በሌሎች ጉዳዮችም ላይ ውይይት ተካሄደ ። ውሳኔ የሚጠይቁ አያሌ ውስብስብ ችግሮች ነበሩ ። ማናቸውም ቤተሰብ በላስ ቬጋስና በማያሚ እንቅስቃሴ ማካሄድ ይችል ዘንድ እነዚህ ከተሞች ክፍት እንዲሆኑ ስምምነት ተደረሰ ። ሁለቱም የወደፊቱ ታዳጊ ከተሞች ናቸው ። ስለሆነም በነዚህ ከተሞች ምንም አይነት ጦርነትና ጥቃቅን ወንጀሎችም ቢሆኑ እንዳይካሄዱ ጥረት ለማድረግ ዶኖቹ ተስማሙ ። ተልእኮ ፈጻሚዎችም ረብሻ የተሞላበት ወንጀልና እርስ በርሳቸውም የግል ቂም በቀል እንዳይፈጽሙ ይደረጋል ። ገዳዮችን ማዋሰን ዳኞችን መደለልን ፣ የቴክኒክ ምክር መለገስ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን በተመለከት አንዱ ቤተሰብ ሌላውን እርዳታ በሚጠይቅበት ወቅት ወደ ኋላ ላለማለትም ቃል ገቡ ። የዚህ ሰፊ ጊዜ የጠየቀ የድብቅ እለም ከፍተኛ ባለስልጣኖች ስብሰባ ፣ ተካፋዮች በዚያው የተዘጋጀላቸውን ምሳና መጠጥ ለመጋበዝ ብቻ አቋርጠው ፣ በፍጹም መግባባት ሲካሄድ ቆየ ።

በመጨረሻ ዶን ባርዚኒ ስብሰባው እንዲጠናቀቅ ፈለገ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይኸው ነው እንግዲህ ። ሰላም መስርተናል ። ወትሮም ቢሆን ቃሉን በመጠበቅ የምናውቀውን ዶን ኮርሌዮኔ አመሰግናለሁ ። ከእንግዲህ አለመግባባት በመ ሀከላችን ቢፈጠር ተሰብስበን በመነጋገር እንፈታዋለን ። ከእንግዲህ ሞኝ አንሆንም ። በበኩሌ መንገዱ አዲስ እና የጸዳ ይመስለኛል ። ስብሰባችን ይህን በመሰለ ሁኔታ በመጠናቀቁ ደስታ ይሰማኛል" አለ ዶን ባርዚኒ ።

ፊሊፕ ታታሊያ ብቻ አሁንም ትንሽ ስጋት ነበረ በት ። አንድ ጦርነት በመሀከላቸው ቢነሳ በሳንቲኖ ኮር ሌዮኔ መገደል ምክንያት ከሁሉም የበለጠ ለአደጋ የተ ጋለጠው ታታሊያ ሆኗል ። በመጨረሻም እንዲህ ሲል ተናገረ ፥

"እዚህ በተነሳው በሁሉም ነገር ተስማምቻለሁ ። በራሴ ላይ የደረሰውን መከራ ለመርሳትም ፈቃደኛ ነኝ ። ነገር ግን ጥብቅ የሆነ ማረጋገጫ ከኮርሌዮኔ ብሰማ ደስ ይለኛል ። የግል ቂም በቀል ይሞክር ይሆን? ጊዜ ሲያ ልፍ በአቋሙም ሲደላደል ለወዳጅነት ቃለ መሀላ መፈጸማችንን ይዘነጋው ይሆን? ሶስት አራት አመት ቆይቶ ፥ ስምምነት የገባሁት ያለፈቃዴ ተገድጄ ነው በግ ለት ለበቀል የማይነሳና የገባውን ቃል የማይጥስ መሆ ኑን በምን አውቃለሁ? ሁልጊዜ እርስ በርሳችን ለጥፋት እንጠባበቃለን? ወይስ በእርግጥ ሰላም አውርደናል ብለን የአእምሮ እረፍት እናገኛለን? እኔ አሁን እንደምገባላችሁ ኮርሌዮኔም እናንተ ባላችሁበት ቃል ይገባልናል?"

ይህን ጊዜ ፥ ዶን ኮርሌዮኔ ከጊዜ በኋላ ስሙ ሲጠ ራበት የኖረውን ፥ ስለሰላም ያለውን አቋም የገለጸበትን ፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አርቆ አስተዋይነቱ የተረጋገጠበትን አባባል ለመናገር ቆመ ። በደረሰበት አደጋ ሰውነቱ ትንሽ ቀንሷል ፥ ምናልባት የባለ ስድሳ አመት አዛውንት ነቱ ይበልጥ ተከስቷል ። ይሁን እንጂ የቀድሞ ጥበቡንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆነ ሀይሉን መልሶ የተቀዳጀ ለመሆኑ ምንም አያጠራ ጥርም ።

"እንግዲያማ ምክንያት አልባ ከሆንን ምን ሰብ አዊ ስርአት አለን? ከዱር አራዊት አልተሻልንም ማለት ነው ። ሁላችንም ምክንያት ይኖረናል ፣ እርስ በር ሳችን በምክንያት እንደራደራለን ። ከሀሊናችንም ጋር በምክንያት እንሟገታለን ። ለምን ብዬ ጠብ ለመጫርና ውዝግብ ለመፍጠር የምነሳ ይመስላችኋል? ልጄ እንደሆነ ሞቷል ። እርግጥ ከባድ መከራ ነው ። ይህን ከባድ መከራ መሸከም መቻል አለብኝ ። ለምን ብዬ በዚህ ምክንያት በአካባቢዬ ያለው ንጹህ አለም እንዲሰቃይ አደርጋ ለሁ ። ስለዚህ ፣ ከቶውንም ብቀላ እንደማልሻ እና ቀድሞ የተፈጸሙ ድርጊቶችን የፈጸመውንም ለማወቅ ጥረት ለማድረግ እንደማልሻ ቃል እገባላችኋለሁ ። ከዚህ ስሄድ ንጹህ ልብ ይገር ነው የምለያችሁ ። ሁላ ችንም ከእንግዲህ ትኩረታችን በአለማችንና በፍላጐ ታችን ላይ መሆን ይኖርበታል ። ከበላያችን ያሉ ሰዎች እንደ አሻንጉሊት በክር እየጐተቱ እንዳይጫወቱበን ያመጽን ሰዎች ነን ። በዚህች አገር ላይ እኛ እድለኞች ነን ። ልጆቻችን ለወግ ማእረግ በቅተዋል ። ጥቂቶቻችሁ ፕሮፌሰሮች ፣ ሳይንቲስቶች ፣ ሙዚቀኞች ፣ በሆኑ ልጆች ታድላችኋል ። ምናልባትም የልጅ ልጆቻችሁ የወደፊቱ ባለስልጣኖች ሊሆኑ ይችላሉ ። ማንኛችንም ብንሆን ልጆቻችን እጅግ አድካሚ በሆነው በኛ ስራ ላይ እንዲ ሰማሩ አንሻም ። እነሱ እኛ በምናመቻችላቸው ደረጃና ዋስትና ሌላ ህይወት ይመራሉ ። እኔ አሁን የልጅ ልጆች አሉኝ ። ማን ያውቃል? የነሱ ልጆች አንድ ቀን አገረገኙ ፣ ፕሬዚዳንት ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። በዚህ በአሜሪካ ምን የማይቻል ነገር አለ? ነገር ግን ከጊዜው ጋር መራመድ አለብን ። እርስ በርስ ለመጨራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረስ ወቅቱ አልፏል ። ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የሚሆን ብዙ ገንዘብ እንዲኖረን እንደነጋዴዎቹ ብልጥ መሆን አለብን ። ማድረግ የሚገባንን በሚመለከት ፥ የገዛ ህይወታችንን እንዴት እንደምንመራ ሊወሰኑልን ለሚደፍሩትና የግል ሀብታቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ በመሀከላቸው የሚያካሂዱትን ጦርነት እኛ እንድንዋጋላቸው ለሚሹት 'ከባድ ሰዎች' ታዛዥ አይደለንም ። የነሱን ፍላጐት የሚያስጠብቁትንና እኛን የሚጐዱትን ህጎቻቸውን መታዘዝ አለብን ያለው ማነው? ማናቸው እነሱ ፥ እኛ በፍላጐታችን በምንመራበት ወቅት በመሀከላችን ጣልቃ የሚገቡት? የግላችን ጉዳይ የራሳችን ብቻ ጉዳይ ነው ። የራሳችን አለም የግላችን ስለሆነች እኛው እራሳችን እንመራታለን ፤ ይህ ሁሉ የራሳችን ብቻ ጉዳይ ነው ። ስለዚህ የውጭ ጣልቃ ገቦችን ለመከላከል እርስ በርሳችን አንድ ላይ መሆን አለብን ። አለበለዚያ ግን በብዙ ሚሊዮን ሰዎች አፍንጫ ላይ የሰኩትን ቀለበት እኛም ላይ ሰክተው ቀስፈው ይይዙናል"

"በዚህ ምክንያት በልጄ መገደል የነበረኝን ቂም በቀል ሁሉ ለሁላችን ደህንነት ስል እርግፍ አድርጌ ትቼዋለሁ ። እኔ የቤተሰቤ ሀላፊ እስከሆንኩ ድረስ ከሌላው ወገን ለጠብ ጫሪነት በቂ ምክንያት እስካልታየ ድረስ ማንም የኔ ወገን በማንም ሰው ላይ ጣቱን እንደ ማያነሳ እምልላችኋለሁ ። የንግድ አላማና ፍላጐቴንም ቢሆን ለሁላችን ደህንነት ስል መስዋእት አደርጋለሁ ። ይህ ነው ቃሌ ፥ ይህ ነው ክብሬ ። ሁለቱንም አጎድያቸው እንደማላውቅ የምታውቁ ሰዎች አላችሁ ። ብቻ አንድ የግሌ የሆነ ፍላጐት አለኝ ። ትንሹ ልጄ ሶሎዞንና ሻምበል ማክለስኪን ገድሏል ተብሎ አገር ለቆ ሄዷል ። ይህ ልጅ ከዚህ የሀሰት ውንጀላ ንጹ መሆኑን አስመስክሬ ወደ አሜሪካ ልመልሰው እፈልጋለሁ ። ይህ የኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳይ ስለሆነ እራሴ እፈጽመዋለሁ ። እውነተኞቹን ወንጀለኞች ማግኘት አለብኝ ። ወይም ምናልባት የሱን ሀቀኝነት አስረድቼ ማሳመን አለብኝ ። ምናልባትም ምስክሮችና ጠቋሚዎች የዋሹትን ያርሙ ይሆናል ። ይህ ሁሌ የኔ ጉዳይ ስለሆነ እኔ አከናውነዋለሁ ። ነገር ግን እዚህ ላይ የምለው ነጥብ አለኝ ። አንዲት ድክመት አለ ችብኝ ። በምልኪ የማምን ሰው መሆኔን ልናዘዝላችሁ ። ስለዚህ ልጄን ወደዚህ ለመመለስ በማደርገው ጥረት ላይ አንድ መጥፎ እድል ቢያጋጥመው ፥ አንድ የፖሊስ ባለስልጣን በስህተት ቢተኩሰበት ፥ ወይም እስር ቤት ውስጥ ራሱን ሰቅሎ ቢሞት ወይንም አዲስ ምስክሮች መጥተው ጥፋተኝነቱን ቢያረጋግጡ ፥ ያ ምልኪዬ እዚህ ካሉት ሰዎች በአንዳንዶቹ ጥፋት ተጠንስሶበት ነው የሚል ግንዛቤ ውስጥ ይከተኛል ። አሁንም ልቀጥልላችሁ ። ልጄን መብረቅ ቢመታው አሁንም እዚህ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ናቸው ደመኞቼ ። የሚሳፈርበት አውሮፕላኑ ቢቃጠል ወይም የሚመጣበት መርከብ ቢሰምጥ ፥ ወይም ሞት የሚያደርስ በሽታ ቢከሰትበት ፥ አውቶሞቢሉ ከባቡር ጋር ቢጋጭ ፥ እዚህ ካሉ አንዳንድ ሰዎች የተጠነሰሰ ተንኮል ነው የሚል ምልኪ ይኖረኛል ። ያ ከይሲ ፈቃድ ፥ ያ መጥፎ እድል ቢከሰት ፈጽሞ ይቅርታ አይኖረኝም ። ከዚህ ውጭ ግን በልጅ ልጄቼ ነፍስ እምልላችኋለሁ ፥ የመሰረትነውን ሰላም እኔ አላፈርሰውም ። እንዲያው ሌላ ቢቀር ፥ ከእነዚያ ሀልቆ መሳፍርት የሌላቸውን ሰዎች የጨረሱ ታላላቅ ሰዎች እንበልጣለን ወይስ እናንሳለን ?''

ይህን ብሎ እንዳበቃ ዶን ኮርሌዎኔ ተነስቶ ፊሊፕ ታታሊያ ወደ ተቀመጠበት አመራ ። ታታሊያም ተነስቶ ተቀበለው ። ሁለቱም ተቃቅፈው ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ ። በዚያ የነበሩ ዶኖች ሁሉ አጨበጨቡላቸውና

t.me/OLDBOOKSPDF

በመታረቃቸው ተነስተው ጨበጧቸው ። ይህ እርቅ ምናልባት በአለም ላይ ያለውን ከፍተኛውን ሞቅ ያለ ወዳጅነትን አልመሰረተም ይሆናል ። የገና ስጦታ አይለዋወጡም ። ነገር ግን ቢያንስ እርስ በርሳቸው አይገዳደሉም ። በዚህ አለም ያን ያህል ወዳጅነት ይበቃል ። የሚፈለገውም ያንኑ ያህል ብቻ ነው ።

ከስብሰባው በኋላ ዶን ኮርሌዮኔ ልጁን ፍሬድን ሲንከባከብለት የነበረውን ወዳጁን ዶን ሞሊናሪን ለማመስገን ሲል ከሱ ጋር ጥቂት ቆይታ አደረገ ። ሞሊናሪም ፍሬድ ሴቶች እንደሚሻሙት ፣ ሆቴል በማስተዳደር ልዩ ብቃት እንዳለውና በዚያ ከተማ የሚመጥነውን ስራ ማግኘቱን ለዶን ኮርሌዮኔ አረጋገጠለት ። በዚህን ጊዜ ፣ ማንም አባት ያልተጠበቀ ተሰጥዎ በልጁ ላይ ሲያይ እንደሚደሰተው ሁሉ ፣ ዶኑም ደስ እያለው በመገረም ራሱን ነቀነቀ ። አንዳንድ እጅግ አስከፊ አጋጣሚዎች ያልተጠበቀ በጐ እድል ማምጣታቸው እውን አይደለም ?

ዶን ኮርሌዮኔ ልጁን በዚህ ቀውጢ ጊዜ ለጠበቀለት ለዶን ሞሊናሪ ውለታ ለመክፈል በጐ ቃል ሰጠው ። በተከታዮቹ አመታት በሀይል ሚዛን ማናቸውም ለውጥ ቢከሰት እንኳን ዶን ኮርሌዮኔ ያለውን ተጽእኖ በመጠቀም ለዚህ ሰው እጅግ ጠቃሚ የሆነውን የአዝ ቅድምድም ውድድር ንግድ የእሱ ሰዎች እንዲገለገሉበት ለማድረግ ወደ ኋላ እንደማይል ገለጸለት ። በተለይም ያልተሸፈነ ቁስል ሆኖ ዘወትር የሚካጉ ሰዎች ግዙፍ እጃቸውን ሲያገቡበት በኖረው በዚህ ጉዳይ ላይ ለሞሊናሪ አስተማማኝ ሁኔታ መፈጠሩ የወርቅ ስጦታ ያህል ነበር ።

ጀምበር ስትጠልቅም ዶኑና ሄገን ጠባቂያቸውና ሹፌራቸው ከሆነው ከሮኮ ላምፖኔ ጋር ሆነው ከጣቢ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያቸው ደረሱ ። ወደ ቤት ሲገባም ዶኑ ሄገንን እንዲህ አለው፥ "ይህን ሹፌር ወዶሬት እያስተዋልክ ። ከዚህ የተሻለ የሚገባው መሰለኝ" አለው ።

ሄገን በጣም ተገረመ ። ላምፖኔ ቀኑን ሙሉ ምንም አልተናገረም ። ሌላ ቀርቶ ከኋላው ተቀምጠው የነበሩትን ዶኑንና ሄገንን እንኳን እንዴም ዞር ብሎ አላያቸውም ። ለዶኑ የመኪናውን በር ከፍቶለታል ። ወደ መኪናዋ እንዲገቡ መኪናዋን ባንኩ በራፍ ድረስ አስጠግቶላቸዋል ። አንድ ሰልጡን ሹፌር ከሚያደርገው በላይ የፈጸመው ነገርም አልነበረም ። የዶኑ አይን ሄገን ያልታየውን አስተውሏል ማለት ነው ።

ዶኑ ሄገንን ከእራት በኋላ ክሌሜንዛንና ቴስዮን ይዞ እንዲመለስና በቆይታ እንደሚነጋገሩ ገልጾለት አሰናበተው ። እስከዚያውም ለነዚህ ሰዎች ስለእለቱ ሁኔታ ሄገን ይገልጽላቸዋል ።

በአራት ሰአት ዶኑ ሄገንን ቴስዮንና ክሌሜንዛን የሀግ መጸሀፍት በተደረደሩበትና ልዩ ቴሌፎን ባለበት ክፍል ውስጥ ተቀበላቸው ። ጠረጴዛው ላይ ውስኪ፥ በረዶና ሶዳ ውሀ በትሪ ተቀምጧል ። ዶኑ መመሪያ ሰጣቸው ።

"በዛሬው እለት ሰላም አውርደናል ። እንግዲህ ምንም ጠብና ብቀላ እንደማናካሂድ ቃል ገብቻላቸዋለሁ ። ወዳጆቻችን ግን እምነት የሚጣልባቸው ላይሆኑ ይችላሉ ። ጥበቃው እንዳለ ይቀጥል ። ከእንግዲህ የማይረባ አስደንጋጭ ሁኔታ አንሻም ። ለመሆኑ ሄገን ለመያዣነት እኛ ዘንድ የነበረው ቦኪኪዮ ተለቀቀ ?"

ሄገን እራሱን በመነቅነቅ ፥ "ቤት እንደደረስኩ ለክሌሜንዛ ደውዬ መመሪያ ሰጥቼዋለሁ" አለ ።

ኮርሌዮኔ የሄገንን መመሪያ ለማረጋገጥ ወደ ክሌሜንዛ ፊቱን አቃና ። ክሌሜንዛም እራሱን በአምንታ ነቀነቀ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፈትቸዋለሁ ። ለመሆኑ የጡት አባቴ ፥ አንድ ሲሲሊያዊ ቦኪኪዮዎቹ ለማስመለል የሚሞክሩትን ያህል ደደብ ሊሆን ይችላል?" ሲል ከሌሚንዛ ዶኑን ጠየቀው ።

ዶኑ በፈገግታ "ጥሩ ኑሮ ለመኖር ዘዴኞች ናቸው ። ከዚያ በላይ ጮሌ መሆን ለምን ያስፈልጋል ? የዚህችን አለም መከራ የፈጠሩት ቦኪኪዮዎች አይደሉም ። ግን እውነት ነው ፥ የሲሲሊያዊ ጭንቅላት የላቸውም" ሲል መለሰለት ።

ጦርነቱ በማብቃቱ ደስ ብሏቸው ተዝናንተዋል ። ዶኑም መጠጥ በየአይነቱ እየቀላቀለ ካደላቸው በኋላ በስደት ላይ ያለው ልጁ ሚካኤል እስኪመለስ አንዳችም ሰላምን የሚያደፈርስ ተግባር እንደማይሻና ልጁ ሲመለስም በደህና መመለሱ መረጋገጥ እንዳለበት አስረዳቸው ። ዶኑ ፍራቻው ከደመኞቹ ከባርዚኒና ከታታሊያ ቤተሰቦች ሳይሆን ከፖሊስ እንደሆነ ነገራቸው ።

"ስጋቱ ከፖሊስ ክፍል ነው ። እንደ እውነቱ ከሆነ በሚካኤል ላይ የሚቆጠረውን ማስረጃ ሁሉ በቀላሉ ማጥፋት ይቻላል ። ነገር ግን የኑማክለስኪ ገዳይ ሚካኤል ኮርሌዎኔ መሆኑን ወሬ አቀባዮቻቸው ያረጋገጡላቸው ስለሆነ ፥ የውሸት መረጃዎች ሊያቀነባብሩበት ይችላሉ ። ስለዚህ ሁሉም ቤተሰቦች በየበኩላቸው ባላቸው ሀይል የፖሊሱን ክፍል አስተሳሰብ መለወጥ ይኖርባቸዋል ። እንደሚመስለኝ ከዛሬው ንግግሬ በኋላ ሁሉም ይህን ለማድረግ የራሳቸው ፍላጐት ይሆናል ። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም ። ሚካኤል ከተመለሰ በኋላ አንዳችም ስጋት እንዳይኖርበት አንድ ልዩ ዘዴ መቀየስ ይኖርብናል ።

"አንድ ሰው በህይወቱ አንድ ስህተት ይፈቀድለታል ። እኔ የበኩሌን ተሳስቻለሁ ። በአካባቢያችን ያለውን መሬትና ቤቶች እንድንገዛ እፈልጋለሁ ። ማንም ሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

በመስኩቱ እያሾለቀ ከየትም ርቀት ቢሆን አትክልቴን እንዲመለከት አልሻም ። የቤቶቻችን ዙሪያ ታጥሮ መዝጊያ ከገባለት በኋላ ሙሉ ጥበቃ ይደረግለት ። በአጭሩ በምሽግ ውስጥ መኖር አለብን ። እኔ ዳግመኛ ወደ ከተማ ሄጄ ስራ አልሰራም ። ከፊል ጡረተኛ እሆናለሁ ። አትክልቴን እየቆፈርኩ ወይንም አምርቼ የወይን ጠጅ እንድጠምቅ የሚገፋፋ ስሜት አድሮብኛል ። ለእረፍት ወይም ለስራ ጉዳይ የምጐበኘው ሰው ሲኖር ብቻ ከምወጣ በስተቀር በቤቴ ውስጥ እኖራለሁ ። ወደ ውጭ ስወጣም ሙሉ ጥንቃቄ ይደረግልኝ ። ይህን ሁሉ ስላችሁ አንድ የተለየ ነገር አቅጄ መስሏችሁ እንዳት ሳሳቱ ። ጥንቁቅነትን በመሻት ብቻ የማደርገው ነው ። እንደ ችላ ባይነት የምንቀው ነገር የለም ። እኛን አባወ ዎራችን ችላ ባይነት አያዋጣንም ። ሁሉም ነገር ቀስ ብሎ ይሰራ ። ተጣድፋችሁ ወዳጆቻችን ማደናገጥ የለባችሁም ። ማንም ሰው ቢሆን የሚያደርገው ስራ ሊመስል ይችላል ።

"ከዚህ በኋላ ስራዎች በሙሉ ይበልጥ በናንተ ሀላፊነት የሚመሩ ይሆናሉ ። የሳንቲኖ ቡድን ይፈርስና አባላቱ በናንተ ስር ይመራሉ ። ይህንንም እርምጃ ሲያዩ ወዳጆቻችን ሰላም ፈላጊ መሆናችንን ይገነዘቡታል ። ቶም ፥ ወደ ላስ ቬጋስ ሰዎች ልከህ በዚያ ስለሚካሄደው ሁኔታ ዘገባ እንዲቀርብልኝ እፈልጋለሁ ። ስለፍሬዶም ልሰማ እፈልጋለሁ ። ዛሬ የራሴን ልጅ እንኳን ላውቀው እንደ ማልችል ሰምቻለሁ ። በአሁኑ ወቅት ወጥ ቤት ሆኗል ይመስለኛል ። የበሰለ ሰው ከሚያደርገው በላይ ከልጃገረዶች ጋር ይዝናናል ። በልጅነቱ ከመጠን በላይ ኮምጫጫ ነበር ። ስለዚህም የቤተሰቡን የንግድ ተግባር የሚመራ ሰው አልሆነም ። ያም ሆነ ይህ እስኪ በዚያ ቦታ ምን መደረግ እንደሚቻል እንወቀው"

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን በጽሞና ፥ "ታዲያ አማችህ ካርሎ የንግሥ ተወላጅ ስለሆነ አካባቢውን በቀላሉ ማወቅ ስለሚችል እሱን ብንልከውስ?" በማለት ዶኑን ጠየቀው ።

"አይሆንም ፥ ባለቤቴ ልጆቿ ሁሉ ተለይተዋት ብቸኝነት ተሰምቷታል ። ስለዚህ ኮንስታንዚያና ባሏ ወደ እኛ ግቢ ይምጡና አንዱን ቤት ይኑሩበት ። ካርሎ ሀላፊነት ያለበት ስራ ይሰጠው ፥ እስካሁን ከመጠን በላይ ሳልጫነው አልቀረሁም " ብሎ ፊቱን አኮማተረ ። "የወንድ ልጆች እጥረት አለብኝ ፥ ካርሎን ከቁማር ንግድ ስራ አውጡትና ከሰራተኛ ማህበራት ጋር የተያያዘ ስራ ስጡት ። በዚያ ብዙ የጽሁፍና የንግግር ስራ ይሰራ ። መቸም ጥሩ ተናጋሪ ነው" ሲል ዶኑ ድምጹ ውስጥ እንደ ንቀት ብጤ ይሰማ ነበር ።

ሄገን ትእዛዙን ለመፈጸም ከክሌሜንዛ ጋር ሆኖ ሰዎች እንደሚያዘጋጁ ከገለጸለት በኋላ ፥

"ፍሬዶ ለጥቂት ቀናት ወደ እኛ ዘንድ ይምጣ?" ሲል ጠየቀ ። ዶኑ አሁንም እራሱን ነቀነቀና በጭካኔ እንዲህ ሲል መለሰለት ፥

"ኧረ ምን ሊያደርግልኝ? እዚያው ይሁን! ሚስቴ እንደሆን አሁንም ቢሆን ምግባችንን ማብሰል ትችላለች"

እዚያ ተቀምጠው የነበሩት ሁሉ ምክንያቱን በማያውቁት ጉዳይ ዶኑ ምን ያህል ልጁን እንዳገለለው ካሁን ቀደም አልተገነዘቡም ነበር ። ዶኑ ተነፈሰና ፥

"እንግዲህ እኔ በዚህ አመት ቃሪያና ቲማቲም ለማብቀል እፈልጋለሁ ። ለናንተም ከዚሁ ላይ ስጦታ አበረክታለሁ ። በስተእርጅናዬ ጸጥታና ሰላም ያስፈልገኛል ። እንግዲህ ይኸው ነው ፥ መጠጥ ልትደግሙ ትችላላችሁ" አላቸው ። ይህ አባባል የስብሰባው ግብ ታት ምልክት ነበር ። ሄገን ቴስዮና ክሌሜንዛን ሲሸኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

የዶኑን መመሪያ መፈጸም የሚያስችል ስብሰባ የሚያ
ደርጉበትን እለት ተነጋግሮ አሰናበታቸው ። ከዚያ በኋላ
ዶኑ ወደሚጠብቀው ክፍል ተመለሰ ።

ዶኑ ኮቱንና ክራቫቱን አውልቆ ሶፋው ላይ ጋደም
ብሏል ።

"ታዲያስ ፥ አማካሪ ፥ ዛሬ ካደረግኳቸው ነገሮች
የማትደግፈው ጉዳይ አለ?" ሲል ሄገንን ጠየቀው ።

ሄገን አሰበና ፥ "የለም ። ነገር ግን ካንተ ባህርይ ጋር
የማይጣጣሙ ሁኔታዎች ናቸው የታዩኝ" አለው ።
"ለምሳሌ ፥ የሳንቲኖን ገዳይ ለማወቅ ክትትልም እንደ
ማታደርግና ብቀላም እንደማትፈልግ ተናግረሀል ። በበኩ
ልህ ሰላም እንደምታሰፍን ቃል ገብተሀል ። ግን ጠላቶችህ
ዛሬ የተቀዳጁትን ድል ታዘልቅላቸዋለህ ብዬ አላምንም ።
የማልፈታው እንቆቅልሽ ነው የፈጠርክብኝ ። ታዲያ እን
ዴት አድርጌ ድጋፍ ወይም ተቃውሞ ልገልጽልህ እች
ላለሁ?"

ዶኑ በሄገን መልስ በጣም ረካ ። "መልካም ። ከማንም
የበለጠ አንተ ነህ የምታውቀኝ ። ሲሲሊያዊ ባትሆንም
እኔ ሲሲሊያዊ አድርጌሀለሁ ። ያልከው ሁሉ እውነት
ነው ። ነገር ግን አንድ መፍትሄ ይኖራል ። አንተም መፍ
ትሄው ገና ሊፈጸም ሲል ትደርስበታለህ ። የሰጠሁትን
ቃል እንደምጠብቅና እነሱም እንደሚያምኑኝ ታውቃ
ለህ ። እኔም ትእዛዜ እንዲከበር እፈልጋለሁ ። ዋናው ቁም
ነገር ሚካኤል ወደዚህ እንዲመለስ ማድረጋችን ነው ።
በአእምሮህም ሆነ በስራህ ይህንን ተቀዳሚ ጉዳይ
አድርገው ። ያወጣኸውን አውጥተህ ህጋዊ መዝጊያ
መንገድ ፈልግ ። ወዲህ ሲመለስ ንጹህነቱን ማረጋገጥ
መቻል አለብን ። የላቁ የወንጀል ህግ ጠበቆችን አማክር ።
በግል የሚያነጋግሩህ ዳኞችን ስም ዝርዝር እሰጥሀለሁ ።
እስከዚያው ግን እንዳንታለል ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረግ"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔም እንዳንተው እውነተኛው መረጃ አያሳስበኝም ። እኔ የምፈራው የሚፈጥሩትን የውሸት መረጃ ነው። ታስሮ ሲቆይ አንዱ ፖሊስ እንዳይገድለው እሰጋለሁ ። ወይም ከዚያው እስር ቤት ውስጥ አንዱ እንዲገድለው እንዳያደርጉ ። ስለዚህ በምንም መንገድ ከስ እንዳይመሰረትበት ወይም እስር ቤት እንዳይገባ መከላከል ይኖር ብናል"

ዶን ኮርሌዎኔ ተነፈሰና ፣ "አውቃለሁ ፣ አውቃለሁ" አለ ። "ዋናው ችግር ያልከው ጉዳይ ነው ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ልንቆይ አንችልም ። ሲሲሊ ውስጥም ችግር እየተከሰተ ነው ። ወጣቶቹ የአዋቆችን ትእዛዝ አልሰማ ብለዋል ። በተለይም ከአሜሪካ የተባረሩትን ሰዎች ጥንታዊ አስተሳሰብ ያላቸው ዶኖች በቁጥጥራቸው ስር ሊያውሏቸው አልቻሉም ። ሚካኤል በዚህ ግርግር ውስጥ ሊሞት ይችላል ። ይህን ሁኔታ ለመከላከል ተገቢውን ከለላ ባደራጅለትም ዘላቂነት ሊኖረው አይችልም ። ለዚህ ነው ቶሎ የሰላም ድርድር ለማድረግ የፈለግኩት ። እዚያ ያሉት የባርዚኒ ወዳጆች የሚካኤልን ዱካ እያነፈሩ ናቸው ። እንግዲህ ለአንዱ እንቆቅልሽ መልስ ያገኘህ ይመስለኛል ። የልጄን ደህንነት ለማረጋገጥ የሰላም ድርድር ከማድረግ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም"

ሄገን ይህን ሁሉ ማስረጃ ዶኑ ከየት እንዳገኘ ሊጠይቀው አልፈለገም ። ይልቁንም ሌላ ጥያቄ አነሳ ።

"ከታታሊያ ሰዎች ጋር ስንሰበሰብ እነሱ የሚያሰማሯቸው ንግድ አስተላላፊዎች ካሁን ቀደም ሪኮርድ የሌለባቸው እንዲሆኑ መገፋፋት አለብኝ ። ምክንያቱም ዳኞቹ ሪኮርድ ያለበት ጥፋተኛ ሲያጋጥማቸው ቀላል ቅጣት ለመስጠት ይቆናጠራሉ"

ዶኑ ትከሻውን ነቀነቀና ፣ "ይህን ጉዳይ እራሳቸው መለየት መቻል አለባቸው ። አንተ ጉዳዩን ማንሳት እንጂ

t.me/OLDBOOKSPDF

ችክ ብለህ መከራከር የለብህም ። ከዚህም በቀር እነሱ አይሆንም ብለው አንዱን ልማደኛ ትንታግ መድበው ቢያዝ ፥ እጃችንን አናስገባም ። ምንም ማድረግ እንዳልተቻለ ብቻ እንገልጽላቸዋለን ። ነገር ግን ባርዚኒ ሳይነ ገረው ማወቅ የሚችል ሰው ነው ። እሱም ቢሆን እራሱን ግዴታ ውስጥ እንዳላስገባ ተገንዝበሀል ። ምን ያህል በጉዳዩ እንዳሰበበት ሰዉ አይረዳው ይሆናል ። ነገር ግን እሱ ድል ከከዳው ወገን ሆኖ እጁን የሚያስይዝ ሰው አይደለም'' አለው ።

''ባርዚኒ እስካሁን ከሶሎዞና ከታታሊያ ጐን ቆሞ ነበር ማለትህ ነው?'' አለ ሄገን ።

''ታታሊያ አቃጣሪ ነው ። ሳንቲኖን ማሸነፍ የሚችል ሰው አልነበረም ። ስለዚህ ነው የሳንቲኖ ገዳይ ማን እንደሆነ ማወቅ የማልፈልገው ። የባርዚኒ እጅ እንዳለበት ማወቁ ብቻ በቂ ነው''

ሄገን ብዙ ለማወቅ ይፈልጋል ። ዶኑ ጠቃሚ ሀሳቦች ይሰጠዋል ። ይሁን እንጂ የቀረ ሚስጥር አለ ። ሄገን ይህን ያልተመለሰ ጥያቄ ያውቃል ። ግን መጠየቅ አይገባውም ። ስለዚህ ደህና ሁን ብሎ ሊሰናበተው ሲል ዶኑ የመጨረሻ ቃል ተናገረው ።

''አስታውስ ፥ ያለህን ጥበብ ሁሉ ተጠቅመህ ሚካኤል የሚመለስበትን ዘዴ ፈልግ ። ሌላው ጉዳይ ደግሞ ፥ ከቴሌፎን ሰራተኛው ጋር ተነጋገርና ከሌሚንዛና ቴስዮ በየወሩ ያደረጉትን የስልክ ጥሪ ዝርዝር አቅርብልኝ ። በምንም አልጠረጠርኳቸውም ። አሳልፈው እንደማይሰጡኝ እምላለሁ ። ነገር ግን አንድ ነገር ከመድረሱ በፊት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረጉ ክፉ አይደለም''

ሄገን በእሽታ እራሱን ነቀነቀና ወጣ ። ዶኑ በሱም ላይ ተመሳሳይ ክትትል ያደርግ ይሆን? ሄገን ይህን በማሰቡ አፈረ ። ዶኑ በረቂቅ አእምሮው ሰፋ ያለ እቅድ

t.me/OLDBOOKSPDF

መዘርጋቱንና የእለቱም ማፈግፈግ ለብልሀት መሆኑን ሄገን እርግጠኛ ሆነ ። ነገር ግን እሱም ቢሆን ደፍሮ ያልጠየቀውና ዶኑም ችላ ያለው አንድ በጭለማ የተጋረደ ሀቅ አለ ። ሁሉም ነገር የሚያመለክተው ወደፊት ፍርድ የሚፈጸምበት ቀን እንደሚመጣ ነበር ።

ምእራፍ ሀያ አንድ

ዶኑ ሚካኤልን ወደ አሜሪካ በድብቅ የሚመልስበትን ሁኔታ እስኪያደራጅ አመት ፈጀበት ። በዚህ ጊዜ ውስጥ መላ ቤተሰቡ ሚካኤል የሚመለስበትን ዘዴ በአእምሮው ሲጨምቅ ቆየ ። ሌላ ቀርቶ ካርሎ ሪዚ እንኳን ዛሬ የሁለት ልጆች አባት ሆኖ ቤተሰብነቱ ይበልጥ እየተረጋገጠ በመሄዱ ተሰሚነት አግኝቷል ። ሁሉም የበኩሉን ሀሳብ ያቅርብ እንጂ ዶኑ የተቀበለው ዘዴ አልተገኘም ።

በመጨረሻ የቦኪኪዮ ቤተሰብ በራሱ ላይ ባጋጠመው ችግር የተነሳ ለዶን ኮርሌዎኔ መፍትሄ አገኘለት ።

ፌሊክስ የተባለ እድሜው ሀያ አምስት አመት የሞላው በአእምሮው ብርቱ የሆነ የቦኪኪዮ ቤተሰብ አባል ቤተሰቡ የሚተዳደርበትን ቆሻሻ የማንሳት ስራ ይጠላ ነበር ። ወጣቱ ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ቅርበት ይበልጥ ለማላላት ሲል የእንግሊዞች ዝርያ የሆነች አሜሪካዊት አገባ ። ማታ ማታ የህግ ትምህርቱን እየተማረ ቀን ቀን የፖስታ ቤት ጸሀፊ ሆኖ ሲሰራ ቆየ ። ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅም ጠንቃቃ ሚስቱ ሶስት ልጆቻቸውንና እራሳቸውን ጭምር የሚያገኘውን መጠነኛ ገንዘብ እያብቃቃች ታስተዳድር ነበር ።

እንደማናቸውም ወጣት ፌሊክስ ቦኪኪዮ ትምህር

t.me/OLDBOOKSPDF

ቱን ተጣጥሮ በማጠናቀቅ ብቁ ባለሙያ መሆኑን ሲያ
ረጋግጥ በችሎታው በቂ መተዳደሪያ የሚያስገኝለት ስራ
እንደሚያገኝ ገምቶ ነበር ። ነገር ግን ይህ አልሆነም ።
አሁንም ኩራቱን ባለመተው የቤተሰቡን እርዳታ አል
ፈልግም አለ ። ወዳጁ የሆነ በአንድ ታዳጊ የህግ አገ
ልግሎት ሰጪ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ ወጣት የህግ
ባለሙያ አንድ ውለታ እንዲሰራለት ፌሊክስን ጠየቀው ።
ጉዳዩ ህጋዊ የሚመስል ኪሳራን የማስታወቅ ሸፍጥ
ነበር ። ይህን የመሰለ ሸፍጥ ይጋለጣል ተብሎ የማይገ
መት በመሆኑ ፥ ፌሊክስም ባለው የህግ ትምህርት በመተ
ማመን ፥ እንዲሁም ይህን የመሰለ ጉዳይ ቢነቃበትም
ወንጀል እንደማይሆን ስለገመተ ሳያወላውል ገባበት ።

ይኸው ሸፍጥ እንደታሰበው ተደብቆ አልቀረም ፥
ተጋለጠ ። የፌሊክስ ጓደኛ የሆነው የህግ ባለሙያም
አልረዳው አለ ። ሌላ ቀርቶ የስልክ ጥሪውን እንኳን
ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም ። ሁለቱ ነጋዴዎች ጥፋ
ተኛነታቸውን በፍርድ ፊት አረጋግጠው ፥ ለዚህ ጥፋት
ያበቃቸው ፌሊክስ መሆኑን ለፍርድ ቤት ገለጹ ። ማጠ
ናከሪያ እንዲሆንም የወንጀል ሬኮርድ ያለባቸውን የፌሊ
ክስ ዘመዶች ስም ለፍርድ ቤቱ ተናገሩ ። ሁለቱ ነጋዴ
ዎች የተፈረደባቸው በገደብ ተነሳላቸው ። ፌሊክስ ግን
የአምስት አመት እስራት ከተፈረደበት በኋላ ሶስቱን
እንደጨረሰ ተለቀቀ ። ዘመዶቹም እርዳታቸውን እምቢ
ብሎ ስለነበር አሁን ማንም እንዲረዳላቸው አልፈለጉም ።

ምህረት የሚገኘው ከቤተሰቡ ብቻ ነው ፤ ከህብ
ረተሰቡ ይበልጥ ሊታመን የሚገባው ቤተሰቡ ነው ።
ይህን እውነት ፌሊክስ ሊማረው ይገባል ፥ ብለው ወገ
ኖቹ አሰቡ ።

ፌሊክስ እስራቱን ጨርሶ ሲፈታ ቤቱ ሄዶ ሚስ
ቱንና ልጁን ስሞ በሰላም ለአንድ አመት ያህል ተቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

መጠ ። ከዚያ በኋላ ግን ቦኪኪዮንቱን ሊያሳይ ተነሳ ። ሽጉጥ ገዝቶ ያንን ለእስር ያበቃውን ወዳጁን በግልጽ ገደለው ። ቀጥሎም ሁለቱን ነጋዴዎች ፊልጮ ገደላቸው። የሟቾቹ እሬሳ ሜዳ ላይ እንደተዘረረ ፌሊክስ ከአንድ ምግብ ቤት ገብቶ ቡናውን እየጠጣ ፖሊሶች መጥተው እስኪይዙት ጠበቃቸው ።

የፍርድ ክርክሩ አጭር ፣ ፍርዱም ምህረት የሌለበት ነበር ። ካሁን ቀደም አንድ የድብቅ አለም ወንጀለኛ ላደረሰው ጥፋት እውነተኛ ምስክርነታቸውን በመስጠት ለእስር ያበቁትን የህግ ምስክሮች በቂም በቀል ገደላቸው ተባለ ። በሰብአዊነታቸው የታወቁ ሰዎች ሳይቀሩ መላው ህብረተሰብ ፌሊክስ ቦኪኪዮ ይገደል የሚል ጥሪ አቀረቡ ። አንድ የመንግስት ባለስልጣን ይህን የመሰለ ጥፋት አይቶ ቢያልፍ እብድ ውሻን በህይወት የማቆየት ያህል ጥፋት ስለሚመስል አገረገዥውም ፍርዱን ሊያቃልልለት አልደፈረም ። የቦኪኪዮ ቤተሰብም ፌሊክስ የፈጸመውን ግድያ እንደጀብዱ ቆጥሮት ኩራት ተሰማው ። የፈለገውን ያህል ይፍጅ እንጂ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይቻላል ። ነገር ግን የትም ቢኬድ ፍርዱ ግልጽ ነበር ። ከእንግዲህ ምን ክርክሩ ቢራዘም ፌሊክስ በኤሌክትሪክ ወንበር ላይ ተቀምጦ ከመሞት ሌላ እጣ የለውም ።

አንድ የቦኪኪዮ ቤተሰብ አባል ፌሊክስን መርዳት የሚቻልበት ዘዴ ይኖር እንደሆን በማለት ባሳሰበው መሰረት ይህን ጉዳይ ለዶን ኮርሌዮኔ ያቀረበለት ሄገን ነበር ። ዶን ኮርሌዮኔ በቀጥታ እምቢ አለ ። አስማተኛ አይደል ። ሰዎች የማይሆን ነገር ይጠይቁታል ። በነጋታው ግን ዶኑ ሄገንን አስጠርቶ የፌሊክስን ጉዳይ አንድ በአንድ እንዲዘረዝርለት አዘዘው ። ጉዳዩን ካዳመጠ በኋላ የቦኪኪዮ ጉሳ መሪ እንዲጠራና እንዲነጋገሩ ወሰነ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የቦኪኪዮ ቤተሰብ መሪ ሲመጣም ዶኑ ሀሳቡን ገለጸለት ። የፌሊክስ ሞት ያለቀለት ጉዳይ ነው ። ከእን ግዲህ እሱን የሚያድን ምንም ሀይል የለም ። ነገር ግን ስለቤተሰቡ ደህንነት ሲል ማክለስኪንና ሶሎዞን የገደል ኳቸው እኔ ነኝ ብሎ ቢናዘዝ ለልጆቹ ማሳደጊያና ለባለ ቤቱ መኖሪያ የሚበቃቸውን ገንዘብ ዶኑ ለቦኪኪዮ መሪ እንደሚሰጥ አስረዳው ።

ብዙ ዝርዝር ሁኔታዎች ተዘጋጁ ። ፌሊክስ ሶሎ ዞንና ማክለስኪን መግደሉን በማያጠራጥር ሁኔታ ማስረዳት እንዲችል ገለጻ ተደረገለት ። ከዚህም በላይ ሻምበል ማክለስኪ ከአደንዛዥ እጽ ጋር በተያያዘ ደባ ይፈጽም እንደነበር መጠቆም ይኖርበታል ። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሰዎች ሲገደሉ አይቶ የነበረው አሳላፊ ገዳዩ ፌሊክስ ነው ብሎ እንዲመሰክር ይደረጋል ። ይህ አድራጐት የፌሊክስን የተቃረበ ሞት ይበልጥ ቢደመድመውም ቦኪኪዮዎች የዚህ ሰው ሞት የማይቀር መሆኑን ማመን ይኖርባቸዋል ። ሁሉ ነገር ተደራጀ ። ገንዘቡ ለቦኪኪዮ ቤተሰብ ተከፈለ ። ፌሊክስ የጉዳዩን ዝርዝር እንዲያጠና ተደረገ ። እቅዱ በተግባር ተተረጐመ ። የዚህ ሰው ኑዛዜም የጋዜጦችን ርእሰ አንቀጽ ሞላው ። አጠቃላይ ድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ተሳካ ። ይሁን እንጂ ጠንቃቃው ዶን ፌሊክስ እስኪገደል ጠበቀ ። ሰውዬው ከሞተ ከአራት ወር በኋላ ነበር ሚካኤል እንዲመጣ ትእዛዙን ያስተላለፈው ።

ምእራፍ ሀያ ሁለት

ሉሲ ማንቺኒ ሶኒ ኮርሌዎኔ በመሞቱ ለብዙ ጊዜ አዘነች ። ከማንም ወዳጅ ይበልጥ ትዝታ የጣለባት ልዩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስጦታ ነበረው ። በአለም ላይ ፍቅር ሊቀሰቅስባት የሚ
ችል እሱ ብቻ እንደሆነ ታምን ነበር ።

ከአመት በኋላ ግን ተስማሚው የነቫዳ ጸሀይ እየ
ሞቃት በምትኖርበት ሆቴል ግቢ ውስጥ ባለው መዋኛ
ዳር አንድ ውብ ወጣት አጠገብዋ ተጋድሞ የእግር
ጣቷን ይከረክራል ።

"ተው እባክህ ጁልስ ፥ ዶክተሮች እንደዚህ ጅሎች
አትመስሉኝም ነበር" አለችው ። ጁልስም ሳቅ ብሎ ፥
"እኔ እኮ የላስቬጋስ ሀኪም ነኝ" አለና ጭኗን ሲኮ
ረኩራት በሳቅ ተንከተከተች ። እንዴት ያለች ምስኪን
ናት! ጁልስ ሲጋል 'ሊተካ የማይችል ፍቅር ምናምን'
የሚባለውን አያምንም ። ስለዚህ ለምን አይሞክራትም፣
ከመዳፉ ስር ያለው ቆዳ እንደሆን ህይወት ያለው ህዋስ
ሲሆን ይህ ህዋስ ሌላ ህዋስ ይፈልጋል ። ሲጋል ዛሬ
ማታ ቤቱ እንድትመጣ መገፋፋት አለበት ። ስትመጣም
በሙሉ ፈቃድዋ ቢሆን ይመረጣል በዘዴ መጠቀም
ቢያስፈልግ ግን ጁልስ ዘዴ አያጣም ። ግን ይህች ምስ
ኪን እራሷስ ብትሆን ሳትመኘው ትቀር ይሆን?

"እባክህ ጁልስ ፥ ተው አትኮርኩረኝ ፥" አለች
ሉሲ ፥ ድምጿ እየተንቀጠቀጠ ። ጁልስ አጥፊነት እየተ
ሰማው ፥ "እሺ ፍቅሬ ፥" ብሎ መኮርኮሩን ተወ ። እራ
ሱን ጭኗ ላይ አንተርሶ እንደተዝናና እንቅልፍ አሸለ
በው ።

ሉሲ የአካባቢውን ሰው እየተመለከተች ፥ በዚህ
ሁለት አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ምን ያህል እንደ
ተለወጠች አስገረማት ። በኮኒ ሰርግ ላይ ከሶኒ ጋር
መተዋወቋ ከመልካም ትዝታ በቀር ቅር የሚያሰኝ
ሁኔታ አላስከተለባትም ። ሶኒ ረቂቅ የፍቅር ጥበብ ሳይ
ሆን ባልተገራ ተፈጥሮው ህዋሳዊ ፍቅር ነበር ሲለግ
ሳት የኖረው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደልማዱ ሊዳራት እንደሚመጣ ሲገልጽላት ፥ ከመጣ እስኪበቃው መቆየቱ እንደማይቀር ስለምታውቅ ፥ በቂ መጠጥና ምግብ መሟላቱን ታረጋግጣለች ። እሷ ዘንድ ከመጣ እሱም እስኪጠግባት እሷም እስክትጠግ በው ይዳሩ ነበር ። የቤቷን በር መክፈቻ ቁልፍ ስለሚ ይዝ በሩን ሳያንኳኳ ከፍቶ ሲገባ ዘላ ግዙፍ ክንዱ ላይ ትንጠለጠልና ሁለቱም ሳይተፋፈሩ አውሬ ይሆናሉ ። ገና ከመሳሳማቸው አንዱ የሌላውን ልብስ ለማውለቅ ይጣደፍና እሱም ወደ ላይ ሲሰቅላት እሷም ጭኑን በእግሯ ትቆልፈዋለች ። በዚህ ሁኔታ የልባቸውን ካደረሱ በኋላ ነበር እንደተሸከመ ከአልጋ የሚያደርሳት ። በዚህ ሁኔታም ለአስራ ስድስት ሰአት እርቃናቸውን አብ ረው ይኖራሉ ። ያልጋ መውረጃውን በሰፊው ታዘጋጅለ ታለች ። አልፎ አልፎ እሷ ዘንድ እያለ የስልክ ጥሪ ይደርሰዋል ። ጥሪው የስራ ጉዳይ ቢሆንም እሷ በዚህን ጊዜ በሱ ገላ ከመጫወት ፥ ከመተሻሸት እና መላ ሰው ነቱን ከመሳም በስተቀር የስልኩን ወሬ ለመስማት ከቶውንም አትሻም ። በመጀመሪያ ላይ እንዲህ መሆኑ ያሳፍራት ነበር ። ኋላ ግን ይህ ሁኔታዋ ወዳጅዋን እንደ ሚያስደስተው ተገነዘበች ። ይህ ሁሉ እንደ እንስሳት የዋ ህነት የሚታይበት ባህርይ ሁለቱንም ሲያስደስታቸው ኖሯል ።

ዶን ኮርሌዮኔ ላይ ጥይት በተተኮሰበት ወቅት የሉሲ ወዳጅ ሶኒም ይህን የመሰለ እድል ሊገጥመው እንደሚችል ተገንዝባለች ። ይህ ሀሳብ አእምሮዋ ውስጥ ከገባ ጀምሮ ሰላም አጥታ ፥ ሶስቱን ሳምንት ሙሉ ሶኒ ሳይመጣ በቀረ ጊዜም ስንቋ መጠጥ ፥ የእንቅልፍ ኪኒንና የራስዋ ስጋት ብቻ ሆነው ሰንብታለች ። ሊሞት አቅራ ቢያ ቢያንስ በየሳምንቱ ይጐበኛት ነበር ።

መሞቱን በጋዜጣ ላይ ባነበበች ጊዜ ለመሞት ፈልጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመጠን ያለፈ የእንቅልፍ ኪኒን ወሰደች ። መድሀኒቱ ከመግደል ፈንታ ከመጠን በላይ ስላቅለሸለሻት ስታስ ታውክ ተገኝታ ሀኪም ቤት ተወሰደች ። ከሶኒ ጋር ያላት ግንኙነትም ስለማይታወቅ ብዙ አልተወራም ።

ሀኪም ቤት ሳለች ቶም ሄገን መጥቶ አጽናንቷታል ። ወደ ላስ ቬጋስ ሄዳ ፍሬድ በሚያካሂደው ሆቴል ውስጥ እንድትሰራ ያደረገው ቶም ሄገን ነው ። ሶኒ በህይወት እያለ አቅዶላት የነበረውን ተቆራጭ አሰጥቷታል ። ከልክ በላይ የእንቅልፍ ኪኒን በመወሰዷ ተጠራጥሮ ምናልባት አርግዛ እንደሆነ ሲጠይቃት አለማርገዟን ገለጠችለት ። ሶኒ በተገደለበት ምሽት እሷ ዘንድ መጥቶ ይሆን? ይህንንም ለማወቅ ሲጠይቃት እንዳል መጣ ነገረችው ።

"ከልቤ የማፈቅረው ሰው እሱ ብቻ ነው ። ከእንግዲህ ሌላ ሰው ማፍቀር አልችልም ፡" በማለት ፡ ለሷ የነበረው ደግነት ሁሉ እየታወሳት አውርታለት ነበር ። ሄገን ካጽናናት በኋላ ምንም አይነት ችግር ቢገጥማት ወይም ብቸኝነት ቢሰማት እንድትደውልለት አሳስቧት አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ ሸኛት ። ሉሲ ወደ ላስቬጋስ ለመሄድ አውሮፕላን ልትሳፈር ስትል ይህን ሄገን የሚ ያደርግላትን ሁሉ ዶኑ ያውቅ እንደሆነ ጠየቀችው ።

አድራጎቱ ሁሉ የዶኑን ፈቃድና የራሱንም በጎ ምኞት የሚያካትት መሆኑን ሄገን ገለጸላት ። ሉሲ ላስ ቬጋስ ስትደርስ የኪራይ ቤት ተዘጋጅቶ ቆያት ።

ከአስራ ስምንት ወራት በኋላ ተደሳች ለመሆን በመብቃቷ ተገረመች ። አንዳንድ ምሽት ሶኒ በህልሟ ይመጣል ። ሌላ ወንድ ሄዳም አታውቅ ። በሆቴሉ መዋኛ ውስጥ ትዋኛለች ። በአቅራቢያው ሀይቅም በጀልባ ትንሸራሸራለች ። ቁመናዋም ሽንቅጥ እያለ ሲመጣ አጠቃላይ ገጽታዋ ተሻሻለ ። አሁንም ድምቡሽ ገላ ብትሆ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንም ከኢጣሊያዊ ይልቅ አሜሪካዊ ቁመና ይዛለች ። በሆቴሉ የህዝብ ግንኙነት ክፍል ውስጥ በእንግዳ ተቀባይነት ትሰራለች ። ፍሬድ አልፎ አልፎ ሲያገኛት ከሚያዋራት በስተቀር ምንም ግንኙነት የላቸውም ። የፍሬድ መለወጥ አስገርሟታል ። ሽክ ብሎ ለብሶ ሴቶችን ማራኪ ሎጋ ወጣት ሆኗል ። የቁማር ቤቶችን ያቀፈ ሆቴል ውስጥ ለመስራት የተፈጥሮ ችሎታ ያለው ይመስላል ።

ሄገን ከስድስት ወር በኋላ ሉሲን ሊያያት በመጣ ጊዜ ተደላድላ አገኛት ። ከደመወዟ ሌላ ተጨማሪ ገንዘብ በቼክ ይደርሳታል ። ለአሰራር እንዲያመችም በሆቴሉ ባለንብረትነት ላይ ድርሻ እንዳላት ሆና እንድትተዋወቅ ተደርጓል ። የቤተሰቡን ሚስጥር ለመጠበቅ የተደረጉትን የህግ ድርድሮች ለማንም እንዳታወራ ሄገን አስጠነቀቃት ። ለሚደርስባት የህግ ጥያቄም ከለላ እንደሚሰጣት አረጋገጠላት ።

ሉሲ የሚጥሉባት ውለታ ከበስተጀርባው እሷን መጠቀሚያ ለማድረግ መሆኑን ብትረዳም ተስማማች ። ነገር ግን በዚህ ላይ የሆቴሉን ደህንነትም በሚመለከት በፍሬድም ሆነ በፍሬድ አለቃ ላይ አይኗን ጣል እንድታደርግ ሲጠይቃት ፣

"ቶም ፣ በፍሬዲ ላይ ወሬ አቀባይ እንድሆንበት እንዴት ትጠይቀኛለህ ?" በማለት ቅሬታዋን ገለጸችለት ።

ሄገን ፈገግ በማለት ዶኑ ስለፍሬድ እንደሚጨነቅና ከሞ ግሪን ጋር ያለው ግንኙነት በፍጥነት እያደገ በመምጣቱ ችግር ውስጥ ይገባል የሚል ስጋት ስለተፈጠረበት ይህን ለመቆጣጠር ክትትል ማስፈለጉን አወሳላት ። ነገር ግን ዋናው ጉዳይ ዶኑ የሆቴሉ ህንጻ እንዲሰራ ገንዘቡን ያፈሰሰው ለልጁ መደበቂያ ብቻ ሳይሆን ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሬት ላስ ቬጋስ ላይ በሰሬው ላቀደው እንቅስቃሴ እንዲን ለግስገቢያ መሆኑን ሄገን ለሉሲ አልገለጸላትም ። ቶምና ሉሲ ይህን ሀሳብ ከተለዋወጡ በኋላ ነው ጁልስ ሲጋል የተባለው ቀጠን ያለና መልከ መልካም ልጅ እግር ሀኪም በሆቴሉ ውስጥ ተቀጥሮ ለመስራት የመጣው ። ሉሲ ክንዷ ላይ እባጭ ወጥቶባት ስለነበር ወደዚህ ሀኪም ዘንድ ሄደች ። ከሀኪሙ ቢሮ በር አጠገብ ሁለት በሆቴሉ የሙዚቃ ቡድን ውስጥ የሚጫወቱ ወጣት ሴቶች ቆመው ያወራሉ ። ሀኪሙ ወጣ ብሎ አንዲቱን ሲጠራ ነበር ሉሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ማራኪ ወጣት ያየችው ።

ሉሲ ይህን ሰው ባየችው ጊዜ ስለሱ የነበራት ግምት ቢሮው ገብታ በቅርብ ስትመለከተው ተለወጠ ። ሰውየው ብዙም የማይናገር ፣ ትህትና የተሞላበት ሆኖ አገኘችው ። ስለ እባጭዋ ስትጠይቀውም የማያሰጋ መሆኑን እየቀለደ አስረዳት ። በመጨረሻም አንድ ትልቅ የህክምና መጽሀፍ አንስቶ እባጩ ላይ ድንገት ሲጥለው እባጩ ጐደለና ጠፋ ። ለጊዜው ያደረገው ህክምና ይኸው ነበር ። ሳምንት ቆይተው ሲገናኙ ስለ እባጭዋ ጠየቃት ።

"ተሽሎኛል ። ጣጣ የማታበዛ አዋቂ ሀኪም ነህ" አለችው ።

እሱም ፈገግ አለና ፣ "አንቺ ምን ያህል ጣጣ የማላበዛ ሰው እንደሆንኩ መረዳት እንዳቃተሽ ሁሉ ፣ እኔም ያንቺን ሀብታምነት አላወቅኩትም ነበር ። ዚ ቬጋስ ሳን የተባለው ጋዜጣ የዚህ ሆቴል ባለቤቶች የሆኑትን ሰዎች ዝርዝር አውጥቶ አየሁት ። አንቺ ከነሱ አንዷ መሆን ሽን ባውቅ ኖሮ በቀደም እለት ብዙ ገንዘብ አስከፍልሽ ነበር" ሲል ቀለደ ።

ሉሲ ሄገን ቀደም ሲል የሰጣት ማስጠንቀቂያ ትዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስላላት ምንም መልስ አልሰጠችውም ። እሱም በፈገግታ፤

"ግድ የለም አትስጊ ፥ ያንቺ እንዳልሆነ አውቀዋለሁ ። በስምሽ ሽፋን ከሚጠቀሙብሽ አንዲ ነሽ ። እሱን ተይውና ፥ ይልቅስ ለምን ዛሬ ማታ ከሚታዩት ትርኢቶች አንዱን አብረን አናይም ። በዚያውም የሩሌት ቁማር መጫወቻዎች እገዛልሻለሁ" አላት ።

ትንሽ ጥርጣሬ ቢገባትም ዶክተር ጁልስ አግባባት ።

"አብሬህ ለማምሸቱ እሺ ፥ ነገር ግን በምሽቱ ማብቂያ ላይ ቅር እንዳይልህ! እንዳራዳ ልጆች ጮሌ እንዳልመስልህ" አለች ሉሲ ።

"ለዚህ ነው አንቺን የምሻው ። ዛሬ ለራሴ እረፍት አዝግሬለሁ" አላት ። ሉሲ ፈገግ ብትልም በሀዘኔታ ፥ "ይህን ያህል ያስታውቅብኛል?" አለችው ። እሱ ግን እራሱን ነቀነቀ ።

ሉሲም ፥ "እሺ ፥ ለእራት እንገናኝ ፥ ስለ ቁማሩ ግን የራሴን ወጪ እራሴ እችላለሁ" አለችው ። በእራት ላይ ትርኢት ከሚቀርብበት ቦታ አብረው ሄዱ ። ዶክተር ጁልስ ስለተለያዩ ጭኖች እና ጡቶች በሀኪሞች አነጋገር እየገለጸ ሲያዝናናት አመሸ ። ኋላም በተሽከርካሪ ሳህን ላይ በሚንቀሳቀስ ኳስ የሚጫወቱትን ሩሌት የተባለ የቁማር ጨዋታ አጫወታት ። በጨዋታው ላይ ከመቶ ብር በላይ በሉ ። ከዚያ በኋላ በጨረቃ ምሽት ወደ ቦልደር ግድብ ጉዞ ሲያደርጉ የፍቅር ልውውጥ ፈለገ ። ከጥቂት መሳሳም በኋላ ፈቃደኛ አለመሆኗን ሲገነዘብ ፥

"ነግሬሻለሁ እኮ ፥ ምንም አላደርግ ብዬሻለሁ አላት"

ሉሲ እንደበደለችው ተሰማት ። ጁልስ ቀጠል አድርጎ ፥

"ምንም ሙከራ ባላደርግ ደግሞ ምን አይቶብኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው የሚል ቅሬታ ያድርብሻል ብዬ ነው" አላት ። ያላት እውነት በመሆኑ ከት ብላ መሳቅ ነበረባት ።

ለተከታዮቹ ጥቂት ወራት የጠበቀ ወዳጅነታቸው ቀጠለ ። ግን ፍቅር እንዳይባል ሉሲ የፍቅር ልውውጥ ግድረጉን አልፈቀደችም ። እንደ ብዙ ወንዶች ተንቄ ነው የሚል ስሜት ባይቀረጽበትም እምቢታዋ ለጁልስ እንቆቅልሽ እንደሆነበት ሉሲ ተገነዘበች ። ይህ ሁኔታ እምነት አሳደረባት ። ውጪውን ከሚታያት ባለሙያ ሀኪምነቱ ውስጥ ጨዋታ ወዳድና ለአደጋ ሲጋለጥም ደስ የሚለው ሆኖ አገኘችው ። በፍጻሜ ሳምንት እረፍቱ ላይ በካሊፎርኒያ የመኪና እሽቅድምድም ላይ ይሳተፋል ። ለእረፍት ፈቃድ ሲወጣ ወደ ሜክሲኮ ግዛት ሂዶ ለጫማቸው ሲሉ ሰዎችን ከሚገድሉ የሽፍቶች መናኸሪያ ዘልቆ እንደተጓዘ ነግሯታል ። ነገር ግን ባጋጣሚ ኒውዮርክ በሚገኝ ዝነኛ ሀኪም ቤት ውስጥ የቀዶ ጥገና ባለሙያ ሀኪም እንደነበረም ተረዳች ። ይህን ሁሉ ስታይ በሆቴል ውስጥ ሀኪም ሆኖ መስራቱ እንቆቅልሽ ሆነባት ። ሚስጥሩን እንዲነግራት ስትጠይቀው ፡

"አንቺ ጭለማ የሆነብኝን ሚስጥርሽን ንገሪኝና እኔም እነግርሻለሁ ፡" አላት ።

አፈረችና ሁሉንም ነገር ተወችው ። ጁልስም አልገፋፋትም ። ነገር ግን ከጠበቀችው በላይ የሆነው ወዳጅነታቸው ቀጠለ ።

አሁን ከመዋኛው ስፍራ ተቀምጣ ጁልስ እራሱን ጭኗ ላይ አስደግፎ ሳለ አንድ ሁለመናዋን ያጥለቀለቀው ስሜት ወረራት ። ጭኗን ሲነዝራት ሳታውቀው አንገቱን በጣቷ አሸት አሸት አደረገችው ። ይህን ሳያጤን የተኛ መስሏል ። ነገር ግን አካሉን በመንካቷ ስሜቱ ተቀስቅሷል ። በድንገት ከተኛበት ከጭኗ ላይ ተነስቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቆመ ። እጅዋን ይዞ በሳሩ ላይ ተጉዞ ወደ እግር መንገዱ አመራ ። በታዛዥነት ተከተለችው ። ወደግል ክፍሉ ሲወስዳትም አላንገራገረችም ። ውስጥ ሲገቡም ለሁለ ታቸውም መጠጥ ቀላቅሎ ቀዳ ። ከዚያ ጸሀይ ሙቀትና ከስሜቷ ንዝረት በኋላ የወሰደችው መጠጥ ራሷ ላይ ወጣ ። ሁለቱም ከመዋኛ የውስጥ ልብስ በስተቀር ምንም አልደረቡም ። ጁልስ አቅፎ ጨመቃት ። ሉሲም "ተው" ብላ ብትናገርም ከልቧ ያልሆነ መከላከል ስለነበር ጁልስ ከቶውንም ደንታ አልነበረውም ። በችኮላ የመ ዋኛ ውስጥ ልብሷን አውልቆ በትላልቅ ጡቶቿ መጫወ ትና አካሏን አገላብጦ መሳም ጀመረ ። ቆም አለና በች ኮላ እየታገለ የራሱን የመዋኛ ልብስ አወላለቀ ። እርቃ ናቸውን ተቃቅፈው አካሉ ሲዋሀዳት ተሰማት ። ከስሜቷ ጣሪያ ላይ ለመድረስ ብዙም አልቆየች ። እሱ የሚሰማውም ይሰማታል ። እሱም ተከትሏት ከስሜቱ ጣሪያ ላይ ደረሰ ።

ጁልስ እቅፉን ሲለቅ ፊቷን አዙራ በእፍረት ማል ቀስ ጀመረች ። ነገር ግን ጁልስ ፣ "አይ አንቺ ምስኪን ገጠሬ ፣ እምቢ ስትይኝ የከረምሽው ለዚህ ነበር ፣ አንቺ ጅል !" በማለት በለሰለሰ አንደበት ሳቀባት ። "አንቺ ጅል" እያለ በፍቅር ሲያነጋግራት ወደሱ ዞር ስትል እንቅ አድርጎ አቀፋት ።

"ፈጽሞ ጥንታዊት ነሽ !" እያለ በፍቅር ሲያጽና ናት ማልቀሷን ቀጠለች ።

ጁልስ ሲጋራውን ከአቀጣጠለ በኋላ ትን ብሏት ልቅሶዋን እንድታቆም ካፏ ውስጥ ከተተው ።

"ስሚኝ" አላት ጁልስ ፣ "ያለንበት ክፍለ ዘመን አስተዳደግ ቢኖርሽ ኑሮ ችግርሽ ከብዙ አመታት በፊት ተቃልሎ ነበር ። አሁን ችግርሽ ምን እንደሆነ ልንገርሽ? ያንቺ ችግር ቀዶ ጥገና የማያስተካክለው መልከ ጥፉ ነት ፣ ወይም የቆዳ ብልሽት ፣ ወይም የሸውራራነት

t.me/OLDBOOKSPDF

አይነት ችግር አይደለም ። ያንቺ ችግር እንደ አንድ እባጭ ወይም በቆዳ ላይ እንደሚታይ አንድ ልስልስ ወይም አንድ ቅርጹ የተበላሸ የጆሮ የውጭ ክፍል የሚቆጠር ነው ። ይህን ከፈቃደ ስጋ አስተሳሰብ አንጻር አትመልከችው ። ያንቺ ችግር ከአጥንትሽ ተዛንፎ መመስረት የመጣ ነው ። የዚህ አይነት ችግር ከወሊድ በኋላ ወይም በተፈጥሮ ይከሰታል ። ይህን የመሰለ ሁኔታ በብዙ ሰዎች ላይ ይታያል ። ብዙ ሴቶች በቀላሉ በቀዶ ጥገና ሊያስተካክሉት ሲችሉ የስቃይ ኑሮ ይገፋሉ ። አንዳንድ ሴቶች ለዚህ ብለው እራሳቸውን እስከ መግደል ይደርሳሉ ። እኔ ግን የሰውነትሽን ግሩም ቅርጽ ተመልከቼ እንዲህ ትሆኛለሽ ብዬ አልገመትኩም ነበር ። እኔ የመሰለኝ ከሶኒ ጋር በነበራችሁ ፍቅር የተነሳ የተፈጠረ ስነ ልቡናዊ ሁኔታ ነበር ። ስለዚህ አሁን የእካል ምርመራ ላድርግልሽና ምን ያህል ስራ እንደሚጠይቅ ልገልጽልሽ እችላለሁ ። በይ ሂጂና ገላሽን ታጠቢ”

ሉሲ ገላዋን ታጠበች ። እምቢ ለማለት ብታንገራ ግርም በለሆሳስ አልጋ ላይ አሰተኛቶ ጭኗን ከፈተው ። ለወትሮውም ትርፍ የህክምና መሳሪያ ከቤቱ ስለሚ ያስቀምጥ በመሳሪያ የመጣ አልተቸገረም ። ወዲያው ስራውን ጀምሮ ምርመራውን ቀጠለ ። ምርመራውን ሲያጠናቅቅ ፥

“ፍቅሬ ፥ እዚያ ታች ባጠቃላይ አዲስ ነገር ነው የማንጽልሽ ። ከዚያ በኋላ ከስራ ፍሬዬ የመጀመሪያውን እራሴ ነኝ የምቀምሰው ። በህክምና ምርመራ ታሪክ የመጀመሪያው ይሆናል ። ለህክምና ሙያ መጽሄትም የምርምር ውጤቴን ላቀርብ እችላለሁ” አላት ።

ጆልስ ይህን ሁሉ ሲያከናውን እያዝናናትና ፍቅሩን እየገለጸ ስለነበር እፍረቷም ጠፋ ። እንዲያውም አንድ የህክምና መጽሀፍ እንሰቶ ስለሁኔታው ሲያስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረዳት የበለጠ የማወቅ ጉጉት ሊያድርባት ቻለ ። ጁልስ በጤንነት አንጻርም ይህን የመሰለውን ሁኔታ በወቅቱ ካለማስተካከል የተነሳ የሚከተለውን ችግር ለሉሲ አነሳላት ። ይህ የተፈጥሮ መዋቅር በወቅቱ በቀዶ ጥገና ካልተስተካከለ አጥንቱ እየደከመ ይሄዳል ። የሚያሳዝነው ግን ሀኪሞችም በቅጡ ችግሩን ሳያገኙት ፥ ብዙ ሴቶችም ደብቀው መኖራቸው እንደሆነ ጁልስ ለሉሲ ሲነግራት ፥ "እባክህ ስለዚህ ነገር አታውራ" ብላ ተማጠነችው ።

እንደተገነዘበው ፥ በዚህ ሁኔታ አሁንም ቢሆን 'አስጸያፊ ጉድለት' ያለባት እየመሰላት ነው ። ስለዚህ ስሜቷ እንዲበረታታ ጨዋታውን መለወጥ ነበረበት ።

"እሺ እንግዲህ ፥ አሁን ያንቺን ምስጢር ስለተረዳሁ የኔንም እነግርሻለሁ ። በምስራቁ ክፍለ ግዛት እውቅ ሀኪም ሆኜ እዚህ ቦታ ምን እንደምሰራ ዘወትር ትጠይቂኛለሽ ። እንደ እውነቱ ከሆነ በጽንስ ማስወረድ ስራ ላይ ተሰማርቼ እሰራ ነበር ። የጽንስ ማስወረድ እንደማናቸውም—የህክምና ሙያ በራሱ መጥፎ ባይሆንም ህገወጥ በመሆኑና እኔም ፈጽሜው በመያዜ ጉዳት ሊደርስብኝ ነበር ። አብረን የተማርነው ኬኔዲ የተባለ ሀኪም ሊረዳኝ ፈለገ ። ኬኔዲ ለኮርሌዎኔ ቤተሰብ የሰራው ውለታ ስለነበር ወደፊት የቤተሰቡን እርዳታ በሚሻበት ወቅት ከመጠየቅ ወደኋላ እንዳይልቶም ሄገን አስገነዝቦት ነበር ። ስለዚህ ኬኔዲ የኔን በችግር ላይ መውደቅ ለቶም ሄገን ነገረው ። በተከታዩ ቀን የተከሰሰኩበት ወንጀል ፋይሉ ተዘጋ ። ነገር ግን የህክምና ሙያ ማህበር እና በምስራቅ ክፍለግዛት ያሉ ተቋሞች በመጥፎ ስም ስለመዘገቡኝ መስራት አልቻልኩም ። ስለዚህ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ይህን ስራ አገኘልኝ ። ጥሩ ህይወት እየመራሁ ነኝ ። መሰራት ያለበትን ስራ አከናውናለሁ ። እነዚህ ትርኢት የሚያሳዩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሴቶች ቶሎ ቶሎ ለእርግዝና ይጋለጣሉ ። እነሱን ማስወ
ረድ ቀላል ሰራ ነው ። መጥበሻ ላይ ያለ እራሪ የመቅ
ረፍ ያህል ቀፍፌ አወጣና አስወግድላቸዋለሁ ። ይገር
ምሻል ፥ ፍሬዲ ኮርሌዎኔ አደገኛ ሰው ሆኗል ። እዚህ
ከመጣሁ እንዳየሁት አስራ አምስቱን አስረግዟቸዋል ።
በጨብጥና በቂጥኝ በሽታ ተለክፎ ሶስት ጊዜ አክሚ
ዋለሁ ። ፍሬድ ጥንታዊ በሌጣ ፈረስ የሚጋልብ ሰው
ነው ። አንድ ቀን ስለዚህ ጉዳይ ምክር ሳልለግሰው
አልቀርም"

ጁልስ ንግግሩን አቆመ ። ይህን ሁሉ የግል ሚስጥር
ለሉሲ የነገራት ማንም ሰው ፥ እሷ የምታውቀው ፍሬድ
ሳይቀር ፥ የሚያሳፍር ሚስጥር እንዳለው እንድትገነዘብ
ነው ።

"ሁኔታውን አንድ መሳብ ሲገባው የመሳብ ችሎ
ታው የተጓደለበት አካልሽ አድርገሽ ገምቺው ። ከላዩ
ላይ ጥቂት ቆርጦ በማውጣት ማስተካከል ይቻላል"
አላት ።

"እሺ ላስብበት ። ግን ምን ያህል ወጪ ይጠይቀ
ኛል?" ስትል ሉሲ ጠየቀችው ።

ጁልስ ፊቱን ጨፍግግ አደረገና ፥ "እኔ ያለኝ መሳ
ሪያ ለዚህ አያገለግልም ። በዚህ ስራም ከፍተኛ ባለሙያ
አይደለሁም ። ነገር ግን በዚህ ሙያ የተካነና ለስራው
የሚሆን የተሟላ እቃና አገልግሎት ያለው ጓደኛዬ
በሎስ አንጀሊስ ከተማ ይኖራል ። እንደውነቱ ከሆነ
መኳኳል ብቻ በቂ አለመሆኑን ለተገነዘቡ የፊልም ተዋ
ንያንም ይህን የመሰለ ህክምና ያደርግላቸዋል ። ሀኪሙ
የኔ ውለታ አለበት ። ስለዚህ ምንም ዋጋ አይጠይቅ
ሽም ። እኔም እሱ ለሚልካቸው የጽንስ ውርጃ የሚፈልጉ
ሴቶች አገልግሎቴን አበርክቼላቸዋለሁ ። የሙያችን ስነ
ምግባር አይፈቅድምና ነው እንጂ ይህን የመሰለ ቀዶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥገና የተደረገላቸውን የፊልም ተዋንያን ስም ልነግርሽ በቻልኩ ነበር" አላት ።

ሉሲ ለማወቅ በመጓጓት ፥ "በል ንገረኝ" ስትል ገፋፋችው ። በወሬ ሞትኩ ባይነኟ ሳይታዘባት የማወቅ ጉጉትዋን ልታሳየው እንደምትችል ተገንዝባለች ።

"ከኔ ጋር እራት በልተሽ ሌሊቱንም አብረሽኝ የምታድሪ ከሆነ እነግርሻለሁ ። ልናካክሰው የሚገባን በየዋህነትሽ ምክንያት የባከነ ብዙ ጊዜ አለን ፥" አላት ጆልስ ።

ሉሲ ጆልስ በሚያሳያት ደግነት ከመጠን ያለፈ ፍቅር አደረባት ። "በአሁኑ ሁኔታዬ ልትደሰትብኝ ስለ ማትችል ከኔ ጋር መተኛት አያስፈልግህም ፥" አለችው ።

ጆልስ ከት ብሎ ሳቀና ፥ "አንቺ ጅል ፥ ሊታመን የማይችል የዋህነት ያጠቃሽ ፍጥረት ! ከዚህ ውጭ ፍቅር መለዋወጥ አይቻልም መሰለሽ ? እንዲያው በርግጥ እስከዚህ ሞኝ ነሽ ?" ሲል ጠየቃት ።

'ከተለመደው የፍቅር ልውውጥ ሌላ' ሲል ምን ማለቱ እንደሆን ሉሲ ስትጠይቀው ፥ ይህን የመሰለው ግንኙነት ጥንትም ይካሄድ የነበረና አዲስ አለመሆኑን ገለጸላት ። እንዲያውም ካሁን ቀደም ከሚቹ ወዳጅዋ ከሶኒ ጋር የነበራትን የፍቅር ልውውጥ ጠየቃት ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በእርግጥ አስደነቀችው ። የሞና ሊዛን የመሰለ ፈገግታ በማሳየት ፥ "ከሶኒ ጋር ያላደረግኩት የፍቅር ልውውጥ የለም" አለችው ። ይህን የመሰለ ግልጽነት ስታሳይ የመጀመሪያዋ ነበር ።

ከሁለት ሳምንታት በኋላ በሎስ አንጀሊስ ሆስፒታል የቀዶ ጥገና አዳራሽ ጓደኛው ዶክተር ኬልነር ቀዶ ጥገናውን ሲያካሂድ ጆልስ ሲጋል ቆሞ ተመለከተው ። ሉሲ ማደንዘዣ መድሀኒቱን ከመውሰድዋ በፊት ጆልስ ወደሷ ጠጋ ብሎ "የኔ ልዩ ወዳጅ መሆንሽን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነግሬዋለሁ ። ስለዚህ በጥንቃቄ ነው የሚገነባሽ” አላት እየቀለደ ። የወሰደችው የመጀመሪያ እንክብል ስላቆዘማት ሳቅም ሆነ ፈገግታ አላሳየችም ።

ቀዶ ጥገናው አድካሚ እና ብዙ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነበር ። በተለይም ተሳስቶ አንድ የደም ስር ወይም ጅማት ቢበጥስ ከፊንጢጣ ጋር የተያያዘ አካል በመሆኑ ብዙ ችግር ሊያስከትል ይችላል ። እያንዳንዷን እንቅስቃሴውን ጆልስ በአንክሮ ተከታትሎታል ።

በመጨረሻ አድካሚው ስራ ተጠናቀቀ ። ሉሲን ወደ ማገገሚያ ክፍል በባለተሽከርካሪ አልጋ ወሰዷት ። ጆልስ ኬልነርን ሲያነጋግረው ኬልነር ፊት ላይ ፈገግታ አየበት ። ስለዚህ ቀዶ ጥገናው ተሳክቷል ማለት ነው ።

“ምንም አስቸጋሪ ሁኔታ አልተከሰተም ። ብዙዎች ላይ እንደሚታየው ሳይሆን ቅርጿ በጣም ማራኪ ነው ። ከዚህ በኋላ ለፍቅር ልውውጥ የሚያከላት አይኖርም ። ብቻ ላንተ አዘንኩልህ ። ግን ጥቂት መቆየት አለብህ ። ታዲያ የስራው ውጤት መልካም እንደሚሆን አረጋግጥልሀለሁ” አለው ኬልነር ።

ጆልስ ሳቀና ፣ “በእርግጥ አንተ ሴቶችን መቅረጽ የምትችል ሀኪም ነህ ። እውነቴን ነው የምልህ ፣ ተአምረኛ ነህ” አለው ።

ኬልነር አጉረመረመና ፣ “የልጆች ጨዋታ እኮ ነው ፣ ልክ እንዳንተ ጽንስ ማስወረድ ። ሀብረተሰቡ በተጨባጩ ሁኔታ ላይ ግንዛቤ ቢወስድ ኑሮ አንተና እኔ ከዚህ የበለጠ ስራ በመስራት ለሌሎች ከበታቾችን ላሉ ባለሙያዎች ይህን ስራ እንተውላቸው ነበር ። በነገራችን ላይ የአንዷን ቆንጆ ጽንስ እንድታስወርድላት በሚቀጥለው ሳምንት መዳንቱ እልካታለሁ ። ስለዚህ የዛሬው ስራዬ ዋጋ ከምትሰራልኝ ስራ ጋር ይጣጣል” አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጆልስ እጁን ጨበጠውና ፥ "እመሰግናለሁ ዶክተር ። እራስህ አንድ ቀን እኔ አካባቢ ብቅ ብትል ያለሁበት ድርጅት የሚያቀርበው መስተንግዶ ሁሉ ይደረግልሀል" ሲል አረጋገጠለት ።

ኬልነር የምጸት ፈገግታ አሳይቶት ፥ "በየቀኑ ስለ ምቆምር ያንተን ሩሌት የምትሉት የተሽከርካሪ ላይ ቁማር አልሻውም ። ዘወትር ከእጣ ጋር ውርርድ እገጥማለሁ ። አንተ ግን እዚያ ጊዜህን እያባከንክ ነው ። አንድ ሁለት አመት ከቆየህ በኋላ ስለ ቀዶ ጥገና መርሳትህ አይቀርም። እዚያ ሁነህ ከጊዜው ጋር መሄድ አትችልም" አለው ።

ይህ አባባል ሊያነቃውና ሊያስጠነቅቀው እንጂ በን ቀት ሊወቅሰው እንዳልሆነ ጆልስ ተገንዝቦታል ። ነገር ግን በዚህ ንግግር ስሜቱ ሳይነካ አልቀረም ። ሉሲ ቢያ ንስ ለተከታዮቹ አስራ ሁለት ሰአታት ከማገገሚያ ክፍል እንደማትወጣ ስለሚያውቅ ከተማ ሄዶ እስኪሰ ከር ጠጣ ። የስካሩ አንዱ ምክንያት የሉሲ ቀዶ ጥገና መሳካት ያስገኘለት እፎይታ ነበር ።

በተከታዩ ቀን ጠዋት ጆልስ ሉሲን ሊጐበኛት ሀኪም ቤት ሲሄድ ካልጋው አጠገብ ሁለት ሰዎች አየ ። ክፍሏ በአበባ ተሞልቷል ። ሉሲ በትራስ ተመቻ ችታ ጋደም ብላለች ። ፊቷ ያበራል ። ቀደም ሲል ሀኪም ቤት ስትገባ አደጋ ካልደረሰባት ከዘመዶቿ ማንም እንዳይሰማ ጆልስን አስጠንቅቃው ስለነበር በአሁኑ ሁኔታ ተደነቀ ። በርግጥ ፍሬድ ለቀላል ቀዶ ጥገና ሀኪም ቤት እንደገባች ያውቃል ። የሉሲን የህክምና ወጪ በሙሉ ሆቴሉ እንደሚሸፍን ለጆልስ ነግሮታል ።

ሉሲ ስታስተዋውቃቸው ጆልስ አንደኛውን ሰውዬ ወዲያው አወቀው ። ይህ ሰው ዝነኛው ጆኒ ፎንቴን ፥ አብሮት ያለው ደግሞ ኒኖ ቫሌንቲ ነበሩ ። ሁለቱም

t.me/OLDBOOKSPDF

የጁልስን እጅ ከጨበጡ በኋላ ከቁም ነገርም አልቆጠሩትም ። ከሉሲ ጋር ይቃለዳሉ ። የጥንቱን የሰፈር ወሬና ጁልስ ስለማያውቃቸው ሰዎች ያወራሉ ። ስለዚህ ጁልስ ሉሲን ፥

"ቆይቼ እመለሳለሁ ፥ ዶክተር ኬልነርን ማየት አለብኝ" አላት ።

ይህን ጊዜ ጆኒ ፎንቴን ወደሱ ዞረና ፥ "ስማ ወንድም ፥ እኛ መሄዳችን ነው ፥ ከሉሲ ጋር አብርሀት ሁን ፥ በሚገባ ጠብቃት ፥ ዶክተር" አለው ። ጆኒ ሲያነጋግረው ድምጹ የሻከረ መሆኑ ጁልስ ተሰማው ። ወዲያው ይህ ሰው ለብዙ ጊዜ አለመዝፈኑ ያገኘውም ሽልማት ለተዋናይነቱ መሆኑ ትዝ አለው ። ይህ ሁኔታ በቅርቡ የደረሰበት ነው? ጋዜጦችስ ለምን ሚስጥር አድርገው ያዙት? ጁልስ ወሬ ይወዳል ። ጆኒ ሲነጋገር ስለድምጹ ሁኔታ ለመረዳት ፈለገ ። ምናልባት ቀላል ነገር ይሆን? ብዙ መጠጥ ፥ ብዙ ሲጃራ ማጨስ ወይስ ብዙ መዳራት ያስከተለበት ጊዜያዊ የድምጽ መሻከር ይሆን? ድምጹ የሚያስጠላ ቃና አለበት ። እንዲህ ሆኖ ከቀጠለማ ጣፋጭ ድምጹን መረዋ ብሎ የሚጠራውም አይኖር ።

"ጉንፋን የያዘህ ትመስላለህ" አለው ጁልስ ጆኒ ፎንቴንን ።

ፎንቴን በትህትና እንዲህ ሲል መለሰለት ፥

"ጊዜያዊ ውጥረት ነው ፥ ትላንት ልዘፍን ሞክሬ ነበር ። የድምጼን መለወጥ ለመቀበል አልቻልኩም ። እያረጀሁም ነው"

ጁልስ በድንገት "ሀኪም እንዲያይልህ አላደረግክም? ምናልባት እኮ ሊስተካከል የሚችል ጉዳይ ሊሆን ይችላል" አለው ።

ፎንቴን ፈገግታው ተለወጠ ። ጁልስን ቀዝቀዝ ያለ አመለካከት አሳየው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ከሁለት አመት በፊት ያደረግኩት አሁን አንተ ያልከኝን ነበር ። በአገሪቱ ላይ አሉ ከሚባሉት ከፍተኛ ስፔሻሊስቶች ዘንድ ሄጃለሁ ። በካሊፎርኒያ ዝነኛ የሆነው የኔ ልዩ ሀኪምም መርምሮኛል ። የተነገረኝ ብዙ እረ ፍት እንዳደርግ ነው ። ምንም ህመም አይደለም ። የእ ድሜ መግፋት ጉዳይ ነው ። ሰው ሲያረጅ ድምጹ እየተ ለወጠ ይሄዳል" አለው ጆኒ ፎንቴን ።

ይህን ካለ በኋላ ችላ ብሎት ፥ ወትሮም ቢሆን ማንኛይቱንም ሴት እንደሚማርክ ሁሉ ፥ ሉሲንም በጨ ዋታው መማረክ ጀመረ ። ጁልስ የፎንቴንን ድምጽ በጽ ሞና አዳመጠ ። አንድ አይነት እባጭ በድምጽ ሳጥኑ ውስጥ መኖር አለበት ። ታዲያ ልዩ ሀኪሙ ለምን መለ የት አቃተው? ቀዶ ጥገና ሊደረግለት የማይችል ነቀርሳ ይሆን?

ጁልስ ፎንቴንን ከጨዋታው አቋረጠውና ፥ "ለመጨረሻ ጊዜ የተመረመርከው መቼ ነበር?" ሲል ጠየቀው ።

ፎንቴን በጥያቄው ተናዷል ። ነገር ግን ለሉሲ ብሎ ትህትና ሊያሳየው ፈለገ ።

"ከአስራ ስምንት ወራት በፊት ነው የተመረመርኩት ፥" አለው ።

"ሀኪምህ በየወቅቱ ያይሀል ?"

"አዎን ያየኛል ፥" አለ ጆኒ በመናደድ ። "ከኮዲን የተሰራ የሚረጭ መድሀኒት ይሰጠኛል ። ድምጼ ግር ጀቱንም ነግሮኛል ። መጠጥ ፥ ማጤስ ፥ እና ሌሎችም ጉዳዮች ናቸው መነሻዎቹ ብሎኛል ። እንግዲህ አንተ ከዚህ የተሻለ የምታውቀው ነገር አለ?"

"የሀኪምህ ስም ማነው?" አለና ጁልስ ጠየቀው ።

ፎንቴን በኩራት "ታከር ይባላል ። ዶክተር ጀምስ ታከር ነው ። ስለሱ ምን ታውቃለህ?" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጆልስ የዚህን ሰው ስምና ተዋንያንን እንደሚያ
ክም ፥ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሀኪም ቤት እንዳለው ያው
ቃል ።

"አለባበስ ያውቃል ፥" አለው ጆልስ በፈገግታ ።

ፍንቴን አሁን ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም ።
"አንተ ከሱ የተሻልኩ ሀኪም ነኝ ብለህ ትገምታለህ?"
ሲል ፍንቴን በንቀት ጠየቀው ።

ጆልስ ሳቀና "አንተስ ከካርሜን ሎምባርዶ የተሻ
ልኩ ዘፋኝ ነኝ ብለህ ታስባለህ?" በማለት ጥያቄውን
በጥያቄ መለሰለት ። ይህን ሲል ኒኖ ቫሌንቲ እራሱን
ከወንበሩ ጋር እያላተመ ሲንከተከት ጆልስ በመገረም
ተመለከተው ። ቀልዱ ያን ያህል የሚያስቅ አልነበረም ።
ኒኖ እንደዚያ እየተንከተከተ ሲገለፍጥ የጠጣው ዊስኪ
ጆልስን ሸተተው ። ይህ ሰው በከፊልም ቢሆን ሰክሯል
ማለት ነው ።

ፍንቴን ጓደኛው ላይ ፈገግ አለና ፥ "ስማ ፥ በኔ
ቀልድ ነው እንጂ በሱ ቀልድ መሳቅ አይገባህም"
አለው ። ይህን ጊዜ ሉሲ እጅዋን ዘርግታ ጆልስን ወደ
አልጋዋ አስጠጋችው ።

"ምንም የማያውቅ ቀሽም ይምሰልህ እንጂ ጐበዝ
የቀዶ ጥገና ሀኪም ነው ። ከዶክተር ታከር እሻላለሁ
ካለ የተሻለ መሆኑ እርግጠኛ ነው ። የሚልህን አድም
ጠው ፥ ጆኒ" አለች ሉሲ ።

ሀኪሙ ለሉሲ የሚያደርግላት ሀክምና ስላለ
ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ ነርሷ ጠየቀቻቸው ። ጆኒና
ኒኖ ሉሲን ሊስሟት ሲጠጓት ጉንጯን ሰጠቻቸው ።
ጆልስን ግን ከንፈሩን ከሳመችው በኋላ ፥ "እባክህን ፥
ከሰአት በኋላ ና" ብላ ጠየቀችው ። ጆልስም በእሽታ
ራሱን ነቀነቀ ።

ወጣ ብለው ኮሪደር ውስጥ እንዳሉ ፥ "ቀዶ ጥገናው

t.me/OLDBOOKSPDF

የምንድነው? የሚያሰጋ ነገር ነው?" ሲል ኒኖ ጁልስን ጠየቀው ።

ጁልስ እራሱን በአሉታ ነቀነቀና ፥ "ሴቶችን የሚ መለከት ቀላል ቀዶ ጥገና ነው ። የሚያሰጋ ነገር የለበ ትም ፥ እመነኝ ። ካንተ የበለጠ ለሷ አስባለሁ ። ይህችን ልጅ እንደማገባት ተስፋ አለኝ" አለው ።

ጆኒና ኒኖ ይህን ሲላቸው ሊገምቱት እንደሚሞክሩ አይነት አዩት ። ሀኪም ቤት መግባቷን ማን እንደነግ ራቸው ሲጠይቃቸው የነገራቸው ፍሬድ መሆኑን ገለጹ ለት ።

"ሁላችንም አንድ ሰፈር ነው ያደግነው ። ያፍሬድ እህት ስታገባ ሉሲ ሚዜዋ ነበረች" አለ ጆኒ ።

ጁልስ ታሪኩን እንደማያውቅ ሆኖ ሰማቸው ። እነሱ ግን የሶኒን እና የሉሲን ወዳጅነት አልገለጹለትም ።

በኮሪደሩ ሲጓዙ ጁልስ ፥ "እኔ በዚህ ሀኪም ቤት ውስጥ የጮብኝ ሀኪም መብት ስላለኝ ለምን ጉሮሮህን አላይልህም?" ሲል ጆኒ ፎንቴንን ጠየቀው ።

"እቸኩላለሁ" አለው ጆኒ ፎንቴን ።

ኒኖ ቫሌንቲም ቀበል አደረገና ፥ "የሱ ጉሮሮ ሚሊ ዮን ብር የሚያወጣ ጉሮሮ ነው ። ማንም ርካሽ ሀኪም ሊመረምረው አይችልም" ብሎ ፈገግታ ሲያሳየው ፥ ጁልስ ኒኖ ለሱ እያገዘ ጓደኛው ላይ እንደሚቀልድ ገባው ።

ጁልስም በመዝናናት ፥ "እኔ ርካሽ ሀኪም አይደ ለሁም ። በጽንስ ማስወረድ ከመወንጀሌ በፊት በምስ ራቅ ክፍለ ግዛት አሉ ከሚባሉት ዝነኛ ሀኪሞች አንዱ ነበርኩ" አላቸው ።

ይህን ጊዜ እነሱም ይህ ሰው ጉዱን ለመናገር ካልፈራ ቀላል አለመሆኑን በመገንዘብ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጡት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ጆኒ ሊጠቀምብህ ካልቻለ አንድ እንድታያት የምፈልግ ወዳጅ አለችኝ ። ታዲያ ጉሮሮዋን አይደለም የምታይልኝ” አለው ኒኖ ።

ፎንቴን በመስጋት ፥ “ጉሮሮዬን ለማየት ምን ያህል ጊዜ ትፈጃለህ?” ሲል ጠየቀው ።

“አስር ደቂቃ” አለው ጁልስ ። ይህን ሲለው እውነቱን እንዳልሆነ ጁልስ ያውቀዋል ። እውነት መና ገርና ህክምና በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር አብረው ሊሄዱ አይችሉም ።

“እሺ ይሁን” አለ ፎንቴን ፥ በሻከረና ፍርሀት በተሞላበት ድምጽ ።

ጁልስ አንድ የምትረዳው ነርስና የምርመራ ክፍል እንዲዘጋጅለት አደረገ ። ክፍሉ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ባይዝም ፥ ለጊዜው በቂ ነበር ። እንዳለው በአስር ደቂቃ ውስጥ በድምጽ መተላለፊያዎቹ ላይ ያበጡ ነገሮችን ብቻ በመመልከቱ ጉዳዩ ቀላል መሆኑን ተረዳ ። ያ ታከር የሚሉት ብቃት አልባ የሆነ የሆሊ ዉድ አታላይ ዘምዛሚ ይህን ቀላል ነገር እንኳን አይቶ መረዳት ነበረበት ። ያንተ ያለህ ፥ ምናልባት ሰውዬው የህክምና ሰራ ፈቃድ ያለውም አይመስልም ። ቢናረ ውም መነጠቅ አለበት ። ጁልስ አሁን ፎንቴንና ኒኖን ምንም ከቁም ነገር አልጣፋቸውም ። ሰልክ አነሳና በሆ ስፒታሉ የሚገኘውን የጉሮሮ ስፔሽያሊስት እንዲመጣ ጠራው ። ወደ ኒኖም ዞረና ፥ “እንደሚመስለኝ ብዙ ስለ ሚያስጠብቅህ ብትሄድ ይሻላል” አለው ።

ፎንቴን ጁልስን ማመን ባቃተው ገጽታ ተመለ ከተው ።

“አንተ የውሻ ልጅ ፥ እዚህ ልታቆየኝ የምትችል ይመስልሀል? ጉሮሮዬስ ያንተ መጫወቻ መሰለህ?” አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጁልስ ደስ እያለው እቅጩን ነገረው ። "እንግዲህ እንደመሰለህ ። የፈለግከውን ማድረግ ትችላለህ ። በድምጽ ቢንቢህ ላይ ያበጠ ስጋ ይታያል ። ለሚቀጥሉት ጥቂት ሰአታት እዚህ መቆየት ከቻልክ ካንሰር ይሁን ወይም ተራ እባጭ ለይተን ለማወቅ እንችላለን ። ከዚያም ቀዶ ጥገና ወይም ሌላ ህክምና ያስፈልገው እንደሆን እንወስናለን ። የበሽታህን ሙሉ ታሪክም ልገልጽልህ እችላለሁ ። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘሁት በአሜሪካ የሚገኘውን ከፍተኛ ስፔሽያሊስትም ዛሬ ማታ በአውሮፕላን እንዲመጣ ላደርግ እችላለሁ ። ታዲያ የገንዘቡ ወጭ ያንተ ነው የሚሆነው ። አይ ካልክም ከዚያ የፈዝ ሀኪምህ ዘንድ ወይም ሌላ ሀኪም ዘንድ ለመሄድ እስክትወስን በፍርሀት መንቀጥቀጥ ወይም ብቃት አልባ የሆነ ሀኪም ዘንድ ሂደህ መታየት ትችላለህ ። እብጠቱ የሚሰራጭ ከሆነም ባጠቃላይ የድምጽ ሳጥንህ መውጣት ይኖርበታል ። አለበለዚያ ትሞታለህ ። ይልቁንስ ከኔ ጋር ቆይና በጥቂት ሰአታት ውስጥ ሁኔታዎችን ማጣራት እንችላለን ። ከዚህ የበለጠ ስራ ይኖርብሀል?" አለና ጁልስ ጆኒን ጠየቀው ።

"እባክህ ትንሽ እንቆይና እንመልከት ፥ ጆኒ" አለኒና ። "ታች ሄጄ ወደስቱዲዮ ደውዬ ሌላ ነገር ሳልገልጽላቸው ትንሽ እንደምንቆይ ብቻ ልንገራቸው ። ከደወልኩ በኋላ እመለስና አብሬህ እቆያለሁ ።"

ጆኒ ለምርመራው የቆየበት ሰአት ረዥም ቢሆኑም ውጤቱ መልካም ነበር ። አፉ አዮዲን በተነከረ ጥጥ ተሞልቶ ስለሰለቸው ለማቋረጥም ፈልጐ ነበር ። ኒና ቫሌንቲ ግን ሊነሳ ሲል ገፍቶ መልሶ አስቀመጠው ። ሁሉ ነገር ሲያበቃ ጁልስ እየሳቀ ተራ እባጭ እንደሆነ ሲገልጽለት ፥

"አንድ አይነት እባጭ ነው ። ቀፈን እናወጣዋለን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በጥቂት መራት ውስጥ ፈጽሞ ይሻልሀል" አለው ።
"ከዚህ በኋላ መዝፈንስ ይቻለኛል?" ሲል ጆኒ ጠየቀው ።

ጁልስ ትከሻውን ነቀነቀና ፥ "ስለሱ እንኳን ዋስ ትና ልሰጥህ አልችልም ። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ስለማትዘፍን ምን ልዩነት ይኖረዋል?ባ አለው ።

ጆኒ ፎንቴን በሸቀና "አንተ ጉር" ፥ ለመሆኑ የም ትናገረውን ታውቀዋለህ? ምናልባት ወደፊት ፈጽሞ ልዘ ፍን እንደማልችል የምትነግረኝ በጎ ነገር የነገርከኝ መሰለህ" አለው ።

በመጨረሻም ጁልስ ትእግስቱ አለቀ ። እንደ መል ካም ሀኪም ምርመራውን በተሳካ ሁኔታ አከናውኗል ። ለዚህ ዲቃላ ይህን የመሰለ በጎ ተግባር ፈጽሞለት ፥ እሱ ግን ቁምነገር እንደሰራለት አልቆጠረውም ። ስለዚህ ጁልስ እንዲህ አለው ፥

"ስማ ሚስተር ፎንቴን ፥ የህክምና ዶክተር ስለ ሆንኩ እገሌ ብለህ ትጠራኛለህ እንጂ ጉርባ አትለኝም ። ስለጉሮሮህ የነገርኩህ ዜናም መልካም ዜና ይመስለኛል ። እዚህ ተኝተህ ስመረምርህ ሊሠራጭ የሚችል በድ ምጽ ሳጥንህ ላይ የደረሰ ደዌ ነበር የመሰለኝ ። እንዲያ ውም ምናልባትም ለሞት የሚያደርስህ ጉዳይ ይሆንና ይህንንም እነግርህ ይሆናል ብዬ ፈርቼ ነበር ። ነገር ግን አሁን ተራ እባጭ መሆኑን ስገልጽልህ በበኩሌ ደስ ብሎኛል ። በእርግጥ ዘፈንህ አስደስቶኛል ። በልጅነቴ ወጣት ሴቶችን ለማሸኮርመም ረድቶኛል ። ጥበበኛ ዘፋኝ እንደነበርክ አይካድም ። በሌላ በኩል ግን ብልሹ ሰው ነህ ። ለመሆኑ አንተ ጆኒ ፎንቴን ስለሆንክ ካንሰር የማይይዝህ መሰለህ? ወይስ አንጐልህ ውስጥ በቀዶ ጥገና ሊድን የማይችል እጢ ሊወጣብህ ወይንም ልብ ድካም ሊይዝህ አይችልም? ከቶውንም የማትሞት ይመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስልህል? ስለዚህ ፥ ሁሉ ነገር ጣፋጭ ሙዚቃ ብቻ አይደ
ለምና ፥ መከራ ውስጥ መግባት ከፈለግህ ከዚህ ሀኪም
ቤት ወጥተህ ሂድና ስለ እባጭ የፍቅር ዘፈን መዝፈን
ትችላለህ ። ይልቁንስ ፍሬ ቢስ መሆኑን ተወውና ማድ
ረግ የሚገባህን ነገር በቁም ነገር አከናውን ። ያንተው
ሥልጡን ሀኪም ጥሩ የቀዶ ጥገና ሀኪም ሊያገኝልህ
ይችላል ። ነገር ግን እኔ ራሴ ላድርግ ካለህ በነፍስ ግድያ
ሙከራ አሳስረው ።"

ይህን ካለው በኋላ ጁልስ ጥሎት ከክፍሉ ሊወጣ
ሲነሳ ኒኖ ቫሌንቲ ፥

"እንዲህ ንገርልኝ እንጂ ፥ ዶክተር!" አለው ።

ጁልስ ወደ ኒኖ ዞር ብሎ ፥ "ሁልጊዜ ነው ከቀትር
በፊት አፍህ የሚተሳሰረው ?" አለው ።

"አዎን" አለ ጆኒ ፥ በጎ ፈቃድ በሚያንጸባርቅበት
ፈገግታ ።

"በዚህ አይነት ከቀጠልክ ከአምስት አመት በኋላ
ሟች መሆንህን ማወቅ አለብህ" አለና ጁልስ አስጠ
ነቀቀው ። ኒኖ እየተቅለሰለሰ በጭፈራ እርምጃ ወደ
ጁልስ ጠጋ ብሎ ሲያቅፈው አፉ ቦርቦን ዊስኪ ያውዳል ።

ኒኖ በጣም ሳቀና ፥ "አምስት አመት? ያን ሁሉ
ዘመን ይፈጃል ?" ሲል አፌዘ ።

ሉሲ ቀዶ ጥገና ተደርጎላት ወር ከቆየች በኋላ
በቬጋስ ሆቴል መዋኛ ዳር ሁና በአንድ እጅዋ መጠጥ
ይዛ በሌላው እጅዋ በጭኗ ላይ የተጋደመውን ጁልስን
እየደባበሰች ቁጭ ብላለች ።

"አትፍሪ ፥ ከቤቴ ማበረታቻ የሚሆን ሻምፓኝ
ይጠብቀናል" አላት ጁልስ ።

"እንዲህ ባጭር ጊዜ ብናደርግ ምንም አይሆንም
እርግጠኛ ነህ ?" ስትል በፍርሀት ጠየቀችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ነኝ ሀኪሙ ፡ ዛሬ ማታ ታላቅ ምሽት ይሆናል ። ለመሆኑ በህክምና አለም ውስጥ የህክምና ሙያውን ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋደሰ ሀኪም እንደምሆን ተገንዝበሻል? ከቀዶ ጥገናው በፊት እና በኋላ ያለውን ሁኔታ ማለት ነው ። ለህክምና ባለሙያዎች በጽሁፍ አቀርባለሁ ። ከስነልቡናዊ ጠቀሜታ አንጻር ከቀዶ ጥገና በፊት የነበረው ያስደሰተኝ ቢሆንም የኋለኛው ግን ስሜትን ከመኮርኮር አንጻር ብልጫ እንደሚኖረው ግልጽ ነው" ሲል ሉሲ ንግግሩ ስላልጣማት ጸጉሩን ስትነጪው አቋረጣት ።

ሉሲ ፈገግ ብላ ቁልቁል አይታው ፡ "ዛሬ ማታ መርካት ካልቻልክ ጥፋቱ ያንተ ነው ማለት እችላለሁ" አለችው ።

"ለስራዬ ዋስትና እሰጣለሁ ። ኬልነር እንዲሰራ ቢደረግም እቅዱ የኔ ነበር ። ይልቅስ አሁን እረፍት እናድርግ ፡ ለረኸም ምሽት የሚያቆየን የምርምር ስራ ይጠብቀናል" አላት ።

ሁለቱ አብረው መኖር ጀምረዋል ። ወደ መኝታ ክፍላቸው ሲገቡ ሉሲ የሚያስደንቅ ነገር አጋጠማት ። በአንድ በኩል ምግብና መጠጥ ተደርድሯል ። ከሻምፓኝ ብርጭቆዋ ጐን ከአልማዝ የተሰራ ትልቅ የጋብቻ ቀለበት ተቀምጧል ።

"በስራዬ ምን ያህል እንደምተማመን እዚህ የም ታዪው ነገር መረጃ ይሆንሻል ። እስኪ የሚገባሽ መሆ ኑን እናረጋግጥ !" አላት ጆልስ ።

ይህን ሲላት ፡ ፍቅርና ጨዋነት በተሞላበት አነጋ ገር ነበር ። በመጀመሪያ እንደ መፍራት ፡ ሲነካትም እንደ መሸሽ ብላ ነበር ። ነገር ግን ከሱ ባገኘችው ማረጋገጫ ተረጋጋች ። ሰውነቷ ካሁን ቀደም ያልገጠመው አይነት የፍቅር ስሜት ሲገነባ ተሰማት ። የመጀመሪያውን ፍቅር

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተለዋወጡ በኋላ ጁልስ ቀስ ብሎ በጆሮዋ ፥ "ስራዬ እኮ ጥሩ ነው" አላት ።

"አዎን ፥ ልክ ነህ ፥ ጥሩ ስራ ሰርተሀል" ብላ መለሰችለት ። ሁለቱም በሳቅ ፈነዱ ። እንደገናም ፍቅር ጀመሩ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ ስድስት
ምእራፍ ሀያ ሶስት

ሚካኤል ኮርሌዎኔ በሲሲሊ ከአምስት ወራት ስደት በኋላ ያባቱን ባህሪና እጣውንም መገንዘብ ቻለ። ሉካ ቭራሲን የመሰሉ ሰዎችን፥ ምህረት የለሹን ክሌሚንዛን፥ እጅ የሰጠችውና ሚናዋን ተገንዝባ የተቀበለች ውን እናቱን ሳይቀር በውል ተረዳቸው። እነዚህ ሰዎች በሲሲሊ የሚኖሩ ቢሆኑና ከእጣቸው ጋር ተጋድሎ አናደርግም ቢሉ ምን ሊደርስባቸው ይችል እንደነበር አወቀ። ዶኑ ዘወትር 'የሰው ልጅ እጣው አንድ ነች' እያለ ይናገር የነበረው አባባል ገና አሁን ገባው። በስልጣን ትምክህተኞች፥ ህጋዊ በሆነው መንግስታዊ ስርአት፥ እንዲሁም የአሜርታን አይቶና ሰምቶ ዝም የማለት ህግ በሚጥስ ሰው ላይ የሚደረገውን ጥላቻ ሁሉ ተገነዘበ።

ወደ ሲሲሊ ተጉዞ ፓሌርሞ ከምትባለው ወደብ ከደረሰ በኋላ አሮጌ ልብሱን ለብሶ፥ ሾጣጣ ቆብ ደፍቶ የአባቱ ባለውለታ የሆነ የማፊያ ሹም ከሚኖርበት የሲሲሊ መሀል አገር ዘለቀ። ከተማይቱ ጥንት ዶኑ ወደ አሜሪካ ተጉዞ ስሙን ሲለውጥ የተጠራባት ኮርሌዎኔ የምትባለው ናት። ዛሬ የዶኑ ዘመዶች የሉም። ሴቶቹ በእርጅና አልፈዋል። ወንዶቹ ደግሞ በእርስበርስ ብቀላ አልቀዋል። ወይም ወደ አሜሪካ ወይም ብራዚል ወይም ወደ ሌላ ኢጣሊያ ክፍለ ሀገር ሸሽተዋል። ይህች ከተማ በአለም ላይ ከፍተኛው የግድያ ወንጀል የሚፈጸምባት እንደሆነች ሚካኤል ሊረዳ ችሏል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል ዶን ቶማሲኖ ከተባለ ብቸኛ የሆነ የማ
ፊያ ሹም ቤት በእንግድነት እንዲኖር ተደረገ ።
አጐትየው በሰባ አመት እድሜው የአካባቢው ሀኪም
ሆኖ ይሰራል ። እድሜው ከአምሳዎቹ መገባደጃ ላይ የሚ
ገኘው የማፊያ ሹም ፤ ዶን ቶማሲኖ ፤ ከሲሲሊ ታላላቅ
መሳፍንት አንዱ ለያዘው ሰፊ መሬት አስተዳዳሪ ነው ።

አንድ የባለርስት አስተዳዳሪ ለተወከለበት እርስት
የበላይ ተመልካች ከመሆኑም በላይ ድሆች ያልታረሰ
መሬት አገኝን ብለው አልፈው አልፈው እንዳያርሱ
ወይም እውስጡ አደን እንዳያድኑ ተገቢውን ጥበቃ ያደ
ርጋል ። ባጭሩ ፥ ይህ ሰው የተወሰነ ገንዘብ እየተከፈ
ለው የሀብታሞችን እርስት በመጠበቅ ድሆች ማናቸውንም
ህጋዊም ሆነ ህገወጥ የመብት ጥያቄ እንዳያነሱ የሚከ
ላከል የማፊያ ሹም ነው ። አንድ ድሀ ፥ ሀጉ በሚፈቅድ
ለት መሰረት ፥ ያልታረሰ መሬት ለመግዛት ቢሞክር
የባለርስቱ አስተዳዳሪ በድብደባ ያስፈራራዋል ፥ ወይም
ይገድለዋል ። ጉዳዩ እስከዚህ ቁልጭ ያለ ነበር ።

ዶን ቶማሲኖ በአካባቢው የሚገኘውን የውሀ ባለ
መብትነት ከመቆጣጠሩም በላይ የጣልያን መንግስት
ለአካባቢው ህብረተሰብ አዳዲስ ግድብ እንዲሰራለት
የሚል ነጥብ ሲያነሳ በድምጽ ማእቀቡ ያከሽፈዋል ።
የግድቦች መሰራት የውሀን ዋጋ በማርከስ ለህብረተሰቡ
የሚሸጠውን የጉድጓድ ውሀ የደራ ገበያ ያዳክመዋል ።
ዶን ቶማሲኖ ይህን የመሰለ ደባ ይፈጽም እንጂ የአደገኛ
እጽና ሽርሙጥና ንግድ ሲያልፉም አይነኩት ። በዚህ
የተነሳ ከአዳዲሶቹና ከታዳጊዎቹ የማፊያ ሹሞች ጋር
ቅራኔ ፈጥሯል ። ዶን ቶማሲኖ በአካሉ ግዙፍነት የተነሳ
ሰዎች ይፈሩታል ። በሱ ከለላ ስር እስካለ ድረስ ሚካኤልን
የሚያስፈራው ነገር ባይኖርም ስደተኛነቱንና ማንነቱን
መደበቅ አስፈላጊ ሆኗል ። ስለዚህ ሚካኤል ዶክተር ታዛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተባለው የዶን ቶማሲኖ አጐት የግንብ አጥር ውጭ እንዳይወጣ ተደረገ ።

ዶክተር ታዛ በሲሲሊያውያን አይን ረኽም ሊባል የሚችል ፥ ፊቱ ብስል ቀይ ፥ ጸጉሩ እንደበረዶ ነጭ ሲሆን ዛሬም በሰባ እመቱ በየሳምንቱ ፓሌርሞ እየሄደ በተለይ ልጅ እግር ሴትኛ አዳሪዎችን ይጐበኛቸዋል ። የዚህ ሽማግሌ ሌላው አመሉ ማንበብ ነው ። ማናቸውንም ጽሁፍ ያነባል ። ያነበበውንም ጽሁፍ ለወዳጆቹ ፥ ማይ ምነት ለሚያጠቃቸው ሰዎችና ፥ ለእረኞች ማውራት ስለ ሚወድ የአካባቢው ሰው እንደሞኝ ቆጥሮታል ። ወትሮስ ቢሆን ለነዚህ ሰዎች መጽሀፍ ምን ይሰራላቸዋል ?

ማታ ማታ ዶክተር ታዛ ፥ ዶን ቶማሲኖና ሚካኤል የእብነበረድ ሀውልቶች በተሞሉበት የአትክልት ስፍራ ውስጥ ቁጭ ይላሉ ። የሀውልቱ ብዛት ልክ በየስፍራው እንደሚታየው የወይን ፍሬ የበቀለ ይመስላል ። ዶክተር ታዛ ስለማፊያ ታሪክና ገድል ማውራት ይወዳል ። ሚካ ኤልም በጽሞና ያዳምጠዋል ። አንዳንድ ጊዜ ለስላሳው አየር ፥ ከፍሬያማ ወይን ተጨምቆ ሞቅ የሚያደርገው ወይንጠጅ ፥ የአትክልቱ ግርማና ምኞት ስሜቱን ሲነ ካው ዶን ቶማሲኖም በሱ በራሱ የደረሰበትን ያወራላ ቸዋል ። ዶክተር ታዛ አፈ ታሪክ ፥ ዶን ቶማሲኖ ግን ተጨባጭ እውነታ ነበሩ ።

በዚያ ጥንታዊ የአትክልት ስፍራ ሚካኤል የአ ባቱ ስረ መሰረት ምን እንደደረሰ ተማረ ። 'ማፊያ' የተባለው ቃል የቀድሞ ትርጉሙ 'የመሸሻ ስፍራ' ማለት እንደነበር ተነገረው ። ቀጥሎ ማፊያ የአንድ ጨቋኝ ገዢዎችን የሚዋጋ ድብቅ ድርጅት ስም ሆነ ። በታሪክ ውስጥ ሲሲሊ ከማንኛውም ሀገር ይበልጥ በጭካኔ የተደፈረች አገር ናት ። ባለእርስት ሹሞችና የሀይማኖት መሪዎች በአራሾች ላይ የፈላጭ ቆራጭ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስልጣን ነበራቸው ። ፖሊስ የነሱ መሳሪያ ሆኖ ከእነሱ ጋር ተደመረ ።

በዚህ ፍጹማዊ ሀይል ስር የማቀቁ ሰዎች እንዳይጨፈለቁ በመፍራት ቁጣቸውንና ጥላቻቸውን መደበቅ ተማሩ ። ህብረተሰቡ ጠላታችን ነው ብለው ገመቱ ። ስለዚህ በደል ሲፈጸምባቸው አቤት ለሚሉበት ለማፊያ ህገወጥ ድብቅ አለም አደሩ ። ማፊያ በ'አሜርታ' ሰምቶና አይቶ ዝም የማለት ህግ እራሱን አጠናከረ ። በገጠሪቱ ሲሲሊ አንድ መንገደኛ ወደሚቀጥለው ከተማ የሚወስደውን መንገድ አቅጣጫ ቢጠይቅ መልስ እን ኳን የሚሰጠው አይገኝም ። ለአንድ የማፊያ አባል የመ ጨረሻው ከፍተኛ ወንጀል የተኮሰበትን ወይም ጉዳት ያደረሰበትን ሰው ስም ለፖሊስ መንገር ነበር ። 'አሚ ርታ' የህዝቡ ሀይማኖት ሆነ ። ባሏ ወይም ልጅዋ የተገደ ለባት ሴት የደመኛዋን ስም ለፖሊስ አትነግርም ።

ፍትህ ከባለስልጣኖች ሰለአልተገኘች ሰዎች ወደ ድብቅ የሮቢን ሁድ አለም ፥ ወደማፊያ መሄድ አዘወ ተሩ ። እስከተወሰነ ድረስ ማፊያ አሁንም የፍትህ ሰጭ ነት ሚና ተጫወተ ። ሰዎች ለማናቸውም ከባድና ድንገተኛ ጉዳይ ወደ ማፊያ ሹም ነው የሚሄዱት ። የማፊያው ሹም የዳቦ ቅርጫቱንና ስራ አዘጋጅቶ የሚጠብቃቸው የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛና የአካባቢ ሹም ሆነ ።

ነገር ግን ዶክተር ታዛ ሳያወራለት ሚካኤል እራሱ በሚቀጥሉት ወራት የተገነዘበው ጉዳይ በሲሲሊ የሚገ ኘው ማፊያ የከበርቴዎች ህገወጥ ክንድ ፥ ሌላ ቀርቶ የሀጋዊና የፖለቲካ መዋቅርም ረዳት ሊሆን መብቃቱ ነበር ። ማፊያ ጸረ ኮሚኒስትና ጸረ ነጻነት አቋም የያዘ ፥ በግናቸውም ንግድ ላይ የራሱን ቀረጥ የሚጥል ፥ የዘቀጠ ካፒታሊስት መዋቅር ሊሆን በቃ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል አባቱና መሰሎቹ የሀጋዊው ህብረተሰብ አካል መሆን ትተው ሌባና ነፍሰ ገዳይ መሆንን ለምን እንደመረጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተረዳ ። ዝቅተኝነት የሚያስከትለውን ድህነትና የመዋረድ ፍርሀት አንድ ወጌ ያለው የሰው ልጅ ሊቀበለው የማይችለው ጉዳይ ናቸው ። ወደ አሜሪካ ፊልሰው የሄዱ ሲሲሊያውያንም በአገራቸው የገጠማቸውን አሰቃቂ ሁኔታ ከዚያም እንደ ሚያገኙት ገመቱ ።

ዶክተር ታዛ ሳምንታዊ የመዝናናት ገብኝቱን ለማድረግ ወደ ሴተኛ አዳሪ ቤት ሲሄድ ሚካኤልን አብሮት እንዲሄድ ጋብዞት ነበር ። ነገር ግን ማክለስኪ መንጋጭላው ላይ በመታው ጡጫ የተነሳ የመንጋጋው ስቃይ ይሰማዋል ። ሲሲሊ በመምጣቱ ምክንያት በወግ ያልተያያዘለት መንጋጋው የፊቱን ቅርጽ ስላቃወሰበት ዝቅተኝነት ተሰምቶታል ። በመልኩ ይኰራ ስለነበር ይህ መጣመም እጅግ አበሳጭቶታል ። ለስቃዩ ማደንዘዣ ዶክተር ታዛ የሚያዝለትን መድሀኒት ቢወስድም የማይረባ ሀኪም መሆኑን ስለተረዳ ፊቱን እንዲያክምለት ግን አልፈቀደም ። ዶክተር ታዛ አይገባኝም ብሎ ከሚናዘዘው የህክምና ጽሁፍ በስተቀር ሁሉንም ጽሁፍ ያነባል ። የህክምና ፈተናውን ያለፈው አንድ በሲሲሊ የሚኖር እውቅ የማፊያ ሹም ፓሌርሞ ድረስ ሄዶ ከፕሮፌሰሮቹ ጋር ስብሰባ እካሂዶ ምን ያህል ነጥብ እንደሚሰጡት ተነጋግሮ ከተመለሰ በኋላ ነበር ። የማፊያ ቡድን የማይጠልቅበት ቦታ ስለሌለ ምን ያህል የህብረተሰቡ ነቀርሳ እንደሆነ በዚህም ሁኔታ መረዳት ይቻላል ። የሙያ ብቃት ዋጋ የለውም ። ተሰጥዎም ዋጋ የለውም ። ስራም ዋጋ የለውም ። የማፊያ ጡት አባት ነው ስራህን እንደስጦታ እቃ የሚያበረክትልህ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል ብዙ ነገሮችን ለማሰብ በቂ ጊዜ ነበረው። ቀን ቀን በዶን ቶማሲኖ እርስት ላይ የሚሰሩ እረኞች አጅበውት ለሽርሽር ወደ ገጠር ይጓዛል ። የሲሲሊ ደሴት እረኞች ለማፊያ በነፍሰ ገዳይነት እየተቀጠሩ ገንዘብ ያገኛሉ ። የእነዚህን ሰዎች ሁኔታ አባቱ ካቋቋመው ድርጅት ተግባር ጋር አዛመዳቸው ። ያባቱ ድርጅት እየበሰ ጸገ ከሄደ በሲሲሊ የሆነው አስከፊ ሁኔታ መድረሱ አይቀርም ። ያኔም መላ አገራቱን ያጠፏታል ። በማፊያና በህጋዊው መንግስት መዋቅር ግጭት የተነሳ ሲሲሊ የጸአረሞት አገር ሆና ህዝቦቿም ጥለዋት ተበታትነ ዋል ። ሰርቶ ለመብላት ወይም ከነፍስ ግድያ ለማም ለጥ ሲሉ ሲሲሊያውያን ወደየሀገሩ ፈልሰዋል ። በእግር ሲንሸራሸር የአገራቱ ግርማ የተሞላበት ውበት አይኑን ይማርከዋል ። በብርቱካን እርሻ ውስጥ የብርቱካኑ ዛፍ ተግጣጥሞ የሰራው ዋሻ ጥላ ሆኖት ጥንታዊ የእባብ ምስል ሀውልቶች ካሉት ቧንቧ የሚፈሰውን ውሀ እየ ተመለከተ በውስጡ ተጓዘ ። እንደ ጥንታዊ የሮማውያን ቪላ መስለው ከተሰሩት ትላልቅ ቤቶች አልፎ አልፎ ፍራሽ ይታይባቸዋል ። ወይም የጠፉ በጎች ሰፍረውባ ቸዋል ። ወደ አድማስ አቅጣጫ ሲመለከትም ውብ ኮረ ብታዎች የሚያብረቀርቁ ከፍተኛ የአጥንት ክምሮች ይመስላሉ ። በረሀማውን ምድር እነዚያ ውብ አትክል ቶች ግርማ ሞገስ ሰጥተውታል ። ሚካኤል አንዳንዴ ጉዞ ውን በመቀጠል ብዛቱ አስራ ስምንት ሺህ የሆነው ህዝቧ በአቅራቢያው ካለው ተራራ ከተገኘ ጥቁር ድንጋይ በተሰራ ደሳሳ ቤቶች ውስጥ ተሸጉጦ ከሚኖርበት ከኮርሌዎኔ ከተማ ይደርሳል ። ባለፈው አመት ብቻ በኮርሌዎኔ ከተማ ስድሳ ግድያ ተፈጽሟል ። ከተ ማይቱ የሞት ጥላ የሚያንጎበጎብባት መስላለች ። ራቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ ሲመለከቱት የፊኩዛ ጫካ የእርሻ ሜዳው ትር ኢት አይን እንዳያሰለች ያግደዋል ።

ሚካኤል በግሩ ጉዞ ሲያደርግ አጃቢዎቹ ሁለት ሉፖራ የተባለ ጠመንጃ ይዘው ይከተሉታል ። ይህ ምቱ የማ ያዳግም የሲሲሊያውያን ጠመንጃ በማፊያ ወንበዴዎች እጅግ ተወዳጅ ነው ። በአንድ ወቅት ሙሶሊኒ ወደዚህች ግዛት የላከው ሹም የማፊያን ቡድን ማጥፋት እንዲቻል ወንበዴዎቹ መሽገው በሉፖራ ጠመንጃቸው ሰዎችን የሚጨርሱባቸው የድንጋይ ግንብ አጥሮች በሙሉ እንዲ ፈርሱና የሶስት ጫማ ከፍታ ብቻ እንዲኖራቸው ትእዛዝ አስተላለፈ ። ይህ ትእዛዝ ምንም ጠቃሚ ሆኖ አልተገ ኘም ። ስለዚህ የፖሊሱ ሚኒስትር ተጠርጣሪ ወንዶችን በማሰርና ወደ ቅጣት ቅኝ ግዛቶች በመላክ ችግሩን አቃለለው ።

በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት 'አክሲስ' በመ ባል የታወቁት ጀርመን ፣ ኢጣሊያና ጃፓን የሚገኙበት የጦር ሀብረት ''አላይድ ኔሽንስ'' የሚል መጠሪያ ከነበረ ው እንግሊዝና አሜሪካን ከሚሳተፉበት ሌላ የጦር ሀብረት ጋር በተለያዩ አገሮች ጦርነት ገጥሞ ነበር ። የአላይድ ኔሽንስ ጦር ድል ሲያደርግ ሲሲሊንም ነጻ አወጣት ። በዚያ ወቅት በሙሶሎኒ ዘመን መንግስት የነበሩ ሁሉ ፣ የፋሺስት ተቃዋሚ ከሆኑ ዲሞክራቶች ናቸው ፣ የሚል እምነት በአሜሪካን የጦር ባለስልጣኖች ላይ አድሮ ነበር ። ስለዚህ ብዙዎቹ የማፊያ አባላት ከእስራት ወጥተው የከተሞቹ ገዢዎች ለወታደራዊ መንግስት አስተርጓሚዎች ሆኑ ። ይህ አጋጣሚ ማፊያን እንደገና እንዲያንሰራራና ከመቸውም የበለጠ ጠንካራ እንዲሆን አደረገው ።

ረኾሙ ሽርሽር ሀይለኛ የወይን ጠጅ እና በርከት ያለ የፓስታ እና የስጋ እራት ሚካኤልን ለመተኛት

t.me/OLDBOOKSPDF

አስችሎታል ። በዶክተር ታዛ ቤተመጻህፍት ውስጥ በኢጣልያንኛ ቋንቋ የተጻፉ መጻህፍት ነበሩ ። ሚካኤል የአገርኛውን ኢጣልያንኛ መናገር ይችላል እንዲሁም በኮሌጅ ትምህርቱ ላይ የኢጣልያንኛ ኮርስ ወስዶ ነበር ቢሆንም ፥ እነዚህን የዶክተሩን መጻህፍት አንብቦ ለመረዳት ብዙ ድካምና ጊዜ ይወስድበታል ።

እንደባላገሩ ቢዘዋወር የአካባቢው ሰው አለመሆኑን ፥ ምናልባትም በስዊዘርላንድ ወይም በጀርመን ጠረፍ ላይ የሚኖር ኢጣሊያዊ ተደርጐ መገመቱ ባይቀርም ፥ ንግግሩ ግን ውጭ አገር ያደገ ተወላጅ አያስመስለውም ። የፊቱ ቅርጽ መናጋትም ይበልጥ ተወላጆቹን ያስመስለዋል ። ምክንያቱም በሲሲሊ በቂ የህክምና አገልግሎት ባለመኖሩ ይህን የመሰለ የቅርጽ መበላሸት የተለመደ ነው ። አነስተኛ ጉዳቶችም ቢሆኑ በገንዘብ ማጣት ሳይ ስተካከሉ ይቀራሉ ። ብዙ ሀጻናትና ብዙ አዋቂች በአሜሪካ ቢሆን በቀላሉ ሊስተካከል የሚችል የቅርጽ መበላሸት ይዘው ይኖራሉ ።

ሚካኤል ዘወትር ኪይን ያስባታል ። ፈገግታዋ ፥ ገላዋ ፥ ሳይሰናበታት ጨክኖ መሄዱ ሁሉ በቅሬታ ይታሰበዋል ። የሚገርመው ግን ሁለቱን ሰዎች በመግደሉ ተጸጽቶ አያውቅም ። ምክንያቱም ሶሎዞ በአባቱ ላይ የግድያ ሙከራ ፈጽሟል ። ሻምበል ማክለስኪም እድሜ ልኩን የፊቱ ቅርጽ እንዲበላሽ አድርጎታል ።

ሚካኤል በተለይ የፊቱ ህመም ስቃይ ሲበዛበት ማስታገሻ መድሀኒት እንዲሰጠው ዶክተር ታዛን በሚጠይቀው ጊዜ ለዚህ በአንድ በኩል ላበጠ ፊቱ ቀዶ ጥገና ቢደረግለት እንደሚሻል ይነግረዋል ። ማንም ሰው ከአይኑ በታች የሚገኘው ነርቩ ከብዙ ረቂቅ ነርቮች ጋር ግንኙነት እንዳለው ታዛ አስረድቶታል ። ማፊያም ችም ይህንኑ ነርቭ ለመፈለግ በጀቸው ላይ የሚወድቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ሰው ያሰቃዩታል ። ምናልባት የሚካኤል ፊት ላይ የምትገኘው ነርቭም በዚህ ሁኔታ ተጎድታ ልትሆን ትችላለች ። ፓሌርሞ ሆስፒታል ሄዶ ቀላል ቀዶ ጥገና ቢደረግለት ስቃዩ ለዘላለም ሊወገድ ይችላል ።

ሚካኤል ግን እምቢ አለ ። ዶክተሩ ለምን እምቢ እንዳለ ቢጠይቀው ሚካኤል ፈገግ በማለት ፡

"ይህ ከቤቴ ይዤው የመጣሁት ቅርስ ነው" ሲል መልሶለታል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ለስቃዩ ደንታ አልነበረውም ፡ ህመሙ ያን ያህልም አልነበረም ።

ሚካኤል በሲሲሊ ያደረገው ሰባት ወር የፈጀ እረፍት የተሞላበት ተራ ህይወቱ በመጨረሻው ሰለቸው ። በዚያ ወቅት ዶን ቶማሲኖ በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ እንደ ወትሮው መታየቱ ቀርቶ መራወጥ በዝቶበት ነበር ። ከቦርነቱ በኋላ በፓሌርሞ በሚካሄደው የግንባታ ስራ ጥቅ ማቸውን ለማግበስበስ የሚሯሯጡ አዳዲስ ማፊያዎች አስቸግረውታል ። 'የድሮ ማፊያዎች እብሪተኞችና ኋላቀር ናቸው' በማለት የሚጠሏቸው እነዚህ አዳዲስ ማፊያዎች በሚያግበሰብሱት ሀብት አማካይነት ይጋፏቸዋል ። ዶን ቶማሲኖም የራሱን ክልል ለማስከበር ሲል በውጥረት ላይ ነበር ። ስለዚህ ሚካኤል ከዶኑ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ባለመቻሉ ዶክተር ታዛን ከመስማት ሌላ አማራጭ አልነበረውም ። የዶክተሩ ታሪኮች ደግሞ መደጋገም እየጀመሩ ነበር ።

አንድ ቀን ጧት ግን ከኮርሌዎኔ ከተማ አልፎ ከበስተጀርባዋ ከሚገኘው ተራራ ድረስ ለመጓዝ ወሰነ ። እንደተለመደው ሁለቱ አጃቢዎቹ አይለዩትም ። እንደውነቱ ከሆነ የነዚህ ሁለት ሰዎች አጃቢነት ጠቀሜታው ሚካኤልን በኮርሌዎኔ ቤተሰብ አባልነቱ ከጠላቶቹ ለመጠበቅ ሳይሆን ለአንድ ባእድ ሰው ብቻውን በገጠር ውስጥ መሄድ አደገኛ በመሆኑ ነው ። አካባቢው በሽፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቶች ተሞልቶ ያገሬው የማፊያ ቡድን አባላትም አንዱ ከሌላው ጋር እለት በእለት ስለሚጋጭ በዚህ ሂደት ውስጥ ማንም ሰው አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል ። በሌላ በኩል የፓሊያዮ ሌባ ነው ተብሎ ሊጠረጠርም ይችላል።

ፓሊያዮ የሚባለው ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ የእጅ መሳሪያዎች የሚቀመጡበት እና ለወዛደሮች መጠለያ የሚያገለግል የሳር ጎጆ ነው ። በሲሲሊ ገበሬው በሚያርሰው እርሻ ላይ አይኖርም ። ምክንያቱም ለደህንነቱ አስጊ ስለሆነ እና መሬቱን በቤትና በጓሮ ላለማባከን ሲል ነው ። ስለዚህ በመንደር ይኖራል ። ጧት ጸሀይ ብቅ ስትል ወደርሻው ይጓዛል ። እርሻው ላይ ሲደርስ ፓሊያዮው ውስጥ ያስቀመጣቸው የእርሻ እቃዎቹ ከተሰረቁበት ከጉሮሮው ላይ ንጀራው የተነ ጠቀበት ሰው ነውና ጉዳቱ እጅግ ይሰማዋል ። በህግ በኩል ይህን የመሰለውን ሌብነት ለማስወገድ ባለመ ቻሉ ማፊያ ወደ ገበሬው ለመዝለቅ መንገድ አገኘ ። የፓሊያዮ ሌቦችን በሙሉ አሳዶ አረዳቸው ። በዚህ ወቅት አንዳንድ ንጹሀንም በስህተት ተገደሉ ።

ስለዚህ ሚካኤል ብቻውን ሲተላለፍ ቢገኝ በስህ ተት ሊገደል ይችላል ። ምናልባት ባንድ በተሰረቀ ፓሊ ያዩ አጠገብ ሲያልፍ ተገኝቶ ቢያዝ እማኝ ማቅረብ ካልቻለ በወንጀለኝነት መጠርጠሩ አይቀርም ።

ሚካኤል አንድ ብሩህ ቀን ጧት ሁለቱን ታማኝ ጠባቂዎቹን አስከትሎ እርሻውን እያቋረጠ ጉዞውን ጀመረ ። ከእነዚህ እረኞች አጃቢዎች አንዱ የቆዘመ ነሆለል ሲሆን ስሙም ካሎ ይባላል ። ሌላው ግን አለሁ አለሁ ባይ ፣ ልጅ እግር እና አለምንም ያያት ሰው ነው ። በኢጣሊያ ባህር ሀይል ውስጥ በባህረኝነት ሲያገለግል ሌሎች እንደሚያደርጉት እሱም በዚያው ሆዱ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚታይበትን የወሊድ ምልክት ለመሸፈን ሲል ፥ ደረቱ ላይ ተነቅሷል ። ኋላም የሚሰራበት መርከብ በእንግ ሊዞች ተማረከ ። በሲሲሊ ንቅሳት ያልተለመደ በመሆኑ ንቅሳቱ ባለበት መንደር ዝነኛ አድርጐታል ። የፋብሪዚዮ ንቅሳት አንድ ባል ጸጉራም ሆዱ ላይ ራቁታቸውን የተቃቀፉትን ሚስቱንና ውሽማዋን በጩቤ ሲወጋቸው የሚያሳይ በሲሲሊያውያን ዘንድ እንደብርቅ የሚቆጠር ንቅሳት ቢሆንም እሱ ግን እስከዚህም አይኮራበትም ። ፋብሪዚዮ ከሚካኤል ጋር ይቀልዳል ። ከአሜሪካ መምጣቱን መደበቅ ስለማይቻል ስለ አሜሪካ ይጠይቀዋል ። ይሁን እንጂ ሚካኤል ከአንድ ሁኔታ የተሰወረ መሆኑንና ስለሱም እንዳያወሩ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ከመረዳታቸው በስተቀር ማንነቱን አያውቁም ። ፋብሪዚዮ አንዳንዴ ትኩስ አይብ ለሚካኤል ያመጣለታል ።

ጉዟቸውን በአቢራማ የገጠር መንገድ ጋሪ ከሚጐትቱ አህዮች ጋር እየተጋፉ ፥ ጽጌረዳ መልክ አበቦች ፥ የብርቱካን እርሻ ፤ ወይራና ሌሎችም ዛፎች አብበው በሚታዩበት መስክ እያቋረጡ ቀጠሉ ። ሲሲሊያውያን መሬታቸው ጠፍ ስለሆነ ድሆች መሆናቸውን ነበር የሰማው ። ይህን ውበትና ልምላሜ የተሞላበት ምድር ሲያይ ግን እጅግ ተደነቀ ። ይህን የመሰለ ውበቷን ጥለው ህዝቦቿ መሰደድን መምረጣቸው አስገረመው ። እንዴት የኤደንን ገነት ጥለው ወደ ሌላ ምድር ይፈልሳሉ? ከባህሩ ጠረፍ ጋር ከተያያዘችው የማዛራ መንደር ድረስ ሄዶ በአውቶቡስ ቢመለስ እንደሚያደክመውና ማታ ደህና እንቅልፍ እንደሚወሰደው ስለገመተ ወደዚያው ለመዝለቅ አቅዶ ነበር ። ሁለቱ ጠባቂዎቹ ለእለቱ ጉዞ የሚበቃቸውን የዳቦና አይብ ስንቅ ይዘዋል ። ሉፓራ ጠመንጃዎቻቸውን ለአደን የወጡ ይመስል በግልጽ አንግበዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እጅግ ደስ የሚያሰኝ ጧት ነበር ። ሚካኤል ድሮ አንዱን የበጋ ቀን ኳስ ሊጫወት ሲወጣ ይሰማው የነበረው ስሜት ተሰምቶታል ። ያኔ እያንዳንዷ እለት የተለየ ውበት ነበራት ። ዛሬም ቢሆን እንዲያ ነው ። ሲሲሊን በተፈጥሯዊ የአበባ ምንጣፍ አስውቧታል ። የነዚህ አበቦችና ፍራፍሬዎች መአዛ አፍንጫውን የታመመውን ሚካኤልንም እንኳን አውደውታል ። በቡጢ የተመታው ግራ ጉንጩ ቢድንም አጥንቱ በወግ ተስተካክሎ አልተገጠመም ። ስለዚህ የግራ አጥንቱ ገፊት አይኑን ይጐዳዋል ፣ ከአፍንጫውም ሳያቋርጥ ፈሳሽ ይመነጫል ።

ድሮ በልጅነቱ ሽማግሌ ጣልያኖች 'መሀረብ የእንግሊዞች ሴታ ሴት ልማድ ነው?' እያሉ በየአስፋልቱ ፈሳሽ መተላለፊያ ላይ ሲናፈጡ ሲያይ ያስጠላው የነበረው ሁኔታ ዛሬ በሱ ደርሶበት ንፍጡ መሀረቡን ሲሞላው አገሬው እንደሚያደርገው በየሜዳው ላይ መናፈጥ ግድ ሆኖበታል ።

ይህን ሁኔታ በቀላሉ ለማስተካከል እንደሚቻልና የህክምናውም ሂደት ምን እንደሚመስል ዶክተር ታዛ ሊያስረዳው ቢሞክርም ሚካኤል በእምቢታው ጸንቷል ። ሚካኤልን ከስቃዩ እና ከንፍጡ መብዛት ይበልጥ ያበሸቀው ፊቱ ክብደት እንደጨመረ ሆኖ የሚሰማው ስሜት ነበር ።

እንዳለው የዚያን እለት ከባህሩ ዳርቻ መድረስ አልቻለም ። አስራ አምስት ማይል ያህል እንደተጓዙ ቀዝቀዝ ያለ ስፍራ መርጠው ከአንዱ የብርቱካን ዛፍ ስር ምሳ ሊበሉ እረፍት አደረጉ ። ፋብሪዚዮ አንድ ቀን አሜሪካ ለመሄድ ያለውን ምኞት አወራለት ። ከምግብና መጠጥ በኋላ ጥላው ስር ሲዝናኑ ፋብሪዚዮ ሸሚዙን ፈትቶ ንቅሳቱ እንዲታይለት ሆዱን አላወሰው ። ደረቱ ላይ የተሳሉት ሁለት እርቃናቸውን የማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታዩ ወንድና ሴት ሲታገሉ ጩቤው ሁለቱንም ዘልቆ የሚገባ ይመስላል ። ይህን ጊዜ ነበር ሚካኤልን ሲሲሊ ያውያን 'መብረቁ' ብለው የሚጠሩት ነገር የመታው ።

ከብርቱካኑ ዛፎች ባሻገር የአንድ ባለርስት እርሻ አረንጓዴ ለብሶ ተንጣሏል ። ከመንገዱ በታችም አንድ ከጥንቱ የሮማ ስልጣኔ ፍራሽ ተቆፍሮ የተገኘ የሚመስል ቤተመንግስት የመሰለ በእብነበረድ አምድ የተዋበ ቤት ይታያል ። ከአምዱ መሀከል ሁለት ወፍራም ሞግዚቶችን ከበው ውብ ልጃገረዶች ይመጣሉ ። እነዚህ ወጣቶች ባለርስቱ እርስቱን ለመጐብኘት ሲመጣ የሚያርፍበትን ቤት ካጸዱ በኋላ ቤቱን ማጌጫ ልዩ ልዩ ቀለማት ያሏቸውን አበቦች ለመልቀም ወደ ሜዳው መሄዳቸው ነበር ። ልጃገረዶቹ ሚካኤልና አጃቢዎቹን ሳያዩዋቸው እነሱ ወዳሉበት እየተጠጉ መጡ ።

ገላቸው ላይ ጥብቅ ያሉ በአነስተኛ ዋጋ የተገዙ ባለደማቅ ቀለማት ቀሚሶች ለብሰዋል ። እድሜአቸውገና በአስራዎቹ ውስጥ ይሁን እንጂ ደርሰዋል ። ሶስት አራቱ እንዲን ልጅ እያሯሯጡ ወደዛፉ ተጠጉ ። የምትሳደደው ወጣት አንድ ትልቅ ሀረግ ይዛ ከላዩ ላይ የበቀለውን የወይን ፍሬ እየሰቀመች ወደነሱ ትወረውራለች ። ጥቁር ወይን የመሰለውን ጸጉሯን ቀለበት የመሰለ ጉንጉን ተሰርታዋለች ። ገላዋም ቆዳዋን ጥሶ ሊፈነዳ ያለ ይመስላል ። ድንገት ባእድ የሆኑ ሰዎች በቅርቧ ስታይ ደነገጠች ። ልክ ልትሮጥ እንደምትነሳ ሚዳቋ በጣቷ ቆመች ። ለሰዎቹ በጣም ቅርብ ስለነበረች ውበቷን በዝርዝር ሊመለከቱት ይችላሉ ። መላ አፈጣጠርዋ ፣ አይኗ ፣ የፊቷ አጥንት ፣ የቅንድቧ ወጣ ገባ ሁሉ እንቁላል ቅርጽ አለው ። እጅግ ውብ የሆነው ብስል ቀይ ወዛም ገላዋ ጐላ ያለ አይንዋ ፣ ከዚያም በላይ ፊቷን ያስጌጠው ያይንዋ ሽፋሽፍት ፣ የወይን ጭማቂ ያቀላው

t.me/OLDBOOKSPDF

ልስልስ ከንፈርዋ ማራኪ ነው ። ከሚታመን በላይ ልብ የምትሰርቅ መሆንዋን ያየው ፋብሪዝዮ 'አምላኬ ፥ መሞቴ ነውና ነፍሴን ተቀበላት!' ሲል ቀለደ ። ይህን ሲል የሰማችው ይመስል ወጣትዋ በእግር ጣቷ እንደ ቆመች ወደነሱ መለስ ካለች በኋላ ፊቷን አዙራ ወደ ሚያሳድዷት ልጃገረዶች ሩጫዋን ቀጠለች ። ሩጫዋ በስሜት የተሞላ የእንስሳ ሩጫ ይመስላል ። ከጓደኞቿ ዘንድ ስትደርስም ዞር ብላ እጅዋን ዘርግታ ወደ ሰዎቹ አመለከተች ። ልጃገረዶቹ እየሳቁ ጥቁር የለበሱ ሞግዚቶቻቸውም እየገሰጿቸው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ሚካኤል ኮርሌዮኔ ግን የልቡ ትርታ ደረቱን እየሰነጠቀው ፥ እንደነሆለለ ተገትሮ ቀረ ። በገላው ውስጥ የሚዘዋወረው ደምም መላ ሰውነቱን ነዘረው ። መላውን የደሴቲቱን መልካም ሽታ ንፋስ እያንከለከለ ሲያመጣለት የብርቱካኑ ፥ የሎሚው ፥ የወይኑ እና የአበቦች ሽታ አወደው ። የራሱ ሰውነት ከአካሉ ላይ መጥቆ የወጣ መሰለው ። ሁለቱ እረኞችም ሲስቁ ሰማቸው ።

"መብረቁ መታህ አይደል?" አለው ፋብሪዚዮ ትከሻውን እየመታ ። ካሎ እንኳን የጓደኝነት እና የፍቅር ስሜት በማሳየት ክንዱን መታ መታ አድርጎት ፥

"ቀስ! ሰውዬ!" አለው ። ሚካኤል መኪና የገጨው ይመስል ሀሊናውን ሳተ ። ፋብሪዚዮ የወይን ጠጅ ጠርሙስ ሲያቀብለው ሚካኤል በረጅሙ ጐንጨት አደረገለት ። አእምሮውን ሲገዛም ፥

"እናንት የበግ ፍቅረኞች ፥ ምናባታችሁ ነው ምታወሩት?" አላቸው ።

ሁለቱም አሽቢዎቹ ሳቁ ። ካሎ ገራገር ፊቱ በቁም ነገር ተሞልቶ ፥

"መብረቁን መደበቅ አትችልም" አለው ። "ሲመታህ ሁሉም ሰው ያየዋል ። ያንተ ያለህ! ለምን ታፍራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለህ አንዳንድ ሰዎች መብረቁ ይምታኝ ብለው ይጸልያሉ ። አንተ እድለኛ ነህ''

ሚካኤል ስሜቱ እንዲህ በግልጽ ስለታወቀበት ደስ አላለውም ። ነገር ግን ይህን የመሰለ ሁኔታ በህይወቱ ሲገጥመው የመጀመሪያው ነበር ። ያሁኑ ሁኔታ እንደ አፍላ ፍቅርም አይደለ ። ለኬይ የነበረውን በለዛዋ፥ በብሩህ አእምሮዋ ላይ የተመሰረተ ፍቅር አይነትም አይደለ ። ያሁኑ 'የኔ ትሁን፥ የኔ ትሁን' የሚል ገደብ የለሽ ፍላጐት ነው ። ያሁኑ፥ ገጽታዋ ሊጠፋ የማይችል የፊቷ ተምሳሌት እትመት ነው ። የራሱ ካላደረጋት ትዝታውን እየወረረች እንደምትኖር ተገነዘበ ።

ሌላውን ነገር ሁሉ ዋጋ ቢስ አድርጐ፥ ሌሎች ጉዳዮችም ለአፍታ እንኳን ትዝ ሳይሉት፥ ህይወቱ ያልተወሳሰበና ቀጥተኛ ሆነበት ። በስደቱ ወቅት ሁሉ ኬይ ዘወትር ትዝ ትበለው እንጂ፥ ሚካኤል ምንም ቢሆን ወንድነቱን ያሳየ የማፊያ አባል መሆኑ ስለታወቀ ከእንግዲህ ፍቅር ወይም ወዳጅነት በመሀከላቸው ይኖራል ብሎ ተስፋ አያደርግም ነበር ። አሁን ግን ኬይ ከሀሊናው ፈጽሞ ተፋቀች ።

ፋብሪዚዮ ቀልጠፍ አለና፥ ''ወደ መንደሯ ሂጂ ማንነቷን አረጋግጣለሁ ። ማን ያውቃል፥ ከምንገምታት ውጭ በቀላሉ የምትገኝ ትሆናለች ። መቸም ለመብረቁ ምታት አንድ መፍትሄ ብቻ ነው የሚኖረው፥ አይደል ካሉ'' አለ ።

ካሎም በአምንታ እራሱን ነቀነቀ ። ሁለቱ ጠባቂዎች ልጃገረዶቹ ወዳመሩባት ወደ አቅራቢያዋ መንደር ጉዟቸውን ሲቀጥሉ ሚካኤል ምንም ሳይል ተከተላቸው ።

መንደሯ ከመሀከሏ ያለውን ፏፏቴ ያለበት አደባባይ በከበቡ ቤቶች ተመስርታለች ። ዋና መንገድ ላይ የተቆረቆረች በመሆኗ ሱቆች፥ የወይን ጠጅ መሸጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቤቶችና አንድ ሰገነት ያላት ቡና ቤት ይታዩባታል ። አረኞቹ እቡና ቤቷ ካሉት ሶስት ጠረጴዛዎች በአንዱ ላይ ሲቀመጡ ሚካኤልም አብሯቸው ተቀመጠ ። የልጃ ገረዶቹን በዚያ አካባቢ መኖር የሚገልጽ ምልክት እንኳ የለም ። ከጥቂት ልጆች እና ከአንዲት በቀዩው ከተሰማራች አህያ በስተቀር መንደሯ የተወረረች ትመ ስላለች ።

የቡና ቤቷ ባለቤት የሆነ አሜር ወፍራም ሰው በፈገግታ ሰላም እያለ ሊጋብዛቸው ወደነሱ ተጠጋና ጠረጴዛዋን ጨርቅ አልብሶ ሽምብራ ያለበት ሰሀን አስቀመጠላቸው ።

"ለዚህ አካባቢ እንግዶች ናችሁ መሰለኝ ። ስለዚህ የኔን የወይን ጠጅ ሞክሩት ። ወይኑ ከእርሻዬ ላይ የተለ ቀመ ፥ የጠመቁትም የራሴ ልጆች ናቸው ። ልጆቹ ሲጠ ምቁት ብርቱካንና ሎሚ ጨምረውበታል ። በኢጣሊያ ከፍተኛ ጥራት ያለው ወይን ጠጅ ነው" ሲል ባለቡና ቤቱ አግባባቸው ።

ወይን ጠጁን እንዲያመጣ አዘውት በመጥለቂያ ሲያ መጣላቸው ቀመሱት ። እንዲያውም ካለው የበለጠ ጥሩ ጣእም ያለውና እንደ ብራንዲ ሀይለኛ ሆኖ አገኙት ። ፋብሪዚዮ ባለቡና ቤቱን እንዲህ አለው ፥

"በዚህ አካባቢ ያሉትን ልጃገረዶች በሙሉ ታው ቃቸዋለህ ። ጥቂት ቆንጆዎች ወደዚህ ሲመጡ አይተ ናል ። በተለይም አንዷ ወንድማችንን በመብረቁ መትታ ዋለች" አለና ሚካኤልን አሳየው ።

ሰውየው ሚካኤልን በጥሞና ተመለከተው ። የተዛባ ፊቱ የተለመደ ስለሆነበት ካንዴ በላይ የሚመ ለከቱት ሰው አልመሰለውም ነበር ። በመብረቁ የተመታ ሰው ግን ሌላ ጉዳይ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለዛሬ ማታ ጥቂት ጠርሙስ የወይን ጠጅ ቤትህ ይዘህ መሄድ አለብህ ። እንቅልፍ እንዲወስድህ ይረዳሀል" አለው ።

ሚካኤልም ባለቡና ቤቱን ፥ "ያችን ዞማ ጸጉር ፥ ወዛም ቆዳ ፥ ጐላ ጐላ ያለ ውብ አይን ያላትን ቆንጆ ታውቃታለህ ? ይህን የምትመስል ልጅ በዚህ መንደር ትኖራለች ?" ሲል ጠየቀው ።

ባለቡና ቤቱ ቆጣ ብሎ ባጭሩ መለሰለት ።

"ፈጽሞ ! ይህን የምትመስል ልጃገረድ አላውቅም" ብሎት ሰገነቱን ጥሎ ወደ ቡና ቤቱ ሄደ ።

ሶስቱ ወይን ጠጆቸውን ቀስ እያሉ ጠጡና ሌላ አዘዙ ። ባለቤትየው ግን አልተመለሰም ። ፋብሪዚዮ ወደ ቡና ቤቷ ውስጥ ገባ ። ሲመለስ ፈገግ እያለ ፥

"ልክ እንደገመትኩት ያቺ ቆንጆ የሱ ልጅ ናት ። ሰውየው ደሙ ፈልቶ ሊተናኩለን እያሰበ ነው ። ስለ ዚህ ጉዟችንን ወደ ኮርሌዎኔ ብንቀጥል ይሻላል" አለው ሚካኤልን ።

ሚካኤል በደሴቲቱ ላይ ለበርካታ ወራት ቢቆይም ህብረተሰቡ ይህን የመሰለው ጉዳይ ሲነሳ አውሬ የሚ ሆንበትን ሊለምደው አልቻለም ። ጠባቂዎቹም ሊደርስ የሚችለውን በመገንዘብ እንዲነሳ ጠበቁት ።

"ያ ዲቃላ ሽማግሌ ሁለት ወጠምሻ ጐረምሶች ያሉት ስለሆነ እንዳይለቅብን እንሂድ" አለ ፋብሪዚዮ ።

ሚካኤል ቀዝ ቀዝ ብሎ ፋብሪዚዮን ተመለከ ተው ። እስካሁን ዝምተኛ ፥ ጨዋ ወጣትና አይነተኛ አሜሪካዊ ነበር ። በሲሲሊ ተደብቆ በመኖሩም የሆነ የወንድነት ጀብዱ ቢፈጽም መሆን አለበት ብለው ከመገመት በስተቀር ባህሪውን አያውቁትም ነበር ። ዛሬ ግን ሚካኤል ፊት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የኮር ሌዎኔዎቹን ፍጥጫ አዩበት ። ዶን ቶማሲኖ የሚካኤልን

t.me/OLDBOOKSPDF

ማንነትና የፈጸመውን ተግባር በውል ስለሚያውቅ በጥንቃቄ እንደ እኩያ ክቡር ሰው ይዞት ነበር ። እነ ዚህ የዋህ እረኞች ግን ሚካኤልን በቀላሉ ገምተ ውታል ። ቀዝቃዛ አመለካከቱ ፥ የማይበገረው ነጭ ፊቱ ፥ እንደ ቀዝቃዛ የበረዶ ጢስ ከላዩ ላይ የሚፈ ልቀው ቁጣ ሳቃቸውን ጨርሶ አጥፍቶት የወትሮውን ወዳጅነታቸውንም አከሰመው ።

ሚካኤል እነዚህ ሰዎች ለሱ የሚገባውን ትህትና የተሞላበት ጥንቃቄ ማሳየታቸውን ሲመለከት ፥

"ሂዱና ሰውየውን እኔ ዘንድ አምጡት!" በማ ለት አዘዛቸው ።

ምንም ሳያንገራግሩ ጠመንጃቸውን አንግበው ወደ ቡና ቤቷ ውስጥ ገቡ ። ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ሰውየውን ከመሀከላቸው አድርገው ተመለሱ ። ድፋ ጩው ባለቡና ቤት ምንም ፍርሀት ባያሳይም ቁጣው ግን ጥንቃቄ የተሞላበት ነበር ።

ሚካኤል መቀመጫው ላይ ተለጠጠና ሰውዬ ውን ለአፍታ ካጤነው በኋላ በጽሞና እንዲህ አለው ፥

"ስለ ሴት ልጅህ አንስቼብህ እንዳስቀየምኩህ ይሰማኛል ። ይቅርታ አድርግልኝ ። እኔ ለዚህ አገር እንግዳ ስለሆንኩ ባህሉን ጠንቅቄ አላውቅም ። እኔ የተናገርኩት ለአንተም ሆነ ለእሷ ተገቢውን ክብር ለመንፈግ ብዬ አይደለም"

እረኞቹ ባባባሉ ተመሰጡ ። ካሁን ቀደም የሚካ ኤልን አንደበት በዚህ ሁኔታ ሰምተውት አያውቁም። አነጋገሩ ይቅርታ የሚጠይቅ ቢሆንም የበላይነትና ሀይልን የሚገልጽ ነበር ። የቡና ቤቷ ባለቤት የሚያነ ጋግረው ሰው ተራ እረኛ አለመሆኑን በመገንዘብ ጥን ቃቄ በተመላበት ሁኔታ ትከሻውን ነቀነቀና ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ማነህ አንተ? ከልጄ ላይ ምን ትፈልጋለህ?" ሲል ጠየቀው ።

ሚካኤል ምንም ሳያንገራግር ፥ መለሰለት ፥

"እኔ ያገሬን ፖሊስ ሸሽቼ በሲሲሊ ተደብቄ የምኖር አሜሪካዊ ነኝ ። ስሜ ሚካኤል ይባላል ። ስሜን ለፖሊስ ነግረህ እድልህን መሞከር ትችላለህ ። ነገር ግን ይህን ብታደርግ ልጅህ አባቷን ታጣለች ። ያም ሆነ ይህ ፥ ልጅህን ፍቀድልኝና አንተ ፊት በስነ ስርአት እና ሙሉ ክብርህን ጠብቄ ላንጋግራት እፈልጋለሁ ። በበኩሌ ክብሬን የምጠብቅ ሰው በመሆኔ ልጅህንም የሚገባትን ክብር ላሳጣት አልፈልግም ። ተገናኝተን ላንጋግራት እፈልጋለሁ ። እና ሁለታችንም መብረቁ ከመታን አገባታለሁ ። ካልሆነ ግን ሁለተኛ አታየኝም ። ደስ ላልላት እችላለሁ ፥ እንዲያ ከሆነ ደግሞ ምንም ማድረግ አይቻልም ። ተገቢው ወቅት ሲደርስም ማናቸውም አማች ሊያውቀው የሚገባውን ያህል ማን ነቴን እገልጽልሀለሁ"

ሶስቱ ሰዎች ሚካኤልን በመገረም ተመለከቱት ። ፋብሪዝዮ በፍርሀት እንዲህ ሲል አንሾካሾከ ፥

"እውነተኛ መብረቅ ነው የመታው!"

የቡና ቤቷ ባለቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ መተማመን አቃተው ። ንቀቱም ጠፋ ፥ መናደዱንም እርግጠኛ መሆን አልቻለም ። ተራው ሲሲሊያዊ 'ማፊያ' የሚለውን ቃል አፍ አውጥቶ ስለማይጠራ ፥ የቡና ቤቷ ባለቤት የሚካኤልን ማፊያ አባልነት ለማወቅ ሲል በመጨረሻ መጠየቅ የቻለው ፥

"የወዳጅቼ ወዳጅ ነህ?" በማለት ብቻ ነበር ።

"አይደለሁም ። እኔ ለዚህ አገር እንግዳ ነኝ"

የቡና ቤቷ ባለቤት ሚካኤልን እንደገና ተመለከተው ። ግራ ፊቱ ተጣሟል ። አቋሙ ረኽቷል ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጥሎም ያላንዳች ፍራቻ ጠመንጃቸውን ያነገቡትን ሁለቱን እረኞች ተመለከተና አለቃቸው እንዲያነጋግረው እሱን ለማምጣት ወደ ቡና ቤቷ ሲገቡ የነበራቸውን ሁኔታ አስታወሰ ። ያኔ የቡና ቤቷ ባለቤት ሲጠሩት ፣ "ያን የውሻ ልጅ ከሰገነቷ አባርረዋለሁ!" ሲል ፎክሮ ነበር ። ነገር ግን ከእረኞቹ አንዱ ፣ "እመነኝ ፣ እራስህ ሄደህ ብታናግረው ይሻልሀል ፣" ስላለው ነበር ሳያውቀው ተከትሏቸው የመጣው ። አሁን ግን ይህን እንግዳ ጥቂት ትህትና ማሳየት እንደሚገባው ተገነዘበ ። በቁጭት አነጋገርም ፣

"እሁድ ከሰአት በኋላ እኔ ዘንድ ና ። ስሜ ቪቴሊ ይባላል ። ቤቴም ከመንደሯ በላይ ከዚያ ኮረብታ ላይ ነው ። በመጀመሪያ ወደዚህ ናና ይዤህ ወደዚያው እንሄዳለን" አለው ።

ፋብሪዚዮ ሊናገር ሲል የሚካኤል ግልምጫ ምላሱን አደነዘዘው ። ቪቴሊ ይህን አስተዋለ ። ስለዚህ ሚካኤል ተነስቶ እጁን ሊጨብጠው ሲዘረጋለት ፣ የቡና ቤቱ ባለቤት ጨበጠውና ፈገግ አለ ። የቀጠሮአቸው ቀን እስከሚደርስ ስለሚካኤል ማንነት ጠይቆ ይረዳል ። የማይስማማው ሆኖ ካገኘውም ሁለቱን ልጆቹን ጠመንጃቸውን አስይዞ በጸብ ይቀበለዋል ። የቡና ቤቷ ባለቤት ከማፊያ ቡድን ጋርም ግን ጭንት አያጣም ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ሲሲሊያውያን እንደሚያምኑት አንድ የመልካም እድል ምልክት መስሎ ታየው ። የልጁ ውበት የራሷንና የቤተሰቧን እድል የሚከፍትላት መሆኑን አንድ ነገር ነግሮታል ። አንዳንድ ወዲያ ወዲህ እያሉ የሚያነፈንፉትን ያካባቢውን ጐረምሶችም ይህ ወልጋዳ ፊት እንግዳ ድራሻቸውን ያጠፋለታል ። ቪቴሊ እንግዶቹን በማክበር በጣም ጥሩ የሆነ ቀዝቃዛ የወይን ጠጅ አስይዞ ላካቸው ። የመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠጡን ዋጋ የከፈለው ከእረኞቹ አንዱ መሆኑን ሲያይ ሚካኤል በእርግጥ የነዚህ ሰዎች የበላይ መሆኑን ተገነዘበ ።

ሚካኤል ሽርሽሩ አስጠላው ። ወደ ኮርሌዎኔ የሚ መልሰው መኪናና ሹፌር ተከራየ ። የሆነውን ነገር ሁሉ እረኞቹ ለዶክተር ታዛ ሳይነግሩት አልቀሩም ። የዚያን እለት ማታ በአትክልቱ ውስጥ ተቀምጠው ሳለ ፥ "ወዳ ጃችንን መብረቁ መትቶታል" ሲል ለዶን ቶማሲና አጫወተው ።

ዶን ቶማሲኖ አልተደነቀም ። ይልቁንም ፥ እየተነ ፈሰ ፥

"ምነው እነዚህን የፓሌርሞ ጐረምሶችም መብ ረቁ በመታልኝና ሰላም ባገኘሁ" አለ ። እነዚያ ጐረ ምሶች ብሎ የጠራቸው ብቅ ብቅ ያሉትንና እሱን መሰ ሎቹን የሚጋፈጡትን አዳዲስ ወጣት የማፊያ አለቆች ነበር ።

ሚካኤል ዶን ቶማሲናን እንዲህ አለው ፥

"እነዚያን የበግ እረኞች ንገራቸው ። እሁድ ብቻዬን ነው ወደዚያ የምሄደው ። የልጅቷ ቤተሰቦች ምሳ ጋብዘ ውኛል"

ዶን ቶማሲኖ እራሱን ነቀነቀና ፥ "እንደጠበቅህ ያባትህ አደራ ስላለብኝ ይህን ጥያቄ አትጠይቀኝ" አለው ። "ሌላው ጉዳይ ደግሞ ፥ ስለጋብቻም እውርተ ሀል ። አባትህ ዘንድ ልኬ መልስ እስከማገኝ ድረስ አልፈቅድልህም"

ሚካኤል ይህ ሰው የተከበረ በመሆኑ ጥንቃቄ በተመላበት አነጋገር ፥

"ዶን ቶማሲኖ ፥ አባቴን ታውቀዋለህ ። የሰውን እምቢታ የሚቀበል ሰው አይደለም ። ብዙ ጊዜ እምቢ ታዬን ሰምቷል ። ስለሁለቱ ጠባቂዎቼ ይገባኛል ። ችግር ውስጥ ልከትህ አልፈልግምና እሁድ እለት አብረውኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊመጡ ይችላሉ ። ነገር ግን አገባታለሁ ካልኩኝ አገባ ታለሁ ። አባቴን እንኳን በህይወቴ ጣልቃ እንዲገባ ሳልፈቅድለት ቆይቼ ዛሬ አንተን በህይወቴ ውስጥ ጣልቃ ግባ ብዬ ብፈቅድልህ በእርግጥ እንደሰደብኩት እቆጥረዋለሁ”

የማፊያው ሹም በረኸሙ ተነፈሰና ፥

“መልካም እንግዲያስ ፥ ውሳኔህ ጋብቻ ነው ማለት ነው” አለ ። “በፍቅር መብረቅ እንደተመታህ ገብቶ ኛል ። ልጅቷ ከጨዋ ቤተሰብ የተገኘች ቆንጆ ናት ። ከብርን ብትነሳት ከአባቷ ግድያ አታመልጥም ። ከዚያ በኋላም ደም መፋሰስ ይከተላል ። ነገር ግን እኔም ቤተ ሰቡን በቅርብ ስለማውቅ አልባሌ ተግባር እንድትፈጽም አልሻም”

“ ልጅቷ አይንህ ላፈር ትለኝ ይሆናል ። በጣም ወጣት ስለሆነች ስታየኝ ሽማግሌ ልመስላት እችላለሁ” ሲል ሁለቱ ሰዎች ፈገግ አሉ ። ሚካኤል ቀጥሎም ፥ “ለስ ጠታ መግጥ የሚሆን ጥቂት ገንዘብና የምጓጓዝበት መኪና ያስፈልገኛል” አለ ።

ዶን ቶማሲኖ እራሱን ነቀነቀና ፥ “ፋብሪዚዮ ሁሉንም ነገር ያዘጋጅልሀል ። ጐበዝ ልጅ ነው ። መርከብ ላይ ሲሰራ ጥገና አስተምረውታል ። ጨት ገንዘብ እሰጥሀለሁ ። ነገር ግን ሁኔታውን ለአባትህ መግለጽ ይሆናርብሀል”

ሚካኤል ወደ ዶክተር ታዛ ዞረና ፥ “ይህን ከአፍን ጫዬ የሚወጣ ምናምንቴ ፈሳሽ የማቆምበት መድሀኒት ይኖርሀል ? ያች ልጅ አስር ጊዜ ስናፈጥ እንድትመለከ ተኝ አልሻም” አለው ።

“እሷን ለማየት ከመሄድህ በፊት መድሀኒት አደር ግልሀለሁ ። ስሜትህ እንደመደንዘዝ ይላል ። ቢሆንም ሳጊዜው ስለማትስማት የሚያሰጋህ ነገር አይኖርም”

t.me/OLDBOOKSPDF

በግለት ዶክተር ታዛ ሲናገር ፥ ዶኑና እራሱ ዶክተሩ ፈገግ አሉ ።

ለእሁድ ጉዞው አንዲት አሮጌ አልፋ ሮሜዎ አው ቶሞቢል ተዘጋጀችለት ። ቀደም ሲል ሚካኤል ፓሌርሞ በአውቶብስ ሄዶ ለልጅቱና ለቤተሰብዋ የሚሆን ስጦታ ገዝቷል ። አፖሎኒያ ተብላ እንደምትጠራ ስለሰማ ስለሚማርክ ስሟና መልኳ ሲያሰላስል ሰነበተ ። እንቅልፍ እንዲወስደውም ካልጋው አጠገብ ብዙ የወይን ጠጅ እን ዲቀመጥ ለሰራተኞች መመሪያ ተሰጣቸው ። የተቀመ ጠለትን መጠጥ ማታውኑ ጨልጦት ያድራል ።

እሁድ እለት ማለዳ የበተስኪያን ደወል በመላ ሲሲሊ በሚያስተጋባበት ሰአት ሚካኤል አልፋ ሮሜውን እየነዳ ወደ መንደሯ ተጓዘ ። ከዚያም ሲደርስ መኪናውን ከቡና ቤቷ በራፍ ላይ አቆመ ። ከኋላው ጠመንጃቸውን ይዘው የተቀመጡትን ካሎንና ፋብሪዚዮን እዚያው እንዲቆዩ አዘዛቸው ። ቡና ቤቷ ተዘግታለች ። ነገር ግን ቪቴሊ ሞር ያለች መናፈሻው ላይ በክንዱ መከለያውን ተደግፎ ይጠብቃቸዋል ።

ሁለቱም ከተጨባበጡ በኋላ ሚካኤል ሶስቱን ስጦታ የያዙ ጥቅሎች ይዞ ቪቴሊን እየተከተለ ወደ ቤቱ በማ ቅናት ዳገቷን ማዝገም ጀመረ ። ቤቱ ከተለመደው የገጠር ጎጆ የላቀ ነበር ።

ወደ ቤቱ ሲዘልቁም በመስተዋት የተከበበ የማርያም ቅርጽ እና ሊያልቁ የደረሱ የጧፍ መብራቶች ይታያሉ ። ሁለቱ ጎረምሶች ለእሁድ ቀን የሚስማማ ምርጥ ጥቁር ልብስ ለብሰዋል ። እነዚህ ልጆች እድሜአቸው በሀያው አካባቢ ቢሆንም በእርሻው ላይ ሲማስኑ የሚውሉ በመ ሆናቸው በእድሜአቸው የገፉ ይመስላሉ ። እናታቸውም እንደ ባሏ ግዙፍ ናት ። ልጃገረዲቱ ግን በአካባቢው መኖሯን የሚገልጽ ምልክት አይታይም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከትውውቅ በኋላም በብዙ አይነት እቃዎች በተ
ሞላችው የእንግዳ ቤት ውስጥ ተቀመጡ ። ቤቱ በሲሲ
ሊያውያን ደረጃ ደህና ኑሮ ያለው ሰው የሚናርበት
ነው ።

ሚካኤል ለሚስተር ቪቴሊ ከወርቅ የተሰራ የሲ
ጋር መቁረጫ ፥ ለሚስዝ ቪቴሊ ደግሞ በፓሌርሞ ከሚገ
ኙት ጨርቆች ምርጥ የሆነ ብትን ጨርቅ አበረከተላ
ቸው። ለነሱ ከሰጠ በኋላ ለወጣቷ ያመጣው አንድ እሽግ
ስጦታ ቀርቷል። ስጦታውን በምጥን ምስጋና ተቀበሉት ።
ስጦታው ትንሽ ወቅቱን የጠበቀ አልነበረም ። ስጦታ
ግበርከት የሚገባው በሁለተኛው ጉብኝት ወቅት
መሆን ነበረበት ።

አባትየው ወንድ ለወንድ የሚጫወተውን ቁም
ነገር ለሚካኤል ገለጸለት ። "አንድ እንግዳ በቤታችን
ተቀብለን በማስተናገዳችን ከግምት ውስጥ የማንገባ
ሰዎች አድርገህ አትመልከተን ። ዶን ቶማሲኖ ጨዋ
ነትህን በማረጋገጥ ስላንተ ነግሮናል ። በአውራጃችን
ውስጥ የዚህን መልካም ሰው ቃል የሚጠራጠር ሰው
የለም ። ስለዚህ የሞቀ አቀባበል ያደረግንልህ ለዚህ
ነው ። ነገር ግን ስለልጇ በቁርጥ ቁምነገር ካሰብህ
ስላንተ ይበልጥ ማወቅ ይኖርብናል ። ስለራስህም ሆነ
ስለዘመዶችህ ጥቂት ግለጽልን ። ቤተሰቦችህ የዚህ
አገር ሰዎች ናቸውና ይህን ግለታችን አያስደንቅህም ።

ሚካኤል እራሱን ነቀነቀና በትህትና ፥ "ማወቅ
የምትፈልጉትን ነገር ሁሉ በፈለጋችሁበት ጊዜ እነ
ግራችኋለሁ" ሲል መለሰለት ።

ሚስተር ቪቴሊ እጁን አነሳና ፥ "እኔ ስለሰው
የግል ህይወት ለማወቅ የማንፈንፍ ሰው አይደለሁም ።
በቅድሚያ አስፈላጊ መሆኑን እንመልከት ። አሁን

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን የዶን ቶማሲኖ ዘመድ በመሆንህ በቤታችን ተስ
ተናገድ'' አለው ።

ሚካኤል የአፍንጫውን ፈሳሽ ለማቆም የተቀባ
ባው መድሀኒት አፍንጫውን ቢያደነዝዘውም የልጅቷ
ጠረን ሸተተው ። ዞር ብሎ ቢመለከት እውነትም ከጀ
ርባው ወደ ጓሮ ከሚወስደው መተላለፊያ በር ላይ
ቆማለች ። የአበቦችና የሎሚ መአዛ ክፍሉን አወ
ደው ። የሚያብረቀርቀው ጥቁር ጸጉር ላይ ምንም
ጌጥ የለበትም ። ለሷ ምርጥ የሆነው ቀሚሷ ከተራ
ጥቁር ጨርቅ የተሰፋ ነው ። ለቅጽበት እየት አድ
ርጋ ፈገግታ ካሳየችው በኋላ አፈር ብላ ከእናቷ ጐን
ሄዳ ተቀመጠች ።

ስግብግብነት የተሞላበት የስጋ ፈቃድ ሳይሆን
የበጐ ፍላጐት ግፊት ሰውነቱን ወሮት ትንፋሽ አጠ
ረው ። ያ ጥንታዊው የጣሊያኖች ቅናት ምን እንደሚ
መስል ተገነዘበ ። በዚያን ወቅት ይህችን ወጣት
በጁ የሚነካትን ወይም የኔ ነች ለማለት የሚሞክረ
ውን ፡ ወይም ሊነጥቀው የሚሻውን ከመግደል ወደ
ኋላ አይልም ። የዚህች ልጅ ባለቤት ከመሆንና የግሉ
አድርጐ እንዲቆልፍባት ከማድረግ የሚያግደው ምንም
ነገር አይኖርም ። ሌላ ሰው እንዲያያት አይሻም ። ዞር
ብላ ከአንዱ ወንድሟ ጋር ፈገግታ ስትለዋወጥ ተመ
ልክቷት ሳይታወቀው የነፍሰ ገዳይ ቁጣ አሳየው ።
የልጅቷ ወላጆችም ይህ ሁሉ ሁኔታ የተለመደው የመ
ብረቁ ምት መሆኑን በመረዳታቸው የሚካኤልን ቁር
ጠኛነት አረጋገጡ ። ይህ ሰው ከእንግዲህ ይህችን
ቆንጆ በእጁ እስከሚያገባት ድረስ በቁጥጥሯ ስር መሆኑ
ነው ። ካገባት በኋላ ሊቀየር ቢችልም ምንም አይደል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል የቪቴሊን ቤተሰብ ሊጐበኝ ሲመጣ የቀድሞ ተራ ልብሱን ጥሎ ሰሞኑን ከፓሌርሞ የገዛውን አዲስ ልብስ ለብሶ ሽክ ብሎ በመምጣቱ ፥ ይህ ሰው እንድ ዶን ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አሳደረባቸው ። በተፈጥሮ መልከ ቀና ስለነበር የተቃወሰው ፊቱ እሱ እንደሚያስበው አላስቀየመበትም ። በአካባቢው ከዚህ የባሰ ሁኔታም በብዛት ይታያል ።

ሚካኤል ቆንጆዋን ክብ ፊት ወጣት ተመለከተ ። ከንፈሯን የደም ግፊት እንዳጠቆረው አየ ። ስምዋን ለመጥራት ሳይደፍር ያናግራት ጀመር ።

"በቀደም እለት የብርቱካኑ እርሻ ውስጥ አየሁሽ ፥ ሸሽተው ሄድሽ ። እንዳላስደነግጥንሽ ተስፋ አደርጋለሁ" አላት ።

ለአፍታ አይኗን ቀና አድርጋ አይታው ራሷን ነቀነቀች ። ፍቅር አዘል አይኖቿን ደፍሮ መመልከት ስላልቻለ ወደ ሌላ አቅጣጫ አይኑን አቀና ።የወጣቷ እናትም ፍርጥም ብላ ፥

"አፖሎኒያ ፥ ይህን ምስኪን ወጣት አናግሪው እንጂ ። ከሩቅ የመጣው እንቺን ለማየት ነው እኮ" አለቻት ። ወጣቷ ግን አይኗን እንኳ ገለጥ አላደረገችም ። ሚካኤል ያመጣላትን በወርቅማ ወረቀት የተጠቀለለ ስጦታ አፖሎኒያ ተቀብላ ጭኗ ላይ አስቀመጠች ።

"እስቲ ክፈችው ፥ አንቺ ልጅ" አላት አባቷ ። ነገር ግን የህጻን የመሰለው ቡናማ ቀለም እጅዋ አል ተንቀሳቀሰም ። የእናቷ ትእግስት ስላለቀ የሚያምረው መጠቅለያ ወረቀት እንዳይቀደድ ተጠንቅቃ የተጠቀለለውን ስጦታ ከፈተችው ።

ቀይ ከፉይ ጨርቅ የለበሰውን የጌጣ ጌጥ ማስቀመጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳጥን ከዚህ ቀደም አይታ ስለማታውቅ መክፈት አልቻለችም ። ነገር ግን እንዲያው በግምት ነካ ስታደርገው ስለተከፈተላት ስጦታውን አወጣችው ። ስጦታው ትልቅ የወርቅ ሀብል መሆኑን ሲያዩ፥ በዋጋው ውድነት ብቻ ሳይሆን በባህላቸው መሰረት የወርቅ ስጦታ የሚካኤልን ለጋብቻ ቁርጠኝነት ስለሚያስገነዝባቸው ተደናገጡ ። ከዚህ በኋላ የዚህን ሰው ቁርጠኝነት ምንም አልተጠራጠሩም ። ሀብታም መሆኑንም በእርግጥ አወቁ ።

አፖሎኒያ ግን አሁንም ስጦታውን አልነካችውም ። እናቷ ስጦታውን ብድግ አድርጋ ስታሳያት ረዥሙን ሽፋሽፍቷን ለአፍታ ከፍታ በዚያ በእርግብ መሰል አይኗ ሚካኤልን ካየችው በኋላ "አመሰግናለሁ" አለችው ። ያኔ ነበር ሚካኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ድምጿን የሰማው ። አይነአፋርነት የወረረው የወጣትነት ረቂቅ ድምጿ በጆሮው አስተጋባ ። ሲያያት ቅጡ ስለ ሚጠፋው ከወላጆቿ ጋር ማውራት ጀመረ ።

ይሁን እንጂ በዚያ ተራ የሆነ ባህላዊ ልብሷ ውስጥ ገላዋ ስሜትን ብቻ እየረጨ እንደሚያንጸባርቅ ተገንዝቧል ። እሷም ብትሆን አይነአፋርነት በወረረው ሰውነቷ እና ወዝ በተሞላበት ገላዋ ስሜት የፈጠረው የደም ግፊት ተሰራጨባት ።

በመጨረሻ ሚካኤል ለመሄድ ሲነሳ ቤተሰቡም አብሮት ተነሳ ። የተለመደ የሰላምታ ልውውጥ ሲያደርጉም ወጣቷ ስትጨብጠው ሙቀት የተመላው ቆዳዋ ሲነዝረው ተሰማው ። ቪቴሊ የሚካኤል መኪና እስከ ቆመችበት ድረስ ሸኝቶት ለተከታዩ አሁድ እራት መጋበዙን ነገረው ። ሚካኤል በእሽታ ራሱን ቢነቀንቅም ይህችን ወጣት ሳያያት ሳምንት ሙሉ ሊቆይ እንደማ ይችል አውቆታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳለውም አልቆየም ። በተከታዩ ቀን አጃቢዎቹን ትቶ ብቻውን ወደ መንደሯ በመኪናው ተጉዞ ከልጅቷ አባት ጋር ቡና ቤቷ ውስጥ ማውራት ጀመረ ። አባት የውም ስላዘነለት ልጅቷን እና እናቷን ልኮ አስመጣ ቸው ። አፖሎኒያ እንደቀደም እለቱ አይነአፋርነት አላ ጠቃትም ። ከበቀደም እለቱ የተሻለም አወራችው ። የዚ ያን እለት ቀሚሷም ተራ ይሁን እንጂ ከፊተኛው ቀን ይበልጥ ተስማምቷታል ።

በተከታዩም ቀን ሁኔታው ተመሳሳይ ነበር ። ብቻ አፖሎኒያ ያመጣላትን የወርቅ ሀብል አጥልቃዋለች ። ይሀን ሲያይ የተቀባይነት ምልክት መሆኑን ስለተገነዘበ ደስ አለው ። እናቷ በቅርብ እየተከተለቻቸው ዳገቱን በእግራቸው ወጡ ። ነገር ግን ሰውነታቸውን ከመነካካት መከልከል አልተቻለም ። እንዲያውም አንድ ጊዜ አፖ ሎኒያ እደናቅፏት ላዩ ላይ ስትወድቅ ስለደገፋት ሀይ ወት የተሞላበት ገላዋ ተሰምቶት ጥልቅ የሙቀት ስሜት ነዝሮታል ። አፖሎኒያ ከሀጻንነት ጀምሮ በዚያ መንገድ ስትጓዝ አንድም ቀን ተደናቅፋ የማታውቅ የተራራ ፍየል መሆኗን እናቷ ስለምታውቅ የዚያን እለቱን መደና ቀፍ አውቃ እንዳደረገችው ተገንዝባ ፈገግ ስትል ወጣ ቶቹ ግን አልተመለከቷትም ። ይህ ወጣት የልጅዋን ገላ የሚነካው በዚህ መንገድ ብቻ መሆኑን በመረዳትዋም ዘዴያቸው አስቋታል ።

ይህ ሁኔታ ለሁለት ሳምንታት ቀጠለ ። በመጣ ቱጥር ስጦታ ያመጣላታል ። ወጣቷም አይነአፋርነቷ እየ ተወገደ ሄደ ። ነገር ግን ያለሞግዚት ብቻቸውን አንድም ቀን ተለቀው አያውቁም ። ወጣቷ ምንም ያህል ያልተ ማረች ፥ ስለአለምም ምንም እውቀት የሌላት ገጠሬ ብትሆንም ፥ ትኩስነትዋ ፥ ለህይወት ያላት ፍቅር ፥ ሌላ ቀርቶ የቋንቋ ገደቡም ሞምር የምትወደድ አድርጓታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም ነገር በሚካኤል ልመና ተፋጠነ ። ልጅቷም እሱን ከመውደዷም በላይ ሀብታምነቱን ስለተገነዘበች ሰርጉ ከሁለት ሳምንታት በኋላ እንዲሆን ሲጠይቅ እምቢ አልተባለም ።

በዚህን ጊዜ ዶን ቶማሲኖ በጉዳዩ እጁን ማስገባት ግዴታው ሆነ ። ከአሜሪካም በተላከለት መልእክት ፥ ሚካኤል ትእዛዝ የማይቀበል ሰው ስለሆነ መሰረታዊ ጥንቃቄዎች ብቻ እንዲደረጉለት ተነገረው ። ዶን ቶማሲኖ የራሱን ጠባቂዎች ለማሰማራት እንዲያመቸው እራሱ የሙሽራው የነገር አባት ሆነ ። ከኮርሌዎኔ ከተማ ካሎ፣ ፋብሪዚዮና ዶክተር ታዛ አጃቢዎች ሆኑ ። ሙሽሮቹ በዶክተር ታዛ ቪላ ውስጥ በትልቅ ግንብ አጥር ተከበው እንዲኖሩ ታቀደ ።

ደምበኛ የገበሬ ሰርግ ነበር ። የመንደሩ ሰዎች መንገድ ላይ ተኮልኩለው በመሀላቸው የሚያልፉት ሙሽሮች ላይ አበባ በተኑ ። የከተማው ሽማግሌችና እንግዶች ሙሽሮቹን አጅበው ከበተስኪያን እስከ ሙሽሪት ቤት በእግራቸው ተጓዙ ። የሰርጉ አጃቢዎች ጣፋጭና የሰርግ ከረሜላ ለሰፈርተኛው በተኑ ። የሙሽሮቹ አልጋም በጣፋጭ ትራፊ ተሞላ ። የሰርጉ ፈን ጠዝያ እስከ ሌሊት ቢቀጥልም ፥ ሙሽሮች በአልፋሮሚዮ መኪናቸው ቀደም ብለው ወጡ ። ያን ጊዜም በሙሽሪት ፍላጎት እናቷ ተከትላት መምጣቷን ሚካኤል ተገነዘበ ። አባትየው ግን ምክንያቱን አስረዳው ። ወጣቷ በእድሜዋ ገና ለጋ ድንግል እና ትንሽም ፍርሀት ያደረባት በመሆኗ ፥ የሚያጫውታት ሰው ያስፈልጋታል ። በጫጉላ ምሽት ምናልባት የሆነ ችግር ወይም ስህተት ቢፈጸም በነጋታው እናቲቱ ነገሮችን ታስተካክላለች ። ሚካኤል አፖሎኒያ በጥርጣሬ ስትመለከተው አያትና ፈገግ አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሙሽራት ጋር አማቱንም ጭምር በመኪናው ጭኖ ወደ ኮርሌዎኔ ከተማ ጉዞ ሆነ ። እዚያም ሲደርሱ አሮጊቷ ከዶክተር ታዛ አሽከሮች ጋር ተመካክረችና ፥ ልጅዋን ጭምቅ አድርጋ ከሳመች በኋላ ከአካባቢው ተሰ ወረች ። ሚካኤልና አፖሎኒያም ብቻቸውን ወደ ጫጉላ ቤታቸው አመሩ ።

አፖሎኒያ አሁንም በሙሽራ ልብሷ ላይ ካባ እንደ ደረበች ነች ። ልብስ የያዘ ሳጥኗና ሻንጣዋ ከመኪና ወደ መኝታ ቤት ተወስዶላታል ። መኝታ ቤቱ ውስጥ የሰ ርግ ኬክና ወይን ጠጅ በትንሽ ጠረጴዛ ላይ ተቀም ጧል ። በአልጋ ልብስ የተሸፈነ ሰፊ አልጋቸው ቅርባ ቸው ነው ። እዚያ ጫጉላ ቤት ከክፍሉ መሀል ላይ ያለ ችው ወጣት ሚካኤል የመጀመሪያውን እርምጃ እንዲ ወስድ ትጠብቃለች ።

እንግዲህ ብቻውን ስላገኛት ፥ አሁን በሀግ ባለቤቷ ስለሆነ ፥ አሁን በዚያ ለብዙ ጊዜ ሲመኘው በነበረው ውብ ገላና ቆንጆ ፊት ለመደሰት ምንም እንቅፋት ስለሌለበት ፥ ሊጠጋት አልተቻለውም ። ከላይ የደረበችውን የሙሽራ ልብሷን አውልቃ ወንበር ላይ ስታስቀምጥ ፥ የሙሽራ ቲያራዋንም አውልቃ ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ስታስቀምጥ ተመለከታት ። ጠረጴዛው እሱ ከፖሌርሞ ባስመጣላት ቅባትና ሽቶዎች ተሞልቷል ። ወጣቷ ለቅ ጽበት በአይኗ ቃኘቻቸው ።

ሚካኤል ወጣቷ ምናልባት ልብሷን ለማውለቅ ትፈራ እንደሆነ በማለት መብራቱን አጠፋላት ። ነገር ግን የሲሲሊ ጨረቃ እንደወርቅ እያበራች በክፍሉ መስኮት ዘልቃ በመግባትዋ መስኮቱን ጨርሶ ሊዘጋ ቢፈልግም ፤ የአየሩን ሙቀት እንዲያቀዘቅዝላት ገርበብ ግድረጉን መረጠ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣቷ አሁንም ጠረጴዛው አጠገብ ቆማለች ። ሚካኤል ክፍሉን ለቆ ወደ መታጠቢያ ቤቱ አመራ ። ከዶክተር ታዛ እና ከዶን ቶማሲኖ ጋር ወይን ጠጁን ሲጠጣ ሴቶቹ እራሳቸውን ለመኝታ ያዘጋጁ ነበር ። ሲመለስም አፓሎኒያ ልብሷን አውልቃ በፒጃማዋ ሆና አልጋው ውስጥ እንደምትጠብቀው ገምቷል ። ነገር ግን ይህን እንድታደርግ እናቷ ምንም አልረዳቻትም ።ምናልባትም አፓሎኒ እሱ ልብሷን እንዲያወልቅላት ፈልጋ ሊሆን ይችላል ። ግን በጣም አይነአፋርነት ስላጠቃት ግልጽ ለመሆን እንዳልቻለች ተገንዝቧል ።

ወደ መኝታው ሲመለስ መጋረጃው ጨርሶ ተዘግቶ ፍጹም ጭለማ ሆኖ አገኘው ። በጭለማው ውስጥ በዳበሳ እየተራመደ ከአልጋው ሲደርስ መኝታው ውስጥ የአፖሎኒያ ገላ እንዳለ ታወቀው ። ጀርባዋን ዞራ እጥፍ ብላ ተጋድማለች ። ልብሱን አውልቆ አንሶላው ውስጥ ገባ ። እጁን ሲዘረጋ ልስልስ ቆዳ ነካ ። እሷም እርቃኗን በመሆኗ ደስ አለው ። ቀስ ብሎ ፣ በጥንቃቄ አንድ እጁን ትከሻዋ ላይ አሳርፎ ወደሱ እንድትዞር ጫን አላት ።

እሷም ቀስ ብላ ዞር ስትል ፣ እጁ ልስልሱንና ሙሉውን ጡቷን ነካው ። ቶሎ ብላ እቅፉ ውስጥ ስትገባ አንድ የኤሌክትሪክ መስመር በሁለት አካሎች ላይ የተዘረጋ ይመስል ገላቸው ተዋሀደ ።በመጨረሻ እጁን በዙሪያዋ አድርጎ ትኩስ ከንፈርዋን ሳም ፣ ገላዋን እና ጡቷን ወደሱ አስጠግቶ ጭምቅ አደረገና በላይዋ ላይ ወጣ ።

በልስልሱ ገላዋ እና የሀር ጉንጉን በመሰለ ጸጉርዋ ፣ አሁን እስዋም በሙሉ ፈቃድ ተሞልታ በድንግላዊ የፈቃደ ስጋ ሞገድ ግፊት ወረረችው ። ከገላዋ ሲቀላቀልም ለቅጽበት የጭንቀት ትንፋሽ አሰምታው ባላት ሙሉ ሀይል ጭኑን በጭንዋ ቆለፈችው ። የፍቅር ልው

t.me/OLDBOOKSPDF

ውጡ እንዳበቃም በሲቃ እንደተሞሉ መለያየት የሞት ያህል ሆኖባቸው እርስ በርሳቸው ተሳሰሩ ።

ሚካኤል በዚያም ምሽት ሆነ በተከታዮቹ ሳምንታት ወግ አጥባቂዎች ለድንግላዊነት ከፍተኛ ግምት ለምን እንደሚሰጡት መገንዘብ ቻለ ። ያ ወቅት ለሚካኤል ካሁን ቀደም ያልተለመደ የተባእት ሀያልነት የተቆላቀለበት ስሜታዊነት ወቅት ነበር ። አፖሎኒያ በነዚያ ቀናት ፍጹም ተገዢው ሆነች ። ተገቢው ግፊት ቢያረግባት እና ፍቅር ቢከፈላት ፣ ከድንግላዊነት ወደ ፈቃደ ስጋ ስሜት የዳበረች ደመ ሙሉ ቆንጆ ወጣት በወቅቱ የደረሰ ጣፋጭ ፍሬ ማለት ነች ።

እሷም በበኩሏ በወንዶች ብቻ ተሞልቶ የነበረውን ሞጋጋም ቤት አንጸባረቀችበት ። ከጫጉላ ምሽት በኋላ እናቷን ወደ ቤቷ ሸኝታ በወጣት ልጃገረድነት ግርማዋ ለመልሱ ብቅ አለች ። ሰሞኑን ዶን ቶማሲኖም አብሯቸው እራት ይበላ ነበር ። ወይን ጠጃቸውን ይዘው በአትክልቱ ስፍራ ሲዝናኑም ዶክተር ታዛያን የጥንት ታሪኩን በየምሽቱ እያወራላቸው ፣ ሲመሽ ሙሽራውና ሙሽሪት ሊጠግቡት ያልቻሉትን ፍቅር እየተለዋወጡ የደስታ ወቅት አሳለፉ ። ሚካኤል በቅርርጿ ፣ በአቋሟ ፣ በቆዳዋ ፣ ሰአሊ የቀረጸውን የኢጣሊያን ማርያም በመሰለ ፊቷ ፣ በአጠቃላይ በመላ አፈጣጠሯ አድናቆት እያደረበት አንዳንዴ እንቅልፍ ሲወስዳት እርቃኗን ይመለከታታል ።

የመጀመሪያውን ሳምንት በመኪናቸው እየተንሸራሸሩ አሳለፉት ። ነገር ግን ያባቱ ጠላቶች እጅ አካባቢውን ስለሚዳስስ ለደህንነቱ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ዶን ቶማሲኖ ለሚካኤል አስረዳው ። የግቢው ዙሪያ በታጠቁ ዘበኞች ይጠበቃል ። ካሎና ፋብሪዝዮም በአጥሩ ግንብ ስር ቋሚ ሆነው ሲጠብቁ ፣ ሚካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኤልና አፖሎኒያም ከግቢያቸው አይወጡም ። ሚካኤል አፖሎኒያን እንግሊዝኛ ማንበብና መጻፍ እንዲሁም በግቢው ውስጥ መኪና መንዳት እያስተማራት ጊዜውን አሳለፈ ። ዶን ቶማሲኖ በአካባቢው ብቅ ብቅ ካሉት አዳዲስ ማፊያዎች ጋር ችግር ስለገጠመው በዚያ ተወጥሯል ።

አንድ ቀን ምሽት በዶን ቶማሲኖ ቤት ሰራተኛ የሆነች ገጠሬ አሮጊት ፍራፍሬ አቅርባላቸው ሳለ ሚካኤልን እንዲህ ስትል ጠየቀችው ፡

"ሰው ሁሉ አንተን የኒውዮርኩ የጡት አባት ፡ የዶን ኮርሌዎኔ ልጅ ነህ እያለ የሚያወራው እውነት ነው ?"

ሚካኤል የዚህ ሚስጥር በግልጽ መታወቅ ዶን ቶማሲኖን እንዳናደደው ተመለከተ ። ነገር ግን አሮጊቷ በጉጉት ትመለከተው ስለነበር እራሱን በአዎንታ ነቀ ነቀና ፡

"አባቴን ታውቂዋለሽ ?" ሲል ጠየቃት ።

ፊቷ የተጨራመተው አሮጊት ሚካኤል ካወቃት ጀምሮ ያሳየውን ፈገግታ ለመጀመሪያ ጊዜ አሳየችው ።

"የጡት አባት ነው በአንድ ወቅት ህይወቴን ያተረፈው ፡ አንጐሌን ከመፍረስ ያዳነው" አለች በእጅዋ አናትዋን እያመለከተች ።

ንግግሯን ለመቀጠል መፈለጓን ሲመለከት ሚካኤል በምልክት አበረታታት ። እሷም በፍርሀት ፡ "ለመሆኑ የሉካ ብራሲ መሞት እውነት ነው ?" ብላ ጠየቀችው ። ሚካኤል የሉካን መሞት በአዎንታ ሲያረጋግጥላት ከስቃይ የመገላገል ስሜት እያሳየች ፡

"ጌታ ይቅር ይበለኝና ፡ ነፍሱ በገሀነም ለዘላለም ትጠበስ" አለች ።

ሚካኤል ስለ ሉካ ለማወቅ የነበረው ጉጉት ትዝ አለው ። ሄገንና ሶኒ ስለሉካ የደበቁትን ታሪክ ይህች

t.me/OLDBOOKSPDF

አሮጊት እንደምታውቅ ተሰማው ። ወይን ጠጅ ቀድዱ ላት እንድትቀመጥ ካደረጋት በኋላ ፥

"ስለ አባቴና ስለሉካ ብራሲ ንገሪኝ ። ጥቂቱን አውቃለሁ ። ነገር ግን እንዴት ወዳጅ ሊሆኑ እንደቻሉና ብራሲም ለአባቴ ታማኝ ሊሆን የበቃበትን ምክንያት ግለጪልኝ ። አትፍሪ ፥ በይ ንገሪኝ" አላት ሚካኤል ።

አሮጊቷ ዶን ቶማሲኖን ቀና ብላ ስታየው እንድትናገር መፍቀዱን በምልክት አሳያት ። ከዚያ በኋላ ምሽቱን ስታወራላቸው አመሸች ።

ከሰላሳ አመት በፊት ፊሎሜና በኒውዮርክ ከተማ ለሚኖሩ ጣልያኖች በአዋላጅነት ታገለግል ነበር ። ብዙዎቹ ስለሚወልዱ ፊሎሜናም ያዋላጅነት ክፍያዋን እየተቀበለች ከበረች ። ሌላ ቀርቶ አሰቸጋሪ ምጥ ሲያጋጥማቸው ሀኪሞችን ታማክር ነበር ።

ወደመጨረሻ እድሜው ሀብቱን በቁማርና በዝሙት ጨርሶት የሞተው ባሏ ነፍሱን ይማረውና ፥ ያኔ በአሜሪካ የምግብ ሽቀጥ መደብር የነበረው ከበርቴ ነበር ። እንድ መጥፎ ምሽት ውድቅት ላይ የቤቷ በር ተንኳኳ ። እንደ ተለመደው ለአዋላጅነት ሊጠሯት መስሏት በሯን ስትከፍት በአስፈሪነት የታወቀው ሉካ ብራሲ መሆኑን ስትመለከት በባሏ ላይ ጉዳት ለማድረስ የመጣ መሰላት ። ነገር ግን ሉካ የመጣው እንዲት የምትወልድ ሴት ስላለች እንድታዋልድ ሊወስዳት ነበር ። ፊሎሜና የዚህን ሰው ፊት በጥርጣሬ ከተመለከተች በኋላ የምታዋልዳቸው ሴቶች ያለፈ ታሪካቸውን የተከታተለቻቸውን ብቻ መሆኑን በመግለጽ እምቢ ለማለት ምከረች ። ብራሲ በእጁ ሙሉ ብር አፍሶ ከሰጣት በኋላ እንድትከተለው በቁጣ ሲያዛት እምቢ ለማለት አልደፈረችም ።

ብራሲና ፊሎሜና ከሰላሳ ደቂቃ ያህል የመኪና ጉዞ በኋላ ነፍሰጡርዋ ካለችበት ቤት ደረሱ ። ወደ መኝታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከፍል ሲገቡም አንዲት ውብ ወጣት ሆዲ አብጠ አል ጋው ላይ ተጋድማ አገኘች ። ወጣቷ ብራሲን ስታይ በፍርሀት ፊቷን አዞረች ። በብራሲ ላይ የነበራት ቁጣ ታይቶም አይታወቅ ። ብራሲ ከፍሉን ለቆ ሲወጣላት ሰዎች እየረዷት አገላገለቻት ። ፊሎሜና ብራሲን ጠርታ በጨርቅ የተጠቀለለውን ህጻን ስትሰጠው ፡

"አባት ከሆንክ ውሰዳት ። እንግዲህ የኔ ስራ አብ ቅቷል" አለችው ።

ብራሲ በቁጣ አውሬ ሆነ ።

"አምን ፡ እኔ ነኝ አባቷ ። ነገር ግን የዚህ ዘር ፍሬ በህይወት እንዲኖር አልፈቅድም ። ታች ምድር ቤት ውሰጂና እሳት ውስጥ ጣያት" አላት ። ይህ ሰው የተናገረው ለጊዜው ሊገባት አልቻለም ። ዘር ሲል ምን ማለቱ ነው ? የህጻንዋ እናት ኢጣሊያዊት ባለ መሆኗ ይሆን ? ዝቅተኛ ደረጃ ያላት ፡ ዝሙት አደር በመሆኗ ነው ? ወይስ ከሱ አብራክ የተገኘ ሁሉ በህ ይወት እንዲቆይ አለመፈለጉ ይሆን ?

ይህ ሰው ደስ የማይል ቀልድ እየቀለደ እንደሆነ ገመተች ።

"እንግዲህ ያንተ ልጅ ናትና የምትፈልገውን ማድረግ ትችላለህ" ብላ የተጠቀለለችውን ህጻን ልትሰ ጠው ሞከረች ።

ይህን ጊዜ የደከመችው ወላድ ወደነሱ ዞር ብላ ስትመለከት ብራሲ ህጻንዋን ወደ ፊሎሚና ሲገፋት ተመለከተች ። በደከመ ድምጽ ፡

"ሉክ ፡ ሉክ ፡ ይቅርታ አድርግልኝ" ብላ ተማጠ ነችው ። ብራሲ ወደሷ ዞሮ ተመለከተ ። ይህን ጊዜ ማየቱ የሚያስጠላ የአበደ አውሬ ሆነ ። ሉካ ወደ ፊሎ ሜና ዞሮ ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

"የምልሽን ፈጽሚ ፥ ሀብታም አደርግሻለሁ" አላት ።

ፊሎሚና ከፍርሀትዋ የተነሳ መናገር አልቻለችም ፥ እራሷን ብቻ በእምቢታ ነቀነቀች ። ቀጥላም ቀስ ባለ ድምጽ ፥

"አንተ አድርገው ፥ አንተ ነህ አባቷ ። የምትፈልገውን ማድረግ ትችላለህ" አለች ። ብራሲ መልስ አልሰጣትም ። ከሸሚዙ ውስጥ ጩቤ መዘዘና "ጉሮሮሽን እንዳልበጥሰው!" ሲል አስፈራራት ።

ከዚያ በኋላ በድንጋጤ ያደረገችውን አላወቀችውም ። ሄዳ ከምድር ቤቱ የሚገኝ እሳት የሚንቀለቀልበት ፊት ለፊት ድምጽ የማታሰማውን ሀጻን እንዳቀፈች መቆሟ ትዝ ይላታል ። "ምናልባት ሀጻኗ ብትጮህ ኖሮ ወይም ፊሎሚና ጮሌ ሆና እንድትጮህ ብትቆነጥጣት ኖሮ ጮህ ያ አውሬ ይቅርታ ያደርግላት ነበር ፥" በማለት ፊሎሚና በቁጭት ተናገረች ። ከጓደኞቹ አንዱ እሳት የሚንቀለቀልበትን ምድጃ ከፈተው ። ብቻቸውን ሲቀሩ ብራሲ ጩቤውን አወጣ ። ሀጻኗን እሳት ውስጥ አልወረውርም ብትል እንደሚገድላት አወቀች ። ብራሲ ወደ እሳቱ ገሩ አደረጋት ። ይህን ጊዜ ፊሎሚና ታሪኳን ማውራት አቆመች ።

ሚካኤል በጽሞና ፥

"ታዲያ አደረግሺው?" ሲል ጠየቃት ። ፊሎሚና በአምንታ እራሷን ነቀነቀች ። አሮጊቷ ከዚያ በኋላ ታሪኳን መቀጠል የቻለችው ሌላ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ከጠጣችና ካማተበች በኋላ ነበር ። ለፊሎሚና ረብጣ ገንዘብ ሰጥታት ወደ ቤቷ አደረሳት ። ስለተፈጸመው ሁኔታ አንድ ነገር ብታወራ እንደምትሞት አወቀች ። ከሁለት ቀናት በኋላ ብራሲ ያቺን ወጣት ገድሏት ታሰረ ። ፊሎሚና ሁኔታው ስላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስፈራት የጡት አባት ኮርሌዎኔ ዘንድ ሄዳ ታሪኩን አወራችለት ። ዶን ኮርሌዎኔም ለማንም ምንም እን ዳታወራ አስጠንቅቋት እሷንም እንደሚጠብቃት አረ ጋገጠላት ።

ዶኑ ሁኔታዎችን ከማመቻቸቱ በፊት ሉካ እስር ቤት እያለ በጠርሙስ ስዓሪ እራሱን ለመግደል ሙከራ አደረገ ። ሲድን ዶኑ ሁሉን ነገር አመቻቸ ለት ። ፖሊስም መረጃ ማቅረብ ስላልቻለ ብራሲ ተለቀቀ ።

ፊሎሜና ምንም እንደማይደርስባት ከዶን ኮርሌ ዎኔ ማረጋገጫ ብታገኝም ሰላም አጣች ። በሙያዋ ለመስራትም ስላልቻለች ባሏን አግባብታ አሜሪካን ለቀው ወደ ኢጣሊያ መጡ ። በብዙ ድካም ያፈሩትን ገንዘብ ባሏ አባክኖት ሲሞት እሷም ለግርድና በቃች። የፊሎሜናም ታሪክ እዚህ ላይ አበቃ ። አንድ ተጨ ማሪ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ከጠጣች በኋላ ፡

"ያባትህን ሰም አመርቃለሁ ። ገንዘብ ስጠይ ቀው ይልክልኛል ። ህይወቴንም ከብራሲ አድኗታል። ቀንና ሌሊት ስለምጸልይለት ሞትን እንዳይፈራ ንገረ ረው" አለችው ።

አሮጊቷ ጥላቸው ከሄደች በኋላ ሚካኤል ዶን ቶማሲኖን ፡

"ያወራችው ታሪክ እውነት ነው ?" ሲል ጠየ ቀው ። የማፊያው ሹም በአምንታ እራሱን ነቀነቀ ። ለካስ ማንም ሰው የሉካን ሙሉ ታሪክ ሊነግረው አለ መፈለጉ የሚያስገርም አልነበረም። አይ ሉካ! አዬ ታሪክ!

በተከታዩ ቀን ጧት ሚካኤል ከዶን ቶማሲኖ ጋር ለማውራት ቢፈልግ ፡ ሰውየው መልእክተኛ ተልኮበት ባስቸኳይ ወደ ፓርሌሞ መሄዱ ተነገረው ። ዶን ቶማሲኖ ሲመለስም ሚካኤልን ከሰው ለይቶ ከወሰደው በኋላ የሳንቲኖ ኮርሌዎኔን መገደል አረዳው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ሀያ አራት

በዚያ ቪላ ውስጥ የመጨረሻ ቆይታቸው በሆነ በት ጧት ክፍሉን ብርቱካንማ ጸሀይ ሞልቶት ሚካ ኤል የሚስቱን ገላ እያያነቀ ፍቅር ተለዋወጡ ።

ዶን ቶማሲኖ በደቡብ ሲሲሊ ባህር ዳርቻ ከምትገኝ ሌላ ከተማ እንዲኖሩ አስፈላጊውን ሁሉ አዘጋጅቶላቸዋል ። አፖሎኒያም በመጀመሪያ ወር እርግዝናዋ ወደ አዲሱ መደበቂያ ቤታቸው ሄዳ ከባ ልዋ ጋር ከመቀላቀሏ በፊት ጥቂት ሳምንታት ከዘመ ዶቿ ጋር ማሳለፍ ፈልጋለች ።

በቀደም ምሽት አፖሎኒያ ከተኛች በኋላ ዶን ቶማሲኖ የሚካኤል ደህንነት በስጋት ላይ ያለ መሆ ኑን አስረዳው ።

"ጋብቻህ አደባባይ አውጥቶሀል ። አባትህ ሌላ ቦታ ሳያዘጋጅልህ እስካሁን መቅረቱ አስገርሞኛል ። ያም ሆነ ይህ ፡ ከነዚያ ወጣት የማፊያ ተቀናቃኞቼ ጋር አንዳንድ ድርድር አደርጌአለሁ ። ነገር ግን እነሱ ሁሉንም ይፈልጋሉ ። ፍላጐታቸውን መረዳት አልቻ ልኩም ። ትንሽ ተንኰል ቢሞክሩም ሊገድሉኝ አልቻ ሉም ። መቸም ወጣቶች ምንም ብልህ ቢሆኑ በቂ ምክ ንያት አይሹም ። በጉድጓዱ ውስጥ ያለውን ውሀ ሁሉ ለብቻቸው ሊጨልጡ ይሻሉ" አለው ። ቀጥሎም ካሎና ቱብሪዚዮ አብረውት በመኪናው እንደሚሄዱና ጥበቃ ውም እንደሚቀጥል ነገረው ። ዶን ቶማሲኖ በተከታዩ ቀን ማልዶ ወደ ሌላ ስፍራ ለስራ የሚሄድ በመሆኑ በዚያኑ ምሽት ተሰናበተው ። ዶክተር ታዛ አፉ ስለማይቋጥር ለሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳያወራ በመፍራት ሚካኤል ስለጉዞው እንዳይነግረው ዶኑ ቶማሲኖ አስጠነቀቀው ።

ዶን ቶማሲኖ በችግር ላይ እንዳለ ሚካኤል ተገነዘበ ። የታጠቁ ዘበኞች የግንብ አጥሩን እየተዘዋወሩ እንዲጠብቁ ተደርጓል ። ታማኝ ጠባቂዎችም ጠመንጃቸውን ይዘው ቤቱን ይጠብቃሉ ። ዶን ቶማሲኖ እራሱ በሚገባ ታጥቋል ። የግል ጋሻ ጃግሬም ያጅበዋል ። ሚካኤል የስራ ልብስ እና ሲሲሊያውያን የሚያደርጉትን ሹል ቆብ አድርጐ በባዶ እግሩ በመስኩቱ ተመላለከተ ። ፋብሪዝዮ በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ መሳሪያውን በግድ የለሽነት ጠረጴዛ ላይ አኑሮ ካንድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ጸጉሩን ያበጥራል ። ሚካኤል ሲያፏጭለት ፋብሪዝዮ ወደ መስኩቱ ተመለከተ ።

"መኪናዋን አምጣት ፣ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ እነሳለሁ ። የታለ ካሎ?" ፋብሪዚዮ ተነሳ ። ሸሚዙ ክፍት ሆኖ ንቅሳቱ ይታያል ። "ካሎ ወጥ ቤት ውስጥ ቡና እየጠጣ ነው ። ባለቤትህ ካንተ ጋር ትሄዳለች?" ሚካኤል ግንባሩን ቋጥሮ ተመለከተው ።

ፋብሪዝዮ ካለፉት ጥቂት ሳምንታት ጀምሮ አፖሎኒያን በአይኑ እንደሚከተላት ሚካኤል ተገንዝቧል ።

የሚካኤል ጥርጣሬ ፋብሪዝዮ የዶኑን ዘመድ ሚስት ይደፍራል ብሎ አይደለም ። በሲሲሊ ይህን ከመሰለ ጥፋት ይበልጥ ወደ ሞት የሚወስድ እርግጠኛ መንገድ የለም ። ሚካኤል ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር ፣

"የለም ። መጀመሪያ ወደ ዘመዶቿ ትሄዳለች ። ከዚያ በኋላ ከኛ ጋር ትቀላቀላለች" አለው ።

ፋብሪዝዮ ወደ ጋራዡ በችኮላ ሲሄድ ሚካኤል ተመለከተው ።

ሚካኤል ወደ መታጠቢያ ቤት አመራ ። አፖሎኒያ የለችም ። ምናልባት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ተለይታው

t.me/OLDBOOKSPDF

መሄዱ ስለሆነ ሀሊናዋን በለጸጸታት ጥፋቷን ለማጽዳት ዛሬ በእራሷ እጅ ቁርስ እያዘጋጀችለት ይሆናል ።

አሮጊቷ ፊሎሜና ቡናውን ለሚካኤል ካቀረበችለት በኋላ በማፈር ተሰናበተችው ። ሚካኤል

"እንቺን ማግኘቴን ላባቴ እነግረዋለሁ ።" ሲላት በእሺታ ራሷን ነቀነቀች ።

ካሎ ሚካኤል ቁርሱን ከሚበላበት መጥቶ ፣ "መኪናው ተዘጋጅቷል ። ሻንጣህን ልሜነው?" ሲል ጠየቀው ።

"የለም ፣ ራሴ ወስደዋለሁ ። የታለች አፓላ ?" ካሎ ፈገግ በማለት ፣ "መኪናው ውስጥ የሹፌር ቦታ ይዛ ለማሽከርከር ቸኩላለች ። አሜሪካ ከመድረሷ በፊት ደምበኛ አሜሪካዊት ትሆንልሀለች" አለ ። ለአንዲት ገጠሬ ሲሲሊያዊት መኪና መንዳት መሞከር ተሰምቶም አይታወቅ ። ሚካኤል ግን አጠገቧ ሆኖ እየተቆጣጠራት አፓሎኒያ ግቢው ውስጥ መኪናዋን እንድታንቀሳቅስ ያደርጋል ።

ሚካኤል ካሎን ፣ "ከፋብሪዚዮ ጋር መኪናው ውስጥ ቆየኝ" ብሎት እቃውን ሊያወጣ ወደ መኝታ ክፍሉ አመራ ። ሻንጣውን ከማንሳቱ በፊት በመስኮቱ ወደ ውጭ ሲመለከት መኪናዋ ወጥ ቤቱ መግቢያ ላይ ሳይሆን አምዶቹ አጠገብ ቆማለች ። አፖሎኒያ መኪናው ውስጥ ቁጭ ብላ እንደሚጫወት ልጅ መሪውን ይዛለች ።ካሎ ምሳቸው የተቋጠረበትን ቅርጫት ከመኪናው የኋላ መቀመጫ ላይ ያስቀምጣል ። ፋብሪዝዮ በአጥሩ በር ሲወጣ ተመልክቶ ሚካኤል ተናደደ ። ምናባቱ እያደረገ ነው? ፋብሪዝዮ በፍርሀት ሲገላመጥ ተመለከተው ። ያን እረኛ ልክ ማስገባት ይኖርበታል ። ሚካኤል ፊሎሜናን ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰናበት ወደ ወጥ ቤት ሄደና ፤

t.me/OLDBOOKSPDF

"ዶክተር ታዛ አሁንም እንደተኛ ነው?" ሲል ጠየቃት ።

አሮጊቷ ፊሎሜናም በጮሌነት ፥ "ያረጁ አውራ ዶሮዎች የጧት ጸሀይን ሰላም አይሏትም ። ዶክተሩ ትላንት ማታ ወደ ፓሌርሞ ሄዶ አምሽቶ ነው የተመለሰው" ስትል ሚካኤል ሳቀ ። በወጥ ቤቱ መግቢያ አድርጉ ሲወጣም የሎሚ አበቦች ሽታ የአፍንጫውን ሀመም ጥሶ ሸተተው ። አፖሎኒያ መኪና ውስጥ ሆና እጅዋን አወዛወዘች ። መኪናውን እሱ ወዳለበት ልትነዳ ስለሆነ ካለበት እንዲቆም ምልክት ሰጠችው ። ካሎም ጠመንጃውን አንግቦ እየሳቀ ይመለከታል ። ፋብሪዝዮ ግን ድራሹ ጠፍቷል ። በዚያ ቅጽበት በአእምሮው አንድ ነገር በድንገት ብልጭ አለበትና ፥ "ተይ ! ተይ!" ብሎ ጮኸባት ። ነገር ግን አፖሎኒያ ገና የመኪናዋን ቁልፍ ከመክፈቷ የተሰማው የፍንዳታ ድምጽ የሱን ጩኸት ዋጠው ። የወጥ ቤቱ በር ተበታተነ ። ሚካኤል ከነበረበት አስር ጫማ ያህል ርቆ ተወርውሮ ወደቀ ። ከቤቱ ግድግዳ ላይ የፈረሰው ድንጋይ ትከሻው ላይ መታው ። ሴላ ድንጋይ ደግሞ አናቱን ጨረፈው ። ሚካኤል በመጨረሻ ያየው ከመኪናዋ አራት የብረት መሽከርካሪያዎችና የተያያዙበት ብረት በስተቀር ሴላ ምንም ነገር እንዳልተረፈ ነበር ።

ሚካኤል በአንድ ጭለማ ክፍል ውስጥ ሆኖ ነፍስ ሲዘራ የከፍሉ መብራት በራ ። ዶን ቶማሲኖ ወደሱ ጠጋ ብሎ ላነጋግርህ አለው ። ሚካኤል በጁ እንዲያነጋግረው ምልክት ሲሰጠው ዶን ቶማሲኖ ጥያቄ አቀረበለት ።

"መኪናውን ከጋራዥ ያወጣው ፋብሪዚዮ ነበር?" ሚካኤል የንዴት ፈገግታ አሳየው ። ዶኑም ንግግሩን ቀጠለ

t.me/OLDBOOKSPDF

"ፋብሪዝዮ ጠፍቷል ። አድምጠኝ ፥ አንተ ለሳምን ንት ያህል ነፍስህን አታውቅም ነበር ። ሰዉ ሁሉ የሞ ትክ ስለመሰለው ክትትሉን በማቆሙ ለደህንነትህ መል ካም ነው ። ወደ አባትህ መልእክት ልኬ መልስ ከሰሞኑ አግኝቻለሁ ። ስለዚህ በቅርቡ ወደ አሜሪካ እንደምትመ ለስ ነግሮኛል ። በዚህ ተራራማ ስፍራ የግሌ በሆነው የግ ጠር ቤት ውስጥ ደህንነትህ ተጠብቆ ታገግማለህ ። ያንተ ሞት ስለተወራ የፓሌርሞ ተቀናቃኞቼም ከኔ ጋር ሰላም መስርተዋል ። ለካ ጠላቶቻችን እኔን የሚፈልጉ መስለው በአንተ ላይ አደጋ ለመጣል ነበር ሲሞክሩ የቆዩት ። ይህን ተገንዘብ ። ሌላ ሌላውን ለኔ ተውልኝና አንተ በረጋ መንፈስ ጤንነትህ እንዲመለስ በርታ"

ሚካኤል ሁሉንም ነገር ማስታወስ ጀመረ ።ሚስ ቱና ካሎ መሞታቸውን ተረዳ ። ፊሎሜናም አደጋ ደር ሶባት እንደሆነ ቢጠይቅ ትንሽ አፍንጫዋ ከመመታቱ በስተቀር ደህና መሆኗን ዶን ቶማሲኖ ነገረው ።

"ፋብሪዝዮ" አለ ሚካኤል በቁጭት ፥ " እረኞችህ ፋብሪዝዮን ይዘው ቢያመጡልኝ በሲሲሊ እጅግ ለም የሆነ መሬት ባለቤት እንደማደርጋቸው ንገርልኝ"

ሁለቱም ከጭንቀት የመገላገል ትንፋሽ ተነፈሱ ። ዶን ቶማሲኖ በአቅራቢያው ከሚገኝ ጠረጴዛ ላይ አእ ምሮውን እንዲያነቃው የሆነ ብጫ መልክ ያለው መጠጥ አንስቶ ጠጣ ።

ዶክተር ታዛም ሚካኤልን ያጽናናው ይመስል፥

"አንተ አሁን ሚስቱ የሞተችበት ወንደላጤ መሆ ንህን ታውቃለህ ። በሲሲሊ ይህ የተለመደ አይደለም" አለው ።

ሚካኤል ዶን ቶማሲኖ ወደሱ ጠጋ እንዲል ምል ክት ሰጠውና ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

“አባቴን ወደቤቴ ውሰደኝ በለው ። ልጅህ መሆን እፈልጋለሁ ብሎህል በለው” አለው ።

ነገር ግን ሚካኤል ከህመሙ ለመዳን አንድ ወር፥ ወደ አሜሪካ ለመመለስ የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች እስ ኪደራጁለት ደግሞ ሌላ ሁለት ወር ፈጀበት ። ከዚያ በኋላ ከፓሌርሞ ወደሮም ፥ ከሮም ወደ ኒውዮርክ በአውሮ ፕላን ተጓዘ ። የፋብሪዝዮ ደብዛ ግን ፈጽሞ ጠፋ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ ሰባት
ምእራፍ ሀያ አምስት

ኬይ አዳምስ የኮሌጅ ትምህርቷን አጠናቃ በኒው ሀምሻየር ውስጥ በተወለደችበት ከተማ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርነት ስራ ያዘች ። ከሚካኤል ከተለያየች እስከ ስድስት ወር ድረስ በየሳምንቱ መጨረሻ እናቱ ዘንድ እየደወለች ስለደህንነቱ ትጠይቃት ነበር ። የሚካኤልም እናት በክፋት ሳይሆን ለኬይ በማሰብ "አንቺ በጣም ጥሩ ልጅ ነሽ ። ሚካኤልን እርሽውና ጥሩ ባል አግቢ" በማለት ንግግሯን ትደመድማለች ።

የመጀመሪያው ተርም ትምህርት እንዳበቃ ጥቂት ልብሶች ለመግዛትና የድሮ ጓደኞቿንም ለመጠየቅ ወደ ኒውዮርክ ከተማ ሄደች ። በዚያውም ደስ የሚላት ስራ ብታገኝ ለመፈለግ አሰበች ። ለሁለት አመት ያህል ያለ ሌላ ፍቅረኛ ብቻዋን ስትኖር ፥ ወደ ሎንግ ቢች እነሚካኤል ቤት በመደወል ስለ ደህንነቱ ትጠይቅ ነበር ። መደወል ካቆመችም በኋላ ፥ ከማንበብና ከማስተማር በስተቀር አብረን እንዝናና ብለው የሚጋብዟትን ሁሉ እምቢ በማለት ኖረች ። እንደዚያ ሁና እንደ ማትዘልቅ ታውቋታል ። ብስጭትና ደስታ አልባ ሆናለች ። አሁንም ቢሆን ሚካኤል እንደሚጽፍላት ወይም አንድ መልእክት እንደሚልክባት ተስፋ ታደርጋለች ። እስከአሁንም ይህን አለማድረጉ ያሳፍራታል ። በሷ እንኳን ሳይቀር አመኔታ ማጣቱ አሳዝኗታል ።

የዚያን እለት ቀድሞ የሚነሳውን ባቡር ይዛ ከሰአት በኋላ ሲሆን ኒውዮርክ ደርሳ ሆቴል ያዘች ። ጓደኞቿን ከስራቸው ላይ ላለማደናቀፍ ስትል ማታ ልት ደውልላቸው ወሰነች ። ጉዞው ስላደከማት ወደሱቅም

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመውጣት አልፈለገችም ። ብቻዋን ሆቴል ክፍሏ ውስጥ ሆና ከሚካኤል ጋር በሆቴል ክፍሎች ውስጥ ያሳለፈችው ጊዜ ትዝ ሲላት ብቸኝነቷ አየለባት ። ይህን ጊዜ ነበር ከሚካኤል እናት ዘንድ ሎንግ ቢች መደወል የታሰባት ።

ስልኩን አንድ የኒውዮርክ አነጋገር ዘይቤ ያለው የወንድ ድምጽ መለሰላት ። ሚስዝ ኮርሌዎኔን ለማነጋገር እንደምትፈልግ ተናገረች ። ለጥቂት ደቂቃ ጸጥታ ሆነና የለመደችው ድምጽ ተሰማት ። ኬይ ትንሽ እንደማፈር አለችና ፥

"ኬይ አዳምስ ነኝ ፡ ሚስዝ ኮርሌዎኔ ፡ ታስታውሺኛለሽ?" አለቻት ።

"በሚገባ ፥ በደንብ ። ለምንድነው እስካሁን ሳትደውይልኝ የቀረሽው ? አገባሽ እንዴ" አለቻት ።

"እረ በፍጹም" አለች ኬይ ። "ስራ ስለበዛብኝ ነው ያልደወልኩት"

ኬይ ስልክ መደወል በማቆሟ አሮጊቷ መናደዷ አስገረማት ።

"ስለ ሚካኤል አንድም ነገር አልሰማሽ? ደህና ነው?" ስትል ኬይ ጠየቀቻት ።

ለጥቂት ጊዜ ጸጥ አለችና አሮጊቷ ድምጿን ከፍ አድርጋ ፥

"ሚኪ ቤት ተመልሷል ። እስካሁን አልደወለልሽም ? እስካሁን አልተገናኛችሁም ?" አለቻት ።
ኬይ ሆዷ ሁሉ ሲሸበርና ለማልቀስ ሲዳዳት ተሰማት ። በተሰባበረ ድምጽ ፥

"ከመጣ ስንት ጊዜ ሆነው?" ብላ ጠየቀች ።

"ስድስት ወሩ ነው"

"እሀ ፥ ገባኝ" አለች ኬይ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚካኤል እናት ልጅዋ ኬይን [redacted] ሳይቆጥራት መቆየቱን ማወቋ አሳፈራት ። ተናደደች ። በሚካኤል ተናደደች ፥ በእናቱ ላይ ተናደደች ፥ በውሟ አገር ዜጐች ሁሉ ላይ ተናደደች ። የፍቅር ልውውጥ ቢቀር እንኳን ስለ መዳጅነት ደንታ በሌላቸው ኢጣሊያኖች ላይም ተናደደች ። ከሷ ጋር ለመዳራት ባይሻ ፥ ወይም ሊያገባት ባይፈልግ እንኳን ፥ ኬይ ሰለሱ ደንታ ያላት መሆኑን ሚካኤል መገንዘብ ያቅተዋል ? ወይስ ድንግልናዋን ከሰጠች በኋላ ችላ ሲላት እራሴን ልግደል እንደምትል የዋህ የጣ ልያን ልጃገረድ አድርጐ ቆጥራት ይሆን ? ይህን ሁሉ ብታስብም በተቻለ መጠን ታገሰች ።

"ግባኝ ፤ አመሰግናለሁ" አለች ኬይ ። "ሚካኤል በደህና በመመለሱ ደስ ብሎኛል ። ይህን ለማወቅ ፈልጌ ነበር ። ሁለተኛ አልደውልልሽም"

የሚስዝ ኮርሌዎኔ ድምጽ ከትእግስት ውጭ ሆኖ ፥ ኬይ የተናገረችውንም እንዳልሰማች ሁሉ ፥ "ሚኪን ለማየት ከፈለግሽ እዚህ ነይ አሁን" አለቻት ። "እስቲ በድንገት ነይና አስደንግጪው ። እጥፍ እከፍላለሁ ብለሽ በታክሲ ነይ ። አለበለዚያ ታክሲ ሎንግ ቢች ድረስ አይመጣልሽም ። ታዲያ ግንዘቡን አትከፈይ ። የባሌ ባለሟል ከግቢው በር ስትደርሱ ይከፍለዋል ።"

"ይህንንስ አላደርገውም ፥ ሚስዝ ኮርሌዎኔ ። ሚካኤል ሊያየኝ ቢፈልግ ኖሮ ቤቴ ይደውልልኝ ነበር ። በግልጽ እንደተገነዘብኩት ፥ መዳጅነታችን እንዲቀጥል አይፈልግም" ስትል መለሰችላት ።

አሮጊቷ ግን ነቃ ብላ ፥

"በጣም ጥሩ ልጅ ነሽ ፥ ጥሩ ባት አለሽ ። ነገር ግን ጥሩ ሞንቅላት የለሽም" ብላት ሳቀች ። ቀጥላም ፥ "ነይና ሚካኤልን ሳይሆን እኔን ታይኛለሽ ፤ ላነጋግርሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

እፈልጋለሁ ። በቀጥታ ነይ አሁን ። ለታክሲው እንዳትከ ፍይው ። እጠብቅሻለሁ" ብላት ስልኩን ዘጋች ።

ኬይ እንደገና ደውላ አልመጣም ማለት ትችል ነበር ። ነገር ግን ሚካኤልን አግኝታ ልታነጋግረው ፈል ጋለች ። አሁን በግልጽ ቤት የሚገኝ ከሆነ ፥ ችግሩ ሁሉ ተወግዶ ሰላማዊ ኑሮ መምራት ይችላል ማለት ነው ። ኬይ ከአልጋዋ ላይ ዘላ ለመለባበስ ተነሳች ።

መልኳን ለማስዋብና ልብሷን ለመምረጥ ጥንቃቄ አደረገች ። ጉዞዋን ከመጀመሯ በፊት ፊቷን በመስ ታወት ተመለከተች ። ሚካኤል ከመሰወሩ በፊት ከነበ ረችበት ወቅት ዛሬ መልኳ ይበልጥ አምሮ ይሆን ? ወይስ አርጅታበት ማራኪነት ያጣባታል ? እርግጥ ቅርጿ ከቀ ድሞ የበለጠ የሴት ቅርጽ ይዟል ። ዳሌዋ ሰፋ ፥ ጡቷ ሞላ ብሏል ። ምንም እንኳን ሚካኤል ቅጥነቷን ይወድ የነበረ ቢሆንም ፥ ጣልያኖች ይህን የመሰለ ፈርጠም ጠም ያለ ቁመና ይወዳሉ ። ብቻ ያ ሁሉ ምንም አይደ ደል ፤ ሚካኤል ከሷ ጋር መዳጅነት አይፈልግም ። ቢፈ ልግ ኖሮ ባለፉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይደውል ላት ነበር ።

ያስቆመችው ታክሲ መጀመሪያ እምቢ ቢላትም ፥ ፈገግታ አሳይታው እጥፍ ዋጋ እንደምትከፍል ከነገረችው በኋላ ግን ወሰዳት ። እዚያው ስትደርስ በሩ ላይ ቆሞ የሚጠ ብቃት አንድ ሰው የታክሲውን ሜትር ለመመልከት ወደ ውስጥ አጐነበሰ ። ቆጣሪውን ከተመለከተ በኋላ ለባለ ታክሲው ሂሳቡን ከፈለው ። ባለታክሲው በከፍያው መደሰቱን ስታረጋግጥ ወርዳ ወደ ቤት አመራች ።

ሚስዝ ኮርሌዎኔ እራሷ በሩን ከከፈተችላት በኋላ እቅፍ አድርጋ ስትቀበላት ኬይ ተደነቀች ። እሮጊቷ ኬይን ከላይ እስከታች ተመልከታት ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ቆንጆ ልጅ ነሽ ። እኔ ግን ደደብ ልጆች ናቸው ያሉኝ" አለቻት ። ኬይን ወደ ውስጥ አስገብታ ምግብ ተዘጋጅቶ ቡናው ምድጃው ላይ ከሚንፈቀፈቅበት ማድ ቤት ይዛት ሄደች ።

"ሚካኤል አሁን ይመለሳል ። እዚህ ሲያገኝሽ ይደነቃል"

አብረው ተቀምጠው ሳለ ፥ ኬይ ምግብ እንድት በላ እየገፋፋች ለማወቅ በመጓጓት ስለ እራሰዋም ጠየቀ ቻት ። ኬይ አስተማሪ መሆኗ ፥ ወዳጆችዋን ለመጠየቅ ኒውዮርክ መምጣቷ ፥ እድሜዋ ገና ሀያ አራት አመት ብቻ መሆኑ አሮጊቷን አስደሰታት ። እናት ኮርሌዎኔ በአእምሮዋ ውስጥ ካለው ፍላጐት ጋር ኬይ የምትሰጣት መልስ የተጣጣመ ይመስል ራሷን በመስማማት ትነቀ ንቀዋለች ። ኬይ እንደማፈር ብላ የጠየቀቻትን ጥያቄ ብቻ ትመልስላት ነበር ።

ሚካኤል በመኪና ሲመጣ በማድቤቱ በኩል ተመለከተች ። ሁለት ሰዎች በቅድሚያ ከመኪና ውስጥ ወጡ ። ቀጥሎ ሚካኤል ወጣና ልብሱን ከአስተካከለ በኋላ ከአንዱ ሰውዬ ጋር ተነጋገረ ። በግራ ፊቱ በኩል ታያት ። ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰበት ስትመለከት አለቀሰች ። ሚካኤል ነጭ መሀረብ አውጥቶ አፍና አፍ ንጫው ላይ ለጥቂት ጊዜ ከያዘው በኋላ ወደ ቤት አመራ ።

ኬይ በሩ ሲከፈትና ሚካኤል ጉዞውን እነሱ ወዳ ሉበት ማድቤት ሲያመራ አዳመጠች ። ወዲያው በሩን ከፍቶ ከሷና ከእናቱ ፊት ብቅ አለ ። በመጀመሪያ ፊቱ ምንም ሁኔታ አላሳየም ። ኋላ ግን በትንሹ ፈገግ አለ ። ሙሉ ፈገግታ እንዳያሳይ የተዛባው አጥንቱ ከለከለው። ኬይም በበኩሏ ፥ "ታዲያስ ፥ እንደምነህ ?" በማለት ብቻ ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ለመስጠት ወሰና የነበረ ችው ቀረና ፥ ከመቀመጫዋ ላይ ተወርውራ ሄዳ ፊቷን

t.me/OLDBOOKSPDF

ትከሻው ውስጥ ቀበረችው ። የሬጠበውን ጉንጯን ላመና ልቅሶዋን እስክታቆም ድረስ አቀፋት ። ከዚያም ወደ መኪናው ይዟት ሄደ ። የግል ጠባቂውን አሰናብቶ ፥ ከጐኑ አስቀምጧት መኪናውን መንዳት ቀጠለ ። ኬይ የተኳለ አይኗና ቅባት ያወዛው ፊቷ በእንባ ርሷል ። ፊትዋን በመሀረቧ ከጠራረገች በኋላ ፥

"እንዲህ አስቤ አልነበረም ። ማንም ሰው እንዲህ ሆነህ መጐዳትህን የነገረኝ የለም" አለችው ።

ሚካኤል እየሳቀ የተሰረጐደውን ፊቱን ነካና ፥

"ይህን ማለትሽ ነው? ምንም አይደል ። ብቻ ትንሽ የአፍንጫ ውስጥ ችግር አስከትሎብኛል ። እንግዲህ ከዚህ ከተመለስኩ ፥ አስተካክለዋለሁ ። ልጽፍልሽ ወይም አንድ ነገር ለማድረግ አልቻልኩም ። ከሁሉም ነገር በላይ ይህ እንዲገባሽ ያስፈልጋል" አላት ።

"እሺ" አለችው ።

"ከተማው ውስጥ ቤት አለኝ ። እዚያ እንሂድ ወይስ ምግብ ቤት ሄደን እራት እየበላን እንጠጣ?" አላት ።

"አልራበኝም" አለች ።

ከጥቂት ጸጥታ በኋላ ፥

"ተመርቀሽ ዲግሪሽን አገኘሽ?" ሲል ጠየቃት ።

"አዎን ። በተወለድኩበት ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተምራለሁ ። ለመሆኑ የፖሊሱ ሻምበል ገዳይ ተገኘ? ስለተገኘ ነው እንተ የተመለስከው ?"

ለአፍታ ያህል ሚካኤል መልስ ሳይሰጣት ቆየና ፥ "አዎን ፥ አግኝተውታል ። ታሪኩ በኒውዮርክ ጋዜጦች ላይ ወጥቶ ነበር ። አላነበብሽውም?" አላት ።

ኬይ እሱ ነፍሰ ገዳይ አለመሆኑን በማረጋገጧ ከስቃይ በመገላገል ሳቀች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣን ብቻ ነው በከተማችን የምናገኘው። ምናልባት ጋዜጣው ዜናውን ከወደመጨረሻ ገጹ ላይ ቀብሮት ይሆናል። ብሰማ ኖሮማ እናትህን ወዲያው እደውልላት ነበር" አለችው። ጥቂት ዝም ካለች በኋላም፣ "እናትህ ትለኝ የነበረው የሚደንቅ ነው። እንዳ ነጋገርዋ አንተ የገደልከው መስሎኝ ነበር። ቅድም አንተ ልትመጣ ስትል ነው እኔ ነኝ የገደልኩት ብሎ ስለተና ዘዘው ሰውዬ ያወራችልኝ" አለች።

"ምናልባት እናቴም እኔ የገደልኩት መስሏት ሊሆን ይችላል"

"የወለደችህ እናትህ?"

"እናቶችና ፖሊሶች አንድ ናቸው። ክፉውን ነገር ብቻ ነው በቅድሚያ የሚጠረጥሩት"

ሚካኤል አንድ ከሚያውቀው ሰው ጋራዥ ውስጥ መኪናውን አቆመና ኬይን ከአንድ ያረጀ የሚመስል የተያያዘ ቤት ይዟት አመራ። ሰፈሩም ያረጀ ነው። ሚካኤል የቤቱን ዋና በር በቁልፍ ከከፈተ በኋላ ውስጥ ሲገቡ ቤቱ በውድ የቤት እቃዎች የተሟላ የአንድ ሚሊዮነር ቤት ሆኖ አገኙትው። ሚካኤል እየመራት ወደ ፎቅ አፓርትማ በሚወስድ ደረጃ ወጡ። ቤቱ ሰፊ እንግዳ ቤት፣ ትልቅ ማድቤትና ወደ መኝታ ቤት የሚያመራ በር አለው። በእንግዳ ቤቱ ውስጥ ካንድ ማእዘን ላይ መጠጥ ተደርድሯል። ሚካኤል ለሁለቱም ቀዳ። ሁለቱም ሶፋ ላይ ተቀምጠው ሳለ፣

"ወደመኝታ ቤታችን ብንሄድ ይሻላል" አላት። ኬይ ከመጠጡ በረሸመ ተጐንጭታ ፈገግ ብላ፣ "እምን" አለችው።

ለኬይ የፍቅር ልውውጡ ያው የምታውቀው የጥንቱ ነው። ብቻ ሚካኤል ትንሽ ኃይለኛ፣ ከቀድሞ የበለጠ ግልጽ ሆኖ፣ ከሷ እራሱን የሚከላከል ይመስል

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደቀድሞው ልስልስ አልነበረም ። እሷ ግን ምንም ቅሬታ ማሰማት አልፈለገችም ። ይተወዋል ። የሚያስገርመው ፡ 'እንዲህ በመሰለ ሁኔታ ወንዶች ከሴቶች ይበልጥ ስሜታዊ ናቸው' ብላ አሰበች ። ከሁለቱ አመታት በኋላ ከሱ ጋር የፍቅር ልውውጥ ስታደርግ ምንም አዲስ ነገር አልመሰላትም ፡ ልክ ተለያታት የማያውቅ ይመስል ።

"ደብዳቤ ልትጽፍልኝና ልታምነኝ ትችል ነበር ። እኔም የአሜርታን ሰምቶና አይቶ ዝም የማለት ሀግ በተግባር አውለው ነበር ። ያንኪዎችም እኮ ጋግርታም ናቸው" አለችው ጉያው ውስጥ እየተሸጎጠች ።

ሚካኤል በጭለማው ውስጥ ሳቅ ብሎ ፡ " ያን ሁሉ ክሰማኝ በኋላ ትጠብቂኛለሽ ብዬ ተስፉ አላደረግኩም ነበር" አላት ።

ኬይ በችኮላ መለሰችለት ፡ "የእናትህን አነጋገር ከሰማሁ በኋላ ጥርጣሬ ቢያድርብኝም እነዚያን ሰዎች ገድለሀል የሚል እምነት ፈጽሞ አልነበረኝም"

ሚካኤል በሲቃ ሲተነፍስ ኬይ አዳመጠችው ።

"እኔ ገደልኩት አልገደልኩት ልዩነት የለውም ። ይህን መረዳት ይኖርብሻል" አላት ።

የድምጹ አቀዛቀዝ አስገርሟት ፡ "እሺ አሁን ንገረኝ ። አርገኸዋል ወይስ አላረግከውም ?" አለችው ።

ሚካኤል በጭለማው ውስጥ ትራሱ ላይ ቁጭ ብሎ ሲጋራ አቀጣጠለና ፡

"አግቢኝ ብዬ ብጠይቅሽ ፡ መልስ ከመስጠትሽ በፊት በቅድሚያ ይህን ጥያቄ መመለስ አለብኝ ?" ሲል ጠየቃት ።

"ግድ የለኝም ። እኔ እወድሀለሁ ። ከወደድከኝ ለኔ እውነቱን ለመንገር አትፈራም አይደለም ? በእርግጥ ወን በዱ ነህ ፡ አይደል ? እኔ ግን ግድ የለኝም ። እኔ የሚ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያሳሰበኝ የአንተን ፍቅር ማጣት ብቻ ነው። አንተ ግን ወደ ቤትህ ስትመለስ እንኳን ሳትደውልልኝ ቀረህ”

ሚካኤል ሲጋራውን ሲስብ ትኩስ አመድ ጀርባዋ ላይ ረገፈ። ጥቂት ተንቃነቀችና በቀልድ አንጋገር፥

“ማሰቃየትህን አቁም፥ አልናገረም” አለች። ሚካኤል አልሳቀም። ለጊዜው በሀሳቡ ርቆ መሄዱ ከአንጋገሩ ያስታውቃል።

“ታውቂያለሽ፥ ወደ ቤቴ ስመለስ ዘመዶቼን፥ እናቴን፥ እህቴን ኮኒን እና ቶምን ሳያቸው ምንም ያህል ደንታ አልነበረኝም። ዛሬ ግን ቤቴ ስመጣ አንቺን በማግኘቴ ደስ አለኝ። ፍቅር ብለሽ የምትይው ይህን ነው?”

“በኔ ግምት አዝማሚያው ወደዚያው ነው”

እንደገና የፍቅር ልውውጣቸውን ቀጠሉ። አሁን ደግሞ ሚካኤል ከቅድመ ይበልጥ ልስልስ ሆኖ ፍቅር አሳያት። ሂዶም ለሁለቱም መጠጥ አመጣ። ሲመለስ ባለ እጅ መደገፊያ ወንበር አምጥቶ ወደ አልጋው አስጠግቶት ተቀመጠ።

“አሁን ሁለታችንም ፍርጥም ብለን ቁም ነገር እናውራ” አለ ሚካኤል። “እኔን ስለማግባት ምን ሀሳብ አለሽ?”

ኬይ ፈገግ ብላ ወደ አልጋው እንዲመጣ ምልክት ሰጠችው። ሚካኤልም ፈገግ አለና፥ “በውል ቁምነገረኛ ሁኚ። ስለደረሰው ጉዳይ ምንም እማወራልሽ ነገር አይኖርም። አሁን ባባቴ ስራ ውስጥ ተሰማርቻለሁ። የቤተሰቡን የወይራ ዘይት ንግድ እንዳካሂድ ስልጠና እየተሰጠኝ ነው። ነገር ግን ቤተሰቤ ጠላቶች እንዳሉት ታውቂያለሽ። አባቴ ጠላቶች አሉት። ምናልባት እኔን ብታገቢ ባሏ የሞተባት ወጣት የመሆን እድል ሊያጋጥምሽ ይችላል። በየእለቱ በቢሮዬ ውስጥ ስለማካሂደው ስራዬ ምንም ነገር አልነግርሽም። ሚስቴ ትሆኛለሽ። ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን በህይወት እንቅስቃሴዬ ውስጥ ተጋሪ አትሆኝም ። እኩል ተጋሪ አላደርግሽም ። ይህ ደግሞ ሊሆን አይችልም'' አላት ።

ኬይ አልጋው ላይ ቁጭ አለች ። የራስጌ መብራት አበራችና ሲጋራ አቀጣጠለች ። ትራሱ ላይ ደገፍ ብላ በጽሞና እንዲህ አለችው ።

''አሁን የምትነግረኝ ወንበዴ መሆንህን ነው ፣ አይደል? ለሚገደሉ ሰዎችና ከግድያ ጋር ለተያያዙ ልዩ ልዩ ወንጀሎች ተጠያቂ መሆንህን ነው የምትነግረኝ ፣ አይደል? እና እኔ ይህን በመሰለው ህይወትህ ውስጥ ምንም ድርሻ የለኝ ። ሌላ ቀርቶ ላስብም አልችልም ። ለክ በፊልም ውስጥ እንደምናየው አስደንጋጭ ታሪክ ፣ አስፈሪ አውሬ ቆንጆ ልጅ እንድታገባው እንደሚጠይቃት!''

ሚካኤል ፊቱን በተናጋው በኩል ወደሷ እያቃና ፈገግ አለ ። አስፈሪ አውሬ ሰትል የፊቱን አስቀያሚነት ያነሳች መስሎት የከፋው መሰላትና በጸጸት ፣

''ማይክዬ ፣ ይህን አስቤ አይደለም እንዲህ ያልኩት። እምላለሁ ፣ አንተን ማለቴ አይደለም'' አለችው ።

''አውቃለሁ ። ከአፍንጫዬ የሚወጣውን ፈሳሽ ብቻ ነው የጠላሁት እንጂ ፣ እንዲህ መሆኑን ወድጄዋለሁ'' አላት ።

''ቁምነገረኛ ሁኚ ብለኸኛል ። ለመሆኑ ብንጋባ ምን አይነት ኑሮ ነው ምኖረው? ልክ እንደ እናትህ ፣ ልክ እንደጣልያን የቤት እመቤት ልጆችና ቤት መጠበቅ ብቻ! አንድ ነገር ቢደርስስ? አንድ ቀን መጨረሻህ እስር ቤት ሊሆን ይችላል''

''እሱስ አይሆንም ። ልገደል እችላለሁ ፣ መታሰር ግን የለም'' አላት ።

ኬይ በሚካኤል ልበሙሉነት ሳቀችና ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት እንደዚህ ለማለት ቻልክ! ክምር!"
ስትል ጠየቀችው።
ሚካኤል ተነፈሰና፥
"ይህ ሁሉ ላንቺ ላወራልሽ የሚገባ ጉዳይ አይደለም። ልናገረውም አልፈልግም" አላት።
ኬይ ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ከቆየች በኋላ፥ "ይህን ሁሉ ጊዜ ሳትጠይቀኝ ቆይተህ አሁን እንዳገባህ ለምን ጠየቅከኝ? አልጋ ላይ ያን ያህል አስደስትህለሁ?" አለችው።
ሚካኤል በአምንታ እራሱን ነቀነቀና፥
"አምን፥" አላት። "ግን እሱንም በነጻ እያገኘሁት ነው። እንዴት ለሱ ብዬ አገባሻለሁ? እኔ አሁኑኑ መልስ እንድትሰጭኝ አልፈልግም። ግንኙነታችን ይቀጥላል። ከወላጆችሽ ጋር ተመካከሪ። አባትሽ በእምነቱ የሚጸና ከባድ ሰው መሆኑን ሰምቻለሁ። ምክሩን አድምጪው።"
"ለጠየቅኩህ መልስ አልሰጠኸኝም። ለምን ልታገባኝ ፈለግህ?"
ሚካኤል ከጠረጴዛው ኪስ ውስጥ መሀረብ ካወጣ በኋላ የአፍንጫውን ፍሳሽ ጠረገው።
"እኔን ላለማግባት ትልቅ ምክንያት አለሽ። ንፉ ጣም ባል ማን ማግባት ይፈልጋል?"
ኬይ ትእግስቷ አልቆ፥ "ተው እንግዲህ፥ ይልቅስ ቁምነገረኛ ሁንና ጥያቄዬን መልስ"
ሚካኤል መሀረቡን እንደያዘ፥ እንዲህ አላት፥
"እሺ፥ የዛሬን ብቻ እመልሳለሁ። የምወደውና የምጨነቅለት ሰው አንቺ ብቻ ነሽ። ስለክ ያልደወልኩልሽ ያን ሁሉ ወሬ ከሰማሽ በኋላ ለኔ የነበረሽ ፍቅር ይቀጥላል ብዬ አልገመትኩም። እውነቱን ነው፥ ላሳድድሽ እችል ነበር። ላባብልሽም እችል ነበር። አልፈለግኩም። አንድ አንቺን በማመን ልገልጽልሽ የምፈልገው

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳይ አለ ። ይህን ጉዳይ ግን ላባትሽ እንኳ ቢሆን እንድትነግሪው አልፈልግም ። ያሰብናቸው ነገሮች ሁሉ ከተሳኩ የኮርሌዮኔ ቤተሰብ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ህጋዊ ይሆናል ። ነገር ግን አንዳንድ የሚወሰዱ አስቸጋሪ እርምጃዎች ይኖራሉ ። ያኔ ባሏ የሞተባት ሀብታም ሴት መሆን ሊያጋጥምሽ ይችላል ። ለምንድነው የፈለግ ከኝ ላልሽኝ ፣ በቅድሚያ አንቺን ማግኘት እፈልጋለሁ ። ቤተሰብ መመስረት እፈልጋለሁ ። ልጆች መውለድ እፈልጋለሁ ፣ ወቅቱ ነው ። እኔ አባቴ የተሰማራበት ሁኔታ ተጽእኖ እንዳሳደረብኝ ልጆቼ የኔ ተጽእኖ እንዲ ያድርባቸው አልሻም ። ይህንም ስልሽ አባቴ አውቆ ተጽእኖ አሳድሮብኛል ማለቴ አይደለም ። ሌላ ቀርቶ በቤተሰቡ ስራ ውስጥ እንኳን እንድሰማራ አልፈለ ገም ነበር ። እኔ ምሁር እንድሆን ፣ እንደሀኪምነት በመ ሳሰለው ሙያ ላይ እንድሰማራ ነበር ፍላጎቱ ። ግን ነገ ሮች ሁሉ መጥፎ መንገድ ስለያዙ ለቤተሰቡ መዋጋት ነበረብኝ ። የተዋጋሁትም አባቴን ስለማፈቅረውና ስለ ማደንቀው ነው ። የሱን ያህል ክብር ይገባዋል ብዬ የማም ነው ሰው የለም ። ጥሩ ባልና ጥሩ አባት እንዲሁም ቀን ለከዳቸው ወዳጆቹም መልካም አለኝታ ነው ። ሌላ ጐንም አለው ፣ ነገር ግን ስለዚያ እኔን የሚያገባኝ ነገር የለም ። ያም ሆነ ይህ ፣ ልጆቼ ላይ ይህን የመሰለው ሁኔታ እንዲ ደርስ አልሻም ። መልካም ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ እፈ ልጋለሁ ። ምናልባትም የነሱ ልጆች በፖለቲካው ውስጥ ገብተው ያገለግሉ ይሆናል ። ምናልባት አንዱ ፕሬዝዳንት ሊሆን ይችላል ። ለምን አይችልም? ትምህርት ቤት ሳለሁ ስለ አሜሪካ ፕሬዝዳንቶች የኋላ ታሪክ ስናጠና እንደተማርኩት የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች አባቶችና አያ ቶች ሳይሰቀሉ የቀሩት እድለኛ ስለሆኑ ብቻ ነው ። ነገር ግን ልጆቼ ሀኪሞች ፣ ሙዚቀኞች ወይም መምህራን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲሆኑ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ ። በቤተሰብ ስራ ውስጥ ፊጽሞ አይሰማሩም ። እነሱ ሲደርሱ እኔ ደግሞ ጡረታ እወጣለሁ ። ያኔም አንቺና እኔ የገጠር ክበብ አባላት ሆነን እንደ ጥሩ ሀብታም አሜሪካዊያን መኖር እንችሳለን ። ይህ እቅድ ምን ያህል ያረካሻል?"

"ግሩም ነው" አለች ኬይ ። "በቻ ባሏ የሞተባት ሴት ስለመሆን ጉዳይ አልተናገርክም"

"እንዲያ ለመሆን እንኳን ብዙ አጋጣሚ አይኖ ርም ። እንዲያው ሊያጋጥም የሚችል መሆኑን ልገልጽ ልሽ ብዬ ነው" አለ ሚካኤል አፍንጫውን በመሀረቡ እየነካካ ።

"እኔ ይህን ላምን አልችልም ። አንተ እንዲህ ያለህ ሰው ነህ ብዬ ላምን ያዳግተኛል ። ፊጽሞ እንዲህ ያለህ ሰው አይደለህም ። አሁን ያልካቸው ሁኔታዎች እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ አላውቅም ።እንዴት ሊሆን ይችላል?"

"እንግዲህ ፣ ከዚህ በላይ ማብራሪያ ልሰጥሽ አል ችልም ። እንደዚህ የመሰለው ጉዳይ ካንቺ ጋር አብረን ከምናካሂደው ህይወት ጋርም የተያያዘ ስላይደለ አት ጨነቂ" ሲል ሚካኤል ሊያዝናናት ሞከረ ። ኬይ ግን ራሷን ነቀነቀችና ፣

"እንዴት አድርገህ ልታገባኝ ትፈልጋለህ?" አለ ችው "እንዴትስ አፈቅርሻለሁ ልትለኝ ትችላለህ ። ቃሉን እንኳን ደፍረህ አልተናገርከውም ። አሁን ስትናገር እንደ ሰማሁህ አባትህን እወዳለሁ ብለህ እኔን ግን ወድሻለሁ ስትል አልሰማሁም ። በህይወትህ ዋናውን ነገር ለመን ገር ልታምነኝ ካልቻልክ እንዴትስ ልታፈቅረኝ ትች ላለህ? የማታምናት ሚስትስ እንዴት ለማግባት ትመ ኛለህ? አባትህ እናትህን እንደሚያምናት አውቃለሁ"

"እውነት ነው ያምናታል ። ታዲያ ሁሉንም ነገር ይነግራታል ማለት አይደለም ። ሊያምናት እንደሚገባ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግልጽ ነው ። የሚያምናት ስለተጋቡና ሚስቱ ስለሆ
ነች አይደለም ። ነገር ግን አራት ልጆች ለመውለድ
አመች ባልነበረበት ዘመን አራት ልጆች ወልዳለታለች።
ሰዎች ሲተኩሱበት ተንከባክባዋለች ። በእሱ ላይ እምነት
አላት ። ይኸውም ለአርባ አመት ሙሉ ከማንም አስቀ
ድማ የመጀመሪያ ታማኝነት የምትሰጠው ለሱ ነው ።
እሷ ያደረገችውን ሁሉ ካደረግሽ በኋላ እኔም አንዳንድ
ልትሰሚ የማትፈልጊያቸውን ነገሮች እነግርሻለሁ''

''እነሱ ከሚኖሩበት ግቢ ውስጥ መኖር አለብን?'' ብላ
ኬይ ስትጠይቀው ሚካኤል በአምንታ ራሱን ነቀነቀ ።

''የራሳችን መጠነኛ ቤት ይኖረናል ። ወላጆቼም
ጣልቃ አይገቡብንም ። ህይወታችንን ራሳችን እንመ
ራዋለን ። ነገር ግን ሁሉ ነገር እስኪስተካከል በግቢው
ውስጥ መኖር አለብኝ''

''ከግቢው ውጭ መኖር ለእንተ አደገኛ ስለሚ
ሆን ነው?''

ከተዋወቀችው ጀምሮ ገና ዛሬ ሚካኤል ሲናደድ
አየችው ። ንዴቱ ከፊቱ ላይ በግልጽ የማይታይ ወይም
በድምጹ ውስጥ በግልጽ የማይለይ ቀዝቃዛ ንዴት ነበር ።
እንደሞት የቀዘቀዘ ንዴት ስለነበር እንዲህ ያለውን
ቅዝቃዜ ስለማትወደው በማንገራገር ላይ ብትሆን ኖሮ
ላለማግባት ትቆርጥ ነበር ።

ነገር ግን ሚካኤል ማብራሪያውን ቀጠለ ።

''በሲኒማና በጋዜጣዎች የሚተላለፈው ዝባዝንኪ
ስላባቴና ስለኮርሌዎኔ ቤተሰብ ያለሽን አመለካከት የተ
ዛባ አድርጎታል ። በዚህ ጉዳይ ላይ የምሰጥሽ ማብራሪያ
የመጨረሻ ይሆናል ። አባቴ ሚስቱንና ልጆቹን እንዲ
ሁም እርዳታቸውን ወዳጆቹን አንድ ቀን ሊሻ የሚችል
ለመንከባከብ የሚጥር ነጋዴ ነው ። እሱን ለመሰለ ፣
ከመጠን በላይ የሆነ ሀይልና ብቃት ላለው ሰው የሚስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግማ ባለመሆኑ ያለንበት ህብረተሰብ ያወጣውን ህግ አይቀበለውም ። መገንዘብ ያለብሽ እሱ እራሱን ከፕሬዚዳንቶች ፥ ከጠቅላይ ሚኒስትሮችና ከገዢዎች እኩል አድርጐ ይገምታል ። የነሱ ህግ እሱን የምርኮኛ ህይወት እንዲመራ ስለሚያደርገው በነሱ ፊቃድ እራሱን ለማስገዛት አሻፈረኝ ብሏል ። ህብረተሰቡ የራሳቸው የግል ጉልበት የሌላቸውን ሰዎች ስለማይጠብቃቸው እሱ ህብረተሰቡን ሊቀላቀል የሚሻው የራሱን ጠንካራ ህይል ጨብጦ ነው ። ይህን ለማድረግም ከህጋዊው ስርአት ይልቃል ብሎ የሚያምንበትን አንድ የአሰራር ስርአት አዋቅሮ ያካሂዳል”

ኬይ ማመን እያቃታት ሚካኤልን ተመለከተችው ።

“ይህን አባባልህን ለመቀበል ፈጽሞ ያስቸግራል ። ሁሉም ሰው በየበኩሉ ተመሳሳይ አመለካከት ቢኖረው ኖሰ? ማህበራዊ እንቅስቃሴ እንዴት በስርአት ሊካሄድ ይችላል? ወደጥንታዊው የዋሻ ሰው ኑሮ መመለሳችን ነው ። ይህን አባባልህን በእርግጥ ታምንበታለህ?”

ሚካኤል ፈገግ አለና ፥ “የምንግርሽ ያባቴን እምነት ነው ፥” አላት ። “እንድትረጂ የምፈልገው ግን አባቴ ምንም ይሁን ምንም ፥ ሀላፊነቱን የሚረሳ ሰው አይደለም ። ቢያንስ እሱ በፈጠረው አለም ውስጥ ሀላፊነቱን በሚገባ ይወጣል ። አንቺ እንደምትገምቺው ሰዎችን በጠመንጃ የሚፈጅ እብድ አይደለም”

“ያንተስ እምነት እንዴት ነው?”

ሚካኤል ትከሻውን ነቀነቀ ። “እኔ እምነቴ በቤተሰቤ ነው ። እምነቴ ባንቺ እና በምንመሰርተው ቤተሰብ ይሆናል ። ህብረተሰቡ ይጠብቀናል የሚል እምነት የለኝም ። እኔ ብቃታቸው የተወሰኑ ሰዎች እንዲመርጧቸው ግባባት እስከመቻል ብቻ በሆነ ሰዎች መዳፍ ውስጥ እጣዬን ላስቀምጥ አልፈልግም ። ያም ሆነ ይህ ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለፈው አልፏል ። ብንወድም ብንጠላም የኮርሌዎኔ ቤተ ሰብ ከዚያ ሀብረተሰብ ጋር መቀላቀል ይኖርበታል ። እኛም ስንገባበት በገንዘብና በሌላ ንብረት የተጠናከረ አቋም ይዘን እንዲሆን እፈልጋለሁ ። ያንን አጠቃላይ እጣ ከመጋራታቸው በፊት የኔም ልጆች ደህንነታቸው መረጋገጥ አለበት"

"ቀድሞ ግን እኮ ለሀገርህ ለመዋጋት በፈቃድህ ዘምተህ ነበር ። የጦር ጀግንነትንንም ተቀዳጅተሀል ። ታዲያ እንዲህ የመሰለውን አቋምህን እንዴት ለመቀየር በቃህ?"

"በዚህ አይነት ክርክራችን ከቀጠልን የትም አንደርስም ። እኔ ምናልባት ወግ አጥባቂ ሳልሆን አልቀርም ። በግሌ ራሴን እጠብቃለሁ ። መንግስታት ለህዝባቸው የሚያደርጉት ምንም ያህል ነገር አይኖርም ። አሁን ግን አባቴን መርዳትና ከሱ ጐን መቆም አለብኝ ። አንቺም ከኔ ጐን ለመቆም መወሰን ይኖርብሻል" ፈገግ እያለ ፥ "እንጃ ፥ መጋባት ጥሩ ሀሳብ አልመሰለኝም" አላት ።

ኬይ አልጋውን መታ መታ አድርጋው ፥ "ስለጋብቻ የማውቀው የለኝም ። ያለወንድ ሁለት አመት የቆየሁ ስለሆነ ግን በቀላሉ የምለቅህ እንዳይመስልህ ። ና ወደ ዚህ" አለችው ።

መኝታው ላይ ተጋድመው መብራቱ ጠፍቶ ሳለ በጆሮው እንዲህ ስትል አንሾካሾከች ፥

"ካንተ ከተለየሁ ወንድ እንዳላገኘሁ ታምነኛለህ ?"

"አምንሻለሁ"

"አንተስ አድርገሀል?" ስትል በለሰለሰ ድምጽ ጠየቀችው ።

"አዎን" ሲላት ሰውነቷ ሲጠጥር ተሰማው ።

"ነገር ግን ባለፉት ስድስት ወራት ምንም አላደርኩም" አላት ። እውነቱን ነበር ። ከአፖሎኒያ ሞት በኋላ ሴት ሲሄድ ኬይ የመጀመሪያው ነበረች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምእራፍ ሀያ ስድስት

ከልክ ያለፈ ደምቆ ያጌጠው የሆቴሉ መኖሪያ ቤት ከውብ ትርኢት ትይዩ ሆኖ ከሆቴሉ በስተጀርባ ይገኛል ። ራቅ ራቅ ብለው የተተከሉት ዘምባባዎች በብር ቱካንማ የኤሌክትሪክ ብርሀን አሸብርቀዋል ። የበረሀማው መሬት ጭለማ ጥቁር ሰማያዊ ብርሃኑን በሁለቱ የመዋኛ ኩሬዎች ላይ ያንጸባርቃል ። የአሸዋና የድን ጋይ ተራራዎች የሚታይበት አድማስም ላስ ቬጋስን በብሩህ ሸለቆው ውስጥ ከቧታል ። ጆኒ ፎንቴን በውድ ጌጥ የተጠለፈውን ሽሮ መልክ መጋረጃ ወደታች ለቀቀውና ፊቱን ወደ ክፍሉ መለሰ ።

አራት አባላትን ያቀፈው ልዩ የዝግጅት ቡድን አንድ የውድድሩ መሪ ፥ አንድ አጫዋች ፥ ተጨማሪ ተለዋጭ ሰው ፥ ጥቂት ልብስ ብቻ በሰውነቷ ላይ የሚታይ የኮክቴል አሳላፊ የሚገኙበት ሲሆን ፥ ለግል ክንውኖች እየተዘጋጁ ነው ።

ኒኖ በውሀ ብርጭቆ የተቀዳ ዊስኪ በጁ ይዞ ሶፋው ላይ ጋደም ብሏል ። አስተናጋጆቹ የፈረስ ኮቴ ቅርጽ ባለው ጠረጴዛ ዙሪያ ለቁማርተኞች መቀመጫ የሚሆኑትን ስድስት ወንበሮች ሲደረድሩ ተመለከታቸው ።

“ግሩም ነው! ግሩም ነው!” በማለት ኒኖ ሙሉ በሙሉ ባልሰከረ ጮርናና ድምጽ ተናገራቸው ። ቀጥሎም ፥ “ጆኒ ናና ከኔ ጋር ሆነህ እነዚህን ዲቃሎች ቁማር እንግጠማቸው ። እደል ከኔ ጋር ናት ። ድባቅ እንመታቸዋለን” አለው ።

ጆኒ በሶፋው ፊት ለፊት ካለው የእግር ማስቀመጫ ላይ ተቀመጠና ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ቁማር እንደማልጫወት ታቃለህ" አለው። "ለመሆኑ ጤንነትህ እንዴት ነው፣ ኒና?" ሲል ጠየቀው።

ኒኖ ቫሌንቲ ፈገግ አለና፣ "በጣም ጥሩ። ዛሬ እኩለ ሌሊት ላይ የሚመጡ ቆነጃጅት አሉኝ። ከዚያ በኋላ ጥቂት እራት እንበላና ወደ ካርታ ጨዋታችን እንመለሳለን። ሀምሳ ሺህ ብር በልቼ ለአንድ ሳምንት ያህል ሲፈጩኝ እንደሰነበቱ አውቀህል?" አለ።

"ለመሆኑ ስትሞት ለማን ታወርሰዋለህ?"

ኒኖ ውስኪውን ጨለጠና "ጆኒ፣ አለሙን ይቀጫል የሚል ዝና ያገኘኸው እንዴት ነው? አንተ ለራስህ ቀሽም፣ እዚህ አገር የሚመጡ ቱሪስቶች እንኳ ካንተ የተሻለ ይደሰታሉ" በማለት መለሰለት።

"ልክ ነህ። ካርታ መጫወቻው ጠረጴዛ የሚያደርስህ መጓጓጥ ያስፈልግሀል?" አለ ጆኒ።

ኒኖ በተቀመጠበት ቀጥ አለና እግሮቹን ምንጣፉ ላይ አኖረ። "ግድየለም እኔው መሄድ እችላለሁ" አለው። ብድግ ብሎ ቆመ። ብርጭቆውን ከእጁ ወደ መሬት ለቀቀውና ወደ ተዘጋጀው የቁማር መጫወቻ ጠረጴዛ አመራ። አጫዋቹ ራቅ ብሎ ተቀምጧል። የኮክቴል አስተናጋጅዋም ኒኖ የሚያሳያትን ምልክት ለመከታተል እንዲያመቻት ፊት ለፊቱ ቁጭ ብላለች።

ኒኖ በአረንጓዴ ወፍራም የሱፍ ጨርቅ የተሸፈነውን የመጫወቻ ጠረጴዛ አንኳኳና የመወራረጃ ገንዘብ መጠን የሚገልጹ ምልክቶች (ቺፕስ) እንዲመጡለት አዘዘ።

የውድድሩ ሀላፊ ከኪሱ ወረቀት አውጥቶ አንድ ገጽ ላይ ከጻፈ በኋላ ከብእር ጋር ከኒኖ ፊት አስቀመጠለት። "ያውልህ፣ ሚስተር ቫሌንቲ። እንደተለመደው የመጀመሪያህ አምስት ሺህ ብር" አለው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኒኖ በቀረበለት ጽሁፍ ግርጌ ሲፈርምለት የውድድሩ ሀላፊ ወረቀቷን መስዶ ከኪሱ ከተተና ጨዋታውን እንዲጀምር ለአጫዋቹ ምልክት ሰጠው ።

አጫዋቹ ጥቁርና ወርቅማ ቀለማት ያላቸው የባለመቶ ብር መወራረጃ ምልክቶች (ቺፕስ) ከማስቀመጫ ሳጥናቸው ውስጥ አውጥቶ ከፊቱ ደረደረ ። አምስት ሰኮንድ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ለኒኖ እያንዳንዳቸው አስር ባለመቶ ብር ቺፕስ የያዙ አምስት ሙሉ ክምሮች ከፊቱ ደረደረለት ።

በአረንጓዴው የጠረጴዛ ልባስ ሱፍ ላይ በነጭ የተሰመሩ ከመጫወቻ ካርታ ጥቂት ከፍ የሚሉ ስድስት ባለ አራት ማእዘኖች በያንዳንዱ ቁማርተኛ አኳያ አሉ ። ኒኖ በሶስቱ ባለ አራት ማእዘኖች ላይ አንዳንድ መወራረጃ አኖረ ። በለስ ሰጠውና የበላውን ከሰበሰበው በኋላ ወደጆኒ ዞር ብሎ ፣ ''እንዲህ ነው ምሽቱን የምንጀምረው ፤ አይደል ፣ ጆኒ?'' አለው ።

ጆኒ ፈገግ አለ ። ኒኖን ለመሰለ ቁማርተኛ ቁማር እየተጫወተ ሂሳቡን የሚገልጽ ማስታወሻ ላይ መፈረም የተለመደ አልነበረም ። ምናልባት ስለሰከረ ይረሳል ብለው ይሆናል ። ኒኖ ግን ሁሉንም ነገር ያስታውስ ነበር ።

በዚህ ሁኔታ ኒኖ ማሸነፉን ቀጠለ ። ከሶስተኛው ዙር በኋላም አሳላፊዋን ወጣት መጠጥ እንድታቀርብለት በጣቱ ምልክት ሲሰጣት የተለመደውን ዊስኪ አመጣችለት ።

''ቆንጂት ፣ ከጐኔ ቁጭ በይና መልካም እድል አምጪልኝ'' አላት ኒኖ ። ወጣቷ አስተናጋጅ ቆንጆ ብትሆንም ለጆኒ ግን የቀዘቀዘች ገንዘብ አሳዳጅ ሴተኛ አዳሪ ሆና ታየችው ። ለኒኖ ፈገግታ ታሳየው እንጂ ጥቁርና ወርቅማ ቀለም ያለውን የመወራረጃ ገንዘብ መጠን የሚያሳየውን ነገር በጉጉት ትመለከት ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኒኖ በምትኩ ሆና እንድትጥልለት ሲያደርግ ቆይቶ ለድካሚ አንዱን ባለመቶ ብር ዋጋ ያለው ማጫወቻ ከሰጣት በኋላ ያሰናበታትን ፥ ጆኒ ደግሞ መጠጥ እንድታመጣለት አዘዛት ። እሷም አይኗን በማቁለጭለጭ ፥ በአረማመዷም ሴስ በተሞላበት ሁኔታ ስትውረገረግ ፥ አጠገቧ ያለውን ነገር የምትገምጥ ይመስል ከንፈሯን አላቅቃ በስሪያ ወቅት ያለች እንስሳ መሰለች ። ነገሩ ግን የማስመሰል ነው እንጂ በእርግጥ ስሜቷ ተነክቶ አይደለም ። ጆኒ እግዚአ አለ ። እሱን የሚፈልጉት ሴቶች በብዛት እንደሷ ያረጋቸዋል ። ቢሰክር ኖሮ እሱን ወደ አልጋ ለመምራት መልካም ዘዴ ነበር ። እሱ ግን አልሰከረም። ይልቁንም ተዝናንቶ "አመሰግናለሁ ፥ እቴ" አለና ፈገግታ ብቻ አሳያት ። ምንም ዘዴ ቢቀየስበት ዛሬ አልሰራም ። ዛሬ ማታ ስሜቱ አልተቀሰቀሰም ።

ኒኖ ለመሄድ ፈልጎ ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ ለመነሳት ሲንገዳገድ የቁማሩ ሀላፊና አጫዋች ይጠብቁት ስለነበር ያዙት ። ቀና አድርገው ካነሱት በኋላ ወደ መኝታ ወሰዱት ።

መጠጥ አሳላፊዋ ወጣት እየረዳቻቸው ሁለት ሰዎች ኒኖን አልጋው ላይ ካጋደሙት በኋላ ልብሱን አውልቀው ሲያስተኙት ዋናው የቁማር ሀላፊም ኒኖ የበላውን መጫወቻ መጠን ቆጥሮ ማስታወሻ ያዘ ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ጆኒ ያስተውል ነበር ።

ጆኒ ይህን የመሰለ ሁኔታ ኒኖን ከጀመረው ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የቁማሩን ሀላፊ ጠየቀው ። ኒኖ ካሁን ቀደምም እንዲህ ያለ ህመም ተነስቶበት ሀኪም ቢጠሩለት ሁለተኛ እንዳይለምዳቸውና እንዲህ ሲሆን ወስደው እንዲያስተኙት እንዳስጠነቀቃቸው ለጆኒ ገለጠለት ። ኒኖ በዚያ ምሽት ቁማር ሶስት ሺ ብር በልቷል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጆኒ ሀኪም እንዲመጣ በጠየቀው መሰረት ዶክተር ጄልስ ሲ.ጋል መጣ ። የዶክተሩ የሀኪም አቋም ማጣት ፥ አለባበስና የህክምና መሳሪያዎቹን አያያዝ ጆኒን አላስደሰተውም ። እቃውን በስርአት ሸክፎ መያዝ እንዳለበት ነገረው ። ሀኪሙ ግን በመቆጣት ፋንታ ፥

"ልክ ነህ ፥" አለ ። "ይህ የህክምና ትምህርት ቤት ቦርሳ ሁሉንም ሰብስቦ እንዲይዝ ታስቦ የተሰራ ስለሆነ የተንዘላዘለ ነው ። ሲያዩት ሰዎች ይፈራሉ ። ሌላው ቢቀር የቦርሳው ቀለም ለ.ለወጥ ይገባል"

ዶክተር ጄልስ ኒኖ ከተኛበት ሄዶ ቦርሳውን እየከፈተ ጆኒን እንዲህ አለው ፥

"ስለላክልኝ ቼክ አመሰግናለሁ ። ያን ያህል አይገባኝም ነበር"

"እሱን ተወውና ስለኒኖ ንገረኝ ። ምን ሆኗል?"

ጄልስ የኒኖን ልብ ትርታ ፥ እና የደም ግፊት በፍጥነት ለካው ። መርፌ ከሻንጣው አውጥቶ ወጋው ። ኒኖ ባንቀላፋው ፊቱ ላይ ይታይ የነበረው ሰም የመሰለ ግርጡንቱ ጠፍቶ ደመ በፍጥነት መዘዋወር የጀመረ መሰለ ።

"ህመሙን በቀላሉ መረዳት የሚቻል ነው ። መጀመሪያ የመጣ ቀን መርምሬዋለሁ ። ወደ ሀኪም ቤት እንዲሄድ አድርጌ ነበር ። የስኳር በሽታ ይዞታል ። ከተጠነቀቀ መቆጣጠር ይቻላል ። ግን እሱ ችላ ይለዋል ። እስኪሞት ለ.ጠጣም ወስኗል ። ጉበቱም እየተጐዳች ናት ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንጐሉም ይቀጥላል ። አሁን ግን የስኳር በሽታ ባስከተለው ጊዜያዊ መደንዘዝ እእምሮው ታውኳል ። የአእምሮ ሀኪም ቤት እንድታስገቡት ነው የምሰጣችሁ ምክር" አለ ሀኪሙ ።

ጆኒ እፎይታ ተሰማው ። ኒኖ እራሱን ከጠበቀ የያዘው ሕመም አደገኛ አይደለም ። የሀኪሙም እምነት

t.me/OLDBOOKSPDF

ተመሳሳይ ቢሆንም ፥ ኒኖ ብሞትም ግድየለኝ ባይ ስለ ሆነ ፥ የአእምሮ ሀኪም ቤት መሄድ እንዳለበት ለጆኒ እያስረዳው ሳለ በሩ ተንኳኳ ።

ጆኒ በሩን ሲከፍት ሉሲ ማንቺኒ በሩ ላይ ቆማ ለች ። ጆኒ እቅፍ ውስጥ ገብታ ሳመችው ። ሁለቱም መነ ፋፈቃቸውን ተገላለጡ ።

ሉሲ መለወጪን ጆኒ ተግነዘበ ። ቀጠን ብላለች ። አለባበሷም ያማረ ፥ የጸጉርዋ አበጣጠርም የተስማማት ወጣት ሆናለች ። እንዲያውም እዚያው ቬጋስ በሚቆይ በት ወቅት አብራው እንድትቆይ ተመኘ ። ከቆንጆ ጋር መገናናት እውነተኛ ደስታ ይሰጣል ። ነገር ግን ርቆ ሳይሄድ የዶክተሩ ወዳጅ መሆኒ ትዝ አለው ። ስለዚህ ይህ ምኞት ተሰረዘ ። የወዳጅነት ፈገግታ ብቻ አሳያትና ፥

"በዚህ ውድቅት ኒኖ መኝታ ቤት ምን አመጣሽ?" አላት ።

ትከሻውን ጐሰመችውና ፥ "ኒኖ መታመሙንና ጁል ስም እዚህ መምጣቱን ሰማሁ ። ምናልባት መርዳት የምችለው ጉዳይ ይኖር እንደሆነ ብዬ መጣሁ ። ኒኖ በጎ ነው ፥ አይደል?"

"ተሽሎታል" ሲል ጆኒ መለሰላት ።

ጁልስ ሲጋል ሶፋው ላይ እጁን ዘርግቶ ቁጭ ካለ በት ሆኖ ፥

"እንዲያም አድርጐ መሻል የለ!" አለ ። "ይልቁ ንስ ሁላችንም ለጤንነቱ ጥንቃቄ እንዲያደርግ አበክረን እናስጠንቅቀው ። ሉሲ ኒኖ አንቺን ስለሚወድሽ ምናል ባት ይሰማሽ ይሆናል ። ጆኒም እውነተኛ ወዳጁ ከሆንክ ጥረት ማድረግ ይኖርብሀል ። አለበለዚያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የኒኖ ጉበት በአንድ የህክምና ትምህርት ቤት ውስጥ የብልሹ ጉበት ምሳሌ ሆኖ ለትርኢት እንደሚቀ ርብ አትጠራጠር"

t.me/OLDBOOKSPDF

የሀኪሙ ደፋር አነጋገር ጆኒን አበሳጨው። ለመሆኑ ማን አባቱ ነውና ነው እሱ እንዲህ የሚናገረው፥ ለማ ለት ፊልጮ ነበር ጆኒ። የኒኖ ድምጽ አቋረጠው እንጂ።

"በል እንጂ፥ የጥንቱ ጓዴ፥ የታለ የምጠጣው?" ኒኖ አልጋው ላይ እንደተቀመጠ። ለሉሲ ፈገግታ አሳያ ትና፥ "በይ፥ ቆንጂት፥ ወደ ጥንቱ ኒኖ ጠጋ በይ" አላት እጁን ዘርግቶ። ሉሲም አልጋው ማእዘን ላይ ቁጭ ብላ አቀፈችው። የሚያስገርመው ነገር፥ ኒኖ አሁን ሲያዩት ምንም ያመመው አይመስልም። ነገር ግን ጣቱን አፋጭቶ ጧ! የሚል ድምጽ አሰማና፥

"በል እንጂ፥ ጆኒ፥ የምጠጣው ስጠኝ። ጊዜው እኩ ለና ነው። የካርታ መጫወቻ ጠረጴዛዬስ የት ደረሰ?" አለ።

ጁልስ ከራሱ ብርጭቆ ላይ በረሾሙ ሳበና፥ "መጠጥ ልትጠጣ አትችልም። ሀኪምህ ከልክሏል" አለው።

ኒኖ ተናድዶ፥ "ሀኪሜ ይነፋ!" ካለ በኋላ፥ ለጨዋታ ያህል የውሸት ጸጸት በፊቱ ላይ ታየበት።

"ውይ! ጁልስ፥ አንተ ነህ እንዴ? ሀኪሜ አንተ ነህ! አንተን የጥንቱን ወዳጄን ማለቴ አይደለም። ጆኒ መጠጥ አምጣልኝ። አለበለዚያ እራሴ ተነስቼ እቀዳ ዋለሁ"

ጆኒ ትከሻውን ነቀነቀና ወደ መደርደሪያው አመራ። ጁልስም በቸልታ፥ "ይህ ሰው መጠጥ መውሰድ አይችልም ብያለሁ" አለ። ሀኪሙ ለምን እንዳናደደው ጆኒ አውቋል። የሀኪሙ ድምጽ ዘወትር ቀዘቀዝ ያለ ነው። ምንም አስደንጋጭ ሁኔታ ቢሆን ለዘብ ብሎ የሚናገር ዝግ ያለና ከቁጥጥር ውጭ ያልሆነ ድምጽ፥ ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም በቃላት ብቻ እንጂ ቸልተኛ በሚመስል፥ ተጽእኖ በሌለበት አነጋገር ነው። ይህን የመሰለው የሀኪሙ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታ ነው ጆኒን ያበሸቀውና መጠጡን ሊያመጣ እንዲ
መስን ያደረገው ። መጠጡን ለኒኖ ከማቀበሉ በፊት ጆኒ
ወደ ሀኪሙ ዞር ብሎ ፥

"ይህችን ብቻ ፥ አይገድለውም አይደል?" አለው ።

"አይገድለውም" አለ ሀኪሙ በለዘበታ ። ሉሲ
በስጋት ጁልስን ተመልከታው አንድ ነገር ለማለት
ከጀመረች በኋላ መልሳ ዝም አለች ። በዚያ ወቅት ኒኖ
ዊስኪውን ወደ ጉሮሮው ላከው ።

ይህን ውርጋጥ ሀኪም ማንነታቸውን ስላሳዩት
ጆኒ ደስ ብሎት ኒኖን ፈገግታ አሳየው ። ከመቅጽበት
ኒኖ የትንፋሽ እጥረት ገጥሞት ፊቱ ሰማያዊ ቀለም
ታየበት ። ለመተንፈስ አልቻለም ፥ አየር መሳብም አቃ
ተው ። ሰውነቱ ከውሀ ውስጥ እንደወጣ አሳ ይወራጭ
ጀመር ። አይኑ ተጉለጉለ ወጣ ። ጁልስ ጆኒና ሉሲ
ከቆሙበት ትይዩ ሆኖ የኒኖን እንገት ይዞ ቀጥ ከአደረ
ገው በኋላ ከትከሻውና እንገቱ መጋጠሚያ ላይ መርፌ
ወጋው ። ኒኖ ተገለፍልፎ አልጋው ላይ ተዘረጋና እንቅ
ልፍ ወሰደው ።

ጆኒ ፥ ሉሲ እና ጁልስ ወደ እንግዳ ቤቱ ሄደው አንድ
የቡና ጠረጴዛ ከበው ቁጭ አሉ ። ሉሲ ሰማያዊውን
የሆቴሉን ስልክ አንስታ ምግብና ቡና እንዲመጣላቸው
አዘዘች ። ጆኒም ወደ መደርደሪያው ሄዶ መጠጥ ለራሱ
ቀላቀለና ሀኪሙን እንዲህ ሲል ጠየቀው ፥

"ለመሆኑ ፥ ኒኖ ያን መጠጥ ከጠጣ በኋላ እንደዚያ
ያለ ሁኔታ ይደርስበት እንደነበር አውቀህ ኖሯል?"

"እንዴታ!"

"ታዲያ ለምን አላስጠነቀቅከኝም?"

"አስጠንቅቄሀለሁ"

"በትክክል አላስጠነቀቅከኝም" አለ ጆኒ በቀዘ
ቀዘ ቁጣ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ድንቄም ሀኪም! ጨርሶ ደንታ ቢስ ነህ። ቅድም ስለ ኒኖ ስታወራልኝ እንኳን 'እብዶች ሀኪም ቤት መግባት አለበት' አልክ። የአእምሮ መታወክ የደረሰ ባቸው ሰዎች መታከሚያ ቤት ብለህ እንኳን ለዘብ አድርገህ ለመናገር አልፈለግክም። አጉል ነገር ሰዎች ላይ መለጠፍ ትወዳለህ"

ሉሲ አቀርቅራለች። ጁልስ በጆኒ ብሽቀት ፈገግ ታውን አላቋረጠም።

"ለኒኖ መጠጥ ከመስጠት የሚያግድህ ምንም ነገር አልነበረም። የኔን ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ የማትቀበል መሆንህን ለማሳየት ትሻ ነበር። ከዚያ የገሮሮህ ሀመም በኋላ የግል ሀኪምህ እንድሆን የጠየቅከኝ ጊዜ ታስታውሳለህ? እምቢ ያልኩህ ልንግባባ ስለማንችል ነው። ሀኪም እራሱን አምላክ አድርጎ ያስባል። የዘመናዊ ሀብረተሰብም ነፍስ አባት ነው። ያ ነው ወሮታው። አንተ ግን እንደዚያ ሆነህ አታስተናግደኝም። እኔ ላንተ ታዛዥ አምላክህ ነበር የምሆነው፣ እንደነዚያ የሆሊውድ ሀኪሞቻችሁ። ለመሆኑ እነዚያን ሰዎች ከየት ነው ያገኘሀቸው! እግዚአ! ለመሆኑ ምንም ነገር አያውቁም? ለምንም ነገር ደንታ የላቸው? ኒኖ ላይ የሚደርስበትን ማወቅ አለባቸው። ነገር ግን እነሱ በዚያው እንዲቀጥል ጊዜያዊ ማስታገሻ ሀክምና ብቻ ነበር የሚያደርጉለት። ያን የሀር ልብሳቸውን ይለብሱና እናንተ የሲኒማ ሀያላን በመሆናቸው ቂጣችሁን ይልሳሉ። እናንተም ከነሱ የተሻለ ሀኪም ያለ አልመሰላችሁም። ርህራሄ ሊኖራቸው ይገባል፣ አይደል? ግን እናንተ ብትሞቱ ወይ ብትኖሩ ደንታ የላቸውም። ነገር ግን ትንሿ የምወዳት ስራዬ ባትወደድልኝም ሰዎች በህይወት እንዲቆዩ ትፈልጋለች። ለኒኖ ያንን መጠጥ ስትሰጠው ዝም ያልኩህ የሚያርስበትን እንድታየው ብዬ ነው" አለና ጁልስ፣

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁንም ድምጹ ጸጥ ያለና ስሜት ያልፈነቀለው እንደ መሰለ ወደ ጆኒ ተጠጋ ።

"ያንተ ጓደኛ መዳረሻው ጫፍ ላይ ነው ፥ ይገባሀል ? ያለ ስነልቡናዊ ህክምናና ጥብቅ የህክምና ክትትል ምንም የመትረፍ እድል አይኖረውም ። የደም ብዛቱ ፥ የስኳር በሽታው እና መጥፎ አመሉ በቅርቡ የአንጐል ውስጥ መድማት ያስከትሉበታል ። አንጐሉም ይፈርሳል ። ግልጽ ሆነልህ? እውነት ነው ፥ የእብዶች ቤት ብያለሁ ። ምን እንደሚያስፈልገው እንዲገባህ ብዬ ነው ። አለበለዚያ አንተም ተገቢውን እርምጃ አትወስድም ። ሁሉን ነገር በትክክል አስረዳሀለሁ ። የአብሮ አደግህን ህይወት የምታተርፈው በቁርጠኝነት የምነገርህን ስትፈጽም ነው ። አለበለዚያ ግን ካሁኑ ደህና ሰንብት ብለህ ሳመው።"

ሉሲ ይህን ጊዜ አጉረመረመች ። "ጁልስ ፥ ፍቅሬ ፥ እባክህ እንደዚህ ሀይለኛ አትሁን ፤ ምክርህን ብቻ ለግሰው " አለችው ።

ጁልስ ተነሳና ቆመ ። የወትሮ እርጋታው ጠፍቷል ፥ ጆኒ ፎንቴንም በእርካታ ተመለከተው ። የጁልስ ድምጽ ስልቱ ጠፍቶበታል ።

"ለመሆኑ ይህን በመሰለ ሁኔታ ላይ እንዳንተ ያሉ ሰዎችን ሳነጋግር የመጀመሪያው ይመስልሀል? በየቀኑ የማደርገው ነበር ። ሉሲ ሀይለኛ አትሁን ትለኛለች ። ነገር ግን እሷ የምትናገረውን አታውቅም ። ታውቃለህ ፥ ሰዎችን እንዲህ እላቸው ነበር ፥ 'ከመጠን በላይ አትብሉ ትሞታላችሁ ፤ ከመጠን በላይ አትጠጡ ፥ አለዚያ ትሞታላችሁ ፤ ብዙ ሲጋራ አታጢሱ ፥ አለበለዚያ ትሞታላችሁ' እንዲህ ሰል የሚሰማኝ የለም ። ለምን እንደሆነ ታውቃለህ! ነገ ትሞታለህ ብዬ አልተናገርኩማ! እንግዲህ ኒኖ ቫን ሊሞት እንደሚችል ልነግርህ እችላለሁ"

t.me/OLDBOOKSPDF

ጁልስ ወደ መጠጥ መደርደሪያው ሄዶ ለራሱ ሌላ መጠጥ ቀላቀለና ፥ "አሁንስ ፥ ጆኒ! ኒኖን የአእምሮ ሀኪም ቤት እንዲገባ ታደርገዋለህ?" አለው ።

ጆኒ ፎንቴን ፥ "እኔ እንጃ" ሲል መለሰለት ፥

ጁልስ መጠጡን ጅው አደርጉ ጠጣና ደግሞ ቀዳ ።

"ታውቃለህ ፥ የሚደንቀው ነገር ፥ በሲጋራ ማጤስ ብዛት ፥ በመጠጥ ብዛት ፥ ሌላ ቀርቶ በምግብ ብዛት እራስህን መግደል ትችላለህ ። ያሁሉ ተቀባይነት አለው ። በሀክምና የምናውቀው ፥ ራስህን መግደል የማትችለው በግብረ ስጋ ብዛት ብቻ ነው ። የሚከለከለውና እንቅፋት የሚደነቀርበት ግን እሱው ነው" አለና መጠጡን እስኪጨርስ ንግግሩን ከአቋረጠ በኋላ ቀጠለ ፥

"እሱም ቢሆን ለሴቶች ችግር ነው ። ተጨማሪ ልጆች መውለድ የማይገባቸው ሴቶች አጋጥመውኛል ። 'እደግኛ ነው ፥ አታርግዙ ፥ ልትሙቱ ትችላላችሁ' እላቸዋለሁ ። ከወር በኋላ ግን ፊታቸው ፈክቶ ብቅ ይሉና ፥ 'ዶክተር አርግዣለሁ መሰለኝ' ይላሉ ። አሁንም 'እደግኛክ ነው' ብዬ አበክሬ እነግራቸዋለሁ ። እነሱም ፈገግ ይሉና ፥ 'ታዲያኮ እኔና ባሌ አጥባቂ ካቶሊኮች ነን ፥' ይሉኛል"

በሩ ተንኳኳ ። ሉሲ ያዘዘችው ምግብና ቡና በተሸከርካሪ መጣላቸው ። ምግቡን ያመጡትን ኢሳላፊ ሴቶች አሰናብተው ትኩስ ሳንድዊቻቸውን በሉና ቡናቸውን ጠጡ ።

ጆኒ ወደ ኋላው ለጠጥ አለና ሲጋራውን ሰኩሶ ፥

"አሺ ፥ ህይወት ታተርፋለህ ። ታዲያ እንዴት ሾን አስወራጅ ልትሆን ቻልክ?" ሲል ጠየቀው ።

ሉሲ ጣልቃ ገባችና ፥ "የተቸገሩ ሴቶችን ፥ በተለይም እርዳታ ካልተደረገላቸው እራሳቸውን ለመግደል

t.me/OLDBOOKSPDF

ወይም ሌላ አስከፊ ተግባር ለመፈጸም ወደኋላ የማይ
ሉትን ልጃገረዶች ለመርዳት ብሎ ነው'' አለች ።

ጁልስ ፈገግ አለና በረኸሙ ተነፈሰ ። ''እንደዚያም
ቀላል አይደለም ነገሩ ። በመጨረሻ የቀዶ ጥገና ሀኪም
ሆንኩ ። ነገር ግን ይኸው ችሎታዬ አጉል ፍርሀት
አሳደረብኝ ። አንዱን ምስኪን ሆዱን እከፍትና መሞቱን
እረዳለሁ ። ቀዶ ጥገና ካደረኩለት በኋላ የያዘው ካንሰር
በሽታ ተመልሶ የሚመጣበትና ሟች መሆኑን ባውቅም
የቆጡን የባጡን ቀባጥሬ በፈገግታ እሸኘዋለሁ ። አንደ
ምስኪን ሴት ትመጣለች ። አንዱን ጡት እቆርጠዋለሁ ።
ከአመት በኋላ ተመልሳ ትመጣለች ፤ ሌላውንም እቆር
ጠዋለሁ ። በሚቀጥለው አመትም ሆድቃዋን የሚሎንና
የፓፓያ ፍሬ እንደሚቀፈፍ ቀፍፌ አወጣዋለሁ ። ከዚያ
ሁለ ስቃይ በኋላ መሞት አይቀርላትም ። በዚህ ጊዜ
ባሎች እየደወሉ 'ምርመራው ምን ያሳያል? ምን ተገኘ?'
እያሉ ይጠይቁኛል ። ስለዚህ ይህን ለመሰለው ጉዳይ
ሰልክ የምትመልስ ተጨማሪ ጸሀፊ ቀጠርኩ ። ከዚያ
በኋላ በሽተኛዬን የማያት ለምርመራ ዝግጁ መሆኗ
ሲረጋገጥ ብቻ ነበር ። በጣም ስራ ይበዛብኝ ስለነበር
ከበሽተኛዋ ጋር የማሳልፈው ሰአት በተቻለ መጠን
አነስተኛ ሆነ ። በመጨረሻም ባልየው ለሁለት ደቂቃ
ምች እንዲያነጋግረኝ እፈቅድለታለሁ ። 'መዳረሻው
ነው ።' ብዬ እነግረዋለሁ ። ይህን ቃል አይሰማኝም ።
ምን ማለት እንደሆነ ያውቀዋል ። ነገር ግን አያዳም
ጠኝም ። ጮክ ብዬ ስነግረው ፣ 'ምን ማለትህ ነው?' ብሎ
ይጠይቀኛል ። ኤድያ! ከዚያ በኋላ ጽንስ የማስወረድ ስራ
ጀመርኩ ። ጥሩና ቀላል ስራ ነው ። ሁሉም ሰው ደስ ይለ
ዋል ። ሰሀኖችን አጣጥቦ የእቃ ማጠቢያውን የማጽዳት
ያህል ቀላል ነበር ። ስራውን ወደድኩት ። ምክንያቱም
የሁለት ወር ጽንስ ሰው ነው ብዬ ስለማልገምት የህሊና

t.me/OLDBOOKSPDF

አጸትም አልነበረኝም ። ወጣት ልጃገረዶችንና ችግር ያጋ ጠማቸውንም ባለትዳሮች እየረዳሁ ብዙ ገንዘብ በማግ ኘት ግንባር ቀደም ሆንኩ ። ስያዝ ከሀዲ ሆኜ ህግ ፊት መቅረቤ ተሰማኝ ። ቢሆንም እድለኛ ነበርኩ ። አንድ ወዳጅ አግኝቼ ጎትቶ አወጣኝ ። ትልልቆቹ ሀኪም ቤቶች ግን ቀዶ ጥገና ላይ እንደሰማራ አልፈቀዱልኝም ። ስለዚህ ወደዚህ መጣሁ ። አሁንም እንደድሮው ሰሚ የማያገኝ በጐ ምክር መለገሴን አልተውኩም”

“እኔስ ምክርህን ችላ አላልኩትም ። እንዲያውም እያሰብኩበት ነው” አለ ጆኒ ፎንቴን ።

በመጨረሻ ሉሲ የጨዋታውን ርእስ ቀየረችው ። “ጆኒ ፣ ቬጋስ ውስጥ ምን ታደርጋለህ? ከታላቁ የሆሊ ዉድ የሲኒማ ሰራ ውጥረት ለመላቀቅ ብለህ ነው ወይስ ለስራ መጥተህ ነው?” ስትል ጠየቀችው ።

ጆኒ እራሱን በአሉታ ከነቀነቀ በኋላ ፣ “ማይክ ኮር ሌዎኔ ሊያነጋግረኝ ይፈልጋል ። ዛሬ ማታ ከሄገን ጋር ወደዚህ በአውሮፕላን ይመጣል ። አንቺንም እንደሚያ ነጋግሩሽ ቶም ነግሮኛል ። ለመሆኑ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ?” አላት ።

ሉሲ ጉዳዩን አለማወቋን ለመግለጽ እራሷን ነቀነ ቀች ።

“ሁላችንም ነገ ማታ እራት አብረን እንበላለን” አለች ። “ፍሬዲም ይኖራል ። እንደገመትኩት ፣ የሚመ ጡት ከሆቴሉ ጋር ለተያያዘ ጉዳይ ነው ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቁማር ቤቱ እየከሰረ ነው ። ሚካኤል ጉዳዩን እንዲያጣራ ዶኑ ይፈልግ ይሆናል”

“ሚካኤል ፊቱ በቀዶ ጥገና ተስተካክሎለታል የሚል ወሬ ሰምቻለሁ” አለ ጆኒ ።

ሉሲ ሳቀችና ፣ “ኬይ አግባብታው ይሆናል” አለች ። “ሲጋቡ ሊያስተካክለው አልፈለገም ። ለምን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሆነ ይደንቀኛል ። ከማስጠላቱም በላይ አፍንጫው ፍሳሽ ያንጠባጥብ ነበር ። ቀደም ብሎ ሲያስተካክለው ይገባ ነበር ። ጁልስም ለቀዶ ጥገናው ተጠርቶ አማካሪና ተመልካች አድርገውት ነበር”

ጆኒ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። “አዬ ነኝ ጁልስን የጠቆምኩዋቸው” አላት ።

“ነው እንዴ? ያም ሆነ ይህ ፣ ማይክ ለጁልስ አንድ ነገር ሊያደርግለት ይፈልጋል ። በነገው እራት ላይ እኛም እንድንገኝ የፈለገው ለዚህ ነው” አለች ።

ጁልስ አሰበና ፣ “ማይክ ማንንም አላመነም” አለ ። “በቀዶ ጥገናው ወቅት እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገውን እንድከታተል አስጠንቅቆኝ ነበር ። ነገር ግን ማንም ብቁ ሀኪም ቢሰራው የሚችለው ቀላል ጥገና ነበር”

ከመኝታ ቤት በኩል ድምጽ ተሰማ ። መጋረጃውን ገለጥ ሲያደርጉት ኒኖ እንደገና ነቅቷል ። ጆኒ ሄዶ አልጋው ላይ ተቀመጠ ። ጁልስ እና ሉሲ ካልጋው ግርጌ ቁጭ አሉ ። ኒኖ የነጻከመ ፈገግታ አሳያቸው ።

“በቃ አጉል ጮሌ መሆኑን እተወዋለሁ ። ሁሉም ነገር አስጠልቶኛል ። ጆኒ ታስታውሳለህ? ከአንድ አመት በፊት ሁለት ቆንጆዎች ፓልም ስፕሪንግ ወስደን ሳለ የሆነውን? በሆነው ነገር ቅናት እንዳልተሰማኝ እምልል ሀለሁ ። ደስ ነበር ያለኝ ። ታምነኛለህ አይደል ፣ ጆኒ?” አለ ኒኖ ።

ጆኒ በመስማማት “አዎን ኒኖ ፣ አምንሀለሁ” አለው ።

ሉሲና ጁልስ እርስ በርሳቸው ተያዩ ። ስለጆኒ ፍንቲን ከሰሙትና ከሚያውቁት አንጻር ጆኒ የኒኖን ወዳጅ ይቀማበታል ብለው ለማመን አቃታቸው ። ታዲያ ለምንድነው አመት ካለፈ በኋላ ኒኖ አልቀናውም

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ የሚያወራው፣ 'ለካስ ኒኖ እስኪሞት ለመጣት የወ
ሰነው ወዳጁ እሱን ጥላው ከጆኒ ፎንቴን ጋር ስለሄ
ደችበት ነው' የሚል ሀሳብ በሉሲና ጁልስ አእምሮ
ብልጭ አለ ። ጁልስ እንደገና ኒኖን መረመረው ።

"ዛሬ ማታ አንዲት ነርስ እንድትጠብቅህ አደር
ጋለሁ ። በእርግጥ ለጥቂት ቀናት አልጋህ ላይ መቆየት
ይኖርብሀል ። ቀልድ አይደለም" አለው ዶክተር ጁልስ ።

ኒኖ ፈገግ አለና ፣ "እሺ ዶክተር ፣ ብቻ ነርሷ ቆንጆ
ልጅ እንዳትሆን" አለው ።

ጁልስ ነርሷን በስልክ ጠርቷት ሉሲና እሱ አብረው
ወጡ ። ጆኒ ነርሷ እስክትመጣ ቁጭ ብሎ ጠበቀ ። ኒኖ
ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው ። ድካም ፊቱ ላይ ይታያል ።
ጆኒ ኒኖ ቅድም ከአመት በፊት ያደረጉትን አስታውሶ
'ቅናት አልተሰማኝም' ሲል የተናገረውን ማሰላሰል
ጀመረ ። ኒኖ ቅናት ያድርበታል ብሎ ከቶውንም አልገ
መተም ነበር ።

ከአንድ አመት በፊት ጆኒ ፎንቴን ተሟልቶ ባሸበ
ረቀው የሲኒማ ኩባንያው ቢሮ ቁጭ ብሎ በህይወቱ
ተሰምቶት የማያውቅ ምሬት ተሰምቶታል ። የሚያስ
ገርመው ግን እሱና ኒኖ በከዋክብት ተዋናይነት የተካፈ
ሉበት የመጀመሪያው ፊልሙ ብር እንዳፈር አስገኝቶ
ለታል ። ሁሉም ነገር እንደታሰበው ተሳክቷል ። ሁሉም
ሰው የበኩሉን ተግባር በሚገባ አከናውኗል ። ፊልሙ
የፈጀው ዋጋ ከታቀደው ያነሰ ነበር ። ሁሉም ተሳታፊ
ብዙ ገንዘብ ያገኙበታል ። ጃክ ዎልትዝ በቁጭትና
በቅናት አሯል ። ጆኒ በአሁኑ ወቅት ሁለት ፊልሞች
እያሰራ ነው ። አንዱን እራሱ ሌላውን ደግሞ ኒኖ ኮከብ
ሆነው ይሰሩበታል ። ኒኖ በፊልሙ ላይ እንደነዚያ
ሴቶች በጡቶቻቸው መሀከል እንደሚያቅፏቸው ማራኪና

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋና ተፈቃሪ ልጆች ሆኖ የሰራው ፊልም ተዋጥቶለ ታል ። የነካው ነገር ሁሉ ገንዘብ ያፈራል ። ገንዘብ እንደ አሸን ፈላ ። የጡት አባትም የራሱን ድርሻ በባንክ በኩል ማግኘቱ ጆኒን አስደስቶታል ። የጡት አባቱ የጣለበትን እምነት ሊያስመሰክር ችሏል ። ዛሬ ግን ይህ ሁሉ ደስታ አላስገኘለትም ።

ዛሬ የተሳካለት እራሱን የቻለ የፊልም አዘጋጅ በመሆኑ ብዙ ሀይል ፥ ምናልባትም ያኔ ዘፋኝ በነበረበት ወቅት ከነበረው ይበልጥ ሀይል አለው ። ቆንጆጅት እንደ ድሮው ይከቡታል ። የዛሬው ከበባቸው ግን ከስራ ግንኙነት አንጻር ጭምር ነው ። ጆኒ የራሱ አውሮፕላን አለው ። የአንድ ንግድ ስራ ባለቤት በመሆኑ ተዋንያን የማያገኙትን ልዩ የግብር ቅነሳ ጥቅም እያገኘ የበለጠ ደልቃቃ ህይወት ይመራል ። ታዲያ ምንድነው የሚያስጨንቀው?

ሰላም የነሳው ምን እንደሆነ ያውቃል ። ጭንቅላቱን ከፊት በኩል ያመዋል ። የአፍንጫው ማስተላለፊያ ቧንቧ ተጐድቷል ፥ ጉሮሮውንም ያሳክከዋል ። ጉሮሮውን ለማከክና ከሚበላው ነገር ለማስታገስ የሚያስችለው መዝፈን ብቻ ነው ። እሱ ግን ዘፈን ለመሞከር እንኳን አልደፈረም ። ጆልሰን ጠርቶ መቼ መዝፈን እንደሚችል ጠይቆት ነበር ። ጆልሰም ዘፈን ባሰኘው ጊዜ መዝፈን እንደሚችል ነግሮታል ። እንዳለው ሞክሮ ድምጹ ስለ ሻከረበት ተስፋ ቆርጦ ትቶታል ። ዘፈን በሞከረም በማ ግስቱ ጉሮሮውን እባጭ ሳይወገድለት በፊት ከነበረው የባሰ አሞታል ። ስለዚህ መዝፈን ፈራ ፥ ምናልባትም ድምጼን ለመጨረሻ ጊዜ አጣዋለሁ ወይም አበላሸዋለሁ ብሎ ፈርቶ ነበር ።

ታዲያ መዝፈን ካልቻለ ሌሎቹ ነገሮች ምናባታቸው ያደርጉለታል? ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ዋጋ ቢሶች ናቸው ። በእርግጥ የሚያውቀው አንድ ነገር ዘፈን ብቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ምናልባትም ስለ እራሱ ዘፈን ከማንም ሰው ይበልጥ የሚያውቀው እሱ እራሱ ነው ። ያን ያህል ነበር ችሎታው ። አሁን ሲያስበው እነዚያ ያለፉት አመታት እውነተኛ ባለሙያ አድርገውት ነበር ። ማንም ሰው ይህ ትክክል ነው ፣ ወይም ይህ አይደለም ብሎ ሊነግረው አይችልም ነበር ። ማንንም መጠየቅም አላስፈለገውም ። እራሱ ያውቅ ነበር ። ምን አይነት መባከን ፣ ከቶውን ምን አይነት ከንቱነት!

እለቱ አርብ ስለነበር ፍጻሜ ሳምንቱን ከመጀመሪያዋ ሚስቱ ከቨርጂኒያና ከልጆቹ ጋር ለማሳለፍ ወሰነ ። ወደ ነሱ ዘንድ የሚመጣ መሆኑን ደውሎ ነገራት ። እንደ እውነቱ ከሆነ እምቢ ማለት የምትችልበት እድልም ሊሰጣት ነበር ። እሷ ግን ከተፋቱ ጀምሮ እምቢ አትምጣ ብላው አታውቅም ። ምክንያቱም ሴት ልጆቿና አባታቸው መገናኘት የሚችሉበትን እድል መዝጋት አትሻም ። 'ምን ያለች ሴት ናት' ብሎ ጆኒ አሰበ ። በቨርጂኒያ የመጣ እድለኛ ነበር ። ምንም እንኳን ከማናቸውም ከሚያውቃቸው ሴቶች ይበልጥ ለሷ ደንታ እንዳለው ቢገነዘብም ሁለቱ የፈቃደ ስጋ ህይወት ለመምራት እንደማይቻላቸው ያውቃል ። ምናልባት ሁለቱም ስድሳ አምስት አመት ሲሆናቸው አብረው ከሁሉም ነገር ታቅበው ጡረተኞች ይሆናሉ ።

ነገር ግን እዚያ ሲደርስ እውነተኛ ሀሳቦቹን ብትንትናቸውን አወጣቸው ። ቨርጂኒያ ትንሽ ትነጫነጫ ለች ። ሁለቱ ልጆቹ ደግሞ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ሴቶች ጓደኞቻቸው ወደ አንድ የከብት ርቢ ስፍራ ወስደው ፈረስ ሊያስጋልቧቸው ቃል ስለገቡላቸው ያባታቸውን መምጣት እንደወትሮው በደስታ አልተቀበሉትም ።

ቨርጂንያ ልጆቹን ወዳሰቡበት እንዲሄዱ እንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታሰናብታቸው ነገራትና በፈገግታ ሳማቸው ። በሚገባ ተረድቷቸዋል ። ማን ልጅ ነው ሲፈልገው ብቻ ለሚጐበኘው ነጭናጫ አባት ብሎ የፈረሰ ግልቢያ ጊዜውን መስዋእት የሚያደርግ?

"እኔም ትንሽ እዚህ እየጠጣሁ ልቆይና እሄዳለሁ" አላት ።

"እሺ" አለች ቨርጂኒያ ።

እሷም አልፎ አልፎም ቢሆን መጥፎ ቀን ያጋጥማታል ። ይህን የመሰለ ኑሮ ለሷ ቀላል አይደለም ።

በርከት አድርጎ ሲጠጣ ተመለከተችው ።

"ለምኑ ነው እራስህን እያጽናናኸው ያለኸው?" አለችው ። "ሁሉም ነገር ተሳክቶልሀል ። እንዲህ የመሰለ ታላቅ የንግድ ስራ ብቃት ይኖርሀል ብዬ አልገመትኩም ነበር"

ጆኒ በፈገግታ ፥ "እስከዚህም ከባድ አይደለም" አላት ። ይህን ሲላትም ምን እንደሚያነጫንጫት እያሰበ ነበር ። ሴቶችን ተረድቷቸዋል ። ቨርጂኒያ ዛሬ እንዲህ በስጨት ያለችው ነገሮች እሱ በፈለጋቸው መንገድ መሄዳቸውን በመገንዘቧ እንደሆነ ገብቶታል ። ሴቶች ወንዶቻቸውን በጣም ሲሳካላቸው አይወዱም ፥ ያበሳጫቸዋል ። በፍቅር ፥ በወሲባዊ ግንኙነት ፥ እና በጋብቻ ማሰሪያ በቁጥጥር ያዋሉት ወንድ የተሻለ ስኬታማ ህይወት ሲገጥመው ተጽእኖአቸው አጠራጣሪ ይሆን ባቸዋል ። ስለዚህ የራሱን ምሬት በመንገር ሊያዝናናት ፈለገ ።

"መዝፈን እስካልቻልኩ ድረስ ምኑስ ምን ልዩ ነት ያመጣል?" አላት ።

የቨርጂኒያ አንጋፈጥ የብሽቀት ነበር ።

'ውይ ጆኒ ፥ ከእንግዲህ ሀጻን አይደለህ ። እድሜህም ከሰላሳ አምስት በላይ ነው ። ስለዚያ የመዝፈን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር ለምን ዘወትር ታስባለህ? ይልቁንም ፊልም አዘጋጅነት የበለጠ ታገኛለህ" አለችው ።

ጆኒ 'ምን ማለቷ ነው' በሚል ተመለከታትና ፣ "እኔ ዘፋኝ ነኝ ። መዝፈን እወዳለሁ ። ከማርጀት ጋር ምን ግንኙነት አለው?" ሲል ጠየቃት ።

ቨርጂንያ ትእግስት አጣች ።

"ያም ሆነ ይህ እኔ ዘፈንህን ወድጀውም አላውቅ ። አሁን ፊልም መስራት ስለምትችል ልትዘፍን አለመቻልህ ያስደስተኛል"

"የመጨረሻ አስቀያሚ አነጋገር ነው የተናገርሽው" አላት በቁጣ እየተንቀጠቀጠ ። ቨርጂኒያ እንዴት እንዲህ ያለ ስሜት ይኖራታል? እንዴትስ እንደዚህ ትጠላዋለች?

ቨርጂኒያ የስሜቱ መነካት ፈገግ አስባላት ። እሷ ላይ መቆጣቱ ሊሆን የማይገባው ነገር ስለሆነባት ፣

"ለመሆኑ በዘፈንህ ምክንያት እነዚያ ሴቶች ሲያሳድዱህ ምን ይሰማኝ ነበር ይመስልሀል? ወንዶች እንዲ ከተሉኝ ተነስቼ እርቃኔን መንገድ ላይ ብወጣ ምን ይሰማህል? ያ ነበር ያንተ ዘፈን ለኔ ። ስለዚህ ድምጽህ ተበላሽቶ መዝፈን እንድታቆም እመኝ ነበር ። ነገር ግን ይህን እመኝ የነበረው ከመፋታታችን በፊት ነበር"

ጆኒ መጠጡን ጨረሰ ። "ምንም ነገር አይገባሽም። ምንም ነገር!" አላት ። ወደ ማድቤት ሄዶ ከዚያ በሚገኘው ስልክ ለኒኖ ደወለ ።

እሱና ኒኖ ፍጻሜ ሰምንቱ ላይ ወደ ፓልም ስፕሪንግ እንዲሄዱ አንዷን ጆኒ የሚፈልጋትን ወጣት ኒኖ እንዲደውልላት የስልክ ቁጥር ሰጠው ።

"ላንተም ወዳጅ ታገኝልሀለች ። ካንተ ዘንድ በአንድ ሰአት ውስጥ እደርሳለሁ" አለው ።

ጆኒ ፎንቴን ሲሄድ ቨርጂኒያ ቅዝቅዝ ብላ ተሰናበተችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምንም ደንታ አልነበረውም ። ከሷ ጋር ከተጣላባቸው በጣም ጥቂት ጊዜዎች አንዱ ነበር ። ገደል ትግባ! በሳ ምንቱ መጨረሻ ከሷ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ይቀርና በላዩ ላይ የተጠራቀመውን መርዝ ያጠራዋል ።

በእርግጥም የፓልም ስፕሪንግ ሽርሽር አስደሳች ሆነ ። ጆኒ በዚያ ቦታ የራሱ ቤት ነበረው ። ሁለቱ ሴቶች ብዙ መጫወት የሚመኙ ፣ ውለታ ለመጠየቅም ገና ጮሌነት ያልተላበሱ ልጅ እግሮች ነበሩ ። እራት እስኪ ደርስ ጥቂት ሰዎች መጥተው አጅበዋቸው ነበር ። ኒኖ የራሱን ወዳጅ ይዟት ለእራት ለመዘጋጀት እና ምሽቱ ደርሶ የበለጠ እስኪወጣላቸው መዳረሻ ፍቅር ለመለዋ ወጥ ወደ ክፍሉ አብረው አመሩ ። ጆኒ ግን አላሰኘውም ። ቲና የተሰኘችውን አጠር ያለች ውብ ወዳጁን መታጠቢያ ቤት ሄዳ እንድትታጠብ ላካት ። ወትሮም ቢሆን ከሸርጂ ኒያ ጋር ከተጣላ በኋላ ከሴት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም አይሆንለትም ።

ፒያኖ ካለበት ከመስታወት ግድግዳ ከተሰራው መዝናኛ ክፍል ገባ ። ድሮ ይዘፍን በነበረበት ወቅት ለመሳቅና አንዳንዴም ያጋጣሚ ድምጽ ለመቅሰም ፒያ ኖውን ያተረማምስ ነበር ። ቁጭ ብሎ ትንሽ ፒያኖውን አስጮኸ ። ውል ያለው ዘፈን ሳይሆን ፣ ያንጐራጉር ጀመር ። እሱ ሳያውቀው ቲና ከሳሎኑ ገብታ መጠጥ ቀላቅላለት ከጐኑ ቁጭ አለች ። ትንሽ ዜማዎችን ሲጫ ወት እሷም አብራው አንጐራጐረች ። እዚያው ፒያኖ አጠገብ እንደተቀመጠች ጥቂት ኀላውን ሊታጠብ ሄደ ። መታጠቢያ ቤት ሆኖ ንግግር የመሰሉ አጫጭር ዜማዎ ችን አንጐራጐረ ። ልብሱን ለበሰና ተመለሰ ። ቲና አሁ ንም ብቻዋን ነች ። ኒኖ ይኸኔ ከፍቅር ወይ ከመጠጥ ከሁለቱ ባንዱ እየተደሰተ ነው ።

ቲና የመዋኛ ኩሬው አካባቢ ስትንሸራሸር ጆኒ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደገና ፒያኖው ጋ ቁጭ አለ ። ከድሮ ዘፈኖቹ አንዱን መዝፈን ጀመረ ። ጉሮሮው ምንም አላቃጠለውም ። ድምጹ እየቀነሰ ቢሆንም በደንብ ቀጠለ ። የመዋኛውን ስፋራ ተመለከተ ። ቲና አሁንም ውጭ እየተዝናናች ናት ። የመስታወቱ በር ዝግ ስለሆነ ልትሰማው አትችልም ። እሱም ቢሆን ፥ ለምን እንደሆነ እንጃ ፥ ሲዘፍን ሰው እንዲሰማው አልፈለገም ። ከድሮ ዘፈኖቹ የሚወደውን አንዱን መዝፈን ጀመረ ። ልክ ለህዝብ እንደሚዘፍነው አድርጐ ተዝናንቶ እየዘፈነ የጉሮሮው ህመም ይነሳበት እንደሆነ ተጠባበቀ ። ጉሮሮው ግን ምንም አልሆነም ።

ድምጹን አዳመጠው ፥ በእርግጥ ለውጥ አለበት ። ነገር ግን ወዶታል ። ጉርነን ያለ የአዋቂ ድምጽ ነው ። የልጅ አይደለም ። ወፈር ያለ የበለጸገ ድምጽ ነው ብሎ ገመተ ። ዘፈኑን ጨርሶ ቁጭ ብሎ ያስብ ጀመር ።

ከኋላው ኒና ፥

"አይከፋም ፥ ጓዴ ፥ አይከፋም!" አለው ።

ጆኒ ወደኒና ተሽከርክሮ ዞረ ። ኒና ብቻውን በሩ መተላለፊያ ላይ ቆሟል ። ሴት ጓደኛው አብራው አይደለችም ። ጆኒ እፎይታ ተሰማው ። ኒና ቢሰማው ግድ የለውም ።

"እህስ! በል እንግዲህ እነዚያን ሁለት ሴቶች ከዚህ እናስወግዳቸው ። ወደ ቤታቸው እንላካቸው" አለ ጆኒ ።

"እራስህ ላካቸው ። ጥሩ ልጆች ናቸው ። ላስቀይማቸው አልፈልግም ። ከዚህም በላይ ከራሴ ጓደኛ ጋር ሁለቴ ፍቅር ተለዋውጫለሁ ። እራት እንኳን ሳላበላ ብልካት ምን ይሰማታል!"

ኤድያ! ጆኒ አሰበ ። ዘፈኑ የሚያስጠላ ቢሆንም ልጃገረዶቹ ይስመት ። ከእዚያው አካባቢ የሚያውቀው

t.me/OLDBOOKSPDF

የሙዚቃ ቡድን መሪ ዘንድ ልኮ ማንዶሊን እንዲመጣ ለት አዘዘ ። የታዘዘው የሙዚቃ መሪም ፥

"በካሊፎርንያ ውስጥ ማንዶሊን የሚጫወት ሰው የለም" አለው ።

"እንደምንም ብለህ ፈልግ ፥" ሲል ጆኒ ጮኸበት ።

ቤቱ የድምጽ መቅረጫ መሳሪያዎች ተሞልተውበታል ። ሴቶቹ ድምጽ ማጉያውንና መቆጣጠሪያውን እንዲቆጣጠሩ ተደረገ ። እራታቸውን ከበሉ በኋላ ጆኒ ስራውን ቀጠለ ። ኒኖ በማንዶሊን እንዲያጅበው አድርጎ የጥንት ዘፈኖቹን ሁሉ ያላንዳች ችግር ዘፈናቸው ። ጉሮሮው ምንም አልሆነ ። ለዘለአለም ሊዘፍን እንደሚችል ሆኖ ተሰማው ።

ሳይዘፍን በቆየባቸው ወራት ስለዘፈን ሲያስብ ፥ ለዘፈን የሚሆኑ ሀረጐች አመራረጡ ከልጅነቱ ዘፈኖቹ የተለዩ እንዲሆኑ ሲያቅድ ነበር ። ያኔ ዘፈኖቹን በራሱ ውስጥ በረቀቀ ስልት ይዘፍናቸው ነበር ። አሁን ግን ለእውነተኛ ዘፈን ተነሳስቷል ። አንዳንዴ በሀሳቡ ሲዘፍን ያልነበረ ስህተት በትክክለኛው ዘፈን ላይ ይከሰታል ። ጮክ ብሎ መዝፈን አለበት ። ዘፈኑን እራሱ ለመስማት ትኩረት አያደርግም ፥ በእንቅስቃሴውና በተግባሩ እንጂ ። በጊዜው መጠን ላይ ቅሬታ ነበረው ። ግን ምንም አይደል ፤ ጥቂት መሻከር ነው ። እጮንቅላቱ ውስጥ ያለው የጊዜ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ይጠብቅለታል ። ትንሽ ልምምድ ብቻ ነው ጆኒ የሚያስፈልገው ።

በመጨረሻ ዘፈኑን ሲያቆም ቲና የሚያብረቀርቁ ዓይኖቿን ወደሱ አቃንታ ጠጋ ብላ በረዥሙ ሳመችው ።

"አንተ የምትሰራቸውን ፊልሞች ሁሉ ለማየት እናቴ ትሄድ የነበረበት ምክንያት አሁን ገና ገባኝ" ይህ አነጋገር በዚያ ጊዜ መሆኑ በጀ እንጂ ስህተት ነበር ። ጆኒና ኒኖ ሳቁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘፈኑን እንደገና አዳመጡት ። ጆኒ በእርግጥ የእራሱን ድምጽ ሰማ ። ትክክለኛው የጆኒ ፎንቴን ድምጽ ከበድ ያለና እድገት ያሳየ ከመሆኑም ሌላ ፥ ዘፋኙ አዋቂ እንጂ ልጅ አለመሆኑ በውል ይለያል ። ድምጹ የበለጠ እውነተኛ ስሜት ፥ የበለጠ ባህርይ ይታይበታል ። የድምጹ ቴክኒካዊ ጥራትም ከድሮው የተሻለ ነው ። ረቂቅ ነው ከማለት ሌላ ቃል አይገኝለትም ። ታዲያ አሁን በዝግታ እንኳን እንደሚታየው ድምጹ ጥሩ ከሆነ በልምምድ ሲሰተካከልለት እንዴት ሊሆን ነው? ጆኒ ኒኖላይ ፈገግ አለና ፥

"በእርግጥ ለእኔ እንደሚመስለኝ ይህ ዘፈን ጥሩ ነው?" ሲል ጠየቀው ።

ኒኖ ደስታ የተሞላበትን የጆኒን ፊት ተመለከተና ፥

"በጣም ግሩም ነው ፥ እስቲ ደግሞ ነገ እንዴት አድርገህ እንደምትዘፍነው እናያለን" አለው ።

የኒኖ ምኞት ጥሩ አለ መሆን ጆኒን ቅር አሰኘው ። "አንተ የውሻ ልጅ! አንተ ብትሆን የዚህን ያህል እንደማትዘፍን ታውቃለህ ። ስለነገው አታስብ ። ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል" አለው ።

ነገር ግን ጆኒ ከዚያ በኋላ ምሽቱን አልዘፈነም ። እሱና ኒኖ ወጣቶቹን ሴቶች ይዘው በየጭፈራ ቤቱ አመሹ ። ቲና ምሽቱን አብራው ብታሳልፍም ጆኒን ብርቱ ሆኖ አላገኘችውም ። 'ታዲያ ምን ይጠበስ! ሁሉ ነገር ባንድ ቀን ሊሳካ አይችል!' ብሎ አሰበ ።

ጆኒ ጧት ሲነሳ ፍርሀት ፍርሀት አለው ። የድምጹን መመለስ በህልሙ ያየ መሰለው ። ነገር ግን የድምጹ መመለስ እውን መሆኑን ሲረዳ ድምጹ እንደገና እንዳይበላሽ በጣም ፈራ ።

ወደ መስኮቱ ጠጋ ብሎ ትንሽ አንጐራጐረ ። ቀጥሎም በጢጃማው እንዳለ ወደ እንግዳ ቤት ወርዶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቪያኖውን እየ፡ጫወተ አብሮ መዝፈን ሞከረ ። ቀስ ብሎ ዘፈነ ። ጉሮሮው ሀመም ሆነ መሻከር አልነበረበትም ። ድምጹን ከፍ አደረገ ። ዜማው እርግጠኛና የበለጸገ ስለሆነ ጥረት ማድረግ አላስፈለገውም ። ቀስ በቀስ ፣ ዜማ እየፈሰሰ ነው ። ጆኒ መጥፎው ጊዜ ያበቃ መሆኑ ተሰማው ። የሚፈልገውን አግኝቷል ። በፊልም ስራው ዜሮ ቢሆን ግድየለውም ፣ ከቪና ጋር ባሳለፈው ምሽት የፍቅር ድክመት ማሳየቱም ምንም አላሳሰበውም ። ተመልሶ ዘፋኝ በመሆኑ ቨርጂኒያ ብትጠላውም ከቶውንም ደንታ የለውም ። ለጊዜው አንድ ቅሬታ ብቻ ነው ያለው ። ትላንት ድምጹ ሲመለስለት ልጆቹ አብረውት ቢሆኑ ኖሮ እንደ'ት ጥሩ ነበር! ምን ያህል በተደሰተ ነበር!

የሆቴሉ ነርስ መድሀኒቶች የተደረደሩበት ጋሪ እያሽከረከረች ወደ ክፍሉ ገባች ። ጆኒ ቀና አለና ወይ ትኝቶ ወይ ሞቶ የሚሆነውን ኒኖን ወደታች ተመለከተው ። በጆኒ ድምጽ መመለስ ኒኖ ቅናት እንደማያድርበት ጆኒ ያውቃል ። ድምጹ ሲመለስለት ጆኒ ያሳየው ደስታ ነበር ኒኖን ያስቀናው ። መዝፈንን ያን ያህል ማፍቀሩ ነበር ኒኖን ያስቀናው ። አሁን ግን ግልጽ የሆነው ጉዳይ ኒኖ ቫሌንቲ በህይወቱ ለመቆየት እንዲፈልግ የሚያደርገው ምንም ነገር አለመኖሩ ነበር ።

ምእራፍ ሀያ ሰባት

ሚካኤል ኮርሌዎኔ መሸት ካለ በኋላ ዘግይቶ ነበር ቬጋስ የደረሰው ። በራሱ ትእዛዝ መሰረት ማንም በአውሮፕላን ማረፊያ የተቀበለው የለም ። አብረውት የነበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሩት ቶም ሂገንና አልበርት ኔሪ የተባለው አዲስ ጋሻ ጃግሬው ናቸው ። እጅግ የተንደላቀቀው የሆቴሉ ማረፊያ ቤት ለሚካኤልና አብረውት ለመጡት ሰዎች ተዘጋጀ ። ሚካኤል ሊያያቸው የሚያስፈልጉ ሰዎች በሙሉ በማረፊያ ቤቱ ይጠብቁታል ።

ፍሬድ ወንድሙን እቅፍ አድርጎ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገለት ። ፍሬድ ከቀድሞው የበለጠ ወፍራም ፥ ይበልጥ በጐ ሰው የሚመስል ፥ ፈገግታ የተሞላበት ፥ እና ይበልጥ ለአለባበሱ ጥንቃቄ የሚያደርግ ሆኗል ። በልኩ የተሰፋ ምርጥ ግራጫ መልክ ሀር ሙሉ ልብስና ተስማሚ አላባሾች ለብሷል ። ጸጉሩን ፣ ፊቱንና የእጅ ጥፍሩን ሳይቀር አሳምሮታል ። ባጠቃላይ ከአራት አመት በፊት ከኒውዮርክ ከተሰደደው ፍሬድ ፈጽሞ የተለየ ሆኗል ።

ወደኋላ ደገፍ ብሎ ሚካኤልን በፍቅር ተመለከተው ።

“ፊትህ በመስተካከሉ ከፊቱ በጣም አምሮብሀል ። መቸም ሚስትህ ነች ያግባባችህ ፥ እ? ኬይ እንዴት ነች ፥ እ? መቸ ነው እዚህ መጥታ የምትጐበኘን?” አለ ፍሬድ።

ሚካኤል ወንድሙን ፈገግታ አሳይቶት ፥ “አንተም በጣም ቆንጆ ሆነሀል” አለው ። “ኬይ ነፍሰጡር በመሆኗ ፥ ትንሹን ልጅዋንም ስለምትንከባከብ ነው እንጂ ከኔ ጋር ትመጣ ነበር። የኔ ጉዞም ለስራ ጉዳይ ነው። ነገ ማታ ወይም ከነገ ወዲያ ጧት ተመልሼ እሄዳለሁ”

“መጀመሪያ ምግብ መብላት ይኖርብሀል ። ሆቴላችን ጐበዝ የምግብ አዘጋጅ አግኝቷል ። በልተህ የማታውቀው ምግብ እናበላሀለን ። ሄደህ እስክትተጣጠብ ሁሉም ነገር ተደራጅቶ ይቆይሀል ። ልታያቸው የምትፈልጋቸውን ሰዎች ሁሉ አሰልፌልሀለሁ ። እየጠበቁ ናቸው”

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል በፈገግታ ፥ "ሞ ግሪንን ለመጨረሻ እና ቆየው ፥ እሺ? ጆኒ ፎንቴንና ኒኖ አብረውን እራት እን ዲበሉ ጠይቃቸው ። እንዲሁም ሉሲና ሀኪሙ ወዳጅ ዋም ይገኙ ። እየበላን ልናወራ እንችላለን" አለውና ወደ ሄገን ዞሮ ፥

"ቶም ሌላ ልትጨምር የምትፈልገው ሰው አለ?" ሲል ጠየቀው ። ሄገን ሌላ ተጨማሪ ሰው እንደሌለው ለሚካኤል መለሰለት ። ፍሬድ ለምን ቶም ሄገንን እንደ ሚካኤል ሞቅ አድርጎ ሰላም እንዳላለው ገብቶታል ። ፍሬድ አባቱ በሚያወግዛቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ መዝግቧል ። ሄገን ይህ ሁኔታ እንዲሻሻልለት አሳደረ ገም የሚል ቅሬታ አለው ። ሄገን ይህን ለማድረግ ደስ ነለው ነበር ። ነገር ግን ዶኑ ለምን እንደሚያወግዘው አልገባውም ። ዶኑ ግልጽ የሆነ የቅሬታ ድምጽ አያሰ ማም ። እንዲያው ያልተደሰተበት መሆኑን ብቻ ያስታ ውቃል ።

የእራት ጠረጴዛ በሚካኤል ማረፊያ ቤት ሲሰናዳ ሰአቱ ከእኩለ ሌሊት አልፏል ። ሉሲ ሚካኤልን ስት ስመው ፤ ስለተስተካከለው ፊቱ ምንም አላነሶችበትም ። ጁልስ ሲጋል ግን በድፍረት የፊቱን ቅርጽ አጤነና ፥

"ጥሩ ስራ ነው ። በጥሩ ሁኔታ ተጠግኗል ። ያፍን ጫህ ውስጥ እብጠቱስ ደህና ነው?" ሲል ጠየቀው ።

"ደህና ነው ። ስለረዳኸኝ አመሰግንሀለሁ"

የእራቱ ዝግጅት ዋና ትኩረት ሚካኤል ላይ ነበር ። በንግግሩም ሆነ በአኳኋኑ ከአባቱ ጋር እንደሚመሳሰሉ ሁሉ የሚገባውን ክብር እንዲሰጡት ፥ አባቱን እንደ ሚፈሩት እንዲፈሩት በሰዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ባህሪ አለው ።

ይሁን እንጂ ፍጹም ተፈጥሮአዊ በሆነ ባህር ይው ሰዎች እንዲዝናኑ ይሻል ። ሄገን እንደ ወትሮው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከወደኋላ ሆነ ። እዚያ ያሉት ሰዎች የማያውቁት አልበርት ኔሪ የተባለ አዲሱ ሰው በጣም ዝምተኛና ልታይ ልታይ የማይል ነበር ። ይህ ሰው አልራበኝም በማለት በሩ አጠገብ ካለ ምቹ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ያነባል ።

ጥቂት መጠጥ ከወሰዱና እራት ከበሉ በኋላ አሳላፊዎቹ እንዲወጡ ተደረገ ። ሚካኤል ጆኒ ፎንቴንን አነጋገረው ።

"ድምጽህ እንደተመለሰልህ ሰማሁ ። የድሮ ቲፎዞዎችህንም አግኝተሀቸዋል ። እንኳን ደስ ያለህ" አለው ።

"አመሰግናለሁ" አለ ጆኒ ።

ሚካኤል ለምን ሊያየው እንደፈለገ ለማወቅ ጆኒ ጓጉቷል ። ምን ውለታ ይሆን የሚጠይቀው ?

ሚካኤል ሁሉን ባጠቃላይ እንዲህ አላቸው ። "የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ወደ ቬጋስ ለመምጣት እያሰበ ነው ። የወይራ ዘይት ንግዳችንን በሙሉ ሸጠን እዚህ ልንኖር አቅደናል ። ዶኑ ፣ ሄገንና እኔ በጉዳዩ ላይ ተነጋግርንበት የቤተሰቡ የወደፊት እድል በዚህ አካባቢ ይሆናል የሚል ሀሳብ አለን ። ይህንንም ስላችሁ አሁን ወይም ለከርሞ ይሆናል ማለቴ አይደለም ። ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሁለት ወይም ሶስት ፣ እንዲያውም አራት አመትም ሊፈጅ ይችላል ። ነገር ግን ይህ አጠቃላይ እቅድ ነው ። ጥቂት ወዳጆቻችን በዚህ ሆቴልና በቁማር ቤቱ ንግድ ከፍ ያለ ድርሻ አላቸው ። እንግዲህ የኛም መነሻ መሰረታችን ይኸው ንግድ ይሆናል ። ሞ ግሪን የራሱን ድርሻ ይሸጥልናል ። የሆቴሉ ንግድ በሙሉ የወዳጆቻችን ንብረት ይሆናል ።"

ይህን ሲሰማ የፍሬድ ክብ ፊት ጭንቀት ታየበት ።

"ማይክ ፣ ሞ ግሪን የራሱን ድርሻ እንደሚሸጥልን እርግጠኛ ነህ? ለኔ አውርቶልኝ አያውቅም ። ንግዱንም በጣም ይወደዋል ። የሚሸጥልን አይመስለኝም ፣" አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል በእርጋታ ፥ "እምቢ ሊለው የማይችለው ድርድር አቀርብለታለሁ" አለው ።

የሚካኤል አንጋገር ምንም ልዩ ነገር የሌለበት የተለመደ አንደበቱ ቢሆንም ፥ አባባሉ የታወቀው የዶኑ ዘይቤ በመሆኑ አስፈሪ ነበር ። ሚካኤል ወደ ጆኒ ፎን ቴን ዞር ብሎ ፥

"እዚህ ስራችንን ለመጀመር እንደምትረዳን ዶኑ ተስፋውን ባንተ ላይ ጥሏል" አለው ። "ቁማርተኞችን ለመሳብ የመዝናኛ አገልግሎት ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ተገልጾልናል ። በአመት አምስት ጊዜ ለአንድ ሳምንት ያህል መጥተህ ደምበኞችን ለማዝናናት ውል እንደምን ፈራረም ተስፋ እናደርጋለን ። በሲኒማ ስራ ላይ የተ ሰማሩ ወዳጆችህም እንደሚተባበሩ ተስፋ እናደርጋለን ። ብዙ ውለታ ጥለህባቸዋል ። ዛሬ ደግሞ ብድራቸውን እን ዲመልሱ ትጋብዛቸዋለህ"

"እሺ ፥ ለክርስትና አባቴ ማናቸውንም ጉዳይ ቢሆን እፈጽማለሁ ። ማይክ አንተም ታውቃለህ" ሲል ጆኒ መለሰለት ። ነገር ግን ድምጹ ውስጥ አንድ ጥር ጣሬ አለበት ።

ሚካኤል ፈገግ አለና ፥ "በዚህ ድርድር ላይ አን ተም ሆንክ ወዳጆችህ የምታጡት ጥቅም አይኖርም ። በሆቴሉ ውስጥ ድርሻ ይኖራችኋል ። ሌላም ጠቃሚ ይሆናል ብለህ የምታምነው ሰው ካለ ለሱም ድርሻ ይያዝለታል ። ምናልባት አታምንኝም ይሆናል ። ነገር ግን ቃሌ የዶኑ ቃል ነው"

ጆኒ ፈጠን ብሎ ፥

"አምንሀለሁ ፥ ማይክ" አለው ። "ነገር ግን በዚህ ሰፈር አስር ተጨማሪ ሆቴሎችና ቁማር ቤቶች እየተ ሰሩ ናቸው ። እናንተ ስትመጡ ገበያው ከተገልጋዩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍላጐት በላይ ይሆናል ። ያ ሁሉ የገበያ ፉክክር ባለበት ሁኔታ በጊዜ ላትደርሱ ትችላላችሁ ።

ቶም ሄገን ፣ "ከጠቀስካቸው ሆቴሎች ሶስቱን የሚሰሩት የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ወዳጆች ናቸው" አለው ።

የሶስቱ ሆቴሎችና የቁማር ቤቶቻቸው ባለቤት የኮርሌዎኔ ቤተሰብ መሆኑን ጆኒ ፎንቴን ወዲያው ተረዳ ። ስለዚህ ጠቃሚ ለሚሆኑ ሰዎች የሚሰጥ ብዙ ድርሻ ይኖራል ማለት ነው ።

"እንግዲህ በጉዳዩ ላይ እተጋበታለሁ" አለ ጆኒ ።

ሚካኤል ወደ ሉሲ እና ጁልስ ሲጋል ዞር ብሎ ፣ "ውለታህ አለብኝ ፡" አለው ጁልስን ። "ወደ ቀድሞው የቀዶ ጥገና ስራህ ለመመለስ እየፈለግህ ፣ በዚያ የጽንስ ማስወረድ ጉዳይ የተነሳ ሆስፒታሎች ሊያሰሩህ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ሰምቻለሁ ። ነገር ግን ያንተ ትክክለኛ ፍላጎት እዚያ መመለስ እንደሆነ ካንተ መስማት እፈልጋለሁ"

ጁልስ ፈገግ አለና ፣ "አዎን ። ነገር ግን የህክምና ተቋሞችን አሰራር አታውቀውም ። ምንም ያህል ሀይል ቢኖርህም ምንም ልታደርጋቸው አትችልም ። በዚያ በኩል ልትረዳኝ የምትችል አይመስለኝም" ሲል አስረዳው ።

ሚካኤል በግማሽ ልብ እራሱን ነቀነቀ ።

"እውነትህን ነው ፣ ትክክል ነህ ። ነገር ግን በጣም ዝነኛ የሆኑ የኔ ወዳጆች በላስ ቬጋስ ትልቅ ሆስፒታል ሊያሰሩ ነው ። ከተማይቱ በያዘችው መስፋፋት ትልቅ ሀኪም ቤት ያስፈልጋታል ። ምናልባት ለነሱ ጥሩ አርገን ብናስረዳቸው ቀዶ ጥገና ክፍል ሊያስገቡህ ይችላሉ ። አንተን የመሰሉ ብቁ የቀዶ ጥገና ሀኪሞች በዚህ በረሀ ውስጥ ከየት ሊያገኙ ይችላሉ? ሌላ ቀርቶ ግማሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቃት ያላቸው ቢሆኑም ሊያገኙ ይችገራሉ ። ይህን ብና ደርግ ለሆስፒታሉ ውለታ ጣልን ማለት ነው ። ስለዚህ ከእዚሁ ባትርቅ ይሻልሀል ። በነገራችን ላይ ፣ አንተና ሉሲ ልትጋቡ ነው የሚል ወሬ ሰምቻለሁ”

ጁልስ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፣ “ጥሩ እድል ማግኘቴን ሳረጋግጥ ይሆናል” አለ ።

ሉሲ ምጸት በተሞላው ቀልድ ፣

“ማይክ ፣ ያንን ሀኪም ቤት ካላሰራሀ ሳላገባ አርጅቼ እንደምሞት እንድታውቀው” አለችው ።

ከጁልስ በስተቀር ሁሉም ሳቁ ። ጁልስ ግን ሚካኤ ልን ፣

“ያን የመሰለ ስራ ውስጥ ከገባሁ ሌላ ግዴታ ውስጥ የምገባበት ሁኔታ አይኖርም?” ሲል ጠየቀው ።

ሚካኤል ቅዝቀዝ ብሎ ፣ “ምንም ግዴታ አይኖ ርም ። ውለታህ ስላለብኝ ብድርህን ለመክፈል ብቻ ነው” አለው ።

ሉሲ በለሆሳስ ፣ “ማይክ ፣ አይክፋህ” አለችው ።

ሚካኤል ፈገግታ አሳያትና ፣ “ፈጽሞ አልተከፋ ሁም” አላት ። ወደ ጁልስም ዞር አለና ፣

“አሁን ያልከው ቃል ጅልነት ነው ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ እንተን ከነበርክበት ችግር ለማውጣት ረድ ቶሀል ። ታዲያ ልታደርግ የማትሻውን ነገር እንድታደ ርግ የምጠይቅህ ጅል ሰው መሰልኩህ? ደሞ ብጠይቅህስ ምናለበት? በችግርህ ጊዜ ሊረዳህ ጣቱን እንኳን ያን ሳልህ ሌላ ማን ነበር? በቀዶ ጥገና ሙያህ ላይ ለመመ ለስ እንደምትፈልግ በሰማሁ ጊዜ እንተ መረዳት የምት ችልበትን መንገድ ስሻ ብዙ ጊዜ ፈጀሁ ። ልረዳህ እችላለሁ ። ምንም እንድታደርግልኝ አልጠይቅህም ። ነገር ግን ቢያንስ ግንኙነታችንን ወዳጅነት የተሞ ላበት አድርገህ ልትገነዘበው ይገባል ። በኔ ግምት ለማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንኛውም ጥሩ ወዳጅ የምታደርገውን ለኔ ታደርገዋለህ። ያ ነው የኔ ማሰሪያ። ይህንንም ቢሆን እምቢ ማለት ትችላለህ" አለው።

ቶም ሄገን እራሱን ዝቅ አድርጎ ፈገግ አለ። ዶኑ ራሱም ቢሆን ከዚህ የተሻለ ጥበብ የተሞላበት ንግግር አያደርግም።

ጁልስ እፍረት ተሰማው። "ማይክ፥ እንደዚያ ማሰቤ አልነበረም። ያንተና ያባትህ ውለታ አለብኝ። የተናገርኩትን ሁሉ እርሳው" አለ።
ሚካኤል ራሱን በመስማማት አነቃነቀና፥

"መልካም፤ አዲሱ ሆስፒታል ተሰርቶ በስራ ላይ እስኪውል የአራቱም ሆቴሎች የህክምና ዲሬክተር ትሆናለህ። የሚያስፈልግህን የሰው ሀይል አሟላ። ደሞዝህ ይጨመርልህል። ይህን በሚመለከት ወደፊት ከቶም ጋር ትነጋገራለህ። ሉሲ፥ አንቺ ደግሞ ከአሁኑ በበለጠ አቢይ ተግባር ላይ እንድትሰማሪ እፈልጋለሁ። በሆቴሉ መተላለፊያዎች ላይ የምንከፍታቸውን ሱቆች ታደራጂያለሽ። በገንዘብ ነክ ጉዳይ ላይ ታተኩሪያለሽ። ምናልባትም በቁማር ቤቶች ውስጥ የሚሰሩትን ልጃ ገረዶች መቅጠር የመሳሰለ ስራ ትሰሪያለሽ። ስለዚህ ጁልስ የማያገባሽ ከሆነ ቢያንስ ሀብታም ያልተዳረች አሮጊት ልትሆኚ ትችያለሽ" አላት።

ፍሬድ በቁጭት ሲጋሩን ያቦናል። ሚካኤል ወደሱ ዞር አለና በለሆሳስ፥

"እኔ የዶኑ መልእክተኛ ነኝ፥ ፍሬዲ" አለው። "አንተ እንድትሰራ የሚፈልገውን ስራ ዶኑ ራሱ ይነግርሀል። ነገር ግን ሊያስደስትህ የሚችል ስራ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። ሁሉም ሰው እዚህ ድንቅ ስራ እያከናወንክ መሆንህን ይነግረናል"

"ታዲያ ለምንድነው በኔ የተከፋው?" አለ ፍሬድ

t.me/OLDBOOKSPDF

በማጉረምረም ። "ምናልባት ካሲኖው እየከሰረ ስለ ሄደ ይሆን? ያን ክፍል እኔ አልቆጣጠረው ፣ ሞ ግሪን ነው እንጂ ። ታዲያ ሽማግሌው ከኔ የሚፈልገው ምንድነው?"

"ስለዚህ አትሰጋ" አለ ሚካኤል ። ወደ ጆኒ ፎን ቱን ዞረና ፣ "ኒኖ የታለ? ላየው ጓጉቼ ነበር" አለው ።

"ኒኖ በጣም ታሟል ። ክፍሉ ውስጥ አንዲት ነርስ እየጠበቀችው ነው ። ይህ ሀኪም ኒኖ እራሱን ለመግ ደል እየሞከረ ስለሆነ በጥንቃቄ መያዝ አለበት እያለ ነው" አለ ጆኒ ።

ሚካኤልም ፣ "ኒኖ ሁልጊዜ ጥሩ ሰው ነው ። ነገር ግን ደንታ የለውም ፣ ለመጠጥ ካልሆነ በስተቀር" አለ ።

"እሞን ፤ ገንዘብ በሽበሽ ሆነ ፣ ብዙ የዘፈንና የሲ ኒማ ስራ ማግኘት ይችላል ። ለአንድ ፊልም ሀምሳ ሺ ብር ይከፈለዋል ፤ ቡን ያረጋታል ። ገዘነኛ ስለመሆን ደንታ የለውም ። ይህን ሁሉ ዘመን ሳውቀው ርካሽ ነገር ሲሰራ አይቼው አላውቅም ። እና ይህ የውሻ ልጅ በመጠጣት ሞቱን እያቀረበ ነው ።"

ጆልስ አንድ ነገር ሊናገረው ሲል በሩ ተንኳኳ ። በሩ ጋ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ያነብ የነበረው ሰው ምንም መልስ ሳይሰጥ ጋዜጣውን ማንበብ መቀጠሉ ጆልስን አስደነቀው ። ሄገን ነበር ተነስቶ የከፈተለት ። በሁለት ሰዎች ታጅቦ የገባው ሞ ግሪን ሄገንን ከመጤፍ ሳይ ቆጥረው ሰተት ብሎ ገባ ።

ሞ ግሪን በብሩክሊን የነፍስ ግድያ ተልእኮ በመ ፈጸም የታወቀ መልከ ቀና ወሮበላ ነው ። ስራውን ወደ ቁማር አዛውሮ ወደ ምእራብ ከተሞች ተጓዘ ። የላስ ቬጋስን ታዳጊነት በቅድሚያ በመገንዘብ በመጀመሪያ ከተሰሩት ሆቴሎችና ቁማር ቤቶች የሱ አንዱ ነበር ። አሁንም ቢሆን የነፍሰ ገዳይ ጠባዩ አልተላቀቀውም ። በሆቴሉ ያሉት ሰዎች ፍሬድ ፣ ሉሲ እና ጆልስ ሲጋል

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞምር ፥ ፈጽሞ ሊጋፈጡት አይፈልጉም ። በተቻለ መጠን ይሸሹታል ።

መልከ ቀና ፊቱ ጭፍግግ እንዳለች ሚካኤልን አነ ጋገረው ።

"ማይክ ፥ ላነጋግርህ ባካባቢው ሆኜ ስጠባበቅ ነበር። ነገ ብዙ የምሰቸራው ነገሮች ስላሉኝ ዛሬ ማታ መገናኘት አለብን ብዬ አሰብኩ ። ይመችህል?" አለው ።

ሚካኤል ወዳጅነት የተሞላበት መገረም በሚመ ስል ገጽታ ተመለከተው ።

"በርግጥ ይመቸኛል" አለና ወደነቶም ሂገን አቅ ጣጫ እራሱን አቃንቶ ፥ "ለሚስተር ግሪን የሚጠጣው ነገር አምጡለት" አለ ።

አልበርት ኔሪ ፥ ለአጃቢዎቹ ደንታ ሳይኖረው ሞ ግሪንን በአንክሮ እንደሚከታተለው ጁልስ ተገነዘበ ። በቬጋስ ለረብሻ ምንም እድል እንደማይኖረው እርግጠኛ ነበር ። ይህማ ቬጋስን ህጋዊ የአሜሪካ ቁማርተኞች መና ኸሪያ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በማደናቀፍ ሞትን የሚጋብዝ ፍጹም የተከለከለ ተግባር ነው የሚሆነው ።

ሞ ግሪን አጃቢዎቹን ፥ "እነዚህ ሰዎች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበትን የቁማር ጨዋታ በቤቱ ሂሳብ አዘጋጁ ላቸው" ሲል ፥ ጁልስ ፥ ሉሲ ፥ ፎንቴንና የሚካኤል ጋሻ ጃግሬ አልበርት ኔሪ እንዲወጡለት ፍላጐቱን ተናገረ ።

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ስምምነቱን እራሱን በማነቃነቅ እያረጋገጠ ፥ "ጥሩ ሀሳብ ነው" አለ ።

ሰዎቹ ከወጡ በኋላ ፍሬድ ፥ ቶም ሂገን ፥ ሞ ግሪንና ሚካኤል በክፍሉ ውስጥ ቀሩ ።

ግሪን የያዘውን መጠጥ አስቀመጠና ፥ ንዴቱን በግድ እየተቆጣጠረ ፥

"ምንድነው እሱ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ከሆቴሉ የኔን ድርሻ ሊገዛ ይፈልጋል የሚባል ወሬ የምሰማው?

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ የእናንተን ድርሻ እገዛለሁ እንጂ እናንተ የኔን መሣ
ሣት አትችሉም" አለው ።

ሚካኤል በለሆሳስ መለሰለት ፥ "የቁማር ቤትህ እየከሰረ ነው ። ከአሰራርህ ስህተት አለ ማለት ነው ። ምናልባት እኛ ብንይዘው በተሻለ ሁኔታ ልናካሂደው እንችላለን"

ግሪን የጭካኔ አሳሳቅ ሳቀ ።

"እናንተ ምናምንቴ ሶላቶዎች ፥ በመከራችሁ ወቅት ፍሬዲን ውለታ በሰራሁላችሁ እኔን ገፍትራችሁ ልታስወጡኝ ፈለጋችሁ? ይህ የናንተ ምኞት ነው ። እኔን ማንም አይገፋኝም ። የሚደግፉኝ ሰዎች አሉኝ" አለው ።

ሚካኤል አሁንም ጽሞናው አልተናጋም ። "ፍሬዲን ያስጠለልከው ሆቴሉን ለማስጨረስና ቁማር ቤትህን ለማደራጀት ረብጣ ብር ስለሰጠንህ ነው ። ከዚህም በላይ የባህሩን ዳርቻ የሚቆጣጠረው የሞሊናሪ ቤተሰብ ስለደህንነቱ ማረጋገጫ በመስጠቱና ፍሬዲን ብትወስድ ውለታ እንደሚመልስ ስላረጋገጠልህ ነው ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብና ያንተ ውለታ ብድር ተመላልሷል ። ለምን እንደምትማረር አይገባኝም ። ያንተን ድርሻ ትክክለኛ ነው ብለህ በምትገምተው ገንዘብ እንገዛለን ። ታዲያ ይህን ማድረግ ምን ክፋት አለበት? ግፍ ተሰራብህ? ይልቁንም ኪሳራ የደረሰበትን ቁማር ቤትህን በመግዛታችን ውለታ ሰራንልህ እንጂ" በማለት ሚካኤል ሊያግባባው ሞከረ ።

ግሪን እራሱን በእምቢታ ነቀነቀና ፥ "የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ከእንግዲህ አንዳችም ጡንቻ የለውም ። የጡት አባት ህመምተኛ ሆኗል ። ሌሎቹ ቤተሰቦች እናንተን ከኒውዮርክ ስላባረሯችሁ እዚህ በቀላሉ የሚቃረም የምታገኙ መሰላችሁ? ጥቂት ምክር ልስጥህ ፥ ሚካኤል! አትሞክረው" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል በለሰለሰ አንደበት ፥ "ለዚህ ነዋ ፍሬዲን ሰው በተሰበሰበበት በጥፊ የመታኸው" ሲል ጠየቀው ።

ቶም ሂገን ደነገጠና ወደ ፍሬድ ተመለከተ ። የፍሬድ ኮርሴዎኔ ፊት ቀልቷል ። "የለምኮ ፥ ማይክ ፥ ያ ምንም አይደል ። ምንም ሊጐዳኝ አይደ ለም ። አንዳንዴ ያመልጠዋል እንጂ እኔና እሱኮ ወዳጆች ነን ። አይደል ፥ ሞ" አለ ፍሬድ ። ሞ ግሪን ጠንቀቅ ብሎ መለሰ ።

"አዎን ፥ በርግጥ አንዳንድ ጊዜ ይህን አካባቢ ሰር አት ለማስያዝ የማይረቡ ሰዎችን መርገጥ አለብኝ ። ፍሬዲን የተቆጣሁት ሁሉንም አስተናጋጅ ሴቶች እየ ተዳራ ከስራቸው እያስተጓጐለ ስላስቸገረ ነው ። ትንሽ ክርክር ገጥሞኝ ነበር ፥ ልክ አገባሁት ።"

ሚካኤል አንዳችም ስሜቱን የሚገልጽ ምልክት ሳያሳይ ወደ ፍሬድ ዞር ብሎ ፥

"አሁን ልክ ገብተሀል ፥ ፍሬዲ!" ሲል ጠየቀው ። ፍሬድ ቁጣው እንደታፈነ ወንድመኝ ትክ ብሎ አየው ። መልስ ግን አልሰጠውም ። ግሪን ሳቀና ፥

"ይህ የውሻ ልጅ በአንድ ጊዜ ሁለት ሴቶች ይዞ አልጋ ላይ ይወጣና ያንን የጥንቱን የሳንድዊች ስራ ይፈጽማል ። ፍሬዲ ፥ ሴቶቹ አንተ ከተገናኘሀቸው በኋላ ማንም እንዳንተ እንደማያስደስታቸው አምንልሀለሁ" አለ ።

ሂገን ይህ አባባል ሚካኤልን ሲያስደንቀው ተመለ ከተ ። ሁለቱም እርስ በርሳቸው ተያዩ ። ዶኑ በፍሬድ ላይ ቅሬታ ያደረበት ስለዚህ መጥፎ ተግባሩ ስለሰማ ሳይሆን አይቀርም ። ዶኑ ስለጸታ ግንኙነት ፈጽሞ ጥብቅ የሆነ ወግ አጥባቂ አቋም አለው ። ይህን የመሰለውን የልጁን የፍሬድን ከሁለት ሴት ጋር በአንድ ጊዜ የመዳ ራት የባህሪ ብኩንነትና የሰብእና ዝቅጠት አድርጎ ይመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለከተዋል ። ፍሬድ በህዝብ ፊት በሞ ግሪን መመታቱ ለኮርሌዎኔ ቤተሰብ ውርደት ነው ። ይህም በአባቱ ጥቁር መዝገብ ውስጥ ያስገባው ሌላው ነጥብ ነው ።

ሚካኤል ስብሰባው ያበቃ መሆኑን ለመግለጽ ከመቀመጫው ተነሳና ፥

"ነገ ወደ ኒውዮርክ መመለስ አለብኝ ። ስለዚህ የምትጠይቀንን ዋጋ አስብበት" ሲል ሞ ግሪንን ነገረው ።

ግሪን አውሬ ሆነ ። "አንተ የውሻ ልጅ! እንዲህ በቀላሉ የምታስወግደኝ መሰለህ?" አለ ። "ግና ሳልጮረምስ ከናንተ የበለጠ ሰው ገድያለሁ ። ኒውዮርክ በርሬ ሄጀ ከዶኑ ከራሱ ጋር ስለዚህ ጉዳይ እነጋገራለሁ ። ለሱ አንድ መደራደሪያ አቀርብለታለሁ"

ፍሬድ ተደናግጦ ፥ "ቶም አንተ ነህ አማካሪ ፤ ዶኑን ልታስረዳውና ልታማክረው ትችላለህ" ሲል ቶም ሄገንን ተማጠነው ።

ይህን ጊዜ ነበር ሚካኤል ወደነዚህ የቬጋስ ሰዎች ዞሮ ቅዝቃዜ የተሞላበት ቁጣውን ያሳያቸው ።

"ዶኑ በከፊል ስራውን ትቷል" አለ ። "አሁን የቤተሰቡን ስራ የምመራው እኔ ነኝ ። እናም ቶምን ከአማካሪነት ቦታው አንስቸዋለሁ ። የሱ ትኩረት በቬጋስ የኔ ጠበቃ ሆኖ መስራት ይሆናል ። በሁለት ወር ውስጥ ቶም ከነቤተሰቡ እዚህ ይመጣና ህግ ጠቀስ የሆኑ ተግባሮችን ይጀምራል ። ስለዚህ ማለት የምትፈልገው ካለህ ለኔ ንገረኝ"

ማንም መልስ አልሰጠም ። ሚካኤል ስርአት በተሞላበት አነጋገር ፥

"ፍሬዲ ፥ አንተ ታላቅ ወንድሜ ስለሆንክ አከብርሀለሁ ። ነገር ግን ከእንግዲህ ከማንም ሰው ጋር ሆነህ የቤተሰባችን ተቀናቃኝ እንዳትሆን ። ይህን ለዶኑም ቢሆን አላነሳለትም" ካለው በኋላ ፥ ወደ ሞግሪን ዞር አለና ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ሊረዱህ የሚሞክሩትን ሰዎች አትስደባቸው" አለው ። "ይልቁንስ ጉልበትህን ቁማር ቤትህን ባከሰረው ጉዳይ ላይ ብታውለው ይሻልሀል ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ በዙ ገንዘብ አፍሷል ። ነገር ግን ተገቢውን ጥቅም አላገኘበትም ። ይሁን እንጂ ፥ አመጣጤ ስለዚህ ልወቅ ስህ አይደለም ። የእርዳታ እጄን ልዘረጋልህ ነው ። እንግዲህ ፥ በበጐ አሳቤ ላይ ብትተፋበት የራስህ ጉዳይ ነው ። ከዚህ በላይ የምለው የለኝም" አለው ።

ይህን ሁሉ ሲናገር አንዴም ሀይለ ቃል ባያሰማም የንግግሩ ተጽእኖ ሁለቱንም ሰዎች አቀዘቀዛቸው ። ሚካኤል ከነበረበት ጠረጴዛ እየራቀ እነሱም እንዲወጡለት በሚጠቁም አኳኋን ትክ ብሎ ተመለከታቸው ። ሄገን ሄዶ በሩን ከፈተ ። ሁለቱም ሰዎች ደህና እደሩ ሳይሉ ወጥተው ሄዱ ።

በማግስቱ ጧት ሞ ግሪን ድርሻውን ለኮርሌዎኔ ቤተሰብ በምንም ዋጋ ቢሆን የማይሸጥ መሆኑን የሚገልጽ መልእክት ለሚካኤል ደረሰው ። መልእክቱን ያመጣው ፍሬድ ነበር ። ሚካኤል ትከሻውን ነቀነቀና ወንድሙን ፥

"ወደ ኒውዮርክ ከመመለሴ በፊት ኒኖን ማየት እፈልጋለሁ" አለው ።

ሚካኤል ኒኖ ካረፈበት የሆቴል ክፍሎች ሲሄድ ጆኒ ፎንቴን ቁርሱን ሲበላ ደረሰበት ። ከበስተኋላው በተከለለው መጋረጃ ውስጥ ጁልስ ኒኖን እየመረመረው ነው ። በመጨረሻ መጋረጃው ተከፈተ ።

ሚካኤል የኒኖን ሁኔታ ሲመለከት ደነገጠ ። ሰውዬው ስነፍጥረቱ እየተፋለሰ ነው ። አይኑ ቦዟል ፥ አፉን መዝጋት አልቻለም ። የፊቱ ጡንቻዎች ዝለዋል ። ሚካኤል ከኒኖ አልጋ ላይ አረፍ ብሎ ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

"ኒኖ ፥ አይንህን ለማየት በመብቃቴ ምንኛ መል ካም ነው ። ዶኑ ዘወትር ስላንተ ይጠይቃል" አለው ። ኒኖ ፈገግ ሲል ፥ ያ የድሮ ፈገግታው ነበር ።

"መሞቴ ነው ብለህ ንገረው ። የተዋናይነት ስራ ከወይራ ዘይት ንግድ ስራ የባሰ አደገኛ ነው ብለህ ንገርልኝ"

"ትድናለህ ፥ ቤተሰቡ ሊረዳ የሚችለው ነገር ካለ ንገረኝ"

ኒኖ እራሱን ነቀነቀና ፥ "ምንም ነገር የለ ፥ ምንም" ሲል መለሰለት ።

ሚካኤል ለጥቂት ደቂቃዎች ካዋራው በኋላ ተሰ ናብቶት ሄደ ። ፍሬድ ሚካኤልንና ተከታዮቹን አውሮፕ ላን ማረፊያ ድረስ ሸኛቸው ። ነገር ግን በሚካኤል ጥያቄ መሰረት መነሻቸው እስኪደርስ ፍሬድ አውሮ ፕላን ማረፊያ አካባቢ አልቆየም ። ሚካኤል ፥ ቶምና አልበርት ኔሪ አውሮፕላን ውስጥ እንደገቡ ሚካኤል ወደ ኔሪ ዞር አለና ፥

"አስተካከልከው?" ሲል ጠየቀው ። ኔሪ እራሱን በጭ መታ አደረገና ፥

"ሞ ግሪን ዋጋውን ያገኛል ። እዚህ ውስጥ መዝግቤዋለሁ" ሲል መለሰለት ።

ምእራፍ ሀያ ስምንት

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ወደ ኒውዮርክ ሲመለስ አውሮፕ ላን ውስጥ ሆኖ ተዝናንቶ ሊተኛ ሞከረ ። ግን ከንቱ ሙከራ ነበር ። በጣም አሰቃቂው ፥ ምናልባትም ከሞት የሚያ ደርሰው ፥ የህይወቱ ክፍለ ዘመን እየተቃረበ ነው ። ከእ ንግዲህ ነገሩ ሊቆይ አይችልም ። ሁሉ ነገር ዝግጁ ሆኗል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለት አመት የፈጁት ጥንቃቄዎች በሙሉ ተስተካክለ ዋል ። ከዚህ በኋላ የሚጓተቱ አይደሉም ። ባለፈው ሳም ንት ዶኑ እሱ የቤተሰቡን ስራ ከመምራት እራሱን ያገለለ መሆኑን በይፋ ለሻምበል አዛጐቹ እና ለሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት ሲያስታውቅ ፣ ይህ ውሳኔው ጊዜው መድረሱን አባቱ ሲጠቁምለት የተናገረው መሆኑን ሚካኤል አውቆታል ።

ሚካኤል ከሲሲሊ ከተመለሰ ሶስት አመት ሊሞ ላው ምንም አልቀረውም ። ኬይ አዳምስን ካገባ ደግሞ ሁለት አመት ሆኖታል ። ይህ የሶስት አመት ጊዜ ሚካኤል የቤተሰቡን ስራ ሲያጠና ያሳለፈበት ወቅት ነበር ። ብዙውን ጊዜ ከቶም ሄገን እንዲሁም ካባቱ ጋር ረዥም ቆይታ በማድረግ አሳለፈ ። ቤተሰቡ ምን ያህል ባለጸጋና ሀያል እንደሆነ ሲገነዘብ እጅግ ተደነቀ ። ቤተሰቡ በመ ሀል የኒውዮርክ ከተማ አያሌ ቢሮዎችን ያቀፉ ትላልቅ ህንጻዎችና ከመጠን ያለፈ ውድ ርስት አለው ። ቤተሰቡ በዎል ስትሪት በሌሎች ሰዎች ስም የተመዘ ገቡ ሁለት ያዋዋይ ድርጅቶች ውስጥ ሽርክና ገብቷል ። በሎንግ አይለንድ አያሌ የባንክ ቅርንጫፎች መስር ቷል ። በጥቂት የልብስ መሸጫ ሱቆች በሽርክና ይነግ ዳል ። እነዚህ ሁሉ በህገወጥ መንገድ በቁማር ንግድ ቤተሰቡ ከተሰማራባቸው ስራዎች በተጨማሪ ናቸው ።

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ስለቤተሰቡ ያለፈ ታሪክ ሲመራመር ካገኘው ግንዛቤ እጅግ ያስገረመው የሙ ዚቃ ሽክላ አስመስሎ በመስራት ለሚያጭበረብር ቡድን ከለላ በመስጠት ገንዘብ ሊያገኝ መቻሉ ነበር ። እነዚህ አጭበርባሪዎች ታዋቂ ዘፋኞች ያስቀረጿቸውን ሽክላ ዎች እያስቀዱ አስመስለው በመስራትና እንዳይነቃባ ቸው ጥበብ በተሞላው ዘዴ በማሸግ ፣ እንዳይያዙ ተጠን ቅቀው ለገበያ ያቀርባሉ ። በግልጽ እንደሚታወቀው

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ዘዴ ከሚመረተው ሸክላ ዘፋኙ ወይም አሳታሚው ድርጅት ቤሳ አያገኝም ። ጆኒ ፎንቴንም ያኔ ታላቅ ዘፋኝ ሳለ በእዚህ አይነት ማጭበርበር ብዙ ገንዘብ ማጣቱን ሚካኤል ተገነዘበ ።

ስለዚህ ጉዳይ ቶም ሄገንን ጠየቀው ። ዶኑ ለምንድ ነው እነዚህን አጭበርባሪዎች ክርስትና ልጁን እንዲ ያታልሉ የፈቀደላቸው? ሄገን ትከሻውን ነቀነቀና ፥ "ስራ ስራ ነው ። በዚህ ላይ ፥ ጆኒ የልጅነት ሚስቱን ፈትቶ ማርጐ አሽተንን ማግባቱ ዶኑን እጅግ ቅር አሰኝቶታል" ሲል መለሰለት ።

"ታዲያ እነዚያ አጭበርባሪዎች እንዴት ስራቸ ውን አቋረጡ? ፖሊሶች ያዟቸው?"

ሄገን ራሱን በአሉታ ነቀነቀና ፥ "ዶኑ ክለላ መስጠቱን አቋረጠ ። ይህንንም ያደረገው ከኮኒ ሰርግ በኋላ ነበር" አለው ።

ዶኑ ራሱ ምክንያት ሆኖ ሰዎች መጥፎ እድል ሲገጥማቸው መልሶ የመርዳት ባህርይውን ሚካኤል ወደፊት አዘውትሮ የሚያየው ጉዳይ ነበር ። ዶኑ ይህን የሚያደርገው ምናልባት በዘዴኝነት ወይም አቅዶት ላይሆን ይችላል ። ነገር ግን የፍላጐቱ አይነቶች መብዛ ታቸው ፥ ወይም ምናልባት የአለም አፈጣጠር ይህን የመ ሰለ መልክ በመያዙ ፥ በጐና ክፉ የተወሳሰበ በመሆና ቸው ፥ የተፈጥሮ ነገር በመሆኑ ይሆናል ።

የሚካኤልና የኬይ የጋብቻ ስነስርዓት በኒው ኢንግላንድ የሚ ቤተሰቦችና ጥቂት ጓደኞቿ በተገኙበት ተፈጸመ ። ከሰርጉ በኋላም ሎንግ ቢች በሚገኘው የዶኑ ግቢ ከአንድኛው ቤት ገቡ ። ኬይ ከሚካኤል ዘመ ዶች እና በዚያ ግቢ ከሚገኙት ሰዎች ጋር በቀላሉ ልትግባባ መቻሏ አስደነቀው ። አንዲት መልካም ወግ አጥባቂ ኢጣሊያዊት እንደምታደርገው ኬይም ወዲ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባያው በማርገዟ ይህም ሁኔታዋ ከአካባቢዋ ጋር ለመግ
ት አስተዋጽኦ አድርጓል ። በሁለት አመት ጊዜ የሁለተ
ኛው ልጅዋ መረገዝ ደግሞ ይበልጥ ለሁኔታዎች ጣእም
ሰጥቷቸዋል ። ኬይ የባሏ ከጉዞ መመለስ ደስ ስለሚያሰኛት
ወትሮም እንደምታደርገው ሁሉ ባሏን በአውሮፕላን ማረ
ፊያ ትጠብቀዋለች ። እሱም ስትቀበለው ደስ ይለዋል ።
አሁን ግን ደስ አላለውም ። ከዚህ ጉዞ በኋላ ላለፉት
ሶስት አመታት ሲያዘጋጁት የነበረውን ተልእኮ መፈጸም
ይኖርበታል ። ዶኑ ይጠብቀዋል ። የሻምበል አዛጦቹም
ይጠብቁታል ። እናም እሱ ፥ ሚካኤል ኮርሌዎኔ ፥ ትእዛዞ
ችን መስጠት ይኖርበታል ። የሚሰጣቸውም ውሳኔዎች
የራሱንና የቤተሰቡን እጣ የሚወስኑ ይሆናሉ ።

ኬይ ልጅዋን በጧት ለመመገብ ስትነሳ ሚሲዝ
ኮርሌዎኔ ለአንድ ሰአት በመኪና ከግቢ ወጥታ ስትመ
ለስ ታያታለች ። አማቷ በየቀኑ የምታደርገው ጉዞ በተስ
ኪያን ለመሳለም እንደሆነ ተገንዘበች ። አሮጊቷ ዘወትር
ስትመለስ የጧት ቡናዋን ለመቅመስና አዲሱን የልጅ
ልጅዋን ለማየት ጐራ ትላለች ።

ሚስዝ ኮርሌዎኔ የኬይ ልጅ ክርስትና የተነሳው
በፕሮቴስታንት ደንብ መሆኑን ብታውቅም ችላ በማለት
ኬይ ለምን ካቶሊክ ለመሆን እንደማትሻ በመጠየቅ ወሬ
ዋን ትጀምራለች ። ስለዚህ ኬይም አሮጊቷ በየቀኑ ጧት
ጧት በተስኪያን ለምን እንደምትሄድና ይህም የካቶሊክ
ሀይማኖት አንዱ ተፈላጊ ምግባር እንደሆነ ጠየቃቻት ።

አሮጊቷ ኬይ ወደ ካቶሊክነት እንዳትለወጥ ያግ
ዳት ይህ ሁኔታ ነው ብላ የገመተች ይመስል ፥

"እረ ፈጽሞ ፥ አንዳንድ ካቶሊኮች ለፋሲካና ለገና
ብቻ ነው በተስኪያን የሚሄዱት ። አንቺም በፈለግሽው

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀን መሄድ ትችያለሽ'' አለቻት ።

ኪይ ሳቀችና ፣ ''ታዲያ ለምንድነው አንቺ ዘወትር ጧት ጧት የምትሄጂው?'' አለቻት ።

በሁልጊዜዋ አንጋገር ፣ ''እኔስ ለባሌ ስል ነው በተ ስኪያን የምሄድ ፤ እንጦርጦስ እንዳይወርድ'' አለች ሚስዝ ኮርሌዎኔ ። ጥቂት ተንፈስ ብላም በመቀጠል ፣ ''ቢሞት ነፍሱ ወደ ሰማይ እንድትወጣ እለት በእለት እጸልያለሁ'' በማለት ወደ ሰማይ አመለከተች ። አሮጊቷ በአንዳች ዘዴ የባልዋን ፊቃድ የምትቀለብስ ወይም ነገሩ ተስፋ የሌለው ይመስል ስትናገር ፈገግ ታዋ የአንድ ተንኰለኛ ሀጻን ፈገግታ ይመስል ነበር ። ንግግርዋ በፈዝ መልክ የቀረበ ይሁን እንጂ የኢጣ ሊያን ባልቴቶች ኮስታራ ዘይቤ አልተለያትም ። ለወት ሮው ባሏ በሌለበት ወቅት እንደምታደርገው ለታላቁ ዶን ተገቢውን ክብር አልሰጠችውም ።

እናት ኮርሌዎኔ ትከሻዋን ነቀነቀችና ፣ ''ከተተኮሰ በት በኋላ እንደድሮው አይደለም'' አለች ። ''ስራውን ሁሉ ሚካኤል እንዲያካሂድ አድርጎት እሱ በአትክልቱ ውስጥ አሁንም እንደድሮው ገበሬ የሆነ ይመስል ቃሪ ያና ቲማቲም በመኮትኮት የሞኘ ስራ ያከናውናል ። ብቻ ወንዶች ሁሉም ያው ናቸው'' አለች ።

ሬፊድ ሲል ደግሞ ኮኒ ኮርሌዎኔ ከሁለት ልጆቿ ጋር ትሆንና ኪይን ለመጠየቅና ከሷ ጋር ለማውራት በቤታቸው ታልፋለች ። ኮኒ በተለይ የደስ ደስ ያላት በመሆኗና ለወንድሟ ለሚካኤል ያላት ፍቅር ግልጽ በመሆኑ በኪይ ዘንድ ተወዳጅነትን አትርፎላታል ። ኮኒ የጣልያኖች ምግብ አዘገጃጀት ለኪይ አስተምራታለች ። ይሁን እንጂ አንዳንዴም የእራሷ ሙያ ውጤት የሆነ ምግብ ሰርታ ለሚካኤል ታመጣለታለች ።

ኮኒ ዘወትር እንደምታነሳው ሁሉ ፣ ዛሬ ጧትም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል ስለ ባኗ ስለ ካርሎ ምን እንደሚያስብ ኬይን ጠየቀቻት ። በእርግጥ ሚካኤል እንደሚያስመስለው ካርሎን ይወደው ይሆን? ካርሎ ሁሌም ከቤተሰቡ ጋር ትንሽ ችግር ነበረው ። አሁን ግን ካለፉት አመታት ጀምሮ የተስተካከለ ይመስላል ። ከሰራተኛ ማህበር ጋር ያለው ስራ እየተሳካለት ነው ። ነገር ግን ለብዙ ሰአታት በመቆየት አድካሚ ስራ መስራት ነበረበት ። እንደ እውነቱ ከሆነ ካርሎ ሚካኤልን እንደሚወደው ኮኒ ትናገራለች ። ሁሉም ሰው ቢሆን ዶኑን እንደሚወደው ሚካኤልንም ይወደዋል ። ሚካኤል ዶኑ ድጋሚ የተወለደ ያህል ነበር ። የቤተሰቡ የወይራ ዘይት ንግድ ስራ በሚካኤል ሊመራ መሆኑ ከሁሉ የበለጠ እርምጃ ነበር።

ኮኒ ካርሎ ከኮርሌዮኔ ቤተሰብ ጋር ስላለው ግንኙነት በምታወራበት ወቅት ተቀባይነት እንዲያገኝ የመሻት ጉጉት እንዳለባት ኬይ ተገንዝባለች ። ሚካኤል ባኗን ይወደውና አይወደው እንደሆን ማወቁ ኮኒን እጅግ ያሳሰባት መሆኑን ኬይ ካልተገነዘበችማ ደደብ ናት ማለት ይሆናል ።

አንድ ማታ ኬይ ለሚካኤል ስለ ሶኒ ማንም ሰው እንደማያወራ አነሳችለት ። አንድ ጊዜ እንዲያውም ኬይ ስለ ሶኒ ሞት የተሰማትን ሀዘን ለዶኑና ለሚስቱ በገለጸችላቸው ጊዜ ያገኘችው አጸፋ ትህትና የጐደለው ዝምታና ቸልታ ብቻ ነበር ። ኮኒንም ቢሆን ስለ ታላቅ ወንድሟ እንድትነግራት ለማድረግ ሞክራ አልተሳካላትም።

የሶኒ ሚስት ፣ ሳንድራ ፣ ልጆቿን ይዛ ወላጆቿ ወደሚኖሩበት ወደ ፍሎሪዳ ሄዳለች ። ሶኒ ምንም ቅርስ ትቶ ባያልፍም የዶኑ ቤተሰብ ለሷና ለልጆቿ መተዳደሪያ የሚሆን በቂ ተቆራጭ አድርጎላታል ።

ሚካኤል እያንገራገረ ሶኒ በተገደለበት ምሽት የሆነውን ለኬይ አስረዳት ። ካርሎ ሚስቱን ስለደበደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ባት ኮኒ ወደ ዶኑ ቤት ስልክ መደወሏን ፥ ስልኩን ያነሳው ሶኒ ስለነበር የእህቱን መደብደብ ሲሰማ በቁጣ ታውሮ ወደነሱ ቤት መብረሩን አወራላት ። ስለዚህ ቤተ ሰቡ ኮኒና ካርሎን ለሶኒ መሞት ምክንያት አድርጎ ይቆጥረናል እያሉ ዘወትር ይሳቀቃሉ ። ግን ነገሩ እንዲያ አልነበረም ። ለኮኒና ለባሏ መኖሪያ ቤት በዶኑ ግቢ ተሰጥቷቸዋል ። ካርሎ በሰራተኛ ማህበር መዋቅር ውስጥ ትልቅ ስራ እንዲይዝ ተደርጓል ። ካርሎም በበ ኩሉ መጠጥም ፥ ዝሙትም ፥ ብልጥ ልሁን ማለትም ትቷል ። ምክር አልሰማ ብሎ ያስቸግር የነበረው አመሉም ተስተካክሏል ። ባለፉት ሁለት አመታት ባሳ የው መሻሻል ቤተሰቡ ተደስቶበታል ። ለደረሰው ጥፋት እሱን የሚወቅሰው የለም ።

"ታዲያ ለምን አንድ ቀን እራት ጋብዘሀቸው እህትህ ያላትን ጥርጣሬ አታስወግድላትም ። ያቺ ምስኪን አንተ ስለባሏ ያለህን አመለካከት ለማወቅ ዘወትር እንደሰጋች ነው ። ያንን ስጋቷን ከሜንቅላቷ እንድታስ ወግደው ንገራት" አለች ኬይ ።

"ይህንስ ላደርግ አልችልም ። በኛ ቤተሰብ ውስጥ ይህን ጉዳይ አናነሳውም" ሲል ሚካኤል መለሰላት ።

"ታዲያ አንተ የነገርከኝን ለኮኒ እንድነግራት ትፈ ልጋለህ?"

ከሱ የምትጠብቀውን ቀላል መልስ ከመናገሩ በፊት በረኸሙ ስላሰበበት ኬይ ተገረመች ። በመጨ ረሻም ፥ "ልትነግሪያት የሚገባ አይመስለኝም" አላት ። "መናገርሽ የሚያመጣው ፋይዳ አይኖርም ። ምንም ብታደርጊ መስጋቷን አትተውም ። እንዲህ ያለው ነገር ሰው ሊያስቀረው የሚችለው ጉዳይ አይደለም"

ኬይ ተገረመች ። ምንም እንኳን እህቱ ኮኒ በጣም ብትወደውም ሚካኤል ለማንም ሰው ከሚያሳየው የበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለጠ ለሷ ቀዝቀዝ ያለ ስሜት ያለው መሆኑን ኬይ አጢ
ናለች ።

"ለሶኒ ሞት እሷን ተወቃሽ ታደርጋታለህ?" ስትል ጠየቀችው ። ሚካኤል በረዥሙ ተነፈሰና ፡ "ፈጽሞ!" አለ ። "እሷ ታናሽ እህቴ ናት ፡ እወዳታለሁ ። ስለሆነው ነገር ሁሉ አዝንላታለሁ ። እንደ እውነቱ ከሆነ ካርሎ ዛሬ እንዲህ የተሻሻለ ሰው ቢሆንም ጥሩ ባል አይደለም ። ስለዚህ የእርሱን ጉዳይ እርሺው"

ኬይ የመነዝነዝ ባህርይ ስለሌላት ነገሩን ተወችው ። ሚካኤል በግፊት ሀሳቡን የሚለውጥ ሰው አለመሆኑንና እምቢ ካለ እንደማይመለስ ልትረዳ ችላለች ። በአለም ላይ የሱን ውሳኔ የማስለወጥ ሀይል ያላት እሷ ብቻ እንደሆነች ታውቃለች ። ነገር ግን ይህን ሀይል አዘውትራ ብትጠቀምበት የሚላሽቅ መሆኑንም አላጣችውም ። ደግሞም ላለፉት ሁለት አመታት አብራው መኖሯ ይበልጥ እንድትወደው አድርጓታል ። የወደደችው ዘወትር ሚዛናዊ ስለነበር ነው ። ነገሩ ይገርማል ። ነገር ግን በአካባቢው ላሉት ሰዎች ፍትሀን እንጂ ትንሽም ጉዳይ ብትሆን በራሱ ፈቃድ ብቻ ተመርቶ የማይሆን ውሳኔ አይሰጥም ። ዛሬ ሚካኤል ታላቅ ሀይል ያለው ሰው ሆኖ ፡ ሰዎች ቤቱ ድረስ ሊያነጋግሩትና ውለታ ሊጠይቁት የሚመጡ ፡ በበጎ ፈቃድና ክብር የሚያስተናግዱት ሰው መሆኑን ኬይ በውል አጢናለች ። ይሁን እንጂ ከልቧ እንድትወደው ያደረጋት ከሁሉም ነገር በላይ አንድ ጉዳይ ነበር ።

ሚካኤል ከሲሲሊ ከተመለሰ ጀምሮ የቤተሰቡ አባል የሆነ ሁሉ የተናጋ ፊቱን በቀዶ ጥገና እንዲያስተካክል ሊያግባባው ሞክሯል ። አንድ እሁድ እለት የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ለእራት ተሰብስቦ ሳለ አሮጊቷ ፡ "በፊልም ላይ የሚታይ ወሮበላ ትመስላለህ ። የሰከረ አይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሪሽ ይመስል አፍንጫህ ንፍጥ ማዝረክረኩን እንዲያቆም ለክርስቶስና ለምስኪኗ ሚስትህ ብለህ ፊትህን ተስተካከል” አለችው ።

ዶኑ ከጠረጴዛው ዋንኛ ቦታ ተቀምጦ የሚሆነውን ሁሉ ተመለከተና ኬይን ፥

“ለመሆኑ የፊቱ መቃወስ ያሳስብሻል?” ሲል ጠየቃት ።

ኬይ ራሷን ነቀነቀች ። ይህን ጊዜ ዶኑ ሚስቱን ፥

“እሱ ከእንግዲህ ከእጅሽ ወጥቷል ። የሚያገባሽ ነገር አይደለም” ሲላት ዝም አለች ። ዝምታዋ ባሏን ፈርታ ሳይሆን በሰው ፊት ከሱ ጋር መጨቃጨቅ ክብሩን መንካት ስለሚሆንባት ነበር ።

ዶኑ ከልጆቹ ሁሉ በላይ የሚወዳት ኮኒም የእሁድ እራታቸውን ስታዘጋጅ ከነበረችበት ኩሽና የምድጃው ወላፈን ፊቷን እንዳቀላው ብቅ አለችና ፥

“ፊቱን እንዲያስተካክሉት ማድረግ ያለባት ይመስለኛል” አለች ። “ይህ ጉዳት ሳይደርስበት በፊት ከቤታችን እጅግ መልከ መልካም እሱ ነበር ። በል እንጂ ፥ ማይክ ፥ እስኪ እሺ በል”

ሚካኤል በማማሽ ልብ ተመለከታት እንጂ መልስ አልሰጣትም ። የሰማትም አይመስል ።

ኮኒ ካባቷ ጐን እንደቆመች ፥

“እሺ አሰኘው” ስትል ዶኑን ሁለት እጆቿን ትከሻው ላይ አሰደግፋ አንገቱን እያሻሸች ተማጠነችው ። ዶኑ ከቤተሰቡ መሀል ይበልጥ ኮኒን ያፈቅራታል ። ኮኒም ለአባቷ ያላት ፍቅር አንጀት የሚበላ ነው ። እንደ ትንሽ ልጅ ፍቅር እምነት የሞላው ነው ።

ዶኑ የኮኒን አንዱን እጅዋን መታ መታ አደረገና ፥

“ሁላችንም በራብ አለቅን ። ስፓጌቲውን ጠረጴዛው ላይ አኑሪና ከዚያ በኋላ ትለፈልፊያለሽ” አላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኮኒ ወደ ባሏ ዞር ብላ ፥ "ካርሎ ፥ ማይክን ፊቱ እንዲስተካከልለት እንዲያደርግ ንገረው ። ምናልባት አንተን ይሰማህ ይሆናል" አለች ። አባባሏ ሚካኤልና ካርሎ ሪዚ ከማንም ይበልጥ ወዳጃዊ ግንኙነት ያላቸው ያስመስላል ።

ጸሀይ ያቀላው ፥ ያማረና ተስተካክሎ የተበጠረ ጸጉር ያለው መልከመልካሙ ካርሎ በቤት የተጠመቀ ወይን ጠጁን ተጎነጨና ፥

"ማንም ሰው ማይክን እንዲህ ስራ ሊለው አይችልም" ሲል መለሰላት ።

ካርሎ ወደ ዶኑ ግቢ ከነቤተሰቡ ከተዛወረ ወዲህ ሌላ ሰው ሆኗል ። በቤተሰቡ ውስጥ ቦታውን ስለሚያውቅ በጥንቃቄ ይጠብቀዋል ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ኬይ አንድ ያልተገነዘበችው ፥ ስውር የሆነባት ጉዳይ አለ ። ኮኒ ሆን ብላ አባቷን ለመማረክ ስትል የምታደርገውን ኬይ በሴትነትዋ አስተውላዋለች ። ሁኔታው ግብታዊ አልነበረም ። የካርሎ መልስም የወንድ ልጅ አቅሙን አውቆ የማደር መልስ ነበር ። ሚካኤል ሁሉን ነገር ችላ ብሎታል ።

ኬይ ስለባሏ ፊት መዛባት ደንታ አልነበራትም ። ነገር ግን የፊቱ መዛባት ስላስከተለው የአፍንጫው የውስጥ እብጠትና ፍሳሽ ስጋት ነበራት ። የቀዶ ጥገና ሀኪምና እብጠቱን ሊያድንለት ይችላል ። በዚህ ምክንያት ሚካኤል ሀኪም ቤት ገብቶ ተፈላጊው መስተካከል እንዲደረግለት ፈልጋለች ። የሚያስደንቀው ግን ሚካኤል የፊቱን መዛባት ይፈልገዋል ። ዶኑም ይህንኑ እንደተገነዘበ እርግጠኛ ነች ።

ኬይ የመጀመሪያ ልጅዋን ከወለደች በኋላ ግን ሚካኤል ፥

"ፊቴን በቀዶ ጥገና እንዳስተካክለው ትፈልጊያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሽ?" ሲላት ደንግጣ እራሷን በአምንታ ነቀነቀች ።

"ህጻናት እንዴት እንደሆኑ ታውቃለህ ። ልጅህ አድጎ የፊትህን መዛባት ሲያጤነው ደስ አይለውም ። እኔ በበኩሌ ልጆችን እንዲያየው አልፈልግም ። እውነቴን ነው የምልህ ለራሴ እንኳን ግድ የለኝም"

"እሺ እንግዲያስ አደርገዋለሁ" አላት ሚካኤል በፈገግታ ። ኬይ ከሀኪም ቤት ወልዳ እስክትመለስ ጠበቀና ሁኔታዎችን አመቻቸ ። ወቅቱ ሲደርስም ቀዶ ጥገናው በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ ። የጉንጩ አጥንት ላይ የነበረው መዛባት ምንም ያህል አያስታውቅም ።

ቤተሰቡ በሙሉ ተደሰተ። የኮኒ ደስታ ግን ከሁሉም ሰው በላይ ነበር ። ሚካኤል ሀኪም ቤት ሳለ በየእለቱ ባሏን ካርሎን በማስከተል ትጠይቀዋለች ። ሚካኤል ወደ ቤቱ ሲመለስም አቅፋ ከሳመችው በኋላ በአድናቆት ፥

"አሁንም እንደገና ቆንጆው ወንድሜ ሆነህል" አለችው ።

ሁኔታው ያላስደነቀው ዶን ግን ፥ "ልዩነቱ ምንድ ነው?" አለ። ኬይ ግን ሚካኤል ከፍላጎቱ ውጭ ፥ እሷ ስለጠየቀችው ብቻ የፈጸመው መሆኑን በመረዳትዋ በልቧ አመሰገነችው ። ሚካኤልን ከራሱ ተፈጥሮ ውጭ አንድ ነገር እሺ እንዲል ማድረግ የሚችል ሰው በዚህ አለም ላይ ኬይ ብቻ ነበረች ።

ሚካኤል ከቬጋስ ሲመለስ ኬይ እንደወትሮዋ እንድትቀበለው ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ሮኮ ላምፖኒ በልዩ መኪና ወሰዳት ። ኬይ ባሏ ወደ ከተማ ሲመለስ የምትቀበለው በዚያ ዝግ ግቢ ውስጥ ያለሱ ጊዜ ማሳለፉ ብቸኝነት ስለሚሰማት ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል ከአውሮፕላን ሲወጣ ቶም እና አዲሱ ጠባቂው አልበርት ኔሪ አጅበውት ነበር ። አልበርት ኔሪ የብራሲን አውሬነት ስለሚያስታውሳት ኬይ አትወደውም ነበር ። ኔሪ ከሚካኤል ወደ ኋላ ቀረት አለና በሚካኤል ዙሪያ የነበረውን ሰው ሁሉ በፈጣን አይኖቹ ቃኘ ። ኬይን ቀድሞ ያያት ኔሪ የሚካኤልን ትከሻ ነክቶ ወደሷ አቅጣጫ እንዲመለከት አሳየው ።

ኬይ ሮጣ ሄዳ ባሏ እቅፍ ውስጥ ስትገባ ሚካኤል ቶሎ ሳም አርጎ ለቀቃት ። እሱና ቶም ሄገን ከኬይ ጋር በልዩ መኪና ውስጥ ሲገቡ አልበርት ኔሪ ተሰወረ ። ኔሪ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር በሌላ መኪና ውስጥ መግባቱን ኬይ አላጤነችም ። የነኔሪ መኪና የነሚካኤልን ልዩ መኪና እየተከተለች እስከ ሎንግ ቢች ተጓዘች።

ኬይ ሚካኤልን የሄደበት ቀንቶት እንደሆን ፈጽሞ አትጠይቀውም ። ጥያቄዎቿ ትህትና የሞላባቸው ቢሆኑም እንኳን በበጐነት አይታዩም ። እሷ ስትጠይቀው ያልሆነ መልስ ይሰጠኛል የሚል ፍራቻ ባይኖራትም ከጋብቻ ህይወታቸው ውጭ የሆነውን ክልል ያስታውሳቸዋል ። ኬይ እንዲህ ለመሰለው ነገር ደንታ መስጠት ትታለች ። ነገር ግን ሚካኤል ቬጋስ ሄዶ ስለመጣበት ጉዳይ ለማስረዳት ምሽቱን ከአባቱ ጋር እንደሚያሳልፍ ሲነግራት በኩምታ ፊቷን መጨፍገጓን ልትደብቅ አልቻለችም ።

"አዝናለሁ" አላት ሚካኤል ። "ነገ ማታ ኒውዮርክ ሄደን ትርኢት እናይና እራትም አብረን እንበላለን ፣ እሺ?"

ሚካኤል የሰባት ወር ጽንስ የያዘውን የኬይን ሆድ በቀስታ መታ መታ አደረገና ፣

"ልጅሽን ስትወልጂ እንደገና ትታሰሪያለሽ ። ኤጭ ! አንቺስ ከአሜሪካዊነትሽ ኢጣሊያዊነትሽ በዛ ። በሁለት አመት ሁለት ልጅ !" ሲል ቀለዳት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"አንተ ደሞ ከሄድክበት ስትመለስ የመጀመሪያውን ምሽት በስራ ጉዳይ የምታሳልፍ ከኢጣልያዊነትህ አሜሪካዊነትህ በዛ ። ለመሆኑ ወደ ቤት የምትመለሰው ዘግይተህ ነው?"

"ከእኩለ ሌሊት በፊት እመለሳለሁ ። ከደከመኝ አትጠብቂኝ ።"

"እጠብቅሀለሁ ።"

በዚያን ምሽት በዶን ኮርሌዎኔ ቤት በሚገኘው ቤተ መጻህፍት ውስጥ በተደረገው ስብሰባ ላይ ዶኑ ራሱ ፣ ሚካኤል ፣ ቶም ሄገን እና ሁለቱ የሻምበል አዛዦች ክሌሜንዛና ቴስዮ ተገኙ ። የስብሰባው መንፈስ ከቀድሞዎቹ ፈጽሞ ተመሳሳይ አልነበረም ። ዶን ኮርሌዎኔ በከፊል ጡረታ ላይ መሆኑን ካሳወቀና ሚካኤል የቤተሰቡን ስራ ከተረከበ አንስቶ አንዳንድ ውጥረቶች ታይተዋል ። ለቤተሰብ ሀላፊነት ስልጣን መብቃት በውርስ የሚተላለፍ አይደለም ። በማናቸውም ቤተሰብ ቢሆን ክሌሜንዛና ቴስዮን የመሰሉ የሻምበል አዛዦች ወደ ዶንነት ደረጃ ከፍ ሊሉ ይችሉ ነበር ። ወይም ቢያንስ ራሳቸውን ችለው እንዲገነጠሉ እና የራሳቸውን ቤተሰብ እንዲመሰርቱ ይፈቀድላቸው ነበር ።

በዚያን ወቅት ደግሞ ዶኑ ከአምስት ቤተሰቦች ጋር ሰላም ከመሰረተ ወዲህ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሀይል አሽቆልቁሏል ። የባርዚኒ ቤተሰብ ያለ አንዳች ተቀናቃኝ በኒውዮርክ አካባቢ እጅግ ሀይለኛ ሆኗል ። ከታታሊያ ቤተሰብ ጋር አንድነት መስርቶ የኮርሌዎኔን ቤተሰብ እየገዘገዘ በቁማር ቤቶች አካባቢም ጉልበታቸውን እያሳዩ ፣ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ምንም አጸፋ አለመመለሱን ሲያጤኑ ደካማ ነቱን በመገንዘብ የራሳቸውን የውርርድ ቤቶች አቋቋሙ ።

የባርዚኒና የታታሊያ ቤተሰቦች ዶኑ እራሱን በጡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረታ ግማሉ አስደሰታቸው ። ሚካኤል አስፈሪነቱ እየ
ተረጋገጠ ቢሆንም በዘዴውም ሆነ በተጽእኖ ከአባቱ
ጋር ለመመጣጠን ቢያንስ አንድ አስር አመት ይፈጅ
በታል ። ስለዚህ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሀይል በማያጠራ
ጥር ሁኔታ እየተቀነሰ ነበር ።

ቤተሰቡ በእርግጥ መጥፎ አጋጣሚዎች ደርሰው
በታል ። ፍሬድ ከቡና ቤት ጠባቂነት የተሻለ ህይወት
አላሳየም ። አንድ ስግብግብ ህጻን ከእናቱ ጡት ከን
ፈሩን አላላቅቅ እንደሚል ሁሉ ፣ እሱም የሴቶች አሜ
ፋሪ ሆኖ ፣ ባጭሩ ወንድነት የጐደለው ሰው ሆኗል ።
የሶኒ ሞትም ትልቅ ውድቀት አስከትሏል ። ሶኒ በቀላሉ
ሊታይ የማይቻል ፣ የሚፈራ ሰው ነበር ። በእርግጥም
ታናሽ ወንድሙን ሚካኤልን ሶሎዞንና ማክለስኪን
እንዲገድል መላኩ ስህተት ነበር ። ከታክቲክ አንጻር
አስፈላጊ ቢሆንም ፣ ከረዥም ወቅት ስትራቴጂ አንጻር
ሲመለከቱት የተፈጸመው ግድያ አደገኛ ስህተት መሆኑ
ተረጋግጧል ። ይሽው ስህተት ዶኑ በውል ሳይድን ከአ
ልጋው እንዲነሳ አስገድዶታል ። ሚካኤልን በስደት
ለቆየባቸው ሁለት አመታትም ቢሆን አባቱ አጠገብ
ሆኖ የሱን ጥበብ ከመማር አግዶታል ። እንዲሁም የአ
የርላንድ ተወላጅ ለአማካሪነት መመረጡ ዶኑ የፈጸ
መው ብቸኛ ስህተት ነበር ። ማንም የአይሪሽ ተወላጅ
እንደ አንድ ሲሲሊያዊ ዘዴኛ እሆናለሁ ብሎ ተስፋ
ማድረግ የለበትም ። እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ግንዛቤዎች
በየቤተሰቡ አእምሮ ውስጥ በመቀረጻቸው ፣ ከኮርሌዎኔ
ቤተሰብ ይልቅ ከባርዚኒና ታታሊያ ቤተሰብ ጋር ላላ
ቸው ወዳጅነት የበለጠ ክብር ሰጡት ። ስለሚካኤል
ያላቸውም ግምት በብልህነት ከሶኒ የተሻለ ቢሆንም
ያባቱን ያህል ብልህ አለመሆኑን ፣ በሀይልም ረገድ ከሶኒ
ጋር እንደማይመጣጠን ነው ። ሚካኤል ከዶኑ ዝቅተኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቃት ያለው ተተኪ ሆኖ ስለተገመተ በብዙ አልተፈራም ።

በሌላ በኩል ፥ ዶኑ ሰላምን ለመመስረት ባሳየው ጥበብ በአጠቃላይ ተደናቂነትን ቢያተርፍም የልጁን መገደል ባለመበቀሉ ቤተሰቡ ብዙ ክብር አጥቷል ። ይህን የመሰለው ጥበበኛነት ከደካማነት እንደመነጨ ተቆጠረ ። ይህ ሁሉ ሁኔታ እዚያች ክፍል ውስጥ ተሰብስበው በነበሩት ሰዎች ይታወቃል ። እንዲያውም አንዳንዶቹ እውነት ነው ብለው ያምናሉ ። ካርሎ ሪዚ ሚካኤልን ቢወደውም ሶኒን ይፈራው እንደነበረው እሱን አይፈራውም። ክሌሜንዛም ቢሆን ሚካኤልን በዚያ ቱርክና በፖሊስ ሻምበሉ ላይ ለፈጸመው ቆራጥነት አድናቆት ቢኖረውም ፥ ለዶንነት ለመብቃት እጅግ ለስለስ ያለ ነው ብሎ ማሰቡ አልቀረም ። ክሌሜንዛ ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ተገንጥሎ ለብቻው የራሱን የድብቅ አለም ቤተሰብ ለመመስረት ይፈቀድልኛል ብሎ ተስፋ አድርጐ ነበር ። ነገር ግን ዶኑ ይህ ሊሆን እንደማይችል ስለጠቆመው ከዶኑ ትእዛዝ ሊወጣ አልፈለገም ። አጠቃላይ ሁኔታዎች ከአቅሙ በላይ እስካልሆኑበት ድረስ ለዶኑ የሚሰጠውን ክብር አያጓድልበትም ።

ቴስዮ ስለ ሚካኤል የተሻለ ግምት አለው ። እውነተኛ ሀይሉን ከህዝብ እይታ በስስት የደበቀ ፥ የዶኑ መመሪያ የሆነውን ‘ወዳጅህ ጥንካሬዎችህን አንኳስሶ ይመልከት ፥ ጠላትህ ድክመቶችህን አጋንኖ ይመልከት’ የሚለውን የአባቱን ግንዛቤ የተከተለ ልዩ ሰው እንደሆነ ተሰምቶታል ።

ዶኑ እራሱም ሆነ ቶም ሄገን ስለሚካኤል ብቃት ምንም ጥርጣሬ የላቸውም ። ዶኑ ልጁ የቤተሰቡን የቀድሞ ሀልውና መልሶ በማስገኘት ረገድ ስላለው ችሎታ ሙሉ እምነት ባይኖረው ኖሮ ፈጽሞ የቤተሰቡን

t.me/OLDBOOKSPDF

ስራ ከመምራት ለመገለል ባልፈቀደ ነበር ። ሄገንም ቢሆን ላለፉት ሁለት አመታት የሚካኤል አስተማሪ ሆኖ ሳለ ሚካኤል ውጥንቅጥ የሆነውን የቤተሰቡን የን ግድ ስራ ፈጥኖ በመረዳት ያሳየው ንቃት አስደንቆ ታል ። እውነትም ያባቱ ልጅ!

ሚካኤል የክሌሜንዛንና የቴስዮን ጀሌዎች በመቀ ነሱና የሶኒንም ተከታዮች እንደገና ባለማደራጀቱ እነዚህ ሰዎች ተቀይመውታል ። የኮርሌዮኔ ቤተሰብ በአሁኑ ወቅት በተግባር ላይ የሚሰማራ ሁለት የጦር ክፍል ብቻ ነው ያለው ። የእነዚህ የተዋጊ ክፍሎች አባላትም ቁጥር ከቀድሞው ተቀንሷል ። በክሌሜንዛና ቴስዮ ግምት በተ ለይ ባሁኑ ወቅት የባርዚኒና የታታሊያ ግፊት በነሱ ግዛት ላይ እየሰፋ ሲሄድ ይህ የሚካኤል እርምጃ እራ ሱን እንደመግደል የሚቆጠር ነው ። ስለዚህ ዶኑ የጠ ራው የእለቱ ልዩ ስብሰባ እነዚህን ስህተቶች በሞላ ለማረም እንደሚያስችል ተስፋ አድርገዋል ።

ሚካኤል ንግግሩን የጀመረው ስለቬጋስ ጉዞውና በዚያም ሞ ግሪን የራሱን ድርሻ ሊሸጥላቸው ፈቃደኛ ስለአለመሆኑ በመግለጽ ነበር ።

"ነገር ግን የምናቀርብለት መደራደሪያ እምቢ ሊለው የማይችል ይሆናል ። እንደምታውቁት የኮርሌዮኔ ቤተሰብ እንቅስቃሴውን ወደ ምእራብ ክፍለ ግዛት ለማዛወር አስቧል ። በዚያ ሰፈር ከሚገኙት የሆቴል ቤት ቁማር ቤቶች አራቱ የኛ ይሆናሉ ። ነገሮች እስኪስተካ ከሉ ጊዜ ያስፈልገናል" ካለ በኋላ ሚካኤል ወደ ክሌሚንዛ ዞሮ ፥ "ፔት ፥ አንተና ቴስዮ ፥ ለአንድ አመት ጊዜ ያለአንዳች ጥያቄና መቆጠብ አብራችሁኝ እንድ ትቆዩ እፈልጋለሁ ። በዚህ አመት መጨረሻ ላይ ከኮር ሌዮኔ ቤተሰብ ተገንጥላችሁ የራሳችሁን ቤተሰብ መስ ርታችሁ የራሳችሁ መሪዎች ትሆናላችሁ ። ይህንንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ስል ወዳጅነታችን መቀጠሉ አያጠያይቅም ። ይህን ስላችሁ ያልሆነ ነገር አስቤ እናንተ ለአባቴ የነበራችሁን ክብር ላበላሸው እንደማልሻ እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ ። እስከዚያ ግን ያለአንዳች ስጋት አመራሬን እንድትከተሉ እፈልጋለሁ ። እናንተ ሊቃለሉ አይችሉም ብላችሁ ለምታስቧቸው ችግሮች ሁሉ መፍትሄ ለመሻት ድርድር እየተካሄደ ነው" አለ ።

ይህን ጊዜ ቴስዮ ፥ "ሞ ግሪን ከአባትህ ጋር ሊነጋገር ከፈለገ ለምን አትፈቅድለትም? ዶኑ ሁል ጊዜ ማንንም ማግባባት ይችላል ። የሱን ምክንያት ድርድር የሚቋቋም ማንም ሰው የለም" ሲል ተናገረ ።

"እኔ በጡረታ እራሴን አግልያለሁ" አለ ዶኑ ። "ከእንግዲህ እኔ ጣልቃ ብገባ ለሚካኤል ተገቢውን ክብር ማሳጣቴ ይሆናል ። ከዚህም በላይ ያንን ሰውዬ እኔ ላነጋግረው አልሻም"

ቴስዮም ሞ ግሪን አንድ ቀን ማታ በቬጋስ ሆቴል ውስጥ በህዝብ ፊት ፍሬድን በጥፊ ስለመምታቱ የሰማው ወሬ ትዝ አለው ። ጥርጣሬው ተቀሰቀሰ ። ወደ ኋላ ለጠጥ አለ ። ሞ ግሪን እንደሞተ ሊቆጠር ይችላል ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሊያግባባው አይሻም ።

ካርሎ ሪዚም "የኮርሌዎኔ ቤተሰብ በኒውዮርክ ያለውን እንቅስቃሴ በሙሉ ሊያቆም ነው?" ሲል ጠየቀ

ሚካኤል እራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ።

"የወይራ ዘይት ንግዳችንን እንሸጠዋለን ። በሚቻለን ሁሉ ወደቴስዮና ክሌሜንዛ እናዛውረዋለን ። ነገር ግን ካርሎ አንተ ስለ ሰራህ እንድትጨነቅ አልፈልግም ። በነሻዳ ያደግህ ስለሆነ ክፍለ ግዛቱን ታውቀዋለህ ። ሰዎቹንም ታውቃቸዋለህ ። ወደዚያ ስንጓዝ ቀኝ እጄ ትሆናለህ ብዬ እየተማመንኩብህ ነው" አለ ።

ካርሎ ወደ ኋላ ተንጋለለ ፥ ፊቱም በደስታ ተሞላ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሀያል ቡድን ውስጥ የሚቀላቀልበት ወቅት እየመጣ ለት ነው ።

ሚካኤል ንግግሩን ቀጠለ ።

“ካሁን ጀምሮ ቶም ሄገን የቤተሰቡ አማካሪ አይ ደለም ። ከዚህ በኋላ ስራው በቬጋስ የኛ ጠበቃ መሆን ነው ። በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በቋሚነት ከነቤተሰቡ ወደዚያ ይዛወራል ። ተግባሩም በጥብቅና ስራ ላይ ብቻ ይወሰናል ። ከአሁኑ ደቂቃ ጀምሮ ከዚህ ውጭ ለሆነ ጉዳይ ማንም ሰው ወደሱ አይሄድም ። የህግ ባለሙያ ስለሆነ ስራውም ይኸው ብቻ ነው ። ቶም የሚወቀስ በት ወይም የሚያሳስበው ጉዳይ የለም ። በዚህ መንገድ እንዲሆን ነው እኔ የምፈልገው ። ከዚህም በላይ ባጋጣሚ ምክር የሚያሻኝ ቢሆን ከአባቴ የበለጠ ማን አማካሪ ይኖረኛል?” አለ ሚካኤል ።

ሁሉም ሳቁ ። አባባሉ ቀልድ የተሞላበት ቢሆንም መልእክቱ ደርሷቸዋል ። ከእንግዲህ ቶም ሄገን ከትር ኢቱ ውጭ ነው ። ከዚያ ጀምሮ አንዳችም ስልጣን አይ ኖረውም ። እዚያ ያሉት ሰዎች የቶም ሄገንን ሁኔታ ለመረዳት ለአፍታ ሲያዩት ሄገን ምንም የተለየ ሁኔታ አላሳየም ።

ክሌሜንዛ በወፍራም ሰው ጭንቀት የተሞላበት የቆጨት ድምጽ ፥ “እንግዲህ እኛ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እራሳችንን እንድንችል ሊፈቀድልን ነው ማለት ነው?” ሲል ጠየቀ ።

“ምናልባትም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ሊሆን ይችላል” አለ ሚካኤል በትህትና ። “ምንጊዜም ቢሆን የቤተሰቡ አካል ሆናችሁ ልትቆዩ ትችላላችሁ ። ያ የናንተ ምርጫ ነው ። ነገር ግን አብዛኛው ሀይላችን የሚሰበሰበው ከዚህ ውጭ በምእራብ ክፍለ ግዛቶች ነው ። ይህም እር

t.me/OLDBOOKSPDF

ምጃ ምናልባት እናንተ በየራሳችሁ መንገድ እንድትደራጁ አመች ሁኔታ ይፈጥርላችኋል”

ቴስዮ በጽሞና እንዲህ ሲል ተናገረ፣

“እንዲህ ከሆነ በየግላችን ለምናቋቁመው ቡድን የሚሆኑን ሰዎች እየመለመልን እንድንቀጥር ፈቃድ ልትሰጡን የሚገባ ይመስለኛል ። እነዚያ የባርዚኒ ዲቃሎች ክልሉን እየቦረብሩ ናቸው ። ምናልባት ትንሽ ስርአት እንዲማሩ ማድረጉ ብልህነት ይመስለኛል”

ሚካኤል ባለመስማማት እራሱን ነቀነቀ ።

“ፈጽሞ ። ፈጽሞ ጥሩ አይደለም ። ትንሽ ብቻ ቆይ። ያ ሁሉ ጉዳይ ድርድር እየተደረገበት ነው ። ማናቸውም ነገር እኛ ከመልቀቃችን አስቀድሞ ይስተካከላል” አለው ።

ቴስዮ በቀላሉ የሚረካ አልሆነም ። ምናልባት ሚካኤል ሊቀየመው ቢችልም በቀጥታ ዶኑን አነጋገረው።

“የጡት አባት ፣ ስለብዙ አመታት ወዳጅነታችን ስትል ይቅርታ አድርግልኝና በዚያ በነቫዳ ጉዳይ ላይ አንተም ሆንክ ልጅህ የተሳሳታችሁ ይመስለኛል ። ከእዚህ የሚደግፉችሁ ሀይል ሳይኖር በዚያ ይሳካልናል ብላችሁ እንዴት ተስፋ ታደርጋላችሁ? ሁለቱም ጐን ለጐን የሚሄዱ ናቸው ። እናንተ ከዚህ ከሄዳችሁ እነባርዚኒና ታታሊያ እኛ ለመቋቋም ከምንችላቸው በላይ ሀይለኞች ይሆኑብናል ። እኔና ፔት ችግር ይገጥመንና ዞሮ ዞሮ በመዳፋቸው ስር እንወድቃለን ። እናም ባርዚኒ ከኔ ጋር ሊጣጣም የሚችል ሰው አይደለም ። እኔ የምለው የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ከዚህ ሲንቀሳቀስ ከሙሉ ሀይሉ ጋር እንጂ በደካማነት ሊሆን አይገባም ። የጦር ሀይላችንን መገንባትና ቢያንስ የተነጠቅነውን በስቴተን ደሴት ላይ ያሉንን ግዛቶች ማስመለስ ይኖርብናል”

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶኑ ራሱን ነቀነቀ ። "ትዝ ይበልህ ፥ ሰላም መስርቻለሁ ። ቃሌን አላጥፈውም" ሲል መለሰለት ።

ቴስዮ ግን ዝም አልል አለ ።

"ባርዚኒ ጠብ ሲጭርባችሁ እንደቆየ ሁሉም ሰው ያውቃል ። ከዚህም በላይ ሚካኤል አዲሱ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሀላፊ ከሆነ ማናቸውንም ተስማሚ የመሰለውን እርምጃ ከመውሰድ ማን ሊያግደው ይችላል ። ያንተ ቃል ሙሉ በሙሉ ሊያስረው አይችልም" አለ ቴስዮ ።

ሚካኤል በቁጣ ጣልቃ ገባ ። ቴስዮን ሲያነጋግረውም በበላይነት ዘይቤ ነበር ።

"ያንተን ጥያቄና ጥርጣሬ የሚመልሱ የስምምነት ድርድሮች እየተካሄዱ ናቸው ። የኔ ቃል አልበቃ ካለህ ዶንህን ጠይቅ" አለው ።

ቴስዮ ይህን ጊዜ ድንበር ማለፉ ገባው ። የዶኑን ቃል ለመጠራጠር ከደፈረ ሚካኤልን ጠላቱ ማድረጉ ነው ። ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፥

"እኔ የተናገርኩት ለቤተሰቡ ደህንነት ስል እንጂ ለራሴ ብዬ አይደለም ። እራሴን ልጠብቅ እችላለሁ" አለ ።

ሚካኤል ወዳጅነት የተመላበት ፈገግታ አሳየው ።

"ቴስዮ በምንም መንገድ በአንተ ላይ ጥርጣሬ የለኝም ። ኖሮኝም አያውቅም ። ነገር ግን በኔ ላይ እምነት ይኑርህ ። ይህን በመሰለው ጉዳይ ላይ ካንተና ከፔት እኩል ባልሆንም ፥ ያባቴ የአመራር ድጋፍ አለኝ ። ስለዚህ በጣም መጥፎ ነገር አልሰራም ፥ ሁላችንም በደህና እንወጣዋለን" አለው ።

ስብሰባው አበቃ ። ትልቁ ዜና ክሌሜንዛና ቴስዮ የየራሳቸውን ቤተሰብ ለመመስረት እንደሚፈቀድላቸው መገለጹ ነበር ። ቴስዮ በብሩክሊን የወደቡን አካባቢና የቁማር ቤቶችን በቁጥጥር ስር ያደርጋል ። ክሌሜንዛም

t.me/OLDBOOKSPDF

በማንሀተን የሚገኙትን የቁማር ቤቶችና በሎንግ አይላንድ የፈረስ እሽቅድምድም ሲፖርት ይይዛል ።

ሁለቱ የድብቅ ጦር መሪዎች በሚገባ ሳይረኩና አሁንም ሳይረጋጉ ነው ከስብሰባው የወጡት ። ካርሎ ሪዚም ያ ይመኘው የነበረ ጊዜ የደረሰለት መሆኑን ተስፋ በማድረጉ የቤተሰቡ ሙሉ አባል መሆኔን ሚካኤል ያበሰረኛል ብሎ ዘግየት ቢልም ፥ ሚካኤል እንዲህ ያላሰበ መሆኑን ተረዳ ። ስለዚህ ዶኑ ፥ ቶም ሄገንን ፥ እና ሚካኤልን ቤተመጸሀፍቱ ውስጥ እንዳሉ ጥሏቸው ሄደ ። ካርሎ ሲወጣ አልበርት ኔሪ በሩን ካሳለፈው በኋላ በሩ ላይ ቆሞ ካርሎ የግቢውን የውጭ መብራቶች አቋርጦ ሲሄድ እንደሚመለከተው አስተዋለ ።

በመጸሀፍት ቤቱ ውስጥ ሶስቱ ሰዎች በአንድ ቤት ውስጥ ለብዙ አመታት አንድ ቤተሰብ ሆነው የኖሩ ሰዎች እንደሚዝናኑ ተዝናኑ ። ሚካኤል ለዶኑ አኒሴት የተባለ መጠጥ ፥ለቶም ሄገን ደግሞ ዊስኪ ቀድቶ አቀረበላቸው ። ለወትሮው አዘውትሮ ባያደርገውም የዚያን እለት እራሱም መጠጥ ወሰደ ። በመዝናናት ላይ ሳሉ ቶም ሄገን በቅድሚያ ተናገረ ፥

"ማይክ ፥ ለምንድነው ከነበርኩበት ስራ ውጭ ያደረገኸኝ?" ሚካኤል በዚህ ንግግር የተገረመ መሰለ ፥

"በቬጋስ ዋናው ረዳቴ ትሆናለህ! እኛ እራሳችን ህጋዊ ስለምንሆን አንተም ተጀምሮ እስከሚጨረስ የህግ ሰዋችን ትሆናለህ ። ከዚህ የበለጠ ምን ነገር ይኖራል ብለህ ታስባለህ?" አለ ።

ሄገን ጥቂት ቅሬታ የተሞላበት ፈገግታ አሳየው ።

"እኔ ስለሱ አይደለም የምናገረው ። የምለው እኔ ሳላውቀው ሮኮ ላምፖኔ በመገንባት ላይ ስላለው ጦር ነው ። እኔ የምለው አንተ በኔ በኩል ወይም በሻምበል አዛዦችህ በኩል ሳይሆን በቀጥታ ከሮኮ ላምፖኔ ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

በመገናኘት ስለምትፈጽማቸው ጉዳዮች ነው ። ምናልባት ሮክ ላምፖኔ በማድረግ ላይ ያለውን ሁሉ አላውቅም እንዳትለኝ እንጂ"

ሚካኤል ለዘብ ብሎ ፥

"ላምፖኔ ስለሚያዘጋጀው ጦር እንዴት አወቅህ" ሲል ጠየቀው ።

ሄገን ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፥

"ግድየለም ፥ አትስጋ" አለው ። "ማንም የሰማ የለም ። ነገር ግን እኔ ባለሁበት ደረጃ የሚሆነውን ነገር ለማወቅ አያስቸግረኝም ። ላምፖኔን የራሱ መተዳደሪያ እና ሰፊ ነጻነት ሰጠኸው ። ስለዚህ ለዚያች አነስተኛ ግዛቱ የሚረዱት ሰዎች ይሻል ። ነገር ግን ስለማናቸውም እሱ ስለሚቀጥረው ሰው ለኔ መግለጽ አለበት ። ግን እንደተገነዘብኩት የሚቀጥረው ሰው ሁሉ ለተፈለገበት ሞያ ከሚፈልገው በላይ በመሆኑ ለዚያ ስራ መከፈል ከሚገባው ገንዘብ በላይ እያወጣ ነው ። በነገራችን ላይ ፥ ላምፖኔን ስትመርጥ ትክክለኛውን ሰው መርጠሀል ። በፍጹም ብቃት ስራውን እየተወጣው ነው"

ሚካኤል ፊቱን አጨፍግጎ ፥

"እንዳጤንከው እንኪን የማይወጣለት ፍጹም ብቁ ቢሆን ኖሮ ባልነቃህበትም ነበር ። ያም ሆነ ይህ ፥ እሱን የመረጠው ዶኑ ነው" ሲል አስረዳው ።

"እሺ" አለ ቶም ። "ታዲያ ለምንድነው እኔ የተገለልኩት?"

ሚካኤል ያላንዳች መበገር በቀጥታ ተጋፈጠው ።

"ቶም ፥ አንተ ለጦርነት ወቅት የምትበጅ አማካሪ አይደለህም ። አሁን ልንወስደው በምንሻው እርምጃ ነገሮች ሁሉ ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ ። ምናልባትም ጦርነት መግጠም ይኖርብናል ። ስለዚህ ድንገት ጦርነት ሲነሳ ከወላፈኑ ላድንህም ፈልጌ ነው" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ፊቱ ቀላ ። አሁን ሚካኤል የተናገረውን ዶኑ ቢናገረው ኖሮ ሄገን በጸጋ በተቀበለው ነበር ። ነገር ግን ሚካኤል ምናባቱ ቆርጦት ነው ይህን የመሰለ ችኩል ፍርድ የሚሰጠው ?

"እሺ" አለ ሄገን ፥ "ነገር ግን እኔ ከቴስዮ ጋር የምስማማበት ነጥብ አለ ። እንቅስቃሴህን የምታደርገው ከድክመት የተነሳ እንጂ ከጥንካሬ አይደለም ። ይህን የመሰለው እርምጃ ምንጊዜም ቢሆን በጎ አይደለም ። ባርዚኒ ተኩላ ነው ። ገላህን ከዳር እስከዳር ቢገነ ጣጥለው ሌሎች ቤተሰቦች ፈጥነው መጥተው የሚረዱህ እንዳይመስልህ"

በመጨረሻ ዶኑ ተናገረ ።

"ቶም ፥ ይህን ውሳኔ ያደረገው ሚካኤል ብቻ አይ ደለም" አለ ። "በነዚህ ጉዳዮች ላይ እኔ ምክር ሰጥቻ ዋለሁ ። እኔ በሀላፊነት ልጠየቅባቸው የማልፈልጋቸው ፥ ነገር ግን ሚካኤል ሊፈጽማቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ ። ያ የኔ ፍላጎት እንጂ የሚካኤል አይደለም ። መጥፎ አማካሪ ነህ ብዬ አስቤም አላውቅም ። ሳንቲኖ ፥ ነፍሱን ይማረውና፥ መጥፎ ዶን እንደነበረ ገምቼ ነበር ። ርህሩህ ልብ ነበረው ። ነገር ግን እኔ መጥፎ አጋጣሚ በደረሰብኝ ወቅት ቤተሰቡን ለመምራት ብቁ አልነበረም ። ፍሬዶንስ ቢሆን እንዲህ የሴቶቹ ታዛዥ ይሆናል ብሎ ማን አስ ቦት ያውቃል? ስለዚህ ምንም አይክፋህ ። ባንተ እንደምተ ማመን ቢሚካኤልም እተማመንበታለሁ ። ልታውቀው በማትችለው ምክንያት ከእንግዲህ በሚደረገው ሁሉ ድርሻ አይኖርህም ። በነገራችን ላይ ፥ የላምፖኔ ሚስጢ ራዊ ጦር ከአንተ አይን ሊያመልጥ እንደማይችል ለሚ ካኤል ንግረው ነበር ። ይህ በአንተ ላይ ምን ያህል እም ነት እንዳለኝ ያሳያል" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚካኤል ላቀ ። "እኔ እውነቴን ነው የምልህ ፥ ቶም ፥ ከቶውንም ስለ ላምፖኔ ጉዳይ ትነቃለህ ብዬ አልገመት ኩም ነበር"

ሄገን ሊያባብሉት እንደሚሞክሩ ተሰማው ።

"ምናልባት ልረዳ እችላለሁ" አለ ።

ሚካኤል ራሱን በእምቢታ ነቀነቀና በቁርጥ ፥ "አንተ ከዚህ ውጭ ነህ ፥ ቶም" አለው ።

ቶም መጠጡን ጨልጦ ከመውጣቱ በፊት በለሆ ላስ ሚካኤልን ወቀሰው ።

"አንተ እንደአባትህ ለመሆን ምንም አልቀረህ ። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን አንድ ልትማረው የሚገባ ነገር አለ" አለው ።

"ምንድነው እሱ ?"

"እንዴት እምቢ እንደሚባል ማወቅ አለብህ" አለ ሄገን ።

ሚካኤል በቁጭት ራሱን ነቀነቀና ፥

"ትክክል ነህ ። ይህን ያልከኝን አጤነዋለሁ" ሲል መለሰለት ።

ሄገን ሲሄድ ሚካኤል እንደቀልድ አድርጎ አባቱን እንዲህ ሲል ጠየቀው ።

"እንግዲህ ሌሎቹን ነገሮች በሙሉ አስተምረኸኛል ። ሰዎች በሚወዱት መንገድ እምቢ እንዴት እንደ ሚባሉ ንገረኝ"

ዶኑ ከትልቁ ጠረጴዛ በስተኋላ ሄዶ ተቀመጠና ፥ "የምትወዳቸውን ሰዎች 'አይሆንም' አትላቸውም" አለው ። "ሌላ ቢቀር ብዙ ጊዜ እምቢ አትላቸውም ። ያ ነው ሚስጥሩ ። እራሳቸው አይሆንም እንዲሉ ማድረግ መቻል ። ይህን ለማድረግ መቸገርና ጊዜ መውሰድ አለ ብህ ። ግን እኮ እኔ የድሮውን ዘይቤ ተከታይ ነኝ ። አንተ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዲሱ ዘመናዊ ትውልድ ነህ ። የኔን መሰማት አይኖር ብህም"

ሚካኤል ሳቀ ። "እሺ ። ግን ቶም መገለሉን ትስማ ማበታለህ ፥ አይደል?" ሲል አባቱን ጠየቀው ።

"እሱማ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ሊገባ አይችልም" በማለት ዶኑ ራሱን ነቀነቀ ።

ሚካኤል ጽሞና በተሞላው አነጋገር ፥

"ልንገርህ" አለ ። "ላደርገው ያቀድኩት ነገር ለአፓሎኒያና ለሶኒ ደም ብቀላ ፈልጌ አይደለም ። መደረግ ያለበት ትክክለኛ ነገር በመሆኑ ነው ። ቴስዮና ቶም ስለነባርዚኒ ያሉት ልክ ነው ።"

ዶን ኮርሌዮኔ እራሱን ነቀነቀ ።

"ቂም በቀል ቀዝቅዞ ሲቀርብ እንደሚጣፍጥ ምግብ ነው ። አለዚያ አንተ በህይወትህ ወደዚህች አገር እንደማትመለስ ስለተረዳሁ ነው እንጂ ከነዚህ ሰዎች ጋር የሰላም ድርድር ባላደረግሁ ነበር ። ግን ባር ዚኒ በሲሲሊ እያለህ እንደገና የመጨረሻ ሙከራ ማድረጉ አስገርሞኛል ። ምናልባትም ይህን ሁኔታ ያዘጋጀው የሰላም ድርድር ከማድረጋችን በፊት ሆኖ ከዚያ በኋላ ሊያስቀረው ባለመቻሉ ይሆናል ። ለመሆኑ ፥ የዚያን ጊዜ ሙከራቸው ዶን ቶማሲኖን በመፈለግ አለመሆኑን እርግጠኛ ነህ?"

"እንደዚያ እንዲመስል ተደርጎ ነበር ሴራው የተጠነሰሰው ፥" አለ ሚካኤል ። "እኔ በመዳኔ ሊታወቅባቸው ቻለ እንጂ ፥ ሴራው ፍጹም የማያስጠረጥር ፥ አንተም ብትሆን ልትደርስበት የማትችል ሆኖ ነበር የታቀደው ። እኔ ፋብሪዚዮ የአጥሩን በር አልፎ ሲሄድ አይቸዋለሁ ። ወዲህ ከተመለስኩ በኋላም ነገሮችን አጣርቻለሁ"

"ያንን እረኛ ፋብሪዚዮን ለመሆኑ አግኝት?" አለ ዶኑ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ነኝ ያገኘሁት ። ከአንድ አመት በፊት ነው ያገኘሁት ። በፍሎ ከተማ ውስጥ የራሱ ፒሳ መሸጫ ሱቅ ከፍቷል ። ስሙን ለውጦ ፥ የሀሰት ፓስፖርት እና መታወቂያ አውጥቶ ያ እረኛ ደህና ኑሮ ይኖራል"

ዶኑ ራሱን ነቀነቀ ። "ከዚህ ወዲያ መቆየቱ ምንም ጥቅም የለውም ። መቸ ትጀምራለህ?" ሲል ጠየቀው ።

"ኬይ እስክትወልድ ለመቆየት እፈልጋለሁ ። ምናልባት ችግር ቢያጋጥም ብዬ ነው ። ቶምም በጉዳዩ እንዳይገባና ጓዙን አንስቶ ቬጋስ ሄዶ እንዲደላደል እፈልጋለሁ ። ምናልባት ከዚህ በኋላ አንድ አመት ያስፈልገኛል ።"

"ለሁሉም ነገር ተዘጋጅተሀል?" ሲል ዶኑ ወደሌላ አቅጣጫ እየተመለከተ ሚካኤልን ጠየቀው ።

ሚካኤል በጽሞና "አንተ ምንም ድርሻ የለህም ። ሀላፊነቱም አይመለከትህም ። ሀላፊነቱን በሞላ እኔ እቀበላለሁ ። የውሳኔ ተጽእኖ ብታደርግብኝም አልቀበልም ። ይህን አሁን አደርጋለሁ ብትለኝ ፥ ቤተሰቡን ትቼ የራሴን መንገድ እይዛለሁ ። በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ሀላፊነት አይኖርህም" ሲል አባቱን ነገረው ።

ዶኑ ለረዥም ጊዜ ጸጥ ብሎ ከቆየ በኋላ ተነፈሰና ፥

"እንዳልከው ይሁን" አለ ። "ምናልባት እኔ ከዚህ ተግባር ተገልዬ ላንተ ሁሉን ነገር ያስረከብኩት ለዚህ ሳይሆን ይቀራል? እኔ በህይወቴ የራሴን ድርሻ ሰርቻለሁ ። ከዚህ በኋላ ፍላጎት አይኖረኝም ። እናም ጎበዞች እንኳን ሊሰሯቸው የማይችሏቸው ጥቂት ተግባሮች ይኖራሉ ። እንግዲህ ይሽው ነው"

በዚያ አመት ኬይ አዳምስ ኮርሌዮኔ ሁለተኛውን ወንድ ልጅዋን ያለችግር ከወለደች በኋላ ወደ ቤቷ ስትመለስ ሰልአልት የሚገባ ታላቅ አቀባበል ተደረገላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኮኒ ኮርሌዎኔ ከጣልያን አገር የመጣ በእጅ የተሰራ እጅግ ውብና ውድ የሆነ የሀር ብርድልብስ በስጦታ አቀረበችላት ። ስጦታውን ስታበረክት ኬይን እንዲህ አለቻት ፥

"ካርሎ ነው የገዛው ። ልዩ ስጦታ ለመምረጥ ሲል በመላ ኒውዮርክ ተዘዋውሮ ነው ያገኘው ። እኔማ ደስ የሚል ነገርም ማግኘት አልቻልኩም"

ኬይ የምስጋና ፈገግታ አሳየቻት ። ይህን አፈታሪክ ለሚካኤል መንገር ያለባት መሆኑ ገባት ። የሲሲሊያው ያንን ጸባይ እየያዘች ናት ።

በዚያው አመት ኒኖ ቫሌንቲ በአንጐል ውስጥ መድማት በሽታ ሞተ ። የመሞቱ ዜና የጋዜጦችን የመጀመሪያ ገጽ ሞላው ። በተለይም ጆኒ ፎንቴን ባዘጋጀው ፊልም ላይ ኒኖ በኮከብ ተዋናይነት የተካፈለበት ፊልም ከጥቂት ሳምንታት በፊት ጀምሮ እየታየ ስለነበር ዜናው አስደንጋጭ ሆነ ። ጋዜጦች ጆኒ ፎንቴን የቀብሩን ስነስርአት እንደሚቆጣጠር ፥ ቀብሩም የግል ሆኖ ቤተሰቡና የቅርብ ወዳጆች ብቻ እንደሚገኙበት ገለጸ ። በአንድ ስሜት የሚቀሰቅስ ዜና እንደተገለጸው ጆኒ በሰጠው ቃለ መጠይቅ ውስጥ ለጓደኛው መሞት እራሱን ተወቃሽ አድርጎታል ። ኒኖ በህክምና ቁጥጥር ውስጥ እንዲውል ጆኒ ሊያስገድደው ይገባ ነበር ። የጋዜጣ ዘጋቢው ግን ይህን የጆኒ ፎንቴንን አባባል ፥ አንድ ምስኪን የሩቅ ተመልካች አንድ አሰቃቂ ሁኔታ ሲፈጸም ዝም በማለቱ እራሱን ተወቃሽ እንደሚያደርግ አድርጎ ነበር ያቀረበው ።

ግን ጆኒ ፎንቴን አብሮ አደግ ጓደኛውን ኒኖ ቫሌንቲን ኮከብ ተዋናይ እንዲሆን አብቅቶታል ። ታዲያ አንድ ጓደኛ ከዚህ በላይ ምን ሊያደርግ ይችላል ?

በቀብሩ ላይ ከፍሬድ በስተቀር ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሌላ ማንም አልተገኘም ። ሉሲና ጁልስ ሲጋል ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበሩ ። ለአንድ ወር ያህል የልብ ሀመም ታሞ ተኝቶ ስለነ በር አልቻለም እንጂ ዶኑ እራሱ ካሊፎርኒያ ሊሄድ ፈልጉ ነበር ። ስለዚህ ትልቅ ያበባ ጉንጉን ላከ ። አልበርት ኔሪ የቤተሰቡ ይፋዊ ተወካይ ሆኖ ወደዚያው ተላከ ።

ከኒኖ ቀብር በኋላ ሁለት ቀን ቆይቶ ሞ ግሪን ሆሊዉድ ውስጥ ተዋናይ ከሆነች ወዳጁ ቤት ጥይት ተተኩሶበት ሞተ ። ከዚያ ወዲህ አልበርት ኔሪ ለአንድ ወር ያህል ወደ ኒውዮርክ አልተመለሰም ። እረፍት ተሰ ጥቶት ወደ ካሪቢያን ደሴቶች ሄዶ ተዝናንቶ ሲመለስ ጸሀይ የጠገበው የቆዳው መልክ ቡናማ ውበት ያሳይ ነበር ። ሚካኤል ኮርሌዎኔ ተቀብሎት ጥቂት የምስጋና ቃል ጣል ካደረገ በኋላ ኔሪ ለመተዳደሪያው የተሻለ ገቢ እንደሚኖረውና ሀብታም ከሆነው ከኢስት ሳይድ የመ ወራረጃ ቤት ንግድ ላይ ድርሻ እንደሚኖረው ገለጸለት ። ኔሪ እዚህ ተግባሩን በሚገባ ለሚፈጽም ሰው ተገቢውን ሽልማት እሚያጎናጽፍ አለም ውስጥ በመግባቱ ረካ ።

ምእራፍ ሀያ ዘጠኝ

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ኋላ ሊደርሱ ስሚችሉ ማናቸ ውም አጋጣሚዎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ አደረገ ። እቅዱ ስህተት የሌለበት ፤ የደህንነት ሁኔታው እንከን አልባ ነበሩ ። መላውን አመት ለመዘጋጀት ብሎ ታግሰ ። ነገር ግን የፈለገውን ወቅት አላገኘም ። ምክንያቱም በሚያስደነግጥ ሁኔታ እድል እራሷ ተቋቋመችው ። ይኸውም የጡት አባት ፥ ታላቁ ዶን እራሱ ፥ ሚካኤል ኮርሌዎኔን አጉል አደረገው ።

አንድ ቀን እሁድ ጧት ፥ ሴቶች በተስኪያን ሳሉ ፥ ዶን ቪቶ ኮርሌዎኔ አትክልቱ ውስጥ ሲሰራ የሚለብሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውን ግራጫ መልክ ሰፊ ሱሪ ፥ ቀለሙ የለቀቀ ሰማያዊ ሸሚዝና በግራጫ መልክ ሀር የተጌጠ ያለቀ ባርኔጣ ለብሶ ተነሳ ። ዶኑ በጥቂት አመታት ክብደቱ ስለጨመረ ለጤንነቴ ይበጀኛል ብሎ በቲማቲም እርሻው ውስጥ ይሰራል ። ነገር ግን ማንንም አላታለለም ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ፥ ዶኑ አትክልቱን መንከባከብ ይወዳል ። ጢት ሲሆንም በእርሻው ትእይንት ይመሰጣል ። ከስድሳ አመታት በፊት የኖረውን የልጅነት ዘመን ያስታውሰዋል ። በአባቱ መሞት የተነሳ የገጠመውን ፍርሀትና ሀዘን ግን አያስታውሰውም ። አሁን ባቄላዎች አናታቸው ላይ አበባ አውጥተዋል ። ጠንካራና አረን ጓዴዎቹ የቅጠል ሽንኩርት አገዳዎች ሌሎቹን አትክልቶች ሁሉ እንደ አጥር ከበዋቸዋል ። ከአትክልቱ በስተ ግርጌ ጡት ያለው በርሜል ከሁሉ በላይ ለም የሆነ ፈሳሽ ማዳበሪያ ፥ የከብቶች ፍግ ተሞልቶ ቆሟል ። እንዲሁም በዚያው የአትክልት ዝቅተኛ ክልል ዶኑ እራሱ በጁ የሰራቸው አራት ማእዘን የእንጨት ክፈፎች በወፍራም ነጭ ገመድ እርስ በርስ ተሳስረው ይታያሉ ። በነዚህ ክፈፎች ላይ ነው የቲማቲሙ ሀረግ እየተሳበ የሚያድገው ።

ዶኑ አትክልቱን ለማጠጣት ተጣደፈ ። ጸሀይዋ የቀለጠ ሰም ሆና ውሀውን ወደእሳት ወላፈንነት ከለወጠች ሰላጣው እንደ ወረቀት መቃጠሉ ነው ። ከውሀ ይበልጥ ጠቃሚ ጸሀይ ናት ። ውሀም እንዲሁ ጠቃሚ ነው ። ነገር ግን ሁለቱ ያለዘዴ ከተቀላቀሉ ጥፋት ያስከትላሉ ።

ዶኑ አትክልቱን የሚያጠፉበትን ጉንዳኖች ለማደን ውስጡን እየተዘዋወረ ይመለከታል ። ጉንዳን ካለበት ፥ የጓሮ አትክልቱ ቀምሷል ማለት ነው ። እንዲህ ሲሆን የተባይ ማጥፊያ ይረጭበታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ልክ በሰአቱ ነው አትክልቱን ያጠጣው ። ጸሀይዋ እየጋለች ነበርና ዶኑ በአእምሮው 'ተጠንቀቅ ፣ ተጠንቀቅ' አለ ። ነገር ግን ጥቂት የቲማቲም ሀረጐች በእንጨት መደገፍ ስለአለባቸው ጐንበስ አለ ። ይህን የመጨረሻ ረድፍ ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ቤቱ ይመለሳል።

በድንገት ጸሀይዋ ከዶኑ እናት አጠገብ የደረሰች መሰለች ። አየሩ በሚወራጭ ወርቅማ ብናኝ ተሞላ ። የሚካኤል ልጅ ሮጠ ዶኑ ከተንበረከከበት ቦታ ሲደርስ የሚያሳውር ወርቅማ የብርሀን ጨረር ከለላ ሸፈነው ። ነገር ግን ዶኑ የሚታለል አይደለም ። ብዙ አይቷላ! ከዚያ ከሚንቀለቀል ቢጫ መከለያ ውስጥ ሞት አደጋ ሊጥልበት ተደብቋል ። እና ዶኑ ልጁ ከአጠገቡ እንዲርቅ እጁን እያወዛወዘ አስጠነቀቀው ። ለትንሽ ! ከደረቱ ውስጥ የመታው ትልቅ መዶሻ የአየር እጥረት አስከተለበት ። ዶኑ ወደፊት ተወርውሮ መሬት ላይ ተደፋ ።

ልጁ አባቱን ሊጠራ ሮጠ ። ሚካኤል ኮርሌዎኔና ጥቂት በሩ ላይ የነበሩ ሰዎች ወደ አትክልቱ ሮጠው ሲሄዱ በጭብጡ አፈር ይዞ በግንባሩ ተደፍቷል ። ወደ ላይ ቀና ካደረጉት በኋላ ተሸክመው ወለሉ በድንጋይ ወደተሰራው መዝናኛ ጥላ ወሰዱት ። ሚካኤል ከአባቱ አጠገብ ተንበርክኮ እጁን ይዞት ሳለ ሌሎቹ ደግሞ ሀኪምና አፖቡላንስ መኪና ሊጠሩ ሄዱ ።

ዶኑ ልጁን አንዴ ለማየት በታላቅ ጥረት አይኑን ከፈተ ። ሀይለኛ የልብ ድካሙ ቀይ ፊቱን ወደ ሰማያዊ ቀለም እየለወጠው ከሞት አፋፍ ላይ ደረሰ ። አትክልቱን አሸተተ ። ቢጫው የብርሀን ውጋጋን አይኑን ጐድቶታል። እና በሹክሹክታ ፣

"ህይወት እንዴት ውብ ናት!" አለ ።

ዶኑ ሴቶቹ ከበተስኪያን ከመመለሳቸው በፊት በመሞቱ እንባቸውን ሲያፈሱ ከማየት ድኗል ። አምቡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላንስ ወይም ሀኪም ከመምጣቱ በፊት ህይወቱ አለፈች። በወንዶች ተከቦ፥ የሚወደውን ልጁን የሚካኤልን እጅ እንደያዘ አረፈ።

የቀብሩ ስነ ስርአት እጅግ ከፍ ያለ ነበር። አምስቱ የድብቅ አለም ቤተሰቦች እንዲሁም የክሌሚ ንዛና የቴስዮ ቤተሰቦች፥ ዶኖቻቸውንና የሻምበል አዛዦቻቸውን በስነ ስርአት ላይ እንዲገኙ ልከዋል። ጆኒ ፎንቴን ሚካኤል እንዳይገኝ ቢመክረውም ቀብሩ ላይ በመገኘት የጋዜጦች አርእስተ ወሬ ሆኖ ነበር። ፎንቴን ለጋዜጦች በሰጠው መግለጫ ቪቶ ኮርሌዮኔ የክርስትና አባቱ እንደነበር እና ከሚያውቃቸው ሰዎች ሁሉ እጅግ መልካም ሰው እንደሆነ፥ ይህን ለመሰለው ታላቅ ሰውም የመጨረሻውን ክብሩን ለመስጠት በቀብሩ ስነስርአት ላይ በመገኘቱ ክብር እንደሚሰማው፥ ከዶኑ ጋር የነበረውን ግንኙነት ማንም ሰው ቢያቀውም ከቶውንም ግድ እንደሌለው በግልጽ ተናገረ።

በቀብሩ ዋዜማ በዶኑ ግቢ የተካሄደው ስነስርአት ጥንታዊ ወግን የተከተለ ነበር። አሜሪጐ ቦናሴራ እንደ ዚህ ያለ ረቂቅ ስራ ሰርቶም አያውቅም። ውለታውን በሙሉ ከፈለ። አንዲት እናት ሙሽራ ልጅዋን ለሰርጓ እንደምታዘጋጅ ጥንታዊ ወዳጁንና የጡት አባቱን አስከሬን አሳምሮ አዘጋጀው። ሁሉም ሰው በሰጠው አስተያየት ሞት ራሱ እንኳን ከታላቁ ዶን ፊት ላይ ክብርና ሞገሱን ሊገፍ እንዳልቻለ ሲገልጽ የአሜሪጐ ቦናሴራ የስራ ውጤት በመሆኑ ኩራትና የሚያስደንቅ ሀያልነት ተሰማው። እሱ ብቻ ነበር ሞት በዶኑ ገጽታ ላይ አሰቃቂ ጥፋት ማድረሱን ያወቀው።

የጥንት ወዳጆችና ሎሌዎች ሁሉ መጡ። ናዞሪኔ፥ ሚስቱ፥ ሴት ልጁ እና ባሏ ከልጆቻቸው ጋር፥ ሉሲ ማንቺኒ ከፍሬድ ጋር ከላስ ቬጋስ መጡ። ቶም ሄገንና

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስቱ ከልጆቻቸው ጋር ፣ የሳንፍራንሲስኮ እና የሎስ አንጀ ሊስ ፣ የቦስተንና የክሊቭላንድ ዶኖች ተገኙ ። ሮኮ ላምፖኔ እና አልበርት ኔሪ ከክሌሜንዛና ቱስዮ እንዲሁም ከዶኑ ልጆች ጋር የአስከሬን ተሸካሚዎች ነበሩ ። ምድረ ግቢ ውና ቤቶቹ በአበባ ጉንጉን ተሞሉ ።

ከአጥር ግቢው ውጭ ጋዜጠኞችና ፎቶግራፍ አን ሺዎች እንዲሁም የኤፍ ቢ አይን ሰዎች መያዟ በታወቀ መኪና ውስጥ ይህን ልዩ ሁኔታ ለመመዝገብ የተንቀሳ ቃሽ ፊልም ካሜራቸውን የያዙ የደህንነት ሰራተኞች ተከልኩለዋል ። ወደ ውስጥ ዘልቀው ለመግባት የሞ ከሩ ጋዜጠኞች የግቢውን በርና አጥሩን በሞሉት የጥ በቃ ዘቦች መታወቂያና የጥሪ ወረቀት ይጠየቁ ነበር ። ከፍተኛ መስተንግዶ እየተደረገላቸው ፣ መጠጦችም እየተላኩላቸው ቢሆንም ፣ ወደ ውስጥ መግባት ግን አልተፈቀደላቸውም ። ጋዜጠኞቹ አንዳንድ ከግቢው ውስጥ የሚወጡትን ሰዎች ለማነጋገር ቢሞክሩም ያገኙት መልስ እንደ ድንጋይ ድርቅ ያለ ፍጥጫ እንጂ ምንም ቃል አልነበረም ።

ሚካኤል ኮርሌዎኔ ቀኑን ያሳለፈው ከኬይ ፣ ከቶም ሄገን እና ከፍሬድ ጋር በግል ቤተመጻህፍቱ ውስጥ ነበር ። ሰዎች እየገቡ ያስተዛዝኑታል ። ጥቂቶቹ ሰዎች የጡት አባት ወይም ዶን ሚካኤል እያሉ ሲጠሩት በሙሉ ትህትና ተቀበላቸው ። ኬይ ብቻ ነበረች ሚካ ኤል በዚህ አጠራር ባለመደሰት ከንፈሩን ማጠጠሩን ያስተዋለችው ።

ክሌሜንዛና ቱስዮ ወደ ሀዘኑ ማእከል ለመቀላቀል ሲመጡ ሚካኤል እራሱ መጠጥ ቀዳላቸው ። አልፎ አልፎ አንዳንድ የስራ ወሬ ነበር ። ግቢውና ቤቶቹ በሞላ ለአንድ የልማት እና የኮንስትራክሽን ኩባንያ እንደሚሸጡ ሚካኤል ገለጸላቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሽያጩ ትርፍም ከፍተኛነት የታላቁን ዶን ብልሀነት የሚገልጽ ሌላ ማረጋገጫ ነበር ። ቤተሰቡ መላ ግዛቱ ወደ ምእራብ ክፍለ ሀገራት እንደሚንቀሳቀስ አውን ሁሉም ገባቸው ። የኮርሌዎኔ ቤተሰብ በኒውዮርክ ያለውን ሀይሉን ያከሰመዋል ። ይህን የመሰለው እርምጃ የቆየው የዶኑን ፈጽሞ ከስራ መገለል ወይም ሞት በመጠበቅ ነበር ።

በዚህ ግቢ ውስጥ ይህን የመሰለ ሰንሰርአት ከተካሄደበትና ብዙ ሰዎች ከተገኙበት አሰር አመት ሊሞላ እንደተቃረበ አንድ ሰው አስታወሰ ። ሚካኤል የአትክልቱ ስፍራ ወደ ሚታይበት መስኮት አመራ ። ያኔ ከብዙ ጊዜ በፊት ከኬይ ጋር አትክልት ውስጥ ተቀምጠ ነበር ። አባቱ ሊሞት ሲል ፣ 'ህይወት እንዴት ውብ ናት!' ብሎ ተናግሯል ። አባቱ ስለሞት ቢፈላሰፍ ሞትን ከብር እንዳይነሳው የፈራ ይመስል አንድም ቃል ስለሞት ተና ግሮ የሚያውቅበትን እለት ሚካኤል አያስታውስም ።

የታላቁ ዶን አስከሬን የሚቀበርበት ወቅት ደረሰ ። ሚካኤል እጁን ከኬይ ጋር አቆላልፎ እጅግ ብዙ ከሆ ነው ለቀስተኛ ጋር ለመቀላቀል ወደ አትክልቱ ስፍራ ሄደ ። እሱንም ተከትለው የሻምበል አዛዦች ከወታደ ሮቻቸው ጋር ፣ ቀጥሎም የጡት አባት በህይወት ሳለ የረዳቸው ምስኪን ሰዎች አብረውት ተጓዙ ። ናዞሪኔ ዳቦ ጋጋሪው ፣ ባሷ ድሮ የሞተባት ወይዘሮ ኮሎምቦ እና ልጆቿ ፣ እንዲሁም በዶኑ አለም ውስጥ ጥብቅ ፣ ነገር ግን ትክክለኝነት የተሞላበት አመራር ይሰጣቸው የነበረ ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው ተከታዮቹ ሁሉ ተገኙ ። ጠላቶቹ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ ክብር ሊሰጡት መጡ ።

ሚካኤል ይህን ሁሉ ሁኔታ ትህትና በተሞላበት ዝግ ፈገግታ አጤነው ። ሁኔታዎቹ አልግረኩትም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሁን እንጂ አንድ ነገር አሰበ ። 'ሕይወት እንዴት ውብ ናት!' ብዬ መሞት ከቻልኩ ከዚህ የበለጠ ቁም ነገር የለም ። ያን ያህል በራሴ መተማመን ከቻልኩ ሌሎች ነገሮች ሁሉ አያሳስቡም ። 'ሚካኤል ባባቱ እግር ይተ ካል ። ልጆቹን ፥ ቤተሰቡን እና የራሱ የሆነውን አለም ይጠብቃል ። ነገር ግን ልጆቹ በተለየ አለም ነው የሚ ያድጉት ። እነሱ ሀኪሞች ፥ ጥበበኞች ፥ ሳይንቲስቶች ነው የሚሆኑት ። አገር ገዢዎች ወይም ፕሬዝዳንቶች ይሆናሉ ። ከድብቅ አለም የውንብድና ተግባር ውጪ ያፈቀዳቸውን ይሆናሉ ። ልጆቹ አጠቃላዩን ቤተሰብ መቀላቀላቸውን ይከታተላል ። ነገር ግን እሱ እንደ አንድ ሀይለኛና ብልህ ወላጅ በዚያ አጠቃላይ ቤተሰብ ላይ ንቁ አይኑን ማሳረፉ ፈጽሞ እርግጠኛ ነው ።

በቀብሩ ስነስርአት ማግስት ዋና ዋናዎቹ የኮር ሌዎኔ ቤተሰብ ባለስልጣኖች በሙሉ በምድረ ግቢው ተሰበሰቡ ። ለእኩለ ቀን ጥቂት ሲቀረው ወደ ዶኑ ቤት እንዲገቡ ተደረገ ። ሚካኤል ኮርሌዎኔ ተቀበላቸው ።

መጸሀፍት ቤቷን ሊሞሏት ጥቂት ነው የቀራቸው ። ሁለቱ የሻምበል አዛዦች ክሌሜንዛና ቴስዮ ብቃት የተ ሞላው ሮኮ ላምፖኔ ፥ ቦታውን የሚያውቀውና ጸጥ ያለው ካርሎ ሪዚ ፥ በዚህ ችግር ጊዜ ለመርዳት ሲል የህግ ስራ ሚና ብቻ እንዲጫወት መደረጉን ለጊዜው ችላ ያለው ሄገን ፥ እንዲሁም ምንም የቅርብ መጥፎ ሁኔታ በኮርሌዎኔ ቤተሰብ ላይ ቢደርስም ፍጹም ታማኝነቱን ለመግለጽ ከሚካኤል አጠገብ ሆኖ ሲጋራውን የሚለኩስ ለትና መጠ ጡን የሚቀላቅልለት አልበርት ኔሪ በስብሰባው ላይ ነበሩ።

የዶኑ እረፍት በቤተሰቡ ላይ መከራን አስከተለ ። ያለ እሱ ግማሽ ሀይላቸው ተቀነሰ ። ይህም ቅናሽ አንድ ነት ከፈጠሩት ከባርዚኒና ከታታሊያ ቤተሰቦች ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመደራደር የሚያስችል ሀይል ነበር ። እዚያች ክፍል ውስጥ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ይሀንን ስለሚያውቅ ሚካኤል የሚለውን ለመስማት ተጠባበቁ ። በነሱ አይን ሚካኤል አዲሱ ዶን አይደለም ፥ ይሀን ደረጃና ስም ለማግኘት ችሎታውን አላሳየም ። የጡት አባት ቢኖር ኖሮ የልጁን በስልጣን መተካት ያረጋግጥለት ነበር ። አሁን ግን በምንም አይነት እርግጠኛ አልነበረም ።

ሚካኤል ኔሪ መጠጥ እስኪያዳርስ ጠበቀ ። ከዚያ በኋላ በጽሞና እንዲህ ሲል ተናገረ "እዚህ ለተገኛችሁ ሁሉ ልል የምሻው ስለአባቴ ምን እንደሚሰማችሁ እንደሚገባኝ ነው ። ሁላችሁም አባቴን ታከብሩት ነበር ። ነገር ግን አሁን ማሰብ የሚኖርባችሁ ስለራሳችሁና ስለቤተሰባችሁ ይሆናል ። ጥቂቶቻችሁ የዶኑ እረፍት ያቀድነውንም ሆነ እኔ የገባሁትን ቃል ያፋልሰው እንደ ሆነ ብላችሁ ትሰጉ ይሆናል ። ለዚህ መልሱ ምንም የሚፋለስ ነገር አለመኖሩና ሁሉም ነገር እንደ በፊቱ እንደሚቀጥል ነው ።"

ክሌሜንዛ ብዙ ጸጉር የተጠቀጠቀበት ራሱን ነቀነቀ ። ጸጉሩ ግራጫማ እና አቋሙ ውፍረት የሞላበትና ደስ የማይል ነው ። "የባርዚኒና የታታሊያ ቤተሰቦች በፍጹም ሀይል ነው የሚነሱብን ፥ ማይክ ። መዋጋት ወይም ከእ ነሱ ጋር ቁጭ ብለህ መነጋገር ይኖርብሀል" አለው ። ክሌሜንዛ ሚካኤልን ያሁኑ ደረጃው በሚፈቅድለት አጠራር "ዶን" ብሎ ሳይሆን እጅግ ባነሰ እንደጠራው እዚያ የተሰበሰበው ሁሉ ተገንዝቧል ።

"እንጠብቅና የሚሆነውን እንይ ፥ እስቲ ። እነሱ በቅድሚያ ሰላሙን ያፍርሱት" አለ ሚካኤል ።

ቴስዮ በለሰለሰ አንደበቱ እንዲህ አለ ፥ "ግና ድሮ አፍርሰውታል ። ዛሬ ጧት በብሩክሊን ሁለት መወራረጃ ቤቶች ከፍተዋል ። ይሀን ዜና ያገኘሁት ለነሱ ከለላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚሰጥ አንድ የፖሊስ ሻምበል ነው ። በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በመላው ብሩክሊን ባርኔጣዬን እንኳን የምሰቅልበት ቦታ አላገኝም"

ሚካኤል አጢኖ ተመለከተው ። "ታዲያ ስለዚህ ጉዳይ አንዳች ነገር ያደረከው አለ?"

ቴስዩ ሾጣጣ ራሱን ነቀነቀና "ፈጽሞ! ችግር ላመጣብህ አልፈለኩም " ሲል መለሰለት ።

"መልካም" አለ ሚካኤል ፥ "ምንም ሳታደርጉ ጸጥ ብላችሁ ቆዩ ። አሁን ለሁላችሁም ልል የምፈልገው ይህን ብቻ ይመስለኛል ። ዝም ብላችሁ ጠብቁ ። ነገር ቢፈልጉዋችሁ አጸፋ እንዳትመልሱ ። ነገሮችን እንዳስተካክል ፥ የሁኔታዎችን አዝማሚያ እንዳጠና ጥቂት ሳምንታት ስጡኝ ። ከዚያ በኋላ ለሁላችሁም የሚመች ስምምነት ላይ እደርሳለሁ ። ከዚያም በኋላ የመጨረሻ ስብሰባ ይኖረንና የመጨረሻ ውሳኔ እናደርጋለን"

ይህን ሲላቸው ሰዎቹ ያሳዩትን መደነቅ ችላ አለው ። አልበርት ኔሪ ስብሰባውን ጨርሰው ሲሄዱ ወደ ውጭ ሸኛቸው ።

ሚካኤል ፥ "ቶም ፥ እስቲ ለጥቂት ደቂቃዎች እዚህ ቆይ" አለ ። ሂገን ምድረ ግቢውን ወደሚያሳየው መስኮት አመራና የሻምበል አዛዦቹ ፥ ካርሎ እና ሮኮ ላምፖኔ በኔሪ ሲሸኙ ተመለከተ ። ከዚያ ወደ ሚካኤል ዞረና "ለመሆኑ የፖለቲካ ግንኙነቶችን መስመር አሲዘሀቸዋል?" ሲል ጠየቀው ።

ሚካኤል በቅሬታ ራሱን በመነቅነቅ ፥ "ሁሉንም አይደለም" አለ ፥ "ግና አራት ወር ይቀረኝ ነበር ። ዶኑ እና እኔ ጀምረነው ነበር ። ይሁን እንጂ ዳኞቹን በሙሉ አግኝቻለሁ ። ያንን ነበር መጀመሪያ ያደረግነው ። ከዋና ዋናዎቹ የኮንግሬስ አባላት ጥቂቶቹን ይዣለሁ ። እዚህ በኒውዮርክ ያሉት ታላላቅ የፓርቲ ሰዎችም

t.me/OLDBOOKSPDF

አያስቸግሩም ። የኮርሌዮኔ ቤተሰብ ማንም ሰው ከሚገም ተው በላይ ጠንካራ ቢሆንም ፥ እኔ ግን ይህ ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ ነበር ተስፋዬ" ሄገንን ፈገግታ አሳየውና "እስካሁን ነገሮቹን ሁሉ ሳትገነዘብ አልቀረህም" አለው ።

ሄገን እራሱን በስምምነት ነቀነቀ ። "ጉዳዩ ከባድ አይደለም ። ያልገባኝ ግን ለምን ከትርኢቱ እንዳስወገድከኝ ነው ። እኔም ግን እንደሲሲሊያዊ ላስብ ብዬ ተነሳሁና በመጨረሻ ያንን ሚስጥር አገኘሁት "

ሚካኤል ሳቀ ። "ሽማግሌውም ጉዳዩን እንደምት ደርስበት አውቆ ነበር ። ነገር ግን እኔ አንተን በነበረህ ቦታ በማቆየት ከእንግዲህ የማልችለው ቅንጦት ውስጥ ልገባ አልፈልግም ። ሰሞኑን እዚህ ታስፈልገኛለህ ። ስለዚህ ቢያንስ ለሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት እንደም ትቆይ ወደ ላስ ቬጋስ ለሚስትህ ደውለህ ብትነግራት ይሻላል ። ለጥቂት ሳምንታት ብቻ ነው በላት" አለው ።

ሄገን በሀሳብ እንደተዋጠ ፥ "ጠላቶችህ በምን መንገድ የሚመጡብህ ይመስልሀል?" አለው ።

ሚካኤል በረዥሙ ተነፈሰና ፥ "ዶኑ ነው የገለጸልኝ ። በአንድ በማልጠረጥረውና በሚቀርበኝ ሰው አማካኝነት ባርዚኒ እርምጃ ሊወስድብኝ አቅዷል"

ሄገን ፈገግ አለና ፥ "እኔን በመሰለ ሰው ነው?" አለው ።

ሚካኤል መልሶ ፈገግ አለ ። "አንተ አይሪሽ ነህ አያምኑህም"

"እኔ ጀርመን — አሜሪካዊ ነኝ"

"ለነሱ ይህ ማለት አይሪሽ ነህ ማለት ነው ።ወደ አንተ አይመጡም ። ኔሪም ፖሊስ ስለ ነበረ ወደእሱ አይሄዱም ። በተጨማሪም ሁለታችሁም ለኔ በጣም ቅርቤቼ ናችሁ ። ስለዚህ ከእናንተ ጋር ቢደራደሩ ልትነግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሩኝ ትችላላችሁ ። ላምፖኔ ግን ቅርቤ አይደለም ። የለም ፥ ከሌሜንዛ ፥ ቴስዮ ወይም ካርሎ — ከእነዚህ አንዱ ነው የሚሆነው”

ሄገን በለሰለሰ አንደበት ፡ “እወራረዳለሁ ፥ ካርሎ ነው የሚሆነው” አለ ።

“እናያለን ፥” አለ ሚካኤል “ጊዜው ሩቅ አይሆንም”

በነገታው ጧት ሄገንና ሚካኤል ቁርሳቸውን ሲበሉ ሚካኤል የስልክ ጥሪ ደረሰው ። በቤተመጻህፍቱ ሆኖ ስልኩን ተቀብሎ ካነጋገረ በኋላ ተመለሰና ፥ “ሁሉ ነገር ተደራጅቷል ። የዛሬ ሳምንት ከባርዚኒ ጋር ልንገናኝ ነው ። ዶኑ ስለሞተ አዲስ የሰላም ድርድር እናደርጋለን” አለና ሚካኤል ሳቀ ።

“ማነው የደወለልህ? ግንኙነቱንስ የፈጠረው ማነው? ሁለቱም እንደተረዱት ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ውስጥ ይህን ግንኙነት የፈጠረው ሰውዬ የከዳ ሰው መሆን አለበት ። ሚካኤል ሄገንን ቅሬታ የተሞላበት ፈገግታ አሳየው ።

“ቴስዮ ነው”

የቅረውን ቁርሳቸውን በጸጥታ በሉ ። ቡና ሲጠጡ ሄገን ራሱን ነቀነቀና ፥ “በበኩሌ ካርሎ ይሆናል ብዬ እናገር ነበር ። ወይም ምናልባት ከሌሜንዛ ይሆናል ። ነገር ግን ቴስዮን ፈጽሞ አልጠረጠርኩትም ። ከሁሉም እሱ ይሻላል”

“እሱ ከሁሉም የበለጠ ብልህ ነው” አለ ሚካኤል ። “ብልህት የተሞላበት የመሰለውን ነገር ነው ያደረገው ። እኔን ለባርዚኒ በትር አሳልፎ ሰጥቶ የኮርሌዎኔን ቤተሰብ ይወርሳል ። ከእኔ ጋር ቢቆይ ግን ድራሹ የሚጠፋ መስሎታል ። በእሱ ግምት እኔ አላሸንፍም”

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ለጥቂት ደቂቃ አረፍ ብሎ ፣ "ይሄ ግምት ምን ያህል ትክክል ነው?" ሲል በቅሬታ ጠየቀው ።

ሚካኤል ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፣ "ሁኔታውን መጥፎ ይመስላል ። ነገር ግን አባቴ ብቻ ነበር የፖለቲካ ግንኙነትና የፖለቲካ ሀይል ከአሰር ጦር እንደሚስተካከል የገባው ። እንደሚመስለኝ አብዛኛው የአባቴ የፖለቲካ ሀይል በእጄ ገብቷል ። ነገር ግን ይህንን የሚያውቅ ከኔ በስተቀር ማንም የለም" ብሎ ልበ ሙሉ ፈገግታ ለሄገን አሳየው ። ቀጥሎ "ዶን ብለው እንዲጠሩኝ አደርጋቸዋለሁ ። ነገር ግን የቴስዮ ድርጊት አሳዝኖኛል" አለው ።

"ለመሆኑ ከባርዚኒ ጋር ለመገናኘት ተስማምተሀል?"

"አዎን ፣" አለ ሚካኤል ። "ልክ የዛሬ ሳምንት ። የተመረጠው ቦታ ለኔ ደህንነት አስተማማኝ በሆነበት በብሩክሊን በሚገኘው በቴስዮ ክልል ነው" አለና እንደገና ከት ብሎ ሳቀ ።

"ከዚያ በፊት እንዳይመቱህ ተጠንቀቅ ፣" አለው ሄገን ።

ሚካኤል ለመጀመሪያ ጊዜ በሄገን ላይ ቀዝቀዝ አለበትና ፣"ይህን ለመሰለ ምክር አማካሪ አያስፈልገኝም" አለው ።

በኮርሌዎኔና በባርዚኒ ቤተሰቦች መሀከል ንግግር ለማካሄድ ከተወሰነው ቀን አስቀድሞ ባለው ሳምንት ውስጥ ሚካኤል ምን ያህል ጠንቃቃ ሰው መሆን እንደሚችል ሄገን እንዲገነዘብ አደረገ ። ጨርሶ ከምድረ ግቢው አይወጣም ። ወይንም ኬሪ አጠገቡ ሳይሆን ማንም ሰው ተቀብሎ አያውቅም ። አንድ የሚያበሽቅ ችግር ብቻ ተፈጠረ ። የኮኒና የካርሎ የበሀር ልጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

በካቶሊክ ቤተክርስቲያን የክርስትና ማረጋገጫ ስነስ ርአት ስለሚፈጸም ኬይ የክርስትና አባት እንዲሆን ሚካኤልን ጠየቀችው ። ሚካኤል እምቢ አለ ።

"ብዙ ጊዜ ለምኜህ አላውቅም ። ይሂኛውን ግን ለኔ አድርግልኝ ። ኮኒ በጣም ትፈልገዋለች ። ካርሎም እንደዚሁ ። ለነሱ ትልቅ ዋጋ አለው ። እባክህ ሚካ ኤል ፣ እሺ በለኝ" አለች ኬይ ። ይህን ጊዜ ችክ በማ ለቷ መናደዱን ተገነዘበችና እምቢታውን ትጠብቅ ነበር ። እሱ ግን በእሺታ ራሱን ሲነቀንቅ ተገረመች ።

"እሺ ግን ከግቢ አልወጣም ። ቄሱ እዚህ መጥቶ ስነ ስርአቱ እንዲፈጸም ንገሪያቸው ። የሚጠየቀውን እኔ እከፍላለሁ ። ይህን በሚመለከት በቤተክርስቲያን በኩል ችግር ቢገጥማቸው ሄገን ሁኔታውን ያስተካክ ለዋል" አላት ።

በዚህ አይነት ከባርዚኒ ቤተሰብ ጋር ስብሰባ ከማ ድረጉ በፊት አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሚካኤል የካር ሎና የኮኒ ሪዚ ልጅ የክርስትና አባት ሆነ ። በጣም ውድ የሆነ የእጅ ሰአትና የወርቅ ማሰሪያ ስጦታም አበ ረከተለት ። በካርሎ ቤት ውስጥ የሻምበል አዛዦቹ ፣ ሄገን ፣ ላምፖኔ እና በምድረግቢው የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ፣ እና መቼም የማትቀረው የሚቹ ዶን ባለቤት በተ ገኙበት ግብዣ ተደረገ ። ኮኒ በስሜት ተውጣ ወንድሟ ንና ኬይን ምሽቱን በሞላ እያቀፈች ስትሰማቸው ነበር ። "እንደመሰለኝ ፣ ካርሎና ማይክ እውነተኛ ወዳጅ እየ ሆኑ ነው ። ይህን የመሰለው ነገር ሰዎችን ያስተሳሰራ ቸዋል" አለች ኮኒ ።

ኬይ የባሏን እህት ክንድ ጨመቅ አድርጋ "እሰ የው! በጣም ደስ ብሎኛል" አለቻት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ ሰምንት

ምእራፍ ሰላሳ

አልበርት ኔሪ በብሮንክስ የመኖሪያ አፓርተማው ውስጥ ሆኖ ሰማያዊውን የቀድሞ የፖሊስ የደምብ ልብሱን ይቦርሻል ። የደረት ላይ ምልክቱን ፈታና ሊወለ ውል ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው ። ሽጉጡ እና ግሀ ደሩ ወንበር ላይ ተንጠልጥለዋል ። ጥንት አዘውትሮ ይሰራው የነበረው ይህን የመሰለ የእለት ተእለት ተግባሩ ትውስ ሲለው ተደሰተ ። ይቺ ቅጽበት ባለፉት ሁለት አመታት ከተደሰተባቸው ጥቂት ጊዜያት አንዷ ነበረች ።

እሱ አዲስ ቅጥር ፖሊስ ሳለ ፣ ወዳጁ ሪታም ሁለ ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትማር በነበረበት ወቅት ነበር የተጋቡት ። አይን አፋርዋ ፣ ጥቁር ጸጉር ያላት ሪታ ፣ ከምሽቱ አራት ሰአት በኋላ ውጭ እንድትቆይ የማይፈቅዱላት ፣ ጥብቅ የጣሊያን ወላጆች ነበሯት ። ኔሪ በልበ ንጹህነቷ ፣ በብልህነቷ እና በጠይም ውበቷ ተማርኮ ፈጽሞ በፍቅሯ ሞቶ ነበር ።

በመጀመሪያ ሪታ በባሏ እጅግ ተማርካ ነበር ።ኔሪ ሲበዛ ጉልበተኛ በመሆኑና ስህተት ወይም ትክክል መስሎ በሚታየው ነገር ባለው የማያወላውል አቋም ሰዎች ሲፈሩት ታያለች ። ፈጽሞ ዘዴ አልባ ነበር ። ከግለሰቦ ቦች ወይም ከብዙ ሰዎች ጋር በሀሳብ ካልተጣጣመ አፉን ዘግቶ መቀመጥ ወይም ፍርጥ አርጎ ተቃውሞ ውን መግለጽ ይወዳል ። እውነተኛ የሲሲሊያዊ ጸባይ ያለውና ቁጣውም አስፈሪ የሆነ ግለሰብ ነው ። ካለው ነገር ግን ሚስቱን ተቆጥቷት ወይም ተጣልቷት አያውቅም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

[illegible] አመታት ጊዜ ውስጥ ኤሪ በኒውዮርክ የፖሊስ ሀይል እጅግ ከሚፈሩ ሰዎች አንዱ ሆነ ። እጅግ ታማኝ ከነበሩትም ፖሊሶች አንዱ ነበር ። ነገር ግን ህግን የሚያስከብርበት የራሱ ልዩ ዘዴ ነበረው ። ወሮበሎችን ይጠላ ነበር ። ረብሸኛ ወጣቶች በየመንገዱ ዳር ማታ ማታ ሲበጠብጡ ካገኛቸው ፈጣንና ወሳኝ እርምጃ ይወስዳል ። ከመጠን በላይ የሆነ ፥ ራሱ እንኳን ልኩን በውል የማያውቀው የጉልበት እርምጃ ይወስዳል ።

አንድ ማታ በሴንትራል ፓርክ ዌስት ፥ ጥቁር የሀር ኮት የለበሱ ስድስት ወጣቶች አይቶ ከመኪናው ዘሎ ከወጣ በኋላ ስድስቱንም ግድግዳ አስጠግቶ በሰልፍ ደረደራቸው ። የስራ ባልደራባው ግን የኤሪን ጸባይ ስለ ሚያውቅ በጉዳዩ ጣልቃ ላለመግባት ሲል ከመኪናውም አልወረደ ። ስድስቱ ልጆች ሁሉም በአስራዎቹ አመታት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው ። ሰዎችን እያስቆሙ በወጣት አጥፊነት ባህሪ ሲጋራ ስጡን ከሚሉ በስተቀር በማንም ሰው ላይ የአካል ጉዳት አላ ደረሱም ። ወጣት ሴቶችን ሲያገኙ ደግሞ ከአሜሪካ ኖች ይልቅ የፈረንሳዮች በሆነ ዘይቤ በብልግና ቃላት ያላግጡባቸዋል ።

ኤሪ ስድስቱንም ሴንትራል ፓርክን ከተከታዩ መን ገድ ጋር ከሚያካልል የድንጋይ ግድግዳ ላይ አስደግፎ አሰለፋቸው ። ጊዜው ግና አመሻሽ ላይ ቢሆንም ኤሪ የሚወደውን እና ዘወትር የማይለየውን አንድ ትልቅ ባትሪ ይዟል ። ሽጉጡን መምዘዝ አይታሰበውም ። አስፈላጊም አይደለም ። ሲናደድ ፊቱ ያውሬ ይሆንና ከዚያ የደንብ ልብሱ ጋር ወሮበሎችን ያስደነግጣቸዋል ። የዛሬዎቹ ወጣቶች ከዚህ ሁኔታ አልተለዩም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጀመሪያውን ጥቁር የሀር ጃኬት የለበሰውን ወጣት ስሙን ጠየቀው ። ወጣቱ የአይርሽ ስም ነገረው ። "በል ከዚህ መንገድ ጥፋ! ሁለተኛ በዚህ ምሽት ውስጥ በዚህ አካባቢ ባይህ እሰቅልሀለሁ!" ብሎት በባትሪው አቅጣጫውን ሲያሳየው ልጁ በፍጥነት እየተራመደ ሄደ ። የሚቀጥሉትን ሁለት ወጣቶችም እንዲሁ አደረገ ። ኢጣሊያዊ ስም ያለው አራተኛው ወጣት ግን ከኔሪ ጋር ዝምድና ያለው ይመስል ፈገግ አለ ። ኔሪ ይህን ወጣት ለቅጽበት ያህል ተመለከተውና ኢጣሊያዊ ነህ?" ሲል አስፈላጊ ያልሆነ ጥያቄ አቀረበለት ። ልጁም በልበ ሙሉነት ፈገግ አለ ።

ይህን ጊዜ ኔሪ በባትሪው ግንባሩን ተረከከው ። ልጁም በጉልበቱ ወደቀ ። የግንባሩ ቆዳና ስጋ ተሰን ጥቆ ደም ፊቱ ላይ ይወርድ ጀመር ። ነገር ግን የስጋ ቁስል ብቻ ነበር ። ኔሪ ጭካኔ በተሞላበት አነጋገር ፥

"አንተ የውሻ ልጅ!" አለው ። "አንተ የኢጣሊያኖች ማፈሪያ ነህ ። አንተ ነህ ሁላችንንም የምታሰድበን ። በል በል ተነሳና ቁም አሁን" አለው ። አሁንም ጮኑ ላይ ጎሰመውና ፥ "ሂድ ቤትህ ። መንገድ ላይ እንዳትታይ ። ሁለተኛ ያንን ጃኬት ለብሰህ እንዳላይህ! አለዛ ሀኪም ቤት ነው የምልክህ ። በል አሁን ወደ ቤት ሂድ ! አባትህ ባለመሆኔ እድለኛ ነህ!"

ኔሪ የቀሩትን ሁለት ወጣቶች ምንም ያህል አልተቆጣቸው ። ቂጥ ቂጣቸውን በጫማ ከረገጣቸው በኋላ በዚያ ምሽት ሁለተኛ በዚያ መንገድ ላይ እንዳያያቸው አስጠንቅቆ አባረራቸው ።

እንዲህ ባለው ግርግር ድርጊቶች ሁሉ ባስቸኳይ ከመከናወናቸው የተነሳ ሰዎች ለመሰብሰብ ወይም የኔሪን ድርጊት ለመቃወም የሚያስችላቸው ጊዜ አልነበረም ። ኔሪ መኪናው ውስጥ ሲገባ ጓደኛው ይዞት

t.me/OLDBOOKSPDF

ይጠፋል ። መቸስ ፥ አልፎ አልፎ ከባድ ጉዳይ ያጋጥ ምና እንደባደብ የሚሉ ወይም ጩቤ የሚመዙ አይጠ ፉም ። እንደዚህ ያሉት ሰዎች በእርግጥ እድለ ቢሶች ናቸው ። ኔሪ በሚያስፈራ ጭካኔ ደብድቦ ደም በደም ያደርጋቸውና ከመኪናው ውስጥ ይወረውራቸዋል ። ይታ ሰሩና 'በፖሊስ መኰንን ላይ አደጋ ለመጣል በመሞከ ራቸው' ይከሰሳሉ ። ነገር ግን ጉዳያቸው ከህኪም ቤት እስኪወጡ ይቆያል ።

በመጨረሻ ኔሪ የተባበሩት መንግስታት ህንጻ ወደ አለበት መስመር ተቀየረ ። ለቅያሪው ምክንያት የሆነው ለክልሉ ሀምሳ አለቃ ተገቢውን ክብር ባለማ ሳየቱ ነበር ። የተባበሩት መንግስታት ስራተኞች ባላ ቸው የዲፕሎማቲክ ከለላ በመመካት መኪኖቻቸውን የፖሊስ ስነ ስርአት ሳይጠብቁ የትም ያቆማሉ ። ኔሪ ለክልሉ ሁኔታውን ቢያመለክት የተቃውሞ ማእበል እንዳይቀሰቅስ ችላ ብሎት እንዲያልፍ ተነገረው ። ነገር ግን አንድ ቀን በግድ የለሽነት በቆሙ መኪናዎች ምክ ንያት መንገዱ ማስተላለፍ አልቻለም ። ጊዜውም ከእኩ ለ ሌሊት በኋላ ነበር ። ስለዚህ ኔሪ ትልቁን ባትሪ ውን ከመዘዋወሪያ መኪናው ውስጥ አወጣና በመንገዱ ያቆሙትን መኪናዎች የፊት መስታወት አንድ በአ ንድ አደቀቀው ። ሌላው ቀርቶ አቅም ላላቸው ከፍተኛ ደረጃ ዲፕሎማቶች እንኳ የመኪኖቻቸውን የፊት መስታ ወቶች ጥቂት ቀናት ሳይፈጁ ማስጠገን አልቻለም ። ለክ ልሉ ፖሊስ ጣቢያ ይህን ከመሰለ አረመኔ እርምጃ ከለላ በመጠየቅ ተቃውሞ ጮረፈ ። ያህል የፊት መስ ተዋቶች ከተሰበሩ ከሳምንት በኋላ ሰባሪው ማን እንደሆነ ቀስ በቀስ ታወቀ ። አልበርት ኔሪ ወደ ሀርለም ተቀየረ ።

ከዚያ በኋላ አንድ ቀን እሁድ ኔሪ ባቷ የሞተባ ትን እህቱን ለመጠየቅ ከሚሰቱ ጋር ሆኖ ወደቤቷ ሄደ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አልበርት ኔሪ እንደማንኛውም ሲሲሊያዊ ለእህቱ ሀይ ለኛ የሆነ የጋሻነት ፍቅር አለው ። ቢያንስ ቢያንስ ደህ ንነቷን ለማረጋገጥ በሁለት ወር አንዴ ይጐበኛታል ። እህቱ የብዙ ጊዜ ታላቁ ስትሆን ፣ እድሜው ሀያ አመት የሆነ ወንድ ልጅ አላት ። ቶማስ የተባለው ይኸው ልጅዋ የአባት ቁጥጥር በማጣቱ ያስቸግራታል ። በአንዳንድ ትናንሽ ረብሻዎች ውስጥ እየገባ አውሬ ሆኗል ። አንድ ጊዜ በዘረፋ ወንጀል ላይ ተሰማርቶ ተይዞ ኔሪ ባለው ግንኙነት ከመከሰስ አስጥሎታል ። ያን ጊዜ ንዴቱን ለመቆጣጠር ቢሞክርም ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠው አላ ለፈም ።

"ቶሚ ፣ እህቴን ብታስለቅሳት ልክ የማገባህ እኔ ነኝ" ብሎታል ።

ያኔ እንዲህ ሲለው ወዳጃዊ የአጐት ማስጠንቀ ቂያ እንጂ ለማስፈራራት አልነበረም ። ቶሚ በብሩክ ሊን ሰፈር የታወቀ ሀይለኛ ወጣት ቢሆንም አጐቱን አልን ይፈራዋል ።

በዚያ የጉብኝታቸው እለት ቶሚ ባለፈው ቅዳሜ አምሽቶ በመግባቱ ከመኝታው ገና አልተነሳም ነበር ። እናቱ መኝታ ቤቱ ሄዳ ተነስቶ ልብሱን እንዲለብስና የሰንበት ምሳቸውን ከአጐቱና ከአክስቱ ጋር እንዲበሉ ቀሰቀሰችው ። የልጁ ስድ አንደበት ጨርሶ ባለተዘጋው በር ዘልቆ ተሰማ ።

"አላቅልሽም ! ይልቅስ ልተኛበት" አላት ። እናቱ በቅሬታ ወደማድቤቷ ተመለሰች ።

ስለዚህ ምሳቸውን እሱ በሌለበት በሉ ። ኔሪ እህ ቱን ልጅዋ ያስቸግራት እንደሆነ ሲጠይቃት እንዲጣሉ ስላልፈለገች ራሷን በአሉታ ነቀነቀች ።

ኔሪና ሚስቱ ሊሄዱ ሲሉ ቶሚ ከመኝታው ተነስቶ መጣ። በወጉ ሰላም ሳይላቸው ወደ ማድቤት አልፎ ሄደ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ስሚ፣ አንቺ እማ ፡ የምበላው አብስይልኝ እስቲ" ብሎ ጮኸ ። አንጋገሩ በጥንቃቄ አልነበረም ። የአንድ ቀበጥ ሰድ አደግ ሀጻን አንጋገር ነበር ። እናቱም በቀ ጭን ድምጽ ፣

"የምሳ ሰአት ሲደርስ በጊዜ ተነስተህ መብላት ትችላለህ ። እንደገና ተነስቼ ላንተ አልቀቅልም" አለ ችው ። ከዚያ በኋላ የተከተለው ደስ የማይል ሁኔታ ነበር ። ቶሚ ገና ከእንቅልፉ በደንብ ባለመንቃቱ እንደ መብሸቅ ብሎ ስለነበረ

"አንቺና ጭቅጭቅሽ ገደል ግቡ ! ውጭ ሂጂ እበላ ለሁ" ካለ በኋላ ይህን በመናገሩ አዘነ ።

ይህን ጊዜ አጮቱ አል ፡ አንዲት ድመት አይጥ ላይ ዘላ ገብ እንደምትል ላዩ ላይ ወጣበት ። አልን ያና ደደው የዚያን እለቱ የልጁ ሰድነት ብቻ ሳይሆን ይህ ልጅ ሁል ጊዜ ከእናቱ ጋር ብቻቸውን ሲሆኑ እንዲህ ይናገራታል የሚል ስሜት ስለተፈጠረበት ነው። ቶሚ እናቱን ወንድሟ ፊት ክፉ ንግግር ተናግራት አያ ውቅም ነበር ። የዚያን እሁድ እለት ግን መጥፎ እድል ጠራ ።

በሁለቱ የተደናገጡ ሴቶች ፊት አልበርት ኔሪ የእ ሀቱን ልጅ ይቅርታ የሌለበት ግን ጥንቃቄ የተሞላበት የአካል ቅጣት ሰጠው ። በመጀመሪያ ጊዜ ቶሚ ለመ ከላከል ሞክሮ ነበር ። ግን ወዲያው ተስፋ ቆርጦ ምህረት ይለምን ጀመር ። ኔሪ የልጁ ከንፈር እስ ኪያብጥና እስኪደማ ድረስ በጥፊ አጮለው ። እንደገና ራሱን አወዛወዘና ከግድግዳ ጋር አጋጨው ። ሆዱን ጐሰመው ። ወደፊት ገፍትሮ ፊቱን ከወለሉ ምንጣፍ ጋር በጥፊ አላተመው ። ሁለቱን ሴቶች እንዲቆዩት ከነ ገራቸው በኋላም ቶሚን በጥበቃ መኪናው ውስጥ አስ ገባው ። ከመኪናው ውስጥ አስቀምጦ ፍርሀት ለቀቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

በት ።"ሁለተኛ እንደዚያ የምትናገር መሆንህን እህቴ ከነገረችኝ ያኔ የምገርፍህ አሁን የመታሁህን ምት በእን ዲት ወዳጅህ እንደመሰም ያስቆጥረዋል ። ልክ እንድትገባ እፈልጋለሁ ። በል አሁን ግባና ሚስቴን እዚህ እንደም ጠብቃት ንገራት" አለው ።

ይህን ባደረገ በሁለት ወሩ ሲሰራ ከቆየበት ጥበቃ ተራ ሲመለስ ሚስቱ እቃዋን ሁሉ ጭና ጥላው ወደ ዘመዶቿ መሄዷን ተረዳ ። የሄደችበትን ምክንያት አባቷ ለኔሪ ሲገልጽለት ፡ ስለ ፈራችውና በዚህ ጸባዩ አብራው ለመኖር ስጋት ስላደረባት መኩበለሏን አስረዳው ። አል ይህን ሲሰማ ማመን አቆቶት ደነዘዘ ። ሚስቱን ደብድቧት አያውቅም ። በምንም ምክንያት አስፈራርቷ ትም እንኳን አያውቅም ። ስለሷ ፍቅር እንጂ ሌላ ነገር ተሰምቶትም አያውቅም ። ነገር ግን ጥላው መሄዷ ግራ አጋብቶት ጥቂት ቀናት ይለፉ በማለት ወደ ወላጆቿ ቤት ሳይሄድ ቆየ ።

ሌላው መጥፎ አጋጣሚ በተከታዩ ሌሊት በጥበቃ ተራው ጊዜ እክል ውስጥ መግባቱ ነበር ። መኪናው ውስጥ ባለው መገናኛ አማካይነት በሀርለም ውስጥ ምት ሊያስከትል የሚችል ጸብ መነሳቱን የሚገልጽ መልእክት ሰማ ። እንደልማዱ መኪናው ጨርሶ ሳይቆ ም ኔሪ ዘሎ ወጣ ። ጊዜው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነው ። እንደተለመደው ትልቁን ባትሪውን ይዟል ። ችግሩ የደ ረሰበትን አካባቢ ለማግኘት አስቸጋሪ አልነበረም ። በመኖሪያ ቤቶች መግቢያ አካባቢ ሰዎች ተሰብስበዋል ።

"ከዚያ ቦታ አንድ ሰውዬ አንዲትዋን ትንሽ ልጃ ገረድ እየቆራረጣት ነው" አለችው ።

ኔሪ ወደ መተላለፊያው አመራ ። በአንድ የመጨ ረሻው ጠርዝ ላይ የሚገኝ ክፍት በር ውስጥ መብራት ይበራል ፡ ለቅሶም ይሰማል ። ባትሪውን እንደያዘ በክ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍቷ በር ዘልቆ ሲገባ ሁለት ወለሉ ላይ የተዘረጉ ሰዎች ላይ ሊወድቅ ነበር ። አንዷ እድሜዋ ሀያ አም ስት ሌላይቱ ደግሞ ከአስራ ሁለት የማይበልጥ ልጃገ ረዶች ሲሆኑ ፥ ሁለቱም ጥቁር አሜሪካውያን ናቸው ። ሁለቱም ፊታቸውና መላ ገላቸው በስለት ተሸ ረካክቶ ደም በደም ሆነዋል ። ኔሪ እዚያው እንግዳ ቤቱ ውስጥ ይህን አደጋ ያደረሰውን ሰውዬ አየው ። ሰውዬ ውን ኔሪ በሚገባ ያውቀዋል ።

ይህ ሰው ዋክስ ቤይንስ የተባለ የታወቀ አቃጣሪ፤ አደንዛዥ እጽ ሻጭና በመደባደብና በማስፈራራት የሚ ያስገብር ነው ። አይኑ በአደንዛዥ እጽ ፈጦ ጭቤውን ይሰብቀዋል ። ከሁለት ሳምንታት በፊት ይህ ሰው አን ዷን ሴተኛ አዳሪ ወዳጁን ስለደበደባት ኔሪ አስሮት ነበር ። ቤይንስ ያኔ ኔሪን ፥

"ስማ ሰውዬ ፥ አንተን የሚያገባህ ነገር የለም" ብሎት ነበር ። የኔሪ የስራ ባልደረባም ጥቁሮች ከፈለ ለጉ እርስ በርሳቸው ሲጨፋጨፉ ቢውሉ ችላ እንዲላ ቸው ቢነግረውም ኔሪ ግን ቤይንስን ህግ ፊት አቅርቦ ታል ። ቤይንስ በነጋታው በዋስ ተለቋል ።

ኔሪ ጥቁሮችን ብዙም አይወዳቸውም ። በሀርለም እንዲሰራ ከተመደበ በኋላም ጥላቻው ይበልጥ አየለ ። ወንዶቹ አደንዛዥ እጽ ሲወስዱ ወይም ሲሰክሩ ሚስቶ ቻቸው ግን ሲማስኑ ወይም ገንዘብ ፍለጋ ወንድ ሲያሳ ድዱ ይታያሉ ። አይወዳቸውም ። ስለዚህ የቤይንስ በድ ፍረት ህግ መጣስ ኔሪን አውሬ አደረገው ። በስለት የተቆራረጠችውን ትንሽ ልጃገረድ ማየትም እጅግ ሰቀ ጠጠው ። ፍጹም በቀዘቀዘ ስሜት ወደፍርድ ላለማቅረ ረብ በአእምሮው ወሰነ ።

ነገር ግን ኋላ ምስክርነታቸውን መስጠታቸው የማ ይቀረው ከህንጻው ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችና የስራ ባል

t.me/OLDBOOKSPDF

ደረባው ተከትለውት ገብተው ከኋላው ተኮልኩለዋል ።

ኔሪ ቤይንስን ፥ "ጩቤህን መሬት ጣል ፥ ከአሁን ጀምሮ በእስር ላይ ነህ" አለው ።

ቤይንስ ሳቀና ፥ "ሰውዬ ፥ እኔን ለማሰር ሽጉጥህን መጠቀም ይኖርብሀል" ብሎ ፤ ጩቤውን ከፍ አደረገና "ወይስ ምናልባት ይህችን ትፈልግ ይሆን ?" አለው ።

ኔሪ ጓደኛው ሽጉጡን ከመምዘዙ በፊት በከፍተኛ ፍጥነት ተንቀሳቀሰ ። ጥቁሩ ጩቤውን ቢያቃናበትም የኔሪ ልዩ የሆነ የስሜቱ ታዛዥነት የቃጣበትን ጩቤ በግራ መዳፉ ለመከላከል አበቃው ። በቀኝ እጁ የቃጣው ባትሪ ቤይንስን አናቱን ስላገኘው እንደሰከረ ሰው በአስቂኝ ሁኔታ ጉልበቱን አጠፈው ። ጩቤው ከጁ ወደቀ ። መልሶ ሊማታ የማይችል ፥ ዝም ቢሉት የማ ይንቀሳቀስ ሆነ ። ጉዳዩ ለፍርድ በቀረበበት ወቅት ሁለ ተኛው የኔሪ በትር በቀረበው መረጃ መሰረት አስፈ ላጊ አልነበረም ። ኔሪ አናቱን በባትሪ ሲበረቅሰው ከምቱ ሀይለኛነት የተነሳ የባትሪው መስተዋት መከላከያና የባ ትሪው አይን ረገፉ ። የባትሪው ጠንካራ የአሉሚንየም ቀፎ በውስጡ ያለው የባትሪ ድንጋይ ባይዘው ኖሮ ጨርሶ ለሁለት በታጠፈ ነበር ። አንድ የደነገጠ ጥቁር ተመልካች ለፍርድ ቤት በኔሪ ላይ በመመስከር ሰው የው ላይ የተሰነዘረውን ዱላ ክብደት በመግለጽ በሰ ጠው ቃል ፤

"እናንተ ፥ ያ ጥቁር ጠንካራ አናት አለው" ብሏል ።

ነገር ግን እንደተባለው የቤይንስ አናት ጠንካራ አልነበረም ። ምቱ አናቱን ሰርስሮታል ። ከሁለት ሰአት በኋላ በሆስፒታል ውስጥ ሞተ ።

አልበርት ኔሪ ከሚያስፈልገው በላይ በመሳሪያ ተጠቅመሀል በሚል መከሰሱ በጣም አስደነቀው ። ከሳ ራው ታማኙ በግድያ ወንጀል ተከሰሰ ። ከአንድ እስከ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስር አመት የሚደርስ እስር ተፈረደበት ። ኔሪ በመላው ህብረተሰብ ላይ ቁጣና ጥላቻ ተፈጠረበት ። ያን የመሰለ አውሬ አቃጣሪ ጥቁር ገደልክ ብለው እሱን እስር ቤት ሲልኩት ፣ እነዚያ ሴቶች እንደዚያ ሆነው አካላቸው ተቆርራጦና እድሜ ልካቸውን መልካቸው ተበላሽቶ እስካሁን ህኪም ቤት መሆናቸው ግን ስሚት የሰጠው የለም ።

ኔሪ እስር ቤቱን አልፈራውም ። ፖሊስ በመሆኑና በተለይም የሰራው ጥፋት የሰራ ስህተት ተደርጐ ስለሚቆጠር በእስር ሲቆይ እንከብካቤ እንደሚደረግለት ገምቶ ነበር ። ብዙዎቹ ጓደኞቹ የሆኑ መኰንኖችም ለወዳጆቻቸው እንደሚነግሩለት አረጋግጠውለት ነበር ። በብሮንክስ የአሳ ሱቅ ባለቤት የሆነው ብልጣ ብልጠ የሚስቱ አባት ኔሪን የመሰለ ሰው በስር ቤት ውስጥ ለአንዲት አመት እንኳ በህይወት የመቆየት እድሉ አነስተኛ እንደሚሆን ገመተ ። አንዱ ሊገለው ይችላል ። ካልሆነም እሱ አንዱን እንደሚገድል እርግጠኛ ነበር ። ልጁ ጥሩ ባልዋን ባልረባ ምክንያት በመከዳትዋ ጸጸት የተሰማው የኔሪ አማች ከኮርሌዎኔ ቤተሰብ ጋር ባለው ግንኙነት ተጠቅሞ በጉዳዩ እንዲገቡበት ለመናቸው ። ይህ ሰው ለቤተሰቡ የከለላ ገንዘብ ይከፍላል ። እንዲሁም በሱቁ ከሚሸጠው አሳ ጥሩውን እየመረጠ ሲልክ ኖሯል ።

የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ስለአልበርት ኔሪ ሰምቷል ። አልበርት ኔሪ በቀላሉ ሊታይ የማይችል ፣ የደንብ ልብሱን ለብሶም ሆነ ሳይለብስ ወይም የተፈቀደለትን መሳሪያ ታጥቆም ሆነ ሳይታጠቅ ብዙ አድናቆትን የተቀዳጀ ለአ ብነት የሚጠቀስ ሀይለኛ የፖሊስ አባል ነው ። የኮርሌ ዎኔ ቤተሰብ ይህን በመሰሉ ሰዎች ላይ ያተኩራል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የፖሊስ አባል መሆኑ ብዙም አላሰጨነቃቸውም ። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች እውነተኛውን እጣቸውን የሚጀምሩት ካልሆነ መንገድ በመነሳት ነው የሚል ግንዛቤ ስላላቸው ነው ። እንዲህ ያሉትን ሰዎች ጊዜ እና እድል ታስተካክላቸዋለች ።

ጥሩ ሰራተኞችን የመመልመል ችሎታ ያለው ፒተር ክሌሜንዛ የኔሪን ጉዳይ ቶም ሄገን እንዲያጤነው አቀረበለት ። ሄገንም ሰውዬውን በሚመለከት የፖሊስ ፋይሉን ግልባጭ ካጠና በኋላ ክሌሜንዛ የሰጠውን አስተያየት በውል አዳመጠው ።

"ምናልባት ሌላ ሉካ ብራሲ አገኘን ማለት ነው" አለ ሄገን ።

ክሌሜንዛ በስምምነት ራሱን በሀይል ነቀነቀው ። ሰውነቱ ወፍራም ቢሆንም ከቶውንም ፊቱ የወፍራም ሰው ደጋደግ መልክ የለውም ።

"እኔም ልክ እንዲያ ብዬ ነው የገመትኩት ። ማይክ ራሱ ይህን ሰውዬ ማየት አለበት" አለ ክሌሜንዛ ።

እንግዲህ ይህ ከሆነ በኋላ አልበርት ኔሪ ከነበረበት ጊዜያዊ እስር ቤት ወደ ዘላቂ እስር ቤቱ ሊዛወር ሲል ዳኛው ከፍተኛ መኰንኖች ባቀረቡለት አዳዲስ መረጃዎችና እማኞች መሰረት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ፍርዱን አሻሻለለት ። እስራቱ 'በገደብ' ሆነለት ።

አልበርት ኔሪ ጅል አልነበረም ። የሚስቱ አባትም የዋህና ልበ ንጹህ እንዳልሆነ ያውቃል ። የተደረገለትን ሁሉ በመረዳቱ የአማቹን እዳ ከሚስቱ ጋር ፍቺ ለማድረግ በመስማማት ከፈለ ። ቀጥሎም ሎንግ ቢች ተጉዞ ለባለውለታዎቹ ምስጋናውን አቀረበ ። እንደሚመጣም ቀደም ብሎ በመታወቁ ሚካኤል በቤተመጻህፍቱ ውስጥ ተቀበለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኔሪ በትህትና ምሲጋናውን ሲያቀርብ ለዚህ ምስ ጋናው በተሰጠው ሞቅ ያለ አጸፋ ተደነቀ ። በጣምም ተደሰተ ።

"ባክህ ተወው" አለ ሚካኤል ። "በአንድ ሲሲሊ ያዊ ያገሬ ልጅ ላይ ይህን የመሰለ ግፍ ሲፈጽሙ እያ የሁ ዝም ብዬ አልመለከትም ። ለፈጸምከው ጀብዱ ሜዳሊያ ነበር መሸለም የሚገባህ ። ነገር ግን እነዚህ እርኩሶች ግፈት የሚያደርጉባቸውን ወገኖች እንጂ ለሌላውማ ከቶውንም ደንታ የላቸውም ። ስማኝ ፥ ሁሉንም ነገር ክትትል አድርጌ ፍትህ የጐደለው ውሳኔ እንዳደረሱብህ ባልረዳ ኖሮ በዚህ ጉዳይ ጣልቃ አልገባም ነበር ። የኔ ሰዎች እህትህን አነጋግረዋት ምንያህል ለሷና ፥ ለልጅዋ እንደምታስብ ፥ እንዴት ልጅዋ እንዳይባልግ ልክ እንዳገባህላት አስረድታቸዋለች ። የሚስትህ አባትም በአለም ላይ እንዳንተ ጥሩ ሰው እንደሌለ ነግሮኛል ። እንዳንተ ያሉ ሰዎች ከስንት አንድ ነው የሚገኙት" ለዘዬው ብሎ የኔሪ ሚስት ጥላው ስለመሄዷ ሚካኤል አላነሳበትም ።

ለአጭር ጊዜ አወሩ ። ኔሪ ለወትሮው ዝምተኛ ሰው ነበር ። ነገር ግን ከሚካኤል ጋር ሲነጋገር ግልጽ ሆነ ። ሚካኤል ኔሪን በአምስት አመት እድሜ ብቻ የሚበልጠው ቢሆንም ኔሪ ግን አነጋገሩ ብዙ አመት እንደሚበልጠው ፥ እንዲያውም በእድሜ ከአባቱ ጋር እንደሚመጣጠን አድርጐ ነበር ።

በመጨረሻ ሚካኤል እንዲህ አለ ፥

"አንተን ከእስር ቤት አውጥቶ ያላንዳች እርዳታ መተው ትርጉም የለውም ። ጥቂት ስራ ላገኝልህ እችላለሁ ። በላስ ቬጋስ ንግድ ለማስፋፋት ፍላጐት አለኝ ። ባለህ ልምድ የሆቴሉ የደህንነት ሰራተኛ ልትሆን ትችላለህ ። ወይም ሌላ አነስተኛ ንግድ ላይ እሰማራለሁ

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትል ከሆነም ፥ ባንኮች እንዲያበድሩህ ላግባባልህ እችላለሁ ”

ኔሪ የቤተሰቡ ውለታ በጣም ከበደው ። ስለዚህ በቁርጥ እምቢታውን ሲገልጽ ፥

“እኔ በገደብ የተፈረደብኝ ስለሆንኩ በፍርድ ቤቱ ስልጣን ክልል ውስጥ መቆየት አለብኝ” አለ ።

ሚካኤል ፈጠን ብሎ ፥ “ያ ሁሉ ዝባዝንኪ ከንቱ ነው ። እኔ አስተካክለዋለሁ ። የነሱን ቁጥጥር እርሳ ። ባንኮችም በሬኮርድህ ምክንያት እንዳያጉላሉህ እንዲፋቅልህ አደርጋለሁ ” አለው ።

ጥፋቱ የሚመዘገብበት ብጫ ወረቀት በፖሊሱ ክፍል መዝገብ ቤት ይቀመጣል ። አንድ ዳኛ በአንድ ተከሳሽ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ግለሰቡ ካሁን ቀደም የተከሰሰበት ወንጀል እንዳለ ለማረጋገጥ ይኸው ብጫ ወረቀት እንዲቀርብለት ያዛል ። ኔሪ ለብዙ ጊዜ በፖሊስ ሰራዊት ውስጥ ስለቆየ ፥ አንድ አጥፊ ተከሶ ለፍርድ ሲቀርብ ፥ ቀድሞ የሰራውን ጥፋት ዳኛው አይቶ ልማደኛነቱን በመገንዘብ ፍርዱን እንዳያጠብቅበት ለፖሊስ ጉቦ ሰጥቶ ንጹህ መዝገብ እንዲቀርብ እንደሚደረግ ያውቃል ። ስለዚህ ሚካኤል ይህን ማድረግ መቻሉ አላስደነቀውም ። ያስደነቀው ግን ለሱ ሲባል ይህን ያህል ለመቸገር ፈቃደኛ መሆኑ ነበር ።

“እርዳታ የምሻ ከሆነ መጥቼ እናገራለሁ”አለ ኔሪ ።

“መልካም ፥ መልካም” አለና ሚካኤል ሰአቱን ሲመለከት ኔሪ ሂድልኝ ማለቱ ነው ብሎ ገመተና ተነሳ ። ነገር ግን ሌላ የሚያስገርም ነገር ገጠመው ።

“የምሳ ጊዜ ነው” አለ ሚካኤል ። “ከኔና ከቤተሰቤ ጋር ትበላለህ ። አባቴም ሊያይህ ይፈልጋል ። ወደ ቤቱ በእግራችን እንሄዳለን ። እናቴ በሲሲሊ አሰራር የተጠበሰ እንቁላል በቃሪያ እና ቋሊማ ታዘጋጃለች ”

t.me/OLDBOOKSPDF

ያ የከሰአት በኋላ ወቅት አልበርት ኔሪ ከልጅነቱ ጀምሮ ፥ በተለይም ወላጆቹ በአስራ አምስት አመቱ ከሞቱ ወዲህ ፥ ከገጠሙት ቀኖች ሁሉ እጅግ የተስማማው አለት ነበር ። ዶን ኮርሌዎኔ ወዶታል ። ኔሪ የተወለደበት መንደር እሱ ከተወለደበት መንደር የጥቂት ደቂቃ ጉዞ እንደሆነ ሲገልጽለት ደስ አለው ። ጨዋታቸው መልካም ፥ ምግቡ ጣፋጭ ፥ የወይን ጠጁም ደመቅ ያለ ቀይ ነበር ። ኔሪ በመጨረሻ በእርግጥ የራሱ በሆኑ ሰዎች መሀከል መሆኑ ተሰማው ። ድንገት እንግዳ መሆኑን ቢረዳም እንዲህ ባለ አለም ውስጥ ደስተኛ ሆኖ የሚኖርበት ዘላቂ ቦታ ሊያገኝ እንደሚችል አወቀ ። ሚካኤልና ዶኑ ወደመኪናው ሸኙት ። ዶኑ እጁን ጨበጠና ፥

"ጥሩ ሰው ነህ አንተ" አለው ። "ልጄን ሚካኤልን የወይራ ዘይት ንግድ እያስተማርኩት ነኝ ። እኔ እያረጀሁ ስለሆነ ማረፍ እፈልጋለሁ ። ሚካኤል እኔ ዘንድ መጥቶ ባንተ ጉዳይ እጁን ሊያስገባ እንደሚፈልግ ነግረኝ ። ያንተን ጉዳይ ትቶ የወይራ ዘይት ንግዱን ብቻ እንዲከታተል ነገርኩት ። እሱ ግን ፈጽሞ አልተው አለ ። 'እየውልህ ፥ አንድ መልካም ሲሲሊያዊ ላይ ተንኰል እየፈጸሙበት ነው' አለኝ ። ያንተን ጉዳይ አልተው ብሎ እኔንም እንድገባበት ገፋፋኝ ። ይህን የማወራልህ በርግጥም ሚካኤል ምን ያህል እውነተኛ እንደሆነ ልነግርህ ብዬ ነው ። አሁን ካየሁህ በኋላ ያን ያህል ጥረት በማድረጋችን ደስ አለኝ ። ስለዚህ ላንተ ልናደርግልህ የምንችላቸው ማናቸውም ጉዳዮች ቢኖሩ አንተ ያለብህ መጠየቅ ብቻ ነው ፥ ገባህ ? አንተን ለመርዳት ዝግጁ ነን" ኔሪ የዶኑን ደግነት ሲያስታውስ ፥ 'ያ ታላቅ ሰው ዛሬ በህይወት ኖሮ እኔ ለቤተሰቡ በመስጠት ላይ ያለሁትን ቅን አገልግሎት በተመለከተልኝ' በማለት ተመኘ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኔሪ በቁርጥ ለመወሰን የፈጀበት ጊዜ ከሶስት ቀን አልበለጠም ። እያባበሉት መሆኑ ቢገባውም ፥ የተረዳው ጉዳይ ከዚያ በላይም ነው ። ህብረተሰቡ ያወገዘውንና መቀጫ የጣለበትን ጉዳይ የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ዋጋ ሰጥቶታል ። ኔሪ በኮርሌዎኔዎቹ አይን ዋጋ አለው ። ህብረተሰቡ ግን ዋጋ አልሰጠውም ። ከድብቁ አለም ውስጥ ተደስቶ ለመኖር እንደሚችል ገባው ። በዚህ ጠበብ ባለው ክልል ውስጥ የሚገኘው የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ከህብረተሰቡ ይበልጥ ሀይለኛ መሆኑንም ተረድቷል ።

ኔሪ ሚካኤልን በድጋሚ ሲጐበኘው የሚፈልገውን ፍርጥ አድርጎ ነገረው ። በቬጋስ መስራት አልፈለገም ። ይልቁንም በኒውዮርክ ከቤተሰቡ ጋር መስራትን መረጠ ። ታማኝነቱን ግልጽ አደረገ ። ሚካኤል በዚህ ውሳኔ መርካቱን ኔሪ ተገነዘበ ። ከዚህ በኋላ ሁሉ ነገር ተደራጀ ። ነገር ግን ኔሪ በቅድሚያ እረፍት እንዲያገኝ ወደ ማያሚ ተጉዞ ወጪው ሁሉ ተችሎለት በቤተሰቡ ሆቴል እንዲያርፍ ፥ በተጨማሪም እንደልቡ በሚገባ ይዝናና ዘንድ የወር ደመወዙን በቅድሚያ እንዲያገኝ ሚካኤል ወሰነ።

ያ እረፍት ኔሪ ለመጀመሪያ ጊዜ የመንደላቀቅን ጣእም የቀመሰበት ወቅት ነበር ። የሆቴሉ ሰዎች ልዩ እንክብካቤ ሲያደርጉለት ፥ "አህ ! አንተኮ የሚካኤል ኮርሌዎኔ ወጃጅ ነህ" ይሉታል ። ትእዛዝ ያርሷቸዋል ። ለማረፊያ የተሰጠው ለአንድ ደህ ዘመድ በግብር ይውጣ የሚሰጠው ክፍል ሳይሆን እጅግ ከተዋቡትና ከተሟሉት የሆቴሉ መኖሪያ ቤቶች አንዱን ነው ።የሆቴሉን የማታ ክበብ የሚያስተዳድረው ሀላፊም ቆንጆ ሴቶች አዘጋጅለት ። ኔሪ ወደ ኒውዮርክ ሲመለስ በአጠቃላይ ስለ ህይወት ያለው አመለካከት ለየት ያለ ሆነ ።

በከሌሚንዛ ቡድን ውስጥ ተመድቦ ፥ የሰው ችሎታ በመመዘን ብቁ በሆነው አለቃው በጥንቃቄ የተገመገመ ፥

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሰው ምንም ቢሆን በአንድ ወቅት ፖሊስ ስለነበር አንዳንድ ጥንቃቄዎች አስፈላጊ ነበሩ ። ነገር ግን የኔሪ ተፈጥሯዊ አውሬነት ከቀድሞ ተቃራኒዎቹ በኩል በመቆሙ የሚሰማውን ማናቸውንም የህሊና ጥያቄ ደመሰሰው ። አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማንነቱን አስመሰከረ ። ከእንግዲህ ወደ ቀድሞው ከቶ አይመለስም ።

ክሌሜንዛ አደነቀው ። ኔሪ ተአምረኛ ሆነ ፣ አዲሱ ሉካ ብራሲ ተገኘ ። ከሉካ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል በማረጋገጥ ክሌሜንዛ ጉራውን ነዛ ። ምንስ ቢሆን ክሌሜንዛ አይደል የመለመለው! አጠቃላይ አቋሙ ሲታይ ንቃቱ እና አእምሮው ከመላ ሰውነቱ ጋር መቀናበሩ የሚያስደንቅ ነበር ። ክሌሜንዛ ሌላው የተገነዘበው ነጥብ ኔሪ እሱን በመሰለ ሰው ቁጥጥር ስር የማይውል መሆኑን ነው ።

ኔሪ አንዳንድ የእለት ተለት ስራዎችን ከቶም ሄገን ጋር ይሰራ እንጂ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለሚካኤል ኮርሌዎኔ ሆነ ። 'ልዩ' በመሆኑ ከፍተኛ ደመወዝ ተቆርጦ ለታል ። የቁማር ቤት ወይም የዘረፋ ተግባር የመሳሰለ ሌላ መተዳደሪያ የለውም ። ለሚካኤል ኮርሌዎኔ ያለው ክብር እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ ቶም ሄገን እንደቀልድ አድርጎ ሚካኤልን እንዲህ አለው ፣

"ደህና ግሩም ነው ። አሁንስ የራስህን ሉካ አግኝተሀል"

ሚካኤል በመስማማት ራሱን ነቀነቀ ። እራሱ ከውድቀት አዘቅት ያወጣው በመሆኑ ከእንግዲህ አልበርት ኔሪ እስኪሞት ድረስ ከሚካኤል ጐን ይቆማል ። ይህችም ብልሀት ከዶኑ ከራሱ የተገኘች ናት ። ሚካኤል የቤተሰቡን ስራ ሲያጠና ፣ ለረዥም ቀናት አባቱ የሚሰጠውን ትምህርት ሲከታተል ሳለ ፣ አባቱን እንዲህ ሲል ጠይቆት ነበር ። "እንዴት አድርገህ ነው ብራሲን በመሰለ አውሬ ሰው የምትጠቀመው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶኑ ሚስጥሩን ሲገልጽለት ፥ "በዚህ አለም ላይ ሞትን በመሻት የሚቅነዘነዙ ሰዎች አሉ" አለው ። እነሱን ልብ ብለህ ሳትመለከት አልቀረህም ። ቁማር ላይ ይጣላሉ ፥ የመኪናችን መከላከያ ተጫረ ብለው እሳት ለብሰው እሳት ጐርሰው ከመኪና ዘለው ይወጣሉ ። አቅመን በማያውቁት ሰው ላይ ይደነፋሉ ፥ ያዋርዱ ታል ። እንዲህ ያለ ሰው ፥ እንዲያ ያለ ጅል ፥ አንዳች ችም መከታ ሳይዝ አደገኛ የሆኑ ሰዎችን ያቀፈ ቡድን እንኳን ሲያስፈራራ አይቻለሁ ። ይህን የመሰሉ ሰዎች "ግደሉኝ ፥ ግደሉኝ ፥ እያሉ ይቅበዘበዛሉ ። ታዲያ ምን ጊዜም ቢሆን ፍላጐታቸውን የሚያረካ ፈቃደኛ ሰው ይኖራል ። ሁልጊዜ ይህን ስለመሰለው ታሪክ በጋዜ ጦች ላይ እናነባለን ። እንዲህ ያሉ ሰዎች በሌሎች ላይም ትልቅ ጉዳት ያደርሳሉ ።

"ሉካ ብራሲ ይህን የመሰለ ሰው ነበር ። ነገር ግን ፈጽሞ ልዩ ሰው በመሆኑ ለረዥም ጊዜ ማንም ሊገድለው አልቻለም ። ይህን የመሰሉ ሰዎች አብ ዛኛዎቹ ለኛ ምናችንም ላይሆኑ ይችላሉ ። እንደ ብራሲ ያለ ሰው ግን ሀይለኛ መሳሪያ ነው ። ይህ ሰው ሞትን አይፈ ራም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ይፈልጋታል ። ዘዴው እን ግዲህ በዚች አለም ላይ እንዲገድለው የማይፈልገው ሰው አንተ ብቻ እንድትሆን ማድረግ ነው ። ያለው ፍራቻ ይህ ብቻ ነው ፥ ሞትን ሳይሆን ምናል ባት የምትገድለው አንተ እንዳትሆን ። ከዚህ በኋላ ይህ ሰው ያንተ ነው "

ዶኑ ከመሞቱ በፊት ሚካኤል ከሱ ካገኛቸው ዋና ትምህርቶች ይህ አንዱ ነበርና እሱም ኤሪን ልክ የራሱ ሉካ ብራሲ በማድረግ የተማረውን በተግባር አዋለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እናም አሁን ፥ በመጨረሻ ላይ ፥ አልበርት ኔሪ ብቻውን በብሮንክስ መኖሪያ ቤቱ ሆኖ እንደገና የፖሊስ ልብሱን ሊያጠልቅ ነው ። ልብሱን በጥንቃቄ ቦረሸው ። ቀጥሎ የሚያጸዳው የሽጉጡን ማህደር ይሆናል ። የፖሊስ መለዮውንም እንዲሁ ። የፊት መከለያው መጽዳት አለበት ። ጠንካራው ጥቁር ጫማው ይወለወላል ። ኔሪ በሙሉ ፈቃድ ሁሉንም ሰራ ። በአለም ላይ ትክክለኛ ቦታውን አግኝቷል ። ሚካኤል ኮርሌዎኔ ሙሉ እምነቱን ጥሎበታል ። እና ዛሬ እምነት የጣለበትን ሰው አያሳፍረውም ።

ምእራፍ ሰላሳ አንድ

በዚያኑ እለት ሁለት ምርጥ አውቶሞቢሎች በለንግ ቢች እኮርሌዎኔ ግቢ ቆሙ ። ከነዚህ ትላልቅ መኪናች አንዱ ኮኒ ኮርሌዎኔን ፥ እናቷን ፥ ባሏንና ሁለት ልጆቿን ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ለመውሰድ ትጠባበቃለች ። የካርሎ ሪዚ ቤተሰብ ወደ ላስ ቬጋስ ለዘለቄታው ከመዘዋወሩ በፊት እረፍት ወስዶ ቦታውን ያየዋል ። ኮኒ ይህን ትእዛዝ ብትቃወምም ትእዛዙን ለካርሎ ያስተላለፈው ሚካኤል ነው ። ሚካኤል የባርዚኒና የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት በምድረ ግቢው ያለው ሰው ሁሉ ለቆ እንዲሄድ መፈለጉን ለማስረዳት ግድ አልነበረውም ። በእርግጥም የስብሰባው መካሄድ በከፍተኛ ሚስጥርነት ተይዟል ። ስለዚህ ስብሰባ ያውቁ የነበሩት የቤተሰቡ ሹሞች ብቻ ነበሩ ።

ሌላዋ አውቶሞቢል ኬይ እና ልጆቿን ወደ ኒው ሃምሻየር የሷን ዘመዶች እንዲጐበኙ የምታጓጉዝ ነበረች ። ሚካኤል ከባድ ስራ ስለገጠመው በግቢው መቆየት ይኖርበታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም ባለው ምሽት ካርሎ ሬዚ ለጥቂት ቀናት በግቢው ውስጥ እንዲቆይ ሚካኤል የሚፈልግ መሆኑ መልእክት ደርሶታል ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር እንደሚቀላቀል ተነግሮታል ። ኪኒ ይህን ስትሰማ እብድ ሆና ነበር ። ሚካኤልን በስልክ ልታነጋግረው ብትሞክርም ወደ ከተማ ሄዷል ተባለች። አሁን በምድረግቢው ውስጥ በአይኗ ብትፈልገው ኩቶም ሄገን ጋር በሚስጥር ዝግ ስብሰባ ላይ ስለነበረ ማንም ሰው ከስብሰባው ሊያሰናክለው አልፈቀደም ። ካርሎ ከመኪና ውስጥ ሲያስገባት ኪኒ ሳመችውና :

"በሁለት ቀን ውስጥ ካልመጣህ እኔ እራሴ ልወስድህ እመለሳለሁ" ስትል አስጠነቀቀችው ።

ካርሎ ፍቅር የሚጠራ ትህትና የተሞላበት ፈገግታውን አሳያትና "እመጣለሁ" አላት ።

መስኮቱን ወደታች መለሰችና ፥ "ሚካኤል የሚፈልግህ ለምን ይመስልሀል?" አለችው ። ፊቷ በስጋት ተሞልቶ ስለተኮማተረ አሮጊትና ደስ የማትል ፤ አስመሰላት ።

ካርሎ ምክንያቱን አለማወቁን ለመግለጽ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፥

"ብዙ ተስፋ ሲሰጠኝ ነበር ። ምናልባት ያንኑ በሚመለከት ሊያነጋግረኝ ይሆናል ። ጫፍ ጫፉን ምልክት የሰጠኝም ይህንኑ ነው" አላት ። ካርሎ በእለቱ ከባርዚኒ ቤተሰብ ጋር ሊካሄድ ስለታቀደው ስብሰባ አላወቀም ።

ኪኒ በጉጉት "እውነትህን ነው ፥ ካርሎ ?" አለች።

ካርሎ በማረጋገጥ ራሱን ነቀነቀ ። አውቶሞቢላቸው የግቢውን በር ሰንጥቃ ተጓዘች ።

ሚካኤል የመጀመሪያዋ መኪና መውጣቷን ሲያረጋግጥ ብቅ አለና ሚስቱንና ልጆቹን ተሰናበታቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካርሎም መጣና ለኬይና ለልጆቹ መልካም ጉዞና መልካም እረፍት ተመኘላቸው ። በመጨረሻም ሁለ ተኛዋም መኪና ተነስታ መንገዷን ቀጠለች ።

"አዝናለሁ እዚህ ስላቆየሁህ ፣ ካርሎ ። ከሁለት ቀናት በላይ አትቆይም " አለው ሚካኤል ።

ካርሎ "ፈጽሞ ግድየለኝም " ሲል ችኩል ብሎ መለሰለት ።

"መልካም " አለ ሚካኤል ። "ስልክህ አጠገብ ቆየኝ ፣ ዝግጁ ስሆን እጠራሀለሁ ። ከዚያ በፊት ሌሎች የማሰባስባቸው ጉዳዮች አሉኝ "

"ይሁን ፣ ማይክ ፣ ይሁን " አለና ካርሎ ወደቤቱ ሄደ ። ቤቱ እንደደረሰም በቼስትበሪ ካስቀመጣት ወዳጁ ዘንድ ደውሎ ማታ ዘግየት ብሎ ሊገባኛት እን ደሚሞክር ነገራት ። ከዚያ በኋላ ጠርሙስ ዊስኪውን ይዞ ቁጭ ብሎ ይጠባበቅ ጀመር ። ለብዙ ጊዜ ጠበቀ ። ከእኩለ ቀን በኋላ መኪኖች ሲመጡ ተመለከተ ። ክሌ ሜንዛ ከአንዷ መኪና ውስጥ ወጣ ። ጥቂት ቆይቶ ቴስ ዮ ከሌላይቱ መኪና ውስጥ ብቅ አለ ። ሁለቱንም ከጠባ ቂዎቹ አንዱ ሚካኤል ወዳለበት ክፍል አስገባቸው ። ክሌ ሜንዛ ጥቂት ቆይቶ ወጣ ። ነገር ግን ቴስዮ ተመልሶ አል ታየም ።

ካርሎ በግቢው ውስጥ በመንሸርሸር ለአስር ደቂቃ ያህል አየር ተቀበለ ። ከግቢው ጠባቂዎች ጋር ከመተዋወቁም በላይ እንዲያውም ከአንዳንዶቹ ጋር ወዳጅ ነው ። ጊዜ ለማሳለፍ ከነሱ ጋር ጥቂት ላውራ ብሎ አሰበ ። ነገር ግን ያስገረመው ፣ ከጠባቂዎቹ መሀል አንድም የሚያውቀው ሰው የለም ። ሁሉም አዳዲሶች ሆነበት ። ሌላ ቀርቶ ከዋናው በር ለጥበቃ የተሰማ ራው ሮኮ ላምፖኔ ነበር ። ልዩ ጉዳይ ካልገጠመ በስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀር እንዲህ ያለው አነስተኛ ስራ ሮኮ ካለው ደረጃ ጋር የሚጣጣም አልነበረም ።

ሮኮ የወዳጅነት ፈገግታ አሳይቶ ሰላም አለው ። ካርሎ ጠንቀቅ አለ ።

"ስማ ፥ ከዶኑ ጋር ለእረፍት የምትሄድ መስሎኝ ነበር" አለው ሮኮ ።

ካርሎ ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ፥"ማይክ ለአንድ ሁለት ቀናት በአካባቢው እንድቆይ ፈልጓል ። እኔ የምሰራው ጥቂት ስራ አዘጋጅቷል" አለ ።

"እህስ!" አለ ሮኮ"እኔንም እንዲሁ ። ታድያ በሩን እንድቆጣጠር ነው ያዘዘኝ ። እንግዲህ እኛ ምንቸገረን አለቃ እሱ ነው"

የሮኮ ላምፓኔ አባባል ሚካኤል አባቱን የሚወዳደር ሰው አለመሆኑን የምትገልጽ የንቀት አነጋገር ናት ።

ካርሎ ይህቺን ንቀት ችላ ብሎ ፥"ማይክ የሚያደርገውን የሚያውቅ ሰው ነው" አለው ። ሮኮ ዘለፋውን በዝምታ ተቀበለው ። ካርሎም ደህና ሁን ብሎት ወደ ቤቱ ተመለሰ ። አንድ ነገር እየተደረገ ነው ። ሮኮ ግን ምን እንደሆነ አላወቀም ።

ሚካኤል እንግዳ ቤቱ መስኮት አጠገብ ቆሞ ካርሎ ወደቤቱ ቀስ እያለ ሲያመራ ተመለከተው ። ሄገን ሀይ ለኛ ብራንዲ አመጣለት ። ሚካኤል በምሲጋና ተቀብሎ ጠጣው ። ከበስተጀርባው የቆመው ሄገን "ማይክ ፥ ወቅቱ ደርሷል ። እንቅስቃሴ መጀመር አለብህ አለው ።"

ሚካኤል በረዥሙ ተነፈሰና ፥"እንዲህ ባፋጣኝ ባይሆን እመኝ ነበር ። ሽማግሌው ለጥቂት ጊዜ ቢኖር ምንያህል ደስ" ባለኝ አለ ።

"ምንም የሚሰናከል ነገር አይኖርም" አለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ። "እኔ ያልወደቅሁ ማንም አይወድቅም ። ጥሩ አድርገህ አቀነባብረኸዋል "

ሚካኤል ከመስኮቱ ዞር አለ ። "አብዛኛውን ያቀደው ሽማግሌው ነበር ። ያን የመሰለ ብልህ ሰው መሆኑን ያኔ አላጤንኩትም ። ነገር ግን አንተ ታውቅ ነበር ይመስለኛል"

"ማን እንደሱ?" አለ ሄገን ። "ግን ያንተውም እጅግ ግሩም ነው ። እንዲያውም እንከን የለበትም ።ስለ ዚህ አንተም የምትሰራው መጥፎ አይሆንም"

"እስኪ እንግዲህ የሚሆነውን እንይ ። ለመሆኑ ከሌሚንዛና ቴስዮ በግቢው ውስጥ ናቸው?"

ሄገን ራሱን በመነቅነቅ አዎንታውን አረጋገጠለት ። ሚካኤል ብርጭቆው ውስጥ ያለውን ብራንዲ ጨለጠና ፥

"ከሌሚንዛን ወደኔ ላከው ፥" አለ ። "በግሌ መመሪያ እሰጠዋለሁ ። ቴስዮን ላየው አልፈልግም ። በግማሽ ሰአት ውስጥ ወደነባርዚኒ ስብሰባ አብሬው ስለም ሄድ እንዲጠብቀኝ ብቻ ንገረው። ከዚያ በኋላ የከሌሚንዛ ሰዎች ያስተናግዱታል"

ሄገን አቋም በማይገልጽ ድምጽ ፥ "ለቴስዮ ምህረት ለማድረግ የሚቻልበት መንገድ አይኖርም ?" ሲል ሚካኤልን ጠየቀው ።

"ምንም መንገድ የለ " ሲል መለሰ ሚካኤል ።

ከበፍሎ ከተማ በሰተሜን የምትገኝ አንዲት ፒሳ መሸጫ ቤት የጦፈ ገበያ አላት ። የምሳ ሰአት እንዳለፈ ግርግሩ ቀዝቀዝ ሲልላት ሻጩ የፒሳ ትራፊ የያዘውን ክብ የቆርቆሮ ትሪ ከመስኮቱ ላይ አንስቶ ከትልቅ የሸክላ ምድጃ መደርደሪያ ላይ አኖረው ። ምድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጃው ውስጥ እየበሰለ ያለውን ፒሳ አየች አደረገ ። ላዩ ላይ ያለው አይብ ገና መንተክተክ አልጀመረም ። ወደ መሸጫው ጠረጴዛ ዞር ሲል አንድ ደልደል ያለ ወጣት ቆሟል ። ሰውየው ፥ "አንድ ፒሳ ስጠኝ" አለ ።

ፒሳ ሻጩ ከእንጨት በተሰራ መዛቂያው ከቀዘቀዙት ፒሳዎች አንዱን ምድጃ ውስጥ ከቶ ሊያሞቅ አነሳ ። ተመጋቢው ውጭ ከመቆም ወደውስጥ ዘልቆ ሊመገብ ፈለገ ። ሱቁ ውስጥ በዚህ ጊዜ ከነሱ ሌላ ማንም ሰው የለባትም ። ሻጩ ምድጃውን ከፍቶ ትኩሱን ፒሳ አወጣና በወረቀት ሳህን አቀረበለት ። ተመጋቢው ግን ገንዘቡን በመክፈል ፋንታ ትክ ብሎ ይመለከተው ነበር ።

"ደረትህ ላይ አሪፍ ንቅሳት አለህ አሉ ። በሸሚዝህ ዘልቆ ይታየኛል ። በሙሉ ብታሳየኝ ?" ሲል ተመጋቢው ጠየቀው ።

ሻጩ በድንጋጤ ደነዘዘ ።

"ከፈት ሸሚዝህን" አለ ሰውዬው ።

ሻጩ እራሱን በእምቢታ ነቀነቀው ። "እኔ ምንም ንቅሳት የለኝም" አለ እንግሊዝኛ ለመናገር እየከበደው ። "ንቅሳት ያለው ሰውዬ የማታው ተረኛ ነው"

ተመጋቢው ከት ብሎ ሳቀ ። ሳቁ ደስ የማይል ፥ ጭካኔና ውጥረት የተሞላበት ነበር ። "ቶሎ በል ፥ ሸሚዝህን ፍታውና ልየው" አለው ።

ሻጩ ምድጃውን ከለላ ለማድረግ ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመረ ። ነገር ግን ተመጋቢው እጁን ከመሸጫው ጠረጴዛ ላይ ብቅ ሲያደርግ ሽጉጥ ይዟል ። ሲተኩስ ጥይቷ የሻጩን ደረት መታችውና ከምድጃው ጋር ተላተመ ። እዚያው እንዳለ ሲደግመው መሬት ላይ ተዘረረ ። ተመጋቢው ወደ ውስጥ ገባና የሰውዬውን ሸሚዝ ሲከፍተው ደረቱ በደም ተበክሏል ። ነገር ግን እነዚያ የተሳሰሩ ፍቅረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኖች ጩቤው እንደተሰካባቸው የተሳሉበት ንቅሳት በግልጽ ይታያል ። ሻጩ ደመነፍሱን ራሱን እንደሚከላከል እጁን አነሳ ። ተኳሹ ግን እንዲህ አለው ፥

"ፋብሪዚዮ ፥ ሚካኤል ኮርሌዎኔ ሰላምታ ልኮልሀል"

ይህን ካለ በኋላ ከአናቱ ላይ አስጠግቶት የነበረውን ሽጉጥ እንደገና አባረቀው ። ከዚህ በኋላ ከሱቁ ወጥቶ በሩን ከፍቶ ወደሚጠብቀው መኪና ውስጥ ዘሎ ሲገባ መኪናው በረረ ።

በመግቢያው በር ላይ የተተከለው ስልክ ጭርር ሲል ሮኮ ላምፖኔ አነሳው ። "እቃህ ተዘጋጅቶልሀል" የሚል ድምጽ ሰማ ። ከዚህ በኋላ ስልኩ ተዘጋ ። ሮኮ መኪናው ውስጥ ገብቶ ግቢውን ለቆ ሄደ ። ሶኒ የተገደለበትን የባህር ዳርቻ መንገድ አልፎ ወደ ባቡር ጣቢያው አመራ ። ከዚያ መኪናውን አቆማት ። አንድ ሁለት ሰዎች የያዘች ሌላ መኪና ትጠብቀዋለች ። አብረው ወደ አንድ ሆቴል ቤት አምርተው ከግቢው ውስጥ ገቡ ። ሮኮ ሁለቱን አብረውት የነበሩ ሰዎች ከመኪናው ውስጥ ትቶ ወደ አንዲ ጐጆ መሳይ መኖሪያ ቤት አመራ ። በሩን በእርግጫ ሲመታው ማጠፊያው ሲበር ሮኮ ዘሎ ገባ ።

የሰባ አመቱ ፊሊፕ ታታሊያ እንደ ሀጻን እርቃኑን ሆኖ አንዲት ወጣት ልጅ ከተጋደመችበት አጠገብ ቆሟል ። የፊሊፕ ታታሊያ ችምችም የራስ ጸጉር ጥቁረቱ ጢስ ይምሰል እንጂ መላው ጸጉሩ ነጭ ሽበት ነው ። ሰውነቱ እንደ ወፍ ገላ ልስልስ ብሏል ። ሮኮ አራት ጥይት በሆዱ ረጨበት ። ከዚያ በኋላ ተመልሶ ወደ መኪናው ሮጠ ። ሁለቱ ሰዎቹ ባቡር ጣቢያ ሲያወርዱት ከራሱ መኪና ገባና ወደ ኮርሌዎኔ ግቢ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተመለሰ ። ሄዶ ሚካኤል ኮርሌዎኔን ካየው በኋላ ወደ ዘብ ጥበቃ ቦታው ተመለሰ ።

አልበርት ኔሪ የደንብ ልብሱን አዘጋጅቶ ጨረሰ ። ቀስ ብሎ ሱሪውን ፣ ሸሚዙን ፣ ካራቫቱን ፣ የሽጉጥ ማህ ደሩንና የሽጉጥ ቀበቶውን ታጠቀ ። ያኔ ከፖሊስነት ሲባረር ሽጉጡን አስረክቧል ። ነገር ግን ባንዳንድ አስ ተዳደራዊ ችልታ የተነሳ የፖሊስ ምልክት 'ጋሻውን' አልመለሰም ። ክሌሜንዛ አድራሻው የማይገኝ አዲስ ባለ 38 ካሊበር ስፔሻል ሽጉጥ አስታጥቆታል ። ኔሪ ሽጉጡን ፈትሾ ዘይት ቀባው ። ቀጥሎም መምቻውን መርምሮ ፣ እንደገና ገጣጥሞ ቃታውን ሳበው ። ከዚያ በኋላ ጥይት አጉርሶ ለመሄድ ተዘጋጀ ።

የፖሊስ መለዮውን በጠንካራ የወረቀት ከረጢት ውስጥ ጨምሮ ያዘና የፖሊስ ልብሱን ለመሸፈን የሲ ቪል ካፖርት ደረበ ። ሰአቱን ተመለከተ ። መኪናዋ መጥታ ታች እስክትጠብቀው ገና አስራ አምስት ደቂቃ ይቀራል ። አስራ አምስቱን ደቂቃ ያሳለፈው እራሱን በመስታወት ሲቆጣጠር ነበር ። በማያጠራጥር ሁኔታ እውነተኛ ፖሊስ መስሏል ።

መኪናዋ ሁለት የሮኮ ላምፖኔን ሰዎች ከፊት ይዛ ትጠብቀዋለች ። ኔሪ ከኋላ ተቀመጠ ። መኪናዋ የመ ኖሪያውን አካባቢ ለቃ መሀል ከተማ ስትዘልቅ የሲ ቪል ካፖርቱን አውልቆ መኪናው ወለል ላይ ተወው። የወረቀት ከረጢቱን ከፈተና የፖሊስ መለዮውን አው ጥቶ አናቱ ላይ ደፋው ።

አምሳ አምስተኛው መንገድና አምስተኛው አቨ ኒው ላይ ሲደርሱ መኪናዋ ዳር ያዘች ። ኔሪ ወጥቶ የእ ግር ጉዞውን ጀመረ ። ድሮ ለብዙ ጊዜ ያደርግ እንደነ በረው በመንገድ ላይ መዘዋወሩ ልዩ ስሜት ፈጠረ

t.me/OLDBOOKSPDF

በት ። ብዙ ህዝብ ይታያል ። ሮክፌለር ማእከል እስ ኪደርስ ወደ መሀል ከተማ በእግሩ ተጓዘ ። መንገዱ ላይ የሚፈልጋትን አውቶሞቢል ተመለከተ ። 'ማቆም ክልክል ነው' በሚል ምልክት መሀል ብቻዋን ቆማ ለች ። ኔሪ እርምጃውን ቀነሰ ። ጥቂት ቀደም ብሏል ። በመጥሪያ ወረቀቱ ላይ ለመጻፍ ቆም አለና እርምጃ ውን ቀጠለ ። ከአውቶሞቢሏ ፊት ለፊት ሆኖ የግጭት መከላከያዋን በዱላው መታ መታ አደረገው ። ይህን ጊዜ ሹፌሩ ቀና ብሎ በመገረም ተመለከተው ። ኔሪ 'ማቆም ክልክል ነው' የሚለውን ምልክት አሳየውና ሹፌሩ መኪናውን እንዲያነሳ አዘዘው ። ሹፌሩ ፊቱን ወደሌላ አዞረበት ። ኔሪ ሹፌሩ ወዳለበት ክፍት መስኮት አመራ ። ሹፌሩ ጉልበተኛ የሚመስል ኔሪ ሊደበድባቸው የሚወ ደው አይነት ወመኔ ነው ። ኔሪ አውቆ ለማናደድ ስለ ፈለገ በዘለፋ አነጋገር ፥

"በል የኛ ጮሌ ፥ መጥሪያ ቂጥህ ላይ እንድለ ጥፍ ትፈልጋለህ ወይንስ ከዚህ ትነሳለህ ?" አለው ።

ሹፌሩ በቸልታ "የክልል አለቆችህን ብታማክር ይሻ ልሀል ። ደስ የሚልህ ከሆነ መጥሪያ ስጠኝ" አለው ።

"ድራሽ አባክ ይጥፋ ከዚህ ! አለበለዚያ ከመኪ ናህ አውጥቼ እርግጫ እንዳላቀምስህ" አለ ኔሪ ። ሹፌሩም አስር ብር አውጥቶ አጣጠፈና ኔሪ ኪስ ውስጥ ሊሸጉ ጥለት ሞከረ ። ኔሪ ወደኋላ አፈገፈገና ሹፌሩን በጣቱ ጠራው ። ይህን ጊዜ ሹፌሩ ከመኪናው ወጣ ።

"የመንጃ ፈቃድህንና የምዝገባ መረጃህን አሳየኝ" አለው ኔሪ ። የኔሪ ፍላጐት ሹፌሩን ከዚያ ለማራቅ ነበር ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ አሁን አላመቸ ውም ። በጨረፍታ ሶስት ከበድ ያሉ አጫጭር ሰዎች የፕላዛን ህንጻ ደረጃ ወርደው ወደ መንገዱ ሲመጡ ተመለከተ ። እነዚህ ሰዎች ባርዚኒና ሁለት ጋሻ ጃግሬዎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቹ ሲሆኑ ፡ ከሚካኤል ኮርሌዎኔ ጋር ሊሰበሰቡ መሄ ዳቸው ነው ። አንዱ ጋሻ ጃግሬ የነኔሪን ሁኔታ ተመለ ከተና የባርዚኒ መኪና ምን እንደደረሰባት ለማየት ከመሀከላቸው ተግንጥሎ መጣ ።

ይህ ሰው ፡ "ምንድነው እሱ?" ሲል ሹፌሩን ጠየቀው ።

ሹፌሩም ቁርጥ ቁርጥ በሚል አነጋገር ፡ "መጥ ሪያ እየተሰጠኝ ነው ። የሚያሰጋ ጉዳይ አይደለም ። ይህ ሰው ለዚህ ክልል አዲስ መሆን አለበት" አለው ።

ይህን ጊዜ ባርዚኒ ከሌላው ጋሻ ጃግሬው ጋር ሆኖ ደረሰ ።

"ደሞ ምን ጣጣ ተፈጠረ?" ሲል አንቧረቀ ። ኔሪ የጥሪ መዝገቡ ላይ ጽፎ ጨረሰና ለሹፌሩ የመንጃ ፈቃ ዱን መለሰለት ። መመዝገቢያ ደብተሩን የጐን ኪሱ ውስጥ ከተተና እጁን ዘለቅ አድርጎ ባለ 38 ካሊበር ሽጉጡን መዘዘ ። ወዲያው ፡ ጠባቂዎቹ እራሳቸውን ለመ ከላከል ከመደፋታቸው በፊት ፡ ሶስት ጥይት በባርዚኒ ደረት ላይ ለቀቀበት ። ኔሪ ከመቅጽበት ከዚያ ህዝብ መሀል ጠልቆ ማእዘኑ ላይ ከሚጠብቀው መኪና ውሰጥ ገባ ። መኪናዋ ከዘጠነኛው አቬኒው ገብታ ወደ መሀል ከተማ ዘለቀች ። ቻልሲ መናፈሻ አጠገብ ሲደርሱ ሽጉ ጡን እና የደምብ ልብሱን አውልቆ መኪናዋ ውስጥ ከተወ በኋላ ሌላ ልብስ ቀይሮ ወደ ሌላ መኪና ተዛወረ ። ከአንድ ሰአት በኋላ ሎንግቢች ኮርሌዎኔ ግቢ በሰላም ደርሶ ከሚካኤል ኮርሌዎኔ ጋር ያወራ ነበር ።

ቴስዮ ሽማግሌው ዶን ቤት ቁጭ ብሎ ቡናውን እየ ጠጣ ሳለ ቶም ሄገን መጣና ፡

"ማያክ ተዘጋጅቷል ። ወደ ባርዚኒ ደውልና መንገዱን እንዲጀምር ንገረው" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቴስዮ ግድግዳው ላይ የተንጠለጠለውን ስልክ አን ስቶ ኒውዮርክ ከሚገኘው የባርዚኒ ቢሮ ደውሎ ፥

"ወደ ብሩክሊን ለመጓዝ ተነስተናል" ሲል መልእክት አስተላለፈ ። ስልኩን ከዘጋው በኋላ ፥

"ማይክ ዛሬ ማታ ደህና ውል እንደሚዋዋል ተስፋ እደርጋለሁ" በማለት ሄገንን ፈገግታ አሳየው ።

ሄገን በሀዘን ፥ "እንደሚፈጽመው እርግጠኛ ነኝ" ሲል መለሰለት ። ሄገን ከቴስዮ ጋር ሆኖ ከማድ ቤቱ ወጥተው ወደ ሚካኤል ቤት አመሩ ። በሩ ላይ ያሉት ልዩ ጠባቂዎች አስቆሟቸው ።

"አለቃችን በሌላ መኪና ነው የምመጣው ብሏል።ሁለ ታችሁ አብራችሁ ሂዱ ተብላችኋል" አለ አንዱ ጠባቂ ።

ቴስዮ ፊቱን አጨፍግጐ ወደ ሄገን ዞረና ፥

"ኤድያ ፥ እንዲህ ማድረግ የለበትም ። ያመቻቸ ኋቸውን ነገሮች ሁሉ ያበላሻቸዋል" አለ ።

በዚህ ወቅት ሌሎች ሶስት ልዩ ጠባቂዎች ከበቧ ቸው ። ሄገን በቀስታ ፥

"እኔም ካንተ ጋር አልሄድም ፥ ቴስዮ" አለው።

ቴስዮ ከመቅጽበት ነገሩ ገባውና ተቀበለው ። በዚያች ቅጽበት የአካል ዝለት ታየበት ። ከዚያ በኋላ ግን እን ደገና አንሰራራና ሄገንን እንዲህ አለው ፥

"ማይክን የስራ ጉዳይ ሆኖብኝ ነው በለው ። እወደው ነበር"

ሄገንም ፥"ይገባዋል" በማለት እራሱን በእሺታ ነቀነቀው ።

ቴስዮ ለአፍታ ዝም አለና ፥ በቀስታ ፥ "ቶም ፥ስለ ድሮው ብለህ ከዚህ ጉድ ታወጣኛለህ?" ሲል ተማ ጠነው ።

ሄገን እራሱን በአሉታ ነቀነቀና ፥ "አልችልም" ሲል መለሰለት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሄገን ቴስዮ በጠባቂዎች ተከቦ ወደሚጠብቀው መኪና ሲያመራ ተመለከተ ። ትንሽ እንደማመም አለው። ቴስዮ በኮርሌዮኔ ቤተሰብ ውስጥ ዋናው ጐበዝ ወታደር ነበር ። ሽማግሌውም ከሉካ ብራሲ በስተቀር ከማንም ይበልጥ በሱ ላይ እምነት ነበረው ። ይህን የመሰለ ብልህ ሰው ይህን አይነት ለሞት የሚያደርስ ስህተት በዚህ እድሜው መፈጸሙ አሳዘነው ።

ካርሎ ሪዚ ሚካኤል እንዲያነጋግረው ሲጠባበቅ ሳለ ወጭ ገቢውን ማየቱ እረፍት ነሳው ። በግልጽ እንደተግነዘበው አንድ አቢይ ጉዳይ እየተካሄደ ነው ። እሱ የማይገባበት መሆኑንም ተረድቶታል ። ትእግስት አጥቶ ለሚካኤል ስልክ ደወለለት ። ስልኩን ያነሳው ልዩ ጠባቂ ሚካኤልን ሲነግረው ቶሎ ወደሱ የሚመጣ መሆኑን ገልጾ በርጋታ እንዲጠብቀው እንዲነግረው አዘዘው ።

ካርሎ ወደ ወዳጁ እንደገና ደውሎ ዘግየት ብሎ እራት እሚበላበት ቤት እንደሚወስዳትና አብሯት እንደሚያድር እርግጠኛ ሆኖ ነገራት ። ሚካኤል ቶሎ እጮ በኝህለሁ ብሎታል ። ያቀደውን ነገር ለመወያየት ከአንድ ወይም ከሁለት ሰአት በላይ አይፈጅም ። ከዚያ በኋላ ዌስትበሪ ድረስ በመኪና ለመድረስ ከአርባ ደቂቃ በላይ አይፈጅበትም ። ስለዚህ ይቻላል ። ይህን ቃል ገብቶ እንዳታኩርፈው አባበላት ። ስልኩን ከዘጋ በኋላ ለኋላጊዜ ለመቆጠብ ሊለባብስ ወሰነ። ገና ንጹህ ሽሚዝ ከመቀየሩ በሩ ተንኳኳ ። ስልኩን ይዤው ስለነበረ ማይክ በስልክ ሊያገኘኝ ስላልቻለ ሰው ልኮብኝ ይሆናል ብሎ አሰበ ። ሂዶ በሩን ከፈተው ። መላ ሰውነቱ በአሰቃቂ ፍርሀት ተወሮ ዛለ ። በሩ ላይ የቆመው ሚካኤል ኮርሌዮኔ እራሱ ነው ። ፊቱ ያ ካርሎ ሪዚ በህልሙ እያየ ሚፈራውን ምትን ይመስላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚካኤል በስተጀርባ ሄገንና ሮኮ ላምፖኔ ነበሩ ። እነሱም ለአንድ ወዳጅ የግዳቸውን መጥፎ ዜና ይዘው የመጡ ይመስል ኮምጨጭ ብለዋል ። ሶስቱም ወደ ቤቱ ሲገቡ ካርሎ ወደ ሳሎኑ መራቸው ። ከመጀመሪያው ድንጋጤ ሲያንሰራራ የነርቭ ህመም ያመመው መሰለው ። የሚካኤል ቃላትም በእርግጥ ህመምተኛ የሚያደርጉ ስለነበሩ አቅለሸለሸው ።

"ለሳንቲኖ ሞት ተጠያቂ ነህ" አለ ሚካኤል ።

ካርሎ ምንም መልስ አልሰጠም ። ያልገባው መሰለ። ሄገንና ላምፖኔ በየበኩላቸው ወደ ትይዩ ግድግዳዎች አፈግፍገው ጥግ ጥግ ያዙ ። ካርሎ እና ሚካኤል ፊት ለፊት ተገጣጠሙ ።

"ሶኒን ለባርዚኒ ሰዎች የጠቆምከው እንተ ነህ" አለው ሚካኤል በቀጥታ ። "ያችን ትንሽ ተውኔት ከእህቴ ጋር በመጣላት ብትጫወት የኮርሌዎኔን ቤተሰብ ማታለል ትችላለህ ብሎ የነገረህ ባርዚኒ ነው ?"

ካርሎ ክብሩን አዋርዶ ፥ ኩራቱ በሙሉ ጭልጥ ብሎ ጠፍቶ ፥ በፍርሀት ሲቃ እንዲህ አለ ፥

"እኔ ፈጽሞ ንጹህ ነኝ ፤ እምላለሁ ። በልጆቼ ፤ እምላለሁ ፥ ንጹህ ነኝ ። ማይክ ፥ እባክህ በእኔ ላይ ይህን አትፈጽም ። ማይክ ፥ እባክህ ምንም አታድርግኝ"

ሚካኤል በዝግታ እንዲህ አለው ።

"ባርዚኒ ሞቷል ። ፊሊፕ ታታሊያም ። ዛሬ የቤተሰቡን ሂሳብ ለመዝጋት እፈልጋለሁ ። ስለዚህ ንጹህ ነኝ ብለህ አትንገረኝ ። ያደረግከውን ብትናዘዝ ይሻልሀል "

ሄገንና ላምፖኔ ሚካኤልን በመገረም ተመለከቱት ። ሚካኤል ግና ከአባቱ እኩል አልሆነም ሲሉ አሰቡ ። ለምንድነው ይህንን ከሀዲ ጥፋቱን እንዲናገር

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚፈልገው ? አንድን ነገር ማረጋገጥ በሚቻለው መጠን ሁሉ እሱ እንዳደረገው ተረጋግጧል ። መልሱ የታወቀ ነው ። ሚካኤል መብቱን ገና ሙሉ በሙሉ አልተማመነበትም ። አሁንም ፍትህ አጓድላለሁ ብሎ ይፈራል ። አሁንም ለኢምንት ጥርጣሬ ስጋት አድሮ በት የካርሎ ሪዚ ኑዛዜ ብቻ ነው ጥርጣሬውን የሚፍ ቅለት ።

አሁንም ካርሎ መልስ አልሰጠም ። ሚካኤል በደግ አንደበት ፥

"እንዲህ ብዙ አትፍራ" አለው ። "እህቴን ባል አልባ የማደርጋት ይመስልሀል ? የእህቴን ልጆችስ ያለ አባት ያስቀራቸዋል ብለህ ታስባለህ ? ሌላ ቢቀር ለአ ንዱ ልጅህ የክርስትና አባቱ ነኝ ። የለም ፥ ላንተ የሚ ሰጥህ ቅጣት ቤተሰቡ ውስጥ አንዳችም ስራ እንዳይ ኖርህ ማድረግ ይሆናል ። ቬጋስ ሄደህ ከሚስትህና ከልጆችህ ጋር ተቀላቅለህ እዚያው እንድትቀር እፈል ጋለሁ ። ለኮኒ ቀለብ እቆርጥላታለሁ ። ይህንን ነው የማ ደርገው ። ነገር ግን ንጹህ ሰው ነኝ እያልህ የማሰብ ብቃቴን ንቀህ እንዳታናድደኝ ። ማነው ያነጋገረህ ፥ ታታሊያ ነው ወይስ ባርዚኒ ?"

ካርሎ ሪዚ ስቃይ እንደተመላበት ህይወቱን ለማ ዳን ተስፋ በማድረግ ፥ አለመገደሉ ከስቃይ ገላግሎት፥ ቀስ ብሎ ፥ "ባርዚኒ ነው" ሲል መለሰለት ።

"መልካም መልካም" አለ ሚካኤል በለሰለሰ አንደበት። በቀኝ እጁ ምልክት ሰጠና "አሁን ከዚህ እንድትወጣ እፈልጋለሁ ። ወደ አውሮፕላን ማረፊያ የሚወስድህ መኪና ይጠብቅሀል" አለው ።

ካርሎ ቀድሞ ሲወጣ ሶስቱ ሰዎች ተጠግተ ውት ነበር ። ጊዜው ማታ ነው ። የግቢው መብራቶች ግን ብሩህ አድርገውታል ። አንዲት መኪና መጣች።

t.me/OLDBOOKSPDF

የራሱ መኪና ነች ። ሹፌሩን ሊያውቀው አልቻለም ። ከኋላ በኩል አንድ ሰው ራቅ ብሎ ተቀምጧል ። ላም ፖኔ የፊት በሩን ከፈተና ካርሎ እንዲገባ ምልክት ሰጠው ።

"ለሚስትህ ደውዬ ወደሷ እየሄድህ መሆንህን እነግራታለሁ" አለ ሚካኤል ። ካርሎ ከመኪናዋ ውስጥ ገባ ። የሀር ሽሚዙ በላብ ተነከረ ።

መኪናዋ ወደ ዋናው በር በፍጥነት አመራች ። ካርሎ ከበስተኋላው ያለውን ሰው ያውቀው እንደሆን ለማጣራት ዞር አለ ። ይህን ጊዜ ክሌሜንዛ በተለመደ ቅልጥፍናና ፍጥነት ገመድ ባንገቱ አጠለቀበትና በሀይል ሳበው ። የካርሎ ሰውነት በመንጠቆ እንደተያዘ አሳ ተወራጨ ።

ክሌሜንዛ ቶሎ ገመዱን አጥብቆ ሸመቀቀው ። ካርሎ ሰውነቱ ዛለ ፣ መኪናውም ድንገት በመጥፎ ሽታ ተሞላ ። ሞቱ ሲቀርብ የካርሎ ሰውነት ቋጠሮው ሁላ ላልቶ የተቅጠነጠነ ሰገራውን ሲለቀው ክሌሜንዛ ገመዱን አወጣና ከኪሱ ከተተው ። የካርሎ ሰውነት ከበሩ ጋር ሲጋጭ እሱ ዘና ብሎ ተቀመጠ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መጥፎውን ሽታ ለማስወገድ የመኪናውን መስኮት ከፈተው ።

የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ድል የተሟላ ነበር ። በዚያው የሀያ አራት ሰአት ጊዜ ውስጥ ክሌሜንዛና ላም ፖኔ ጦራቸውን ለቀው ሰርጐ ገቦችን አይቀጡ ቅጣት ቀጧቸው ። የቴስዮ ጦር በአልበርት ኔሪ እንዲመራ ተደረገ ።

የባርዚኒ መወራረጃ ቤቶች ከስራ ውጭ ሆኑ ። ሁለቱ ታላላቅ የባርዚኒ አስገዳጆች በአንድ የጣሊያን ምግብ ቤት ምሳቸውን በልተው ቁጭ ብለው ጥርሳቸውን ሲኮረኩሩ የጥይት ራት ሆኑ ። የፈረስ እሽቅድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምድም የሚያወራርድ አንድ አስቸጋሪ አዋዋይ ከእ ለቱ ውርርድ ደህና ጥቅም አግኝቶ በደስታ ሲመለስ እሱም ተተኩሶበት ሞተ ። በባህሩ ዳር የሚገኙ ሁለት አራጣ አበዳሪዎች የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ቆይቶ ከወራት በኋላ ሬሳቸው በኒው ጀርሲ ረግረግ ውስጥ ተገኘ ።

በዚህ አውሬነት በተሞላበት በትር ሚካኤል ኮር ሌዎኔ ታላቅ ዝና አትርፎ ቤተሰቡን በኒውዮርክ የድብቅ አለም ቤተሰቦች መሀከል ቀድሞ ከነበረው ታላቅ ስፍራ መለሰው ። ክብርን የተቀዳጀው ስለረቀቀ ታክ ቲኩ ብቻ ሳይሆን እጅግ ታላቅ የነበሩት የጠላቶቹ የባርዚኒና የታታሊያ ቤተሰቦች ሹሞች ወደሱ በመቀ ላቀላቸው ጭምር ነበር ።

እህቱ ኮኒ የደረሰባት የእብደት ያህል ድንጋጤና ብስጭት ሰላም ባያሳጣው ኖሮ ፣ ያገኘው ድል ፈጽሞ የተሟላ ይሆን ነበር ።

ኮኒ ልጅዋን ቬጋስ ጥላ ከእናቷ ጋር ወደ ሎንግ ቢች መጣች ። መኪናው ከግቢ እስኪያደርሳት ድረስ ሀዘኗን አምቃ ቆየች ። ግቢ ስትደርስ ግን ወደ ሚካ ኤል ቤት እየሮጠች ሄደች ። በሩን ጥሳ ስትገባ ሚካ ኤልና ኬይ ሳሎን ተቀምጠዋል ። ኬይ ልታጽናናት ወደሷ ለመሄድ ተነስታ ሳለ ኮኒ በወንድሟ ላይ እየ ጮኸች ስትሳደብ ደንግጣ ቆመች ።

“አንተ ቅጣላም ዲቃላ! አባታችን እስኪሞት ጠብ ቀህ ባሌን ገደልከው ። ማንም የሚከለክልህ የለ ፣ ገደልከው አይደል! ሶኒን ያስገደለው እሱ ነው እያልክ ትወቅሰው ነበር ። ሁሉም ይወቅሰው ነበር ። ለኔ ግን ምንም አላሰብክልኝም ። ለኔ አንዳችም ደንታ የለህም ። አሁን እንግዲህ ምን እደርጋለሁ ፣ ምን ልሁን?” አለችና ኮኒ እሪ ብላ አለቀሰች ። ይህን ጊዜ ሁለት የሚካኤል

t.me/OLDBOOKSPDF

ልዩ ጠባቂዎች ከኋላዋ ቆመው ትእዛዙን ይጠብቃሉ።ነገር ግን በቸልታ ቆሞ እህቱ ቁጣዋን እስክታበቃ ጠበቃት።

ኬይ በደነገጠ ድምጽ ፥ "ኮኒ ፥ በጣም ተበሳጭ ተሻል ፥ እንዲህ አትበይ" አለቻት ።

ኮኒ ከቁጥጥር ውጭ ከሆነው ቁጣዋ መለስ አለች ። ድምጿ የሚገድል መርዝ ያለው ይመስ ላል ። "ለምን ይመስልሻል ሚካኤል ሁልጊዜ እንደባዳ የሚሆንብኝ? ለምን ይመስልሻል ካርሎን እዚህ ያቆየው? ይህን ሁሉ ጊዜ ያቆየው ሊገድለው ስላቀደ ነው ። አባቴ በህይወት በነበረበት ወቅት ግን አልሞከረውም ። ያኔ ቢሞክር ኖሮ አባቴ ይከለክለው እንደነበር ያውቃል ። ስለዚህ ቀኑን ጠበቀ ። እኛንም ለማዘናጋት የልጇ የክርስትና አባት ለመሆን ፈቃደኛ ሆነ ። ይህ አረመኔ ዲቃላ! ለመሆኑ ባልሽን የምታውቂው ይመስልሻል ? ባሌን ካርሎን ጨምሮ ምን ያህል ሰው እንደገደለ ታውቂያለሽ? ጋዜጦችን ብቻ አንብቢ ። ባርዚኒን ፥ ታታ ሊያንና ሌሎቹንም የገደላቸው የኔ ወንድም ነው"

ኮኒ እንደገና እንደ እብድ ሆነች ። ሚካኤል ላይ ልትተፋበት ነበር ። ነገር ግን ምራቅ አልነበራትም ።

"ወደ ቤቷ ውሰዷትና ሀኪም ይያት" አለ ሚካኤል ። ሁለት ጠባቂዎች እጅና እጅዋን ይዘው ከቤት አስወጧት ። ኬይ አሁንም ደንግጣለች ፥ ፈርታለች ። ባሏን እንዲህ አለችው ።

"ኮኒ ይህን ሁሉ እንዴት ልትናገር ቻለች ፥ ሚካኤል? ይህን ሁሉ እንድታምን ያደረጋት ምንድነው?"

ሚካኤል ትከሻውን ከፍ ዝቅ አድርጐ ፥ "አእምሮዋን ስታለች" አላት ። ኬይ አይን አይኑን አየችው።

"ሚካኤል ፥ እውነት አይደለም ። እባክህ እውነት አይደለም በለኝ" አለች ኬይ ።

ሚካኤል በመሰልቸት ራሱን ነቀነቀና ፤ በእርግጥ እው

t.me/OLDBOOKSPDF

ነት አይደለም። ለአሁን ብቻ ስለግል ጉዳዩ እንድትጠይቂኝ እፈቅድልሻለሁ። መልስ ልሰጥሽም ፈቃደኛ ነኝ። እመኚኝ ፥ እሷ የምትለው ሁሉ ሀሰት ነው" አላት ።

እንዲህ እንደዛሬው አድርጐ በቀላሉ ሲመልሳት የቻለበት እለት አልነበረም ። አይኗን በቀጥታ ተመለከተው ። በጋብቻ ህይወታቸው እስከዛሬ የገነቡትን መተማመን በመጠቀም እንድታምነው አደረጋት ። እሷም ከዚያ በኋላ ጥርጣሬ አልነበራትም ። በጸጸት ፈገግ ብላ እንዲስማት እቅፉ ውስጥ ገባች ።

"ሁለታችንም መጠጥ ያስፈልገናል" አለችው ። በረዶ ለማምጣት ወደ ማድ ቤት ሄዳ ሳለ የፊት በሩ ተከፈተ ። ከማድ ቤቱ ስትመለስ ክሌሜንዛ ፥ ኔሪ እና ሮኮ ላምፖኔ ከጠባቂዎች ጋር ገቡ ። ሚካኤል እሷ ካለችበት አቅጣጫ ጀርባው ብቻ ነው የሚታየው ። በጐን በኩል ልታየው ብላ ትንሽ ዞር አለች ። ይህን ጊዜ ክሌሜንዛ ባሏን በስርአት ፥

"ዶን ሚካኤል" ብሎ እጅ ነሳው ።

ሚካኤል የታዛዥነት ማረጋገጫቸውን ለመቀበል ሲቆም ሚስቱ ተመለከተችው ። ኬይ የጥንት ሮማውያን ሀውልት ፥ እነዚያ የታሪክ ቅርስ የሆኑ ፥ እነዚያ አምላክ ሰጠን በሚሉት ስልጣን የተከታዮቻቸውን ህይወትና ሞት በመዳፋቸው የጨበጡ ሮማውያን ነገስታት ትዝ አሏት ። ሚካኤል አንድ እጁን ዳሌው ላይ አድርጓል ። ከጐን ስትመለከተው ፊቱ ቀዝቀዝ ያለ ኩሩነትና ሀይልን ተቀዳጅቷል ። ሰውነቱ በማድ የለሽ ነትና በኩራት ተዝናንቷል ። መላ ክብደቱ ትንሽ ወደ ኋላ መለስ ባለው እግሩ ላይ አርፏል ። የጦር አዛ ዦቹ ከፊቱ ቆመዋል ። በዚያ ወቅት ኮኒ ሚካኤልን አድርጓል ብላ የከሰሰችው ሁሉ እውነት መሆኑን ስላወቀች ወደ ማድቤቷ ተመልሳ አለቀሰች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መጽሀፍ ዘጠኝ

ምእራፍ ሰላሳ ሁለት

በብዙ ደም መፋሰስ የተገኘው የኮርሌዎኔ ቤተ ሰብ ድል ፥ ሚካኤል ኮርሌዎኔን በመላ ዩናይትድ ስቴትስ ታላቅ የድብቅ አለም ቤተሰብ ሹም በማድረግ ሙሉ ለሙሉ ለማሳካት ጥንቃቄ የሚሹ የፖለቲካ ግንኙነቶችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነበር ። ይህን ለማድረግ ተጨማሪ አንድ አመት አስፈለገ ። ለአስራ ሁለት ወራት ፥ ሚካኤል ጊዜውን ሁለት ላይ ከፍሎ ገሚሱን ሎንግ ቢች በሚገኘው ዋና ጽህፈት ቤቱ፥ ገሚሱን ደግሞ ላስ ቬጋስ በሚገኘው አዲሱ መኖሪያው አሳለፈ ። ነገር ግን በዚያው አመት መጨረሻ ላይ የኒውዮርክ እንቅስቃሴውን ዘግቶ መላ ንብረቱን ለመሸጥ ወሰነ ። ለዚህ ሲል መላ ቤተሰቡን ለመጨረሻ ጉብኝት ወደ ኒውዮርክ አመጣ ። ለአንድ ወር ይቆዩና ፥ ያላቸውን ጉዳይ ያጠናቅቃሉ ። ኬይም የቤተሰቡን የግል ንብረት መልክ መልክ በማስያዝ ለጭነት ታመቻቻለች ። ሌሎችም አያሌ ጥቃቅን የሚጠናቀቁ ጉዳዮች ነበሩ ።

አሁን የኮርሌዎኔ ቤተሰብ ሊቋቋሙት የማይቻል ሆነ ። ክሌሜንዛም የራሱን የድብቅ አለም ቤተሰብ አቋቋመ ። ሮኮ ላምፖኔ የቤተሰቡ የጦር ሹም ሆነ ።

አልበርት ኔሪ በነቫዳ ላሉ የቤተሰቡ ንብረት የሆኑ ሆቴሎች የደህንነት ሹም ተደረገ ። ሄገንም ሚካኤል በም እራብ ክፍለ ግዛት ባቋቋመው ቤተሰብ አባል ሆነ ።

የቀድሞዎቹን ቂሞችና ቅሬታዎች ለማስወገድ ጊዜው ረዳ ። ኮኒ ኮርሌዎኔ ከወንድሟ ከሚካኤል ጋር ታረቀች ። እንዲያውም ሚካኤል ዘንድ ሂዳ ከጮኸችበት ከአንድ ሳምንት በኋላ ይቅርታ ጠየቀችው ። የተናገረችው ሁሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈጽሞ ሀሰት እንደነበረ ፥ አንዲት ባሏን ያጣች ሴት አእምሮዋን ስትስት የምትዘላብደው ቃል ብቻ እንደነበረ ለኬይ ነገረቻት ።

ኮኒ በቀላሉ አዲስ ባል አገኘች ። እንዲያውም የዝን አመቷን እንኳን ሳትጨርስ አንድ ከኮሌጅ ተመርቆ በኮርሌዎኔ ቤተሰብ ውስጥ በጸሀፊነት ሊሰራ የተቀጠረ መልከ ቀና ኢጣሊያዊ ወጣት አልጋዋን ሰፈረበት ። ለሱም የዶኑን እህት በማግባቱ የወደፊት እድሉ ተከፈተለት ።

ኬይ አዳምስ ከነልጆቿ የካቶሊክን እምነት ትምህርት በመከታተል አማኞቿን አስደሰተቻቸው ። ሚካኤል ግን ልጆቹ ፕሮቴስታንት ቢሆኑ ይመርጥ ነበር።

ኬይ ያልጠበቀችው ጉዳይ ነቫዳን መውደዷ ነበር። አካባቢውን ፥ ተራራ ሸንተረሩን ፥ በረሀውንና ሀይቆቹን ሁሉ ወደደቻቸው ። ሁለቱ ወንዶች ልጆችም የየራሳቸ ውርንጭላ ፈረሶች ይጋልባሉ ። የቤት ሰራተኞችም የውነት ሰራተኞች እንጂ ልዩ ጠባቂዎች አይነት አል ነበሩም ።

ሚካኤል ሰላማዊ ኑሮ ይመራ ጀመር ። የህንጻ ስራ ንግድ ባለቤት ሆኖ ፥ የነጋዴዎች ክበቦች አባል ሆነ ። በበጐ አድራጐት ተግባር ላይ ተሰማርቶ ሰላማዊ ህይ ወት ይመራ ጀመር ። ከኒውዮርክ ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ቬጋስ መምጣታቸው ኬይን አስደስታት ።ኒውዮር ክን ተመልሳ በአይኗም ለማየት አልፈለገችም ። ያኔ ወደ ቬጋስ ሲነሱ እቃዎቿን በሙሉ እንዳያዳግማት ሙልጭ አድርጋ ጭና ፥ አንድ ሀመምተኛ ከሀመሙ ድኖ ከሀ ኪም ቤት ሊወጣ እንደሚጠባበቅ ነበር ለመነሳት የጓጓ ችው ። እንደምኞቷ ቤተሰቡ በሙሉ ጥርግ ብሎ ወደአዲሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

መኖሪያ ተዛወረ ። በሚነሱበት እለት ጧት ኬይ ከመ
ታጠቢያ ቤት ስትወጣ ሚካኤል ፥

"ለምንድነው በየቀኑ ጧት ጧት በትስኪያን የም
ትሄጂው? እሁድ እሁድ እለትስ ይሁን ፤ በየእለቱ ግን
ለምን? እንቺስ ከእናቴም አትሻይ" አላት ። በጭለማው
ውስጥ የራስጌ መብራቱን ፈልጎ አበራው ። ኬይ ከመ
ኝታው ጠርዝ ላይ ሆና ስቶኪንጓን ወደ ላይ ከፍ አደ
ረገች ።

"አዲስ አማኞች እንዴት እንደሆኑ አታውቅም።
በጣም ስርአት አጥባቂዎች ናቸው" አለች ። ሚካ
ኤል ሲደባብሳት የጭኗ ሙቀት ተሰማው ።

"እረፍ ፥ ዛሬ ጧት እቆርባለሁ" ብላው ተነሳች ።
ሊይዛት አልፈለገም ።

"አንቺ እንዲህ አጥባቂ ሀይማኖተኛ ከሆንሽ
ልጆቹንስ እንዴት መደ ቤተክርስቲያን እንዲሄዱ ሳታስገድ
ጃቸው ቀረሽ ?" አላት ።

ጭንቀት ቢሰማትም አነጋገሯ ጥንቃቄ የተሞላበት
ነበር ። ሚካኤል በ'ዶን' አይኑ በጥንቃቄ ፊቷን አጠናው ።

"እነሱ ብዙ ጊዜ አላቸው ። ቬጋስ ካለው ቤታ
ችን ስንገባ ይበልጥ እንዲከታተሉ አደርጋቸዋለሁ"
ብላ ሰማው ወደ ቤተክርስቲያን ሄደች ።

ከውጭ አየሩ እየሞቀ ነው ። የጧት ጸሀይም
ደምቃለች ። ኬይ መኪናዋ ከቆመችበት ስትሄድ እናት
ኮርሌዎሬ የሀዘን ልብሷን ለብሳ ቀድማ ገብታ ጠብቃ
ታለች ። ዘወትር ጧት ቅዳሴ ሳይጀመር አብረው ቤተስ
ኪያን መሳለም የእለት ተእለት ተግባራቸው ሆኗል ።

ኬይ የአሮጊቷን የተሸበሸበ ጉንጭ ሳመችና ከመ
ሪው ጎላ ተቀመጠች ። እናት ኮርሌዎሬም በጥርጣሬ

"ቁርስ በልተሻል " አለቻት ።

"አረ ፈጽሞ" አለች ኬይ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አሮጊቷ በደስታ ራሷን ነቀነቀች ። ኬይ ቀደም ብሎ አንድ ቀን ለቁርባን ሲኬድ ቁርስ መብላት መከልከሉን ረስታ እንደነበር አሮጊቷ ስለምታስውስ ሁልጊዜ ትጠ ረጥራታለች ። አለመድከሟን ለማረጋጋጥ "ደህና ነሽ?" ብላ ትጠይቃታለች ።

ኬይም "አዎን" ብላ ትመልስላታለች ።

ኬይ በተስኪያን ገብታ ስለባሷ ሌላ ህይወት ታስ ባለች ። ከአንድ አመት በፊት በዚያን የጭንቀት ምሽት ሚካኤል በመሀከላቸው ያለውን ፍቅር መከታ አድርጉ ካርሎን አለመግደሉን ዋሽቶ ሲነግራት እንድታ ምነው ያደረጋት ትዝ አላት ።

በመግደሉ ሳይሆን በመዋሸቱ ተቀይማው ልጆቿን ይዛ ጥላው ወደ ዘመዶቿ ሄዳ ነበር ። ሚካኤል የመ ጀመሪያው ቀን ቢደውልላትም ንዴቷ እንዲበርድላት ዝም አላት ። ከሳምንት በኋላ ግን ቶም ሄገን በመኪና ወደ ኒው ሃምሻየር ተጓዘ ።

ኬይ ከቶም ሄገን ጋር ያሳለፈችው ከሰአት በኋላ ረዥ ምና ሰቃይ የተሞላበት አሰቃቂ ወቅት ነበር ። አብ ረው እየተነጋገሩ ወደ ጫካ በእግራቸው ተጓዙ ።

ኬይ ያለወትሮዋ ከመጠን በላይ አፍ አው ጥታ ደስ የማይል ንግግር ተናገረች ።

"ማይክ እዚህ የላከህ እንድታስፈራራኝ ነው? እኔስ የጠበቅኩት ሰዎቻችሁ መትረየሳቸውን ይዘው መጥ ተው አስገድደው መልሰው ይወስዱኛል ብዬ ነበር"

ሄገንን ካወቀችው ጀምሮ አይታበት የማታውቀ ውን ቁጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ያኔ አየችበት ።

"ይህ እስካሁን ሰምቼው የማላውቅ የመጨረሻው አሰጸያፊ የጨቅላ ትርጉም የለሽ ልፍለፋ ነው ። ይህን የመሰለ አነጋገር ፈጽሞ አንቺን ከመሰለች ሴት አልጠብቅም ። ተይ እንጂ ኬይ" አላት ሄገን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ" አለች ።

አረንጓዴውን የገጠር መንገድ በእግራቸው ዘለቁ።

"ለምን ኮበለልሽ ?"

"ሚካኤል ስለዋሸኝ ። ለኮረ ልጅ የጡት አባት ሆኖ ስላታለለኝ ነው ። ከዳኝኮ ። ይህን የመሰለ ሰው ማፍቀር አልችልም ። ከዚህ ሁኔታ ጋር አብሬ መኖር አልችልም ። እሱ የልጆቼ አባት እንዲሆን ልፈቅድለት አልችልም "

"ምን ማለትሽ ነው ?"

አሁን ንዴቷን የምትገልጽበት ምክንያት ስላገኘች ወደሱ ዞራ ፥

"የምለው የእህቱን ባል ገድሏል ነው ። ይኸስ ይገባህል ?" ብላ ጸጥ ካለች በኋላ እንደገና ፥ "እና እኔን ዋሸኝ " አለች ።

በዝምታ ረዥም መንገድ ተጓዙ ። በመጨረሻም ሄገን እንዲህ አላት ።

"ይህ ሁሉ ወሬ እውነት መሆኑን የምታውቂበት ምንም መንገድ የለሽም ። ነገር ግን ለክርክር ያህል ያልሽው እውነት ነው እንበል ። ይህን ስልሽ እውነት ሆኗል ማለቴ አይደለም ፤ አስታውሺ ። በቂ ምክንያቶች ናቸው ብዬ የማስባቸውን ብነግርሽ ወይም አንዳንድ ማሳመኛ ነጥቦች ባነሳልሽስ ?"

ኬይ በንቀት ተመለከተችው ። "ጠበቃ ጐንህን ለመጀመሪያ ጊዜ አሁን ባልከው አየሁት ፥ ቶም ። ግን አልወደድኩልህም "

ሄገን ፈገግ አለና ፥

"ይሁን እሺ ፤ ብቻ አዳምጪኝ" አላት ። "ካርሎ ሶኒን ለምት እንዲበቃ የጠቆመው ቢሆንስ ? ካርሎ ያን

t.me/OLDBOOKSPDF

እለት ኮኒን የደበደባት ሶኒ በቁጣ ወደነሱ ቤት ሲበር ለጠላቶች እንዲጋለጥ አቅዶ እንደሆነስ? ሶኒ የሚሄድበት መንገድ የታወቀ ነው ። ካርሎ ሶኒን ለማስገደል በመር ዳት ገንዘብ ተከፍሎት እንደሆነስ? ያኔ ምን ይሆናል ”

ኬይ ዝም አለች ። ሄገን ቀጠለ ።

“እናም ዶኑ፥ ያ ታላቅ ሰው ፥ የልጁን ሞት መበቀል ሲገባው በሌላ በኩል የልጁን ባል ለመግደል አለመፈለ ጉስ ? ይህ ሁኔታ ከብዶት የሚካኤልን ጀግንነት ስለ ሚያውቅ ወራሹ በማድረግ የከበደውን ሸክም እን እንዲያቀልለትና በቀሉን እንዲወጣለት አድርጐ እንደ ሆንስ ?”

“ያ ሁሉ እኮ ድሮ ያለቀለት ጉዳይ ነበር” አለች ኬይ እያለቀሰች። “ሁላችንም ደስተኞች ነበርን ። ካርሎስ ለምን ይቅርታ ሊደረግለት አልተቻለም ? ሁሉም ሰው ቂሙን ረስቶ ሁኔታዎችን በሰላም ለምን አይቀጥልም ነበር ?”

የሳሩን ሜዳ አልፋ የዛፍ ጥላ ወዳለበት ምንጭ መራችው ። ሄገን ሳሩ ላይ አረፈና በረሸሙ ተነፈሰ ። ዙሪያውን ተመለከተና እንደገና ተነፈሰ ።

“በዚህ አለም ውስጥ እንዲህ ማድረግ ትችያለሽ ለሽ”

“ከእንግዲህ ሚካኤል ያኔ ያገባሁት ሰው አይደለ ለም”

ሄገን ባጭሩ ሳቀና ፥“እሱም ያኔ ያገባሽውን ሰው ቢሆን ኖሮ ይኸኔ ሞቶ ነበር ። አንቺም ባሏ የሞተባት ሴት ሆነሽ ያሁኑ ችግርም አይኖርብሽም ነበር” አላት።

ኬይ ብልጭ ብሎባት እየተመለከተችው ፥ “እን

t.me/OLDBOOKSPDF

ዲህ ስትል ከቶ ምን ለማለት ነው ? በል ቶም ፥ በህይወ ትህ ለአንድ ጊዜ በቀጥታና በግልጽ ተናገር ። ሚካኤ ኤል እንደማይችል አውቃለሁ ። አንተ ግን ሲሲሊያዊ ስላልሆንክ ፥ አንዲትን ሴት ከወንድ እኩል አድርገህም ስለምትመለከት እውነቱን ግልጽ አድርገህ መናገር ትች ላለህ ” አለች ።

አሁንም ሌላ ረኸም ዝምታ ሰፈነ ። ሄገን ራሱን ነቀነቀ ።

“ማይክን በትክክል አልተረዳሽውም ። የተቆጣ ሽው ስለዋሸሽ ነው ። ደህና ፥ ግን እኮ ስለ ስራ ጉዳይ እንዳትጠይቂው አስጠንቅቆሽ ነበር ። ለካርሎ ልጅ የከርስትና አባት ስለሆነ ተቀይመሽዋል። ነገር ግን ይህን እንዲያደርግ የገፋፋሽው አንቺ ነሽ ። እንደ እውነቱ ከሆነ እንዲህ ማድረጉ ሚካኤል በካርሎ ላይ ለሚ ወስደው እርምጃ አስፈላጊ ነበር ። ለዘመናት ሲሰራበት የቆየ ፤ጠላትን የማዘናጋት ዘዴ ነው ” ሄገን ሳቅ የሌለ በት ፈገግታ አሳያት ። “ይሽስ አነጋገር በቂና ግልጽ ሆነልሽ ?” ሲል ጠየቃት ። ኬይ ግን ራሷን ደፍታ ነበር ።

ሄገን ንግግሩን ቀጠለ ። “አሁንም ተጨማሪ ግልጽ መረጃ አቀርብልሻለሁ። ዶኑ ከሞተ በኋላ ሚካኤልን ለመ ግደል ሴራ ተጠንስሶ ነበር ። ማን የሴራው ተባባሪ እን ደሆነ ታውቂያለሽ? ቴስዮ ነበር ። ስለዚህ ቴስዮ መገ ደል ነበረበት ። ካርሎም መገደል ነበረበት ። ምክንያቱም ለጠላት አሳልፎ መስጠት ይቅርታ የሚደረግለት ጥፋት አይደለማ! ሚካኤል ይቅርታ ማድረግ ይችል ነበር ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን አያርሙም ። ሁልጊዜ አደገኛነታቸውን ይቀጥላሉ ። እንደእውነቱ ከሆነ ሚካ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኤል ቴስዮን ይወደው ነበር ። እህቱን ሲበዛ ይወዳታል ። ነገር ግን ቴስዮንና ካርሎን በነጻ ከለቀቃቸው ላንቺና ለልጆቹ ፥ ለመላ ቤተሰቡ ፥ ለኔና ለቤተሰቤ ፥ ያለበትን ግዴታ ችላ ብሎታል ማለት ይሆን ነበር ። እነዚህ ሰዎች ለሁላችንም እድሜ ልካችንን አደገኛ ይሆኑ ነበር ”

ኬይ ይህን ስትሰማ እምባዋ ይወርድ ጀመር ። “ይህን እንድትነግረኝ ነው ሚካኤል እዚህ የላከህ ?”

ሄገን በእውነተኛ መደነቅ ተመለከታት ። “ፈጽሞ። እሱ እዚህ የላከኝ የምትፈልጊው ነገር ሁሉ እንደሚኖርሽ ፥ ልጆችሽን እስከተንከባከብሽ ድረስ ያፈቀደሽን ማድረግ እንደምትችይ እንድነግርሽ ነው ” ብሎ ሄገን ፈገግ አለና ፥ “አንቺ የሱ ዶን መሆንሽን እንድነግርሽ ነው ” አላት ።

ኬይ እጅዋን የሄገን ክንድ ላይ አሳረፈችና ፥ “ሌላውን የነገርከኝን ግን እንድትነግረኝ አልላከህም?” ብላ ጠየቀችው ።

ሄገን አንድ የመጨረሻ ቁምነገር መናገር ያለበት መሆን አለመሆኑን ለመለየት አንገራገረና “አሁንም አልገባሽም ። ዛሬ ያወራሁልሽን ሁሉ ለሚካኤል ብትነግሪው እኔ ሟች ነኝ ። አንቺና ልጆቹ ብቻ ናችሁ በዚህች ምድር ላይ ሊጐዳችሁ የማይፈልገው ” አላት ።

ለአምስት ደቂቃ ያህል በዝምታ ቆዩ ። ኬይ ከሳሩ ላይ ተነሳችና ወደቤት መራመድ ጀመሩ ። ቤት ሲደርሱም ኬይ ሄገንን ፥

“ከእራት በኋላ እኔና ልጆቹን በአንተ መኪና ወደ ኒውዮርክ ትወስደናለህ?” ስትል ጠየቀችው ።

“ለዚሁ ነው የመጣሁት” አለ ሄገን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኬይ ወደ ቤቷ ተመልሳ ሳምንት እንደቆየች ወደ አንድ ቄስ ዘንድ ሄዳ ካቶሊክ ለመሆን ትምህርት መቀበል ጀመረች ።

አዲሱን እምነት ተቀብላ ስታበቃ ቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንደተንበረከከች ስለራሷ ፥ ስለ ልጆቿ ፥ ስለ ማናቸውም አመጽ ፥ ስለማናቸውም ጉዳይ ማለብና መጨነቅን ተወች ። ካርሎ ሪዚ ከሞተበት እለት አንስቶ ታደርገው እንደ ነበር ሁሉ የሚካኤል ኮርሌዮኔ ነፍስ ይቅርታን እንድታገኝ ብቻ ጸለየች ።

t.me/OLDBOOKSPDF